## Contents

ክፍል አምስት ........ 13

የአስፈፃሚ አካላትን የሚመለከቱ ህጎች ........ 13

ሀ/ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ........ 13

አዋጅ ቁጥር 1097/2011 ........ 13

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ 13

አዋጅ ቁጥር 943/2008 ........ 64

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 64

ለ/ ለጠቅላይ ሚኒስትር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች ........ 82

አዋጅ ቁጥር 257/1994 ........ 82

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ........ 82

ደንብ ቁጥር 98/1996 ........ **Error! Bookmark not defined.**

የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 459/1997 ዓ.ም ........ 85

የቤተመንግሥት አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 85

አዋጅ ቁጥር 591/2000 ዓ.ም ........ 88

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ........ 88

ደንብ ቁጥር 172/2002 ........ 108

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተዳደርን እንደገና ለማደራጀት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.. 108

ደንብ ቁጥር 277/2005 ........ 111

ብሔራዊ የኢኮኖሚ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 111

ሐ/ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች.. **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 54/1991 .................................................................. **Error! Bookmark not defined.**

የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 158/2001 .................................................................. 113

የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.........**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 433/1997 .................................................................. **Error! Bookmark not defined.**

የተሻሻለው የፈዴራል የሥነ-ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 587/2000 .................................................................. **Error! Bookmark not defined.**

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ... **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 160/2001 .................................................................. 621

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................ 621

ደንብ ቁጥር 171/2002 .................................................................. 136

የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................... 136

ደንብ ቁጥር 244/2003 .................................................................. 497

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................................. 497

አዋጅ ቁጥር 720/2004 ዓ.ም .................................................................. 141

የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ.................................................................. 141

ደንብ ቁጥር 96/1996 ዓ.ም .................................................................. 153

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............... 153

ደንብ ቁጥር 281/2005 ........ 113

ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት እና ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 113

አዋጅ ቁጥር 804/2005 ዓ.ም ........ 159

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ........ 159

አዋጅ ቁጥር 808/2006 ዓ.ም ........ 170

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ........ 170

ደንብ ቁጥር 320/2006 ........ 177

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 177

ደንብ ቁጥር 401/2009 ........ 186

የሳይበር ሠራዊት ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትርቾ ምክር ቤት ደንብ ........ 186

ደንብ ቁጥር 311/2006 ዓ.ም ........ **Error! Bookmark not defined.**

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 313/2006 ........ 118

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድን እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 118

አዋጅ ቁጥር 857/2006 ዓ.ም ........ **Error! Bookmark not defined.**

የፌደራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 474

ደንብ ቁጥር 321/2006 ዓም ........ 645

መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 645

ደንብ ቁጥር 363/2008 ........ **Error! Bookmark not defined.**

ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 383/2008 ............................................................ 318

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............................................................ 318

አዋጅ ቁጥር 1071/2010 ............................................................ 273

የፌደራል የፍትህና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩትን ............................................................ 273

ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ............................................................ 273

ሐ/ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች............................................................ 213

ደንብ ቁጥር 347/2007 ............................................................ 207

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............................................................ 207

ደንብ ቁጥር 409/2009 ............................................................ 213

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ ............................................................ 213

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............................................................ 213

ሐ/ ለፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 22/1990 ዓ.ም ............................................................ **Error! Bookmark not defined.**

የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 365/1995 ዓ.ም ............................................................ 250

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ............................................................ 250

ደንብ ቁጥር 278/2005 ............................................................ **Error! Bookmark not defined.**

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 379/2008 ...... 269

የፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 269

መ/ ለፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች ...... **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 256/2004 ...... 636

የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...... 636

ሠ/ ለገንዘብ እና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 208/1992 ...... **Error! Bookmark not defined.**

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 184/2002 ...... 223

የመንግስት ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...... 223

ደንብ ቁጥር 332/2007 ዓ.ም ...... 228

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...... 228

ረ/ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች......**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 79/1989 ...... 281

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ...... 281

አዋጅ ቁጥር 274/1994 ...... 289

የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ...... 289

ደንብ ቁጥር 198/2003 ........ 294

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 294

ደንብ ቁጥር 284/2005 ዓ.ም ........ **Error! Bookmark not defined.**

የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 364/2008 ዓ.ም ........ 310

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 310

ሰ/ ለእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች........**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 272/2005 ዓ.ም ........ 300

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 300

ደንብ ቁጥር 304/2006 ........ 304

ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 304

ሸ/ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች .......... **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 181/2002 ........ 338

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 338

ደንብ ቁጥር 182/2002 ........ 343

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ... 343

ደንብ ቁጥር 287/2005 ዓ.ም ........ 366

የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..... 366

ደንብ ቁጥር 288/2005 ዓ.ም ..... 374

የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..... 374

ደንብ ቁጥር 295/2005 ዓ.ም ..... 381

የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 381

ደንብ ቁጥር 373/2008 ..... 388

የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 388

ቀ/ ለኢትዮጵያ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 320/1995 ዓ.ም ..... 263

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ..... 263

ደንብ ቁጥር 193/2003 ..... 349

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 349

ደንብ ቁጥር 194/2003 ..... 358

ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 358

ደንብ ቁጥር 257/2004 ..... **Error! Bookmark not defined.**

የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .....**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 279/2005 ዓ.ም ..... **Error! Bookmark not defined.**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 388/2008 ዓ.ም ........ 403

የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤትና ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 403

ደንብ ቁጥር 393/2009 ........ 414

የኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤትን እና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 414

ቀ/ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች ........ **Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 66/1989 ዓ.ም ........ 443

የመንገድ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 443

ደንብ ቁጥር 247/2003 ........ 450

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 450

ደንብ ቁጥር 300/2006 ........ 456

የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 456

በ/ ለከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 555/2000 ........ **Error! Bookmark not defined.**

የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 251/2003 ........ 461

የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 461

ደንብ ቁጥር 374/2008 ........ 467

የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 467

ተ/ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነ አስፈፃሚ አካል ማቋቋሚያ ህግ**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 289/2005 ዓ.ም ........ 481

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 481

ቸ/ ለውሃ፣ የመስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች........**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 201/1973 ........ 492

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 492

አዋጅ ቁጥር 268/1994 ዓ.ም የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ 711

ደንብ ቁጥር 151/2000 ........ **Error! Bookmark not defined.**

የአባይ ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 156/2000 ........ **Error! Bookmark not defined.**

የአዋሽ ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 253/2003 ........ **Error! Bookmark not defined.**

የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 293/2005 ዓ.ም ........ 502

የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 502

ደንብ ቁጥር 308/2006 ........ 507

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................... 507

ነ/ ለአካባቢና ደን ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች ........................................................................................ **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 291/2005 ........................................................................................................ 656

የኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........... 656

ደንብ ቁጥር 327/2007 ዓ.ም ................................................................................................ 663

የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 663

ደንብ ቁጥር 411/2009 ........................................................................................................ 674

የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ......... 674

ኘ/ ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 199/2003 ........................................................................................................ 535

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ....... 535

ደንብ ቁጥር 245/2003 ........................................................................................................ 541

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................................................................................................................ 541

ደንብ ቁጥር 260/2004 ........................................................................................................ 530

ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ530

ደንብ ቁጥር 261/2004 ........................................................................................................ 546

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ. 546

ደንብ ቁጥር 276/2005 ዓ.ም ................................................................................................ 550

የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ......................... 550

አ/ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 276/1994 ........................................................................................................ 554

ሀገር አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........................................................... 554

አዋጅ ቁጥር 553/1999 ........................................................................................................ 563

የመድኃኒት ፈንድን እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ............................ 563

ደንብ ቁጥር 189/2002 ........................................................................................................ 571

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................................................................................ 571

ደንብ ቁጥር 191/2003 ........................................................................................................ 575

የኢትዮጵያ የጤና መድህን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..................... 575

ደንብ ቁጥር 301/2006 ዓ.ም ............................................................................................... 581

የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....... 581

ደንብ ቁጥር 330/2007 ........................................................................................................ 588

የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................ 588

ደንብ ቁጥር 376/2008 ........................................................................................................ 593

የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....... 593

አ/ ለማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች...........**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 194/1992 ዓ.ም ............................................................................................... 525

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ማቋቋሚያ አዋጅ....................................................................... 525

ኀ/ ለሰራተኛና እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች .............. 600

ደንብ ቁጥር 202/2003 ........................................................................................................ 600

የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 600

ደንብ ቁጥር 203/2003 ........ 641

የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 641

ከ/ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 575/2000 ዓ.ም ........ 669

የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 669

ደንብ ቀጥር 174/2002 ........ 604

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 604

ደንብ ቁጥር 254/2003 ........ 610

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትርን ለማቋቋም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 610

ደንብ ቁጥር 258/2004 ........ **Error! Bookmark not defined.**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 294/2005 ዓ.ም ........ 614

የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ 614

ወ/ ለወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች**Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 249/2003 ........ 678

የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ........ 678

ደንብ ቁጥር 400/2009 ...................................................................................................... 684

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ...................................................................................................................... 684

ዘ/ ለመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች ......**Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 113/1987 ዓ.ም ........................................................ **Error! Bookmark not defined.**

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ .......................... **Error! Bookmark not defined.**

ደንብ ቁጥር 319/2006 ................................................................ **Error! Bookmark not defined.**

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ................**Error! Bookmark not defined.**

ፐ/ ለብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች....... **Error! Bookmark not defined.**

አዋጅ ቁጥር 442/1997 ዓ.ም ........................................................................................... 696

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........................................................ 696

አዋጅ ቁጥር 1079/2010 ................................................................................................ 421

የኢትዮጵያ ጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ.......................... 421

## ክፍል አምስት

## የአስፈፃሚ አካላትን የሚመለከቱ ህጎች

### ሀ/ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች

### አዋጅ ቁጥር 1097/2011

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አወቃቀር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለዉን ለዉጥ ውጤታማ፣ ዘላቂ እና ተቋማዊ ለማድረግ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀፅ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1097/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "ሕገ-መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው።

2. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል።
3. “ምክር ቤት” ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው።
4. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴት ፆታንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

### 3. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 74 የተመለከተው ነው።

### 4. የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 75 የተመለከተው ነው።

### 5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕጉ መንግሥቱ አንቀፅ 77 የተመለከተው ነው።

### 6. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትር፣
   ለ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 የተመለከቱትን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመሩ ሚኒስትሮች፣ እና
   መ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣኖች።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዴኤታዎች በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋሉ። ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል።

7. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ስነ-ሥርዓት</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡-

ሀ) ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊው የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ) በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ሐ) ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይኖራል፤

መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምፅ ይሆናል፣ በተባበረ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ ድምፅ ይወሰናል፣ የተሰጠው ድምፅ እኩል ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡-

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፣፤

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል።

3. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል።

8. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

2. የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

## ክፍል ሶስት

## ስለሚኒስቴሮች

9. <u>የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መቋቋም</u>

በዚህ አዋጅ የሚከተሉት ሚኒስቴሮች ተቋቁመዋል፡-

1. የሰላም ሚኒስቴር
2. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር
3. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
4. የገንዘብ ሚኒስቴር

5. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ
6. የግብርና ሚኒስቴር
7. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
8. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
9. የትራንስፖርት ሚኒስቴር
10. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
11. የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር
12. የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
13. የትምህርት ሚኒስቴር
14. የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
15. የጤና ሚኒስቴር
16. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር
17. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
18. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
19. የገቢዎች ሚኒስቴር

10. <u>የሚኒስቴሮች የወል ሥልጣንና ተግባር</u>

እያንዳንዱ ሚኒስቴር፡-

1. በስራው መስክ፡-

ሀ) የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ በዘርፉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤

ለ) በጥናት ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፤

ሐ) የፌደራል መንግሥት ሕጎችን ያመነጫል፣ ያስፈጽማል፤

መ) የፌደራል መንግሥቱን ፖሊሲ በሥራ ላይ ለማዋል ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር አስፈላጊውን ቅንጅት በመመሥረት ይሠራል፣

ሠ) ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤፤

ረ) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ዉጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) ለክልሎች እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በሰላም ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጋል፤

ሸ) ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

ቀ) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤

2. በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈጻሚ አካላት አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤ አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የሥራ ፕሮግራሞቻቸውንና በጀቶቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፤
3. በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችን፣ የሕፃናትንና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፤
4. የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5. በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌደራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
7. ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

## 11.የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት

እያንዳንዱ ሚኒስትር፡-

1. ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤
2. የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፣
3. ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
4. በሚኒስቴሩ ውስጥ የአፈጻጸም አመራር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

## 12.የሚኒስትር ዴኤታዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

1. የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

2. ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ሚኒስትር ዴኤታው ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ተክቶት ይሠራል።

13. <u>የሰላም ሚኒስቴር</u>

1. የሰላም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ሰላምን ለማስጠበቅ አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ የአገርና ሕዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ነፃነት እንዲከበሩ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፣

ለ) ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚኖሩ ዜጎች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሐ) በተለያዩ ኃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች፣ እንዲሁም በተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባህልና የኃይማኖት ተቋማት፣ እንዲሁም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

መ) በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሠ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አገራዊ አንድነትና መግባባትን የሚያጎለብት የባህል ልውውጥ፣ የስነ-ዜጋ ትምህርት እና ኪነ-ጥበብ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ረ) በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የሰላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና ንቅናቄ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

ሰ) ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፤ ኅብረተሰቡ ወደ ግጭትና አለመረጋጋት እንዳያመራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመለክት ጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሸ) የሃይማኖት ድርጅቶችንና ማኅበራትን ይመዘግባል፤

ቀ) የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነትና የፋይናንስ

ደኅንነት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

በ) የፌደራል ፖሊስ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ተ) የዜግነት፣ የብሔራዊ መታወቂያ፣ ኢሚግሬሽንና ፓስፖርት፣ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥራዎችን ይመራል፤

ቸ) የስደተኞች፣ የፖለቲካ ጥገኞችና ወደ አገር ተመላሾችን ጉዳዮች ይመራል፤

ኀ) ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፤ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራርን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

ነ) የጦር መሣሪያ፣ የተኩስ መሣሪያ ወይም ፈንጂ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ይወስናል፤ እነዚህን መሣሪያዎች ለመያዝ፣ ለመጠቀም እንዲሁም ለመሸጥ የሚያስፈልገውን ቅድመ-ሁኔታ ይወስናል፤

ኘ) በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌደራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

አ) የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 48 እና 62 (6) እንዲሁም ሌሎች አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

ከ) አግባብ ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኸ) ፌደራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈጻጸሙን ያስተባብራል፤

ወ) ለክልሎች በተለይም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፤ ሌሎች የፌደራል መንግሥት አካላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚያደርጓቸውን ድጋፎች ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ዐ) አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት

ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሰላም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

14.<u>የአገር መከላከያ ሚኒስቴር</u>

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገሪቱን የግዛት ሉዓላዊነት ያስከብራል፤ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋና ጥቃት ይከላከላል፤
2. አገር መከላከልን በሚመለከት አግባብ ያላቸውን የፌደራልና የክልል አካላት በማስተባበር ይሠራል፤
3. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፣
4. መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል፣ ይቆጣጠራል፣ የውጊያ ብቃቱን ያረጋግጣል፤
5. የመከላከያ ሠራዊት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል፤
6. የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፣ ያሠራል፤
7. የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽዖ ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል፣
8. ተግባሩን ለሕገመንግሥቱ ተገዢ እና ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤
9. ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሠረት ሰላምና መረጋጋትን ያሰፍናል፤
10. ማንኛውም ክልል ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥልና በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ያስከብራል፤
11. የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ በአገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወስናል፤ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት

ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

12. በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፣ እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ ዕገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፤
13. አገሪቱ የሚቀርብላትን ዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሰላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል፤
14. የሠራዊቱ አባላት በሰላም ጊዜ በአገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤
15. ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኘውን ገቢ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለአገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፡-
    ሀ) የመከላከያ ተቋማት በሰላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም ለገቢ ማስገኛ ተግባር እንዲውል በማድረግ የሚገኘውን ገቢ፤
    ለ) ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ፤ እና
    ሐ) በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚገኘውን የትርፍ ድርሻ፣
16. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15 የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል።

15. <u>**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**</u>

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

2. አገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ አገሪቱ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፣
3. ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲፀድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤
4. ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ አገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤
5. ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣
6. ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ውሎች ሁሉንም የተመሰከረላቸውን ዋናዎቹን ቅጂዎች መዝገቦ ይጠብቃል፤
7. የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤
8. በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሃገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤
10. በውጭ አገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፣

11.አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፤

12.የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ፡-

ሀ) የአገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣

ለ) የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣

ሐ) ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣

መ) የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድዖ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣

ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ይሠጣል፤

13.በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ በኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማኅበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

14.የዳያስፖራ ተሳትፎን በማረጋገጥ ዲያስፖራው በአገር ልማት እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

15.በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣

16.በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የአገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል

16.<u>የገንዘብ ሚኒስቴር</u>

1. የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የኢኮኖሚ ትብብርና የፊስካል ፖሊሲዎችን በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ የማሻሻያ ሀሳቦች ያመነጫል፤

ለ) ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የሁለትዮሽ ኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል ፤ የዚህ ዓይነቱ ትስስር በአገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፣

ሐ) የውጭ ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

መ) የፌደራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፤

ሠ) የፌደራል መንግሥቱን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፣ የበጀቱን አፈጻጸም ይገመግማል፤

ረ) የፌደራል መንግሥቱን የግዢና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

ሰ) የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና አንድ ወጥ የፌደራልና የክልል መንግሥታት የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓቶች የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ያሳልጣል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

17. <u>ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ</u>

በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ: -

1. በፌደራል ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤
2. በምርመራ ሥራ ላይ የተሰማሩ መርማሪዎችና ኃላፊዎችን የሥራ ስምሪት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የሥራ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤
4. ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመመካከር የመርማሪዎችና የምርመራ ክፍል ኃላፊዎች የደመወዝና ጥቅማጥቅም ሁኔታን በማጥናት እንዲወሰን ያደርጋል።

18. <u>የግብርና ሚኒስቴር</u>

1. የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፣
   ለ) ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና፣ ከፊል አርብቶ አደሮች ተደራሽ የሆነ የገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ለሚመለከታቸው የፋይናንስ አካላት ያመቻቻል፤
   ሐ) የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ውሃን ማዕከል ያደረጉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የተፈጥሮ እና የመስኖ ግጦሽ መሬት ልማት እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአነስተኛ መስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
   መ) የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ይመራል፤
   ሠ) በገጠር የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራን የሚመለከቱ ተግባራትን ያስተባብራል፤
   ረ) በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ተፋሰስ ሥራዎች፣ መሠረተ ልማትና የመኖ ባንኮች መስፋፋታቸውን ይከታተላል፤
   ሰ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፤
   ሸ) የሰብል፣ እንስሳትና የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል፣ የምርት ጥራት ለማሳደግና ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎች፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የሥልጠና፣ የአቅም ግንባታ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
   ቀ) ብሔራዊ የእንስሳት ርቢ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም ይቀይሳል፤
   በ) የእንስሳትና ዓሣ ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል፣ በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ በአገር ውስጥ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣
   ተ) በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ላይ ተፅዕኖ ለሚያስከትሉ

ወቅታዊ ሁኔታዎች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ይዘረጋል፣

ቸ) የሰብል ምርት፣ የእንስሳትና ዓሣ ግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት አቅምን በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦትን ያረጋግጣል፤ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ የገበያ ትስስር በመፍጠር አቅርቦትን ለማሻሻል የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤

ኀ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለገበያ የሚቀርብ ማንኛውም የሰብል ምርት፣ እንስሳ፣ ዓሣ፣ የእንስሳትና ዓሣ ምርትና ተዋጽዖ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብትና. የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣

ነ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውጤታማ ቅንጅት በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፤

ኘ) የግብርናና ኢንዱስትሪውን ትስስር ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣፤

አ) የሰብል ምርትና የእንስሳት ልማት ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

ከ) የጸረ-ተባይ ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖ ጥራትና የእንስሳት ሕክምና አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

ኸ) የእጽዋትና የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለዚህ የሚያስፈልገውን ጥናትና ምርምር ይመራል፤ ወደ አገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር በሚወጡት እፅዋትና አዝዕርት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽዖዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

ወ) የቡና እና የሻይ ልማት እና ግብይት የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

ዐ) የግብርና የኀብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

ዘ) የአፈር መሸርሸር መንስኤዎችን በመለየት የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤና የሚጠበቅበትን እና አገራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓት የሚዘረጋበትን ስልት ይነድፋል፤

ዠ) የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂነት እንዲለማና እንዲጠበቅ፣ የጥምር እርሻ ቴክኖሎጂ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

የ) የድርቅ ተጋላጭነትን ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል፤

ገ) በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎች የሚያስፈልጋቸውን ሰርቲፊኬቶች የሚሰጥበትን አግባብ ይወስናል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለግብርናና እንስሳት ሃብት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

19.<u>የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

1. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የንግድና ኢንዱስትሪ ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣

ሐ) የአገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፣ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

መ) የአገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሠ) በአገልግሎት፣ በግብርናና፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሠማሩ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን

ይመሠርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን በሕግ መሠረት ይፈራረማል፣ ያስፈጽማል፤

ሰ) የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤

ሸ) የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤

ቀ) ቀላል፣ ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፣፤

በ) የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

ተ) የንግድና የዘርፍ ማኅበራት፣ የሸማቾች ማኅበራት፣ የኢንዱስትሪ፣ የዘርፍና የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

ቸ) የአገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤

ኀ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

ነ) የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኘ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂካዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች የአገሪቱን ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን ዕድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ ይተገብራል፤

ኦ) በኢንቨስትመንት አዋጁ መሠረት የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

ከ) የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መረጣ፣ ማላመድና ማስረጽ ተግባራትን፣ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የክህሎት ልማት እና አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያመቻቻል፤

ኸ) የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

ወ) የኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ዐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚያስችልበትን ስልት ይቀይሳል፣

ዘ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሥራት የግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ዠ) ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ ገቢ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤ ገበያው ሊያቀርባቸው ያልቻለው ወይም እጥረት በሚታይባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘርፍ መንግስት የሚያቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

የ) በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣

ገ) ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

ደ) የአገሪቱን የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃዎች አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አጠቃቀምን ያስተባብራል፣ የተቀናጀ መረጃ ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለንግድ ሚኒስቴር እና ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

20.<u>የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር</u>

1. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የአገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ አገራዊ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፤ በብቃት ለማስፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም እና የሰው ኃይል ልማት ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣፤

ለ) ለክልሎች ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፤

መ) በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ግንባታን ይደግፋል፤ የሙያ ማኅበራትንና አካዳሚዎችን ይደግፋል፣ ያበረታታል፤

ሠ) የአገሪቱ ሥርዓተ-ትምህርት ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

ረ) የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሰ) ለአገሪቱ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፣ አገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

ሸ) አገር-በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል፣ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋጽ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችን፣ የሙያ ማኅበራትንና አካዳሚዎችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፣

ቀ) ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች ዕድገት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

በ) በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ ኮዲፋይ የማድረግና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣዩ ሥራ እንቅስቃሴም እንዲውሉ ያደርጋል፤

ተ) ለሕዝብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ ሲስተሞችና አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑና ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤

ቸ) የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችን ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣

ኀ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፤

ነ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፌደራልና የክልል መንግሥታዊ ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ይገነባል፣ ያቀናጃል፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንፎርሜሽን መረብ የመዘርጋት ሥራን ይደግፋል፤

ኘ) የአገሪቱን ከፍተኛ ደረጃ መለያ ዶሜይን ስም አገራዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመለከታቸውን ያስተባብራል፣ ይከተታተላል፤ በመንግሥታዊ ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ለመገንባትና ለማቀናጀት የዶሜይን ስም ይደለድላል፣ አድራሻ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፤

አ) የጨረራና ጨረር አመንጪ ቁሶች አጠቃቀምና አወጋገድ ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

ከ) ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያወጣል፥ ቁጥሮችን ይመድባል፣

ያስተዳድራል፣ አጠቃቀማቸውን ይቆጣጠራል፤

ኸ) የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎቶች በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፤ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ያረጋግጣል፤

ወ) ለኢትዮጵያ የተመደበውን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አጠቃቀም ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት፤ ቴክኖሎጂን በተመለከተ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

21.<u>የትራንስፖርት ሚኒስቴር</u>

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገሪቱን የልማት ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ የልማት ማዕከላትንና የዕድገት ኮሪደሮችን የትራንስፖርት ፍላጐት ለማሟላት የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
2. የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን በተመለከተ አገራዊ ዕቅዶች ያወጣል፤ አስተማማኝና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የቁጥጥር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
3. የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች መዘርጋታቸውን፣ መስፋፋታቸውንና መጠገናቸውን ያረጋግጣል፤ የአጠቃቀም፣ የአያያዝና የአስተዳደር ደረጃዎችና ሥርዓቶችን ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤
4. በትራንስፖርት ዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፤
5. የትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች በአካባቢና አየር ንብረት የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

6. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን የማስፋፋትና የማስተዳደር ሥራን ያስተባብራል፣
7. የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን ለማሻሻልና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግርን በመሰረታዊነት ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፣ ይተገብራል፣
8. የአውሮፕላን ትራንስፖርት አደጋ ምርመራ ተቀባይነት ባለው ደረጃ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤
9. የወጪና ገቢ ዕቃዎችን የተመለከቱ የትራንዚት ሥራዎችን ይቆጣጠራል፤ የአገሪቷ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ቀልጣፋና ተወዳዳሪ መሆኑን ያረጋግጣል፤
10. የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅትን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ይከታተላል፤
11. ለአገሪቱ ጠቀሜታ ያላቸውን አማራጭ የወደብ አገልግሎቶች እያጠና ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከወደብ አገልግሉት ጋር በተያያዘ ከሌሎች ሀገራት ጋር የስምምነት ሰነዶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
12. የአገሪቷን የትራንስፖርት መረጃዎች ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል።

22. <u>የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር</u>

1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-
   ሀ) የከተማ ልማትንና ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን የልማት ፓኬጆችን እና ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
   ለ) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና አገራዊ ስፓሻል ፕላን እንዲሰራ በማድረግ የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
   ሐ) ከተሞች ከአገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን አቅጣጫ ይነድፋል፣
   መ) ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ

መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሠ) የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገትና የህዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤

ረ) የከተሞችን መሬት በቁጠባ መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ስልት ይነድፋል ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ሰ) የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ዕዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ሸ) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፤ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

ቀ) የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፤ የከተማ የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

በ) የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፣

ተ) የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤ በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሠጣል፤

ቸ) የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ኀ) ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤

ነ) የኮንስትራክሽን ዘርፉን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የረጅም ጊዜ

ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ይተገብራል፣ ለዘርፉ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ይተገብራል፤

ኘ) በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤፤

አ) በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፣ መከበራቸውን ይከታተላል፤

ከ) በፌደራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

ኸ) የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፣

ወ) አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ዐ) በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፤ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

23.<u>የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር</u>

1. የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የውሃ ሀብትና የመስኖ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ለዘርፉ ዕድገት የሚያስፈልጉ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ይቀርጻል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ለ) የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የአገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሐ) ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያግዝ ዘላቂ እና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፣

መ) በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፤

ሠ) የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና ስርጭቱም እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረትን ለማስወገድ ከውሃ ኃይል፣ ከንፋስ ኃይል እና ከሌሎች አማራጭ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራን ይደግፋል፣ ይመራል፤

ረ) ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፤

ሰ) አገራዊ ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ አለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ሸ) ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ የውሃ ብክለትን እንዳይኖር ክትትል ያደርጋል፤

ቀ) የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

በ) የመካከለኛና የከፍተኛ መስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ተ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ረ) እና (ሰ) በተጠቀሱት የውሃ አካሎች ላይ የውሃ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

ቸ) የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲስፋፋ ድጋፍ ያደርጋል፣ ከዘርፉ የሚገኘውን መረጃዎች የመጠቀም አቅምን ያሳድጋል፤

ኀ) የውሃ ሀብት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

24.**<u>የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር</u>**

1. የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን የሚመለከቱ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ይቀርጻል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ለ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞችን እንዳስፈላጊነቱ ያደራጃል፤

ሐ) በማዕድን፣ በነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስክ በየደረጃው የሚፈለገውን የሰው ሀብት ለማልማት ከትምህርት ተቋማትና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

መ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ የስነ ምድር ካርታ ሽፋን ጥራትን ያሳድጋል፣ የመረጃዎችን ተደራሽነት ያረጋግጣል፣

ሠ) ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን ሥርዓት ይዘረጋል፤ በመስኩ ለሚሰማሩ አልሚዎች አበረታች ፖሊሲ ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ያስፈጽማል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣

ረ) በባህላዊ መንገድ ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን ያደራጃል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣

ሰ) ኢንቨስትመንትን በማበረታታት የማዕድን፣ ነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ ተጨማሪ ዕሴት ያላቸው ምርቶችን ያበረታታል፤

ሸ) የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ምርት ፍለጋን በበላይነት ይመራል፣ ምርቱን ወደ ገበያ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘመናዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ይፈጥራል፣፤

ቀ) በማዕድን፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሠማሩ የግል

ባለሃብቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ በገቡት ውል መሠረትም ሥራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታቸውን መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

በ) የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ለነዋሪዎች የሥራ ዕድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ከመሠረተ ልማቱ ተጠቃሚ የማሆኑበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

ተ) የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ምርቶችን የጥራት ደረጃ ያረጋግጣል፣ የማከማቻና ማከፋፈያ ተቋሞችን ደረጃ ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

ቸ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የነዳጅና መጠባበቂያ ክምችትን መጠን ይወስናል፣ ክምችቱ እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል

ኀ) ከማዕድን፣ ከነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ይደራደራል፣ ይፈርማል፤

ነ) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝን የተመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጠበቁና ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

25.<u>የትምህርት ሚኒስቴር</u>

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርድ ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) አገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

ለ) አጠቃላይ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

ሐ) የመምህራን የትምህርት ብቃት መለኪያ ያወጣል፣

መ) የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ ያወጣል፣

3. የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ሳይጨምር በየደረጃው ባሉ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

4. የአገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት ያደረጉ አገር አቀፍ ፈተናዎች ዝግጅት፣ ሪከርድ መያዝና የምስክር ወረቀት የመስጠት ሂደቶችን በበላይነት ይመራል፤
5. ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ አገራዊ የአህዝቦት ተግባራትን ያከናውናል።

26. <u>የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር</u>

1. የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦
   ሀ) የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፤
   ለ) የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ከዘርፎች ዕድገት ጋር አብሮ ለማስኬድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤
   ሐ) የአገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ይቀርጻል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲጸድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።
   መ) የከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመሠረታዊ የሳይንስ ጥናትና ምርምር የጎለበቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ የሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ያመቻቻል፣
   ሠ) በከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
   ረ) የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤
   ሰ) የከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ ያወጣል፤ በተቋማቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሠጠቱን ይከታተላል፣
   ሰ) የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አፈጻጸም ይከታተላል፤
   ሸ) የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያን በሚመለከት ለትምህርት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና

ተግባራት፤ ሳይንስን በሚመለከት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

27.<u>የጤና ሚኒስቴር</u>

የጤና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጤናውን ዘርፍ ልማት አገራዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
2. የጤና ሥርዓቱን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ድጋፍ ያደርጋል፣
3. የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤ የጤና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤
4. የአገሪቱን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤
5. አገራዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂ አፈጻጸምን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤
6. ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
7. የኅብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የሌሎች አካላት ሥራዎችን በማስተባበር ለችግሩ አፋጣኝና ውጤታማ መፍትሄ ይሰጣል፤
8. አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
9. በአገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድሃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎች በቂ አቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
10. የፌደራል ሆስፒታሎችን አስተዳደር በበላይነት ይቆጣጠራል፤ የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ሆስፒታሎችን አቅም በማጎልበት ረገድ ተባብሮ ይሠራል፤
11. በአገሪቱ ውስጥ የሚሰጠው የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤
12. የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤
13. አገራዊ የጤና መድህን ሥርዓቱን ይመራል፤ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፤

14. አገራዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

28. **የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር**

1. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ሴቶችና ወጣቶች በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፤

ለ) የሴቶችና የሕፃናት መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር እንቅስቃሴን ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሐ) ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ) በአገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

ሠ) በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ረ) በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን በአግባቡ ለመከላከል እንዲሁም ጥቃቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤

ሰ) ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች የተሟላ የጤና፣ የስነ-ልቦና፣ የሕግና የተሃድሶ አገልግሎት የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይሰጣል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

ሸ) ሴቶችና ወጣቶች እንደፍላጎቶቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

ቀ) ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ሴቶችና ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩባቸውን የሥራ ዕድሎች በጥናት ይለያል፤ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ይቀርጻል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፣

በ) ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የልማት ፈንዶች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ተ) በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ሴቶችና ወጣቶችን ኑሮ ለማሻሻል፣ የቁጠባ ባህላቸውን ለማዳበር፣ በአማራጭ ኤነርጂና በሌሎች የተለያዩ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

ቸ) በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣፤

ኀ) የሕፃናት መብትና ደኅንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ያስተባብራል፤

ኘ) የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕፃናት መልካም አስተዳደግና ሰብዕና ግንባታ፣ ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ተሀድሶ ላይ ለወላጆችና አሳዳጊዎች ተገቢውን ግንዛቤና ሥልጠና በመሥጠት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

አ) በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በአገር ውስጥ ባሉ አማራጭ ድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዓለም አቀፍ ጉዲፈቻ ከአገር የወጡ ኢትዮጵያዊ ሕፃናት በእንክብካቤ እንደተያዙ ለማረጋገጥ ጉዳያቸውን ይከታተላል፤

ከ) ሕፃናትን ከአገሪቱ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የልማት ተቋማት ማኅበራዊ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ስልት ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

ኸ) ቤተሰብ እንደኅብረተሰብ ዋና መሠረት የተሰጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ በተግባር ለማዋል የሚያስፈልጉ ስልቶችን ከሚመለከታቸው ክልላዊ መንግሥት አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይነድፋል፤ ተግባራዊነቱን ይከተላል፣

ወ) በፌደራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

አ) ሴቶችና ሕፃናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን በሕግ መሠረት

ይዋዋላል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፣

ዘ) የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለሴቶችና ሕፃናት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት፣ ወጣቶችን በሚመለከት ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

29.**<u>የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>**

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች፣ የሠራተኞች አስተዳደር ሕጎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
2. ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ድርጅቶችን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
3. በሥራ ላይ የሚከሠቱ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነትና ደኅንነት ደረጃዎች ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣
4. የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፣
5. አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤
6. በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ፣ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሶስትዮሽ የውይይት መድረኮች እንዲደረጉ ድጋፍ ያደርጋል፤
7. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማኅበራት ይመዘግባል፤
8. በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኅበራትንና የሕብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፣ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት

ተግባሮችን ያከናውናል፣ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፣

9. የሥራ ክርክሮችን ክስተት ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ሲከሰቱም መፍትሄ የሚያገኙበት የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፣
10. የአሠሪና ሠራተኛ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አገራዊ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
11. የማኀበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር የዜጎች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደኅንነት እና ዋስትና የሚሻሻሉባቸውና የሚጠበቁባቸው ዘዴዎችን በሚመለከት በተለይም፡-

    ሀ) የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣

    ለ) አረጋዊያን እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙና ተሳትፏቸው እንዲጎለብት፣

    ሐ) የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ በተለይም አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፣

    ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
12. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተመባበር መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በአሠሪና ሠራተኛ አስተዳዳር ግንኙነት ዙሪያ ይዘረጋል፤
13. ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
14. ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤
15. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያውያን የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን ይቆጣጠራል።

30. <u>የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር</u>

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችና ዕሴቶች እንዲጠኑና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

2. በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
3. ማኅበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባሮች ያከናውናል፣
4. የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ-ጥበብ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ የአገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤
5. በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤
6. በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ ስነ-ጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
7. የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ ዕውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ተግባሮችን ያከናውናል፤ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤
8. የቱሪዝም ዘርፍን ዕድገት ለመምራት የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ይተገብራል፤
9. ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣
10. የአገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በአግባቡ እንዲመሩ ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያደርጋል፤
11. በሰው ኃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካኝነት የባህልና የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፣
12. የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል።

**31. <u>የገቢዎች ሚኒስቴር</u>**

1. በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።
2. የጉምሩክ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣ ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

**32. <u>ስለሌሎች አስፈጻሚ አካላት</u>**

1. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፤

ለ) የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ በቀጣይነት የሚሻሻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ የመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ሐ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያደርጋል፣

መ) ብቃት ያለውና ውጤታማ አመራርና ሲቪል ሰርቪስ እንዲገነባ ስልት ይቀይሳል፣ የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሠ) የሲቪል ሰርቪሱ በብቃትና በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ ውጤታማነቱን ይገመግማል፣ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፣

ረ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አስተዳደር ሕጎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ የሠራተኞች ሥነ-ምግባር መከታተያ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ያረጋግጣል፤

ሰ) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የውስጥ አደረጃጀት አግባብነት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቶችን የሥልጣንና ተግባራት ወሰን፣ አወቃቀርና አደረጃጀትን በተመለከተ ጥናት በማካሄድ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሸ) በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

ቀ) የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራር መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ያደርጋል፤ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

በ) በሕግ መሠረት የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ተ) በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች በሚቀርብ ይግባኝ ላይ የፍሬ ነገር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

ቸ) በፌደራል ደረጃ የሚከናወኑ የካይዘን አመራር የለውጥ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

2. ቱሪዝም ኢትዮጵያ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ አገርና በአገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤

ለ) ሥልጣንና ተግባራቱን ለማስፈጸም እንዲያስችለው የቱሪዝም ፈንድ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ ስልት ነድፎ ይተገብራል ፤ መስህቦችና የአገልግሎቶች መረጃ ማዕከላትን በመግቢያ በሮችና በማዕከል ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

መ) የአገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት በዓለም አቀፍ ቅርስነት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሠ) የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ረ) የማርኬቲንግ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ መረጃዎችንና የጥናት ዓይነቶችን ይለያል፣ ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

ሰ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

ሸ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የየአካባቢው

ማኀበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቻል፣

ቀ) የቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ የአገልግሎት ክፍተት በመለየት የሥልጠና ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

በ) ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር ይፈጥራል፤

ተ) የቱሪዝም ዘርፉን ዕድገት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ያከናውናል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ይተገብራል፤

ቸ) ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የልማት ክፍተት በጥናት በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

ኀ) የሰመረ የቱሪዝም አገልግሎት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ የመንግሥትና የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፤

ነ) በውጭ አገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ትብብራዊ ግንኙነት ይመሰርታል።

3. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎችና በአገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል;

ለ) በመንግሥትም ሆነ በግል የሚወጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎች መርሐ ግብሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሥርዓቱ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፣

ሐ) ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ፍትህን በሚያራምድና ከሚገኘው

ጥቅም ትልቁን ድርሻ በእርምጃው ለሚነኩ ማህበረሰቦች በሚያስገኝ አካሄድ ከደን ምንጣሮና ጉስቁልና ሊከተል ይችል የነበረውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የመቀነሻ ሥርዓት ያዘጋጃል፤

መ) ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በየዘርፉና በየክልሉ ለመገንቢያ የሚውል ሃብት የሚያስገኙ ተግባራት ዝግጅትን ያስተባብራል፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍንና የምክር አገልግሎትን ይሰጣል፤

ሠ) በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት ለልማት ፕሮጀክት እና ፕሮግራም የይሁንታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ እና ፕሮግራሙ ትግበራ በአካባቢ ላይ የሚያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከተው የዘርፍ የፈቃድ ሰጪ አካል ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ተገምግሞ ውሣኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ረ) ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ሃብቶች መሠረት፣ ከበረሀማነት፣ ከደን፣ ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ ከኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች እና ከሰው ሰራሽ የአካባቢ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ጋር በተያያዘ ያፀደቀቻቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶችን በየዘርፉና በየአስተዳደር እርከኑ በመተግበር ወቅት የድግግሞሽ፣ የሃብት ብክነትንና ክፍተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ መርሐግብሮችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ መተግበራቸውንም ይከታተላል፣

ሰ) በዓለም አቀፍ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ በዘርፉ አገራዊ ምላሽን በማስተባበሩ በኩል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፣፡ እንደአግባቡ ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፣

ሸ) ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን፣ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፤ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ቀ) አደገኛ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን፣ እንዲሁም ሕያዋንን በዘረመል ምሕንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ አገር ማስገባትን፣ አያያዝንና

አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

በ) በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓቶችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤

ተ) ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ ሃሣብ ያቀርባል፣

ቸ) የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

ኀ) የአካባቢና የደን አያያዝን፣ በጥቅም ማዋልንና ፍትሃዊ የጥቅም ተጋሪነትን የሚያራምድ እንዲሁም አረንጓዴ የሥራ ዕድልን የሚፈጥር ምርምርንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ያስተባብራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ራሱ ያካሂዳል፣

ነ) አግባብነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢና የደን ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በፌደራሉ ሥልጣን ሥር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ በመግባት ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፣

ኘ) የአገሪቱን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በሚመለከት ዘገባን በየወቅቱ እያዘጋጀ ያሰራጫል፣፤

አ) መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፤ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፤

ከ) አነስተኛና ሰፋፊ የደን ልማት፣ ቀርከሀን ጨምሮ በግል፣ በወል ይዞታ እና በተፋሰስ ውስጥ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፣

ኸ) የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን እንዲጠበቅና እንደአስፈላጊነቱ ዘላቂ ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ትግበራውንም ያረጋግጣል፣

ወ) የተጎዱና የተራቆቱ የደን መሬቶች እንዲያገግሙና የአካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እንዲሻሻል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል።

4. የስፖርት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

ለ) የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሐ) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን፤ ያስፋፋል፤

መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ሕክምና አገልግሎት ያደራጃል፤ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሠ) የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

5. የተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችና ምርምሮችን ያደርጋል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ይተገብራል፤

ለ) በተፋሰሶች ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

ሐ) በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች በይዘታቸው፣ በጊዜ ሠሌዳቸው፣ በውጤታቸውና በአመራራቸው ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

መ) የተፋሰሶችን ጥበቃና ዘላቂ ጥቅም በተመለከተ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሠ) የተፋሰሶችን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፤

ረ) ተፋሰሶችን ከብክለትና ከጉዳት ለማዳን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይተገብራል፤

ሰ) ለክልሎች በሕግ የተሰጠ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሶች ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፣ በፈቃዱ ላይ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣፤

ሸ) በተፋሰሶች ውስጥ የሚደረጉ የመስኖ ማስፋፋት ሥራዎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

ቀ) የወንዝ አቅጣጫ አመራር ሥራ ይሠራል፤

በ) ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ ይሰበስባል፤

ተ) በተፋሰሶች የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሠራጫል፤

ቸ) የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ማሜሚኒስቴር ተገቢውን የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሠጣል፣

ኀ) ከክልል መንግሥት አካላት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

ነ) ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ከሌሎች አገሮች ጋር ለመወያየት አግባብ ላለው አካል አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሠጣል።

6. የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በሥራ ላይ ባሌ ሕጎችና ድንጋጌዎች ከተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 67/1992 ዓ.ም ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና

ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ተሰጥተዋል።

7. በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች የግብርና ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ለሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፤ የሆርቲካልቸር ዘርፉን ልማት በተመለከተ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተሰጥተዋል።
8. የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2004 ዓ.ም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት ተሰጥተዋል።
9. የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1079/2010 ዓ.ም ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ፣ እንዲሁም ጂኦስፓሻል ዳታና መረጃን በተመለከተ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 808/2006 ዓ.ም ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት ተሰጥተዋል።
10. የገቢዎች ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።
11. የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 54/1991 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት፣ እና በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት ተሰጥተዋል።

12. የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
13. የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
14. የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
15. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
16. የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
17. የመስኖ ልማት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
18. የውሃ ልማት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።
19. የፕላንና ልማት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በብሔራዊ ፕላን ምክር ቤትና የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 281/2005 ዓ.ም ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

33. <u>ተጠሪ የፌደራል አስፈጻሚ አካላት</u>

1. በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች የተደረጉት የተጠሪነት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የፌደራል መንግሥቱ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት በተቋቋሙባቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ።
2. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን

ለ) የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

ሐ) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

መ) የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት

ሠ) የፌደራል ሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን

3. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

ለ) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ሐ) የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

መ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን

ሠ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ረ) ቱሪዝም ኢትዮጵያ

ሰ) የቤተ-መንግሥት አስተዳደር

4. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሰላም ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

ለ) የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ

ሐ) የፋይናንስ ደኅንነት መረጃ ማዕከል

መ) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

ሠ) የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ

ረ) የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

ሰ) የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

ሸ) የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂክ ጥናት ኢንስቲቲዩት

5. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የአገር መከላከያ ኢንጂነሪንግ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

ለ) ጋፋት አርማሜንት

ሐ) ሆሚቾ አሙኒሽን ኢንጂነሪንግ

መ) ደጀን አቪየሽን ኢንጂነሪንግ

ሠ) ብራና ማተሚያ ድርጅት

ረ) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ

ሰ) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት

ሸ) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት

6. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

ለ) የዲያስፖራ ኤጀንሲ

7. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የመንግሥት የልማት አስተዳደር ኤጀንሲ ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

ለ) የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

ሐ) የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

መ) የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

8. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይሆናል፡-

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

ለ) የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

ሐ) የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

መ) የፍትህና የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲቲዩት

ሠ) የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ

ረ) የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ

9. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለግብርና ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

ለ) የግብርና ምርምር ካውንስል ሴክሬታሪያት

ሐ) የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ

መ) የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

ሠ የቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን

ረ) የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች

ሰ) የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ሸ) ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል

ቀ) የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል

በ) የብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት

ተ) ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት

10.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ) የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሐ) የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

መ) የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሠ) የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ረ) የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሰ) የፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለሥልጣን

ሸ) የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን

ቀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን

በ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት

ተ) የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ

ቸ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት

ኀ) የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ

ነ) የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅራቢ ልማት ድርጅት

11.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከል ባለሥልጣን

ለ) የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ሐ) የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት

መ) የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት

ሠ) የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት

12.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን

ለ) የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን

ሐ) የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን

መ) የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን

ሠ) የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት

ረ) የመድህን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ

ሰ) የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን

ሸ) የኢትዮ-ጅቡቲ ስታንዳርድ ጌጅ ባቡር ትራንስፖርት አ.ማ.

ቀ) የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት

በ) የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ

13. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የፌደራል ከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ለ) የፌደራል ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

ሐ) የተቀናጀ መሠረተ-ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ

መ) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት

ሠ) የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

ረ) የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን

14. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የመስኖ ልማት ኮሚሽን

ለ) የውሀ ልማት ኮሚሽን

ሐ) የተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን

መ) የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ሠ) የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ረ) ብሔራዊ የሜትሪዮሎጂ ኤጀንሲ

ሰ) የኢትዮጵያ ኤነርጂ ባለሥልጣን

ሸ) የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

ቀ) የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

15. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ

ለ) የኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማት ማስፋፊያ ማዕከል

ሐ) የኢትዮጵያ ነዳጅና ጋዝ ምርትና አቅርቦት ኮርፖሬሽን

16. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የአገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ

ለ) የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት

17. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል

ለ) የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

ሐ) የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

መ) የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች

ሠ) የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

ረ) የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ

ሰ) የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት

18. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) ቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ትምህርትና

ለ) ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

ሐ) ቅዱስ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

መ) የመላ አፍሪካ ሥጋ ደዌ መከላከያና ትምህርት መስጫ ማዕከል

ሠ) የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን

ረ) የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

ሰ) የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ

ሸ) የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ

ቀ) ብሔራዊ የደም ባንክ አገልግሎት

በ) የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት

ተ) ብሔራዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

19. የግል ድርጅት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተጠሪነት ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል።

20. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል፡

ሀ) የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

ለ) ብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት ኤጀንሲ

ሐ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር

መ) የሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል

ሠ) የስፖርት ኮሚሽን

21.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የጉምሩክ ኮሚሽን

ለ) የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር

22.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

ለ) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት

23.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

ለ) መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ

ሐ) የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት

መ) የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት

ሠ) የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

24.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን

ለ) የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን

25.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ብዝሃ-ሕይወት ኢንስቲትዩት

ለ) የኢትዮጵያ አካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት

ሐ) የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን

26.የውሃ ልማት ፈንድ ተጠሪነት ለውሃ ልማት ኮሚሽን ይሆናል።

27.የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለስፖርት ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ

ለ) አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል

ሐ) ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽ/ቤት

**34.የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት፣ ማንኛውም አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ፣ ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል በማድረግ፣ ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ በማድረግ ወይም አዲስ አስፈጻሚ አካል እንዲቋቋም በማድረግ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና የማደራጀት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**35.የተሻሩ ሕጎች**

1. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

**36.መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ**

1. የፌደራልና አርብቶ አደር አካባቢ ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሰላም ሚኒስቴር ተላልፈዋል።
2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።
3. የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ተላልፈዋል።
4. የግብርናና እንስሳት ሃብት ሚኒስቴር እንዲሁም የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለግብርና ሚኒስቴር ተላልፈዋል።
5. የንግድ ሚኒስቴር እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።
6. የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

7. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተላልፏል።
8. የዉሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተላልፏል።
9. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተላልፏል።
10. የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተላልፏል።
11. ከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን በተመለከተ የትምህርት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተላልፏል።
12. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጤና ሚኒስቴር ተላልፏል።
13. በወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ወጣቶችን የሚመለከቱ መብትና ግዴታዎች፣ እንዲሁም የሴቶችና የሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ተላልፏል።
14. በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ስፖርትን የሚመለከቱ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለስፖርት ኮሚሽን ተላልፏል።
15. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተላልፏል።
16. የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት እና የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት ተላልፏል።
17. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተላልፏል።
18. የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለቱሪዝም ኢትዮጵያ ተላልፏል።
19. የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት አገልግሎቶች መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ተላልፏል።

20.የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ ተላልፈዋል።

21.የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ተላልፈዋል።

22.የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እና የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

23.የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተላልፈዋል።

24.የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

25.የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ማዕከል መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

26.የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን፣ የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን እና የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን ተላልፈዋል።

27.የኢትዮጵያ ባህል ማዕከል መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

28.የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተላልፈዋል።

**37.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሕዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 943/2008

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ወጥነት ያለው፣ ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ፣ የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም በተሟላ ሁኔታ የሚያስጠብቅ አንድ ጠንካራ ሕግ አስከባሪ የዓቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሕጎች በሚገባ መደራጀታቸውንና የመንግስት ሥራዎች በሕግ መሠረት መመራታቸውን የሚያረጋግጥ እንዲሁም የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር ተቋም እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የሕዝብ ተአማኒነት ያለው፣ በተሟላ ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት የሚያገለግል እንዲሁም ለሙያዊ፣ ተቋማዊና ሕዝባዊ ተጠያቂነት የሚገዛ፣ በግልጽነትና አሳታፊነት የሚሰራ የዓቃቤ ሕግ ተቋም ማደራጀት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "ሕገ መንግስት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ነው፤
   2. "የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች" ማለት ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል መንግስቱ በጀት የሚተዳደሩ አካላት ሲሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በጀት የሚተዳደሩ ተቋማትን እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

3. “የፌዴራል መንግስት ሕጎች” ማለት አዋጆች፣ ደንቦች እና ሥልጣን በተሰጣቸው የፌዴራል መንግስት አካላት የወጡ መመሪያዎች እና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ወይም የተቀበለቻቸው አለምአቀፍ ስምምነቶችን ያጠቃልላል፤
4. “የወንጀል ሕግ” ማለት በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት በወጣ አዋጅ መሠረት የተደነገገ የወንጀል ሕግ ነው፤
5. “ክልል” ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልላዊ መንግስት ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
6. “ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ” ማለት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ኃላፊ ነው፤
7. “ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ” ማለት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሾመ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ምክትል ሀላፊ ነው፤
8. “ዓቃቤ ሕግ” ማለት በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ተሹሞ በዓቃቤያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚተዳደር የሕግ ባለሙያ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 (1) መሠረት የተሾሙ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉንና ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግን ይጨምራል፤
9. “ዓለም አቀፍ ስምምነት” ማለት በኢትዮጵያ እና በሌላ መንግስት፣ መንግስታት እንዲሁም ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች መካከል የተፈጸመና በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተዛማጅ ሰነዶች በጽሁፍ የሰፈረ ማንኛውም ስያሜ የተሰጠው በዓለም አቀፍ ሕግ የሚገዛ ስምምነት ሲሆን ስምምነቶች፣ ኮንቬንሽኖች እና ፕሮቶኮሎችን ይጨምራል፤
10. “ፖሊስ” ማለት ስልጣን ያለው የፌዴራል ወይም የክልል ፖሊስ ማለት ነው፤
11. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
12. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ (ከዚህ በኋላ “ፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ”) እየተባለ የሚጠራ፣ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. **ዓላማዎች**

የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር፤
2. የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤
3. የወንጀል ሕግን ማስከበር፤
4. የፌዴራል መንግስቱን እና የሕዝብን የፍትሐ ብሔር ጥቅም ማስከበር።

6. **ሥልጣንና ተግባራት**

የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
2. በሕግ ጉዳዮች የፌዴራል መንግስት ዋና አማካሪ እና ተወካይ ሆኖ ይሰራል፤
3. የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ፦

   ሀ/ በሌሎች ህጎች ለፖሊስ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር ያደርጋል፣ የተጀመረ የወንጀል ምርመራ ላይ የክትትል ሪፖርት እንዲቀርብ እንዲሁም ምርመራው በአግባቡ ተከናውኖ እንዲጠናቀቅ፣ በሕዝብ ጥቅም መነሻ ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠው የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ያደርጋል፣ ምርመራው በሕግ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፤

ለ/ በፖሊስ የተጀመረ የወንጀል ምርመራ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፣ የምርመራ አካሄዱን በተመለከተ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣ በምርመራ መዝገብ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ከፖሊስ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፣ እንዲሁም በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠ የዓቃቤ ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ያሳውቃል፣ የወንጀል ምርመራ መዝገቦችን አስመልክቶ በየደረጃው ባሉ ዓቃቤያን ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ ይግባኞችን ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሐ/ የተጠናቀቁ የምርመራ መዝገቦችን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር መርምሮ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት የተቀመጡ መመዘኛዎች ሲሟሉ የአያስከስስም ወይም የተዘግቷል ውሳኔ ይሰጣል፤

መ/ የጥፋተኝነት ድርድር ይወስናል፣ ድርድር ያደርጋል፣ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሠ/ የፌዴራል መንግስትን በመወከል የወንጀል ጉዳዮች ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፣ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ያነሳል፣ የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ያደርጋል። ሆኖም ጉዳዩ ሀገራዊ ይዘት የሚኖረው ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩን በማማከር ክስ ስለሚያነሳበት አግባብ መመሪያ ያወጣል፤

ረ/ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጡዋቸው ውሳኔዎችና ትእዛዞች መፈፀምና መከበራቸውን ይከታተላል፣ ሳይፈፀሙ ከቀሩ ወይም አፈፃፀማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ሰ/ በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ያደራጃል ወይም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ/ የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ያቀርባል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

4. የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ፦

ሀ/ በፌዴራል የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ እና የፌዴራል መንግስት መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል፣ ያስከብራል፣ እንዲከበሩ ያደርጋል፣ የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ/ በግዙፍ የመንግስት ፕሮጀክቶች የውል ዝግጅት እና ድርድር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያደርጋል፣ የሕዝብና የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን በሌሎች ጉዳዮች ውል ዝግጅትና ድርድር ያደርጋል ወይም የሚመለከታቸውን አካላት ያማክራል፤

ሐ/ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤትን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ይመሰርታል፤ በከሰሱበት ወይም በተከሰሱበት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ክርክር ያደርጋል፤ በተጀመረ ክርክር ተቋማትን ተክቶ በተናጠል ወይም በጋራ ይከራከራል፣ ወይም በክርክር አመራር ላይ ለመሥሪያ ቤቶች አቅጣጫ ይሰጣል፣ በሕግ መሠረት ፍርድን ያስፈፅማል፤

መ/ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዩች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ ባለ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድ እንዲወሰን ውሳኔ ይሰጣል፣ በውሳኔው መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

ሠ/ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ወክሎ ይከራከራል፤

ረ/ የገንዘብ አቅም የሌላቸው የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ተበዳዩች እንዲካሱ መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲሁም ከጉዳቱ የተያያዙ የፍትሐ ብሔር ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እነሱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ያቀርባል ወይም ይደራደራል፤

ሰ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በዓለምአቀፍ የዳኝነትና ከፊል ዳኝነት አካላት በሚከስበት ወይም በሚከሰስበት ጉዳይ መንግስትን በመወከል እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ክርክር ያደርጋል፤ ድርድር ያካሂዳል፤ ውሳኔውንም ያስፈፅማል፤

5. የሕግ ማርቀቅ ሥራን በተመለከተ፦

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት የሚወጡ ሕጎች የሕግ ረቂቅ ዝግጅት ይሰራል፤ የመንግስት አካላት የሚያዘጋጁት ረቂቅ ሕግ ከሕገ መንግስቱና ከፌዴራል ሕጎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ለሚመለከታቸው ክፍሎችም

አስተያየት ያቀርባል፤ በክልሎች ጥያቄ ሲቀርብለት የሕግ ረቂቆችን በማዘጋጀት ይረዳል፤

ለ/ የሕግ ማሻሻያ ጥናቶችን እንዲሁም የኮዲፊኬሽንና የፌዴራል ሕጐችን የማሰባሰብና ማጠቃለል ሥራ ይሰራል፤ የክልል ሕጎችን ያሰባስባል፣ እንደአስፈላጊነቱም እንዲጠቃለሉ ያደርጋል፤

ሐ/ ኢትዮጵያ የምትፈርመው ወይም የምትቀበለው ዓለም አቀፍ ስምምነት ሕገ መንግስቱን እና የአገሪቱን ሌሎች ሕግጋት ያገናዘበና ከብሔራዊ ጥቅም አንፃር ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

6. የፌዴራል መንግስቱ ሕጐች ተግባራዊ መደረጋቸውን እና አተገባበራቸውም ወጥነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ እንዲሁም አስፈፃሚ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሥራቸውን በሕግ መሰረት ማከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

7. የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ለፌዴራል መንግስት ባለስልጣናት፣ ሹመኞች፣ ተመራጮች፣ ሰራተኞች እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎች እንደየአስፈላጊነቱ የሕግ ሥልጠና ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

8. ሰብአዊ መብትን በተመለከተ፡-

ሀ/ ነፃ የሕግ ድጋፍን አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን ይቀርፃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ያስተባብራል፤

ለ/ ብሔራዊ የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

ሐ/ በፖሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤት ቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎችን ይጎበኛል፣ አያያዛቸው እና ቆይታቸው በሕግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ ሕገ ወጥ ተግባር እንዲታረም እንዲሁም ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሰረት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

መ/ የሰብአዊ መብት ትምህርት እና የንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች ትምህርት ይሰጣል፤ በዘርፉ የተሰማሩ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፤

ሠ/ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ወይም የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ለሚነሱ ጉዳዮች እንደ አግባብነታቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ምላሽ ይሰጣል፤ የስምምነቶቹን ብሔራዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤

9. ስለ ሕግ ጥናትና ስልጠና፦

ሀ/ አሰራሩን ውጤታማ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤

ለ/ የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈፅማል፤

ሐ/ ዓቃቤያነ ሕግ ስለ ስራቸው ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት በተከታታይ እና በየደረጃው ለማሳደግ ሥልጠና ይሰጣል ወይም ስልጠና እና ትምህርት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤

10. የዓቃቤ ሕግ የውሳኔ አሰጣጥ እና የፍቅደ ሥልጣን አጠቃቀም ወጥነትን ለማረጋገጥ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የፀደቀ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

11. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ደረጃ የጥብቅና አገልግሎት ለሚሰጡ ጠበቆች በሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤ ጠበቆችንና የጥብቅና አገልግሎትን ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

12. በፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር ስር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀልና ፍትሐብሔር ጉዳዩች ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፤

13. በዓቃቤያነ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥ የኢንስፔክሽን ክፍል ያደራጃል፣ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣ መልካም ተሞክሮዎችን ያስፋፋል፤

14. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 916/2008 የተመለከተውን የሚኒስትሮች የወል ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፤

15. የንብረት ባለቤትና የይዞታ ባለመብት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
16. በሕግ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ወይም ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አቋም</u>**

ፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፦

1. በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾም አንድ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግ፤
2. የሥራ ዘርፎች፤
3. የማኔጅመንት ኮሚቴ፤
4. የፌዴራል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ፤
5. በዓቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የሚሾሙ ዓቃቤ ሕጎች፤ እና
6. አስፈላጊ ሰራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የበላይ ኃላፊ በመሆን፣ በሙያውና በሕግ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 (በአዋጅ ቁጥር 883/2007 እንደተሻሻለ/ እና የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ ቁጥር 434/1997 (በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለ/ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለኮሚሽነሩ ተሰጥተው የነበሩ እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ

አዋጅ ቁጥር 587/2000 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ለዋና ዳይሬክተሩ ተሰጥተው የነበሩ የወንጀል ክስና ምርመራን የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራትን ሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/ የፌዴራል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደርን በተመለከተ በፌዴራል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የተዘጋጀውን ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ዓቃቤያነ ሕግን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት ይሾማል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሠ/ በምክትል ጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይሽራል፣ ይለውጣል፣ ያሻሽላል፣ ወይም ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም ውሳኔውን በሰጠው አካል እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፤

ረ/ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሰ/ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚረዱ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ያለክፍያ የሚሰሩ አማካሪዎችን በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

ሸ/ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ስትራቴጂክ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ቀ/ ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በተፈቀደለት በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

በ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ይወክላል፤

ተ/ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፤

ቸ/ በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ፦

ሀ/ ለሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ጠቅላይ ዓቃቤነ ሕግ፣ ዓቃቤያነ ሕግና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ፤

ለ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ ለሌሎች አካላት አስቀድሞ በሚዘረጋ የአፈፃፀም፣ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መሠረት በውክልና ሊያስተላልፍ፤

ይችላል።

9. **የምክትል ጠቅላይ ዓቃብያነ ሕግ ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ጠቅላይ ዓቃቢያነ ሕግ፦

1. ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉን ያግዛሉ፤
2. የሚመደቡባቸውን ዘርፎች ይመራሉ፣ ያስተዳድራሉ፤
3. በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ተለይተው የሚሰጡዋቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፤
4. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና ያልተሰጠ እንደሆነ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግነት ሥራን ተክቶ ይሰራል፤
5. ለሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባራቸው በከፊል ለዓቃቤያነ ሕግና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

10. **ከሹመት ስለመነሳት**

ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ እና ምክትል ጠቅላይ ዓቃቢያነ ሕግ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሳኔ ከሹመታቸው ሊነሱ ይችላሉ።

11. **የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር**

1. የዓቃቤያነ ሕግ አስተደደር በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
2. የዓቃቤያነ ሕግ ሹመት በሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፦

   ሀ/ ለሕገ መንግስቱ እና ለሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ እንዲሁም ለሕግ የበላይነት ያለው ተገዢነት እና እምነት፤

   ለ/ ሕዝባዊ አገልጋይነት፤

   ሐ/ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሚዛናዊ ተዋፅኦ፤

   መ/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት፤

   ሠ/ ጥብቅ የሥነ ምግባር ሁኔታ፤

   ረ/ ለዓቃቤ ሕግ ሥራ አስፈላጊ የሆነ የህግ የትምህርት ዝግጅትንና ክህሎት፤

ሰ/ በዘርፉ የሚሰጠውን የቅድመ ሥራ ሥልጠና ተከታትሎ በስኬት ማጠናቀቁ፤

ሸ/ የዓቃቤ ሕግ አገልግሎት የሚጠይቀውን ኃላፊነት የመወጣት ቁርጠኝነት፤

ቀ/ ዓቃቤ ሕግ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች ገለልተኛ መሆን።

3. የዓቃቤያነ ሕግ ውስጣዊ አስተዳደር በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡-

ሀ/ ዓቃቤያነ ሕግነት የሚመደቡበት የስራ መደብ፤ የሥራውን ዓይነት፣ ሥራው የሚመራበት ሥርዓት እና የሚያስፈልገው አደረጃጀት፣ የሚጠበቀውን ውጤት በግልጽ ባስቀመጠና ለሕዝብ ተጠያቂ መሆንን መሠረት አድርገው በተዘረጉ ሥርዓቶች ላይ የተመሠረተ፤

ለ/ የዓቃቤያነ ሕግ የሥራ አፈፃፀም፤ ተለክቶ የተሰጠ ተግባር መኖርን፣ የሥራ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን፣ እንዲሁም በጎ ተፅዕኖ ፈጣሪነት እና በሕዝብ ዘንድ ተአማኒነት እና ሌሎች በዓቃቢያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የሚወሰኑ መመዘኛዎችን መሠረት አድርገው የሚዘረጉ ሥርአቶች ላይ የተመሠረተ፤

ሐ/ የዓቃቤያነ ሕግ የሥነ ምግባር ሁኔታ፤ ሕገ-መንግስታዊነትን፣ ሕግ አክባሪነትን፣ ገለልተኝነትን፣ ተጠያቂነትን ታሳቢ አድርጎ የተዘረጉ ሥርዓቶችን የተከተለ፤

መ/ በበታችና በበላይ ዓቃቤያነ ሕግ መካከል ያለው የሥራ ግኑኝነት፤ ትብብርንና መተጋገዝን፣ የሥራው ሕጋዊነትን፣ ቅልጥፍና ማረጋገጥን፣ እንዲሁም የዕውቀትና ክህሎት ሽግግርን ታሳቢ አድርገው የተዘረጉ ሥርዓቶችን የተከተለ፤

ሠ/ የዓቃቤያነ ሕግ ዕድገት፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ እንዲሁም የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም አሰጣጥ፤ በሥራ አፈፃፀማቸው፣ በውጤታማነታቸው እና በሥነ-ምግባራቸው ሁኔታ ላይ የተመሠረተ፤

ረ/ የዓቃቤያነ ሕግ የውስጥ ዝውውር፤ ሥራን፣ የአቃቤ ሕጉን የግል ሁኔታዎች፣ ገለልተኝነቱን፣ እንዲሁም የግል ምርጫን ታሳቢ አድርገው በተዘረጉ ሥርዓቶች ላይ የተመሰረተ፤

ሰ/ የዓቃቤያነ ሕግ የሕግ ትምህርት እና ሥልጠና ዕድል እንዲሁም የስብሰባ ተሳታፊነት፣ ዓቃቤ ሕጉ የተመደበበት እና የሚሰራው ሥራ ከጉዳዩ ጋር ያለውን ቅርበት፣ የሥራ አፈፃፀም፣ የብሔር፣ የፆታን እና የአካል ጉዳተኞችን ተዋጽኦ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ሥልጣንና ተግባር ለማስፈጸም የሚኖረው አስተዋጽዖ፣ ውጤታማና ፈጣን አገል ግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ፣ ለሠልጣኙ ዕውቀትን ወይም ክህሎትን የሚጨምሩ መሆናቸው እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎች ግምት በማስገባት የተዘረጉ ሥርዓቶች ላይ የተከተለ፤

ሸ/ ዓቃቤያነ ሕግ ነፃነት፤ ሥራቸውን በማከናወናቸው ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ቀጥተኛና ቀጥተኛ ካልሆነ ጥቃት በቂ ጥበቃ መሰጠቱን በሚያረጋግጡ ሥርአቶች ላይ የተመሰረተ፤

ቀ/ የዓቃቤ ሕግ ስንብት፤ የሥራ አፈፃፀም ዝቅተኛነትን፣ የሥነ ምግባር ጉድለትን፣ የጤና ሁኔታን እና ፈቃደኝነትን እንዲሁም ጡረታን ታሳቢ አድርጎ በተዘረጋ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ።

12. **<u>የፌዴራል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ</u>**

1. ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የሆነ የፌዴራል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል፤ የጉባኤውን አባላት፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓትና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡
2. የፌዴራል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የዓቃቤያነ ሕግ ሹመት፣ ዝውውር፣ የዕረፍት ጊዜ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ ደረጃ፣ ሥነ-ምግባር፣ አደረጃጀት፣ መዋቅር፣ ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም እና የመሳሰሉ ጉዳዩችን ያካተተ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የማቅረብ ኃላፊነት ይኖርበታል።

13. **<u>ሕዝባዊ ተጠያቂነት</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት ሕዝባዊ ተጠያቂነት እና የሕዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ አለበት።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚከተሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት የሕዝብ መድረክ በየሩብ ዓመቱ ያመቻቻል፦

   ሀ/ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተመረጡ ሕዝባዊ አደረጃጀቶች፤

ለ/ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተመረጡ የንግድ ማኅበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፤

ሐ/ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተመረጡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች፤

መ/ ከባለድርሻ አካላት፤

ሠ/ ሌሎች አስፈላጊነታቸው በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የታመነባቸው ግለሰቦች ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን አካላት የሚወክሉ ግለሰቦች።

3. ሕዝባዊ መድረኩ በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሥራ አፈፃፀም ላይ የሚታዩ ችግሮች እና ክፍተቶች፣ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች፣ ስትራቴጂካዊና ዓመታዊ ዕቅዶች እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ውይይት ይደረጋል።

4. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ከሕዝባዊ መድረኩ በሚሰጡ አስተያየቶች እና ግብአቶች መሠረት ማጣራት ያደርጋል፣ የእርምት ወይም የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ የደረሰበትን ደረጃ ለሕዝባዊ መድረኩ ያሳውቃል።

14. <u>በጀት</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ይተዳደራል።

15. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ነፃነትና ተጠያቂነት</u>

16. <u>የዓቃቤያነ ሕግ የሙያ ነፃነት</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣኑንና ተግባሩን ሲያከናውን ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ በሕግ መሠረት ይፈፅማል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚያወጣው የአሠራር መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በሕግ መሠረት በነፃነት ያከናውናሉ።
3. በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ የዓቃቤ ሕግ ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንዲሁም

ዓቃቢያን ሕግ በሕግ መሠረት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር በማከናወናቸው ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሕግ ተጠያቂነት አይኖርባቸውም።

17.<u>ተጠሪነትና ተጠያቂነት</u>

1. የዓቃቤያነ ሕግ የበላይ ኃላፊ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ይሆናል።
2. ዓቃቤያነ ሕግ ለበላይ ኃላፊያቸውና ለዘርፍ ኃላፊዎቻቸው ተጠሪ ይሆናሉ።
3. ዓቃቤያነ ሕግ በሥራ አፈፃፀማቸውና በሥነ-ምግባራቸው ለሚታየው ጉድለት በሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ።

18.<u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

1. ዓቃቤ ሕግ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በየደረጃው ለሚገኙ የዓቃቤ ሕግ ኃላፊዎች አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤ አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን በአፋጣኝ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አለበት።
2. አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን ለማጣራት አግባብ ያላቸውን ባለሙያዎች የሚያካትት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል።
3. አቤቱታውን የመረመረው ኃላፊ የሕግና የማስረጃ ምክንያቱን በመጥቀስ በበታች ዓቃቤ ሕግ የተሰጠውን ውሳኔ ለማገድ፣ ለመለወጥ፣ ለማሻሻል፣ ለመሻር፣ ለማጽደቅ ወይም ጉዳዩን አስቀድሞ ወዳየው ክፍል ለመመለስ ይችላል።

19.<u>ጥቆማ ወይም አስተያየት የማቅረብ መብት</u>

1. ማንኛውም ሰው በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ውስጥ የሚወድቅ ማንኛውም መታረምና መስተካከል አለበት የሚለውን ጉዳይ ወይም ተፈጽሟል የሚለውን የሥነ-ምግባርና የሕግ ጥሰት በማናቸውም መንገድ ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጥቆማ ወይም አስተያየት ለማቅረብ ይችላል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጥቆማ፣ አስተያየትና ቅሬታዎችን የሚቀበልበት፣ የሚያጣራበትና የመፍትሄ እርምጃ የሚወስድበት እና ለሕብረተሰቡ የሚገለጽበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

20.<u>የጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግ የጋራ ምክር ቤት</u>

1. የጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግ የጋራ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “የጋራ ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና የክልል ዓቃቤ ሕግ

ተቋማት የበላይ አመራሮች በትብብርና በቅንጅት የሚሰሩበት በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል።

2. የጋራ ምክር ቤቱ በፍትሕ ዘርፍ የጋራ እና ተመሳሳይነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ አሰራራቸውን እና አፈፃፀማቸውን ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እና ወጥነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ ያወጣል።
3. የጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ሆኖ የክልል የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ኃላፊዎች በአባልነት ይሳተፋሉ።
4. የጋራ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ይወስናል።
5. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የምክር ቤቱን ሥራዎችና ስብሰባዎች ያመቻቻል።

21. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።
3. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ሰፊ ስርጭት ባላቸው ማናቸውም መገናኛ ዘዴዎች እንዲታተሙ እና እንዲሰራጩ ይደረጋል፡

22. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ  አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 እና በሌሎች ሕጎች ለፍትሕ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተላልፈዋል።
2. በፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 (በአዋጅ ቁጥር 883/2007 እንደተሻሻለ/ እና የተሻሻለው የፀረ- ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ 434/1997 (በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለ/ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኑ ተሰጥተው የነበሩ የዓቃቤ ሕግነት ሥልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተላልፏል።

3. በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 (በአዋጅ ቁጥር 883/2007 እንደተሻሻለ/ እና የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርአትና የማስረጃ አዋጅ 434/1997 (በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለ/ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለኮሚሽኑ ተሰጥቶ የነበረው የወንጀል ምርመራ የማድረግ ሥልጣን ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተላልፏል።
4. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለባለስልጣኑ ተሰጥቶ የነበረው የዓቃቤ ሕግነት ሥልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተላልፏል።
5. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለባለሥልጣኑ ተሰጥቶ የነበረው የታክስና የጉምሩክ ወንጀል ምርመራ የማድረግ ሥልጣን ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተላልፏል።
6. በንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ተሰጥቶ የነበረው የዓቃቤ ሕግነት ሥልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተላልፏል።
7. በንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ተሰጥቶ የነበረው የወንጀል ምርመራ የማድረግ ሥልጣን ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተላልፏል፤
8. በልዩ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ 22/1985 ለልዩ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣን፣ መብትና ግዴታዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተላልፈዋል።

23.<u>የመተባበር እና የመፈጸም ግዴታ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግና ዓቃቤያነ ሕግ በሕግ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት ትብብር የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ ያልሆነ እና አደጋ የማያስከትልበት ከሆነ የመተባበር ግዴታ አለበት።
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ የዓቃቤ ሕግ ተቋማት አመራር እና ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደረገውን ሽግግር የመተባበርና የመደገፍ ግዴታ አለባቸው።
3. ማንኛውም የፖሊስ አባል የዓቃቤ ሕግን የመጨረሻ እና ሕጋዊ ውሳኔ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት።

**24.የወንጀል ተጠያቂነት**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና ዓቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በነፃነት እንዳያከናውኑ ጣልቃ የሚገባ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና ዓቃቤያነ ሕግ የሚሰጡትን ውሳኔ የማያከብርና የማያስፈጽም እንዲሁም የመተባበር ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፫ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
3. ማንኛውም የፖሊስ አባል የዓቃቤ ሕግን የመጨረሻ እና ሕጋዊ ውሳኔ በመቃወም ያልታዘዘ እንደሆነ አግባብ ባለው ሕግ ይጠየቃል።

**25.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጡ ደንቦች፣ በፍትሕ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን የወጡ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ለማስፈፀም አግባብነት ያላቸው መመሪዎች እና ማኑዋሎች በሌሎች ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ማኑዋሎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።
2. በፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ በፍትህ ሚኒስቴር እና በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ተቀጥረው በሥራ ላይ የሚገኙና መሥፈርቱን አሟልተው ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚዛወሩ ዓቃቤያነ ሕግ በዚህ አዋጅ መሠረት በዓቃቤ ሕግነት እንደተሾሙ ተቆጥረው ሥራቸውን ይቀጥላሉ።
3. በፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ በፍትህ ሚኒስቴር እና በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ለዓቃቤ ሕግ የሥራ ክፍሎች በድጋፍ ሰጪነት ሥራ ላይ የሚገኙና በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ውሳኔ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚዛወሩ የመንግስት ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሠራተኞች ሆነው ሥራቸውን ይቀጥላሉ።

4. በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ሆነው ነገር ግን በተለያዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም በክልል ዓቃቤ ህግ ተይዘው በመታየት ላይ የሚገኙ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ጉዳዩች የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በስድስት ወር ውስጥ እስኪረከባቸው ድረስ በተጀመሩበት አኳኋን መታየት ይቀጥላሉ፤ እንዲሁም የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር በነበረበት ሁኔታ ይቀጥላል።
5. በዲስፕሊን ኮሚቴዎች ወይም በሌሎች የዓቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤዎች በመታየት ላይ ያሉ የዓቃቤ ሕግ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ተላልፈዋል።
6. ሌሎች በፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን የሚገኙ የዓቃቤ ሕግ መዛግብትና ሰነዶች እንዲሁም የተያዙና በክርክር ላይ ያሉ ንብረቶች ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይዛወራሉ።

26.<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. ስለዓቃቤያነ ሕግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 74/1986 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚት አይኖራቸውም።

27.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ለ/ ለጠቅላይ ሚኒስትር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

### አዋጅ ቁጥር 257/1994

### የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት ባልተጠበቀ ሁኔታ ከሚከሰቱም ሆነ አመጣጣቸው ሊታይ ከሚችል አደጋዎችና ፈተናዎች በመጠበቅ ረገድ ተጨማሪ ዋስትና ሊያስገኝ የሚችል አሠራር መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 257/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ከዚህ በኋላ (ምክር ቤቱ) እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
   2. ምክር ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላል።

3. **የምክር ቤቱ አባላት**

   1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት ቋሚ አባላት ይኖሩታል፣

      ሀ/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ................................ ሰብሳቢ

      ለ/ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ............... ም/ሰብሳቢ

      ሐ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ .......................... አባል

      መ/ የመከላከያ ሚኒስትሩ .............................. "

      ሠ/ የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ................................................... "

      ረ/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ........... "

      ሰ/ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ኃላፊ .......... አባልና ፀሐፊ።

   2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፤

      ጠቅላይ ሚኒስትሩ፦

      ሀ/ ተጨማሪ የምክር ቤት አባላትን ለመሰየም፣ እና

ለ/ ማንኛውም ሰው ሙያዊ ምክር ለመስጠት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት እንዲገኝ ለመፍቀድ ይችላል።

4. **የምክር ቤቱ ተግባር**

1. ምክር ቤቱ የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት የሚመለከቱ የውጭና የመከላከያ ፖሊሲዎች እንዲጣጣሙ በማድረግና በሚገባ ተግባራዊ መደረጋቸውን በመከ ታተል ረገድ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ያማክራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምክር ቤቱ፣

   ሀ/ ለሀገሪቱ ብሔራዊ ደህንነት የሥጋት ምንጭ የሆኑ ሁኔታዎችን በመገምገም ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ሃሣብ ያቀርባል፤

   ለ/ የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚመለከቱ የአፈጻጸም መመሪያዎች ያመነጫል፤

   ሐ/ የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት በሚነካ ማናቸውም ጉዳይ ላይ ይመክራል።
3. ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 93 መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲደነገግም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰኑ ተግባሮችን ያከናውናል።

5. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

1. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይኖራል።
3. ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

6. **የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች የሚኖሩዋቸው አባላትና ዝርዝር ተግባራቸው በምክር ቤቱ ይወሰናል።

7. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት 2 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 2 ቀን 1994 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**አዋጅ ቁጥር 459/1997 ዓ.ም**

**የቤተመንግሥት አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

የቤተመንግሥት አስተዳደርን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለዉ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ እንዲቋቋም ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የቤተመንግሥት አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 459/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

1. የቤተመንግሥት አስተዳደር (ከዚህ በኋላ "አስተዳደር" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የአስተዳደሩ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

3. <u>**የአስተዳደሩ ዋና መስሪያ ቤት**</u>

የአስተዳደሩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቤተመንግሥት ባለበት በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ይኖረዋል።

4. <u>**የአስተዳደሩ ዓላማ**</u>

የአስተዳደሩ ዓላማ ቤተመንግሥቶችን የማስተዳደርና የቤተመንግሥት ቅርሶችን የመጠበቅ ይሆናል።

5. <u>**የአስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

አስተዳደሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፤

1. ብሔራዊ ቤተመንግሥትንና ይህ አዋጅ እስከፀናበት ድረስ በሥሩ የቆዩትን ቤተመንግሥቶችና ሌሎች በፌደራል መንግሥት የሚቋቋሙ ቤተመንግሥቶችን ያስተዳድራል፣
2. የቤተመንግሥት ቅርሶችን ይንከባከባል፣ እንዳስፈላጊነቱ እንዲጠገኑ ያደርጋል፣
3. የቤተመንግሥት ተቋሞችና ቅርሶች ደህንነታቸው በማይጎዳ ሁኔታ የቱሪስት መስህብ ሆነው እንዲያገለግሉ ያደርጋል፣
4. በቤተመንግሥት የሚደረጉ የመንግሥት መስተንግዶዎችን ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፤
5. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
6. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባሮችን ያከናውናል።

6. <u>**የአስተዳደሩ አቋም**</u>

ኮሚሽኑ፣

1. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተር[1]፣ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

---

[1] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) መሠረት "ዋና አስተዳዳሪ" እና "ምክትል አስተዳዳሪ" በ"ዋና ዳይሬክተር" እና በ"ምክትል ዋና ዳይሬክተር" ተተክተዋል፡፡

7. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የአስተዳደሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የአስተዳደሩን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ለአስተዳደሩ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፣
   ለ/ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግና በመንግሥት በሚፈቀድ የደመወዝ ስኬል መሠረት የአስተዳደሩን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
   ሐ/ የአስተዳደሩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እያዘጋጀ ለመንግሥት ያቀርባል፣
   መ/ በተፈቀደው የአስተዳደሩ በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ አስተዳደሩን ይወክላል።
3. ዋናው ዳይሬክተር ለአስተዳደሩ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ለአስተዳደሩ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

8. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል አስተዳዳሪው፣

1. ዋና ዳይሬክተሩ በሌለ ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣
2. በዋና ዳይሬክተር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

9. **<u>የአስተዳደሩ በጀት</u>**

የአስተዳደሩ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፣

1. በፌዴራሉ መንግሥት ከሚመደብ በጀት፣
2. የቤተመንግሥት ተቋሞችንና ቅርሶችን ከማስጎብኘት የሚገኝ ገቢ፣ እና
3. በቤተመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኝን መሬት በመጠቀም ከሚካሄድ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ።

10. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. አስተዳደር የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትና ሠነዶች ይይዛል።
2. የአስተዳደሩ የሂሳብ መዛግብትና ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

11.**ስለሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት**

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሥልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደሩ የቤተመንግሥት ቅርሶችን የመጠበቅና የማስተዳደር ሥልጣንና ተግባሩን በሥራ ላይ የሚያውለው ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በመከተል ይሆናል።

12.**ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻፀም ደንብ የማውጣት ሥልጣን አለው።

13.**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ከሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 591/2000 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት የተረጋጋ የዋጋ፣ የውጭ ምንዛሬ ምጣኔና የጤና የፋይናንስ ሥርዓት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተመጣጠነ ዕድገት ተስማሚ የሆኑ ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን ስለአለበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 591/2000 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. “ሥልጣን የተሰጠው መንዛሪ” ማለት ከባንኮች በስተቀር በውጪ አገር ገንዘብ ግብይት ለመሠማራት ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው
2. “የባንክ ሥራ” ማለት የሚከተሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፤

   ሀ/ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አለው ብሎ በፈቀደው የገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል፤

   ለ/ የባንክ ሥራ በሚሠራው ሰው ሂሣብና ኃላፊነት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የተመለከተውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው ብድሮች፣ ኢንቨስትመንቶችና ሌሎች ጉዳዮች የማዋል፤

   ሐ/ በገንዘብ መልክ ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የመግዛትና የመሸጥ፤

   መ/ በራሳቸውም ሆነ በደንበኞቻቸው ስም ለሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች ገንዘብ የማስተላለፍ፤

   ሠ/ በገንዘብ ማስከፈያ፣ በሐዋላና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች በተረጋገጡ የዕዳ ሰነዶች በቅናሽ የማበደርና የማስተላለፍ፤

   ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሠ) በተመለከቱት ተግባራት የተሠማራ ባንክ እንዲሠራቸው በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያገኙ በተለምዶ እንደባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፤
3. “ባንኮች” ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠሩ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሠጣቸው ኩባንያዎች ወይም የመንግሥት ባንኮች ናቸው፤
4. “የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የሚቋቋም ፈንድ ነው፤
5. “የውጭአገር ገንዘብ” ማለት ከኢትዮጵያ ገንዘብ በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጭ፣ በማናቸውም ሃገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ያሳወቀው ማናቸውም ገንዘብ ነው፤

6. “የውጭ ምንዛሪ” ማለት በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸው የውጭ ሃገር ገንዘቦችና በውጭ ሃገር ገንዘብ የተዘጋጁ የክፍያ ማዘዣ ቼኮች፣ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ ሰነዶች፣ ድራፍቶች፣ ሴኪዩሪቲዎች፣ እንደዚሁም ሌሎች የሚተላለፉ ሰነዶችና በውጭ ሃገር ገንዘብ የተያዙ የባንክ ሂሳቦች ወይም የሚከፈሉ ወይም በውጭ ሃገር ሂሣብ ወይም የማቻቻል አሠራር የሚደረግባቸው ንብረቶች ማለት ነው፤
7. “መንግስት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፤
8. “መድን ሰጪዎች” ማለት አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋሙ የመድን ኩባንያዎች ናቸው፤
9. “ገንዘብ-አከል ንብረት” ማለት ከገንዘብ ተቋማት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

   ሀ/ ጥሬ ገንዘብ፤

   ለ/ በብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባንኮች ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፤

   ሐ/ በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸውና ያለገደብ ሊተላለፉ የሚችሉ በብር ወይም በውጭ ምንዛሪ ተከፋይ የሆኑ ንብረቶች፤

   መ/ በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ገንዘብ-አከልተብለው ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች ንብረቶች፤
10. “ሌሎች የገንዘብ ተቋማት” ማለት አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግና ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የተቋቋሙ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሞች፣ የፖስታ ቁጠባ፣ የገንዘብ አስተላላፊዎችና ሌሎች መሠል ተቋማት ማለት ነው፤
11. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
12. “ብሔራዊ ባንክ” ማለት የሀገሪቱ ማዕከላዊ ባንክ የሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤
13. “በውጪ ምንዛሪ የሚፈፀም ግብይት” ማለት

   ሀ/ የውጭ ምንዛሪ ማስተላለፍ፣ መበደር፣ ማበደር፣ ማዛወር፣ መመንዘር፣ መግዛት፣ መሸጥ፣መቀበል፣ መክፈል ወይም ሂሣብ ውስጥ ማስገባት፤ እና

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ የውጭ ምንዛሪ ማስተላለፍን፣ መበደርንና ማበደርን፣ ማዛወርን፣ መመንዘርን፣ መግዛትን፣ መሸጥን መቀበልን፣ መክፈልን ወይም በሂሣብ ውስጥ ገቢ ማድረግን የሚያስከትል ውለታ፣ ስምምነት ወይም መግባባት ነው፤

14.“ዋጋ ያለው ዕቃ” ወይም “ዋጋ ያለው ነገር” ማለት ማናቸውም የገንዘብ ዋጋ ያለው ዕቃ ነው።ሆኖም በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ላይ የተመለከተውን የመንገደኛ ሻንጣና መንገደኛ ወደ ኢትዮጵያ ይዞት የሚመጣውን የውጭ ምንዛሪ አይጨምርም።

15.“ኩባንያ” ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ህግ የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ በሙሉ በኢትዮጵያዊያንና በኢትዮጵያዊያን ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ የአክስዮን ማህበር ነው።

## ክፍል ሁለት

## የብሔራዊ ባንክ አደረጃጀት[2]፣ አመራርና ተግባራት

### 3. ሕጋዊ አቋም

1. በትዕዛዝ ቁጥር 30/1955 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ራሱን ችሎ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር ተቋም ሆኖ ይቀጥላል።
2. ብሔራዊ ባንክ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ኖሮት፣ በተለይም

   ሀ/ ውል የመዋዋል፣

   ለ/ የመክሰስና የመከሰስ፣ እና

   ሐ/ ንብረት የመያዝ፣ የማግኘት፣ ባለቤት የመሆንና ንብረቱን በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የማስወገድ፣

   ችሎታ ይኖረዋል።
3. የብሔራዊ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል። ባንኩ፣

   ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ማቋቋምና መዝጋት፣ እና

   ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ እና በውጭ አገር ወኪሎች እና አገናኝ ባንኮች መሰየምና መሻር፣

   ይችላል።

---

[2] በ16/8(2002) ደ.172 የባንኩ አደረጃጀት ተለወጠ፡፡

4. የብሔራዊ ባንክ ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል።
5. ብሔራዊ ባንክ፣

   ሀ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣

   ለ/ በመንግሥት የሚሾሙ ገዥና ምክትል ገዥ፣እና

   ሐ/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣

   ይኖሩታል።
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩታል። የብሔራዊ ባንክ ገዥ እና ምክትል ገዥ የቦርዱ ቋሚ አባላት ይሆናሉ። የቦርዱ ሊቀመንበር እና ቀሪዎቹ አባላት በመንግስት ይሾማሉ።

## 4. ብሔራዊ ባንክ ዓላማዎች

የብሔራዊ ባንክ ዓላማ የተረጋጋ የዋጋና የውጭ ምንዛሪ ተመን ማስፈን፣ ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት መገንባትና ለኢትዮጵያ ፈጣን ኢኮኖሚ ልማት አመቺ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን ይሆናል።

## 5. የብሔራዊ ባንክ ሥልጣንና ተግባር

ብሔራዊ ባንክ ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. ሕጋዊ ገንዘብን የመቅረጽ፣ የማተም ወይም የማስቀረጽ፣ የማሳተምና የማሠራጨት፤
2. በሕጋዊ መንገድ የወጡትን ሣንቲሞችና የገንዘብ ኖቶችን ማስወገድ ወይም እንዲወገዱ የማድረግ፤
3. የራሱን የዕዳና ክፍያ ሰነዶችን የማውጣት፤
4. የገንዘብና ብድር አቅርቦት በተፈለገው መጠን መገኘትን፣ እንዲሁም የወለድ ተመንና ሌሎች ክፍያዎችን የመወሰንና የመቆጣጠር፤
5. የውጭ ምንዛሪ ተመን ፖሊሲ የመቅረጽና ተግባራዊ የማድረግ፤
6. የኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሣቦች የማስተዳደርና የመምራት
7. ለባንኮች፣ ለመድን ሰጪዎችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ፈቃድ የመስጠትና ሥራቸውን የመቆጣጠር፤
8. የባንክ፣ የመድንና ሌሎች የገንዘብ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን የመፍጠር፤

9. ባንኮችና ፈቃድ የተሰጣቸው መንዛሪዎች ሊይዙት የሚችሉትን ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ገደብ የመወሰን፤
10. ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የሚይዙትን የተጣራ የውጭ ምንዛሪ ልክ፣ እንዲሁም የውጭ ዕዳ ስምምነቶችና የዕዳውን ገደብ የመወሰን፤
11. ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የአጭርና የረጅም ጊዜ የብድር አገልግሎት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲያገኙ የማድረግ፤
12. ማናቸውም ዓይነት ተቀማጭ ገንዘብ ከውጭ አገር ምንጮች የመቀበል
13. ከማንኛውም ሰው መረጃዎችን በመሰብሰብ የክፍያ ሚዛን፣ የገንዘብ አቅርቦትና የዋጋ ትንበያዎችን እንዲሁም ለትንተናና የገንዘብ፣ የቁጠባና የምንዛሪ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽና ለመወሰን የሚረዱትን ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጠቋሚ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የያዘ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠቃሚ የሆኑ ጥናቶችን በየጊዜው የማካሄድ፤
14. መንግሥትን በባንክ አገልግሎት፣ በገንዘብ ውክልናና በፋይናንስ አማካሪነት የማገልገል፤
15. የክፍያ፣ የማጣራትና የማወራረድ ሥርዓት የማቋቋም፣ ዘመናዊ የማድረግ፣ የማካሄድ፣ የመከታተልና የመቆጣጠር፤
16. ኢትዮጵያ የተዋዋለቻቸውን ዓለም አቀፍ የገንዘብና የባንክ ስምምነቶች በማክበር የመሥራትና አገሪቱን በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንዲሁም በሌሎች በማዕከላዊ ባንኮች በተቋቋሙ ዓለምአቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ዘንድ የመወከል፤
17. ልዩ የመታሰቢያ ሣንቲሞች የመቅረጽ፤
18. የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የማቋቋምና የመምራት፤
19. ዓላማዎቹን ለማስፈጸም ማዕከላዊ ባንኮች በተለምዶ የሚኖራቸውን ሌሎች ሥልጣኖች መጠቀምና ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

6. <u>ካፒታልና የመጠባበቂያ ሂሣቦች</u>

1. የብሔራዊ ባንክ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤነት የተያዘ ይሆናል። የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ብር 500 ሚሊዮን (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ሊጨምር ይችላል።

2. ከተጣራ ትርፍ ውስጥ 20 በመቶ (ሃያ በመቶ) የባንኩ የመጠባበቂያ ሂሣብ የተከፈለው የካፒታል መጠን ጋር እስኪስተካከል ድረስ በየበጀት ዓመቱ ወደዚሁ ሂሣብ ገቢ ይሆናል፤ ቀሪው 80 በመቶ (ሰማንያ በመቶ) ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሂሣብ ገቢ ይሆናል።
3. ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከተከፈለው ካፒታል ጋር እኩል ሲሆን፣ የተጣራው ትርፍ በሙሉ በየበጀት ዓመቱ ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሂሣብ ገቢ ይሆናል።
4. የተጣራ የብሔራዊ ባንክ ኪሣራ ከጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ላይ ተቀናሽ ይሆናል።
5. ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም ጊዜ በደረሰበት የተጣራ ኪሣራ የተነሣ ጠቅላላው የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከካፒታሉ ያነሰ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከባንኩ ካፒታል ጋር እንደገና እስኪስተካከል ድረስ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
6. መንግሥት የብሔራዊ ባንክ ካፒታል በማናቸውም ጊዜ ሳይቀነስ እንደተጠበቀ መቆየቱን ያረጋግጣል።

7. <u>የሂሣብ ዓመትና የሂሣብ መግለጫዎች</u>

1. የብሔራዊ ባንክ የሂሣብ ዓመት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ቀን ያበቃል።
2. የብሔራዊ ባንክ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የሂሣብ ሚዛንና ከሂሣቦቹ ጋር የተያያዙ ማስታወሻዎች የሚሠሩት በዓለም አቀፍ የሂሣብ አያያዝ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃ መሠረት ይሆናል።
3. የብሔራዊ ባንክ የሂሣብ ዓመት ባለቀ በሦስት ወርጊዜ ውስጥ ባንኩ ኦዲት ያልተደረገ የሂሣብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና የኪሣራውን መግለጫ አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል።

8. <u>የውጭ ኦዲት</u>

1. የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ በየዓመቱ የውጪ ኦዲተር ይሾማል። የኦዲት ሪፖርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የባንኩ ቦርድ ኦዲት ኮሚቴ መርምሮ እንዲያፀድቀው መቅረብ አለበት። እያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በኦዲት ኮሚቴ የፀደቀው የኦዲት ሪፖርት ለመንግሥት መላክ ይኖርበታል

2. በኦዲተር በሚገባ የተመረመረና የተፈረመ የሂሣብ ሚዛንና የዓመቱን ትርፍና ኪሣራ የሚያሳይ መግለጫ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ ይታተማሉ።

9. <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን፣ ተግባር እና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት የብሔራዊ ባንክ ሥልጣኖች፣ ኃላፊነቶች እና ተግባሮች ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተሰጥተዋል።
2. ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አራቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል። ሆኖም ከተገኙት አባላት አንዱ የባንኩ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ መሆን ይኖርበታል
3. የቦርዱ ስብሰባዎች በሊቀመንበሩ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በወከለው የቦርድ አባል ይጠራል።
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል። ሆኖም ሊቀመንበሩ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በእርሱ የተወከለ ሰው ወይም ገዥው ወይም ከቦርዱ አባላት ሦስቱ ሲጠይቁ ስብሰባው በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።
6. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈለው አበል መጠን በመንግሥት ይወሰናል
7. ማናቸውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባሎች አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤ቦርዱ በድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ቦርዱ በሚወስነው አኳኃንና በትክክል ይመዘገባል። ቦርዱ በይፋ እንዲታወቅ ካልፈቀደ በቀር ማናቸውም ቃለጉባኤ በሚስጥር ይጠበቃል።
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣኑን ለገዥው በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።
11. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ ሦስት የቦርድ አባላትን ያካተተ የኦዲት ኮሚቴ ይኖረዋል። ኮሚቴው የውስጥና የውጭ ኦዲተሮችን ግኝትና የመፍትሄ ሃሣብ ተቀብሎ ይመረምራል፤ ለአፈጻጸሙም አስፈላጊውን መመሪያ ይሠጣል።

10. <u>የብሔራዊ ባንክ ገዥ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የብሔራዊ ባንክ ገዥ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በዚህ አዋጅና በቦርዱ ውሣኔዎች መሠረት የባንኩን ኮሚሽንና ሥራ ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
2. ገዥው የብሔራዊ ባንክን ዕቅድና አመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሲጸድቅም በሥራላይ ያውላል።
3. ገዥው የብሔራዊ ባንክ ዋና ተጠሪ በመሆን ባንኩ፣
   ሀ/ ከሌሎች ሰዎች፣ ከመንግሥት፣ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ብሔራዊ ባንክ አባል ከሆነባቸው የገንዘብ ድርጅቶች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ባንኩን ይወክላል፣
   ለ/ የሚያደርጋቸውን ውሎች፣ የሚያሳትማቸውን የገንዘብ ኖቶችና የዋስትና ሰነዶች፣ ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ የሂሣብ ሚዛን ሰነዶች፣ የትርፍና የኪሣራ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤ ዎችና ሌሎች የባንኩን ሰነዶች ብቻውን ወይም ከተፈቀደላቸው ሌሎች የባንኩ ሹማምንት ጋር በአንድነት ይፈርማል፣ እና
   ሐ/ በሚከስበት ወይም በሚከሰስበት ማናቸውም ጉዳይ ራሱ ወይም በነገረፈጅ አማካይነት የባንኩ ወኪልይሆናል።
4. ገዥው ለብሔራዊ ባንክ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ተግባሩንና ሥልጣኑን በከፊል ለምክትል ገዥውና ለሌሎች የባንኩ ሹማምንት በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።
5. ገዥው በማናቸውም ተግባሩ በአንቀጽ 4 ላይ በተመለከቱት የብሔራዊ ባንክ ዓላማዎች ይመራል።

11.<u>የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ ስልጣን እና ተግባር</u>

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ የባንኩን ገዥ ይረዳል፤ ገዥው በሌለ ጊዜ ለገዥው የተሰጡትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ብሔራዊ ባንክ ከመንግስት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

12.<u>የመንግሥት የገንዘብ አስተዳደር ተወካይና ባንክ መሆን</u>

ብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት የመንግሥት ወኪልና ባንክ ሆኖ ይሠራል፤ በዚህም መሠረት በመንግሥት ስም እና ሂሣብ ለመንግሥት የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፦

1. ተቀማጭ ገንዘብ ይቀበላል፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቀማጭ ገንዘቦችን ይሰበስባል፣ በአደራ ያስቀምጣል፣ ክፍያም ይፈጽማል ወይም ያስተላልፋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ሌሎች ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ስም እነዚህን ተግባራት እንዲያከናውኑ ሊወክል ይችላል፤ በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[3] ሲጠየቅ በዚህ አኳኋን የተያዙ ሂሣቦችን በሚመለከት መረጃዎችን ያቀርባል፤
2. ቼኮች፣ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ ሰነዶችና የዋስትና ሰነዶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል ወይም በአደራ ተረክቦ ያስቀምጣል፤
3. እንደ ወርቅና ብር ያሉትን የከበሩ ማዕድናትና የውጭ አገር ገንዘብ ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል ወይም በአደራ ተረክቦ ያስቀምጣል፤
4. ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በተለይ የተዘረዘሩ የመንግሥት ሂሣቦችን ያስተዳድራል፤
5. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን ሲሰጠው የመንግሥት ዕዳን ያስተዳድራል፣ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነዶችንና ቦንዶችን እንዲሁም ሌሎች የዋስትና ሰነዶችን ይሸጣል፣ ያስተዳድራል፣
6. ለመንግሥት ብድር ይሰጣል፤
7. በመንግሥት የወጡ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተላለፉ የግምጃ ቤት ሰነዶችና ቦንዶች ይገዛል፣ ይሸጣል።

13. <u>ብድር</u>

1. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት የሚሰጠው የብድር መጠን ከባንኩ ጋር በሚደረግ ምክክር የሚወሰን ሆኖ የዋጋና የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ መረጋጋትን ከማስፈን ዓላማ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።
2. ባንኩ ለመንግሥት፣ ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም ሰው በቀጥታ ብድር አይሰጥም።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ብሔራዊ ባንክ ለባንኮች፣ ለመድን ሰጭ ድርጅቶች ከሌሎች የገንዘብ ተቋማት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

[3] በአዋጁ ውስጥ "የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር" ተብሎ የተጠቀሰው በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(6) መሰረት "የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር" ተብሎ ይነበብ፡፡

14.<u>ፍቃድ ስለመስጠትና መቆጣጠር</u>

ብሔራዊ ባንክ ለባንኮች፣ለመድን ሰጭ ኩባንያዎችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረተ ፈቃድ ይሰጣል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል።

15.<u>የብድር አሰጣጥና አስተዳደር</u>

1. ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ/ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሚዛናዊ ዕድገት ተስማሚ የሆነ የተረጋጋ የዋጋና የምንዛሪ ምጣኔ ለማስፈን፣

(1) ከባንኮችና ከሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ጋር ስላለው የብድር ግንኙነት፣ እና

(2) በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ስለሚሰጡ የብድር አገልግሎቶች፣

መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

ለ/ እንደነገሩ ሁኔታ በአግባቡ የተፈረሙና በባለቤቱ በጀርባ በመፈረም የተረጋገጡ የሐዋላ ሰነዶች፣የተስፋ ሰነዶች፣ አክሴፕታንሶችና ሌሎች የገንዘብ መክፈያ ሰነዶች በቅናሽ ወይም ድጋሚ ቅናሽ በማድረግ የሚገዛበት ወይም የሚሸጥበት፣ ከባንኮችና ከሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ጋር የሚሠራበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፤

ሐ/ ቅናሽ ወይም ድጋሚ ቅናሽ በማድረግ በሚቀበላቸው ሕጋዊ ሰነዶች ላይ የሚከፈለውን የወለድ መጠን ይወስናል፣

መ/ በሚያወጣጡ መመሪያ በሚወሰኑ ግዴታዎችና ሁኔታዎች መሠረት ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ብድር ሊሰጥ ይችላል።

2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሀገሪቱ ውስጥ በሰፊው በሚሠራጩ ጋዜጦች ታትመው እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል።

16.<u>ሌሎች ተግባሮችና አገልግሎቶች</u>

1. ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ/ ባንኮች፣ መድን ሰጪ ኩባንያዎችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት በተቀበሉት ተቀማጭ ገንዘብ ላይ ወይም በሌላ መለኪያ ላይ ተመሥርቶ በሚሠላ መጠን በጥሬ ገንዘብ፣ በሌላ ገንዘብ አከል ንብረቶችና በመንግሥት የዋስትና ሰነድ

የሚይዙትን የሀብት መጠን ሊወስንና ይሄው ሀብት በባንኩ እንዲቀመጥ በየጊዜው ሊያዝ ይችላል፤

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ከተገለጸው በተጨማሪ ከባንኮችና ከሌሎች የገንዘብ ተቋማት በአደራ ገንዘብ ተቀብሎ ሊያስቀምጥ እንዲሁም በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ስም ወይም ስለእነርሱ ሆኖ ገንዘብ ሊቀበል ይችላል፤

ሐ/ ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት የክፍያና የክሊሪንግ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፤

መ/ የባንኮችንና የሌሎችን የገንዘብ ተቋማት ሂሣብ ሊይዝና ወኪላቸው ወይም ተጠሪያቸው ሆኖ ሊሠራ ይችላል።

2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፤ የክፍያውን መጠን ለባንኮቹ እና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት በቅድሚያ ያሳውቃል።

## ክፍል አምስት

## የገንዘብ መደብ ልክና ሕጋዊ ገንዘብ

### 17.የገንዘብ መደብ

1. የኢትዮጵያ የገንዘብ መደብ ብር ሲሆን የሀገሪቱ ሕጋዊ ገንዘብ ይሆናል። የብር ኦፊሴላዊ አጭር ስያሜ “ብር” የሚል ይሆናል። “ኢትብ” የሚለው የብር ዓለም አቀፋዊ አጭር ስያሜ ይሆናል።
2. የገንዘብ መደቡ “ሳንቲሞች” ተብለው በሚጠሩና እኩል በሆኑ አንድ መቶ ክፍልፋዮች ይከፈላል።የሣንቲም አጭር ስያሜ “ሳ” ይሆናል።
3. በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተደረገ ስምምነት እስካልሆነ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉ ማናቸውም የገንዘብ ስምምነቶችና ውሎች በብር እንደተፈጸሙ ይቆጠራል።
4. ብሔራዊ ባንክ በሌላ አኳኋን ካልፈቀደ ወይም ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም የአገሪቷ ሕጎች ላይ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም የገንዘብ ግንኙነቶች ሁሉ የሚመዘገቡትና የሚከፈሉት በብር ይሆናል።

**18.ሕጋዊ ገንዘብ**

1. በገንዘብ ኖቶች ላይ የሚጻፈው ጽሑፍ፣ የኖቶቹ ስፋት፣ ቅርጽና መደባቸው እንዲሁም ሌሎች ልዩልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።
2. የቅንስናሽ ገንዘቦች ክብደት፣ ጥራት፣ ጽሁፍ፣ ስፋት፣ ቅርጽ፣ መደብና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናሉ። በተመሣሣይ የመታሰቢያ ሣንቲሞች ሕጋዊ ተቀባይነት፣ ብዛት፣ ክብደት፣ ጥራት፣ ጽሑፍ፣ ስፋት፣ ቅርጽና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።
3. ኢትዮጵያ ውስጥ በዝውውር ላይ ያሉ ሕጋዊ የብርኖቶች ሁሉ ማናቸውንም የመንግሥተም ሆነ የግል ዕዳ ያለገደብ ለመክፈል ሕጋዊ ገንዘብ ናቸው።
4. ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ሆነው በዝውውር ላይ ያሉ ቅንስናሽ ገንዘቦች ማናቸውንም የመንግሥትም ሆነ የግል ዕዳ ለመክፈል ሕጋዊ ገንዘብ ናቸው። ተዋዋይ ወገኖቹ በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር ዕዳ ለመክፈል የሚውለው የቅንስናሽ ገንዘብ መጠን ከአሥር ብር አይበልጥም። ሆኖም ብሔራዊ ባንክም ሆነ ሌሎች ባንኮች በማንኛውም አምጪ ጥያቄ ቅንስናሽ ገንዘቦቹን ወደ ኖቶች መቀየር አለባቸው።
5. ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም ጊዜ የብር ኖቶችን ወይም ሣንቲሞችን የአስመስሎ ሥራት መከላከያ ግልጽና ስውር ምልክቶች የቀየረ እንደሆነ፣ ወይም በሥራ ላይ የነበረ ኖት ወይም የተለየ መደብ ያለው ኖት ወይም ሣንቲም ከተወሰነ ቀን በኃላ ሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብነቱ መቅረቱን፣ መመሪያ በማውጣት ሊያሳውቅ ይችላል፤ የተደረገውን ለውጥ በሰፊው በሚሰራጩ ጋዜጦችና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ይገልጻል፤ የሚለወጡትን ኖቶችና ሣንቲሞች የያዙ ሁሉ በአዲሶቹ ኖቶችና ሣንቲሞች የሚለውጡበት በቂ ጊዜ ይሰጣል።
6. ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ማንኛውም ሰው በባንኩ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው በላይ የኢትዮጵያን ገንዘብ ይዞ ወደሃገር ውስጥ ለመግባት ወይም ለመውጣት አይችልም።

**ክፍል ስድስት**

**ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ እና የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር**

**19.ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ ስለመያዝ**

1. ብሔራዊ ባንክ የውጭ አገር ገንዘብ፣ የግዴታ ሰነዶች፣ ወርቅ ወይም ሌሎች ዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ንብረቶችን ያካተተ ሂሣብ ይኖረዋል።
2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚይዘው ዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሣብ በማናቸውም ጊዜ፣

   ሀ/ በአስቸኳይና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ክፍያን፣

   ለ/ የውጭ አገር ዕዳ ክፍያ ግዴታዎችን፣ እና

   ሐ/ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ክፍያን፣

   በበቂ ሁኔታ ለመሸፈን የሚያስችል እንዲሆን ጥረት ያደርጋል።
3. የዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ገንዘብ ከሚያስፈልገው መጠን ያነሰ እንደሆነ ወይም ሊያንስ እንደሚችል ገዥው ካመነበት ወይም የመጠባበቂያ ገንዘቡ በቂነት የመቀነስ አዝማሚያ እያሣየ መሆኑን ሲገነዘብ የመጠባበቂያ ገንዘቡን ይዞታ፣ ለሁኔታው መንስኤ የሆኑትን ወይም ሊሆኑ የሚችሉትን ምክንያቶች እና ሁኔታውን ለማሻሻል አስፈላጊ የመሰለውን የመፍትሄ እርምጃ የያዘ የወሳኔ ሃሳብ ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል።ችግሩ እየተባባሰ መሄዱን ከተገነዘበ ገዥው የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዳይሰጥ ሊያግድ ይችላል።
4. ብሔራዊ ባንክ ለባንኩና ለሃገሪቱ ጠቃሚ ሆነው የሚታዩትን የሁለትዮሽና ሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብና የክፍያ እንዲሁም ተዛማጅ ስምምነቶች ሊዋዋል ይችላል።

20.<u>የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር</u>

1. ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ፈቃድ ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሔራዊ ባንክ የተለየ ፈቃድ ካላገኘ በቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሠማራት አይፈቀድለትም።
2. ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ፣ ነዋሪ ያልሆኑና ለጉብኝት የመጡ ሰዎች ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው የውጭ ምንዛሪ የሚይዝበትን ወይም በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚፈጽምበትን ወይም የክፍያ ማዘዣዎችን የሚይዝበትንና የሚጠቀምበትን ሁኔታዎችና ገደቦች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።
3. ማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ የሚተላለፍ የውጭ ምንዛሪ፣ በወጪ፣ ወይም በገቢ ንግድ አማካይነት ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ወደ ሀገር

ውስጥ የሚገቡ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ወይም ሌሎች ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች በማናቸውም አኳኋን የኢትዮጵያን የጉምሩክ ድንበር አቋርጠው የሚወጡበት፣ እነዚህ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚመለሱበት፣ ወይም ከላይ የተመለከቱት ወደ ውጭ የተላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ወይም ከውጭ የተመለሱ ዕቃዎች በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚያስከትሉት ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤት የሚመለከቱ ግዴታዎችና ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

4. ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን ካላረጋገጠ በስተቀር የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማናቸውንም ዋጋ ያለው እቃ ወይም የውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ወይም እንዲገባ አይፈቀድም፡
5. ባንኮች፣ የመድን ሰጪ ኩባንያዎችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት በወጭ ምንዛሪ የሚያደርጉትንልውውጥ ወይም ግብይት ብሔራዊ ባንክ በቦታው ተገኝቶ በመመርመር ወይም በሚቀርቡለት መረጃዎች መሠረት በመከታተል መቆጣጠር ይችላል።
6. ማንኛውም ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ሥልጣን የተሰጠው ምንዛሪ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተደነገጉት መፈጸም ወይም አለመፈጸማቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በእጁ የሚገኙትን ወይም የሚያዝባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች፣ የሂሣብ መዛግብትና ሴሎች ሰነዶች በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ለባንኩ ወይም ባንኩ ለመደበው ወኪል ማቅረብ አለበት።

21.<u>በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ንብረቶች ስለሚደረግ ግብይት</u>

1. ብሔራዊ ባንክ የውጭ ሃገር ገንዘብ ኖቶች እና ቅንስናሽ ገንዘቦች እንዲሁም በዓለም አቀፍ ክፍያ ወይም ለገንዘብ ማስተላለፊያነት በተለምዶ የሚሠራባቸውን የገንዘብ ማዘዋወሪያና ሌሎች ሰነዶች፣ ሐዋላዎች የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለመግዛት፣ ለመሸጥና ለመያዝ ይችላል።
2. ብሔራዊ ባንክ በውጭ ሃገር ማዕከላዊ ባንኮች፣ በራሱ ወኪሎች ወይም የውጭ ተጠሪ ባንኮች ዘንድ በውጭ ሃገር ገንዘብ ሂሣብ ሲኖረውና ይህንንም ገንዘብ እንደአስፈላጊነቱ በጊዜ ገደብ ተቀማጭ፣ በወርቅ፣ እንደልብ ሊተላለፉ በሚችሉ የውጭ ሃገር የዋስትና ሰነዶችና በሌሎች ኢንቨስትመንቶች ሊያውል ይችላል።

3. ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ/ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት፣

ለ/ ከመንግሥት፣ ከመንግሥት መሥሪያ ቤትችና ተቋሞች፣

ሐ/ ከውጭ ሃገር ማዕከላዊ ባንኮች፣ ከውጭ ሃገር ባንኮችና የገንዘብ ተቋሞች፣

መ/ ከውጭ መንግሥታትና መሥሪያ ቤተቻቸው፣ እና

ሠ/ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት፣

ጋር የውጭ ሃገር ገንዘብ ምንዛሪ ሥራ ሊሠራ ይችላል።

4. ሌላ ተቃራኒ የሕግ ድንጋጌ ሳያግደው ብሔራዊ ባንክ በራሱ ውሳኔ ብቻ ወርቅና ብር የመሳሰሉ የከበሩ ማዕድናት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለመግዛት፣ ለመሸጥ፣ ለማስቀመጥ ወይም በሌላ ሁኔታ ለመገበያየት ይችላል።

5. ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ/ የመድን ሰጪ ኩባንያዎች፣ ሌሎች የገንዘብ ተቋማትና ሥልጣን የተሰጣቸው መንዛሪዎች በውጭ ምንዛሪ፣ በወርቅ ወይም በብር ግብይት እንዲሳተፉ ሥልጣን ሊሰጣቸው ይችላል፤

ለ/ የውጭ ምንዛሪ ፣ የወርቅና የብር ግብይትን አስመልክቶ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል

ሐ/ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዲሰጡ ሊወክላቸው ይችላል

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 22. መረጃ ስለመሰብሰብና ስለመስጠት

1. ብሔራዊ ባንክ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስፈልገውን ማናቸውንም መረጃ ከባንኮች፣ ከመድን ሰጪዎች፣ ከአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከማንኛውም ሰው መጠየቅና መቀበል ይችላል።

2. መረጃው የሚሰጠው፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ለማስፈጸም፣

ለ/ የባንኮች፣ የመድን ሰጪዎችና የሌሎች የገንዘብ ተቋማት የፋይናንስ ጤናማነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሐ/ መረጃውን ለመቀበል ሕጋዊ ሥልጣን ላላቸው፣

መ/ ባንኩ ተጠሪ ለሆነለት አካል፣ ወይም

ሠ/ በፍርድ ቤት የታዘዘ፣

ካልሆነ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የተቀበለውን መረጃ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ላለ ማንኛውም ሰው አሣልፎ አይሰጥም።

3. ማናቸውም ባንክ፣ መድን ሰጪ፣ ሌላ የፋይናንስ ተቋም ወይም በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ማናቸውንም ተግባሮች የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት ያወቀውን ወይም የያዘውን ማንኛውንም ሰው ወይም ድርጅት የሚመለከት መረጃ፣

ሀ/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሲጠይቅ፣

ለ/ መረጃውን ለመቀበል ሕጋዊ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሲጠይቁ፣ ወይም

ሐ/ በፍርድ ቤት ትሰዛዝ፣ ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚገኝ ለማንኛውም ሰው መስጠት አይችልም።

23.<u>ከግብርና ከቀረጥ ነጻ ስለመሆን</u>

1. ብሔራዊ ባንክ ከገቢ ግብር እንዲሁም ከውጭ ሃገር በሚያስገባቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር ገንዘብ ኖቶችና ሣንቲሞች እንዲሁም የመንገደኞች ቼኮች ላይ ሊጣል ከሚችለው ተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ ከጉምሩክ ታክስ ወይም ቀረጥ ነጻ ይሆናል።

2. ብሔራዊ ባንክ ወርቅና ብር እንዲሁም የብርኖቶችንና ቅንስናሽ ሣንቲሞች በወጭ ምንዛሪም ሆነ በሃገር ወስጥ ገንዘብ ወደ ሃገር ውስጥ ሲያስገባም ሆነ ሲያስወጣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የመሙላት ግዴታ የለበትም።

24.<u>ስለሰራተኞች አስተዳደር</u>

የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞችና የሥራ አመራር አባላት አስተዳደር በሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ይሆናል።

25.<u>ስለተቀማጭ መድን ፈንድ ተቋም</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተቀማጭ መድን ፈንድ ስለሚቋቋምበትና ስለሚተዳደርበት ሁኔታ ደንብ ሊያወጣይችላል።

26.<u>ስለቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ፣

(1) በወጭ ምንዛሪ ግብይት የተሳተፈ ወይም የውጭ ምንዛሪ ሲያገኝ ወይም ለማግኘት መብት እንዳለው ሲያወቅ ለባንክ ወይም ፈቃድ ለተሰጠው ምንዛሪ ያላሳወቀ እንደሆነ፣

(2) የውጭ ምንዛሪ የተቀበለ ወይም በወጭ ምንዛሪ ክፍያ የፈጸመ እንደሆነ፣

(3) የውጭ ምንዛሪ የሚቀበልበትን ግዜ ያዘገየ ወይም የመቀበል መብቱን የተወ እንደሆነ፣

(4) በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያ ገንዘብ ይዞ ከኢትዮጵያ የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ወይም የገባ ወይም ለመግባት የሞከረ እንደሆነ፣ ወይም

(5) በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የውጭ ምንዛሪ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፣

ለ/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ወይም አተገባበራቸውን ለማዛባት በማሰብ ማናቸውንም ሰነድ ያጠፋ፣ የቀደደ፣ ይዘቱን የቀየረ፣ የደለዘ ወይም የደበቀ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረበ ወይም ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ እንደሆነ፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 የተደነገገውን በመተላለፍ ማናቸውንም መረጃ ለማይገባቸው ሰዎች የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ/ ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በማናቸውም ሌላ መንገድ የተላለፈ ወይም አተገባበራቸውን ያሰናከለ እንደሆነ፣

ወንጀል የሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ሕጉ መሠረት ይቀጣል፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት በወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

   ሀ/ ወንጀሉ የተፈጸመው ሥልጣንን አለአግባብ በመጠቀም ወይም በመንግሥት ሥራ አጋጣሚ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ለማካበት ወይም በተደጋጋሚ ሲሆን ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከ15 ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 የገንዘብ መቀጫ ይሆናል፤

   ለ/ የወንጀል ድርጊቱ ከገንዘብ፣ ከወርቅ፣ ከዋስትና ሰነድ፣ ከዕቃ ወይም ከማናቸውም ሌላ ንብረት ጋር የተያያዘ ሲሆን ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱና የእሥራት ቅጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል(ሀ) መሠረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር እስከ ንብረቱ ዋጋ ሦስት እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል፤

   ሐ/ ወንጀሉ የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ሲሆን ወንጀሉ የተሠራበት ንብረት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር ድርጊቱ ከተፈጸመበት ወርቅ፣ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነድ፣ ዕቃ ወይም ሌላ ንብረት ዋጋ እስከ ስድስት እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል፤

3. የገቢ ወይም የወጪ ንግድ ዕቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሣንሶ ያቀረበ ማንኛውም ሰው፣ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ ከተመለከተው የገንዘብ ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር ድርጊቱ ከተፈጸመበት ንብረት ዋጋ እስከ ሦስት እጥፍ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣትና ከ15 እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

4. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ማንኛውም የወንጀል ድርጊተ የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅተ ከሆነ ድርጅቱን ይመራ የነበረው ዳይሬክተር ወይም ባለሥልጣን ድርጅቱ ድርጊቱን መፈጸሙን እንደማያውቅና በተገቢው ጥረትም ሊያውቀው እንደማይችል በበቂ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር ከድርጅቱ ጋር ተጠያቂ በመሆን ከሰባት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ

እሥራትና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

5. የወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ሠራተኛ ወይም ወኪል ከሆነና ሠራተኛው ወይም ወኪሉ የድርጊቱን መፈጸም የማያውቅና በተገቢው ጥረትም ሊያውቀው እንደማይችል በበቂ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ይቀጣል።

27.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል።

28.<u>ስለተሻሩና ተፈፀሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

1. የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/1986 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

29.<u>አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ግዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

**ደንብ ቁጥር 172/2002**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተዳደርን እንደገና ለማደራጀት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (አዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተዳደርን እንደገና ለማደራጀት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤትደንብ ቁጥር 172/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 591/2000 ነው፤
   2. "ባንክ" ማለት በትዕዛዝ ቁጥር 30/1955 የተቋቋመውና በአዋጁ አንቀጽ 3(1) መሠረት ራሱን ችሎ የሚተዳደር ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል የተደረገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤
   3. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተመለከተው ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል።

3. **አቋም**

   ባንኩ፦

   1. የዳይሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣
   2. በመንግሥት የሚሾሙ ገዥና ምክትል ገዥዎች፣ እና

3. አስፈላጊ ሠራተኞች፣

   ይኖሩታል።

4. **የቦርዱ አባላት**

ቦርዱ ሰባት አባላት ይኖሩታል። የባንኩ ገዥ የቦርዱ ቋሚ አባል ይሆናል። የቦርዱ ሊቀመንበር እና ቀሪዎቹ አምስት አባላት በመንግሥት ይሾማሉ፤ ሆኖም ከምክትል ገዥዎቹ አንዱ ከሚሾሙት የቦርድ አባላት መካከል ይሆናል።

5. **የቦርዱ ሥልጣን፣ ተግባር እና ስብሰባ ስነ ስርዓት**

1. በአዋጁ የተመለከቱት የባንኩ ሥልጣኖች፣ ኃላፊነቶች እና ተግባሮች ለቦርዱ ተሰጥተዋል።
2. ከቦርዱ አባላት አራቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤ ሆኖም ከተገኙት አባላት አንዱ የባንኩ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ መሆንይኖርበታል።
3. የቦርዱ ስብሰባዎች በሊቀመንበሩ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በወከለው የቦርድ አባል ይጠራል።
4. የቦርዱ ስብስባ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤ ሆኖም ሊቀመንበሩ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በእርሱ የተወከለ ሰው ወይም ገዥው ወይም ከቦርዱ አባላት ሦስቱ ሲጠይቁ ስብሰባው በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።
5. ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።
6. ለቦርድ አባላት የሚከፈለው አበል መጠን በመንግሥት ይወሰናል።
7. ማናቸውም የቦርድ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባሎች አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤ ቦርዱ በድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
8. የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ቦርዱ በሚወስነው አኳኋንና በትክክል ይመዘገባል። ቦርዱ በይፋ እንዲታወቅ ካልፈቀደ በቀር ማናቸውም ቃለጉባኤ በሚስጥር ይጠበቃል።
9. ቦርዱ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።
10. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሊያገኘው ሥልጣኑን ተፈላጊ ሆኖ በተገኘ መጠን ለገዥው በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11. ቦርዱ ቢያንስ ሦስት የቦርድ አባላትን ያካተተ የኦዲት ኮሚቴ ይኖረዋል። ኮሚቴው የውስጥና የውጭ ኦዲተሮችን ግኝትና የመፍትሄ ሃሳብ ተቀብሎ ይመረምራል ፣ ለአፈጻጸሙም አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጣል።

6. <u>የባንኩ ገዥ ስልጣን እና ተግባር</u>

1. የባንኩ ገዥ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በአዋጁና በቦርዱ ውሳኔዎች መሠረት የባንኩን አስተዳደርና ሥራ ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
2. ገዥው የባንኩን ዕቅድና ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል።
3. ገዥው የባንኩ ዋና ተጠሪ በመሆን፦

ሀ/ ባንኩ ከሌሎች ሰዎች፣ ከመንግሥት፣ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና አባል ከሆነባቸው ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባንኩን ይወክላል፤

ለ/ ባንኩ የሚያደርጋቸውን ውሎች፣ የሚያሳትማቸውን የገንዘብ ኖቶችና የዋስትና ሰነዶች፣ ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ የሂሳብ ሚዛን ሰነዶች፣ የትርፍና የኪሣራ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎችና የባንኩን ሌሎች ሰነዶች ብቻውን ወይም ከተፈቀደላቸው ሌሎች የባንኩ ሹማምንት ጋር በአንድነት ይፈርማል፤

ሐ/ ባንኩ በሚከስበት ወይም በሚከሰስበት ማናቸውም ጉዳይ ራሱ ወይም በነገረ ፈጅ አማካይነት የባንኩ ወኪል ይሆናል።

4. ገዥው ለባንኩ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ተግባሩንና ሥልጣኑን በከፊል ለምክትል ገዥዎች እና ለሌሎች የባንኩ ሹማምንት በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።
5. ገዥው በማናቸውም ተግባሩ በአዋጁ አንቀጽ 4 ላይ በተመለከቱት የባንኩ ዓላማዎች ይመራል።

7. <u>የባንኩ ምክትል ገዥዎች ስልጣን እና ተግባር</u>

1. የባንኩ ምክትልገዥዎች የባንኩን ገዥ ይረዳሉ፤ በባንኩ ገዥ ተለይተው የተሰጡ ሥራዎችን ያከናውናሉ።
2. ገዥው በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ገዥ ለገዥው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

8. <u>ደንቡ የሚጸናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ ከኅዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 5 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 277/2005

## ብሔራዊ የኢኮኖሚ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወስን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "ብሔራዊ የኢኮኖሚ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 277/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. ብሔራዊ የኢኮኖሚ ምክር ቤት (በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ለምክር ቤቱ የሴክሬታሪያት አገልግሎት ይሰጣል።

3. **የምክር ቤቱ ዓላማ**

   የምክር ቤቱ ዓላማ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም የሕዳሴውን ጉዞ ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ማማከር ይሆናል።

4. **ተግባርና ኃላፊነት**

   ምክር ቤቱ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም የሕዳሴውን ጉዞ ቀጣይነት ለማረጋገጥ፡-

1. የኢኮኖሚ ነክ ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች ውስጣዊ መስተጋብራቸው ተጠብቆ ለፈጣንና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፆ ማድረግ እንዲችሉ የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና ይህንኑ ማስተባበርን፤
2. የኢኮኖሚ ፖሊሲና ዕቅድ በታቀደው መጠንና ጊዜ እንዲሳካ አስፈላጊ የሆነውን እገዛና ክትትል ማድረግን፤
3. ከኢኮኖሚ ነክ የመንግስት ተቋማት በሚቀርቡ ወቅታዊ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት አጠቃላይ የአፈፃፀም ግምገማ በማድረግ ለቀጣይ ተግባር የሚያግዝ አመራር መሰጠትን፤ እና
4. ሌሎች የአገር ውስጥና ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ ጉዳዮችን፤

በሚመለከት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ያማክራል።

5. **የምክር ቤቱ አባላት**
   1. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።
   2. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራ ይሆናል።
6. **የምክር ቤቱ ስብሰባ**
   1. ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
   2. ለምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሳባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
   3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
7. **ከመንግስት የኢኮኖሚ ነክ ተቋማት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት**
   1. የመንግሥት የኢኮኖሚ ነክ ተቋማት ምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[4] በኩል ያቀርባሉ።
   2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከመንግሥት ኢኮኖሚ ነክ ተቋማት የሚቀርበውን ሪፖርትና መረጃ በማሰባሰብ የተጠቃለለ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

---

[4] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(6) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

3. የመንግሥት የኢኮኖሚ ነክ ተቋማት በምክር ቤቱ ተመክሮባቸው የሚሰጡ አጠቃላይ አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ በሕግ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ።

8. **ደንቡ የሚፀናበት ግዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 281/2005

## ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት እና ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲምክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት እና ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 281/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47/1/ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባን እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት

3. **መቋቋም**

ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት (በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

4. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. ጠቅላይ ሚኒስትር ............................. ሰብሳቢ፤
2. የካቢኔ ሚኒስትሮች ......................... አባላት፤
3. የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች .................. አባላት፤
4. የክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች ........ አባላት፤
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ………………… አባል፤
6. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች አካላት ................ አባላት።

5. **<u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአሥራ አምስት ዓመት የረጅም ጊዜና የተከታታይ አምስት ዓመታት አጠቃላይ የአገራዊ የምርት እና አጠቃላይ የአገራዊ ምርት የነፍስ ወከፍ ድርሻ እድገት ግቦችን ይጥላል፤
2. በየአምስት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የፕላን አዘገጃጀትና የልማት የቅድሚያ ትኩረት አቅጣጫዎችን በሚመለክት መመሪያ ይሰጣል፣ በመጨረሻም የተዘጋጀውን ፕላን ያጸድቃል፤
3. በብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን በየጊዜው በሚቀርብለት የፕላን አፈጻጸም ግምገማ ውጤት ላይ ይመክራል፤ፕላኑ በፌደራልና በክልል አስፈጻሚ አካላት ተቀናጅቶ መተግበሩን ያረጋግጣል።

6. **<u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>**

1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሶስት

## ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን

7. **መቋቋም**

1. ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) በህግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

8. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።

9. **ዓላማ**

የኮሚሽኑ ዓላማ በተመጣጠነ አገር አቀፍ የዕድገት ማዕቀፍና በአሥራ አምስት ዓመታት የረጅም ጊዜ አመላካች ፕላን ላይ በመመሥረት የየአምስት ዓመት አገራዊ የልማት ፕላን ማዘጋጀትና አፈጸጸሙን በየጊዜው መገምገም ይሆናል።

10. **ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ ይሰጣል
2. በፕላኑ የተቀመጠውን ዓመታዊ አጠቃላይ አገራዊ የምርት ዕድገትን ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት እድገት መነሻዎችን ይገምታል
3. ከአጠቃላይ አገራዊ የምርት እድገት ግቦችና ከፖሊሲና ከህግ ሪፎርም እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት እና የወጪና የገቢ ንግድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤
4. ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎችን የተናጠል ድርሻ ይለያል፤
5. ፕላኑ ትግበራውን ለመምራት እንዲያስችል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከቱትን የኢኮኖሚ ዘርፎች ከንዑስ ዘርፎቻቸው እስከምርት ዓይነቶቻቸው ወይም የኢንዱስትሪ ክፍሎቻቸው ድረስ ይተነትናል፤
6. የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ግብዓቶችን አቅርቦት ለመተመን በግብርናና በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል፤

7. ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚተገበሩ ፕሮግራምችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎችን የሚዘረዝር የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፤
8. የፌደራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና የክልል ቢሮዎች አንድን የዘርፍ አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በየበኩላቸው የሚፈጽሟቸውን ተግባራት የሚያሳይ የተቀናጀ የፕላን አፈጻጸም መርሐ ግብር ያዘጋጃል፤
9. የፕላን አፈጻጸሙን በየጊዜው ይከታተላል፣ይገመግማል፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

11. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፦

1. በመንግሥት የሚሾሙ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር፤ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል።

12. <u>የኮሚሽነሩ ስልጣን እና ተግባር</u>

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራ ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፦
   
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   
   ለ/ የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   
   ሐ/ የኮሚሽኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤
   
   መ/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   
   ሠ/ ኮሚሽኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ/ የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል

3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ኮሚሽነሩ እና ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

13.**<u>በጀት</u>**

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

14.**<u>የሂሣብ መዛግብት</u>**

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብመዛግብት ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

15.**<u>ደንቡ የሚጸናበት ግዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበትቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 4 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 313/2006**

**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድን እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 5 እና 35 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 313/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

   1. "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅቁጥር 769/2004 (በአዋጅ ቁጥር 849/2006 እንደተሻሻለ) ነው፤
   2. "የኢንቨስትመንት ደንብ" ማለት የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 (በደንብ ቁጥር 312/2006 እንደተሻሻለ) ነው፤
   3. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

**ክፍል ሁለት**

**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ**

3. **መቋቋም**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

4. **የቦርዱ አባላት**

1. ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታልኦ

ሀ/ጠቅላይ ሚኒስትሩ............................. ሰብሳቢ፤

ለ/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም የመንግሥት ኃላፊ.............. ምክትል ሰብሳቢ

ሐ/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ የመንግሥት ኃላፊዎች................ አባላት፤

2. ኮሚሽኑ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።

5. **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 29 እና አግባብ ባላቸው ሌሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች እንዲሁም አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት ደንብ ድንጋጌዎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤
2. እንዳስፈላጊነቱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣ ሰብሳቢዎቻቸውንና አባላቱን ይሰይማል።

6. **የቦርዱ ስብሰባዎች**

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆነው የቦርዱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልረጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

7. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

8. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ወይም ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

9. **ዓላማ**

የኮሚሽኑ ዓላማ ግልጽና ቀልጣፋ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ኢንቨስትመንትን ማበረታታትና ማስፋፋት ይሆናል።

10. **የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 28 እና አግባብ ባላቸው የአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች እንዲሁም በኢንቨስትመንት ደንብ አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፣
2. የኢንቨስትመንት ቦርዱን መመሪያዎችና ውሳኔዎች ያስፈጽማል በሚመለከታቸው ሌሎች አካላትም መተግበራቸውን ይከታተላል፤
3. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።
4. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

11. **የኮሚሽኑ አቋም**

ኮሚሽኑ፡-

1. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነርና እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ እና
2. አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል።

12. **የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር**

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ሥራዎች ይመራል ያስተዳድራል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፦
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት ላይ ያውላል።
   ለ/ የኮሚሽኑን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኮሚሽኑን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኮሚሽኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፣
   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤
   ረ/ የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል።
3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

13.<u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

14.<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛገብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15.<u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 269/2005 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

16.<u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 269/2005 እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮሚሽኑ ተላልፈዋል።

17. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ. ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 419/2010</u>

## <u>የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተዋንያን ዘርፉን በተቀናጀ መንገድ የሚመራበትን እና ቀልጣፋና ዘመናዊ አሰራር የሚሰፍንበትን ራዕይና አቅጣጫ በመተለይም ውጤታማ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱሰትሪ ልማት በማሳደግ ረገድ ጉልህ እና የማይተካ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ፤

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለአገሪቱ አጠቃላይ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ የሚያግዙ የፖሊሲ ሀሳቦችን እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉት ክፍተቶች በጥናት እየተለዩ የመፍትሔ ሀሳብ የሚመነጭበት፣ አዋጭ የሆኑ ዓለም አቀፍ ልምዶች የሚቀመሩበትና ተግባራዊ የሚደረጉበትን ሥርዓት በማስፈን ኢንዱስትሪውን በተመለከተ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ሕጎችና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ዘርፉን የበለጠ የሚያበለፅጉ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ሀሳቦችን የሚያመነጭ እና የሚመክር አገራዊ ባለድርሻ መድረክ መፍጠር አስፈሊጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እና አግባብነት ባላቸው የምህንድስና፣ የአርኪቴክቸር፣ የቴክኖሎጂ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የቴክኒክና ሞያ ተቋማት መካከል ትስስር በማጠናከር በጥናትና ምርምር የበለፀገ የሰው ሀብት በማፍራት እና የተፈጠረውን የሰው ኃይሌ ክህሎት በመገንባት የኢንዱስትሪውን ፍላጎት እንዲያሚሊ በማድረግ የላቀ ብቃት እና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መፍጠር እንዲቻል ጉሌህ ድርሻ የሚጫወት ምክር ቤት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 419/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃለ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "ኮንስትራክሽን" ማለት ከመሬት በታች እና በላይ የሚከናወኑ የምህንድስና ፊዚካል መሠረተ ልማትን ጨምሮ በቋሚ ንብረቶች፣ በአገሎግልቶች እና በመሣሪያዎች የሚታገዙ የጉልበት ሥራዎች ጥቅም የሆነ እንደ አዲስ የማልማት፣ የማስፋፋት፣ የመገጣጠም፣ የመጠገን፣ የማሻሻል፣ የመቆጠር፣ የማወላለቅ ወይም የማፍረስ ተግባር ነው፤
2. "የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ" ማለት የተለያዩ ተፈጥሯዊ እና የተፈበረኩ ግብዓቶችንና ሀብቶችን ወደ ግንባታ ውጤቶች የሚለውጥ፣ ያለበትን ሁኔታ በመገምገም ለማሻሻል እንዲሁም ግምታቸውን የሚተምን፣ በሥራው ላይ ባለሙያዎችንና ተቋማትን ያቀፈ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፍ ጥምረት ነው፤
3. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
4. "ምክር ቤት" ማለት በዚህ ደንብ የተቋቋመው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ነው፤
5. "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 የተመለከቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዱሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆኑ ክልሎች ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ያካትታል፤
6. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **መቋቋም**

ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

4. **ዓላማ**

የምክር ቤቱ ዓላማ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማነቆዎች ለመፍታት፣ ለማዘመን እና ኢንዱስትሪው ለአገሪቱ አጠቃላይ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ በሚያግዙ የፖሊሲ ሀሳቦች ላይ ምክክር በማድረግ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይሆናል፡፡

5. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጎ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎች ትግበራ ይገመግማል፤ አተገባበራቸውን ለማሳለጥ የሚጠቅሙ ሀሳቦችን ይሰጣል፤ የፖሊሲ ሀሳቦች፣ ሕጎች እና የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ምክክር ያደርጋል፤ ስለአተገባበራቸው አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
2. ሚኒስቴሩ የዘርፉን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም መሠረት አድርጎ የሚያቀርበውን ወቅታዊና ስትራቴጂያዊ ሪፖርት ያድምጣል፣ ውይይት ያደርጋል፤ የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን ይሰጣል፤
3. በፌደራል መንግሥት የሚካሄዱ ታላላቅ ፕሮጀክቶች የጥናት ውጤትና አፈጻጸም ላይ ውይይት ያደርጋል፤ የመደገፍና የማማከር ስራ ይሰራል፤ የአተገባበር አቅጣጫ ይሰጣል፤
4. በዘርፉ ውስጥ ያለ ተዋናይ እና ባለድርሻ አካላት እንደየአግባብነታቸው የሚያቀርቧቸውን የጥናት ውጤቶችና ምርጥ ተሞክሮዎች ያዳምጣል፣ ውይይት ያደርጋል፤ የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤
5. የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት በለውጥ ጎዳና እንዲጓዝ የሁሉንም ተዋናዮች አቅም ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ይገመግማል፤
6. የዘርፉ የሙያ ማህበራት የኢንዱስትሪውን ጥራት እና ጤናማ ተወዳዳሪነት እንዲያጎለብቱና እንዲያስፋፉ እንዲሁም ብልሹ አሠራር በመዋጋት ረገድ ሚናቸው የጎላ ይሆን ዘንድ የአደረጃጀትና የአፈጻጸም አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤

7. አዋጭ የሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ አገሮች የኮንስትራክሽን ሥራ ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ ጥናት፣ ትንተና፣ ቅመራ ያደርጋል፣ ትግበራ ሪፖርት ያድምጣል፤ ይወያያል፤ ለአፈጻጸማቸው አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
8. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አፈጻጸም ለማሻሻል እና የአሠራር ሥርዓቱን ለማዘመን የሚረዱና የሚደገፉ የአቅም ግንባታና እና ተዛማጅ ስራዎች ተጠናክረው እንዲሰሩ እና የባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄደ አቅጣጫ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
9. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የገንዘብ ምንጭ ከማስፋት አኳያ የተለያዩ አማራጮች በጥናትና ምርምር እንዲለዩና ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲሰባሰቡ የአፈጻጸም አቅጣጫ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤
10. የአገሪቱን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አገልግሎት ተወዳዳሪ በማድረግ ከውጪ የሚገባውን አገልግሎት የመተካትና አገልግሎቱም ለውጪ ሀገር እንዲቀርብ የማድረግ የሚያስችል ምክክር ያደርጋል፤ የዘርፉ ተዋንያን ወደ ኮንስትራክሽን ማንፋክቸሪንግ የሚሸጋገሩበት የፖሊሲ አቅጣጫ ይሰጣል፣ የድርጊት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ክትትል ያደርጋል፤
11. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እና አግባብነት ያላቸው የምህንድስና፣ የሥነ-ሕንጻ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት ተቋማት ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ ኢንዱስትሪው የሚመጥን ክህሎትና ሥነ ምግባር ያለው የተማረ የሰው ኃይል በሚመረትበትና በሚቀርብበት ሁኔታ ይመክራል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
12. ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት እውቅና እና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ይመክራል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
13. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መፈፀማቸው ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

6. **የምክር ቤቱ አባላት**

1. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ፡-

ሀ) አግባብ ያላቸው የፌደራል መንግሥት ተቋማት ኃላፊዎችን፤

ለ) የክልል ፕሬዚዳንቶች እና የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ ከንቲባዎችን፤

ሐ) የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ተወካዮችን፤

መ) የግሉ ዘርፍ ተወካዮችን፤

ሠ) የሌሎች አግባብ ያላቸው አካላት ተወካዮችን፤

በአባልነት የሚይዝ ይሆናል፡፡

2. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ይመራል፤ የኮንስትራክሽን ሚኒስትር ጸሐፊ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የፌደራልና የክልል ባለሥልጣናት እንዲሁም ሙያዊ አስተያየት እንዲያቀርቡ የሚጋበዙ ባለሙያዎች በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

7. **<u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>**

1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ዴንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. **<u>የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት እና ቴክኒክ ኮሚቴ</u>**

ምክር ቤቱ፡-

1. በሚኒስቴሩ ውስጥ የሚደራጅ ሴክሬታሪያት እና
2. በመንግሥት የሚሰየም የቴክኒክ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

9. **<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

10. **<u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በደንቡ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

11. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 22 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 426/2010**

**የሪፐብሊኩን የጥበቃ ኃይል ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 (በአዋጅ ቁጥር 942/2008 እና 1084/2010 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 37 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሪፐብሊኩ የጥበቃ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 426/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ቤተ መንግሥት" ማለት የመንግሥትና የሀገር መሪዎች የሚሰሩበትና የሚኖሩበት ማንኛውም ስፍራ ሲሆን፤ ሁለቱም ቤተ መንግሥቶች፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግቢና የቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፍያ ቪአይፒ ተርሚናልን፤ እንዲሁም የጠቅላይ ሚንስትሩን፣ የርዕሰ ብሔሩንና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጊዜያዊ የስራና ማረፊያ ቦታዎችን ያጠቃልላል፤
   2. የመሪዎች ቤተሰብ" ማለት የጠቅላይ የርዕሰ ብሄሩና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የትዳር አጋሮች እና በስራቸው የሚተዳደሩ እስከ 21 ዓመት የሆናቸው ልጆቻቸውን ያጠቃልላል፤

3. “ግቢ” ማለት በጥበቃ ኃይሉ ጥበቃ የሚሸፈን ሕንጻ ዙሪያ፣ በውስጥ ያሉትን ቢሮዎች፣ ወደ ግቢ የሚገቡና የሚወጡ ማናቸውንም ሰዎች፣ ቁሶችን፣ ቴክኖሎጂዎችን፣ በግቢ ውስጥ የሚገኙ ሀብቶችንና መሠረተ ልማቶችን ያጠቃልላል፤
4. “አስፈላጊ ቴክኖሎጂ" ማለት በዚህ ደንብ የጥበቃ ሽፋን ያገኙ መሪዎችንና የቤተሰቦቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያግዝ፣ ተሽሽከርካሪ፣ ሰው አልባ አውሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ ደረጃውን የጠበቀ ትጥቅ፣ እንስሳትና ሌሎች የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን ያጠቃልላል፤
5. “መለዮ ለባሽ ኃይል" ማለት በዋናነት የጥበቃ፣ ፍተሻና እጀባ ሥራ የሚሰራው የታጠቀ ኃይል ነው፡
6. “የመንግሥትና የሀገር መሪዎች" ማለት እንደቅደም ተከተሉ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና ርዕሰ ብሔር ነው፤
7. “ድጋፍ ሰጪ ኃይል" ማለት የተለያየ የተፈጥሮ ሳይንስ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ቴክኒካዊ እውቀት ያላቸው ሙያተኞች የተሰባሰቡበት ኃይል ነው፤
8. “ኦፕሬሽናል" ማለት የዕዝ ሰንሰለት እና በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ዋና ተግባራት ያጠቃልላል፤
9. “አስተዳደራዊ ሥራዎች" ማለት ከሰው ኃይል አስተዳደር፣ ከበጀት አስተዳደርና ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ጋር የተያያዘ ሥራ ነው፤
10. “ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴርና ሚኒስትር ነው፤
11. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የሪፐብሊኩ የጥበቃ ኃይል (ከዚህ በኋላ “የጥበቃ ኃይል" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የጥበቃ ኃይሉ ለኦፐሬሽናል ሥራዎች ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሲሆን፤ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲባል ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የጥበቃ ኃይሉ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

የጥበቃ ኃይሉ ዓላማ አስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለውን ቅደመ ዝግጅት በማድረግ የመንግሥትና የሀገር መሪዎችን ደህንነትና ቤተ መንግሥትን መጠበቅ ነው።

6. **የጥበቃ ኃይሉ ተግባራትና ላፊነት**

የጥበቃ ኃይሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. የቤተ መንግሥት ጥበቃ የአሠራር ሥርዓትና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል ሲፀድቅም በኃላፊነት ይፈጽማል፤
2. የሰው ኃይል ምልመላ፣ ስልጠና፣ ወቅታዊ ግምገማና ዝውውር ወይም ስንብት መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል ሲጸድቅም በኃላፊነት ያስፈጽማል፤
3. ከሚኒስቴሩና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊ የሰው ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል ይቀጥራል፣ ያሰማራል፤
4. ለተልዕኮው አፈጻጸም የሚያስፈልጉት ማናቸውም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፤ ቁሳቁስ፣ ትጥቅና አስፈላጊ ቴክኖሎጂ ይታጠቃል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚስፈልገውን ድጋፍ በጊዜያዊነት ከሌሎች ተቋማት ያገኛል፤
6. የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የቤተሰቡን፣ እንዲሁም የርዕሰ ብሔሩንና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ቤተሰቦቻቸውን ድህንነት ያረጋግጣል፤
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (6) የተጠቀሰው እንደጠበቀ ሆኖ የደህንነት ጥበቃው የቀድሞ ርዕሰ ብሔርን፣ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትርን፣ የቀድሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርንና ቤተሰቦቻቸውንም የሚያካትት ሲሆን፣ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የተሾሙትን አያካትትም፤
8. ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ የሌሎች ሀገራት የመንግሥትና የሀገር መሪዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ኃላፊዎችን እንዲሁም በዚህ ደረጃ ለሚታዩ ሰዎች ጥበቃ ያደርጋል፤
9. የክብር ዘብ አገልግሎት ይሰጣል፤

10. ልዩ ተልዕኮውን ታሳቢ በማድረግ ለተልዕኮ አፈጻጸም የሚያስፈልጉትን አደረጃጀቶች አጥንቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በኃላፊነት ያስፈጽማል፤
11. የሀገርና የመንግሥት መሪዎችን ደህንነትና ቤተ መንግሥትን ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳል፤
12. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ሃ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
13. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **የጥበቃ ኃይሉ አደረጃጀት ፦**

የጥበቃ ሐይሉ፡-

1. በመንግሥት የሚሾሙ አዛዥና ምክትል አዛገርች፤
2. እንዲሁም አስፈላጊ መለዮ ለባሽና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሲቪል ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. **የአዛዡ ፡ ሥልጣንና ተግባር**

አዛገ፡ ለኦፕሬሽናል ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት፤ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲባል ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የጥበቃ ኃይሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤ ያዛል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

አዛገ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የጥበቃ ኃይሉን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በሚወጡ መመሪያዎች፣ የአሠራር ሥርዓቶችና ስታንዳርዶች መሠረት ስራውን በበላይነት ያስተባብራል፤

ሐ) እንደ የሁኔታው አዳዲስ አሰራሮችንና አደራጃጀቶችን እያጠና ለውሣኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) የጥበቃ ኃይሉ ሠራተኞች የሰራተኞቹን ስብጥር ታሳቢ አድርጎ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፤

ሠ) የጥበቃ ኃይሉን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ረ) በጥበቃ ኃይሉ በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ክፍያዎችን ያፀድቃል፣ ይፈጽማል፤

ሰ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደርጉ ግንኙነቶች ሁሉ የጥበቃ ኃይሉን ይወክላል፣

ሸ) የጥበቃ ኃይሉ ከኦፐሬሽናል ውጭ ያሉትን የሥራ ክንውኖችና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

3. አዛዡ ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል ከስልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለየጥበቃ ኃይሉ ምክትል አዛገፐችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9. <u>**የምክትል አዛዥ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ምክትል አዛዥ ተጠሪነቱ ለአዛዡ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በሚጸድቅ የስልጣን ውክልና መመሪያ መሰረት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ያከናዉናል፤
2. ከአዛዡ ተለይተው የሚሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ያከናውናል፤
3. አዛዡ በሌለበት ጊዜ የሥልጣን ውክልና ያልተሰጠ እንደሆነ በማዕረግ ቅድሚያ ያለው ምክትል አዛዥ በዚህ ደንብ ለአዛዥ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በኃላፊነት ያከናውናል።

10.<u>**የጥበቃ ኃይሉ በጀት**</u>

የጥበቃ ሐይሉ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

11.<u>**ስለ ሒሣብ መዛግብት**</u>

1. የጥበቃ ኃይሉ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሒሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የጥበቃ ኃይሉ የሒሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

12.<u>**የመተባበር ግዴታ**</u>

1. ማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል የጸጥታናሕግ አስፈጻሚ አካል እና ሌላ ተቋም በዚህ ደንብ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማስፈጸም ሲባል ከጥበቃ ኃይሉ ለሚቀርብለት የትብብር ጥያቄ የመተባበር ግዴታ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ትብበር፣ የሰው ኃይል፣ ተሽከርካሪ፣ ቢሮ፣ መረጃ ወይም ሌላ ቁሳዊና ኢቁሳዊ ሀብት ሊሆን ይችላል።

13.<u>**ስለ መብት መተላለፍ**</u>

ከቤተ መንግሥት ጥበቃ፣ እጀባና የክብር ዘብ አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማናቸውም ቁሳዊና ሌሎች ተዛማጅ ሀብቶች በዚህ ደንብ መሠረት ለጥበቃ ኃይሉ ተላልፈዋል።

14. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያዎችን ያወጣል።

15. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ 11 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አሕመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 435/2011</u>**

## <u>የሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነትን እና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የሥራ ፈጠራ ኮሚሽን የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 32(13) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፣

የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን በዚሁ አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32(13) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽንን ተግባርና ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 435/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1. "ሥራ" ማለት ሰብአዊ መብትን ሳይጥስ የሚደረግና በአይነት ወይም በገንዘብ ገቢ የሚያመነጭ ማንኛውም ተግባር ነው፡፡

2. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሠጠው አካል ነው፡፡
3. በወንድ ጾታ የተገለፀው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍች ሊኖሩት ይችላል፡፡

4. <u>የኮሚሽኑ ዓላማ</u>

የኮሚሽኑ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የስራ ቅጥር አስተዳደርና የሥራ ዕድልን በተመለከተ ግልጽ ተቋማዊ ማዕቀፍ እንዲዘረጋ ለማድረግ፣
2. ስራ ፈላጊዎች ምርታማ እና በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሰረቱ የስራ እድሎች እንዲኖሩ ለማበረታታት፣
3. ምርታማ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና ክህሎት ያለው የሥራ ሃይል እንዲኖር ለመደገፍ፡፡

5. <u>ኮሚሽኑ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

ኮሚሽኑ የሚከተለት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በስራ ፖሊሲ፣ እቅዶች እና እስትራቴጂዎች ዝግጅት ላይ ምክር ይሰጣል፤
2. በስራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያሉትን ክፍተቶች ያጠናል፣ ይተነትናል፤
3. በተለያዩ የመንግስት አካላት የስራ እድል ፈጠራን በተመለከተ የሚሰሩ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
4. የስራ እድል ፈጠራ ፈንድ ያፈላልጋል፤
5. ከሌሎች የሚመከታቸው ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር በሥራ ገበያ ላይ የሚታዩ የክህሎት ክፍተቶችን በተመለከተ ወቅታዊ የዳሰሳ ጥናቶችን ያካሂዳል፣
6. የስራ እድልን ለማስፋፋት በፌደራል እና ክልል መንግሥት አካላት፣ የግል ዘርፍ፣ መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ፣ የልማት አጋሮች እና ተቋማት መካከል ትብብር እንዲኖር ያግዛል፣ ያስተባብራል፣
7. ሥልጠናዎች እና የሥራ ልምዶች ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሥልጠና ተቋማትን እና ሥራ ፈላጊዎችን በተገቢው ሁኔታ ያማክራል፣

8. የስራ ፖሊሲ መርሃ ግብሮችንና ትግበራዎችን ይቆጣጠራል፣
9. የሁለንም ሥራ ፈላጊዎች በተመለከተ የተቀናጀና ወቅታዊ የሆነ መረጃ ይይዛል፣
10. የስራ ፈላጊዎች ቅጥር እና ምደባ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ የቅጥር ዓይነት በሃገር ውስጥ እና በውጭ ሃገር እንዲመቻቹ ያደርጋል፣
11. የስራ እድል ፈጠራ ክህሎት ሌላቸው አካል ጉዳተኞች ድጋፍ ይሰጣል፤
12. በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ የሚገኙ የስራ እድሎችን ያፈላልጋል፣ አሟጦ ይጠቀማል፤
13. የስራ ዕድል ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ሰዎች ያበረታታል፤
14. በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት የሚታዘዙትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

6. <u>**የኮሚሽኑ አቋም**</u>

ኮሚሽኑ፦

1. በመንግሥት የሚሾም ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር፤ እና
2. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. <u>**የኮሚሽነሩ ሥልጣን እና ተግባራት**</u>

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ያገለግላል፣ የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ፤

   ኮሚሽነሩ፦

   ሀ) በአንቀጽ 5 ሥር የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣን እና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ) የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል የመንግሥት ሠራተኞች ሕግጋት መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

   ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ይተገብራል፤

   መ) ክፍያዎች ይፈጽማል፤

   ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

   ረ) የኮሚሽኑን የአፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

3. ኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስገልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል ኮሚሽነሩ ወይም ለኮሚሽኑ ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

8. **የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣን እና ተግባራት**

ምክትል ኮሚሽነሩ፦

1. የኮሚሽኑን ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ እና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፤
2. በኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ሌሊች ተግባራት ያከናውናል፤
3. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል።

9. **በጀት**

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

10. **የሂሳብ መዝገብ**

1. ኮሚሽኑ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል፡፡
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገብ እና ገንዘብን የሚመለከቱ ሰነዶች በየዓመቱ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተሩ በሚመድበው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

11. **ተፈፃሚ የማይሆኑ ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በደንቡ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

12. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ህዳር 4 ቀን 2011ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

ለ/ <u>ለሰላም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች</u>

**<u>ደንብ ቁጥር 171/2002</u>**

**<u>የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 5 እና 34 እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 657/2002 አንቀጽ 21(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

   ይህ ደንብ "የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 171/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

   1. "አዋጅ" ማለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 657/2002[5] ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተመለከተው ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤[6]

3. <u>**መቋቋም**</u>

---

[5] በ19/25(2005) አ.780 ተሽሯል፡፡

[6] ለትርጓሜው 19/25(2005) አ.780ን ተመልከት፡፡

1. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል (ከዚህ በኋላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ማዕከሉ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. **የማዕከሉ አላማ**

ማዕከሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የሚመለከታቸውን ተቋማት የማስተባበር፣ የሚደርሱትን መረጃዎች የማደራጀት፣ የመተንተንና የማሰራጨት እና አዋጁን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን የማከናወን ዓላማ ይኖረዋል።

6. **የማዕከሉ ስልጣን እና ተግባር**

ማዕከሉ የሚከተለት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በአዋጁ አንቀጽ 21(2) የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል
2. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
3. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **የማዕከሉ አቋም**

ማዕከሉ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
2. ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

8. **የቦርድ አባላት**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩታል። የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ ቋሚ አባል ይሆናል። የቦርዱ ሊቀመንበርና ቀሪዎቹ አምስት አባላት በመንግሥት ይሾማሉ።
2. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈለው አበል መጠን በመንግሥት ይወሰናል፡

9. **<u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ እንዲውሉ ያደርጋል፤
2. የአዋጁን አፈጻጸምና የማዕከሉን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤
3. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከቱ የሕግ፣ የቁጥጥርና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
4. አዋጁንና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤ እና
5. የማዕከሉን የአሠራር ፖሊሲዎችና የሥራ ዕቅድ፣ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት ያጸድቃል፤ የሲቪል ሰርቪሱን ሕጎች መሠረታዊ ዓላምዎች ተከትሎ የተዘጋጀ የማዕከሉ ሠራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ በመንግሥት እንዲጸድቅ ያቀርባል።

10. **<u>ስለ ቦርድ ስብሰባና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት</u>**

1. ቦርዱ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሥራው በሚጠይቀው መጠን በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤ ሆኖም ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መሰብሰብ ይኖርበታል።
2. ቦርዱ፣

   ሀ/ የሰብስባ ሥነ-ሥርዓቱን ይወስናል፤

   ለ/ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ እስካገኘው ድረስ ከማንኛውም ሰው ማናቸውም ምክር ወይም እርዳታ መጠየቅ ይችላል፤

   ሐ/ ሥራውን ለማከናወን የሚረዱ ኮሚቴዎች ከአባላቱ ማቋቋም ይችላል።

3. በማናቸውም የቦርዱ ስብሰባ አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉብዔ ይኖራል፡ማናቸውም ውሳኔ ወይም እርምጃ በስብሰባ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምፅ ይወሰናል።

11.**<u>ስለማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር</u>**

1. የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በመንግስት ይሾማል።
2. ዋና ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የማዕከሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ/ የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባራት ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 9(5) በተጠቀሰው የሠራተኞች መተዳደሪያ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የማዕከሉን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ የማዕከሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል

ሠ/ ማዕከሉን ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ይወክላል፤

ረ/ ሥልጣንና ተግባሩን ለማዕከሉ የሥራ ቅልጥፍና እና ውጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለማዕከሉ ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል፤

ሰ/ በመንግሥት ፖሊሲ ወይም የማዕከሉ የስትራቴጂ አቅጣጫ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጉዳዮች ሲኖሩ ለቦርዱ ያሳውቃል፤

ሸ/ ሌሎች ከቦርዱ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

12.**<u>ስለሪፖርት</u>**

1. ማዕከሉ በሚስጥር የሚጠበቁትን ሳይጨምር የሚከተሉትን ያካተተ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡-

ሀ/ በአዋጁ መሠረት የተቀበላቸውን ሪፖርቶች፣ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የተመሩ ጉዳዮች፣ ከተመሩት ውስጥ ክስ የተመሠረተባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቀረቡ የእርዳታ ጥያቄዎችና የመሳሰሉ ስታትስቲክሳዊ የቁጥር መረጃዎች፤እና

ለ/ በቦርዱ ውሳኔ እንዲካተቱ የተወሰኑ ሌሎች መረጃዎች።

2. ማዕከሉ ወቅታዊ የሆኑ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በተመለከተ የተከሰቱ የመፈጸሚያ ዘዴዎችንና ሌሎች ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ግብይቶችን ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎች ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ያሰራጫል።

13.<u>በጀት</u>

ማዕከሉ በመንግሥት በሚመደብለት በጀት ይተዳደራል።

14.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ማዕከሉ ትክክለኛና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የማዕከሉ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተሩ በሚሾም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

15.<u>ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

ማዕከሉ በአዋጁ የተደነገጉትን የፋይናንስ ተቋማትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን በማማከር ይሠራል።

16.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ ከህዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 5 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 720/2004 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የፌዴራል ፖሊስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትንና ሕገ-መንግሥቱን መሠረት አድርገው የሚወጡ ሕጎችን የማስከበር ተልዕኮውን በብቃት በመወጣት የዲሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት፣ ሠላምን ለማስፈንና ልማትን ለማፋጠን በሚደረገው ሀገራዊ እንቅስቃሴ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት እንዲችል በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፌዴራል ፖሊስ ተቋም ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ገለልተኛ የሆነ፣ ሕብረተሰቡን በእኩልነት የሚያገለግል፣ በፖሊሳዊ ሥነ-ምግባሩ የታነፀና ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍልአንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “የፖሊስ አባል” ማለት መሠረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ስልጠና ተሰጥቶት በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተቀጥሮ የሚሠራ የፌዴራል ፖሊስ አባል ነው፤
2. [7]
3. “የጦር መሳሪያ” ማለት በሰው ሕይወት ወይም አካል ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል በሚፈነዳ ኃይል አማካይነት ተተኩሶ ጥይት ወይም አረር የሚያወጣ ሽጉጥ ወይም ጠመንጃ ሲሆን ተያያዥነት ያላቸው ዕቃዎችን ይጨምራል፤
4. “የማዕረግ ቀደምትነት” ማለት የማዕረግ ብልጫ መኖር ወይም አቻ ማዕረግ ኖሮ የሹመት ቅድሚያ መኖር ወይም አቻ ማዕረግና ሹመት ኖሮ በሥራ ኃላፊነት ከፍ ያለ መሆን ወይም አቻ ማዕረግ፣ሹመትና የሥራ ኃላፊነት ኖሮ በቅጥር ዘመን መብለጥ ነው፤
5. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

## ክፍልሁለት

## የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ “ኮሚሽን” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል[8]።

### 4. ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን በማናቸውም ሥፍራ ሊያቋቁም ይችላል።

### 5. የኮሚሽኑ ዓላማ

ኮሚሽኑ የሀገሪቱን ሕገ-መንግሥት፣ ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱንና ሌሎች ሕጎችን በማክበርና በማስከበር እንዲሁም ሕብረተሰቡን በወንጀል መከላከልና ምርመራ

---

[7] በ22/63(2008) አ.944 በግልፅ ሳይነገር ተሻረ፡፡
[8] በ22/63(2008) አ.944 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

በማሳተፍ የሕዝብንና የመንግሥትን ሠላምና ደህንነት የመጠበቅና የማረጋገጥ ዓላማ ይኖረዋል።

6. **የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሕገ-መንግሥቱና በሕገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱ፣ በመንግሥትና በሀገር ፀጥታ እና በሰብዓዊ መብት ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውም ዓይነት የወንጀል ስጋቶችና ድርጊቶችን ይከላከላል፣ ይመረምራል፤
2. የወንጀል ምርመራን በተመለከተ ከየፍትህ ሚኒስቴርና[9] ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በጋራ ይሠራል፤
3. በፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን ትእዞችና ውሳኔዎች ይፈፅማል፤
4. በሌሎች ህጐች ለሌሎች የፌዴራል መንግሥት አካላት የተሰጠ ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ ይመረምራል፤
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   ሀ/ የሃሰት ገንዘብና የክፍያ ሰነዶችን በመሥራት የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ ይመረምራል፤
   ለ/ ከመረጃ መረብና ከኮምፒዩተር ሥርዓት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤
   ሐ/ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና እገታ፣ የአደገኛ ዕፆች ዝውውርና ስርጭት፣ የአውሮፕላን ወይም የመርከብ ጠለፋ፣ የተደራጀ ዘረፋ፣ ውንብድና፣ አሸባሪነት እና የፀጥታ ማደፍረስ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ ይመረምራል፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን እንዲከላከሉና እንዲመረምሩ ለክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች የውክልና ስልጣን ይሰጣል፤ በውክልናው መሠረት ስለተፈጸሙ ጉዳዮች ሪፖርት ይቀበላል፤
7. በፖሊስ ምልመላና ቅጥር፣ በትምህርትና ሥልጠና፣ በማዕረግ አሰጣጥ፣ በደንብ ልብስ አለባበስ፣ በትጥቅና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ሀገር አቀፍ ደረጃዎችን ያወጣል፤

---

[9] በ22/62(2008) አ.943 "የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ" በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

8. የፖሊስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ያቋቁማል፤ አባላቱ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
9. የፌዴራል መንግሥት ተቋማትን ይጠብቃል፤ ለከፍተኛ የፌዴራሉ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ ለውጭ አገር የክብር እንግዶችና ዲፕሎማቶች ጥበቃ ያደርጋል
10. ወንጀልን ለመከላከልና ለመመርመር የሚረዱ የሲ.ሲ. ቲቪ ካሜራዎችን ተገቢ በሆኑ ቦታዎች ይተክላል፤
11. የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 18 የተመለከቱትን ኃላፊነቶች ይወጣል፤
12. የሀገሪቱን ጥቅሞች በሚነኩ ጉዳዮች ላይ በውጪ ሀገር የሚፈፀሙ ማናቸውንም ወንጀሎች ከየሀገራቱ ጋር በሚደረግ የጋራ ስምምነት መሠረት ይመረምራል፤
13. የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰትና አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር ሠላምና ፀጥታን በማስፈን የተጎዱ ሰዎችን ለመርዳት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤
14. የግለሰቦችን የወንጀል ሪከርዶች በማዕከል አደራጅቶ ይይዛል፤ የወንጀል ሪከርድ ለሌለባቸው ግለሰቦች ከወንጀል ነፃ ማስረጃ ይሰጣል፤
15. የፎረንሲክ ምርመራ ያደርጋል፣ ስለመረመረው ጉዳይ ማስረጃ ይሰጣል፣ ለፍርድ ቤት ወይም ለጠያቂው አካል የሙያ ምስክርነት ይሰጣል፤
16. በፎረንሲክ ምርመራ ጉዳዮች ከክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
17. በማስረጃነት አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ የወንጀል ምርመራ መዛግብቶችን፣ ሰነዶችን፣ አሻራዎችንና ተያያዥነት ያላቸው ሪከርዶች ከብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃሕፍት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር እንዲወገዱ ያደርጋል።
18. የሽብርተኝነት ድርጊት ሊፈፀም እንደሚችል ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖርና ድርጊቱንም ለመከላከል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት በተጠረጠረው አካባቢ የተገኙ ተሽከርካሪዎችና እግረኞችን በማስቆም ድንገተኛ ፍተሻ ያደርጋል፤ ተጠርጣሪ ሰዎችና ማስረጃዎችን በመያዝ ይመረምራል፤
19. ከሽብርተኝነት ድርጊት ጋር በተያያዘ የሀገርን ብሔራዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመመርመር የሚረዳ መሆኑ የታመነበትን መረጃ ወይም ማስረጃ ከማንኛውም ሰው ጠይቆ ይወስዳል፤
20. ተልዕኮውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችሉና የፖሊስ ሙያ ብቃትና

አገልግሎትን ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

21. ከክልል የፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር በመተባበር ስለወንጀል መከላከልና ምርመራ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና አንድ ወጥ የሆኑ የአሠራር ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ በመንግሥት ሲጸድቁም ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
22. በፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት በክልሎች ሕግና ሥርዓትን ያስከብራል፤
23. ስለወንጀልና ስለትራፊክ አደጋ መንስኤዎች ሀገር አቀፍ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
24. ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት በመስጠት ለክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች የትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና፣ የቴክኒክ እና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤
25. ለአባላቱ የሚያገለግሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ያደራጃል፤
26. የጦር መሳሪያ ወይም ፈንጂ ለመያዝ፣ ለመጠቀም፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለመሸጥ እና ለመጠገን ፈቃድ ይሰጣል፤ ዝውውራቸውን ይቆጣጠራል፤
27. መወገድ የሚገባውን ማናቸውንም የጦር መሣሪያ ወይም ፈንጂ ያስወግዳል፤
28. የጥበቃ አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ መሠማራት ለሚፈልጉ የግል ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
29. የፎረንሲክ ምርመራ አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ መሠማራት ለሚፈልጉ ሰዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
30. ከፀጥታ አካላት ጋር በጥናት፣ በሥልጠና እና በመረጃ ልውውጥ ረገድ በቅንጅት ይሠራል፤
31. ለፖሊስ አባላት የሚያገለግሉ የደመወዝ ስኬል እና ልዩ ልዩ አበሎችን አጥንቶ ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ያደርጋል፤
32. ለሥራ ክፍሎቹና ለፖሊስ አባላት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ቢሮዎችና የመኖሪያ ካምፖች እንዲሠሩ ያደርጋል፤
33. በከተማ ውስጥ የሚሰሩ የወንጀልና የድንገተኛ አደጋ ስጋት ይፈጥራሉ ተብለው የሚገመቱ ግንባታዎችን የሚመለከቱ ፕላኖች ለወንጀልና አደጋ መከላከሉ ተግባር

አመችነታቸውን በማረጋገጥ ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

34. ሀገሪቱ የሚቀርብላት ዓለም አቀፍ የሠላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚችል የሠላም አስከባሪ ፖሊስ ያዘጋጃል፤
35. ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት የሚያስችል ሥልጠና ለፖሊስ አባላት ይሰጣል፤ በአዋጅ ቁጥር 600/2000 አንቀጽ 5(2) መሠረት በትራንስፖርት ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ሲሰጠውም መንጃ ፈቃድ ይሰጣል፤
36. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በሚያስተዳድራቸው መንገዶች ላይ የመንገድ ትራፊክ ደንቦች መከበራቸውን ይቆጣጠራል፣ የትራፊክ አደጋዎችን ይመረምራል፤
37. ፖሊስ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አግባብ ካላቸው የውጭ ሀገር መንግስታት ፖሊስ ተቋማትና መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይመሠርታል፤
38. ከዓለም አቀፍ ፖሊስ ጋር ግንኙነት በመፍጠር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈላጊ የሆኑ ወንጀለኞችን መረጃ ለክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ያሰራጫል፣ ተከታትሎ ይይዛል፤
39. በሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለፌዴራል ፖሊስ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፤
40. ውል ይዋዋላል፣የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል።

7. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፡-

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነር ጀነራልና ምክትል ኮሚሽነር ጀነራሎች፤
2. የማኔጅመንት ኮሚቴ፤
3. የፖሊስ አባላት፤እና
4. አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>የኮሚሽነር ጀነራሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

1.ኮሚሽነር ጀነራሉ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑ ሥራዎች

ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነር ጀነራሉ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኮሚሽነሮችን፣ የምክትል ኮሚሽነሮችንና የረዳት ኮሚሽነሮችን ሹመት ለሚኒስትሩ አቅርቦ ያጸድቃል፤

ሐ/ የፖሊስ አባላትና የኮሚሽኑ ሌሎች ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር የዚህን አዋጅ አንቀጽ 14 ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 መሠረት የወጡ ደንቦችን ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

መ/ የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ሰ/ የኮሚሽኑን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ኮሚሽነር ጀነራሉ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## 9. <u>የምክትል ኮሚሽነር ጀነራሎች ስልጣን እና ተግባር</u>

1. ምክትል ኮሚሽነር ጀነራሎች፡-

ሀ/ የኮሚሽኑን ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነር ጀነራሉን ይረዳሉ፤

ለ/ በኮሚሽነር ጀነራሉ ተለይተው የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ።

2. ኮሚሽነር ጀነራሉ በማይኖርበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ ካልወከለ በስተቀር የማዕረግ ቀደምትነት ያለው ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል ኮሚሽነር ጀነራሉን ተክቶ ይሠራል።

## 10. <u>የማኔጅመንት ኮሚቴ</u>

1. የኮሚሽኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ኮሚሽነር ጀነራሉ ..................... ሰብሳቢ

ለ/ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራሎች............................ አባላት

ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ በኮሚሽነር ጀነራሉ አቅራቢነት በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች የኮሚሽኑ ኃላፊዎች..................... አባላት

2. የማኔጅመንት ኮሚቴው ፀሐፊ በኮሚሽነር ጀነራሉ ይመደባል።

3. የማኔጅመንት ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ለመንግሥት የሚቀርቡ የኮሚሽኑ የአደረጃጀት ጥናቶች፣ የበጀት ረቂቆች እና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ይገመግማል፤

ለ/ ኮሚሽኑ የሚመራባቸውን በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን አፈጻጸም ይገመግማል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

ሐ/ የኮሚሽኑን የሥራ መመሪያዎች ያፀድቃል፤ በሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

መ/ የፖሊስ አባላት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅዶችን በፍላጎት ግምገማ ጥናት ላይ ተመሥርቶ ያጸድቃል፤

ሠ/ በኮሚሽኑና በክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ረ/ በኮሚሽነር ጀነራሉ በሚመሩለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል።

11. <u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡

12. <u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የፌዴራል ፖሊስ አስተዳደር</u>

13. <u>የሰው ሃብት ዕቅድ</u>

ኮሚሽኑ የስትራቴጂክ እቅዱን መሠረት በማድረግ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሰው ኃይል እቅዶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል።

14. <u>የሰው ሃብት አስተዳደር</u>

1. ኮሚሽኑ የፖሊስ አባላትን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት

ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።

2. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።

15. <u>ስለፖሊስ ማዕረጎች</u>

1. የፖሊስ አባላት ማዕረጎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ/ ኮንስታብል፤

ለ/ ረዳት ሳጅን፤

ሐ/ ምክትል ሳጅን፤

መ/ ሳጅን፤

ሠ/ ዋና ሳጅን፤

ረ/ ረዳት ኢንስፔክተር፤

ሰ/ ምክትል ኢንስፔክተር፤

ሸ/ ኢንስፔክተር፤

ቀ/ ዋና ኢንስፔክተር፤

በ/ ምክትል ኮማንደር፤

ተ/ ኮማንደር፤

ቸ/ ረዳት ኮሚሽነር፤

ኀ/ ምክትል ኮሚሽነር፤

ነ/ ኮሚሽነር፤

ኘ/ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል፤እና

አ/ ኮሚሽነር ጀነራል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የፖሊስ አባላት ማዕረጎች የየራሳቸው ምልክት ይኖራቸዋል።

16. <u>ሜዳይ፣ ሪባንና የምስክር ወረቀት</u>

ለፖሊስ አባላት በከፍተኛ የግዳጅ አፈጻጸም ውጤትና በሚያስመሰግን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተመሥርተው የሚሰጡ ሜዳዮች፣ ሪባኖችና የምስክር ወረቀቶች በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናሉ።

17. <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

1. የፖሊስ አባላት የጡረታ መውጫ ዕድሜ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ/ ከኮንስታብል እስከ ዋና ሳጅን ማዕረግ ላላቸው 50 ዓመት፤

ለ/ ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር ማዕረግ ላላቸው 52 ዓመት፤

ሐ/ የዋና ኢንስፔክተርና ከዚያ በላይ ማዕረግ ላላቸው 55 ዓመት።

2. ለኮሚሽኑ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማንኛውም ፖሊስ አባል አገልግሎት በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጡረታ መውጫ እድሜ በኋላ ከ5 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. ከክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

1. ኮሚሽኑና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች በየበኩላቸው የሚኖራቸው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል የጋራ ጉባኤ ያቋቁማሉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋመው የጋራ ጉባኤ በኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀነራል ሰብሳቢነት ይመራል።

3. የጋራ ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ በፖሊሳዊ ሙያና ሥነ-ምግባር የታነፁ አባላትን ያቀፈና በተገቢው ቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የፖሊስ ተቋም በየክልሉ የሚገነባበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ለ/ በፖሊስ አባላት ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ቅጥርና አስተዳደር ጉዳዮች ወጥነት ያለው አሠራር በየክልሉ እንዲኖር መደረጉን ይከታተላል፤

ሐ/ ሀገራዊ እንድምታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመስራት የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥራል፤

መ/ የወንጀል ስጋትንና የወንጀል ድርጊትን ለመቀነስ የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፤ በወንጀል መከላከል የህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ አፈፃፀሙን ይገመግማል፤

ሠ/ የወንጀል መከላከልና የምርመራ ሥራዎች በቅንጅትና በመደጋገፍ የሚሠሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ረ/ በኮሚሽኑና በክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የሚዘረጋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሰ/ የፖሊስ አባላትን ተቋማዊ አመለካከትና አንድነት ለማጠናከር የስፖርት

ውድድሮች እንዲካሄዱ ያበረታታል፣ ይደግፋል።

4. ከክልሎች አቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች ኮሚሽኑ በመንግሥት ውሳኔ መሠረት በክልሎች ውስጥ ጣልቃ ገብቶ በሚሠራበት ወቅት የሚመለከታቸው የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ትብብር ማድረግ አለባቸው።

19. **የጋራ ጉባዔው ስብሰባ**

1. የጋራ ጉባዔው በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳ ይስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የጋራ ጉባዔው አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓት ጉባኤ ይሆናል።
3. የጋራ ጉባዔው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የጋራ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

20. **ስለአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ፖሊስ ኮሚሽኖች**

1. የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ፖሊስ ኮሚሽኖች ተጠሪነት ለኮሚሽኑ ይሆናል፤ ሆኖም ኮሚሽኑ በሚሰጠው ውክልና መሠረት ተጠሪነታቸው ለየከተሞቻቸው አስተዳደር እንዲሆን ሊደረግ ይችላል።
2. የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ፖሊስ ኮሚሽኖች ዓመታዊ ዕቅዳቸውንና የሥራ አፈፃፀማቸውን ሪፖርት ለኮሚሽኑና ለየከተሞቻቸው አስተዳደር ያቀርባሉ፤ ሆኖም በጀታቸው በየከተሞቻቸው አስተዳደር ምክር ቤቶች ይመደባል።

21. **የአሠራር መርህ**

1. በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር ዋና የተግባር አፈፃፀም አቅጣጫ ይሆናል። የቡድን አሠራሮች የጋራና የግል ኃላፊነትን ያስከትላሉ ።
2. በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው ።
3. የኮሚሽኑ አሠራር የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህን የተከተለ መሆን ይኖርበታል ።
4. የኮሚሽኑ አሠራር የሕዝብ ተሳትፎን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት ።

5. የኮሚሽኑ አሠራር የገለልተኝነት የአሠራር መርህን የተከተለ ይሆናል።

22. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን ከወንጀል መከላከልና ምርመራ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ሲወጣ የሚመለከታቸው ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

23. **<u>የፖሊስ ስልጣንን በውክልና ስለመስጠት</u>**

1. ልዩ ሙያ ለሚጠይቁ ጉዳዮች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች ለሚተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች የፖሊስ ሥልጣን በውክልና ሊሰጥ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚሰጠው የፖሊስ ሥልጣን ለጉዳዩ አስፈላጊ በሆነው መጠን ብቻ ይሆናል።

24. **<u>ክልከላዎች</u>**

የፖሊስ ተግባራትን በመፈጸም ረገድ፡-

1. ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ድርጊት መፈጸም፤ ወይም
2. በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ማድረግ፤

   የተከለከለ ነው።

25. **<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

   ሀ/ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 313/1995

   ለ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 14(1)(በ)፤

   ሐ/ የደህንነት፣የኢምግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 6/1987 አንቀጽ 5(8)።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

26. **<u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

የፌዴራል ፖሊስ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ ተላልፈዋል።

27. **<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ኮሚሽኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

28. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ህዳር 8 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## <u>ደንብ ቁጥር 96/1996 ዓ.ም</u>

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 313/1995 አንቀጽ 24(4) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 96/1996 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፣

1. "ፖሊስ" ማለት መሠረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚሽን ፖሊስ ኮሚሽን ተቀጥሮ የሚሠራ ነው።
2. "የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚሽን ፖሊስ ኮሚሽን ነው።
3. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው።
4. "ኮሚሽነር" ማለት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ነው።

### <u>ክፍል ሁለት</u>

## ስለአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን መቋቋም

**3. መቋቋም**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ተቋቁሟል።
2. ኮሚሽኑ በሕግና በሙያ የሚኖረው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ይሆናል።
3. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አሠራር፣ ሥልጠና ፤ ወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥራ የሚመለከቱ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የስታንዳርዳይዜሽን አቅጣጫዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል ።
4. የከተማው አሰተዳደር የኮሚሽኑን ዕቅድና በጀት ይወስናል፣ የኮሚሽኑን ስምሪትና የዕለት ተዕለት ሥራ ይከታተላል።

**4. ውክልና ስለመስጠት**

ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች መካከል በዚህ ደንብ በዝርዝር የተለዩት ተግባሮች በአዲስአበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን እንዲከናወኑ ለከተማው አስተዳደር ውክልና ተሰጥቷል

**5. ዓላማ**

የኮሚሽኑ ዓላማ በከተማው አስተዳደር ውስጥ የሀገሪቱን ሕገመንግሥትና ሌሎች ሕጎችን በማክበርና በማስከበር የሕዝብን ተሳትፎ መሠረት በማድረግ ወንጀል በመከላከል የከተማውን ነዋሪዎች ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ነው።

**6. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ ፦

1. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 4 ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጡት የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ውጭ ባሉ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚነሱ ማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች የመመርመርና የመከላከል ሥልጣን ይኖረዋል።
2. በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የወንጀል እና የደንብ መተላለፍ የዳኝነት ሥልጣን ሥር ያሉ ጉዳዮችን ይመረምራል፣ ይከላከላል ።

3. የከተማውን አስተዳደር ቻርተር በመጣስ አስተዳደሩን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ይከላከላል፤
4. በከተማው አስተዳደር ጥቅሞችና ተቋሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ይከላከላል
5. የከተማው አስተዳደር ተቋማትን ይጠብቃል፣
6. ለከተማው አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጥበቃ ያደርጋል፣
7. በፌዴራልና በከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይፈጽማል፣
8. የወንጀል ምርመራን በተመለከተ ከፌዴራል ዐቃቤ ሕግና ከከተማ አስተዳደር ዐቃቤ ሕግ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ይፈጽማል፤
9. በከተማው ደረጃ ለወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥራ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፣ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንና ለከተማው አስተዳደር ያቀርባል፤
10. በኮሚሽኑ ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና ለከተማው አስተዳደር ያስተላልፋል፣
11. ከጸጥታ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥና የሥራ ቅንጅት ያደርጋል፣
12. የከተማውን የትራፊክ እንቅስቃሴ ሥርዓት ያስከብራል፣
13. በከተማው በሚደረጉ ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት፣ በስፖርትና በመሳሰሉት ዝግጅቶች የጥበቃ አገልግሎት ይሰጣል፣
14. ውል ይዋዋላል ፣ በራሱ ስም ይከሳል ፣ ይከሰሳል ፣

7. **<u>የኮሚሽኑ አቋም ፤</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን፦

1. በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር አቅራቢነት በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የሚሾም አንድ ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር፣
2. ኮሚሽነሩን፣ ምክትል ኮሚሽነሩን እና የመምሪያ ኃላፊዎችን ያቀፈ የሥራ አመራር ጉባዔ፣ እና
3. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች፣

ይኖረዋል።

8. **<u>የኮሚሽኑ የሥራ አመራር ጉባዔ</u>**

የሥራ አመራር ጉባዔ፣

1. በከተማው ውስጥ ወንጀልን ለመከላከልና ለመመርመር የሚረዱ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጥናቶችን በመመርመር ከአስተያየት ጋር ለከተማው ከንቲባ እና ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር እንዲቀርብ ያደርጋል፣
2. የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አወቃቀርና አሠራር የሚመለከቱ ጥናቶችን ይመረምራል፣ በጥናቶቹ መሠረት ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ከአስተያየት ጋር ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ያቀርባል ፣
3. በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በሚወሰነው የፖሊስ ሥልጠና ስትራቴጂና ስታንዳርድ መሠረት የኮሚሽኑን መሠረታዊ የፖሊስ ሥልጠና ዕቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲጸድቅለትም ለከተማው አስተዳደር ያቀርባል፣
4. የኮሚሽኑን ዓመታዊ ዕቅድ ሪፖርትና የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ከአስተያየት ጋር ለከተማው አስተዳደር ከንቲባ እና ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ያቀርባል።

9. <u>የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ሥልጣንና ተግባር</u>

የከተማው አስተዳደር ከንቲባ

1. የኮሚሽኑን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል ፣
2. በኮሚሽኑ የቀረበለትን ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀት፣ ሪፖርትና የሥራ አፈፃፀም በሚመለከት ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሚሰጠውን አስተያየት በማካተት ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥ ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣
3. የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ የስታንዳርዳይዜሽን፣ የሥልጠና ጥናቶች በመመርመር ከአስተያየቱ ጋር ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ያቀርባል ፣
4. በከተማው ውስጥ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር ኮሚሽኑ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ የከተማው ነዋሪዎች ቅንጅትና ትብብር እንዲጠናከር ያደርጋል ።

10. <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽነር ተጠሪነቱ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ሆኖ የኮሚሽኑን ሥራ በበላይነት ይመራል ፣ ያስተዳድራል ፣
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አነጋገር እንደተጠበቀሆኖ ኮሚሽነሩ ፣

   ሀ/ የኮሚሽኑን መምሪያ ኃላፊዎች እንዲሾሙ ከከተማው አስተዳዳሪ ጋር በመመካከር ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ያቀርባል ፣

   ለ/ የኮሚሽኑን የመተዳደሪያ ደንብ ያስፈጽማል ፣

ሐ/ በፖሊስነት ከተቀጠሩት ውጪ ያሉትን የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል፣

መ/ የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አወቃቀር፣ አሠራር፣ የወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥራዎች የሚመለከቱ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

ሠ/ የኮሚሽኑን የሥራ ዕቅድ እና ረቂቅ በጀት በማዘጋጀት ለከተማው አስተዳደር ከንቲባ ያቀርባል ፣በጀት ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

ቀ/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ሥራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል ፣

ረ/ የኮሚሽኑን የሥራ አመራር ጉባዔ በሰብሳቢነት ይመራል፣

11.<u>የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ምክትል ኮሚሽነሩ፡-

ሀ/ የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ ፣ በማደራጀት፣ በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፣

ለ/ በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች መካከል ከፊሉን ይከታተላል፣

ሐ/ ኮሚሽነሩ በማይኖሩበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፣

መ/ በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነር ይሆናል።

12.<u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ይመደባል።

13.<u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል ።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

14.<u>የፌዴራል ፖሊስ አዋጅና ደንብ ተፈፃሚ ስለመሆናቸው</u>

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 313/1995 ዓ.ም [10]አንቀጽ15፣16፣17፣18፣19፣20፣21፣24፣25፣ 26 እና 27 ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 86/1995[11] በኮሚሽኑ ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ።

15.<u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ለማውጣት ይችላል፡

16.<u>ደንቡ የሚፀና በት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 27 ቀን 1996 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

[10] በ18/2(2004) አ.720 ተሽሯል፡፡

[11] በ19/1(2005) ደ.268 ተሽሯል፡፡

## አዋጅ ቁጥር 804/2005 ዓ.ም

## የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት መጠናከር የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሉዓላዊነት፣ ሕገ መንግስትና የሕገ መንግስታዊ ስርዓትን ለመጠበቅና ለመከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፡

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የአገሪቱን የሰላም፣ የልማት፣ የዲሞክራሲ እና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ለመደገፍ እንዲችል ሥልጣኑን፣ ተገባሩን እና ተጠያቂነቱን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፡

ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት በታማኝነትና በጽናት የቆመ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ፣ ዘመናዊና ጠንካራ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት መገንባት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (7) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 804/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

1. "ሠራተኛ" ማለት በመደበኛ ወይም በኮንትራት ሠራተኛነት ተቀጥሮ ወይም በትውስት መነሻነት በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የሚሠራ ማንኛውም ሰው ነው፤
2. "የደህንነት ማረጋገጫ" ማለት አንድ ሰው ለታጨበት ወይም ለሚመደብበት የሥራ ኃላፊነት ታማኝነትና ተፈላጊ ስብዕና ያለው መሆኑን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚደረግ የማጥናትና የማጣራት ሂደት ነው፤
3. "መረጃ" ማለት አግባብ ላላቸው የመንግስት አካላት የሚቀርብ የአገሪቷን ብሔራዊ ደህንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚረዳ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የተሰበሰበ፣ የተተነተነና የተዘጋጀ መረጃ ነው፡
4. "የመረጃና የደህንነት እቃዎችና መሣሪያዎች" ማለት መረጃ ለማሰባሰብ ወይም መረጃ እንዳይወሰድ ለመከላከል ወይም የደህንነት ወይም የኮሚውኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ያጠቃልላል፤
5. "ፍርድ ቤት" ማለት እንደየሁኔታው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፤
6. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
7. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላ አገሪቱ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት</u>

4. <u>መቋቋም</u>

1. የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "አገልግሎት" እየተባለ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በሚኒስቴር ደረጃ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡
2. አገልግሎቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።
3. በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግስታት ደረጃ ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ተቋም ማቋቋም አይቻልም።

5. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

6. **ዓላማ**

የአገልግሎቱ ዓላማ ጥራት ያለው መረጃ በማቅረብና አስተማማኝ የደህንነት አገልግሎት በመስጠት የአገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት መጠበቅ ይሆናል።

7. **አጠቃላይ ስልጣንና ተግባር**

አገልግሎቱ የሚከተሉት አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በአገር ውስጥና በውጭ አገር የመረጃና የደህንነት አገልግሎት ስራን በሃላፊነት የመምራት፤
2. የብሔራዊ መረጃና የደህንነት አገልግሎት ፖሊሲዎችን የማዘጋጀት፤ ሲፀድቁም ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስልት የመቀየስ፤
3. ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት የሚያስችለውን አደረጃጀትና መዋቅር አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የማቅረብና ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ፤
4. የመረጃና የደህንነት ሙያ የስልጠናና የምርምር ተቋም የማቋቋምና የማስተዳደር
5. በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ተባብሮ የመስራት፣ አስፈላጊውን መረጃና ማስረጃ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከውጭ አገር አቻ ተቋማት ጋር ትብብር የማድረግ፣ መረጃ የመቀበል ወይም የመስጠት እና በጋራ ኦፕሬሽን የማካሄድ፤
7. ሥልጣንና ተግባሩን በሚገባ ለመወጣት የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

8. **የመረጃ ሥልጣንና ተግባራት**

አገልግሎቱ የሚከተሉት የመረጃ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የሚደረጉ ማናቸውንም የውስጥና የውጭ እንቅስቃሴዎችን፣ በአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገትና የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ሊቃጡ የሚችሉ ጥቃቶችን፣ ከባድ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እና አሻጥሮችን የመከታተል፣ የማጣራት፣ መረጃና ማስረጃ የማሰባሰብና ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤

2. አገራዊ የፀረ-ሽብርተኝነት ትብብርን እና ቅንጅትን በሃላፊነት የማስተባበር፡ በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የፀረ-ሽብርተኝነት ግንኙነትና ትብብር ሃላፊና ተጠሪ በመሆን አገሪቷን የመወከል፤
3. ሽብርተኝነትንና ጽንፈኝነትን የመከታተልና የማጣራት እንዲሁም መረጃና ማስረጃ የማሰባሰብ፡
4. የኢኮኖሚ ደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤
5. በአገርና በህዝብ ጥቅም ላይ የሚፈፀም የስለላ ተግባር የመከታተልና የማጣራት፤ መረጃ የማሰባሰብና የፀረ- ስለላ ተግባር የማከናወን፤
6. የአገሪቱን ጥቅምና ደህንነት የሚጎዱ ሌሎች ከባድ ወንጀሎችን የመከታተል፣ መረጃና ማስረጃ የማሰባሰብ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመሥራት፤
7. ብሔራዊ ደህንነትን ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (3)፣ (4)፣ (5) ወይም (6) በተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተጠረጠረን ማንኛውንም ሰው በማንኛውም ስፍራ በመግባትና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ክትትል የማድረግ።

9. <u>የደህንነት ሥልጣንና ተግባራት</u>

አገልግሎቱ የሚከተሉት የደህንነት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ለኢትዮጵያ እና ለውጭ አገር ዜጎች በኢሚግሬሽን እና በዜግነት አዋጅ መሠረት አገልግሎት የመስጠትና የመቆጣጠር፤ የአገልግሎቱን ክፍያ ተመን አጥንቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የማቅረብና ሲፀድቅም ተግባራዊ የማድረግ
2. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ መስረት ለስደተኞች አስፈላጊውን አገልግሎት የመስጠት፤
3. በኢትዮጵያ የአቭዬሽን ሴኩሪቲ አዋጅ መሰረት የአቬዬሽን ሴኩሪቲን በበላይነት የመምራት፤ የአቭዬሽን ሴኩሪቲ አገልግሎት የመስጠት እና ሌሎች የአቬዬሽን ሴኩሪቲ ባለድርሻ አካላትን የማስተባበር፤
4. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ለአገሪቱ ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ አገር መሪዎች ጥበቃ የማድረግ፤

5. ለአገሪቱና ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ ክፍተኛ ባለስልጣናት አጠባበቅ መመሪያና ስታንዳርድ የማውጣት እና የተሟላ ጥበቃ እየተደረገላቸው ስለመሆኑ የማረጋገጥ፤
6. የቁልፍ ተቋማትን የአጠባበቅ መመሪያና ስታንዳርድ የማውጣት፤
7. ፈንጂ ለማምረት፣ ለመያዝ፣ ለመጠቀም፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለመሸጥ፣ ለመጠገን እና ለማስወገድ ፈቃድ የመስጠትና ዝውውራቸውን የመቆጣጠር
8. ለቁልፍ የመንግስት ሠራተኞች የደህንነት ማረጋገጫ አጣርቶ የመስጠት፤
9. ለግል የጥበቃ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው የደህንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አጣርቶ የመስጠት፡
10. የመረጃና የደህንነት እቃዎችንና መሳሪያዎችን ወደ አገር ውስጥ የማስገባት፣ ከአገር የማስወጣት፣ የመሸጥ፣ የማዘዋወር፣የመያዝ የማምረትና የማስወገድ ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም የመወሰንና ቁጥጥር የማድረግ፡
11. ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ የመስጠት ስራን በበላይነት የመምራት፡
12. የመረጃዎች ሚስጥራዊነት ደረጃ አመዳደብ መስፈርቶችን እና የጥበቃ ደረጃዎችን አዘጋጅቶ ለመንግስት የማቅረብና ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን የመከታተል።

10. <u>ስለውክልና</u>

አገልግሎቱ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሊያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን አግባብነት ላላቸው የመንግሥት አካላት በከፊል በውክልና ሊሰጥይችላል።

11. <u>አደረጃጀት</u>

አገልግሎቱ፦

1. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ዳይሬክተር ጀነራል፡
2. የመረጃ አካላት፡
3. የደህንነት አካላት፡
4. ድጋፍ ሰጪ አካላት፡ እና
5. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

12. <u>የዳይሬክተር ጀነራሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዳይሬክተር ጀነራሉ የአገልግሎቱ ዋና ሥራአስፈፃሚ በመሆን የአገልግሎቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዳይሬክተር ጀነራሉ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የአገልግሎቱን ሥልጣንናተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው የአገልግሎቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የአገልግሎቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ/ ለአገልግሎቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ/ ብሔራዊ ጥቅምንና አገራዊ ደህንነትን ሊጎዳ የሚችል ሚስጥር ይባክናል የሚል ምክንያት ሲኖረው የአገልግሎቱን የሰው ኃይል ፕሮፋይል፣ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች፣ የክፍያ ማስረጃዎች፣ የሥራ መሣሪያዎች፣ የመረጃ ምንጮች፣ አሠራሮች እና መመሪያዎች እንዲሁም የሥራ ውጤቶች እጅግ ብርቱ ሚስጥር ብሎ በመሰየም ለማንኛውም አካል እንዳይገለፁ ያደርጋል፣

ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች አገልግሎቱን ይወከላል፣

ሰ/ ስለአገልግሎቱ የሥራ እንቅስቃሴ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ያቀርባል።

3. ዳይሬክተር ጀነራሉ ለአገልግሎቱ የሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአገልግሎቱ ሌሎች የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

**13.<u>በጀት</u>**

የአገልግሎቱ በጀት፡-

1. በመንግሥት ከሚመደብ ገንዘብ፣ እና
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩን በማስፈቀድ ለተልዕኮው ማስፈፀሚያ እንዲውል ከሚደረግ፡-

ሀ/ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ የተለያዩ ንብረቶቹንና የሥራ መሣሪያዎቹን በመሸጥ ከሚገኘው ገቢ፣

ለ/ ከኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ አገልግሎት ከሚገኘው ገቢ 50 በመቶ እና

ሐ/ ከሌሎች የገቢ ምንጮች፤

ይሆናል።

14.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. አገልግሎቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የአገልግሎቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውስጥ ኦዲተሮች ይመረመራሉ።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(2)(ሠ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

15.<u>ስለግዥና ንብረት አስተዳደር</u>

1. አገልግሎቱ በመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት ግዥ በራሱ ይፈፅማል ፣ ንብረቱን ያስተዳድራል፣ ያስወግዳል።
2. አገልግሎቱ ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን የመረጃና የደህንነት እቃዎችና መሣሪያዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል።
3. አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱትን እቃዎችና መሣሪያዎች በሚመለከት የጉምሩክ ዲክላራሲዮንና አባሪ ሰነዶችን እንዲያቀርብ፣ ዕቃዎቹን እንዲያስፈትሽ እና ሰነዶችን እንዲያስመረምር አይገደድም።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለአገልግሎቱ ሠራተኞች</u>

16.<u>ቃለ መሃላ ስለመፈጸም</u>

በአገልግሎቱ ሠራተኛነት የተቀጠረ ማንኛውም ሰው ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት እና ለሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ህዝባዊ አደራና ሙያዊ ሃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሃላ ይፈጽማል።

17.<u>ስለ ሠራተኞች መብት</u>

ማንኛውም የአገልግሎቱ ሠራተኛ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

1. በመንግሥት በሚፀድቅ ስኬል መሰረት ደመወዝ የማግኘት፣

2. በአገልግሎቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ልዩ ልዩ ፈቃዶች፡ የህክምና አገልግሎትና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች የማግኘት፡
3. በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሠረት የአገልግሎትና የጉዳት ጡረታ መብት የማግኘት፡
4. በሕግ የተሰጠውን ሃላፊነት በአግባቡ ሲወጣ በወቅቱ በነበሩት አስገዳጅ ሁኔታዎች የፈፀመው መሆኑን አገልግሎቱ ሲያምንና ሲያረጋግጥ በቀረበበት የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ክስ በአገልግሎቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አስፈላጊውን የሕግ ድጋፍ የማግኘት።

18. <u>ስለ ሠራተኞች ግዴታ</u>

ማንኛውም የአገልግሎቱ ሠራተኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

1. ለሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ታማኝ የመሆን፣ የተቋሙን ሚስጥራዊነት በአግባቡ የመጠበቅ፣ የተሟላ ስብዕናን እና አብሮ የመሥራት መንፈስን የመላበስ እና ሙያዊ ብቃቱን በቀጣይነት የማሳደግ፡
2. አገልግሎቱ በሚመድበው ማንኛውም ቦታና ጊዜ የተሰጠውን ግዳጅ በአግባቡ የመወጣት፡
3. ከአገልግሎቱ የበላይ ወይም የቅርብ ሃላፊዎች እውቅናና ፈቃድ ውጪ ሌሎች ሥራዎችን ያለመስራት፡
4. በሥራ ላይ እያለም ሆነ ከሥራ ከተሰናበተ በኃላ ከአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊ እውቅናና ፈቃድ ውጪ በሥራ ላይ እያለ ያወቃቸውን ሚስጥሮች፣ አሰራሮች፣ የሥራ እንቅስቃሴ፣ አደረጃጀት፣ ሰነዶች እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመለከተ ለማንኛውም አካል ወይም ግለሰብ ያለመግለጽ፤ ያለማተም፣ ያለማሳተም ወይም ያለማሰራጨት፤
5. በራሱና በቤተሰቡ ባለቤትነት ወይም ይዞታ ስር የሚገኝ ሀብት እና የራሱንና የቤተሰቡን የገቢ ምንጮች ለአገልግሎቱ የማሳወቅና የማስመዝገብ፤ እና
6. አገልግሎቱ በሚያወጣቸው መመሪያዎች ውስጥ የሚገለጹ ሌሎች ግዴታዎችን የመፈጸም።

19. <u>የግል ደህንነት ጥበቃ</u>

1. በቁልፍ ሥራ ላይ የተመደበ ማንኛውም የአገልግሎቱ ሃላፊ ወይም ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል ወይም ወደ ሌላ ሥራ ሲዛወር ጥበቃ ይደረግለታል።

2. የጥበቃ ሃይሉ ስብጥርና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል።

20.**ስለሕግ ከለላና ስላለመገደድ**

1. ማንኛውም የአገልግሎቱ ሃላፊ ወይም ሠራተኛ ከሥራ ሲሰናበት ወይም ወደ ሌላ ቦታ ሥራ ሲዛወር በአገልግሎቱ ተመድቦ በሚሰራበት ወቅት ከተልዕኮው ጋር ተያይዞ ስላወቃቸው መረጃዎች ወይም በእጁ ስለገቡ ሰነዶች ለፍርድ ቤት ወይም ለአጣሪ ኮሚቴ ወይም ለሌላ አካል እንዲገልጽ ወይም እንዲያቀርብ አይገደድም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የሕግ ከለላ ከአገልግሎቱ ተልዕኮ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መልኩ ባለው ትስስር ምክንያት የመረጃና የሰነዶች እውቀት ባለው ማንኛውም ሰው ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

21.**ስለተጠያቂነት**

1. ማንኛውም የአገልግሎቱ ሠራተኛ፡-
   ሀ/ በዚህ አዋጅ ለአገልግሎቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ያለአግባብ ከተገለገለ፤ ወይም
   
   ለ/ አገልግሎቱ በሚያወጣው የሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን መመሪያ የተመለከቱ የሥነ-ምግባርና የሙያ ሃላፊነቶቹን ከተላለፈ፤
   
   አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።
2. የአገልግሎቱ ሠራተኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው በአገልግሎቱ ወይም በሃላፊው ወይም በሠራተኛው ስም በቃል ወይም በድርጊት ለማታለልና ለማስመሰል የሞከረ ወይም በማታለልና በማስመሰል የማንኛውንም ዜጋ ወይም የተቋም ሰላማዊ እንቅስቃሴ ወይም ዕለታዊ ተግባር ያወከ እንደሆነ አግባብ ባላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

**ክፍል አራት**

**ስለቁጥጥር**

22.**የሕግ አውጪ አካል ቁጥጥር**

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አግባብ ያለው ቋሚ ኮሚቴ የአገልግሎቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ኮሚቴው የሚያደርገው ክትትል የአገርን ብሔራዊ ደህንነት ለአደጋ በማያጋልጥ አግባብ መሆን አለበት።

23.**የአስፈፃሚ አካል ቁጥጥር**

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአገልግሎቱን የሥራ እንቅስቃሴ አፈፃፀም ይከታተላል ይቆጣጠራል።

24.**የዳኝነት አካል ቁጥጥር**

አገልግሎቱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8(7) ላይ የተመለከቱትን ተግባራት ለመፈፀም የሚያስፈልገውን የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት።

25.**ዋና ኦዲተር**

ዋናው ኦዲተር የአገልግሎቱን የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(3) መሠረት ይመረምራል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26.**ዓርማ**

አገልግሎቱ ዓላማውንና ተልዕኮውን የሚያመለክት የራሱ ዓርማ ይኖረዋል።

27.**የመተባበር ግዴታ**

1. ለአገልግሎቱ ስራ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ወይም ማስረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው መረጃውን ወይም ማስረጃውን በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለአገልግሎቱ መረጃ ወይም ማስረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው መረጃ ወይም ማስረጃ መጠየቁን ወይም መስጠቱን በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተመለከቱ ግዴታዎችን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

28.**ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. አገልግሎቱ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

29.**ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

1. የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 6/1987 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

30. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ያሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 17 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 808/2006 ዓ.ም

## የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በመስፋፋት ላይ ያሉ የአገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች እና ኢንዱስትሪዎች በኮምፒውተር ላይ የተመሰረቱ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለጥቃት በመጋለጣቸው እና ወደፊት ይበልጥ ተጋላጭ እየሆኑ የሚሄዱ በመሆናቸው ደህንነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኮምፒውተሮች አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ትስስር ምክንያት የተፈጠረው የሳይበር ምህዳር ለብሔራዊ ደህንነት ስጋት እንዳይሆን መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ ኢንፎርሜሽን ቁልፍ ማህበራዊ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሃብት በመሆኑ ለደህንነቱ ጥበቃ ማድረግ ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ፣

ብሔራዊ ጥቅምን እና የዜጎችን መብት ለማረጋገጥ ኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትን ማረጋገጥ ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ፣

ኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረገ ቁልፍ መሰረተ ልማት ደህንነት ለመጠበቅ የሚደረገውን አገራዊ ጥረት የሚያቀናጅ እና ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂን በብቃት ማስፈጸም የሚችል ጠንካራ ተቋም መገንባት በማስፈለጉ፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 808/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

   1. "ኢንፎርሜሽን" ማለት ከማንኛውም ጥሬ ዳታ የሚመነጭ በድምፅ፣ በፅሁፍ በምስል፣ በካርታ ወይም በሌላ ማንኛውም መልኩ ተቀነባብሮ የሚገኝ ሀብት ሲሆን ማሽኖችን ለማዘዝ እና ለመምራት የሚያገለግሉ ኮዶችን እና ፕሮግራሞችን ያጠቃልላል፣

2. “ኮምፒውተር” ማለት በሶፍትዌር እና ማይክሮቺፕ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የዳታ ፕሮሰሲንግ፣ ክምችት፣ ትንተና፣ ስርጭት፣ ግንኙነት ወይም ሌሎች ሂሳባዊ ወይም አመክንዮአዊ ተግባራትን የሚያከናውን ማንኛውም መሳሪያ ነው
3. “ኮምፒውተርን መሰረት ያደረገ ቁልፍ መሰረተ ልማት” ማለት ኢንዱስትሪያዊ የቁጥጥር ስርዓቶችን፣ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ስርዓቶች እና መሰረተ ልማቶችን፣ የሳይበር እና የቴሌኮም መሰረተ ልማቶችን፣ ኤሌክትሮማግኔቲክ መሰረተ ልማቶች፣ የጂኦስፓሻል መሰረተ ልማቶች፣ ወታደራዊ የእዝ እና ቁጥጥር ስርዓቶች ወይም ኢንፎርሜሽንን ለመተንተን፣ ለማሰራጨት፣ ለማከማቸት እና መልሶ ለማግኘት የሚያስችሉ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ወይም ስርዓቶችን ያጠቃልላል።
4. “ቁልፍ መሰረተ ልማት” ማለት ለጥቃት ከተጋለጠ በህዝብ ደህንነት እና ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሰረተ ልማት ነው
5. “ጥቃት” ማለት ኮምፒውተርን መሰረት ያደረገ ቁልፍ መሰረተ ልማት የተሟላ አገልግሎት እንዳይሰጥ ወይም እንዲወድም ማድረግን ወይም የኢንፎርሜሽንን ተዓማኒነት፣ ሚስጥራዊነት ወይም ተደራሽነት ማሳጣትን ወይም ኮምፒውተርን መሰረት አድርጎ በዜጎች ስነ ልቦና ላይ የሚሰነዘር ጥቃትን ወይም ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚፈጸም የማንነት ስርቆት ተግባርን ያጠቃልላል፡
6. “የደህንነት ኦዲት” ማለት ኮምፒውተርን መሰረት ባደረገ ቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ ተጋላጭነትን ለማወቅ የዘልቀ ገብ ፍተሻ ተግባራትን ማከናወን እና አገራዊ የኢንፎርሜሽን ፖሊሲ እና ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ የተቋማትን የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስርዓት በመገምገም እንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረግን ይጨምራል።
7. “የደህንነት ፍተሻ እና ግምገማ” ማለት በአገራዊ የደህንነት ስታንዳርድ እና መመዘኛ መሰረት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶችን፣ ስርዓቶችን ወይም የስራ ሂደቶች የቅድመ ልማት፣ ቅድመግዢ ወይም ቅድመ ትግበራ ፍተሻ እና ግምገማ የማድረግ ተግባር ነው፡
8. “የኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል” ማለት በኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ባደረገ መሰረተ ልማት ላይ የሚሰነዘር ጥቃትን ለመከላከል እንዲቻል የጥቃት አደጋዎችን አስቀድሞ የመለየት የመተንተን፣

ዜጎችን የማስጠንቀቅ፣ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ምክርን የማቅረብ፣ የማገገሚያ መንገዶችን የመዘየድ እና በዚህ ዘርፍ አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ቅንጅት እንዲፈጠር የማስቻል ተግባራትን የሚያከናውን ማዕከል ነው፤

9. "ክሪፕቶግራፊ" ማለት ከታሰበው ተቀባይ ውጪ የኢንፎርሜሽን ልውውጥን ማንም ሰው ወይም ማሽን እንዳያነበው ወይም እንዳይቀይረው የሚያስችል የምስጠራ ወይም በኤሌክትሮኒክ ንግድ መተማመንን እና አለመካካድን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሳይንስ ነው፡

10. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

የኤጀንሲው ዓላማ የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትን በማረጋገጥ ለአገሪቱ የሰላም፣ የልማት እና የዲሞክራሲ መርሃግብሮች ማስፈጸሚያ እንዲሆኑ ማስቻል ይሆናል።

6. <u>የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተመግባራት ይኖሩታል፦

1. በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረቱ የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ምርቶችን እና አገልግሎቶችን የማበልጸግና ስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ፡
2. የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ብሔራዊ የፖሊሲ፣ የህግ፣ የስታንዳርድ እና ስትራቴጂ ረቂቆችን የማዘጋጀትና ሲጸድቁም ተፈጻሚነታቸውን የመከታተል

3. መንግስታዊ እና የግል ተቋማት አገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ እና ስታንዳርድ ማዕቀፎችን ተከትለው የየራሳቸው ፖሊሲና ስታንዳርድ ቀርጸው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍ የመስጠትና አፈጸጸማቸውን የመቆጣጠር ፡
4. ኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ባደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ወይም ስርዓቶች ላይ ወይም በዜጎች ስነልቦና ላይ የሚሰነዘሩትን የሳይበር እና ኤሌክትሮማግኔቲክ ጥቃቶችን ለመከላከል አስፈላጊ አጸፋዊ እርምጃ የመውሰድ
5. በማንኛውም ወቅት የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ኦዲት የማድረግ፣ መመዘኛውን አሟልተው ለተገኙ ተቋማትም የደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የመስጠት ወይም እነዚህን ተግባራትእንዲያከናውኑ ለሌሎች ተቋማት ውክልና የመስጠት፡
6. አገራዊ የኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከልን የማደራጀትና በበላይነት የመጋምራት፡
7. የሳይበር ወንጀሎችን በመከላከልና በመመርመር ሂደት ለፖሊስና ሌሎች በህግ ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት ትብብር የማድረግ፣ ድጋፍ የመስጠት፡
8. ጥቃትን ለመከላከልና ዜጎችን አስቀድሞ ለማስጠንቀቅ ሲባል የጥቃት ሰለባ ወይም መነሻ ናቸው ተብለው በተጠረጠሩ ኮምፒውተሮች ወይም መሰረተ ልማቶች ላይ በርቀት ወይም ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማውጣት እና ከፖሊስ ጋር በመተባበር በአካል በመገኘት የዲጅታል ፎረንሲክ ምርመራ የማካሄደግ፡
9. የክሪፕቶግራፊ ምርትን እና ዝውውርን የመቆጣጠር አስፈላጊውን መስፈርት በማውጣት የአጠቃቀም ስርዓት የመዘርጋት የክሪፕቶግራፊ መሰረተ ልማት የማበልጸግና የመዘርጋት፡
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተደነገጉትን ተግባራት ለማከናወን ብሔራዊ "ሩት ሰርተፍኬት ባለስልጣን" በመሆን የማገልገል፡
11. ወደ አገር የሚገቡና ከአገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች፣ የመረጃ አነፍናፊዎች እና የጥቃት ቴክኖሎጂዎች በአገር ደህንነት ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ ከመከላከል አንጻር ከሚመለከታቸጡ አካላት ጋር በመቀናጀት የመቆጣጠር፡
12. ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የደህንነት ፍተሻ እና ግምገማ የሚያገለግል የላብራቶሪ ማዕከል የማቋቋም፡

13.አገራዊ የስፓሻል ዳታ መሰረተ ልማትን የማበልጸግና የማስተዳደር እንዲሁም የስፓሻል ዳታ ማሰባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፦

ሀ/ ማናቸውም አይነት የጂኦስፓሻል መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የመተንተን፣ የማከማቸት እና የማሰራጨት

ለ/ ዳታ በሚሰበሰብበት፣ በሚከማችበት፣ በሚተነተንበት ወይም በሚሰራጭበት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የደህንነት ተጋላጭነቶችን እና ስጋቶችን ለመቀነስ አስፈላጊ እርምጃ የመወሰድ

14.በተመረጡ ድንበር ዘለል የብሔራዊ ደህንነት ስጋት እንቅስቃሴዎች ዙሪያ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተን፣ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ እንዲሁም ለፀጥታ ሃይሎች ድጋፍ የመስጠት፡

15.አገራዊ አቅም ባልተፈጠረባቸው ክፍተቶች ደህንነታቸው የተጠበቁ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት መሰረተልማቶችን እና ስርዓቶችን የማበልጸግና የመዘርጋት፤ እንዲሁም ለሚያቀርበው ምርትና ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ የማስከፈል፡

16.ኢንፎርሜሽን ወይም ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ዙሪያ የትምህርት እና ስልጠና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ በራሱ ማሰልጠኛ ማዕከል ወይም ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር የመስጠት፡

17.በመንግስት ውሳኔ መሰረት ለውጭ አጋር አገራት የደህንነት ምርት እና አገልግሎት የማቅረብ

18.ተልዕኮውን ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖሲገኝ ዓለም አቀፋዊ ቅንጅትን የመፍጠር

19.የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፡

20.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎችተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

7. <u>የኤጀንሲው አደረጃጀት</u>

ኤጀንሲው፦

1. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡ እና
2. አስፈላጊ ሰራተኞች

ይኖሩታል።

8. <u>የዋናው ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ የኤጀንሲውን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ስልጣን እና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፣
   ለ/ የኤጀንሲውን ሰራተኞች በመንግስት በሚጸድቅ መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
   ሐ/ የኤጀንሲውን የስራ ፕሮግራም እና በጀት ያዘጋጃል በመንግስት ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፣
   መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ በደንብ የሚደነገጉ የአፈጻጸም ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ ብሔራዊ ደህንነትን ሊጎዳ የሚችል ሚስጥር ሊባክን ይችላል ብሎ ለመገመት ምክንያት ሲኖረው የኤጀንሲው የሰው ሃይል ፕሮፋይል፣ የተወሰኑ የሂሳብ ሰነዶች፣ መሳሪያዎች፣ አሰራሮች፣ የስራ ውጤቶች እንዲሁም የእቅድና የስትራቴጂ ሰነዶች ጥብቅ ሚስጥር ብሎ በመሰየም ለማንኛውም አካል እንዳይገለጹ ያደርጋል፤
   ረ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፡
   ሰ/ የኤጀንሲውን የስራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል ለሚመለከተው አካል ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ስልጣን እና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

9. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት፦

1. በመንግስት ከሚመደብ ገንዘብ፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(15) መሰረት ተሰብስቦ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በማስፈቀድ ለተልዕኮው ማስፈፀሚያ እንዲውል ከሚደረግ የአገልግሎት ክፍያ እና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚውጣጣ ይሆናል፡ ፡

10. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8(2)(ሠ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡ ፡
3. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውስጥ ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

11.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. ኤጀንሲው ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

12.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ኤጀንሲው ስልጣን እና ተግባሩን በዚህ አዋጅ መሰረት በሰራ ላይ ለማዋል እንዲችል የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል።

13.<u>የተሻረ ህግ</u>

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 250/2003 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

14.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 24 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 320/2006**

**የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 35 እንዲሁም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 808/2006 አንቀጽ 11(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 320/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 808/2006 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር ለተመለከቱት ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   3. "ኢጀንሲ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፤
   4. "የአባልነት ምዝገባ" ማለት ኤጀንሲው በድረ-ገጽ አማካኝነት የአባልነት ክፍያ በመክፈል ከተለያዩ የደህንነት ተቋማት ጋር ስምምነት በመፈጸም ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለማግኘት የሚካሄድ ምዝገባ ነው፤
   5. "የሳይበር ኦፕሬሽን" ማለት የሳይበር መረጃንና ዲጂታል ፎረንሲክ ማስረጃን ለመሰብሰብ፣ ሀገራዊ ደህንነትንና የዜጎች ደህንነትን የሚጎዱ የሳይበር እንቅስቃሴዎችን ለመግታት ወይም በሉአላዊነት ላይ የሚቃጡ የሳይበርና

ኤሌክትሮማግኔቲክ ቴክኖሎጂ ጥቃቶችን ለመከላከል በስራ ላይ የሚውል ዘዴ ነው፤

6. “ዋና ዳይሬክተር” ማለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለኤጀንሲው መረጃዎች፣ ኦዲት እና ግምገማ

### 3. ስለሚስጥራዊ መረጃዎች

በሌሎች ሕጎች የተደነገገው ቢኖርም ዋና ዳይሬክተሩ፡-

1. የኤጀንሲውን የሰው ሃይል ፕሮፋይል፣ የተወሰኑ የሂሳብ ሰነዶች፣ መሳሪያዎች፣ አሰራሮች፣ የስራ ውጤቶች እና የእቅድና የስትራቴጂ ሰነዶችን እጅግ ጥብቅ ሚስጥር ብሎ በመሰየም ለማንኛውም አካል እንዳይገለፁ ያደርጋል፤
2. ለብሔራዊና ተቋማዊ ደህንነት፣ ለተቋሙ መወዳደር አቅም እና ለሠራተኞቹ ደህንነት አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን የኤጀንሲውን ማንኛውም የሥራ ስፍራ፣ ቁሳዊና ኢ-ቁሳዊ የሀብት መረጃዎችና ሌሎች የቦታ ምልከታ መረጃዎች ጥብቅ ሚስጥር እና ሚስጥር ብሎ በመሰየም ለማንና መቼ ተደራሽ መሆን እንዳለበት በመመሪያ ይወስናል።

### 4. ስለሂሳብና የክዋኔ ኦዲት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ንብረት በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ሙሉ በሙሉ እንዳይመረመር ወይም በከፊል እንዳይመረመር ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቦ ያፀድቃል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በየጊዜው የመረጃውን ሚስጥራዊነት እየፈተሸ መመሪያውን እንዲሻሻል ያደርጋል።
2. የኤጀንሲው የውስጥ ኦዲተር ዋና ዳይሬክተሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተመለከቱ ሃብቶችን፣ ሰነዶችን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ይመረምራል፣ የሂሳብና የክንዋኔ ኦዲት ያካሂዳል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በውስጥ ኦዲተር የሚደረገው የምርመራ ሪፖርት ለዋና ዳይሬክተሩ ብቻ የሚቀርብ ይሆናል።

### 5. የደህንነት ኦዲት

1. ኤጀንሲው ኢንፎርሜሽንና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል በሚያደርገው የደህንነት ተጋላጭነት ኦዲት፣ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ስታንዳርዶች፣ መመዘኛዎች፣ አሰራር ስርዓቶች፣ የደህንነት ኦዲተሮች የሚመሩበት የአፈጻጸም መመሪያ እና የኦዲት ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ይቀርጻል፤ ለኦዲት ተደራጊ ተቋማት አስቀድሞ እንዲያውቁት ያደርጋል።
2. የኦዲት ተደራጊ ተቋማት የደህንነት ኦዲት መርህ ግብር ተቋማቱ ያላቸውን ሀገራዊ ፋይዳና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዋና ዳይሬክተሩ በየጊዜው ይወሰናል።
3. ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በደህንነት ኦዲት ሪፖርቱ ላይ ማብራሪያ የመጠየቅ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በኤጀንሲው የሚሰጣቸውን ምክረ ሃሳብ መቀበልና የእርምት እርምጃ መውሰድ አለባቸው።
4. ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በራሳቸው የደህንነት ኦዲት እንዲያደርጉ ለማድረግ እንዲችሉ ኤጀንሲው አስፈላጊውን የቴክኒክና ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ ይኖርበታል።

6. <u>ስለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደህንነት</u>

1. ኤጀንሲው ሀገራዊ ፋይዳ ካላቸው ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች፣ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ስርዓቶችና የጂኦ ስፓሻል መረጃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ሥራ ላይ ከመዋላቸውና ተያያዥነት ያላቸው ግዥዎች ከመፈጸማቸው በፊት፡-

   ሀ/ የፕሮጀክት ጥንስስ ወይም የግዥ ፍላጎት ሂደቱ የደህንነት መመዘኛ ማሟላቱን የማረጋገጥ፤

   ለ/ ለፕሮጀክቱ ግብአት የሚውሉ ምርቶችና አገልግሎቶች ወይም ሥርዓቶች የደህንነት መመዘኛዎችን አሟልተው መመረታቸውንና በአምራቾቹ ወይም በአገልግሎት ሰጪዎቹ የደህንነት ደረጃውን የጠበቀ የስጋት አመራር የሥራ ሂደት መኖሩን የማረጋገጥ፤

   ሐ/ ምርቱ፣ አገልግሎቱ ወይም ሥርአቱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት አስፈላጊ መመዘኛዎችን ማሟላቱን የማረጋገጥ፤

መ/ የትግበራና ኮንፌግሬሽን ሂደቱ በደህንነት መስፈርቱ መሰረት መከናወኑን የማረጋገጥ፣ እና

ሠ/ ቀጣይ የድህረ ትግበራ ሥርዓት ደህንነትና የስጋት አመራር መኖሩን የማረጋገጥ፣

ኃላፊነት አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ለማድረግ የሚመለከታቸው ተቋማት የፕሮጀክት ትግበራ እቅዳቸውንና ተያያዥ ግዥዎችን አስቀድመው ለኤጀንሲው የማሳወቅና የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

7. <u>ስለደህንነት ፍተሻና ግምገማ</u>

1. ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5(1) የተመለከቱትን ተግባራት የሚያከናውነው ሀገራዊ ደህንነትንና ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ፣ ሳይንስን፣ የፈጠራ እድሎችን፣ የቴክኖሎጂ እድገትን፣ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያበረታታ ሁኔታ እና የተደራጁ ላቦራቶሪዎችን በመጠቀም ይሆናል።

2. ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5(1) የተመለከቱትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችለው መሰረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂ፣ የስራ ሂደትና አስፈላጊ ሙያተኞች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

8. <u>ከሀገር ስለሚወጡና ወደ ሀገር ስለሚገቡ እቃዎች እና ቴክኖሎጂዎች ደህንነት</u>

1. ኤጀንሲው የኢንፎርሜሽንና ኮምፒዩተርን መሰረት ያደረገ ቁልፍ መሠረተ ልማት ደህንነትን ለማረጋገጥ ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ መግባትና ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው እና ከሀገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ቴክኖሎጂዎችን አስመልክቶ ስታንዳርድና መመዘኛ ያወጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትም ያስፈጽማል።

2. ዋና ዳይሬክተሩ ብሔራዊ ደህንነትን ሊጎዳ የሚችል ወይም በፍተሻና ሌሎች ተያያዥ ሂደቶች ምክንያት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም ተያያዥ እቃዎች ወይም ሰነዶች ሚስጥር ሊባክን ይችላል ብሎ ሲያምን ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ከሀገር የሚወጡና ወደ ሀገር የሚገቡ የኤጀንሲው እቃዎችና ተያያዥ ሰነዶች እንዳይፈተሹ ሊያደርግ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም የተሻሻሉ የኢንፎርሜሽንና ሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂዎች፣ የክሪፕቶግራፊክና ኤሌክትሮማግኔቲክ ቴክኖሎጂዎች ለሀገራዊ ደህንነት ካላቸው ፋይዳ አንጻር ወደ ውጭ እንዳይወጡ የሚከለክል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

9. **<u>የሳይበር ኦፕሬሽን</u>**

1. በሌሎች ሕጎች ለሌሎች አካላት የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ኦፕሬሽንን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል።
2. የሳይበር ኦፕሬሽን፡-
   ሀ/ የሳይበር መረጃንና የዲጂታል ፎረንሲክ ማስረጃን ለመስብሰብ፣
   ለ/ በአገር ሉዓላዊነት ላይ የሚቃጡ የሳይበርና የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ቴክኖሎጂ ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ወይም
   ሐ/ ብሔራዊ ደህንነትን ወይም የዜጎችን ደህንነት የሚጎዱ የሳይበር እንቅስቃሴዎችን ለመግታት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን፣
   በማናቸውም ጊዜ ሊካሄድ ይችላል።
3. የሳይበር ኦፕሬሽን፡-
   ሀ/ በፌዴራል መንግስት ትዕዛዝ ወይም በክልል መንግስታት ጥያቄ፤
   ለ/ በጠቅላይ አቃቤ ህግ ወይም በአቃቤ ህግ ተቋም የበላይ ሃላፊ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትእዛዝ፣ ወይም
   ሐ/ በኤጀንሲው በራሱ ተነሳሽነት፤
   ሊካሄድ ይችላል፤ ሆኖም ኤጀንሲው ለጠያቂው አካል አፕሬሽኑ የሚካሄድበትን የጊዜ ገደብ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች አስቀድሞ ያሳውቃል።
4. ኢጀንሲው በሳይበር ኦፕሬሽን ሂደት የሚገኙ መረጃዎች ከጠያቂው አካል ውጭ በሌላ አካል እጅ እንዳይገኙ በሚስጥራዊነት እንዲያዙ ይደረጋል።
5. ኤጀንሲው የሀገሪቱን የሳይበር ኦፕሬሽን ተግባራት የሚፈጽምበት እና የሚያስፈጽምበት ስርዓት ይቀርፃል።

10. **<u>ስለደጂታል ፎረንሲክ</u>**

በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 6(8) በተደነገገው መሠረት እና በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ መሰረት ከመርማሪ አካላት ጋር በመተባበር የዲጂታል ፎረንሲክ ምርመራ ያካሂዳል፤
2. የፍትህ አካላት በራሳቸው የዲጂታል ፎረንሲክ ምርመራ አቅም እንዲፈጥሩ እና እንዲያጎለብቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

11.<u>ስለመረጃ</u>

1. ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ 6 (14) ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 (3) መሰረት ከሚሰበስበው መረጃ መካከል ለወንጀል ምርመራ መነሻ የሚሆን መረጃ ካለው ለመርማሪ አካላት ሊሰጥ ወይም በፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ማስረጃ ካለና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በአቃቤ ጥያቄ ሲቀርብ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም የመረጃ ምንጮቹና መረጃዎቹ የተገኙባቸውን ዘዴዎች እንዲገልጽ አይገደድም።
2. ዋና ዳይሬክተሩ የመረጃ አሰባሰብ፣ ክምችትና ስርጭት እንዲሁም የመረጃ ኦፊሰሮች የሚመሩበት የአሰራር ስርዓት ይቀርፃል፤ የሙያ ስነ ምግባር መመሪያ ያወጣል።

12.<u>ስለየኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል</u>

ኤጀንሲው ቁልፍ ተቋማት ክብሔራዊ የኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ ማእከል ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ ልዩ ልዩ ጥቃቶች ሪፖርት ስለሚደረጉበት ዘዴና ስርዓት እንዲሁም ትስስር በመመሪያ ይወስናል።

13.<u>ስለስታንዳርድ</u>

1. ኤጀንሲው ኢንፎርሜሽንና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማት ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስታንዳርዶችን የማውጣትና አፈጸጸማቸውን የመከታተል ስልጣን ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ በተደነገገው መሰረት የሚወጡ የደህንነት ስታንዳርዶች አስገዳጅ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸውን በግልጽ የሚያሳይ ድንጋጌ ማካተት ይኖርባቸዋል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለፕሮጀክት አስተዳደር፣ ስለክፍያዎች እና ልዩ ግዢ</u>

14.<u>ስለፕሮጀክት አስተዳደር</u>

1. ኤጀንሲው የራሱ የፕሮጀክት የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ይኖረዋል።
2. ኤጀንሲው በሀገር ውስጥ በጨረታ ተወዳድሮ ምርት ወይም አገልግሎት አያቀርብም ወይም ፕሮጀክት አይወስድም።
3. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኤጀንሲው የሚያከናውንላቸውን ፕሮጀክቶች ወጭዎች በሙሉ መሸፈን አለባቸው፤ እንደአስፈላጊነቱም ሙሉውን ወጭ በቅድሚያ ሊከፍሉ ይችላሉ።
4. በሌላ ደንብ ወይም መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም ወይም በሌላ አኳኋን በአሰራር ተፈፃሚ የሚደረግ የአሠራር ሥርዓት ቢኖርም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በኤጀንሲው የሚሰሩላቸውን ፕሮጀክቶች ወጭዎች በሙሉ ወይም በከፊል በቅድሚያ ሊከፍሉ ይችላሉ።
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌን ተፈጻሚ ለማድረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[12] ኤጀንሲውን በመወከል በደብዳቤ ዋስትና ሊሰጥ ይችላል።
6. ኤጀንሲው የውል ማስክበሪያና የቅድመ ክፍያ ዋስትናዎችን አይጠየቅም።

15.**ስለተመጣጣኝ ክፍያ**

ኤጀንሲው፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 18(2) መሰረት የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን ያለምንም የአገልግሎት ክፍያ ለህብረተሰቡ በነፃ ያቀርባል፤
2. ለባለ በጀት መስሪያ ቤቶች ለሚሰራቸው ፕሮጀክቶችና ለሚሰጣቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ሙሉ ወጭውን የሚሸፍን ክፍያ ያስከፍላል፤
3. ለመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ለግል ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለሚያቀርበው ምርቶችና አገልግሎቶች ሙሉውን ወጪ የሚሸፍንና ከመደበኛ የገበያ ዋጋ አንጻር ዝቅ ያለ የትርፍ ህዳግን የሚያካትት ክፍያ ያስከፍላል፤
4. ለሌሎች ሀገራት ተቋማት የሚሰጡ ምርቶችና አገልግሎቶች ክፍያን በተመለከተ የመንግስትን የዲፕሎማሲ አቅጣጫና ሌሎች ዓላማዎችን ታሳቢ በማድረግ ይወስናል።

16.**ልዩ ግዢ**

[12] በ22/12(2008) አ.912 አንቀጽ 9(6) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

1. ኤጀንሲው ከኢንፎርሜሽንና ሳይበር ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ለደህንነት ስጋት ምንጭ ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ወይም ውስን አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዥ ሊፈጽም ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው፦
   ሀ/ የመረጃ ትንተናዎችና ሪፖርቶች እንዲሁም የደህንነት ሥልጠና አገልግሎቶች ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ይገዛል፤
   ለ/ የኢንፎርሜሽንና የሳይበር ደህንነት ተቋማት የአባልነት ክፍያ በቀጥታ ይፈጽማል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱት ግዥዎች የመንግስትን ጥቅም በሚያስጠብቅና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መንገድ መፈጸም የሚያስችል መመሪያ ያወጣል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17.ስለቅንጅትና ትብብር

ኤጀንሲው፡-

1. ከአገር ውስጥ ልዩ ልዩ የደህንነት፣ የሕግ አስከባሪና ሌሎች አጋር ተቋማት ጋር የሚያደርገው ትብብር ኤጀንሲው የተቋቋመበትን ዓላማ በሚያሳካ እና የጋራ ጥቅምን በሚያስከብር መልክ ይሆናል፤
2. ከአቻ የውጭ አገር መንግስት ተቋማት የደህንነት ተቋማት ወይም ማህበራት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅና ሉአላዊ የግንኙነት መርሆችን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል።

### 18.ስለማህበራዊ ኃላፊነትና ግዴታ

ኤጀንሲው፡-

1. በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለሚኖሩ የመልሶ ማልማትና ግንባታ ስራዎችና ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ አቅሙ በፈቀደለት መጠን ኃላፊነቱን ይወጣል፤

2. ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የህዝቡን የኢንፎርሜሽንና የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ያዳብራል፤ ፀረ ቫይረስና መሰል ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ያደርጋል፤
3. ለስራ የሚጠቀማቸው ጨረራ አመንጪ ቴክኖሎጂዎች በአካባቢና በሠራተኞች ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
4. ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ፣ በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እና ለሠራተኞቹ ደህንነት ሲባል የሚያስፈልጉ መኖሪያዎችን ወይም ካምፖችን በሁሉም ኦፕሬሽን ጣቢያዎች ሊገነባ ይችላል።

19.<u>ስለሠራተኞች ግዴታ</u>

1. በዚህ ደንብ ከአንቀጽ 4 እስከ 10 በተመለከተ ተግባራት የሚሳተፉ ሠራተኞች የአሰራር ስርዓትና አፈጻጸም እና የሙያ ሥነ-ምግባር መመሪያዎችን ተላልፈው የተገኙ እንደሆነ በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የዲሲፒሲን ቅጣት የወንጀልና ፍትሐ ብሔር ተጠያቂነትን አያስቀርም።

20.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም አግባብ ያለው አካል ይህንን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

21.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

22.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ኤጀንሲው ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪዎችን ሊያወጣ ይችላል።

23.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 12 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 401/2009**

**የሳይበር ሠራዊት ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትርች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 808/2006 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 16 እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 14 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሳይበር ሠራዊት ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትርች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 401/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "የአካዳሚክ ሰራተኛ" ማለት በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ ሰራተኛ ነው፤
   2. "የአስተዳደር ሰራተኛ" ማለት በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ ያልተሰማራ ለማስተማር ወይም ለምርምር ሠራተኛ ድጋፍ የሚሰጥ ሠራተኛ ነው፤
   3. "ኤጀንሲ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፤
   4. "ሳይበር" ማለት ባልተማከለ የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት፣ ኢንፎርሜሽንና ኤልክትሮ-ማግኔቲካዊ ስፔስ ትስስር በዓለም አማካኝነት በዓለም ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ባህልና አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እየፈጠረ የሚገኝ ዓለም አቀፋዊና ድንበርየለሽ መስተጋብራዊ ሥርዓት የፈጠረ ምህዳርና ኃይል ነው፤

5. “ሳይበር ኮማንዳንት” ማለት ወታደራዊ ሳይንስና ጥበብን ከሳይበር ምህዳር ባህሪያት ጋር በማጣመር የሳይበር ታለንት ልማት ፕሮግራሞችን መምራት የሚችል አመራር ነው፤
6. “ኢንፎርሜሽን” ፣ “ቁልፍ መሰረተ ልማት” ፣ “ክሪፕቶግራፊ” እና ልሎች አግባብ ያላቸው ቃላቶች የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 808/2006 አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ይኖራቸዋል፤
7. “የኢንፎርሜሽን ደህንነት” ማለት ኢንፎርሜሽን በሚሰበሰብበት፣ በሚተነተንበት፣ በሚከማችበት እና በሚሰራጭበት ወቅት ተአማኒነቱን፣ ሚስጢራዊነቱን እና ተደራሽነቱን ከሚያሳጡ ጥቃቶች መጠበቅ ነው፤
8. “አዋጅ” ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ነው፤
9. “ተሰጥኦ” ማለት የአዕምሮና የስሜት ብልህነቶችን ያጣመረ ላገራና ላያድግ የሚችል እምቅ ሰብአዊ አቅም ነው፤
10. በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም ድንጋጌ የሴትንም ያካትታል።

## 3. መቋቋም

1. የሳይበር ሠራዊት ልማት ኢንስቲቲዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲቲዩት” ተብል የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲቲዩቱ ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ይሆናል።
3. ኢንስቲቲዩቱ በዚህ ደንብና በአዋጁ ጠቅላላ መርሆዎች መሠረት ይተዳደራል።

## 4. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተለት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በሳይበር ምህዳሩ ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ደረጃውን የጠበቀ መደበኛ ትምህርት በመስጠት በሥነ-ምግባር የታነፀ፣ ብሔራዊ ጥቅምንና ፍላጎትን የሚያስከበር እንዲሁም ለአገሪቱ የሳይበር ጦርነት ምላሽ መስጠት የሚችል የሳይበር ሠራዊት ማልማት፤
2. አጫጭር የሳይበር ኢንደስትሪ አመራርና ሙያዊ ሥልጠና መስጠት፤
3. በሳይበር ኢንደስትሪ ዙሪያ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማረጋገጥ የሰው ሀብት ልማትን ማስፋፋትና በዘርፉ የእውቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤

4. በሳይበር ኢንደስትሪ ዘርፍ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ፤ በዘርፉ የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እና የማማከር አገልግሎት መስጠት።

5. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዳስ አበባ ይሆናል።

6. <u>የተቋሙ ስልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተለት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል: -

1. በሳይበር ዋርፌር ተሰጥኦ ልማት፣ በሳይበር ኢንተለጀንስ ተሰጥኦ ልማት፣ በሳይበር ቴክኒካል ትንተና ተሰጥኦ ልማት፣ በክሪፕቶግራፊና ባዮሜትሪክስ ተሰጥኦ ልማት፣ በኤልክትሮኒክ ዋርፌር ተሰጥኦ ልማት እና በልሎችም ተያያዥነት ባላቸው ፕሮግራሞች የተለያዩ የትምህርትና የምርምር ክፍልችን በማቋቋም የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን መቀየስና ማካሄድ፤
2. ትምህርታቸውን ላጠናቀቁ ተማሪዎች የምስክር ወረቀት፤ ዳግሪ እንዲሁም ልሎች የትምህርት ሜዳላያ ሽልማቶችንና ማዕረግ መስጠት፤
3. በሳይበር የሰው ሀብት ልማት ዙሪያ ለሀገር እድገት ቅድሚያ በሚሰጣቸው መስኮች ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤
4. በሳይበር ምህዳሩ የተለየ ተሰጥኦ ያላቸውን ግለሰቦች መመዘኛዎችን በማውጣት መለየትና ልዩ የትምህርት ፕሮግራም በመቅረጽ ማሰልጠን
5. በሳይበር የሰው ሀብት ልማት ዙሪያ ሴሚናሮችን፤ አውደ ጥናቶችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀትና ማካሄድ፤
6. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ካለ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋራ የሥራ ግንኙነት በመመስረት የእውቀት ሽግግር መፍጠር፤
7. በሳይበር የሰው ሀብት ልማት ዙሪያ የማማከር፤ የስልጠናና ልሎች አገልግሎቶች ለቁልፍ ተቋማት እና ለልሎች መስጠት፤
8. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤
9. ለሚሰጠው አገልገሎት በቦርዱ በሚወሰነው ተመን መሠረት በከፊል ወይም በሙለ የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፤
10. የኢንስቲትዩቱን ዓላማ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ልሎች ተዛምጅ ተግባራትን ማከናወን።

7. <u>የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. ሰኔት፤
3. ኮማንዳንት እና ዳኖች፤
4. የአስተዳደር ኮሚቴ፤ እና
5. አስፈላጊው የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞች

ይኖሩታል።

## ክፍል ሁለት

## ስለኢንስቲትዩቱ የፖሉሲና የሥራ አስፈፃሚ አካላት

### 8. ስለ ቦርዱ

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ፣ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን አባላት ይኖሩታል።
2. ኮማንዳንቱ ድምጽ የሌለው የቦርዱ ጸሐፊ ይሆናል።

### 9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

አዋጁ አንቀጽ 44 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኢንስትቲዩቱ በዓላማው መሰረት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ይከታተለል፤ ያረጋግጣል፤
2. የአስተዳደር ፖሊሲ ያመነጫል፤ በኤጀንሲው ቀርቦ ሲፀድቅም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
3. የኢንስትቲዩቱን የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ለኤጀንሲው ቀርቦ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
4. የትምህርት ጉዳዮችንና የሥልጠና ፕሮግራሞችን ይወስናል፤
5. የአንስቲትዩቱን ቢዝነስና የስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ለኤጀንሲው ቀርቦ ሲጸድቅ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
6. የተማሪዎችና የሠልጣኞች የአቀባበል ሁኔታን አስመልክቶ መስፈርት ያዘጋጃል፤ ለኤጀንሲው ቀርቦ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
7. የኢንስቲትዩቱን መተዳደሪያ መመሪያ ያዘጋጃል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

8. የኢንስቲትዩቱን አደረጃጀት ይወስናል፤ ኢንስትቲዩቱ የሚስፋፊበትን፣ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል፤
9. የኢንስቲትዩቱ ኮማንዳንት በኤጀንሲው እንዳሾም የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
10. የኢንስቲትዩቱን ዳኖች ይሾማል፤
11. በኢንስቲትዩቱ አካዳሚክ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን መመሪያ ከተመሳሳይ ተቋማት አሠራር ልምድ ጋር በማገናዘብ ያወጣል፤
12. የኢንስቲትዩቱን ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ ለኤጀንሲው ያቀርባል፤ ለመንግሥት ቀርቦ ሲቀጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
13. የኢንስቲትዩቱ መለያ ዓርማ ይወስናል፤
14. ኢንስትቲዩቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች ተመን ይወስናል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
15. የኢንስቲትዩቱ ወጪዎቹ በተያዘላቸው በጀት መሰረት መሆኑን ይከታተላል፤
16. ኢንስቲትዩቱ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር አቻ ተቋማት ጋራ የሚያደርጋቸውን የትብብር ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል፤
17. ኢንስቲትዩቱ ወይም ማንኛውም የኢንስቲትዩቱ አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚነሳን ቅሬታ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
18. የቦርዱን የውስጥ መተዳደርያ ደንብ ያፀድቃል፤
19. ኢንስቲትዩቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረደላልች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

10. <u>የቦርድ ስብሰባ</u>

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በየሦስት ወሩ ይካሄዳል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ቢያንስ ሁለት የቦርድ አባላት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ላካሄድ ይችላል።
2. በማንኛውም የቦርዱ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋለ፤ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**11.ስለሴኔት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉትን አባላት የያዘ ሴኔት ይኖረዋል: -

1. የኢንስቲትዩቱ ኮማንዳንት.........................ሰብሳቢ፤
2. የኢንስትቲዩቱ ዳኖች.............................. አባል፤
3. አጠቃላይ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ............ አባል፤
4. በኢንስቲትዩቱ ተማሪዎች የሚመረጥ አንድ የተማሪዎች ተወካይ.......... አባል፤
5. በኢንስቲትዩቱ ቋሚ መምህራን የሚመረጥ አንድ የመምህራን ተወካይ.... አባል፤
6. የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች.................አባል፤
7. ልሎች ቦርዱ የሚሰይማቸው አግባብነት ያላቸው ኃላፊዎች............ አባል፤
8. የኢንስትቲዩቱ ሬጅስትራር..................... ፀሐፊ

**12.የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር**

ሴኔቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል: -

1. የቦርደ ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
2. የኢንስትቲዩቱን ልዩ ልዩ የትምህርት ፕሮግሞችና ካላንደር መርምሮ ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፤
3. የተለያዩ ዳግሪዎችን፣ ሰርተፍኬትና ልዩ ልዩ ሽልማቶች ስለሚሰጥበት ሁኔታ በትምህርት

   ክፍሎች ተዘጋጅተው በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያሰጣል፤
4. የትምህርት ደረጃ አወሳሰንን፣ ምዘናን፣ የምረቃ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችንና የዳስፕላን መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥ ዘድና ሁኔታን ይወስናል፤
6. አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚከፈቱበትን ሁኔታ መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቦርዱ ያቀርባል፤
7. የአካዳሚክ ሠራተኞችን ዕድገት በተመለከተ በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ይወስናል፤

8. ወደሚቀጥለው የትምህርት እርከን የሚሸጋገሩ ተማሪዎችን ዝረዝር መርምሮ ይወስናል፤
9. ኢንስቲትዩቱ የሚሰበስባቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤
10. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

13.<u>የሴኔት ስብሰባዎች</u>

1. ሴኔቱ እንደ አስፈላጊነቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ያካሂዳል።
2. በማንኛውም የሴኔቱ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
3. የሴኔቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የሴኔቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ሴኔቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ላያወጣ ይችላል።

14.<u>ስለኮማንዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ኮማንዳንቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የኢንስትቲዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ኢንስትቲዩቱን ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮማንዳንቱ: -
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የኢንስቲትዩቱ የተለያዩየሥራ ክፍልች ተግባራቸውን በኢንስትቲዩቱ ዓላማና መሪ እሴቶች መሠረት በትክክል መወጣታቸውን ክትትል ያደርጋል፤
   ሐ) በኢንስቲትዩቱ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ሕጎች በአግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤
   መ) ኢንስቲትዩቱ በትምህርት፤ በሥልጠና፤ በሳይበር የሰው ኃይል ልማት በምርምር፤ በማማከርና በማህበረሰብ አገልግሎቶች የኤጀንሲውን ተልዕኮ በሚያሳኩና የማህበረሰቡን ፍላጎት በሚያረኩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) በኢንሰትቲዩቱ የሚሰጡ የሳይበር የሰው ኃይል ልማት ትምህርቶች ደረጃቸውን የጠበቁ ስለመሆናቸው ይቆጣጠራል፤ ክትትል ያደርጋል፤

ረ) የሳይበር የሰው ኃይል ልማት ሥራዎች እንዳዳብሩ ያደርጋል፤

ሰ) የኢንስትቲዩቱ የተማሪዎች መቀበያ መስፈርቶች እንዳዘጋጁ ያደርጋል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

ሸ) ኢንስትቲዩቱ በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀት እና አሰራሩ ለተልዕኮው የሚመጥን ብቃት ያለው የውስጥ አመራርና አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖረው ያደርጋል፤

ቀ) የኢንስትቲዩቱን እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤

በ) ቦርዱ፣ የኢንስትቲዩቱ ማህበረሰብ እና ኤጀንሲው ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ተ) የኢንስትቲዩቱን የገቢ ማመንጫ ተግባራትን፤ የኢንስትቲዩቱን የቢዝነስ ክፍሎችና የልማት ተግባራትን እቅድ ያዘጋጃል፤ በቦርዱ ሲፈቀድ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

ቸ) ቦርዱ በሚጠይቅበት ወቅት እና ቢያንስ በየሶስት ወሩ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤

ኀ) የኢንስቲትዩቱን ዲኖች ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል፤

ነ) ኢንስትቲዩቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋራ ግንኙነት ያደርጋል፤

3. ኮማንዳንቱ፣ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለዲኖች ወይም ለትምህርት ክፍል ኃላፊዎች በውክልና መስጠት ይችላል።

15.<u>ስለትምህርት ዲን ሥልጣንና ተግባር</u>

የትምህርት ዲን ተጠሪነቱ ለኮማንዳንቱ ሲሆን የሚከተለት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. ትምህርት ዩኒቶችን፤ ላይብራሪ፤ ሬጂስትራርና ላብራቶሪዎችን ይመራል፤
2. የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችን ይሰበስባል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤
3. የኢንስትቲዩቱ ካሪኩለም በአግባቡ እየተተገበረ መሆኑን ይገመግማል፤

4. የመማር ማስተማር ሂደቱን ይከታተላል፤ አዳዲስ ፕሮግራሞች እንዲጀመሩ አስፈላጊውን ጥናት ያደረጋል፤ አስፈላጊ ሲሆንም ለኮማንዳንቱ ጥያቄውን ያቀርባል፤
5. ከኮማንዳንቱ ጋር በመመካከር የተመራቂ ተማሪዎችን ዝርዝር ለሴኔቱ ያቀርባል፤
6. የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥር በበላይነት ይመራል፤ የቅጥር ውላቸውን ይፈርማል፤
7. በትምህርት ክፍሎች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲዳብር የሚያችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
8. ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የትምህርት ግንኙነቶችንና ትብብሮችን ያፈላልጋል፤ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል
9. ከአካደሚክ ሠራተኞች ለዕድገትና ለትምህርት ሹመት ብቁ የሆኑ እጩዎችን በመመልመል ለሴኔት ያቀርባል፤
10. በትምህርት ጉዳዮች ኮማንዳንቱን ያማክራል፤ ይወክላል፤
11. ኮማንዳንቱ በሥራው ላይ መገኘት በማይችልበት ወቅት እርሱን ተክቶት ይሰራል፤
12. ሌሎች በኮማንዳንቱና በሴኔት የተሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

16. <u>ስለጥናትና ምርምር ዲን ሥልጣንና ተግባር</u>

የጥናትና ምርምር ዲን ተጠሪነቱ ለኮማንዳንቱ ሲሆን የሚከተለት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኢንስቲትዩቱን የሳይበር የሰው ኃይል ልማት ምርምር እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፤ ይመራል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
2. በኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ላይ ያተኮረ በየጊዜው የሚታተም የጥናት ጆርናልን በበላይነት ይመራል፤
3. ኮማንዳንቱንና ሴኔቱን በምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ያማክራል፤
4. በኢንስቲትዩቱ የሳይበር የሰው ኃይል ልማት ጥናትና ምርምር እንዲስፋፋ አስፈላጊ ግብአቶች እንዲሟላ ያደርጋል፤
5. የተለያዩ የሳይበር የሰው ኃይል የምርምር ማዕከላትንና ላቦራቶሪዎችን ያደራጃል፤ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል

6. ሌሎች በኮማንዳንቱና በሴኔቱ የተሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

17.<u>ስለአስተዳደር ዲን ሥልጣንና ተግባር</u>

የአስተዳደር ዲን ተጠሪነቱ ለሳይበር ኮማንዳንቱ ሲሆን፣ የሚከተለት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ኢንስትቲዩቱ ተልእኮውን መፈፀም እንዲችል አስፈላጊውን የአስተዳደርና የድጋፍ አገልግሎቶች የሚሰጡ ክፍልችን ይመራል፤
2. የኢንስትቲዩቱን ሀብትና ንብረት ያስተዳድራል፤
3. የኢንስትቲዩቱን የዕቅድ፣ የዲዛይን፣ የግንባታና የጥገና አገልግልቶች ይመራል፤
4. የኢንስትቲዩቱን ሰላማዊና ምቹ የመማሪያና የምርምር ቦታ እንዲሆን አስፈላጊ ግብአቶች እንዲሟለ ያደርጋል፤
5. ለኢንስትቲዩቱ የተመደበለትን ፋይናንስ ወጪና ገቢ ያስተዳድራል፤
6. የኢንስትቲዩቱ ደንቦችና አጠቃላይ ፖሊሲዎች በኢንስትቲዩቱ ማህበረሰብ እንዲታወቁና እንዲተገበሩ ያደርጋል፤
7. እርሱን የሚመለከቱ እና ኢንስቲተቲዩቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋራ የገባቸው ስምምነቶችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤
8. በሚያስተዳድራቸው ጉዳዮች በየጊዜው ለኮማንዳንቱ ሪፖርት ያቀርባል፤
9. የኢንስቲቱዩቱን የአስተዳደር ሰራተኞች ቅጥር በበላይነት ይመራል፣ የቅጥር ውል ይፈርማል፤ አስፈላጊውን የአስተዳደር ሠራተኛ ኃይል ያሟላል፤
10. ሌሎች በሳይበር ኮማንዳንቱና በሴኔቱ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

18.<u>ስለአስተዳደር ኮሚቴ</u>

1. ኮማንዳንቱ ላልች አግባብነት ያላቸውን የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች በአባልነት ለማካተት ያለው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የአስተዳደር ኮሚቴ የሚከተለት አባላት ይኖሩታል፦
   ሀ) ኮማንዳንት..................................ሰብሳቢ
   ለ) ዲኖች.............................................. አባላት
   ሐ) የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ.........................አባል
   መ) ኮማንዳንቱ የሚመድበው የሥራ ኃላፊ...ጸሐፊ
2. የአስተዳደር ኮሚቴው ተጠሪነት ለኮማንዳንቱ ይሆናል።

19.<u>የአስተዳደር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

የአስተዳደር ኮሚቴው፡-

1. በስትራቴጂክ ጉዳዮች እና ሌሎች በጋራ መታየት አለባቸው ተብለው በሚታመኑ ጉዳዮች ላይ ኮማንዳንቱን ያማክራል፤
2. የኢንስትቲዩቱን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች የመከታተያ የማስተባበሪያና የመገምገሚ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፤
3. ኢንስቲትዩቱ በአወቃቀር፤ በሰው ኃይልና በአሰራር ብቃቱን እያረጋገጠ እንዲሄድ ቀጣይ ጥረት ያደርጋል።

20.<u>የአስተዳደር ኮሚቴ ስብሳባ</u>

1. የአስተዳደር ኮሚቴው ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. በማንኛውም የአስተዳደር ኮሚቴ ስብሰባ ሊይ ከአባሊቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
3. የአስተዳደር ኮሚቴ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የኮሚቴው ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የአስተዲደር ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ- ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

21.<u>የትምህርት ክፍል ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የትምህርት ክፍል ኃላፊ ተጠሪነቱ ለየትምህርት ዲኑ ሆኖ የሚከተለት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በትምህርት ክፍለ የሚሰጡ ትምህርቶችና ምርምሮች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፤
2. በትምህርት ክፍለ አዲዱስ ፕሮግራሞች እንዲጀመሩ አስፈሊጊው ጥናት እንዱካሄድ የደርጋል፤ አስፈሊጊ ሲሆንም ለትምህርት ዲኑ ጥያቄውን ያቀርባል፤
3. የትምህርት ክፍለን የምዘና ደረጃ ይገመግማል፤
4. ትምህርት ክፍለ የሚያስፈልገውን የመምህራንና ሌሎች መርጃ ቁሳቁሶች ዓይነትና ብዛት ይገመግማል፤ አስፈሊጊ ሲሆኑም የመምህራን ቅጥር እንዲካሄድ ጥያቄ ያቀርባል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
5. በትምህርት ክፍለ ያለ መምህራን የዕድገት ጥያቄያቸውን ይመረምራል፤ አስፈላጊ ሲሆንም ለትምህርት ዲኑ ጥያቄውን ያቀርባል፤

6. የትምህርት ክፍሉ ሠራተኞችን የሥራ ብቃት ይመዝናል፣
7. በትምህርት ክፍሉ የሚመደቡ ተማሪዎች አስፈሊጊው የመማሪያ ቁሳቁሶችና ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው ያደርጋል፣
8. በየሴሚስተሩ የሚሰጡ ኮርሶችን ለትምህርት ዲኑ ያሳውቃል፣
9. የትምህርት ክፍለን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም በስራ ሊይ መዋለን ይከታተላል፣ አፈጻጸሙን በሚመለከት ለትምህርተ ዲኑ ሪፖርት ያቀርባል፣
10. የትምህርት ክፍሉን ዓመታዊ እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ለትምህርትዲኑ ስለአፈፃፀሙ ሪፖርት ያቀርባል፣
11. ሌሎች በትምህርት ዲኑ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 22. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተለት መንጮች የተውጣጣ ይሆናል፣

1. ከፌዳራል መንግስት ከሚመደብለት በጀት፣
2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ከሰበሰበው የውስጥ ገቢ የሚፈቀድ ገንዘብ።

### 23. የሂሳብ መዛግብት

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራለ።

### 24. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራሊዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 363/2008

## ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የተቀናጀ፣ በተጠያቂነት ላይ የተመሠረተና ያልተማከለ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በየደረጃው ከአደጋ በፊት፣ በአደጋ ጊዜና ከአደጋ በኋላ መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በየደረጃው በተሟላ ሁኔታ እንዲወሰዱ ማድረግ በማስፈለጉ፤ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራርን ተግባራዊ በማድረግ በአደጋ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ለማሳተፍ በሕግ ማዕቀፍ መደገፍ በማስፈለጉ፤

በዋናነት ድርቅ ተኮርና አደጋ ከተከሰተ በኋላ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ዕርዳታ በማቅረብ ሕይወት ማዳን ሥራ ላይ ያተኩር የነበረውን የአደጋ ሥራ አመራር አሠራር ወደ ተሟላ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር አሠራር ማሸጋገር በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀፅ 5 እና 39 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፦

   1. "አደጋ" ማለት የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስተጓጉል፣ በሰው፣ በንብረት በኢኮኖሚ ወይም በአካባቢ ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳትና ተጽዕኖ የሚያስከትልና በአደጋው የተጠቃው ህብረተሰብ የራሱን አቅምና ጥሪት ተጠቅሞ ሊቋቋመው የማይችል ክስተት ነው፤

2. “የአደጋ ሥጋት” ማለት በተወሰነ ህብረተሰብ ወይም ህዝብ ሕይወት፣ አካባቢ፣ ጤና፣ መሠረታዊ የኑሮ ገቢ ምንጮች፣ ንብረትና መሠረታዊ አገልግሎቶች ላይ ወደፊት ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ስጋት ነው፤
3. “የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር” ማለት የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ እንዲቻል ስርዓት ባለው መልኩ የአስተዳደር መመሪያዎችን፣ የተቋምችን፣ የአሠራር ክህሎቶችን እና አቅሞችን የመጠቀም ሂደት ነው፤
4. “ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት” ማለት በአደጋ መንስኤ እና በተያያዥ አደጋዎች ሊጠቁ የሚችሉ ግለሰቦች፣ ሕብረተሰብና ድርጅቶች እንዲዘጋጁ የማድረግና ተገቢውን እርምጃ በወቅቱ በመውሰድ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋትና ጉዳት ለመቀነስ ወቅታዊ ማስጠንቀቂያን ለማስተላለፍ የሚያስችል የተደራጀ አቅም ነው፤
5. “የአደጋ መንስኤ” ማለት ማንኛውም ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ የሆነ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል፣ የሰው ህይወት ሊያጠፋ፣ አካል ሊጎዳና ሊያቆስል ወይም ጤና ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ወይም በንብረት፣ በመሠረታዊ የኑሮ ገቢ ምንጮችና አገልግሎቶች ላይ ጉዳት ሊያደርስ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት መስተጓጎል ሊያስከትል ወይም አካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል አደገኛ ክስተት፣ ቁስ-አካል፣ የሰው እንቅስቃሴ ወይም ሁኔታ ነው፤
6. “ፕሮፋይል” ማለት በአደጋ ተጋላጭነትና አደጋ የመቋቋም አቅም ላይ ትንተና በማድረግ የአደጋ ስጋት ሁኔታንና ክብደትን ለማወቅ የሚካሄድ የአደጋ ሥጋት አመላካች ጥናት ውጤት ነው፤
7. “መሪ ሴክተር መሥሪያ ቤት” ማለት በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ላይ መሪ ተብለው የተሰየሙ የፌደራልና የክልል አስፈጻሚ አካላትን ያካትታል፤
8. “የአደጋ ሥጋትን መቀነስ” ማለት ለአደጋ መንስኤዎች ያለውን ተጋላጭነት መቀነስን፣ የህበረተሰቡንና የንብረትን ለአደጋ ተጋላጭነት ማቃለልን፣ መሬትና አካባቢን በአግባቡ ማስተዳደርንና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ክስተቶችን ለመቀነስ የዝግጁነት አቅም ማጠናከርን ጨምሮ የአደጋ ሥረ-መንስዔዎችን ለመቆጣጠር ጥናት መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት ሥርዓት ባለው መልኩ በማከናወን የአደጋ ክስተት ስጋትን የመቀነስ ጽንሰ ሃሳብና ተግባር ነው፤

9. “የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል” ማለት የአስቸኳይ ጊዜ የአደጋ ምላሽ ሥራን የሚመለከታቸውን መሥሪያ ቤቶች በአንድ ላይ በማሰባሰብ በጋራ የምላሽ ሥራ የሚመራበት ሥፍራ ነው፤
10. “አደጋን ማሳወቅ” ማለት አደጋ በደረሰበት አካባቢ የሚገኝ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል የአደጋው መጠን በአካባቢው ያለው አቅም አደጋውን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመቋቋም የማያስችል በመሆኑ የሌሎች ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ሲወስን በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት በይፋ ማሳወቅ ነው፤
11. “የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ” ማለት በአደጋ ጊዜ የተጎጂውን ህዝብ ህይወት ለማዳን፣ የኑሮው መሠረት የሆኑ የገቢ ምንጮችን ለመጠበቅና ቀጣይነት ባለው መልኩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች ማቅረብና ማከፋፈል ነው፤
12. “መልሶ ማቋቋም” ማለት ጉዳት የደረሰበት አካባቢ፣ ሀብረተሰብና የኢኮኖሚ ዘርፎችን ከጉዳቱ መታደግና ወደ መደበኛ ኑሯቸውና ተግባራቸው እንዲመለሱና ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን መቋቋም የሚያስችላቸው አቅም እንዲገነቡ ማድረግ ነው፤
13. “የአደጋ ምላሽ ፈንድ” ማለት አደጋ በተከሰተበት ወቅት ለአደጋ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል በዝግጁነት የሚያዝ ጥሬ ገንዘብ ነው፤
14. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47(1) ተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
15. “ሰው” ማለት በተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
16. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

3. **መቋቋም**

1. ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ “ኮሚሽን” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ይሆናል።

4. **ዓላማ**

የኮሚሽኑ ዓላማ፦

1. ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ በተሟላ መልኩ እንዲተገበርና ዓላማዎቹ እንዲሳኩ ለማስቻል አግባብ ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፣ እና
2. በመሪ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የማስተባበር ክትትል ማድረግና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ይሆናል።

5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረውይችላል።

6. **የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችፓ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች፣ በግል መሥሪያ ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በሥርዓተ ትምህርት መካተቱን ያረጋግጣል ከዚህ ጋር በተያያዘም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያደርጋል፤
2. በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ላይ መሪ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
3. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የአደጋ ሥጋት ስራ አመራር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የትግበራ ዕቅዶችን አሰባስቦ ያደራጃል፤ አፈፃፀሙን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ለአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት ስለሥራ አፈፃፀሙ ቢያንስ በበጀት ዓመቱ ሁለት ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፤
4. የአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ይገመግማል፤
5. ማንኛውንም መሪ ሴክተር መሥሪያ ቤትን የማይመለከት ወይም ከመሪ ሴክተር መሥሪያ ቤት አቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ሥራውን ይሰራል፣ይመራል፣ ያስተባብራል፤

6. ለአደጋ ምላሽ ሥራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ክምችት ይይዛል፣ያስተዳድራል፤
7. የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራተጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል ያሰራጫል፤
8. ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ሥጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፤
9. የአደጋ ሥጋት ፕሮፋይሉን መሠረት በማድረግ የተሟላ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት በየደረጃው ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የተዘረጋው ሥርዓት ተደራሽ፣ ለአደጋ ምላሽ ሰጪና ዝግጁ እንዲሁም ለድንገተኛ ደራሽ አደጋዎች የታቀዱ ዕቅዶች ተግባራዊ መሆን መቻላቸውን ለማረጋገጥ በየደረጃው በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የማስተካከያ እርምጃምችንም ይወስዳል፤
10. በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ሥጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን ይመራል፤ያስተባብራል፤
11. የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ሥራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤ እንዳስፈላጊነቱም ተመሳሳይ ማዕከል በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ያደርጋል፤
12. የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋሥጋት ሥራ አመራር ሥራ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤ በብሔራዊ ደረጃ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንዳስፈላጊነቱ የክልል መስተዳድሮች ተመሳሳይ የመረጃ ማዕክል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል፤
13. አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት ሲወስን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሃገር ሀብት ያሰባስባል፣

14. የተገኘውን ሀብት በራሱና በሌሎች በሚመለከታቸው በፌደራልና ክልል መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ የሴክተር መሥሪያ ቤቶች አማካኝነት ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ሥራ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
15. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት በፍላጎት በተደራጁና በውጤት ላይ የተመሠረተ የአደጋ ሥጋት ሥራዎችን በሚሰሩና በበጐ ፈቃደኞች የሚታገዝበትን አሠራር ይዘረጋል፤ በተሟላ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
16. አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች መሠረት ለብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ አመች ሁኔታን ለመፍጠር አግባብነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የመንግስትና የግል መሥሪያ ቤቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፣ ይተባበራል፤
17. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፤
18. የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮችን ያከናውናል።

7. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፦

1. የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>የምክር ቤት አባላት</u>

1. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ መሪ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎችን የሚያካትት በመንግስት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኮሚሽኑ ኮሚሽነር የምክር ቤቱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል።

9. <u>የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራትይኖሩታል፦

1. ለብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ፖሊሲውና ስትራቴጂው እንዲከለስ ያደርጋል፤
2. ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን በአግባቡ ለመተግበር በየደረጃው መሪ ተብለው በተሰየሙ የሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጭምር አግባብነት ያለው ሕግ፣መመሪያ፣ ስትራተጂክ ፕሮግራም፣ ኢንቨስትመንት ማዕቀፍና ዕቅድ እንዲሁም በቂ የማስፈፀም አቅምና በጀት መኖሩንና አግባብ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤
3. በፖሊሲውና ስትራቴጂው መሠረት ያልተማከለ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋቱንና በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ጊዜ ምላሽ በየደረጃው ለመስጠት የዝግጁነት አቅም መገንባቱን ያረጋግጣል፤
4. በፖሊሲውና ስትራቴጂው መሠረት የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር በልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ውስጥ መካተቱን እንዲሁም ከአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ መቋቋምና ከማህበራዊ ጥበቃ ሥራዎች ጋር በተናበበና በተቀናጀ መልኩ መሰራቱን ያረጋግጣል፤
5. አደጋ ስለመከሰቱ በይፋ ሕዝብ እንዲያውቅ ያደርጋል፤
6. የአደጋ ክስተት በይፋ እንደተገለፀም የምላሽ ሥራውን በበላይነት ይመራል፤
7. ለምላሽ ሥራ ተጨማሪ ሀብት ከመንግስት ግምጃ-ቤት እንዲመደብ ያደርጋል፤ እንዳስፈላጊነቱም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር እንዲሰበሰብ ለኮሚሽኑ ትዕዛዝ ይሰጣል፤
8. የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ዕርዳታ አቅርቦት ድጋፍ ከልማት ፕሮግራሞች ጋር በተገናኘና ለዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ በሚያበረክት መንገድ መከናወኑንና በማንኛውም ሁኔታ ለተረጂነት መንፈስ መፈጠር ወይም መስፋፋት አመች ሁኔታን የማይፈጥር መሆኑን ያረጋግጣል፤
9. የአደጋ ምላሽ ፈንድ፣ ምግብና ምግብ-ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ እንዲሁም በተጨማሪ በመንግስት የሚመደብና በዕርዳታ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የሚሰበሰብ ሀብት ለአደጋምላሽ ሥራ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

10. ሌሎች የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ዓላማን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔና መመሪያ ይሰጣል።

10. <u>የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፦

ሀ/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ (6) የተመለከተውን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ ኮሚሽኑን ያደራጃል፣ የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኮሚሽኑን የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ/ የኮሚሽኑን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ በማኔጅሜንት ኮሚቴ ምክክር ከተደረገ በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

3. የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11. <u>የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነሮች የሚከተሉትሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፦

1. በኮሚሽኑ ኮሚሽነር ተለይተው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናሉ፤
2. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ በኮሚሽነሩ ውክልና የተሰጠው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል።

12. <u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፦

1. በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤ እና
2. በመንግሥት ሲወሰን ከዕርዳታና ከሌሎች ምንጮች ከሚሰበሰቡ ገቢዎች፤

13.<u>ስለሂሣብ መዛግብት አያያዝ</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብመ ዛግብትን ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ሰነዶች እንዲሁም ኮሚሽኑ የሚያስተዳድረው የአደጋ ምላሽ ፈንድ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት በየዓመቱ በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራል።

14.<u>ስለግዥና ንብረት አስተዳደር</u>

1. ኮሚሽኑ ለአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ምላሽ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በመንግስት የግዥና ንብረት ኮሚሽን ሕግ መሠረት በራሱ ግዥ ይፈጽማል።
2. ኮሚሽኑ ከውጭ በግዥ ወይም በዕርዳታ መልክ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ሥራ የሚውሉ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ምግብ-ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 47 እስከ 49 በተመለከተው መሠረት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15.<u>ተፈፃነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

16.<u>መብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር 212/1992 ተቋቁሞ የነበረው የብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮሚሽኑ ተላልፏል።

17.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ ከኅዳር 15 ቀን 2008ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 4 ቀን 2008 ዓ. ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 347/2007**

**የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 347/2007 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤
2. "ምክር ቤት" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የሚቋቋም የኢንስቲትዩቱ አማካሪ ምክር ቤት ነው።

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።
3. ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣቸው አጠቃላይ መመሪያዎች መሠረት ይተዳደራል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ መንግሥትን በማስፈቀድ ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል።

5. **የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አኳያ በአፍሪካ ቀንድ፣ በአፍሪካና በሌሎች የዓለም ክፍሎች በሚገኙ ሀገራት መካከል ዘላቂ ሰላምና ደህንነት

ለማስፈን የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ተግባራትን በማከናወን የልህቀት ማዕከል ሆኖ የማገልገል፤

2. የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነትና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የምርምር ሥራዎችን፣ ጥናቶችን፣ ትንተናዎችን፣ ሴሚናሮች፣ ዐውደ-ጥናት፣ የውይይት እና የገለጻ መድረኮች በማከናወን አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ምክረ-ሃሳብ የማቅረብ፤
3. የምርምር፣ ጥናትና ትንተና ሥራ ውጤቶች እንዲሁም የጉባኤ፣ ሴሚናር፣ ዐውደ-ጥናት፣ የውይይት እና የገለጻ መድረኮች ዘገባዎችን በሕትመትና በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተደራሽ የማድረግ።

6. <u>**የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር**</u>

ኢንስቲትዩቱ በአንቀጽ 5 የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ዓበይት የሆኑ አገራዊ፣ ክፍለ-ዓለማዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተንና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፡
2. የውጭ ግንኙነትና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም በአፈጻጸም፣ በአጠቃላይ ዲፕሎማሲ እና ዲያስፖራ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ አማራጭ የአፈጻጸም ሥልቶች ላይ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፤ እንዲሁም የግንዛቤ ማጎልበቻ ተግባራትን ያካሂዳል፡
3. በውጭ ግንኙነት ዙሪያ ስትራቴጂካዊ በሆኑ በመልካም አጋጣሚዎችና በተግዳሮቶች ላይ ጥናት፣ ግምገማና ትንተና በማካሄድ የማማከር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
4. የዓለም አቀፍ ሰነዶች እና የሌሎች መሰል ሰነዶች መረጃ ቋት በማደራጀት ያገለግላል፤
5. የውጭ ግንኙነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች አጫጭር ሥልጠናዎች፣ ሴሚናሮች፣ ዐውደ-ጥናቶች፣ ሲምፖዚየሞች፣ ጉባዔዎች እና ሌሎች የዕውቀት የልምድ ልውውጥና የክርክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤
6. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ዓለም አቀፍና ሀገር-በቀል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር የትብብር ፡ግንኙነት ይመሰርታል፣ የጋራ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

7. የጥናት እና የምርምር ውጤቶችን ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤
8. የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
9. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. የአማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈሳጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራኞች ይኖሩታል።

8. <u>የምክር ቤቱ አወቃቀርና የስራ ዘመን</u>

1. አማካሪ ምክር ቤቱ በሚኒስቴሩ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ በመንግሥት ይወሰናል።
2. የምክር ቤቱ አባላት ተቋማዊ አግባብነትን መሠረት በማድረግ ከመንግሥታዊ አካላት እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚመረጡ ይሆናል።
3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር በምክር ቤቱ ስብሰባ ያለ ድምጽ በፀሐፊነት ይሳተፋል።
4. የምክር ቤቱ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ሊራዘም የሚችል ሲሆን ቀጣይነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመተካካት አሰራር ይዘረጋል።

9. <u>የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኢንስቲትዩቱን ያማክራል፤
2. የኢንስቲትዩቱን የጥናት፣ የምርምር እና የሥልጠና መርሀ-ግብሮች መርምሮ ምክር ይሰጣል፤
3. የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ ዕቅድን እና በጀት መርምሮ ምክር ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩቱን የውስጥ ረቂቅ ደንቦች በሚኒስቴሩ ከመጽደቃቸው በፊት መርምሮ ምክር ይሰጣል፤

5. በዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ መክሮ አስተያየት ይሰጣል፤
6. የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል።

10. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

1. ምክር ቤቱ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሲሰበሰብ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ምክረ-ሀሳቦች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ምክረ-ሀሳብ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣን እና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስትሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኢንስቲትዩቱን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ መርሀ-ግብሮች አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ የምክር ቤቱን ምክረ-ሀሳብ አካቶ በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ በማቅረብ ምክረ-ሀሳብ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤ ለመንግሥት ቀርቦ ሲጸድቅ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት የሥራ መርሀ-ግብርና በጀት መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ረ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ አስተያየት ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣን እና ተግባራቱ በከፊል ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ወይም ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.**<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣን እና ተግባራት</u>**

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

ሀ/ የኢንስቲትዩቱ ሥልጣን እና ተግብራት አፈፃፀም በሚመለከት ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

ለ/ በተመደቡበት የሥራ መስኮች የሚከናወኑ ተግባራትንና ፕሮጀክቶችን ሥራ ይቆጣጠራሉ፤

ሐ/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን አፈጻጸም ይከታተላሉ፤ ያስፈጽማሉ፤

መ/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ።

2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር የኢንስቲትዩቱን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ በተለያየ ምክንያት ውክልና ካልሰጠ፣ ሚኒስቴሩ የሚወክለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር የኢንስቲትዩቱን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል።

13.**<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል።

14.**<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

15. **የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ የሠላምና የልማት ዓለም አቀፍ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 5/1988 በዚህ ደንብ ተሽሯል።

16. **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 5/1988 ተቋቁሞ የኢትዮጵያ የሰላምና የልማት ዓለም አቀፍ ኢንስቲትዩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

17. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 21 ቀን 2008ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

ሐ/ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 409/2009

## የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 39 እንዲሁም በውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 50(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎትማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 409/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 ነው፤
   2. በአዋጁ የተሰጠ ትርጓሜ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

3. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት ተቋም ሆኖ በዚህነ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

   የኢንስቲትዩቱ ዓላማ፡-

   1. በውጭ ግንኙነት አገልግሎት የሙያ ብቃት እና ክህሎት ያለው፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በላቀ ሁኔታ ተወዳዳሪ የሆነ፣ በየደረጃው የተቀመጠውን

የሙያ ክህሎት ያሟላ፣ አገራዊ ተልዕኮውን በብቃት መወጣት የሚችል የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ማፍራት፣ እና

2. የሚኒስቴሩን የዲፕሎማሲያዊ አቅም በማጠናከር አገራችን በውጭ ግንኙነት ያላትን ተደማጭነት በአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ደረጃ ማጎልበት፣ ይሆናል።

6. <u>**የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞችን የዲፕሎማሲ ሙያ ክህሎት ለማዳበር የሚያስችል ሥርዓተ-ትምህርት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር ማዘጋጀት፤
2. የሥልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ለአዳዲስ ዲፕሎማቶች የዲፕሎማሲ ክህሎት ሥልጠና መስጠት፤
3. ስልጠናቸውን በአጥጋቢ ውጤት ላጠናቀቁ አዳዲስ ዲፕሎማቶች ድህረ-ምረቃ ዲፕሎማ ይሰጣል።
4. ትምህርታዊ ውይይት፣ ሴሚናሮች እና ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፤
5. ከአንድ የሥራ ደረጃ ወደ ሌላ የሥራ ደረጃ ለሚያድጉ ሠራተኞች የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
6. የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች በያዙት ደረጃ የሥራ አፈፃፀማቸውን ለማዳበር የሚረዳ ተጨማሪ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፤
7. ዝቅተኛ የሥራ አፈጻጸም በማግኘታቸው ምክንያት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ቋሚ ሠራተኞች ሥልጠና መስጠት፤
8. የውጭ አገር ቋንቋ ክህሎት ማሻሻያ ሥልጠናዎችን መስጠት፤
9. የሚኒስቴሩ የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞችን ሙያዊ ብቃት፣ የውጭ ቋንቋ እና የመረጃ ቴክኖሎጂ ዕውቀት ለማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ የሆነ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ማዘጋጀት፣ መፈተን፤ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፤
10. የመስሪያ ቤቱን የሰው ሀይል ልማት መሰረት ያደረገ የሥልጠና ፍላጎቶች በጥናት መለየት፤

11. በዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት እውቀትና ልምድ ያላቸው ምሁራን፣ ጡረታ የወጡ ወይም በሥራ ላይ ያሉ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች መካከል ለማሰልጠን ብቃት ያላቸውን በመለየት ሥልጠና የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
12. ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ዓለም አቀፍና ሀገር-በቀል ተቋማት ጋር የልምድና የሰው ኃይል ልውውጥ ማድረግ፣ ግንኙነቶችን መመስረትና በጋራ ሥልጠናዎችን መስጠት፤
13. የንብረት ባለቤት መሆን፤ ውል መዋዋል፤ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤
14. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማናወን።

7. **የኢንስቲትዩቱ አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግሥት የሚሰየሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. **የቦርዱ የአባላት**

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን እና ምክትል ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚሰየሙ እና ቁጥራቸው እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰኑ አባላት ይኖሩታል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰየሙ የቦርዱ አባላት ያላቸው የትምህርት ዝግጅት፣ ዕውቀት፣ ለኢንስቲትዩቱ ተግባርና ዓላማዎች ያላቸው አግባብነት እና ለአገራችን የውጭ ግንኙነት መሻሻል ሊያበረክቱት የሚችሉትን አስተዋጽኦ መሠረት ያደረገ ይሆናል።
3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

9. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኢንስቲትዩቱ በሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ላይ ኢንስቲትዩቱን ያማክራል፤
2. ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች በማቀድና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ ረገድ ምክር ይሰጣል፤

3. ከዋና ዳይሬክተር በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮችላይ በመምከር የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባል።

10.**<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>**

1. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን በየሦስት ወሩ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን እንደአስፈላጊነቱ ያደርጋል።
2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

11.**<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የኢንስቲትዩቱን ሰራተኞች በፌደራልሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
   ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዕቅድ አዘጋጅቶ ከቦርዱ አስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ከቦርዱ አስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲጸድቅ ሥራ ላይ ያውላል፤
   ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤
   ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብሪፖርቶች በማዘጋጀት ከቦርዱ አስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. **<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከመንግስት የሚመደብ ይሆናል።

13. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖሩታል፤
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

14. **<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

15. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 23 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 432/2011**

**የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እንዲሁም በውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 56(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 433/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
   2. "አዋጅ" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 ነው፤
   3. "የኢትዮጵያ ዳያስፖራ" ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ በቋሚነት የሚኖር የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ ነው፤
   4. "ምክር ቤት" ማለት በዳያስፖራ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በዚህ ደንብ የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን የተቋቋመ አካል ነው፤
   5. "ሚሲዮን" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ፣ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤት፣ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ወይም የንግድ ጽ/ቤት ነው፤
   6. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን ያካትታል፡፡
   7. በአዋጁ አንቀጽ (2) የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፤
   8. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" ተብሎ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ስፍራዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

የኤጀንሲው ዓላማ፡-

1. የኢትዮጵያ የዳያስፖራ ፖሊሲን ማስፈጸም፤እና
2. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራዎች መብትና ጥቅም እንዲከበር ማድረግ ነው።

6. **የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባራት**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የዳያስፖራ ጉዳዮችን ያስተባብራል፣
2. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ የምዝገባ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት ይዘረጋል፤
3. በውጭ አገራት የተቋቋሙ እና አዲስ ለሚቋቋሙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ድጋፍ ያደርጋል፤
4. ከዳያስፖራው የሚገኙ የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እድሎችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
5. የዳያስፖራ የገንዘብ እና የሃብት አስተዋጽኦ አሰባሰብ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፤
6. በአገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በኢትዮጵያ ዳያስፖራ ለሚዘጋጁ መድረኮች እና ዝግጅቶች ድጋፍ ያደርጋል፤
7. በውጭ አገራት የተመሰረቱ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች ሕጋዊ እውቅና የሚያገኙበትን እና ተቋማዊ አቅም የሚያጎለብቱበትን እንዲሁም በአገር ውስጥ ያሉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበራት ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ድጋፍ ይሰጣል፤
8. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ በአገር ውስጥ የበጐ ፈቃድ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ያስተባብራል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

9. የዳያስፖራውን ተሳትፎ ለማስተባበር በፌደራል እና በክልሎች ለሚገኙ የዳያስፖራ ማስተባበሪያ አደረጃጀቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
10. የዳያስፖራ አባላት በአገራችን የኢንቨስትመንትና የእውቀት ሽግግር መስክ እንዲሰማሩ ያበረታታል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
11. በዳያስፖራ ጉዳዮች እና ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ጥናቶችን ያከናውናል፣ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያቀርባል፤
12. ተገቢነት ካላቸው የአገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ጋር የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፣
13. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>**የኤጀንሲው አወቃቀር**</u>

ኤጀንሲው፦

1. አማካሪ ምክር ቤት፣
2. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤
3. አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል።

8. <u>**የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት**</u>

1. አማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት ይሰየማሉ፣ ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የአማካሪ ምክር ቤቱ ፀሐፊ እና አባል ይሆናል።

9. <u>**የአማካሪ ምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**</u>

አማካሪ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የኤጀንሲውን ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዱ ስትራተጂያዊ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤
2. የኤጀንሲውን የሥራ ዕቅድ እና አፈጻጸም ይገመግማል፤
3. ከዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ በመምከር የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባል።

10. <u>**የአማካሪ ምክር ቤት ስብሰባዎች**</u>

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ ይካሄዳል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በስምምነት ይወሰናሉ። ሆኖም ውሳኔዎችን በስምምነት መወሰን ካልተቻለ በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አማካሪ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

11.<u>የዋና ዳይሬክተር ሥልጣን እና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ኤጀንሲውን ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ (6) የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሰራተኞችን በአዋጅ ቁጥር 790/2005 እንዲሁም በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሰራተኞች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 399/2008 መሠረት እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በፌደራል ሰርቪስ ህግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያሰተዳድራል፡፡
   ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ የሥራ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤
   ሠ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
   ረ) የኤጀንሲውን የሂሳብ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

12.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖሩታል፤
2. የኤጀንሲውን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

14.<u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

15.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 19 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

መ/ **ለገንዘብ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 184/2002**

**የመንግስት ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 60 (1) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመንግሥት ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 184/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "ሚኒስቴር" የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[13] ነው።

3. **መቋቋም**

   1. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "አገልግሎት እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. አገልግሎቱ ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[14] ይሆናል።

4. **ዓላማ**

   አገልግሎቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

   1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ በተገቢው ጊዜና በተፈላጊው ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል፤

---

[13] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 9(6) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[14] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(6)(ሐ) ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

2. በሽያጭ እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረቶች በተቀላጠፈ አኳኋን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲወገዱ ማስቻል፤
3. ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዕቃና አገልግሎት ግዥ እንዲሁም በንብረት ማስወገድ ረገድ እገዛ ማድረግ።

5. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የአግልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

6. <u>የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. አገልግሎቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

ሀ/ ዝርዝራቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ የሚወሰን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤

ለ/ ግምታቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት ስር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፤

ሐ/ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለክልል መንግሥታትና ለግሉ ዘርፍ፣

1) በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሠረተ የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

2) የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፤

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሐ) መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤

ሠ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

ረ/ ዓላማውን ለማሳከት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማች ተግባሮችን ያከናውናል።

2. አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ሲያውል፦

ሀ/ የመንግሥት ግዥና ንብረት የማስወገዱ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

ለ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

ሐ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አግልግሎቶች ዓለም ዐቀፍ ግዥ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚ አካላቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

መ/ ልዩ ሙያዊ እውቀት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ ተቋማት መጠየቅና ማግኘት ይችላል።

7. **የአገልግሎቱ አቋም**

አገልግሎቱ፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈሳጊነቱ ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

8. **የቦርድ አባላት**

1. ቦርዱ ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።
2. ለቦርዱ አባላት የሚከፈለው አበል በመንግሥት ይወሰናል።

9. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. አገልግሎቱን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የአገልግሎቱን ስትራቴጂዎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
3. የአገልግሎቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት መርምሮ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
4. የአገልግሎቱን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት ያፀድቃል፤ የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ይሰማል፤ በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

5. አገልግሎቱ የሚያስከፍለውን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚያማክሩት ኮሚቴዎች ያቋቁማል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሲሰበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሣኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የቦርዱ አጠቃላይ አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የአገልግሎቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የአገልግሎቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የአግልግሎቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የአገልግሎቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ አገልግሎቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ አገልግሎቱን ይወክላል፤

ሠ/ ስለ አገልግሎቱ የሥራ እንቅስቃሴ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤

ረ/ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለአገልግሎቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የአገልግሎቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. አገልግሎቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛገብት ይይዛል።
2. የአገልግሎቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

14.<u>ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ. ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 332/2007 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 5 እና 35 እና በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 4(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ነው፤
   2. "ድርጅት" ማለት የሂሣብ ሙያ አገልግሎት ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ በቦርዱ የተመዘገበ ድርጅት ነው፤
   3. "ባለሙያ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት እንደተመሠከረለት የሂሣብ ባለሙያ ወይም እንደተመሠከረለት ኦዲተር በቦርዱ የተመዘገበ እና እንደ አግባብነቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤
   4. በአዋጁ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል[15]።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **የቦርዱ ዓላማዎች**

ቦርዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በሪፖርት አቅራቢ አካላት የሚቀርቡ የፋይናንስ እና ተያያዥነት ያላቸውን ሪፖርቶች አዘገጃጀት እና አቀራረብ ጥራት ማስጠበቅ፤
2. የኦዲተሮች እና የሂሳብ ባለሙያዎችን የሙያ ደረጃ ማስጠበቅ፤
3. የሂሳብ አያያዝና የኦዲት አገልግሎትን ጥራት ማስጠበቅ፤
4. የሂሣብ ሙያ የህዝብ ጥቅምን ማስጠበቁን ማረጋገጥ፤
5. የሂሳብ እና ኦዲት ባለሙያዎችን የሙያ ነፃነት ማስከበር፤

6. **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ለቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 4 የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ዓለም አቀፍ የሂሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ወይም እርሱን የሚተካው አካል ከሚያወጣው የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ጋር የተጣጣመ የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችና የተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የሚመሩበት የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፤ ይፋ ያደርጋል እንዲሁም በየጊዜው ይገመግማል፤
2. የባለሙያዎችን ማመልከቻ ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ፣ ባለሙያዎችን ስለማገድ ወይም ከባለሙያዎች ዝርዝር ስለመሠረዝ፤ ፈቃድ ስለማደስ እና ሌሎች ባለሙያዎችን የሚመለከቱ መመሪያዎች ያወጣል፤
3. የራሱን የፈተና እና የብቃት መሥፈርት መመሪያዎች ያወጣል፤

[15] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(6)(ሐ) ተሻሻሎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

4. የሂሣብ ሙያን እና የባለሙያዎችን አቅም ለማጎልበት ከአገር ውስጥና ውጭ ሀገር ካሉ አግባብነት ካላቸው ባለሥልጣኖች፣ ማህበራት፣ የህብረተሰብ ተቋሞች ወይም አካላት ጋር ይነጋገራል፣ ይመካከራል፣ ግንኙነት ያደርጋል ወይም ይተባበራል፤
5. ዓላማውና ተግባሩ ተመሳሳይ ከሆነ ማናቸውም አለም አቀፍ አካል ጋር ይተባበራል ወይም የዚህ አይነቱ አካል አባል ወይም ተባባሪ አባል ይሆናል፤
6. በባለሙያዎች እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በግልግል ወይም በዕርቅ መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፣
7. በሂሣብ ሙያ ላይ ተጽዕኖ ባላቸው በሥራ ላይ ባሉ ወይም ረቂቅ ህጎች ላይ የማሻሻያ ሃሣብ ያቀርባል፤
8. የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችን ለመመዝገብ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይሰጣል፤ ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. በኢትዮጵያ ውስጥ የሂሳብ እና ኦዲት ሥራ ሙያን ይወክላል፤
10. እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር በመሆን በቦርዱ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የብቃት መሥፈርቶችን በማውጣት በእነዚሁ መሥፈርቶች መሠረት ባለሙያዎችን መዝግቦ ይይዛል፤
11. ለባለሙያዎች ለሚሰጡ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ፕሮግራሞች መሥፈርት ያወጣል፣ ሥልጠና ይሰጣል ወይም ሥልጠና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤
12. በራሱ አነሳሽነት ወይም ከሌላ ሰው በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ቅሬታ መሠረት በተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ወይም በተመሰከረሳቸው ኦዲተሮች የሚፈጸም የሥነምግባር ደንብ ወይም የዚህን ደንብ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ ድንጋጌዎች መተላለፍን አስመልክቶ የቀረበን ክስ ይመረምራል፤ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤
13. የላቀ የኦዲት ሥራ ጥራት መኖሩን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት በሥራ ላይ ያውላል፤
14. ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች የሚሠሩ ኦዲተሮችን የሥራ ጥራት ይመረምራል ወይም እንዲመረመር ያደርጋል፤
15. የሂሣብና የኦዲት ሙያን የሚመለከቱ አለም አቀፍና የሀገር ውስጥ መረጃዎችን በየጊዜው በመከታተል ለባለሙያዎች እና ለሌሎች ሰዎች ያሰራጫል፣

16. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የቦርዱ አቋም</u>**

1. ቦርዱ፡-

ሀ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ

ለ/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

ሐ/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

2. ቦርዱ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያግዙትን የተለያዩ የአማካሪ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

8. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ</u>**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከግሉ ዘርፍና ሙያውን ከሚወክሉ የሙያ ማህበራት የተውጣጡ 12 አባላት ይኖሩታል።
2. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመረጡት አብዛኞቹ ሰዎች በሂሳብ ሙያ እና ለሙያው ቀረቤታ ካላቸው የትምህርት መስኮች ይሆናሉ።

9. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን</u>**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለሌላ ሦስት ዓመት በአባልነት በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል።
3. ለሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመናት ያገለገለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ከኃላፊነት ከተነሳ ከሦስት ዓመታት ቆይታ በኋላ በድጋሚ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ሊመረጥ ይችላል።

10. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር</u>**

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቦርዱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤
2. ለመንግሥት የሚቀርበውን የቦርዱን በጀትና የሥራ ፕሮግራም እና ሪፖርት ይመረምራል፤
3. ቦርዱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖች ለመንግሥት ከመቅረባቸው በፊት ይመረምራል።

## 11. <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ</u>

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ መካከል ቢያንስ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት ሲጠይቁ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
2. በማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የቦርዱ ዋና ዳይሬክተር በስብሰባ ላይ እንዳይገኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካልወሰነ በስተቀር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በማናቸውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል።
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## 12. <u>ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አባልነት ብቁ አለመሆንና ከአባልነት ስለመሰናበት</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-
   - ሀ/ በማንኛውም ጊዜ በሙስና፣ በስርቆት፣ በማጭበርበር፣ አስመስሎ በመስራት፣ በሀሰት በመመስከር፣ ወይም በማናቸውም የእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፤
   - ለ/ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በማንኛውም ሕግ መሰረት የገንዘብ ቅጣት አማራጭ በሌለው ከስድስት ወር ባላነሰ የእስራት ቅጣት በሚያስቀጣ ወንጀል ተግባር የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈበት ከሆነ፣
   - ሐ/ በአባልነት ቢሾም የጥቅም ግጭት የሚያስከትልበት ከሆነ፣
   - መ/ በሌላ ማናቸውም ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ባለአደራ ለማገልገል በሕግ ብቁ ካልሆነ፣

   ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ ሊሆን አይችልም።
2. ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ይሰናበታል፡-
   - ሀ/ በራሱ ፈቃድ ከአባልነት ለመሰናበት ለሚኒስትሩ የጽሑፍ ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

ለ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያወጣውን የአባላቱን የሙያና የሥነምግባር ደንብ ጥሶ ሲገኝ፣

ሐ/ በዳይሬከተሮች ቦርድ አባላት አብላጫ ድምጽ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት አልተወጣም ተብሎ ሲወሰን፣ ወይም

መ/ በአስራ ሁለት ተከታታይ ወራት ውስጥ ከተደረጉ ስብሰባዎች ቢያንስ በግማሹ ላይ ካልተገኘ

13.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የቦርዱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የቦርዱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የቦርዱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የቦርዱን ዓላማ በማስፈፀም ሥራ ላይ የሚስማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል

   ሐ/ የቦርዱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ ከታዬ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም፤ ተግባራዊ ያደርጋል

   መ/ ለቦርዱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ቦርዱን ይወክላል፣

   ረ/ የቦርዱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በዳይሬከተሮች ቦርድ ከታየ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለቦርዱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለቦርዱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

14.<u>የበጀት ምንጭ</u>

የቦርዱ የበጀት ምንጭ፦

1. መንግሥት ከሚመድብለት ዓመታዊ በጀት፤ እና

2. ከሌሎች ምንጮች ይሆናል።

15. ስለሂሳብ መዛግብት

1. ቦርዱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የቦርዱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ክፍል ሶስት

## ባለሙያዎችን ስለመመዝገብ፣ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት እና ስለመቆጣጠር

16. ስለመመዝገብ

ቦርዱ የባለሙያዎችን ስምና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች የያዘ መዝገብ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል።

17. የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ስለመመዝገብ

1. በሂሣብ ሙያ አግባብነት ያላቸው የብቃት መስፈርቶችን የሚያሟላና ቢያንስ የሦስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ማንኛውም ሰው እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ለመመዝገብ ቦርዱ በሚያወጣው ፎርምና ሥርዓት መሠረት ማመልከት ይችላል።
2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያና በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰኑ መረጃዎች ጋር እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።
3. ቦርዱ፡-

   ሀ/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለውን ወይም ኢትዮጵያዊ ካልሆነ የሥራ ፈቃድ ያለውን ወይም የሥራ ፈቃድ ከማቅረብ ግዴታ በሕግ ነፃ የተደረገን፤

   ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ የሆነን፤

   ሐ/ መልካም ሥነ ምግባር ያለውና እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል በማንኛውም ሀገር ጥፋተኛ ሆኖ ያልተገኘን፤

   መ/ በቂ የሂሣብ ሙያ እውቀትና ክህሎት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጠውን ፈተና ወይም ምዘና ያለፈን፤ እና

   ሠ/ ተገቢውን ክፍያ የከፈለን፤

አመልካች ስምና አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ሌሎች መረጃዎች በተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ይመዘግብዋል።

4. ቦርዱ አንድ ሰው እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ መሥራት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት የመውሰድ ግዴታን እንዲያሟላ ሊጠይቀው ይችላል።

18.<u>የተመሰከረላቸውን ኦዲተሮች ስለመመዝገብ</u>

1. ኦዲተር በመሆን ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ እንደተመሰከረለት ኦዲተር እንዲመዘገብ ቦርዱ በሚያወጣው ፎርም እና ሥርዓት መሠረት ለቦርዱ በጽሑፍ ማመልከት ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰኑ መረጃዎች ጋር መቅረብ አለበት።
3. ቦርዱ አመልካቹ፦

 ሀ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ መሆኑን፣

 ለ/ ቦርዱ ባወጣው መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን፣

 ሐ/ ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት ለመውሰድ ዝግጅት ማድረጉን፣

 መ/ እንደተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ ለመስራት የሚያስችል ብቃት ያለውና ቦርዱ ባወጣው መመሪያ የሚጠየቀውን ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት በፈጸመበት እና በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻውን ባቀረበበት ጊዜ መካከል አንድ ዓመት ያለፈ መሆኑን፣ እና

 ሠ/ ቦርዱ በሚወስነው ጊዜና አኳኋን መሠረት ለጥራት ማረጋገጫ ምርመራ እራሱን ያዘጋጀ መሆኑን፣

 ሲያረጋግጥ የአመልካቹን ስምና ሌሎች መረጃዎች በተመሰከረላቸው ኦዲተሮች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደተመሰከረለት ኦዲተር ይመዘግበዋል።

4. ቦርዱ አንድ ሰው እንደተመሰከረለት ኦዲተር መስራት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርትና ስልጠና የመውሰድ ግዴታን እንዲያሟላ ሊጠይቀው ይችላል።

19.**<u>የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች እና የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ስላለመመዝገብ፣</u>**

1. ቦርዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ወይመ 18 መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት፣

ሀ/ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብ የቀረበው አመልካች፡-

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች ካላሟላ፣
2) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ እንዲሠራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ ወይም፣
3) በሌላ ማንኛውም ምክንያት እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

አመልካቹን እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ አይመዘግበውም

ለ/ እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ የቀረበው አመልካች፡-

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች ካላሟላ፣
2) የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዲሠራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፣ ወይም
3) በሌላ ማንኛውም ምክንያት እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

አመልካቹን እንደተመሰከረለት ኦዲተር አይመዘግበውም።

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበን ሰው ላለመመዝገብ ሲወስን ምክንያቱን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
3. ቦርዱ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር ስላልመዘገበው ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ሊያስቀይር በሚችል የሕግና የፍሬ ነገር ትንታኔ በማስደገፍ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ቅሬታውን በጽሑፍ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሊያቀርብ ይችላል።
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

20.**ድርጅቶችን ስለመመዝገብ**

1. ማንኛውም የሂሳብ ሙያ አገልግሎት ወይም የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ድርጅት ቦርዱ እንዲመዘግበው ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ሥርዓት መሠረት በጽሑፍ መቅረብ አለበት።
3. ቦርዱ፡-

   ሀ/ ሁሉም የድርጅቱ ሽሪኮች በቦርዱ የተመዘገቡ መሆኑን፣

   ለ/ ድርጅቱ እና እያንዳንዱ ሽሪክ አባል በተናጠል ቦርዱ የሚያወጣውን የሙያ ስነምግባር ደንብ ለማክበር በጽሑፍ ግዴታ የገቡ መሆኑን፣

   ሐ/ ድርጅቱ ቦርዱ በሚወስነው የገንዘብ መጠን የሙያ መድን የገባ ወይም ሌላ ዓይነት የገንዘብ ዋስትና የሚያቀርብ መሆኑን፣

   ሲያረጋግጥ የአመልካቹን ድርጅት ስም እና ሌሎች መረጃዎች በድርጅቶች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደ ድርጅት ይመዘግበዋል።
4. የድርጅት ምዝገባን በሚመለከት ለሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ የዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (4) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

21.**የምዝገባ እና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት፣**

1. ቦርዱ አንድን ግለሰብ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም አንድን ድርጅት እንደ ድርጅት ሲመዘግብ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።
2. ቦርዱ አንድን ሰው እንደተመሰከረለት ኦዲተር ሲመዘግበው የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።
3. የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት አመልካቹ ተገቢውን ክፍያ ሲፈጽም ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም መሠረት ይሰጣል።
4. በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት፣

   ሀ/ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ራሱን የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ብሎ መጥራት እና "ሲ.ፒ.ኤ." የሚለውን ምህጻረ ቅል መጠቀም ይችላል፣

   ለ/ እንደተመሰከረለት ኦዲተር የተመዘገበ ሰው ራሱን የተመሰከረለት ኦዲተር ብሎ መጥራት እና "ሲ.ኤዩ." የሚለውን ምህጻረ ቃል መጠቀም ይችላል።

5. የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ሆኖ የሚቆየው የምስክር ወረቀቱን የያዘው ሰው ምዝገባ እስከፀና ድረስ ብቻ ይሆናል። ምዝገባው የተሰረዘ ወይም የታገደ ማንኛውም ሰው የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ለቦርዱ ወዲያውኑ መመለስ አለበት።

22. <u>ምዝገባን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ</u>

1. ቦርዱ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድን የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት ምዝገባ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ እና ከመዝገብ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል።
   ሀ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅቱ የተመዘገበው በማጭበርበር ወይም በማስመሰል መሆኑን ሲደርስበት፣
   ለ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ ማንኛውንም የቦርዱን መመሪያ የማያከብር ሲሆን ወይም የሚጥስ ተግባር መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣
   ሐ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ አባል ከሆነበት ሌላ የሂሳብ ሙያ ማህበር የታገደ ወይም የተሰረዘ ሲሆን፣
   መ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ አዋጁን ወይም ይህንን ደንብ ተላልፎ ከተገኘ፣
   ሠ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ ከእምነት ማጉደል ጋር በተያያዘ ወንጀል በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ጥፋተኛ ሆኖ የገንዘብ ቅጣት አማራጭ በሌለው እስር ከተቀጣ ወይም ድርጅቱ የገንዘብ ቅጣት ከተጣለበት፣
   ረ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ በሕግ ችሎታ ያጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
   ሰ/ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠቱ ሲረጋገጥ፣
2. ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲሰርዝ የምስክር ወረቀቱን የያዘውንም ሰው ከባለሙያዎች መዝገብ ይሠርዘዋል።
3. ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲያግድ የምስክር ወረቀቱ ለታገደበት ጊዜ የምስክር ወረቀቱን የያዘውንም ሰው ከባለሙያነት ያግደዋል።

4. ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ይህንኑ ከሁለት በማያንሱ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ዕለታዊ ጋዜጣዎች ለሶስት ተከታታይ ቀናት በማውጣት ህዝብ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት።

## 23.የምዝገባ የቆይታ ጊዜ እና እድሳት

1. ቦርዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የሚሰጠው የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል።
2. ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ስርዓት መሠረት የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይችላል።
3. ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ስርዓት መሠረት የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ እና ቦርዱ በመመሪያ ከሚወስነው መረጃ ጋር መቅረብ አለበት።
5. ቦርዱ፡-

ሀ/ አመልካቹ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት እንደአግባብነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ያድስለታል፣

ለ/ አመልካቹ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት፡-

1) እንደአግባብነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ ወይም
2) በሌላ ማናቸውም ምክንያት እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን አያድስለትም።

ሐ/ አመልካቹ የተመሰከረለት ኦዲተር በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ያድስለታል፣

መ/ አመልካቹ የተመሰከረለት ኦዲተር፡-

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ ወይም
2) የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዲሰራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፣ወይም
3) በሌላ ማናቸውም ምክንያት እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን አያድስለትም።

6. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የአንድን አመልካች የምስክር ወረቀት ላለማደስ ሲወስን የምስክር ወረቀቱን የማያድስበትን ምክንያት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

24.<u>ያለምስክር ወረቀት መሥራትን ስለመከልከል</u>

ማንኛውም ሰው ቦርዱ የሚሰጠው ሕጋዊ የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ወይም የምስክር ወረቀቱ በሚፈቅደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእራሱም ሆነ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር በሽርክና ወይም በማኅበር እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር መሥራት ወይም እራሱን ማቅረብ አይችልም።

25.<u>የስም ወይም የሌላ መረጃ ለውጥ</u>

ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት በተመዘገበው ስሙ ወይም ሌላ መረጃ ላይ ለውጥ ሲኖር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለውጡ በተደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

26.<u>የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ስለማከናወን፣</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 25 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ የሚፈቅድለት የሌላ ሀገር የሂሣብ ሙያ ተቆጣጣሪ ድርጅት፣ አህጉራዊ ወይም

ክፍል አህጉራዊ የሂሣብ ሙያ ማህበር የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ሥራ ጥራት መመርመር ይችላል። ለዚህ ዓላማ፡-

ሀ/ በኦዲተሩ፣ በሸሪኩ፣ በተቀጣሪው ወይም ከእርሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ባለው ሰው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለውን መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀትና ማህደር፣ ሰነድና መዝገብ መመርመርና ፎቶ ኮፒ መውሰድ፣ ወይም አጭር ማስታወሻ መያዝ ይችላል፣

ለ/ ከኦዲተሩ፣ ከሸሪኩ ወይም ከተቀጣሪው ወይም ከኦዲተሩ ጋር የሥራ ግንኙነት ካለው ሰው ማንኛውንም መረጃ ወይም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል።

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር፣ ሸሪኩ፣ ተቀጣሪው ወይም ከሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው በቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ በወከለው ሰው ሲጠየቅ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለው መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀት፣ ማህደር ወይም ሰነድ ማቅረብ አለበት።

27.<u>መረጃን ይፋ ስለማድረግ፣</u>

1. ቦርዱ፡-

ሀ/ የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከሁለት በማያንሱ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ዕለታዊ ጋዜጣዎች ለሦስት ተከታታይ ቀናት ዓመታዊ የባለሙያዎችን ስም ዝርዝር በማውጣት ይፋ ማድረግ አለበት፣

ለ/ ለህዝብ ይፋ በሆነ መዝገቡ እና በድረ-ገጹ ወቅታዊውን የባለሙያዎች ስም ዝርዝር መያዝ አለበት።

2. የባለሙያዎችን መዝገብ ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ ማየት ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው አመቺ በሆነ ማንኛውም ጊዜ ክፍት ይሆናል።

3. ቦርዱ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች የያዘ ሪፖርት በየጊዜው ያወጣል።

4. ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን መረጃ የያዘ ኤሌክትሮኒክ መጽሔት የሚያወጣበት ድረ-ገጽ ይኖረዋል።

5. ቦርዱ ከባለሙያዎች እና ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች በሪፖርቱ ወይም በድረገጹ፣ በኤሌክትሮኒክ መጽሔቱ ወይም በዕለታዊ ጋዜጣ ይፋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

## ክፍል አራት

## ትምህርት እና ፈተናዎች

**28.የሙያ ብቃት መስፈርቶች እና የትምህረት ፕሮግራም ይዘቶች፣**

ቦርዱ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ የመንግስት እና የግል ዘርፍ ፍላጎቶችን ማሟላት በሚያስችል አኳኋን የሙያ ብቃት መስፈርቶችን እና የትምህርት ፕሮግራም ይዘቶችን ያዘጋጃል።

**29.የፈተና አስተዳደር እና የጥራት ማረጋገጫ፣**

የቦርዱ የሙያ ብቃት መስፈርቶች ከፍተኛ ጥራትና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥና ከልምድ ልውውጥ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል ቦርዱ በፈተና እቅድ ረገድ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል እውቅና ካላቸው የሂሳብ ሙያ ማህበራት ጋር ጥምረት በመፍጠር በትብብር ይሰራል።

## ክፍል አምስት

## የዲሲፕሊን ክስ

**30.. በቦርዱ ስለሚታይ የዲሲፕሊን ክስ**

1. በአዋጁ ከአንቀጽ 36 እስከ 42 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከመርማሪ ሹሙ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሣብ ወይም ቦርዱ በራሱ ተነሳሽነት ባገኘው መረጃ መነሻ አዋጁ ወይም ይህ ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣ መመሪያ ወይም የሙያ ስነምግባር ደንብ በተመሠከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ በተመሠከረለት ኦዲተር ወይም በድርጅት ተጥሷል ብሎ እንዲያምን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ጥሰት በፈጸመው ሰው ላይ ክስ በመመሥረት ጉዳዩን በአዋጁ አንቀጽ 38(3) መሠረት ለሚሰየሙ የክስ ሰሚዎች ይመራል።
2. የክስ ሰሚዎች የቀረበውን ማስረጃ ከሰሙ በኋላ ክሱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተረጋግጧል ብለው ካመኑ፣ በተከሳሹ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የቅጣት ውሳኔ ያስተላልፋሉ፣

   ሀ/ ተከሳሹ ተግሳጽ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፣

   ለ/ የተከሳሹ የሙያ ሥራ ወይም የምዝገባ ምሥክር ወረቀት እንዲወሰድ፣

ሐ/ ተከሳሹ ለተወሰነ ጊዜ ከሙያው እንዲታገድ፣

መ/ የተከሳሹ ስም ከመዝገብ ላይ እንዲሠረዝ፣

ሠ/ ተከሳሹ ከብር 25ሺ ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሙያ ሥራ ወረቀቱ የታገደ ወይም ስሙ ከመዝገቡ የተሠረዘ ግለሰብ ወይም ድርጅት እራሱን እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት ማቅረብ አይችልም፣ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱም እገዳው ለሚፀናበት ጊዜ ወይም በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት ስሙ ተመልሶ መዝገብ ላይ እስኪሰፍር ድረስ እንደተሠረዘ ይቆጠራል።

4. የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም፣ የክስ ሰሚዎች የይግባኙ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ውሳኔው እንዳይፈጸም ካልወሰኑ በስተቀር ተከሳሹ እንዲታገድ ወይም ስሙ ከመዝገብ እንዲሠረዝ እና የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱ እንዲወሰድ ወይም እንዲታገድ የክስ ሰሚዎች የሰጡት ውሳኔ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 31.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ ደንብ የተደነገገው ቢኖርም፣ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት-

ሀ/ ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ ሥራም ሆነ የኦዲት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው ይህ ደንብ ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ ደንብ መሠረት የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ ለመሥራት የሚፈለገውን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር ከአምስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል፣

ለ/ በራሱም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና በድርጅት ስም ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሣብ ወይም የኦዲት ሥራ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው ደንቡ ከፀናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ድርጅቱ እንዲመዘገብለት ማመልከቻ

ካቀረበ በዚህ ደንብ መሠረት ድርጅቱ ለመመዝገብ ማሟላት የሚፈለግበትን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር ከአምስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሳይመዘገብ አገልግሎቱን እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ወይም ድርጅት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ ደንብ እና ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ ቦርዱ የሚያወጣውን መሥፈርት ካላሟላ ከአምስት ዓመት በኋላ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

32. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ቦርዱ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡

33. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ሀ/ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን በድጋሚ ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 121/1998 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

ለ/ ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

34. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 445 /2011 ዓ.ም</u>

## <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነትን ለመወሰን የወጣ ደንብ</u>

በፌደራል የመንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32(15) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፤

የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን በዚሁ ኤጀንሲውን ባቋቋመው አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና 32/15/ መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 445/ 2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ:-

   1. “የመንግስት የልማት ድርጅት” ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 2 (1) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ ድርጅት ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ አክሲዮን ማህበር ሲሆን በሌሎች ሕጎች ወይም በመንግስት ውሳኔ የተለየ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተሰየመላቸውን ድርጅቶች አይጨምርም፤
   2. “አክሲዮን ማህበር” ማለት በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ አክሲዮን ያለው ማህበር ማለት ሲሆን መንግስት በልማት ድርጅቶች አማካኝነት ባለአክሲዮን የሆነባቸውን አክሲዮን ማህበራትን አይጨምርም፡፡
   3. “ቦርድ” ማለት የመንግስት የልማት ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ ነው፡፡
   4. “ኤጀንሲ” ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
   5. “ይዞታ” ማለት ለኤጀንሲው ተጠሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች እና የመንግስትን የአክሲዮን ድርሻ የሚመለከት ነው
   6. “ሚኒስቴር እና ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
   7. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
   8. በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ያካትታል፡፡

3. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፤ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖሩት ይችላል፡፡

4. **የኤጀንሲው ዓላማ**

የኤጀንሲው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውጤታማ፣ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆኑ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋትና ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አመራርና አስተዳደር መከታተል፤
3. በመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ውስጥ መንግስትን በመወከል የመንግስትን የባለቤትነት መብት ማስከበር፤
4. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አስተዳደር የመንግስት የባለቤትነት፣ የተቆጣጣሪ እና የፖሊሲ አውጪውን አካላት ኃላፊነትና ሚናን በለየ መልኩ መተግበሩን ማረጋገጥ፤ እና
5. በመንግስት የልማት ፖሊሲ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ስምሪት መካከል የሚኖረውን ቅንጅት ማሳለጥ፡፡

5. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዛቸውን ያረጋግጣል፣ ዕቅዶቹን ያፀድቃል፣ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ኦዲት ሪፖርቶች ያፀድቃል፣በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፤
3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ለማድረግ፣ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን ይዘረጋል፤
4. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ችሎታ፣ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

5. አዳዲስ የኢንቨስትመንት መስኮችን እና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በማጥናት እንዲፈቀድ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
6. የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲፈርሱ፣ እንዲዋሃዱ ወይም እንዲከፋፈሉ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. በሚኒስቴሩ አጠቃላይ አመራርና አቅጣጫ በመመራት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወሩ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲወሰንም በሥራ ላይ ባሉት በአዋጅ ቁጥር 146/1991 እና 182/1992 ድንጋጌዎች መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
8. የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ ያዘጋጃል፣ በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግስት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
9. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ መሰረዝን በሚመለከት ለሚኒስቴሩ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
10. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም እና ሁኔታ የሚያሳይ የመረጃ ስርዓት ያደራጃል፣የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን፣ የብድር አወሳሰድና አመላለሳቸውን በቅርበት በመከታተል የተጠቃለለ የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
11. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለምርምር እና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ፣ የተገኘውን የምርምር እና የፈጠራ ውጤት እንዲያሰራጩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
12. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ማዕከላዊ አስቀማጭ ሆኖ ያገለግላል፣ የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም የሚመለከቱ የወል መረጃዎች ያሳውቃል፤
13. በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ቦርድ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ቅጥር እና ስንብት ላይ ይሁንታ ይሰጣል፤
14. የልማት ድርጅቶች ተሞክሮ የሚለዋወጡበትን መድረክ ያዘጋጃል፣ የድርጅቶቹን የአመራር አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

15.ከሕግ አግባብ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን አስመልክቶ በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 572/2000 እና በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል፤

16.ለኤጀንሲው ተጠሪ የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር 25/1984 ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፡፡

17.በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በአክሲዮን ማህበራት ውስጥ መንግስት ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤

18.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

19.ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

6. <u>ኤጀንሲው የሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች</u>

ኤጀንሲው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው አባሪ የተዘረዘሩትን የልማት ድርጅቶች ይቆጣጠራል፡፡ ሆኖም መንግስት እንደ አስፈላጊነቱ ኤጀንሲው የሚያስዳድራቸውን የልማት ድርጅቶች ዝርዝር ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

7. <u>የኤጀንሲው አደረጃጀት ኤጀንሲው፡-</u>

1. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
2. አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

8. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

1. ዋና ዳይሬክተር የኤጀንሲው ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ ያገለግላል፣ የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል ፤ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ 5 ሥር የተዘረዘሩትን የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የኤጀንሲውን ሰራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ) የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል ፤ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደለት የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች በሙሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ለኤጀንሲው ለሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል ፡፡

9. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፡-

1. የኤጀንሲውን ስራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

10. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

11. <u>የሂሳብ መዝገብ</u>

1. ኤጀንሲው የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል፡፡
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዝገብ እና ገንዘብን የሚመለከቱ ሰነዶች በየዓመቱ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተሩ በሚመደበው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

12. <u>ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በደንቡ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ፡፡

13. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ሠ/ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

## አዋጅ ቁጥር 365/1995 ዓ.ም

## የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር[16] ማቋቋሚያ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ታማኝና በሕገ መንግሥቱ መሠረት ለሚወጡ ሕጎች ተገዥ የሆነ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፣

ማረሚያ ቤቶች የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን በመፈጸም ሂደት ታራሚዎችን የመጠበቅ እና የማረም ተግባራትን በማከናወን ወንጀልን በመከላከል ረገድ የበኩላቸውን ተገቢ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በመሆኑ፣

---

[16] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) መሰረት "ኮሚሽን" የሚለው ስያሜ "አስተዳደር" በሚል ተተክቷል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ማቋቋሚያአዋጅ ቁጥር 365/1995 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. “አስተዳደር” ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ነው፤
2. “የጋራ ጉባኤ” ማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና የክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች የጋራ ጉባኤ ማለት ነው፤
3. [17]
4. “ማረሚያ ቤት” ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሚላኩ ታራሚዎች የተወሰነባቸውን የእሥራት ቅጣት የሚፈጽሙበት፣ የሚታረሙበት፣ እንዲሁም በፍርድቤት ትዕዛዝ የሚላኩ ውሳኔ እስከሚያገኙ እንዲቆዩ የሚደረግበት የፌዴራል ማረሚያ ተቋም ነው፤
5. “ታራሚ” ማለት በሕግ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የፍርድ ውሳኔ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በመፈጸም ላይ የሚገኝ የሕግ ታራሚ ሲሆን በማረሚያ ቤት በቀጠሮ እንዲቆይ የተወሰነበትንም ይጨምራል፤
6. “የማረሚያ ጠባቂ” ማለት መሠረታዊ የሆነ የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በአሰተዳደሩ ተቀጥሮ የሚሠራ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አባል ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር መቋቋም

3. **መቋቋም**

[17] በ22/64(2008) አ.945 አንቀፅ 2 መሰረት በግልፅ ሳይነገር ተሻረ፡፡

1. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ከዚህ በኋላ “አስተዳደር” እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. አስተዳደሩ በሕግና በሙያው የሚኖረው ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይሆናል[18]።

4. <u>የአሰተዳደሩ ዋና መሥሪያ ቤት</u>

1. የአሰተዳደሩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፡
2. ከዚህ በፊት በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ስር ሲተዳደሩ የነበሩት ማረሚያ ቤቶች በአሰተዳደሩ ስር ሆነው ይዋቀራሉ።
3. አሰተዳደሩ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውኑ አካላትን በማናቸውም ቦታ ማቋቋም ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

የአሰተዳደሩ ዓላማ ታራሚዎችን ተቀብሎ መጠበቅ፣ ለታራሚዎች የተሐድሶ አገልግሎት በመስጠት የአስተሳሰብና የስነ-ምግባር ለውጥ እንዲያመጡ እንዲሁም ሕግ አክባሪ፤ ሰላማዊና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

6. <u>የአስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

አሰተዳደሩ የሚኩተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በፍርደ ቤቶች ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት የሚላኩለትን ታራሚዎች በመቀበል ይጠበቃል ያርማል፣ እንዲሁም ከፍርድ ቤት የሚሰጡ ሌሎች ትእዛዞችይፈጽማል፣
2. ታራሚዎችን ፍርድ ቤት ያቀርባል፣
3. የታራሚዎችን ጤንነት ይጠብቃል፤ በዚህ አዋጅ በሚወጣው ደንብ መሠረት ታራሚዎች ነፃ ሕክምና፤ ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል።ለታራሚዎች አካላዊና አዕምሮአዊ እንክብካቤ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ያከናውናል፣ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ዝርዝሩ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣
4. ታራሚዎች ከተለቀቁ በኋላ ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚችሉና ለሕግ ተገዢ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የቀለም ትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና፣ ማኀበራዊ

[18] በ22/64(2008) አ.945 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

አገልግሎትና የምክር አገልግሎት ይሰጣል። ዝርዝሩ በደንብና በመመሪያ ይወሰናል፤

5. በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ታራሚዎችን ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ወደ ክልል ማረሚያ ቤቶች ወይም ከአንድ ማረሚያ ቤት ወደሌላ ማረሚያ ቤት አጅቦ ያደርሳል፤
6. ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የማረሚያ ቤቱን የሥነ ሥርዓት መመሪያ በመጣስ ለሚፈጽሙት ጥፋት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት የሥነ ሥርዓት ቅጣቶችን ይወሰናል፣ይፈጽማል፤
7. በሀገር አቀፍ ደረጃ ታራሚዎችን በሚመለከት መረጃዎችን እና ስታስቲኮችን ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤
8. ታራሚዎች በሚያሳዩት የባህሪይ ለውጥ በሕግ መሠረት፤

   ሀ/ በአመክሮ ወይም

   ለ/ በይቅርታ፤

   እንዲፈቱ ስልጣን ለተሰጠው አካል ያቀርባል።
9. አሰተዳደሩ ለሥራ አስፈላጊ የሆነ የማረሚያ ጥበቃ አባላት ይመለምላል፣ ይቀጥራል፣ ያሰለጥናል፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑት ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤
10. የአሰተዳደሩን ሠራተኞች የሙያ ብቃት ለማሳደግ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሥልጠና ዕድሎችን ያመቻቻል፣
11. የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል ፣ የማረሚያ ጥበቃ አባላትና ሠራተኞችን ሙያ ብቃትና አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፤
12. ለክልል ማረሚያ ቤቶች የሙያና የቴክኒክ እንዲሁም የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤
13. ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል።

7. <u>**የአስተዳደሩ አቋም**</u>

   1. አስተዳደሩ፡-

      ሀ/ በፌዴራል መንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር[19] እና አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣

[19] በ12/1(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) "ኮሚሽነር" የሚለው "ዋና ዳይሬክተር" በሚል ተተክቷል፡፡

ለ/ ዋና ዳይሬክተሩን ፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩንና የዋና መምሪያ ኃላፊዎችን ያቀፈ የሥራ አመራር ጉባኤ ፣ እና

ሐ/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የማረሚያ ጥበቃ አባላትና የመንግሥት ሠራተኞች ይኖሩታል።

2. የአሰተዳደሩ አደረጃጀት ዝርዝር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ይወሰናል።

8. <u>የአሰተዳደሩ የሥራ አመራር ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

የሥራ አመራር ጉባዔው፡-

1. የታራሚዎችን አጠባበቅ፣ አያያዝ እና የማረሚያ ቤቶችን አስተዳደር ለማሻሻል የሚረዱ ሀገር አቀፍ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የስታንዳርዳይዜሽን ጥናቶችን በመመርመር ከአስተያየት ጋር ለፌዴራል ማረሚያ አስተዳደርና ለክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች የጋራ ጉባዔ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣
2. የአሰተዳደሩን አደረጃጀት፣ አወቃቀርና አሠራር የሚመለከቱ ጥናቶችን ይመረምራል፣ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ከአስተያየት ጋር ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤ የአሰተዳደሩን የሥልጠና ዕቅድ ያዘጋጃል፣
3. የአሰተዳደሩን ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል፣ በፌዴራል መንግሥት እንዲፀድቅለትም በዋና ዳይሬክተሩ በኩል ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤
4. የአሰተዳደሩን ዓመታዊ ዕቅድ፣ ኦዲትና ሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፤ ከአስተያየት ጋር ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣
5. በአሰተዳደሩ እና በክልል ማረሚያ ቤቶች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል።

9. <u>የሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሚኒስትሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

1. የአስተዳደሩን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፡
2. የአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሹመት እንዲጸድቅለት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፡
3. የአስተዳደሩን ዋና መምሪያ ኃላፊዎች ምደባ ያፀድቃል፡
4. የአስተዳደሩን ዓመታዊ ዕቅድ፣ ረቂቅ በጀት፣ ሪፖርትና የሥራ አፈፃፀም ከአስተያየት ጋር ለፌዴራል መንግሥት ያቀርባል፡

5. የታራሚዎች መብት መከበሩንና በአግባቡ ጥበቃ መደረጉን እንዲሁም ታርመውና አምራች ዜጋ ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል፡
6. በአስተዳደሩ የሚቀርቡትን የአደረጃጀት፣ እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብር ጥናቶች ይመረምራል፤ ያፀድቃል፣
7. የአሰተዳደሩን የሥራ ብቃትና ውጤታማነት ለማሳደግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ የቁጥጥር ሥራ ያከናውናል፡
8. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ አስፈላጊ እርምጃዎች ይወስዳል።

10.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የአሰተዳደሩን ሥራ በበላይነት ይመራል፡ ያስተባብራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ የዋና መምሪያ ኃላፊዎች ምደባ እንዲፀድቅለት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤
   ለ/ የአሰተዳደሩን መተዳደሪያ ደንቦች ያስፈጽማል፤
   ሐ/ ለሥራ አስፈላጊ የሆነ የማረሚያ ጥበቃ አባላት ይመለምላል፣ ይቀጥራል፣ ያሰለጥናል፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   መ/ በፌዴራል ማረሚያ አቤቱታ ሰሚ አካል እና በዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚሰጡ ውሳኔዎች በይግባኝ ሲቀርቡለት ይወስናል፤
   ሠ/ የአስተዳደሩን ዓመታዊ የሥራ እቅድና ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣ በፌዴራል መንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
   ረ/ ለአሰተዳደሩ በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ የኦዲትና የኢንስፒክሽን ሥራዎች እንዲሠሩ ያደርጋል፣
   ሰ/ የአስተዳደሩን አደረጃጀት፣ አሠራርና አቅም ግንባታ የሚመለከቱ ጥናቶች፣ የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶች፣ እንዲሁም የማረሚያ ጥበቃ ሙያና አገልግሎት ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
   ሸ/ በአስተዳደሩ እና በክልል ማረሚያ ቤቶች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፣
   ቀ/ የአስተዳደሩን የአመራር ጉባዔ በስብሳቢነት ይመራል፣

በ/ አስተዳደሩን አስመልክቶ የውጭ ግንኙነት ያደርጋል።

**11.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ የአስተዳደሩን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፣
   ለ/ በአስተዳደሩ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍሎች በማድረግ ከአስተዳደሩ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፣
   ሐ/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፤
   መ/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።
2. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል።

**12.<u>በጀት</u>**

የአስተዳደሩ በጀት በፌዴራል መንግሥት ይመደባል።

**13.<u>የሂሣብ መዛግብትን የሂሳብ ምርመራ</u>**

1. አስተዳደሩ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብ ትይይዛል፣
2. የአስተዳደሩ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ስለ ፌዴራል ማረሚያ ጥበቃ አስተዳደር</u>**

**14.<u>ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>**

1. በፌዴራል ማረሚያ ጥበቃ አባልነት ለመመልመል ፈቃደኛ የሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚከተሉትንመመዘኛዎች በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል፡-
   ሀ/ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ተገዥ የሆነ፣
   ለ/ ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት ለመመልመል የሚያበቃ የትምህርት ደረጃ፣ አካላዊ ብቃት እና የተሟላ ጤንነት ያለው፣
   ሐ/ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣
   መ/ በፍርድ ቤት የተወሰነ የወንጀል ጥፋተኛነት የፍርድ ሪከርድ የሌለው፣
   ሠ/ ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣
   ረ/ የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ሥልጠናን ያጠናቀቀ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረገው ምልመላ የፆታ፣እንዲሁም የብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሚዛናዊ ተወጽኦ ያካተተ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተመለመለ ማንኛውም ዜጋ የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆነ እንደሆነ በማረሚያ ጥበቃ ሲቀጠር የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን መተው ይኖርበታል።

15.**ቃለ መሐላ ስለመፈፀም**

ለማረሚያ ጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ማንኛውም ምልምል ለፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ሙያዊ ኃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሐላ ይፈጽማል። የቃለ መሐላው ይዘት በደንብ ይወሰናል።

16.**የአገልግሎት ዘመን**

1. የማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፣
2. የማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ቅጥር ከሚከተሉት መካከል በማናቸውም ምክንያት ይቋረጣል፦

ሀ/ በሞት፣

ለ/ በደንቡ መሠረት የስንብት ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ፣

ሐ/ በሐኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ሕመም ወይም የአካል ጉዳት ለሥራው ብቁ ሳይሆን ሲቀር፣

መ/ በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና በደንቡ መሠረት ወንጀሉ ለሥራው ብቁ እያደርገውም ተብሎ ሲወሰን፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

ሠ/ በሥራ አፈጻጸም ወይም ዲሲፕሊን ጥፋት፣

ረ/ በጡረታ ሲገለል።

17.**መብት**

1. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፦

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት በሚፀድቅ የደመወዝ ስኬል መሠረት ደመወዝ ያገኛል፤

ለ/ በአስተዳደሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቀለብ ልዩ ልዩ አበሎች፤ የደንብ ልብስና የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ/ በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፤

መ/ ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በመሥሪያ ቤቱ ወጪ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፣

ሠ/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን በዘላቂነት ያጣ የማረሚያ ጥበቃ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል።

2. ማንኛውም የማረማያ ጥበቃ አባል፦

ሀ/ የበላይ ኃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፤ ስህተት ሲያይ የመጠቆም እና ችግሮችን በውይይት የመፍታት መብት አለው፤

ለ/ የሥልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

18.<u>ግዴታ</u>

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፡—

1. በሕገ መንግሥቱና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለምአቀፍ ደንጋጌዎች መሠረት የተረጋገጡትን ሰብዓዊ መብቶችና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ በማክበር እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ሥራውን የማከናወን፣

2. የማረሚያ ጥበቃ ስራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ የማሳየት ግዴታ አለበት።

19.<u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በጡረታ የሚገለልበት ዕድሜ ጣሪያ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት ለመንግሥት ሠራተኞች የተወሰነው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ይሆናል።

20.<u>ስለ ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አቤቱታ ሰሚ</u>

በአስተዳደሩ ውስጥ አቤቱታ የሚሰማ የፌዴራል ማረሚያ አስተዳደር አቤቱታ ሰሚ አካል ይቋቋማል፣ዝርዝሩ አሰተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

21.<u>ስለ መተዳደሪያ ደንብ</u>

የማረሚያ ጥበቃ አባሎች መተዳደሪያ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወጣል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለታራሚዎች አያያዝ</u>

**22.መርህ**

1. ታራሚዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፤
2. የታራሚዎች አያያዝ፣ ታራሚዎቹ የተወሰነባቸው ቅጣት ጨርሰው ሲወጡ ሕግ አክባሪ ሆነው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችላቸው መሆን ይኖርበታል፤
3. በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ያሉ እንዲሁም የፍትሐብሔር ታራሚዎች ከወንጀል ድርጊት ነፃ እንደሆኑ ተቆጥረው በወንጀል ቅጣት ከተወሰነባቸው ታራሚዎች ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል።

**23.ታራሚን ስለመቀበል**

በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር አሰተዳደሩ ማንኛውንም ሰው በማረሚያ ቤት እንዲቆይ መቀበል የለበትም።

**24.ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ስለመሆኑ**

በታራሚዎች መካከል በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በብሔር ብሔረሰብ አባልነት ወይም በማኅበራዊ ምንጭ ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

**25.ታራሚዎችን በፈርጅ ለይቶ ስለመያዝ**

1. ሴት ታራሚዎች ከወንድ ታራሚዎች ሙሉ በሙሉ የተለዩ ክፍሎች ይኖራቸዋል፣
2. ሁኔታው በፈቀደ መጠን ታራሚዎች በዕድሜያቸው፣ በፈጸሙት ወንጀልና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል።

**26.የታራሚዎች ክፍሎች ሁኔታ**

1. ታራሚዎች የሚኖሩባቸው ክፍሎች እና ግቢያቸው በጤና ላይ ጉዳት የማያስከትሉ፣ ንፁህ አየርና በቂ ብርሃን የሚያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎች ሲዘጋጁ ታራሚው በሚያሳየው የባህርይ ለውጥና በወንጀል ድርጊት የመፀፀት ሁኔታ አኳያ ለይቶ ለመጠቀም የሚያስችሉና ታራሚዎችን በቀና ተወዳዳሪነት መንፈስ ወደመታረምና ተሃድሶ የሚያተጉ ሊሆኑ ይገባል።

**27.ስለምግብና የጤንነት እንክብካቤ**

ታራሚዎች በተቻለ መጠን ጤናቸውን ለመጠበቅ የሚያበቃቸውን በቂ ምግብና አስፈላጊውን የሕክምና አገልግሎት በነፃ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

**28.ሕፃን ልጅ ስላላት ሴት ታራሚ**

1. ለልጁ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ወራት ያልበለጠና የእናቲቱ የቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው ሕፃን ከሴት ታራሚ እናቱ ጋር አብሮ ማረሚያ ቤት ውስጥ ሊቆይ ይችላል፣
2. አስተዳደሩ ለልጁ ጤንነትና እንክብካቤ አስፈላጊውን የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
3. የእናቲቱ የእሥር ቆይታ በልጁ አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ አቋም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሆኖ ሲገኝ ሕፃኑ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት እንዲያገኝ አስተዳደሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

**29.ከጎብኚዎች ጋር ስለመገናኘት**

ታራሚዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከሕግ አማካሪዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር የመገናኘት መብት አላቸው፣ ዝርዝሩ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**30.ስለመታሠርና ዝውውር መረጃ የማስተላለፍ መብት**

ማንኛውም ታራሚ መታሠሩን ወይም በማናቸውም ምክንያት ከታሠረበት ተቋም ወደ ሌላ ተቋም መዛወሩን ወዲያውኑ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚፈልገው ሰው የመናገር መብት አለው።

**31.በሥራ ስለማሠማራትና ስለ ፈቃድ**

1. በፍርድ ቤት የተወሰነበትን ቅጣት በማረሚያ ቤት በመፈፀም ላይ ያለ ማንኛውም ታራሚ ከችሎታውና ከሙያው ጋር የሚስማማና ጤንነቱን የማይጎዳ ተመጣጣኝ ሥራ እንዲሠራ ይደረጋል፣ በአስተዳደሩ በሚወጣ መመሪያ መሠረት እንደሁኔታው ለሥራው ክፍያ ያገኛል፣
2. ታራሚዎች በማረሚያ ጥበቃ አባል አጃቢነት ለልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮቻቸው ማቃለያ ፍቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

**32.የታራሚ ግዴታዎች**

ለጥበቃ ሥራ፣ ሥነ ሥርዓት አከባበር፣ ጽዳት፣ ጤና አጠባበቅ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት እና ስለሌሎችም ጉዳዮች በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የሚገለጹ የሥነ ሥርዓት ግዴታዎችን ታራሚዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው።

**33.የወንጀል ድርጊት**

ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

**ክፍል አምስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

34.**አስተዳደሩ ከክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች ጋር ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት**

1. የማረሚያ ቤቶችን አስተዳደርና አሠራር፣ የታራሚዎችን አያያዝና አጠባበቅ ለማሻሻል፣ እንዲሁም ለማረሚያ ጥበቃ አባሎች እና ሠራተኞች የሥልጠና ዕድሎችን ለማመቻቸት፣ ከክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።
2. አስተዳደሩና የክልል ማረሚያ ቤት ኃላፊዎች በጋራ በሚወስኑት በማናቸውም ጊዜ የጋራ ጉባኤ ሊያካሂዱ ይችላል፣
3. የጋራ ጉባኤውን የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ዋና ዳይሬክተር ይመራል፤
4. የጋራ ጉባኤው፡-

   ሀ/ የጋራ የአሠራር ውስጠ ደንብ ያወጣል፣

   ለ/ የማረሚያ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመገምገም የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፣ የአሠራር ደንብና መመሪያዎች በይዘት ረገድ እንዲሻሻሉና ወጥነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

   ሐ/ የማረሚያ ጥበቃ የሥልጠናን አቅጣጫ ይዘትና ደረጃን በሚመለከት በጋራ ይቀይሳል፣

   መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በአሰተዳደሩ በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ ይወያያል፣ በጥናቶቹ መሠረት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰኑ ለሚመለከተው አካል ያቅርባል፣ እንደየሁኔታው በአግባቡ ይወሰናል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።
5. አስተዳደሩና የክልል የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች በጋራ ጉባኤው ያስተላለፏቸው ውሳኔዎች መተግበራቸውን በየበኩላቸው ይከታተላሉ።
6. የክልል ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን አጠቃላይ ሁኔታ በሚመለከት ሪፖርትና ስታትስቲክስ በየጊዜው ለአስተዳደሩ ያስተላልፋሉ።

35.**ወታደራዊ ማዕረግ ስለመቅረቱ**

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የማረሚያ ጥበቃ አባል ወታደራዊ ማዕረግ አይኖረውም፣ ሆኖም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሆነ ማዕረግና ምልክት ይኖረዋል።ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤
2. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሥራ መደቡን የሚያመለክት የመለያ ደንብ ልብስ እንዲሁም ማንነቱን የሚገልጽ ስሙን፣ መለያ ቁጥሩን፣ ከፍሉንና ኃላፊነቱን የያዘ ባጅ ወይም ምልከት ይኖረዋል።

36.<u>አሠራር</u>

1. በአስተዳደሩ መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር የዋና ተግባር አፈጻጸም አቅጣጫ ይሆናል። የቡድን አሠራሮች የጋራና የነጠላ ኃላፊነትን ያስከትላሉ፣
2. በአስተዳደሩ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው።
3. የአስተዳደሩ አሠራር የተጠያቂነትና የግልጽነትን መርህ የተከተለ፤ እንዲሁም የሕዝብ ተሳትፎን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

37.<u>የተከለከለ ድርጊት</u>

ማንኛውም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ድርጊት የተከለከለ ነው።

38.<u>የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የወህኒ ቤቶች አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 45/1936 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፣
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

39.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣
2. አስተዳደሩ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን የማውጣትሥልጣን ይኖረዋል።

40.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጳጉሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 320/1995 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈጽም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግሥታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 320/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

1. "አእምሯዊ ንብረት" ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፤ የንግድ ምልክትን፣ የምስክር ወረቀትንና ኮፒራይትን ይጨምራል።
2. "ፓተንት" ማለት የፈጠራ ሥራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ፣ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 መሠረት በፈጠራ፣ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት፣ የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን ይጨምራል።
3. "የንግድ ምልክት" ማለት አንድን ምርት ወይም አገልግሎት ከተመሳሳይ ምርት ወይም አገልግሎት ለመለየት የሚያስችል ምልክት ወይም የምልክቶች ቅንጅት ነው። ምልክቶቹ ፊደላት፡ ቃላት፣ ቁጥሮች፣ ምስሎችና የቀለሞች ቅንጅት ወይም የተዘረዘሩት ምልክቶች ማንኛውም ቅንጅት ሊሆን ይችላል።
4. "ኮፒ ራይት" ማለት እንደ ሥነ ጽሑፍና ኪነ ጥበብ ባሉሥራዎች ላይ ያለ መብት ሲሆን አጎራባች መብትንም ይጨምራል።
5. "አጎራባች መብት" ማለት ከዋኞች፤ የቀረፀ ድምጽና የኦዲቪዥዋል አሳታሚዎች የብሮድካስቲንግ ኬብል አሰራጪዎች በሥራዎቻቸው ላይ ያላቸው መብት ነው።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ይሆናል[20]።

4. <u>ዋናው መሥሪያ ቤት</u>

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ድሬዳዋን ጨምሮ በክልሎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. <u>የጽሕፈት ቤቱ ዓላማዎች</u>

ጽሕፈት ቤቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፣

1. አእምሯዊ ንብረት በቂ የሕግ ጥበቃ የሚያገኝበትንና በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

[20]ተጠሪነቱ በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 33(11)(ለ) ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

2. በፓተንት ሰነዶች የታቀፉ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ ማሰራጨትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማበረታታት፣
3. የአእምሯዊ ንብረት ፖሊሲዎችን ህጎችን ማጥናት፡ መተንተንና ለመንግሥት ሃሳብ ማቅረብ፣
4. በሕዝቡ ዘንድ የአእምሯዊ ንብረት እውቀትና ግንዛቤ እንዲዳብር ማድረግ።

6. **የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የፓተንትና የንግድ ምልክት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊውን ምርመራ በማካሄድ ወይም እንዲካሄድ በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት፣
2. በሕጋዊ ሰነድ ጥበቃ የተደረገላቸውን የውጭና የአገርውስጥ የፈጠራ ሥራዎችን በጥቅም ላይ መዋላቸውንመከታተል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግዴታ ፈቃድ መስጠት፣
3. የፓተንት ማመልከቻ ከመቅረቡ ወይም ቴክኒካዊ ችግሮችን ለመፍታት ምርምር ከመደረጉ በፊት በመስኩየተሰሩ ተመሳሳይ የፈጠራ ሥራዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የፍለጋ መጠይቆችን መቀበል፤ የፍለጋ አገልግሎትመስጠት፤
4. የንግድ ምልክት ማመልከቻዎች ከመቅረባቸው በፊትቀደም ሲል ተመሳሳይ ምልክቶች አለመመዝገባቸውንለማረጋገጥ የፍለጋ መጠይቆችን መቀበል፤ የፍለጋ አገልግሎት መስጠት፤
5. የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች ማተምና ማሠራጨት፣
6. የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን የሚመለከት የመረጃ ሥርዓት መፍጠርና ለተጠቃሚዎች አገልግሎትመስጠት፣
7. መንግሥት የሚያወጣቸው የአእምሯዊ ንብረት አዋጆችና ደንቦች ሥራ ላይ ማዋል፤
8. በቅድሚያ የትኩረት መስኮች በፓተንት ሰነዶች የታቀፉ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን መምረጥና ማሰራጨት እንዲሁም ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲውሉ ማበረታታት፤
9. የፓተንትና የንግድ ምልክት የጥበቃ ጊዜ ማራዘምና የእድሳት ማመልከቻዎችን መቀበል፤ መሰብሰብና ማደራጀት፤ በሕግ መሠረት ውሳኔ መስጠት፤

10.በሕዝቡ ዘንድ የአእምሯዊ ንብረት ግንዛቤ ለመፍጠርና ለማጠናከር ሰፊና የተቀናጀ የአህዝቦት ስልት መቀየስና ሥራ ላይ ማዋል፤

11.በአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮችና ጭብጦች ላይ ጥናቶች ማካሄድ፣ በብሄራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በአእምሯዊ ንብረት መስክ ያሉትን እድገቶች መከታተል፤ የሕግና የፖሊሲ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ማቅረብ፤

12.የአእምሯዊ ንብረት ፖሊሲዎችንና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሥራ ላይ ማዋል እና/ወይም ሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተል፤

13.በአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮች ላይ ለሕዝብ፣ ለመንግሥት፣ለግል ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት እንዲሁም ለግለሰቦች የምክር አገልግሎት መስጠት፤

14.የፈጠራ ሠራተኞች፣ የደራሲያን፣ የሙዚቀኞችና መሰል ማኅበራት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ማኅበራቱን መደገፍና ማጠናከር፣

15.የአእምሯዊ ንብረት ባለቤቶችንና የፈጠራ ሥራቸውን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሹ ባለሃብቶችን ለማገናኘት የሚረዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

16.ከሌሎች የውጪ አገር፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የእእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤቶች ጋር ግንኙነትና ትብብር መፍጠር፣

17.ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣

18.የንብረት ባለቤት መሆንና ውል መዋዋል፤ በራሱ ስም የመክሰስና መከሰስ፣

19.ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን።

7. **<u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>**

ጽሕፈት ቤቱ፤

1. ብሔራዊ የአእምሯዊ ንብረት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር[21] እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

---

[21] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) "ዳይሬክተር ጀኔራል" የሚለው "ዋና ዳይሬክተር" በሚል ተተክቷል፡፡

የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ።

9. <u>**የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ለመንግሥት በሚቀርቡ የፖሊሲ ሃሳቦች ላይ ጽሕፈት ቤቱን ማማከር፤
2. በጽሕፈት ቤቱ ተዘጋጅተው በሚቀርቡ መመሪያዎች፣ፕ ሮግራሞች እና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ማማከር፤
3. በዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርቡ የጽሕፈት ቤቱ አስተዳደር እና አመራር በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ማማከር፤ እና
4. የራሱን የአሠራር ደንብ ማውጣት።

10.<u>**የምክር ቤቱ ስብሰባ**</u>

1. ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል።
3. ምክር ቤቱ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርበው በተባበረ ድምፅ ይሆናል። የተባበረ ድምፅ ከሌለ በድምፅ ብልጫ የውሳኔ ሃሳብ ይተላለፋል። የድምጽ አሰጣጡ እኩል በእኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

11.<u>**የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተር የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ጽሕፈት ቤቱን የማስተዳደርና ሥራውንም የመምራት ኃላፊነት አለበት።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተር ፣

   ሀ/ በፌዴራል የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣

   ለ/ የጽሕፈት ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶች አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

   ሐ/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፤

መ/ ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ጽሕፈት ቤቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል።

3. ዋና ዳይሬክተር ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

ሀ/ ከፌዴራል መንግሥቱ የሚመደብ ድጎማ፣

ለ/ ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ እና፣

ሐ/ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ።

2. ጽሕፈት ቤቱ የሚያገኘውን ገቢ በአገሪቱ የፋይናንስ ሕግና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል።

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማናቸውም ሰው ወይም መንግሥታዊ ወይም የግል ድርጅት ወይም ተቋም ለጽሕፈት ቤቱ ሥራ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

15.<u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ህጎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

16.<u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በዚህ አዋጅ፤

1. በአዋጅ ቁጥር 7/19987 ፣ በአዋጅ ቁጥር 123/1987 እና በአዋጅ ቁጥር 90/1990 ፓተንትና የመሳሰሉትን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን የተሰጠውን መብትና ግዴታ፤

2. ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ በንግድና ኢንዱስትሪ ያሉ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችና
3. በአዋጅ ቁጥር 179/1991 ኮፒራይትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተ መፃሕፍት ድርጅት ያለው መብትና ግዴታ፣ ለጽሕፈት ቤቱ ተላልፏል።

17.<u>**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**</u>

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ማመልከቻን የመቀበልና የማስተናገድ ተግባራትን የንግድ ምልክት ሕግ እስኪወጣ ድረስ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይጠቀምበት በነበረው መመሪያ መሠረት ያከናውናል።

18.<u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ. ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፕሬዝደንት**

## <u>ደንብ ቁጥር 379/2008</u>

## <u>የፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እንዲሁም የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 4 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ ደንብ "የፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 379/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

1. "አዋጅ" ማለት የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 ነው፣
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

3. “ሚኒስቴር” ማለት የፍትህ ሚኒስቴር ነው[22]፤
4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል።

3. **መቋቋም**

1. የፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል[23]።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ይኖሩታል።

5. **ዓላማዎች**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በፌዴራል ደረጃ እና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት መስጠት፤ እና
2. የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ተግባራት በሀገር አቀፍ ደረጃ ማስተባበር እና መደገፍ እንዲሁም ተረጋግጠው የተመዘገቡ ሰነዶችን መረጃ በማዕከል የሚደራጁበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መያዝ።

6. **ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአዋጁ የተጠቀሱትን ሰነድ የማረጋገጥና መመዝገብን እንዲሁም ያለአግባብ ተረጋግጠው የተመዘገቡ ሰነዶችን አግዶ የማቆየት ተግባራትን የማከናወን፤
2. በክልሎች ለሚገኙ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ተቋማት የሙያ፣ የቴክኒክና ሌሎች መሰል ድጋፎችን የመስጠት፣ እንዲሁም የምክክር፣ የልምድ ልውውጥ እና የሥልጠና መድረኮችን የማዘጋጀት፤
3. በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት የሰነድ ማረጋገጥ እና መመዝገብ ተግባራት እንዲያከናውኑ ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች የፌዴራል መንግስት አካላት

[22] በ22/62(2008) አ.943 መሰረት የጠቅላይ አቃቤ ህግ በሚል ይነበብ፡፡
[23] በ22/62(2008) አ.943 አንቀጽ 22(1) በግልጽ ሳይነገር ተሻሻለ፡፡ ተጠሪነቱም ለፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆኗል፡፡

እንዲሁም ከክልል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ተቋማት ጋር በቅርበትና በትብብር የመስራት፤

4. በአገሪቱ ተረጋግጠው የተመዘገቡ ሰነዶችን በአንድ የመረጃ ማዕከል የማደራጀት፣ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመረጃ መረብ የማገናኘት፤
5. በአዋጁ አንቀጽ 8 ለተመለከቱትና እንደአስፈላጊነቱ ለሌሎች ልዩ ልዩ የውል እና የስምምነት ሞዴል ሰነዶችን የማዘጋጀት፣ በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ሥርዓት እንዲኖር ያግዛሉ ተብለው በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ሞዴል ሰነዶችንና ፎርማቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ሰነድ አረጋጋጭና መዝጋቢ ተቋማት የማሰራጨት፤
6. ዓላማውን ማሳካት የሚያስችሉ የፖሊሲ ሀሳቦችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፣ ሲወሰንም በሥራ ላይ የማዋል፤
7. የውስጥ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ የማዋል፤
8. ከሥልጣንና ተግባራቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች የመሰብሰብ፣ የመተንተን እና የማሰራጨት፤
9. ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በትብብር የመሥራት፤
10. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤
11. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

7. **<u>የኤጀንሲው አደረጃጀት</u>**

ኤጀንሲው፦

1. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ የኤጀንሲውን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የስራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ሰ በሚኒስቴሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባራት</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፦

1. በዚህ ደንብ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ዓላማዎች ተግባራዊ በማድረግ፣ ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ በማዋል፣ የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት እና በማስተባበር ረገድ ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤
2. በኤጀንሲው መዋቅር መሠረት በኃላፊነት የሚመሩትን ዘርፎች ተግባራት ይከታተላሉ፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሠራል፤
4. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

10. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል።

11. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

12. <u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 467/1997 መሰረት ለሚኒስቴሩ ተጠሪ ሆነው ስራቸውን ሲያከናውኑ የነበሩ ለአዲስ አበባ እና ለድሬዳዋ ከተሞች የሰነድ ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤቶች የተሰጡ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ መሰረት ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

13. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 15 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## <u>አዋጅ ቁጥር 1071/2010</u>

## <u>የፌደራል የፍትህና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

ሕጎችን ከወቅታዊ የአገሪቱ የእድገት ደረጃና የልማት ፍላጎት ጋር በማጣጣም እና የፍትህ ሥርዓቱን ዘመናዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትን በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ ለማዋል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ የእድገት አቅጣጫን መሰረት ያደረገ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትን እውን ለማድረግ የሚረዱ የፍትህና የሕግ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት እያሳካ መሆኑን የሚያሳይ አስተማማኝና የተሟላ መረጃ መኖር ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ ለሚከናወኑ ሥራዎች በግብዓትነት የሚያገለግል መሆኑን በመገንዘብ፤

በእውቀቱ፣ በክህሎቱ፣ በአመለካከቱ፣ እንዲሁም በሥነ ምግባሩ ብቁ የሆነና የተሟላ ስብዕና ያለው አመራር እና ባለሙያ ለማፍራት የሚያስችሉ ስልጠናዎችን በመስጠት የፍትህ ዘርፉን የማስፈጸም አቅም ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በፍትህ ሥርዓቱና በሕግ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ የሚደረጉ የማሻሻያ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ለመምራትና ለማስፈጸም የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተለያዩ ተቋማት በተበታተነ ሁኔታ ይሰሩ የነበሩ የሕግ ጥናትና ምርምር፣ አቅም ግንባታና፣ የፍትህ ማሻሻያ ተግባራትን በማጠቃለል በአንድ ተቋም እንዲከናወኑ ማድረግም ሆነ በተቋማቱ መካከል ያለውን የኃላፊነት ድግግሞሽ ማስቀረት ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ እንደሚረዳ በመገንዘብ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌደራል የፍትህና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1071/2010 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

   1. "የፍትህ አካላት" ማለት ፍርድ ቤትን፣ የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግን፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽንን እና የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደርን የሚያጠቃልል ሲሆን እንደ አግባብነቱ ከፍትህ እና ህግ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚያከናውኑ ሌሎች አካላትን ሊጨምር ይችላል፤

   2. "የፍትህ አካላት ባለሙያዎች" ማለት ዳኞችን፣ ዐቃብያነ ሕጎችን፣ ሬጅስትራሮችን፣ የፖሊስ እና ማረሚያ ቤት አባላትን እና ተከላካይ ጠበቆችን የሚያጠቃልል ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ሙያተኞችን ሊጨምር ይችላል፤

3. "የፍትህ መረጃ ትንተና" ማለት ከሕግ እና ፍትህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በማደራጀት እና በመተንተን የአገሪቱን የፍትህ ሥርዓት ትክክለኛና የተሟላ ገጽታ የሚያሳይ አስተማማኝ መረጃ የማቅረብ ሂደት ነው፤
4. "ክልል" ማለት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 47(1) የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
5. በዚህ አዋጅ ዉስጥ ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸ ለሴትም ያገለግላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ ሥልጣን እና ተግባራት

### 3. መቋቋም

1. የፌደራል የፍትህ እና የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡

### 4. ዋና መስሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡

### 5. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. ጥናት እና ምርምሮችን፡-

   ሀ) የአገሪቱን ህጎች የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትን በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ ለማዋል፣ የፍትህ እና የሕግ ሥርዓቱን ብቁና ዘመናዊ ለማድረግ፣ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና የእድገት አቅጣጫ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማትን ለማፋጠን በሚያስችሉበት ሁኔታ ለማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት፤ እና

ለ) የፍትህ አካላትን ዘመናዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ በፍትህ ሥርዓቱ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፤

እንዲረዳ ማካሄድ፡፡

2. የአገሪቱን የፍትህ ሥርዓት ትክክለኛና የተሟላ ገጽታ የሚያሳይ መረጃ እንዲኖር ማድረግ፤ የፍትህ እና የሕግ መረጃ ማዕከል መሆን፤

3. የፍትህ አካላት አመራሮችን እና ባለሙያዎችን በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት እና በሥነ-ምግባር በማነጽ የፍትህ ሥርዓቱ ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት እና ሥነ-ምግባር እንዲሁም ሕዝባዊ አመኔታና ተቆርቋሪነት ባላቸው እና ለሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱ መከበር በጽናት በሚቆሙ ባለሙያዎች የተገነባ እንዲሆን ማስቻል፤

4. የፍትህ ሥርዓት እና የሕግ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን እና ሌሎች በፍትህ ዘርፉ ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በማቀናጀት እና በማስተባበር ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ፡፡

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሕግ ማሻሻያና ማሟያ የጥናትና ምርምር መርሃ-ግብር በመንደፍ፡-

ሀ) በየዘርፉ ያሉ ነባር ሕጎችን ለማጠቃለል፣ ከወቅቱ የእድገት ደረጃ ጋር ለማጣጣም እና ለአጠቃቀም ምቹ ሆነው እንዲሻሻሉ ለማድረግ፤

ለ) የአገሪቱን የሕግ ሥርዓት ለማሟላት የሚያስችሉ አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት፤

ሐ) የሕግ ትምህርት እና ሥልጠናን ለማጠናከር፤

መ) የፍትህ አካላትን የሰው ሃብት ብቃት ለማሳደግ፣ አደረጃጀታቸውን እና አሰራራቸውን ለማሻሻል፤ እና

ሠ) ከሕግ ብዝሃነት ጋር የተያያዙ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች እና ሌሎች ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፤

የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፡፡

2. የፍትህ መረጃ ትንተና በማከናወን የአገሪቱ የፍትህ ዘርፍ ተልዕኮውን በአግባቡ እያሳካ መሆኑን ለማወቅ የሚያስችል አስተማማኝና የተሟላ መረጃ እንዲሁም በዘርፉ በአደረጃጀት፣ በሰው ሃብት ብቃት፣ በሃብት አቅርቦት፣ በአሰራር እና በሌሎች መስኮች የሚታዩ ክፍተቶችን ለማስተከካከል የሚያግዙ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

3. የፍትህ ሥርዓት እና የሕግ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን እና ሌሎች በፍትህ ዘርፉ ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ያቀናጃል፤ ያስተባብራል፤

4. ከክልል የሕግ ምርምር እና ስልጠና ማዕከላት ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚነት የሚኖረው የስልጠና ካሪኩለም ያዘጋጃል፤

5. ወደ ፌደራል የፍትህ ሥርዓት ለሚቀላቀሉ እንዲሁም ከክልሎች ጋር በሚኖረው ትብብር መሠረት የራሳቸው ስልጠና ማዕከል ለሌላቸው ክልሎች ጀማሪ የሕግ ባለሙያዎች የቅድመ ሥራ ስልጠና ይሰጣል፤

6. በፌደራል እና ከክልሎች ጋር በሚኖረው ትብብር መሠረት የራሳቸው ስልጠና ማዕከል በሌላቸው ክልሎች የፍትህ አካላት ውስጥ በማገልገል ላይ ለሚገኙ ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠና ይሰጣል፤

7. ለፍትህ ዘርፉ አመራር የሚሆን የስልጠና ፓኬጅ በማዘጋጀት ስልጠና ይሰጣል፤

8. የፍትህ ሥርዓቱን ለሚያገለግሉ በግል ለተሰማሩ ጠበቆች ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

9. ለሕግ ትምህርት ተቋማት መምህራን እና በፌደራል እና ከክልሎች ጋር በሚኖር ትብብር መሠረት በክልል የስልጠና ማዕከላት ለሚሰሩ አሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል፤ ብቃታቸዉን ያረጋግጣል፤

10. ከዓላማው ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የጥናትና ምርምር፣ ማማከር እና ስልጠና አገልግሎት ይሰጣል፤

11. የጥናትና ምርምር ውጤቶቹን ያሰራጫል፤ የሥልጠና ጽሁፎችን ያዘጋጃል፣ ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤

12. ሕግ እና ፍትህ ነክ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት የፍትህ መረጃ ማዕከል ያቋቁማል፤ እና

13. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## አደረጃጀት እና አሰራር

### 7. የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ ፡-

1. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣
2. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

### 8. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፡-

   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣን እና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ) ዕቅድ፣ መርሃ-ግብር እና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   ሐ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ መርሃ-ግብር መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   መ) የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የሌሎች የምርምር እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤

ሰ) ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣን እና ተግባራቱ በከፊል ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

9. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣን እና ተግባራት</u>

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

1. በኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት የሚመደቡበትን የሥራ ዘርፍ ይመራሉ፤ ያስተዳድራሉ፤

2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፤

3. ተለይቶ ካልተወከለ በስተቀር ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶት ይሠራል፡፡

10.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

1. በመንግስት የሚመደብ በጀት፤

2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ከሰበሰበው የውስጥ ገቢ የሚፈቀድ ገንዘብ፡፡

11.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

12.**አማካሪ ምክር ቤት**

1. የኢንስቲትዩቱን ተግባራት ለማቀናጀት እና ለማስተባበር የፌደራል የፍትህ አካላት በጋራ የሚሰሩበት አማካሪ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. አማካሪ ምክር ቤቱ፡-

   ሀ) የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች አካሄድ በሚመለከት ሃሳብ እና ምክር ይሰጣል፤ በትግበራ ወቅት ድጋፍ ያደርጋል፤

   ለ) በኢንስቲትዩቱ በኩል ለመንግስት በሚቀርቡ ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች፣ እቅዶች፣ በጀት፣ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቶች እና በዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርቡ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ሃሳብ እና አስተያየት ይሰጣል፤

   ሐ) በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ ጥናትና ምርምሮችን ይገመግማል፡፡
3. የአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማሉ፡፡
4. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የአማካሪ ምክር ቤቱ ጸሃፊ ይሆናል፡፡
5. አማካሪ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ይወስናል፤
6. ኢንስቲትዩቱ ለአማካሪ ምክር ቤቱ ሥራዎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

13.**መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

የፍትህና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት እና የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል መብት እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ወደ ኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

14.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

የፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩትን እና የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከልን ስልጣን እና ተግባር ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎች እና የተዘረጉ አሰራሮች በሌሎች መመሪያዎች እና አሰራሮች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

15.**የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

1. የፍትህ እና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 22/1990 እና የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 364/1995 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

16. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኢንስቲትዩቱ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

17. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ረ/ <u>ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች</u>

### <u>አዋጅ ቁጥር 79/1989</u>

### <u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት[24] ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማትና ለሕዝቦቿ ማህበራዊ ዕድገት መሠረት የሆነውን ግብርናን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያገለግሉ የግብርና ተክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ፣ አገር በቀል የሆኑትን ለማበልጸግና ከውጭ የተገኙትንና/የሚገኙትን ከአገሪቱ የግብርና ልማት ፍላጐት ጋር ለማጣጣም ምርምር ወሳኝነት ያለው የልማት እንቅስቃሴ በመሆኑ፤

---

[24] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) መሰረት "ድርጅት" የሚለው "ኢንስቲትዩት" በሚል ተተክቷል፡፡

ምርምር ለአገሪቱ የግብርና ክፍለ-ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ማደግ አስተዋጽኦ የሚኖረው በአንድ ወጥ ሥርዓትና በቅንጅት ሲራመድ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአጠቃላይም የአገሪቱን ወቅታዊና ዘላቂ የግብርና ልማት ፍላጐት በውጤታማ ምርምር ለማሟላት የሚያግዙ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ የማበልጸግና የማላሙድ የማስተባበር የመደገፍና የማበረታታት ተልዕኮ ኃላፊነት ያለው ድርጅት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 79/1989" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካልተፈለገ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "የግብርና ምርምር" ማለት በእጽዋት፣ በእንስሳት እና በተፈጥሮ ሀብት፣ መስክ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚከናወን ምርምር ነው፤
   2. "የተፈጥሮ ሃብት" ማለት አፈር፣ ደንን እና ከግብርና ጋር የተዛመደ ውሃን የሚያጠቃልል ነው፤
   3. "የግብርና ምርምር ማዕከል" ማለት በፌደራል መንግስት ወይም በክልል መስተዳድር የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም ወይም የሚተዳደር የግብርና ምርምር የሚያከናውን አካል ነው፤
   4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ኢንስቲትዩት ነው፡

3. **<u>መቋቋም</u>**

   1. የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
   2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል[25]።

4. **<u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

   የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ይሆናል።

---

[25] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(7)(ሀ) በግልፅ ሳይነገር ተሻሽሎ ተጠሪነቱም ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

5. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች፤

1. የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ ማበልጸግና ማላመድ፤
2. በግብርና ምርምር ማዕከላት ወይም በውል አማካይነት የግብርና ምርምር በሚያከናውኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች መሰል ተቋማት የሚካሄዱ የግብርና ምርምር ተግባራትን ማስተባበር፤
3. የግብርና ምርምርን ቀልጣፋ ውጤታማ እና በልማት ፍላጎት ላይ ያተኮረ ለማድረግ የሚያስችል አቅም መገንባት እና ስርዓት መዘርጋት፤
4. የግብርና ምርምር ውጤቶችን ለሕዝብ ማሳወቅ ናቸው።

6. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ ቀጥሎ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በሀገሪቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲዎች መሠረት የግብርና የምርምር ስትራቴጂ መንደፍና ቅደም ተከተል መወሰን፣ የሥራ ፕሮግራምና እቅድ ማውጣት፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በሚመለከታቸው ክፍሎች ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፤
2. የግብርና ምርምር ፖሊሲ አፈጻጸምን መከታተል፤ አዳዲስና የማሻሻያ የፖሊሲ ሃሳብ ማመንጨት፤ ለመንግሥት ማቅረብ ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ፤ ተግባራዊነቱን መከታተል፤
3. ከአገሪቱ የልማት ፍላጐት ጋር የሚጣጣም የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽና ለማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያ ማውጣት፣ እንደአግባቡም ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና በጀት መገምገምና በመመሪያው መሠረት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣ ለመንግሥት፣ አቅርቦ ማጸደቅ፤
4. በግብርና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት የግብርና ምርምር ማከናወን ወይም እንዲከናወን ማድረግ፤
5. ማንኛውም በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚተዳደር የግብርና ምርምር ማዕከል እንደገና እንዲደራጅና እንዲታጠፍ፥ አዲስ ማዕከላት እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ሥነ ምህዳሮች እንዲቋቋሙ‧ማድረግ፤

6. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ የግብርና ምርምር ውጤቶች ተጠቃሚው ክፍል እንዲያውቃቸው፣ በሥራ ላይ እንዲውሉ በፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ውጤታማ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት መዘርጋት፣ ተግባራዊ ማድረግ ተግባራዊነቱን መከታተል፤
7. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ ለማስፋፋት ከምርምር የተገኙ ጤቶችን ለማስተዋወቅ አመች በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ የብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የአህዝቦት ተግባር ማከናወን፤
8. በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱና የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማስባሰብ፥ ማከማቸትና ማሠራጨት፥ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት መገንባትና መምራት፤
9. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በግብርና ትምህርት፣ ምርምርና ሥርፀት፣ እንዲሁም ምርት እንቅስቃሴ መካከል የርስ በርስ መደጋገፍ እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
10.በግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና ያለውንም ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ ፣ በኢንስቲትዩቱ የተሰማራውን የሰው ኃይል አቅም ማሳደግና መገንባት የሚያስችል ስልት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፤
11.በግብርና ምርምር ጠቃሚ ውጤቶችን ላስመዘገቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት መዘርጋት፤ ሽልማት ወይም ማበረታቻ መስጠት፤
12.የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚደራጁበትንና የሚጐለብቱበትን መንገድ ማመቻቸት፥ መርዳትና ማበረታታት፤
13.የግብርና ተመራማሪዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችንየ ሚያበረታታ አመቺ የሥራ ሁኔታዎችን መፍጠር፥ ተመራማሪዎችን በተመለከተ በሙያ ላይ የተመሠረተ የዕድገት መሰላል መዘርጋት፣ማ ሻሻል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ፤

14. በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያተኞች ማህበራትን ማበረታታት፣ እንዲሁም ለግብርናው ምርምር በመረጃዎች ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
15. የግብርና ምርምርን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ መሳተፍና መንግሥትን ማማከር፤
16. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መመስረት፥ ትብብር ማድረግ፤ ስምምነቶችን መፈራረም፥ተግባራዊ ማድረግ ወይም ተግባራዊነታቸውንም መከታተል፤
17. ለክልል የግብርና የምርምር ማዕከላት ተገቢውን የመረጃ አገልግሎት መስጠት፥ ጥያቄም ሲቀርብ አቅሙ በፈቀደ መጠን የቴክኒክ ድጋፍና እገዛ ማድረግ፤
18. በፌዴራልና በክልል የምርምር ማዕከላት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽና የሀብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ግምገማ ሥርዓት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት፤
19. በግብርና ምርምር ላይ የተሰማራ ወይም የሚሰማራ ማንኛውንም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን መያዝ፤
20. የንብረት ባለቤት መሆን፥ ውል መዋዋል፥ መክሰስና መከሰስ፤
21. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን።

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ፦

1. የግብርና ምርምር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም ዋና ዲሬክተር፤
3. በፌዴራሉ መንግሥት የተቋቋሙ ወይም የሚቋቋሙ የግብርና ምርምር ማዕከላት እንዲሁም፤
4. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንናተግባራት በበላይነት ይመራል፣ የአዋጁን አፈጻጸም በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤
2. የኢንስቲትዩቱን መዋቅርና የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ያጸድቃል፤
3. የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ይመረምራል፤ ለመንግሥት ቀርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤
4. በፌዴራልና በክልል የግብርና ምርምር ማዕከላት መካከል ሊኖር የሚገባውን የሥራ ግንኙነት አግባብ ካለው የክልል መስተዳድር ጋር በመመካከር ይወስናል፤
5. የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፤ አባላቱን ይሰይማል፤ ለሚቀርቡ የምርምር ሃሳቦች፤ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በጀት ከመፈቀዱ በፊት የቴክኒክ ግምገማ ሪፖርት ከኮሚቴው ይቀበላል፤ ይወስናል፤
6. የራሱን ውስጠ ደንብ ያወጣል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

11. <u>የዋና ዲሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዲሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዲሬክተሩ፦

ሀ/ የፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከላትን የፕሮግራምና የፕሮጀክት አፈጻጸም፣ የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤

ለ/ ቦርዱ በሚያጸድቀው መመሪያ እና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል

ሐ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶና አጠናቅሮ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በጸደቀው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ለምርምር ማዕከላት ይመድባል፤ የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ቦርዱ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናቅሮ ለቦርዱ ያቀርባል።

3. ዋና ዲሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ከተግባሩ በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል ።

12.<u>የፌዴራል የግብርና ማዕከል ሥልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከል ተጠሪነት ለኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአገሪቱ የግብርና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም በማዕከሉ እንዲካሄዱ በተነደፉ ፕሮግራሞች መሠረት የውስጥ አስተዳደርና የቴክኒክ ነጻነት ኖሮት የግብርና ምርምር ተግባራትን ማከናወን ፤
2. በማዕከሉ የሚከናወኑ የምርምር ተግባራትን በሚመለከት ሪፖርት ማዘጋጀት ፥ የተዘጋጀውን ሪፖርት ለዋናው መሥሪያ ቤት ማቅረብ፤
3. ማዕከሉ እንዲያከናውን በተፈቀደለት ፕሮግራም መሠረትዝ ርዝር የምርምር ፕሮጀክቶችንና በጀት ማዘጋጀት፤ ሲፈቀድም ተግበራዊ ማድረግ፤
4. የማዕከሉን የወደፊት አቅጣጫና እድገት በመተለም የሚያስፈልጉ የማቴሪያልና የሰው ኃይል በማዘጋጀት ለዋና መሥሪያ ቤቱ ማቅረብ

5. በዋና መሥሪያ ቤቱ በኩል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

13.<u>የገቢ ምንጭ</u>

1. ኢንስቲትዩቱ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ገቢ ይኖረዋል

ሀ/ መንግሥት ከሚመድብለት በጀት፤

ለ/ ከቤተ ሙከራ አገልግሎት ወይም ከምርምር ተረፈ ምርት ሽያጭ፤ እንዲሁም

ሐ/ ከማናቸውም ሌላ ምንጭ የሚገኝ ገቢ፣ ዕርዳታና ስጦታ፡፡

2. ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም በሚወክለው ሌላ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ በመንግሥት የፋይናንስ ሕግ መሠረት ለኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ይውላል ፡፡

14.<u>ስለሂሣብ መዝገብ</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትይይዛል፡፡

2. ኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብቱን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላአ ዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል ፡፡

15.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት ፡፡

16.<u>የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጐች</u>

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል

ሀ) የእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ትዕዛዝ ቁጥር 42/1958፤ እና

ለ) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 12(5) ድንጋጌ ውስጥ የምርምር ማዕከላትን የሚመለከተው ገጽታ፡፡

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

17.<u>ስለመብና ግዴታ መተላለፍ</u>

1. የእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታ፤

2. በግብርና ሚኒስቴር ሥር የሚተዳደሩ የደን ምርምር፣ የደን ውጤቶች አጠቃቀም ምርምር፣ የአሣ ምርምር፣ የአፈር ጥናት ላቦራቶሪ እና ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምር ተቋማት መብትና ግዴታ፤ እንዲሁም

3. በዓለማያ ግብርና ዩኒቨርስቲ ስር የሚተዳደረው የደብረዘይት የምርምር ማዕከል መብትና ግዴታ፤

በዚህ አዋጅ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፏል ።

18. <u>**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት 28 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 28 ቀን 1989 ዓ.ም**

**ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## <u>አዋጅ ቁጥር 274/1994</u>

## <u>የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ[26] ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

በገጠርና በከተማ የሚኖረው ሕዝብ በአካባቢው ሀብት ላይ በመመስረት የተለያዩ ዓይነቶችና ደረጃዎች ባላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የሚገጥመውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግር በጋራ እንዲፈታና በራሱም እንዲተማመን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

[26] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) "ኮሚሽን" የሚለው "ኤጀንሲ" በሚል ተተክቷል፡፡

ይህንን ዓላማ ለማስፈጸም በፌዴራል ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማሕበራትን የሚመዘግብና በአገሪቱ ውስጥ ላሉ ሕብረት ሥራ ማህበራት እገዛ የሚያደርግ፣ ሥልጠና የሚሰጥ፤ ምርምር የሚያደርግና ሌሎች ቴክኒካዊ ድጋፎችን የሚሰጥ የፌዴራል መንግሥት አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) እና በሕብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 55 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 274/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው እራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
   2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለገጠር ልማት ሚኒስቴር[27] ይሆናል።

3. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል።

4. **የኤጀንሲው ዓላማ**

   የኤጀንሲው ዓላማ በገጠርና በከተማ የሚኖረው ሕዝብ በአካባቢው ሀብት ላይ በመመሥረት የተለያዩ ዓይነቶችና ደረጃዎች ባላቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት እየተደራጀ የሚገጥመውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በጋራ እንዲፈታ እና በራሱም ላይ እንዲተማመን ማድረግ ይሆናል።

5. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**

   ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

   1. ለሕብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴና ዕድገት የሚበጁ የፖሊሲ ሃሣቦችንና የሕግ ረቂቆችን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

[27] ተጠሪነቱ በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(7)(ለ) በግልፅ ሳይነገር ተሻሽሎ ተጠሪነቱም ለእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

2. የሕብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረትና በዓለም አቀፍ የሕብረት ሥራ መርሆዎች መሠረት እንዲራጁ ያበረታታል፤
3. በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋመውን የሕብረት ሥራ ማሠልጠኛ ተቋም ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤
4. ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማኅበራት ወደ ዘመናዊ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚያድጉበት ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ የጥናቱንም ውጤት ያስተዋውቃል፤ ያሰራጫል፤ በተግባር መተርጐሙንም ይከታተላል፣
5. የሕብረት ሥራ ዕሴቶች፣ መርሆዎች፣ አደረጃጀት እና ጠቀሜታ በኅብረተሰቡና በትምህርት ተቋማት ይበልጥ እንዲታወቁ ያደርጋል፤
6. በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ፡-
   ሀ/ በልዩ ባህርያቸው ምክንያት በክልላዊ ማህበር መደራጀት የማይችሉና በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መሠረታዊ ማኅበራት የሚያቋቁሙትን ሕብረት ሥራ ማህበር፤
   ለ/ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚገኙ ክልላዊ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚያቋቁሙትን ሕብረት ሥራ ማኅበር
   ሐ/ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት የተደራጁ ማኅበራት በጋራ የሚያቋቁሙትን የሕብረት ሥራ ማህበር ወይም በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ለ/ መሠረት የተደራጁ የተለያዩ ማኅበራት በጋራ የሚያቋቁሙትን ሕብረት ሥራ ማኅበር ይመዘግባል፣ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣
7. በፌዴራል ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ ይመረምራል፤ ሂሣብ አጣሪም ይመድባል፤ ሲፈርሱም ከመዝገብ ይሰርዛል፤ በመላ ሀገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤
8. የሕብረት ሥራ ማኅበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ በሀገር ውስጥ ሸማቹና አምራቹ በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

9. የሕብረት ሥራ ማኅበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት ወይም ዋጋ እንዲኖራቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እና የእጅ ጥበብ ምርቶች እንዲያድጉ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤
10. የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል የሚያስችል በባሕሉና በልምዱ ላይ የተመሠረተ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት እንዲኖር የሙያ እገዛ ያደርጋል፣
11. ለሕብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት የሚበጁ ፕሮጀክቶችን በማጥናትና በማዘጋጀት እንደአስፈላጊነቱ ከክልሎች ጋር በመተጋገዝ ማኅበራት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤
12. በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የምርት፣ የገበያ ኢንፎርሜሽንና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
13. በክልል ለሚደራጁ ቢሮዎችና የሕብረት ሥራ ማኅበራት የቴክኒክና የሙያ እገዛ ያደርጋል፤
14. የሕብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴን እና ዕድገትን ለማፋጠን ከሕብረት ሥራ ማኅበራት ጋር ግንኙነት ካላቸው የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤
15. እንደየኅብረት ሥራ ማኅበራቱ ዓይነትና ደረጃ ሊለዋወጥ የሚችል የማህበራት ሞዴል የመተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፣ ስለሥራው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፣
16. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከስሳል፣ ይከሰሳል፤
17. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

6. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

1. ኤጀንሲው በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር[28]፤ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

7. <u>ስለዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

[28] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) "ኮሚሽነር" የሚለው "ዋና ዳይሬክተር" በሚል ተተካ፡፡

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተመለከተውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፣
   ለ/ በፌዴራሉ የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራሞችና በጀት ያዘጋጃል፤ሲፈቀድም በሥራ ላይ
   መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፣
   ረ/ ስለኤጀንሲው የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተሳልፍ ይችላል።

8. <u>ስለምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፡-

1. ዋና ዳይሬክተሩ በማይገኝበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶ የኤጀንሲውን ሥራ ይሠራል፤
2. በተጨማሪ ከዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል።

9. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው ገቢ፡-

ሀ/ በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤

ለ/ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ከሚገኝ እርዳታና ክሌሎች ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡

10. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትይይዛል።

2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

11. **ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

12. **መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ገዳዮችን በተመለከተ የሌሎች የመንግሥት አካላት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

13. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከግንቦት 6 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 6 ቀን 1994 ዓ. ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 198/2003**

**የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 198/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤
2. "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤[29]
3. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

**ክፍል ሁለት**

**የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት**

3. **መቋቋም**

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኃላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

4. **የምክር ቤቱ አባላት**[30]

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

   ሀ/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ............. ሰብሳቢ

   ለ/ በሰብሳቢው የሚሰየሙ አግባብ ያላቸውን ሚኒስቴሮች የሚመሩ ሚኒስትሮችና አግባብ ያላቸው የክልል መንግሥታት ኃላፊዎች.... ...አባላት

   ሐ/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ..............................ጸሐፊ
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች የፌዴራልና የክልል ባለሥልጣኖች እንዲሁም የኤክስፐርት አስተያየት እንዲያቀርቡ የሚጋበዙ ባለሙያዎች በምክር ቤቱ ስብሰባ እንዲሳተፉ ሊፈቀድ ይችላል።

5. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

[29] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 9(7) የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[30] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) በ22/51(2008) ደ. 380/2008 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሰርዞ ነባሮቹ ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) እንደቅደም ተከተላቸው ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

ሀ/ የግብርና ልማትን ውጤታማነት የሚገቱ መሰረታዊ ማነቆዎች እንዲለዩ፣ የሚፈቱበት ስልት በአግባቡ እንዲቀመጥና በውጤታማነት እንዲተገበር የሚያስችል አመራር ይሰጣል፤

ለ/ በግብርና ልማት ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ከፍተኛ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫና አመራር ይሰጣል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን ዕቅድ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይገመግማል ፣ እንደአስፈላጊነቱ የስራ መመሪያ ይሰጣል።

መ/ ምክር ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

6. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

1. ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል አስፈላጊ ሲሆን በሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰበ ሊያደርግ ይችላል።[31]
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ይችላል።

## ክፍል ሶስት

## የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

7. **መቋቋም**

1. የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ይሆናል።[32]

8. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፎችን ሊከፍት ይችላል።

---

[31] በ22/51(2008) ደ.380 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

[32] በ22/51(2008) ደ.380 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡

9. **የኤጀንሲው ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. የግብርና ልማትን ቀጣይነት ለማረጋገጥና መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ማፈላለግና ተግባራዊነቱን መደገፍ፤
2. የግብርና ልማት አፈጻጸም ውጤታማነት እንዲረጋገጥ በግብርና እና ተዛማጅ ተቋማት መካከል እንዲሁም የግብርና ልማትን ለመደገፍ በሚቀረጹና በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲኖር ማድረግ።

10. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**[33]

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤
2. የሰብልና እንስሳት ሀብት ግብርና ምርትና ምርታማነት መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩና የሚፈቱበት ስልት እንዲነደፍ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
3. ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን ግብይት ለማሳደግና እሴት ለመጨመር የግብርና ንግድና ግብይትን መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩ ያደረጋል፣ የመፍትሄ ሃሣብ ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
4. ዘላቂና አሳታፊ የሆነ የአካባቢ ጥበቃና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፤ አፈጸጸሙንም ይከታተላል፤
5. ግብርናን አስመልክቶ የሚከናወኑ ሥራዎችን በአግባቡ ለመፈጸምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ተቋማዊ አቅምን ለማሳደግ መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩ ያደርጋል፤ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርበል፤ አፈጸጸሙንም ይከታተላል፤

[33] የዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ ንዑስ አንቀጽ (9) ያሉት በ22/51(2008) ደ.380 አንቀፅ 2(4) ተሠርዘው በአዲስ ንኡስ አንቀጾች (2) እስከ (8) ተሻሽለው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (10) እና (11) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጾች (9) እና (10) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

6. የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማቀላጠፍ በትኩረት የሚፈፀሙና ቅድሚያ የተሰጣቸው ተግባራትን ዝርዝር ያዘጋጃል፤
7. በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ መሠረት ከምክር ቤቱ በሚቀርብበት ጥያቄ መሠረት ፕሮጀክቶችን ያስተዳድራል፤ ይመራል፤
8. የግብርና ልማት አፈጻጸምን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረጹ ፕሮጀክቶች መካከል መልክዓ ምድርን መሠረት ያደረገ ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
10. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

11. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፡-

1. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

12. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባራት</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤[34]
   ሐ/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
   መ/ ኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

---

[34] በ22/51(2008) ደ.380 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡

ሠ/ ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የስራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

13.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤

1. የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጠውን ስራ ያከናውናል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

14.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

15.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

16.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ ከታህሳስ 22 ቀን 2003ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም።**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 272/2005 ዓ.ም

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 272/2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 ነው፤
2. "የእንስሳት መድኃኒት" ፣ "መኖ" እና "የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር" በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጣቸዉን ትርጉም ይይዛሉ።
3. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[35]
4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስአበባንና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
5. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለስልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ባለስልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል[36]።

4. **ዋና መስሪያ**

የባለስልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

---

[35] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 9(8) መሰረት የእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

[36]በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(8)(ሀ) ለእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

የባለሥልጣኑ ዓላማ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና ጤናማ የእንስሳት ምርት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲቀርብ ማስቻል ይሆናል።

6. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 20 እና አግባብ ባላቸው ሌሎች አንቀጾች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያዉላል፤

ለ/ በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበሰባል፤

ሐ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል

መ/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

2. ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል አግባብ ላላቸዉ የክልል አካላት ዉክልና ሊሰጥ ይችላል።

7. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፦

1. አማካሪ ቦርድ፤
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ይኖሩታል።

8. <u>የአማካሪ ቦርዱ አባላት</u>

አማካሪ ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

1. በሚኒስትሩ የሚሰየም ኃላፊ .......... ሰብሳቢ፤
2. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ ......... አባል፣
3. አግባብ ካላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የሙያ ማኅበራት እና የተጠቃሚዎች ማኅበራት ተውጣጥተው በሚኒስትሩ የሚሰየሙና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ሰዎች ............... አባላት።

9. <u>የአማካሪ ቦርድ ተግባርና ኃፊነት</u>

አማካሪ ቦርዱ፦

1. የእንስሳት መድኃኒት ደህንነትና ፈዋሽነት እና የመኖ የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ሥርዓትን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች ፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ዝግጅትና አፈጻጸም፤

2. የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ወይም የጥራት ደረጃውን ያላሟሉ የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎችና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች በአግባቡ በሚወገዱበት ሥርዓት፣ እና
3. የእንስሳት መድኃኒትና መኖን በሚመለከቱዓ ለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር፤ ላይ የማማከር ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

10.**የአማካሪ ቦርዱ ስብሰባዎች**

1. አማካሪ ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።
3. ከግማሽ በላይ የሚሆነው የአማካሪ ቦርዱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
4. የአማካሪ ቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አማካሪ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.**የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የባለሥልጣኑን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለባለስልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ አፈጸጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ

ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለስልጣኑ ሌሎች ኃፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ባስሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u> ደንቡ የሚፀናት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሀዳር 25 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 304/2006</u>**

**<u>ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 35 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 304/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. “የቆላ ዝንብ” ማለት የእንስሳት ደም ብቻ የሚመገብና የገንዲ በሽታ ህዋስን ከእንስሳ ወደ እንስሳ የሚያስተላልፍ ነፍሳት ነው ፤
2. “እንስሳ” ማለት ማንኛውም የቤት ወይም የዱር እንስሳ ነው፤
3. “የገንዲ በሽታ” ማለት በደም ውስጥ በሚኖሩ ጥገኛ ተህዋስያን የሚመጣ በሽታ ነው፤
4. “ተህዋስ” ማለት የገንዲ በሽታ መንስዔ የሆነ ባለአንድ ህዋስ የደም ውስጥ ጥገኛ ወይም ፕሮቶዞዋ ነው፤
5. “የገንዲ መድኃኒት” ማለት የገንዲ በሽታን ለማከም ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ንጥረነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውሁድ ነው፤
6. “ባዮሎጂካል” ማለት ለላብራቶሪ ምርመራና ለቆላ ዝንብ እርባታ አገልግሎት የሚውል ሪኤጀንት፣ የዝንብ ዘርና የእንስሳ ደምን ያጠቃልላል፤
7. "ቴክኖሎጂ” ማለት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ዓይነት ዘዴ ነው፤
8. "የልህቀት ማዕከል” ማለት የቴክኖሎጂ ማመንጫ፣ መጠቀሚያ፣ ማሰራጫና የዕውቀት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው፤
9. "ሚኒስቴር” ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤[37]
10. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል የመንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል[38]።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተጠቁ የአገሪቷ አካባቢዎችን

---

[37] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 9(8) መሰረት የእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡
[38] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(8)(ሐ) ተሻሽሎ ለእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

ከችግሩ ነፃ በማድረግ፣ የእንስሳትና የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እና ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳት ምርት ለተጠቃሚ እንዲቀርብ በማድረግ ህብረተሰቡን በምግብ ራሱን በማስቻል ሂደት ተገቢውን አስተዋፆ ማድረግ ይሆናል።

6. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራትይኖሩታል፦

1. ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን ይለያል፣ ይገመግማል፣ ይመዝናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፤
2. ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ጋር በተያያዘ መመሪያዎችን ያወጣል፤
3. በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተጠቁ አካባቢዎችን በመለየት ለስራ በሚያመች መልኩ ያደራጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም ይሠራል፤
4. በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራ የልህቀት ማዕከል በመሆን የአገር ውስጥና ዓለምአቀፍ ስልጠናዎችና የአቅም ማጎልበቻ መርሀ ግብሮችን ያዘጋጃል፤
5. ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች፣ የላብራቶሪ ዕቃዎች፣ የመስክ መገልገያዎች፣ ቋሚ ዕቃዎችና አላቂ ዕቃዎች ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፤
6. የአገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍና ለማስፋፋት የሚረዱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
7. በዘርፉ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ካላቸው የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር አቅሙን ይገነባል፤
8. አሠራሩን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዘርፍ የተደረጉ አዳዲስ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብና በማጣጣም ጥቅም ላይ ያውላል፤
9. የቆላ ዝንብ፣ የገንዲ በሽታ፣ የሶሾ-ኢኮኖሚና አካባቢያዊ ሁኔታ መረጃ ይሰበሰባል፤ መረጃውን መሰረት በማድረግ፦

   ሀ/ የቁጥጥር ዘዴዎችና ስልቶችን ይለያል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤቱን ይገመግማል፤

ለ/ በዘርፉ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ የወቅታዊ መረጃዎች ተደራሽነትን ያረጋግጣል፤

ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መረጃዎችን ለባለሙያዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

10. ለእርባታና ለምርምር የሚሆኑ የቆላ ዝንቦችና ሌሎች ባዮሎጂካል ውጤቶችን የአገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ወደ አገር ውስጥ ያስገባል፣ ይጠቀማል፤ ወደ ውጭ አገርም ይልካል፤

11. የቆላ ዝንብ ዕርባታ፣ የጥራት ቁጥጥርና ምርምር በማካሄድ ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን ያመርታል፣ አምክኖ መስክ ላይ ይለቃል፣ ይከታተላል፤

12. ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ መስራት የሚፈልጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሊሳተፉ የሚችሉበት መስፈርት ያዘጋጃል፤ በመስፈርቱ መሰረት እንዲሳተፉ ይፈቅዳል፣ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ከመስፈርቱ ውጭ የሚሰሩትን ያግዳል፤

13. ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ወይም ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችና መድሃኒቶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ የአገልሟሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ኬሚካሎችና መድሃኒቶች ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፤

14. የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በራሱ ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

15. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>**

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራዎች ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ)
2. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የምክር ቤቱ አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የምክር ቤቱ ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል።

9. <u>**የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**</u>

ምክር ቤቱ፦

1. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት እንዲቻል የቁጥጥርና ማጥፋት ስራዎችን ለመተግበር የሚያስፈልጉ በኢንስቲትዩቱ የሚዘጋጁ ስትራቴጂዎችንና እቅዶችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤
2. በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤
3. የኢንስቲትዩቱን እቅድ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ ይገመግማል፣ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል።

10. <u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. ምክር ቤቱ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አብዛኞቹ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>**የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ስራ ላይ የሚስማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኢንስቲትዩቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

መ/ በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ይመደባል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብመ ዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 20 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

## ደንብ ቁጥር 364/2008 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 39 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 364/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "የቡናና ሻይ ልማት" ማለት የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እና ጥራትን ለማሻሻል በምርምር የተገኙና በአምራቹ ተፈትሸው ውጤታማ የሆኑ ከዘርና ችግኝ ዝግጅት ጀምሮ ያሉትን የቅድመ ምርት እና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን በተገሊጋይ ተኮርና ተሳትፏዊ

የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ለቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም አምራች አርሶ አደሮች፣ አልሚ-ባለሃብቶች፣ ጥምር እርሻ አርሶ አደሮች እና ምርት አዘጋጆች በፍጥነትና በስፋት ተደራሽ ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት ድምር ነዉ፤

2. “የቡናና ሻይ ግብይት” ማለት በአምራቹና በአቅራቢው ወይም በላኪው፣ ወይም በአቅራቢውና በላኪው፣ ወይም በአቅራቢው ወይም በላኪውና በጅምላ ነጋዴው፣ ወይም በላኪውና የውጭ ሀገር ገዥው፣ ወይም በጅምላ ነጋዴውና በቸርቻሪው፣ ወይም ቸርቻሪውና ተጠቃሚው መካከል የህጋዊ ንግድ አሰራርን ተከትሎ የሚከናወን የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርትና የአገልግሎት ሽያጭና ግዥ ሂደት ነው፤

3. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት ቡናን፣ ሻይን ወይም ቅመማ ቅመምን በአልሚ ባለሀብት ለማምረት፣ ወይም ለመግዛት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ወይም የማጓጓዝ፣ የመቁላት፣ የመፍጨት እና የማሸን አገልግሎት ለመስጠት ወይም ከቡና፣ ከሻይ ወይም ከቅመማ ቅመም ግብይት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራት ላይ ለመሰማራት ብቃት መኖሩን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ነዉ፣

4. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡

5. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተዉ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል።

6. “ሰው” ማለት ማንኛዉም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠዉ አካል ነው፡

7. ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ “ባለሥልጣን” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

2. የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሀገር ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. አነስተኛ ይዞታ ባለው አርሶ አደር እና በአልሚ ባለሀብት የሚለማ ቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም በቴክኖሎጂ፣ በተሻሻለ እና ዘመናዊ አሰራር ከመሰረቱ እንዲለወጥ ተሳትፏዊ የኤክስቴንሽን ድጋፍ በማጠናከር የሰብሎቹ ምርት እና ምርታማነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማስቻል፤
2. አርሶ አደሩን፣ አልሚ ባለሀብቱን እንዲሁም ነጋዴውን ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ በጥራት ላይ የተመሰረተ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ግብይት ሥርዓት በመዘርጋት፣ ሀገራችን ባላት ልዩ ጣዕም ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ላይ እሴት በመጨመር በሀገር ውስጥና በዓለም ገበያ ላይ በማስተዋወቅ ለሀገሪቱና ለዘርፉ ተዋንያን የተሻለ ገቢ የሚገኝበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
3. በአርሶ አደሩ እና የግሉ ዘርፍ የቡና፣ የሻይ እና ቅመማ ቅመም ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች እና የአርሶ አደሮችና የግል ኩባንያዎች ምርት ማከማቻ መጋዘኖች፤ ግንባታ አስፈላጊ ብቃትን ፣ ቀልጣፋ የግብይት አገልገሎትን በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ ምርት በዘላቂነት ማቅረብን እና ዘመናዊ ምርት ክምችት አያያዝን እንዲሁም አካባቢ ጥበቃንና ዘላቂነት ያለው ልማትን ባገናዘበ መልኩ መካሄዱን እና ሥራ ላይ መዋላቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መደገፍ፣ መከታተልና መቆጣጠር ነው።

6. **የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በሀገሪቱ ዘመናዊ የቡናና ሻይ እንዲሁም የቅመማ ቅመም ሰብሎች ልማትና ግብይትን ለማስፋፋት፣ ለማጠናከርና መልካም ተሞክሮዎችን ለመቀመር የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዳስፈላጊነቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮችን በማሳተፍ ያዘጋጃል፣ በሚኒስቴሩ ይሁንታ ሲያገኝ ለመንግስት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2. የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትንና ግብይትን በቀጣይነት ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚረዱ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች በጥናት ላይ ተመስርቶ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
3. ከክልሎች፣ ከምርምርና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር አርሶ አደሮች፣ አልሚ ባለሀብቶች እና የንግዱ ማህበረሰብ በቡና፣ሻይ እና በቅመማ ቅመም ልማት፣ ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አቅማቸውን በቀጣይነት ለማሳደግ የሚያስችል አገልግሎት በመስጠት የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች እና መልካም ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤታማነታቸውንም ይከታተላል፤
4. የቡና፣ሻይና የቅመማ ቅመም ምርት ማሳደጊያ እና ማዘጋጃ ግብዓቶችን፣ ማሽነሪዎች፣ የምርት ማሸጊያዎችንና የጥራት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ለአምራቾች፣ ምርት አቅራቢዎች፣ ለአዘጋጆች፣ለላኪዎች፣ ለቡና ቆይዎች እና ጅምላ ነጋዴዎች በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ የሚቀርቡበት አሠራር የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣
5. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ዘመናዊ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት ለማስፋፋትና ዘርፉን ለማጠናከር፣ በእሴት ሰንሰለት በተግባር የሚታዩ ማነቆዎችን ለመለየትና ለመፍታት የሚያሰችሉ ጥናቶችን የጥናት ግኝት ውጤቶች ሥራ ላይ የሚውሉበትን ስልቶችና አሠራሮችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ላይ እሴት መጨመር፣ ንግድ ወይም ዝግጅት ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶችንና ነጋዴዎችን በተመለከተ በሕግ ለሌላ አካል የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣ ዝርዝራቸውንም ለንግድ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፤
7. ሥራ ላይ ባለው ሕግ ለምርት ገበያ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገራችንን የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርት በሕግ ኃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት ጋር በመተባበር ልዩ ባህርይ በጥናት ይለያል፣ የብሔራዊ ጥራት ደረጃን

ይወስናል፣ የንግድ ምልክትና የብራንድ ስያሜ ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

8. ወደ ውጭ የሚላኩ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ምርቶችን እንዳስፈላጊነቱ የጥራትና ጣዕም ምርመራ በማድረግ ደረጃ፣ ኤክስፖርት ሽኘት አገልግሎት እንዲሁም ለቡና ላኪዎች የዓለም ቡና ድርጅት መለያ ቁጥርና የምርት ሀገር ሰርቲፊኬት ይሰጣል፤

9. የቡና፣ ሻይ እና የቅመማ ቅመም ምርቶችን ዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይደግፋል፣ ይከታተላል፤ የምርቶቹን ሕገ-ወጥ ግብይትና ዝውውርን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣

10. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ወጪ ንግድ በነባርና አዳዲስ ገበያዎች የሚያድግበትን አሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ውጤታማ የገበያ ማስፋፊያ ሥራ ይተገብራል፣ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ክምችትና ኮንትራትን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

11. በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት ወቅታዊ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የምርትና ግብይት መረጃዎችን ይሰበሰባል፤ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ትንበያዎችን ያካሂዳል፣ በየወቅቱም ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ወቅታዊ ገበያ ሁኔታ ላይ የምክር አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ይሰጣል፡

12. የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ብቃት እና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚያሻሽሉ አሰራሮችን ያስተዋውቃል፣ የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም በተመለከተ ልዩ የማሰልጠኛ ማዕከል በመክፈት በአጫጭርና መካከለኛ ሥልጠናዎች ለባለሙያዎች፣ ለአምራቹና ለነጋዴው አቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሙያተኞችንና የተቋማት የብቃት ደረጃ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

13. በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ ተጠቃሚነታችንን ለማሳደግ በምርቶቹ ላይ እሴት ለመጨመር የሚያስችል ሀገራዊ አቅም እንዲገነባ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤ በምርቶቹም ወደ ዓለም ገበያ ለመግባት የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

14. አግባብ ባለዉ ሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸዉ አካላት ጋር በመተባበር የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም የአቅርቦትና ኤክስፖርት ጥራት ደረጃ አመዳደብና አጠባበቅ መመሪያ ያወጣል፣ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፤ የምርቶቹ ጥራትና ጣዕም ምርመራ ማዕከላትን አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች ያቋቁማል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ጥራትና ጣዕም ምርመራ አገልገሎት ለሚሰጡ ተቋማት እውቅና ይሰጣል፣
15. ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይትን አስመልክቶ ሀገሪቱ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ግዴታዎች ይፈፅማል፣ በሚደረጉ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስብሰባዎች እና በሚካሄዱ መድረኮች በመገኘት ሀገራችን በቡና፣ በሻይና በቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት ያላትን ተጠቃሚነት ለማስጠበቅ ይሠራል፤
16. የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት አቅምን የሚያሳድጉና የሚያጠናክሩ የባለድርሻዎች ፎረምችን ያቋቁማል፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ኮንፍረንሶችና ጉባኤዎችን ያዘጋጃል፣ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በሚደረጉ መሰል ዝግጅቶች ላይ ይሳተፋል፤
17. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ይከሰሳል፤
18. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የባለስልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፡-

1. አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግሥት የሚሾሙአንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል።

8. <u>የቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ ስብሳቢውን ጨምሮ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ ተቋማት የተውጣጡ፣ የቡና አምራች ገበሬዎች፤ የህብረት ሥራ ዩኒየኖች እና የግሉን ዘርፍ የሚወክሉ በሚኒስቴሩ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

2. የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ድምጽ የማይሰጥ የቦርድ አባል ይሆናል።
3. ማንኛውም የቦርድ አባል ሥራ ዘመን አምስት አመት ይሆናል ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን ለተጨማሪ አንድ ዙር እንደገና ሊሰየም ይችላል።
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ኃላፊዎች ወይም ሙያተኞች የኤክስፐርት አስተያየት እንዲያቀርቡ ቦርዱ ስብሰባ እንዲሳተፉ ሊጋበዙ ይችላሉ።

9. **<u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የባለሥልጣኑን የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አቅድ ለማዳበር የሚያስችል ሀሳብ ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
2. በቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት በሂደት የሚከሰቱትን ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ማነቆዎች ተለይተው እንዲጠኑ ምክረ-ሀሳብ ለባለሥልጣኑ ይሰጣል፤
3. የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ልማት እና ግብይትን ውጤታማ ለማድረግ በዘርፉ የሚገኙትን መንግስታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና የግሉን ዘርፍ ተዋናዮች ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችሉ ምክረ-ሀሳቦችን ያቀርባል፤ ተግበራቸውንም ይደግፋል፤
4. የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ግብይት እና እሴት የመጨመር ተግባር ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል በሚዘጋጁ ሀገራዊ ስትራቴጂዎች ላይ ሀሳብ ያቀርባል፤ የዘርፉ ተዋናዮች በብቃት እንዲሳተፉ አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤
5. ባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት እንዲችል ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፤ በተገቢው መልኩ ያማክራል፤ ይደግፋል።

10. **<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>**

1. ቦርዱ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢዉ በኩል በሚደረግ ጥሪ በማናቸዉም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ዉሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣን ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ /የባለሥልጣኑን ሠራተኞች በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ህግ ደንብ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ እና ለገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   መ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲደረግ ያደርጋል፤

   ሠ/ ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፡

   ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩና ለገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ሠራተኞች በዉክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. **መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

15. **ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸዉም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

16. **ደንቡ የሚፀናበት ግዜ**

ይህ ደንብ ከህዳር 15 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ቀን ታህሳስ 4 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 383/2008**

**የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀፅ 5 እና 39 መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕሰ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 383/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት" ማለቅ በአገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርምር ተግባር የተሰማሩ ተቋማት ስብስብ ነው፤
2. "ተቋም" ማለት ግብርና ምርምርን እንዲያካንድ በሕግ የተፈቀደለት የፌዴራል የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ ወይም መንግስታዊ የልማት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

3. "ግብርና ምርምር" ማለት በእንስሳት እና በተፈጥሮ ሀብት መስክ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚከናወን ምርምር ነው፤
4. "የተፈጥሮ ሀብት" ማለት አፈርን፣ ደንን እና ከግብርና ጋር የተዛመደ ውሃን የሚያጠቃልል ነው።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

### 4. ዓላማ

የምክር ቤቱ ዓላማ ቅንጅትና የምርምር ትብብር በመፍጠር የግብርና ምርምር ሥርዓቱ ቴክኖሎጂና ዕውቀት በማቅረብ ለሀገሪቱ ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችል አገራዊ የንብርና ምርምር ሥርዓትን ማስተባበር፣ መምራት፣ አቅጣጫ ማስያዝ እና አቅም መገንባት ይሆናል።

### 5. የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

1. በመንግሥት የሚሰየም .............................. ሰብሳቢ ፣
2. የእርሻ እና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር............................ አባል፣
3. የእንስሳት እና የዓሳ ኃብት ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ................... አባል፡
4. የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ሚኒስትር ............. አባል፡
5. የክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊዎች ................................ አባል ፣
6. የክልል እንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ ኃላፊዎች.................................. አባል፣
7. የክልል አርብቶ አደር ልማት ኃላፊዎች ......................................... አባል፣
8. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር............. አባል
9. የክልል ምርምር ኢንስቲትዩቶች ዋና ዳይሬክተሮች.......................... አባል
10. የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ............ አባል ዳዳይሬክተር

11.የግብርና ምርምር ከሚያካሄዱ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በክላስተር ደረጃ የሚወከሉ ሰባት የምርምር ምክትል ፕሬዝደንቶች ............አባል፣

12.የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን ዳይሬክተር ............ አባል

13. ሌሎች የግብርና ምርምርን የሚያከናውኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና የግል ድርጅቶች አንድ ተወካይ ............ አባል።

6. **<u>የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የግብርና ምርምር በአገራዊ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ በመመርኮዝ ሳይንሳዊ ይዘቱን ጠብቆ እንዲካሄድ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን አቅጣጫ ማስያዝ፣ መደገፍ፣ ማስተባበር እና መምራት፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የግብርና ምርምርን የሚያካሂዱ ተቋማት ተቀናጅተውና ተናበው የግብርና ቴክኖሎጂ የማቅረብ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስተባበርና መምራት፤

ለ/ የግብርና ምርምር ፖሊሲን በሚመለከቱ ጉዳዮች መንግስትን ማማከር፤

ሐ/ የአገራችንን የቴክኖሎጂ ፍለጎት መሠረት በማድረግ የምርምር ተቋማት ለምርምር አስፈላጊ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ዘመናዊ የምርምር መሠረተ ልማት እንዲያደራጁ ድጋፍ ማድረግ፤ የማበረታቻና የሽልማት ሥርዓት መዘርጋት፤

መ/ የምርምር መሣሪያዎች የዓለም አቀፍ ሳይንሳዊ ደረጃን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ውጤታማና ብቃት ያለው የግዥ፣ የተከላ፣ የካሊብሬሽን፣ የፍተሻ፤ የጥገና እና የአወጋገድ ሥርዓት ማስፈን፤

ሠ/ የምርምር መሠረተ ልማቶችን ውጤታማነት ለማሳደግ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ በቅንጅትና በጋራ የሚጠቀሙበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

ረ/ የግብርና ምርምር ፕሮግራሞች ከአገራዊ የልማት ዕቅድና ስትራቴጂ ጋር ተገናዝበው እንዲዘጋጁ ማድረግ እና ቅደም ተከተልም ማስያዝ፡

ሰ/ የምርምር ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች የአገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎት በማማከል ሳይንሳዊ ይዘታቸውን ጠብቀው በቅንጅትና በትብብር እንዲተገበሩ

ድጋፍ መስጠት፣ የተመረጡና በቅንጅት የሚተገበሩ የምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በበጀት እንዲደገፉ ማድረግ፣ መከታተል፣ መገምገም፣ ማጽደቅ፤

ሸ/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ለሚቀርቡ የተሻሻለ የሰብል እና የእንስሳት ዝርያዎች፣ ዕውቀቶች እና ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የመነሻ ብዜትን እና የቴክኖሎጂ ፍላጎት የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

ቀ/ በምርምር ሥርዓቱ ያለውን የሰው ኃይል ለስራ ለማነሳሳትና ጠብቆ ለማቆየት የሚያስችል በውጤት ላይ የተመረኮዘ የማበረታቻና የማቆያ ሥርዓት መዘርጋት፤

በ/ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላትን የምርምር አቅም ለመገንባት የሚገኝ የፋይናንስ በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት።

7. **የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሰልጣንና ተግባር**

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሴክሬታሪያቱን በበላይነት ይመራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ፤

ሀ/ የምክር ቤቱን መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፤ በሰብሳቢነት ይመራል፤

ለ/ የሴክሬታሪያቱን የምርምር ዘርፍ አስተባባሪ ዕጩዎችን ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል።

8. **የምክር ቤቱ ስብሰባ**

1. ምክር ቤቱ በሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሶስት

## የግብርና ምርምር ሴክሬታሪያት

9. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ሴክሬታሪያት (ከዚህ በኋላ "ሴክሬታሪያት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የሴክሬታሪያቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

10. **ዋና መስሪያ ቤት**

የሴክሬታሪያቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

11. **የሴክሬታሪያት ስልጣንና ተግባር**

ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ከምክር ቤቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት የግብርና ምርምርን በመደጋገፍ ፣ በመቀናጀት እና በመናበብ በውጤታማነት እንዲያካሂዱ አቅማቸውን ይገነባል፤ ይደግፋል፤ ያስተባብራል
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሴክሬታሪያቱ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 (2) የተመለከቱትን የምክር ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ በማዋል ረገድ ለምክር ቤቱ ድጋፍ ይሰጣል፤

   ለ/ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

   ሐ/ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ተቋማዊ የምርምር አፈጻጸምን መገምገም ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ግብረ መልስ መስጠት፣ ተጠሪ ለሆነበት መስሪያ ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣

   መ/ ከምርምር ሥርዓቱ ለወጡ ቴክኖሎጂዎች፤ ዕውቀት፣ አሰራሮችና ኢንፎርሜሽን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአዕምሮአዊ ንብረት መብት ባለቤትነትን እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፡

   ሠ/ የግብርና ምርምር ማእከላትን አቅም ግንባታ መደገፍ የብቃት ደረጃ የመለኪያ መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱ መሠረት ይገመግማል፣ ሲያሟሉም የልህቀት ማዕከልነት ዕውቅና ይሰጣል፤

   ረ/ በግብርና ምርምር ተቋማትና የምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች መካከል የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

ሰ/ የግብርና ልማት ፖሲሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ከአገር ውስጥ የግብርና ምርምር ተቋማት ጋር ምርምርን በጋራ ማካሄድ ለሚፈልጉ የውጭ የምርምር ድርጅቶች የግብርና ምርምር ማካሄድ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፤ ይገመግማል፣ ፈቃድን የሰርዛል፤

ሸ/ የአገራዊ ግብርና ምርምር ሥርዓት አቅምን ለመገንባት በአገር ደረጃ ከውጭ አገራት ወይም ተቋማት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን እና ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤

ቀ/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት የሚቀርቡ አገራዊ መረጃዎችን እና ሳይንሳዊ ጽሁፎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

በ/ የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል፤

ተ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤

ቸ/ ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል።

12.<u>**የሴክሬታሪያቱ አቋም**</u>

1. ሴክሬታሪያቱ፡-

ሀ/ በመንግሥት የሚመደብ ዋና አስተባባሪ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል አስተባባሪ፣

ለ/ የምርምር ዘርፍ አስተባባሪዎች፤

ሐ/ አስፈላጊው የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይኖሩታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚመደቡ አስተባባሪዎች በግብርና ምርምር ዘርፍ በቂ ልምድ እና አስፈላጊው የትምህርት ያላቸው መሆን አለባቸው።

13.<u>**የዋና አስተባባሪው ስልጣንና ተግባር**</u>

1. የሴክሬታሪያቱ ዋና አስተባባሪ የሴክሬታሪያቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን ከምክር ቤቱ ሰብሳቢ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የሴክሬታሪያቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሴክሬታሪያቱ ዋና አስተባባሪ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 የተመለከቱ የሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/ የሴክሬታሪያቱን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ፡ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የሴክሬታሪያቱን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባልጀ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለሴክሬታሪያቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲደረግ ያዛል፤

ሠ/ ሴክሬታሪያቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች ሁሉ ሴክሬታሪያቱን ይወክላል፤

ረ/ የሴክሬታሪያቱን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

3. የሴክሬታሪያቱ ዋና አስተባባሪ ለሴክሬታሪያቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሴክሬታሪያቱ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

14.<u>የምክትል አስተባባሪው ስልጣንና ተግባር</u>

ምክትል አስተባባሪው፡-

1. የሴክሬታሪያቱን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና አስተባባሪውን ያግዛል፤
2. በዋና አስተባባሪው ተለይቶ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል።
3. ዋና አስተባባሪው በማይኖርበት ጊዜ ዋና አስተባባሪውን ተክቶ ይሰራል።

15.<u>የሴክሬታሪያቱ በጀት</u>

የሴክሬታሪያቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

16.<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ሴክሬታሪያቱ የተሟላና ትክክል የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤
2. የሴክሬታሪያቱ የሂስብ መዛግብትና ገንዘብነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

17.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ታትሞ ከወጣበት ቀን ደምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 14 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 422/2010

## ብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 38 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 422/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "እንስሳት" ማለት የምግብ ምርትና የጭነት ወይም ተቀጽላዎችን የመጎተት ኃይል መስጠት የሚችሉ ለማዳ እንስሳት ሆኖ የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል፣ ዶሮ፣ ዓሳማ፣ የጋማ ከብት እና ጥንቸል፣ የመሳሰሉትን ያካትታል፤
   2. "የእንስሳት ምርት" ማለት ከእንስሳት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገኝ ለሰው ወይም ለእንስሳ ፍጆታ የሚውል፣ ወይም ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚዉል ሥጋ፣

ወተት፣ ማር፣ ቅቤ፣ ዕንቁላል፣ ፀጉር፣ ቆዳ እና ሌጦ ወይም የጭነት ወይም ተቀጽላዎችን የመጎተት ኃይል እና የመሳሰሉትን ይጨምራል

3. “ዝርያ” ማለት ተመሳሳይ ውጫዊ እና ውስጣዊ ወይም የጀኔቲክስ ባህርያት ያላቸውና እነዚህንም ባህርያት በተከታታይ ውልደት ማስተላለፍ የሚችሉ የእንስሳት ስብስብ ነዉ፤
4. “አባላዘር” ማለት በሰው ቴክኒካዊ አሠራር ከርቢ ኮርማ ተሰብስቦና በላቦራቶሪ ተቀነባብሮ በቀሰም ዉስጥ የታሸገ የወንዴ ዘር ሲሆን፣ በሰው ቴክኒካዊ አሠራር ከርቢ ኮርማ ተሰብስቦ በላቦራቶሪ ሳይቀነባበርና በቀሰም ዉስጥ ሳይታሸግ ወዲያዉ አገልግሎት ላይ ሊዉል የሚችል የወንዴ ዘርንም ያጠቃልላል፤
5. “ሽል” ማለት የሴቴ እንቁላልና የወንዴ አባላዘር በመዋሃድ ሕይወት ለማፍራት ጅምር ላይ የደረሰ ሆኖ ከሴቴ ማህጸን የሚሰበሰብ ጽንስ/ሽል ነው፤
6. “የለማ እንቁላል” ማለት የወንዴና ሴቴ ዘር በመዋሃድ ወደ ሽል ሊለወጥ የሚችል እንቁላል ነዉ፤
7. “ማዳቀል” ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዝርያዎችን በማገናኘት የተሻለ ምርታማ የእንስሳት ዝርያ የሚገኝበት ዘዴ ነው፤
8. “የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ” ማለት በመረጣ ወይም በማዳቀል ወይም በሁለቱ ዘዴ በመጠቀም የሚደረግ የእንስሳት ምርታማነት የማሻሻል አሠራር ነዉ፤
9. “የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት” ማለት ሥነ-ህይወታዊና ቴክኒካዊ ቁሶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚጠቅሙ እንደ ርቢ ቁም እንስሳት፣ አባላዘር፣ ሽል፣ የለማ እንቁላል እና የሥነ-ተዋልዶ ቁሳቁሶችን የሚያጠቃልል ይሆናል፤
10. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነዉ፤
11. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፡

3. <u>መቋቋም</u>

1. ብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

4. <u>**ዋና መስሪያ ቤት**</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡

5. <u>**ዓላማ**</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዓላማ የእንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል፣ ዘላቂ የዝርያ አቅርቦት በማስፋፋትና የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በማገዝ የአርቢውን ህብረተሰብና የሀገሪቱን ብሔራዊ ገቢ በማሳደግ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ማምጣት ይሆናል፡፡

6. <u>**የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻል፣ ዘላቂ የዝርያ አቅርቦት ለማስፋፋትና የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ለማገዝ የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል ለቴክኖሎጂ ሽግግር ይሰራል፤
2. ብሔራዊ የእንስሳት የርቢ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ በመንግስት ሲፀድቅም በኃላፊነት ይፈጽማል፣ የክልሎችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
3. ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት ወደ ሀገር በማስገባትና ሀገር ውስጥም በማምረት፣ በማባዛት አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
4. ለአባላዘር ማቆያ ባንክና ለመስክ አገልግሎት የሚሆን ፈሳሽ ናይትሮጂንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በበቂ መመረቱንና መኖሩን ያረጋግጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
5. በሀገር አቀፍ ደረጃ የዝርያ ማሻሻያ ዕቅድ ያወጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
6. የዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ወጥ የሆነ ሀገራዊ የእንስሳት ብዜት ሪከርድ አያያዝ ሥርዓትና የመረጃ ቋት እንዲሁም ድረገጽ ያደራጃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
7. የመረጃ ትንተናና ሥርጭት አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመዘርጋት የዝርያ ማሻሻያ ዉጤት በምርት ግኝት፣ የባህርያት ለዉጥ የልኬትና ምዝገባ ሥርዓት ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች በመረጃ ሥርጭትና ቅብብሎሽ ሂደትና ግብረ-መልስ ይከታተላል፤

8. ለእንስሳት ዝርያ መሻሻል አስተዋጽዖ የሚያደርጉ የእንስሳት ብዜት ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፤ በእንስሳት ዝርያ መሻሻል ዙሪያ መንግሥትን ያማክራል፡፡
9. የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን በብዙሀን መገናኛ፣ በድረገፅ፣ በበራሪ ጽሁፎች፣ ፖስተሮችና ሌሎች ትምህርት ሰጪ መልዕክቶችን ያሰራጫል፣ የተገኘውንም ውጤት ይከታተላል፤
10. በዝርያ ማሻሻያ ተግባራት የተቋሙንና የሌሎች ባለድርሻ አካላት የሥራ እንቅስቃሴ ትስስር ሥርዓት በመዘርጋት የተገኘውን ውጤት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
11. በእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ተግባራት ላይ ለተጠቃሚዎች ሥልጠናዎች ይሰጣል፤ አውደ ጥናት፣ ሲምፖዚዬምና ሴሚናሮችን ያዘጋጃል፤ በእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ተግባራት ላይ በሚሳተፉ የተለያዩ አካላት መካከል የልምድ ልዉዉጥ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
12. የእንስሳት ሀብት ምዝገባ፣ ዝውውር፣ ልውውጥና አጠቃቀም ላይ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት እንዲከናወን ያደርጋል፤
13. ከእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓቶችና መሣሪያዎች ሽያጭ በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የወጪ መሸፈኛ ገቢ ይሰበስባል፤
14. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
15. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት**</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ፣
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣
3. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

8. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

የቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ፣ ከእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር፣ ከእንስሳት ምርምር ተቋማት፣ አግባብ ካላቸዉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣የብዝሃህይወት ኢንስቲቲዩት፣ሌሎች ባለድርሻ አካላት እና የሙያ ማህበራት የተውጣጡ ቁጥራቸው

እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየሙ ይሆናል፡፡

9. **የአማካሪ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት**

ቦርዱ ሌሎች ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ጨምሮ በሚከተሉት ላይ ኢንስቲትዩቱን ያማክራል፡-

1. በብሔራዊ የርቢ ፖሊሲ፣ የዝርያ ማሻሻያ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች፣ የአፈጻጸም መመሪያዎች ዝግጅትና አፈጻጸም፤
2. ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት ወደ ሀገር ማስገባት፣ ማላመድ፣ ሀገር ውስጥም ማምረት፣ ማባዛት፣ ሥርጭትና ስርፀት፤
3. ሀገር በቀል እና የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች ልየታ፣ መረጣ፣ ብዜት እና ምዝገባ እንዲሁም አጠቃቀም፤
4. በእንስሳት ሀብት ዝውውር፣ ልውውጥና አጠቃቀም እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር፡፡

10. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ ቦርዱ የሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንስቲቲዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኢንስቲቲዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃለይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞችን በፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደርጉ ግንኙነቶች ሁሉኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የየሦስት ወር እና ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ሰ) በኢንስቲትዩቱ የሚካሄደውን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ውጤታማ እንዲሆን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

11.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣን እና ተግባራት</u>

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

1. በኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የሚመደቡበትን የሥራ ዘርፍ ይመራሉ፤ ያስተዳድራሉ፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፤
3. ተለይቶ ካልተወከለ በስተቀር ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዳይሬክተሩን ተክቶት ይሠራል፡፡

12.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል

1. በመንግሥት ከሚመደብ በጀት እና
2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከውስጥ አገልግሎት ከሚሰበሰብ ገቢ፡፡

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

14.<u>መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን</u>

ኢንስቲትዩቱ ስለ እንስሳት ሀብት አጠቃቀምና ብሔራዊ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች መመሪዎችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፡፡

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም**

ኃይለማሪያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

ሰ/ **ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚነስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 180/2002**

**የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**[39]

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንተሻሻለ/ በአንቀፅ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**[40]

   በዚህ ደንብ ውስጥ።

   1. "ሚኒስቴር" ማለት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው[41]።

---

[39] 19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 2(1) መሰረት "የጨርቃ ጨርቅ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት" የሚለው በ "የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ አንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት" ተተክቷል፡፡

[40] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) በ19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 2(3) መሰረት አዲስ የገቡ ሲሆን ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (4) ንዑስ አንቀጽ (6) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

[41] በ19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

2. "ኢንዱስትት" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ (11) እና (12) የተሰጣቸው ትርጓሜ ይይዛሉ።[42]
3. "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው።
4. “ጥጥ” ማለት ለስላሳ፣ በቀላሉ የሚተጣጠፍ፣ እርጥበት የሚስብ፣ ነጭ እና ጭረታማ በቆላማና ሞቃታማ አካባቢዎች የሚበቅል ለጨርቃጨርቅ ምርት በግብዓትነት የሚያገለገል የተፈጥሮ ዕፅዋት ወይም በዘረመል የተዳቀለን የሚያካትት ነው፤
5. “የጨርቃጨርቅ የእሴት ሠንሠለት” ማለት በጥጥ ልማትና በጨርቃጨርቅ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የአመራረት ሂደት ውስጥ ለግብዓት አቅርቦት እስከ አልባሳት ገበያ መዳረሻ የሚኖር ተያያዥነትና ተመጋጋቢነት ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትየቱ ዋና መሥሪየ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የጥጥ ልማትን እና የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ይሆናል።[43]

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር[44]</u>

---

[42] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጓሜ የ22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2(13) እና (14)ን ተመልከት፡፡
[43] በ19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 4 ተሻሻለ፡፡
[44] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 15 እስከ 29 ያሉት በ19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 5 መሰረት አዲስ የገቡ ሲሆን የቀድሞዎቹ ንዑስ አንቀፅ (15) እስከ (18) እንደቅደምተከተላቸው ንዑስ አንቀፅ (30)፣ (31)፣ (32) እና (33) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችና፣ ስትራተጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤
2. ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ በዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማስራጨት
3. የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚስችሉ የፕሮጀክት ፕፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት
4. በጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
5. የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትዎችን ዘርፍ ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤ ለሠልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፤
6. የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትዎችን ዘርፍ ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤
7. በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤
8. ተመሳሳይ አላማ ካላቸው ውስጥ እና በውጭ ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግና እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር ማበረታታት፤
9. የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊየደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፤

10. ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤
11. የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፣
12. ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት፣ ኢንዲስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፣
13. ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወን፣
14. ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፣
15. የመንግሥትን አገራዊ የጥጥ ልማት ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ማናቸውንም ከጥጥ ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማስተባበር፣ መቆጣጠር እና ማስፈፀም፤
16. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በጥጥ ልማት ለመሰማራት ለሚያመለከቱ ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦትን፣ ማስተላለፍንና ማስተዳደርን በሚመለከት ድጋፍ ማድረግ፤
17. ለጥጥ ልማትና ግብይት ፖሊሲ ቀረጻ የሚያግዙ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ሲጸድቁም የአፈጻጸም ማኑዋሎችን ማዘጋጀትና እንዲተገበሩ ማድረግ፤ የዘርፉን ቀጣይ እድገት የሚያረጋግጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
18. ለጥጥ ልማቱ ድጋፍ የሚያደርጉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ማስተባበር እና በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ፤
19. ሰፋፊ እና ሜካናይዝድ የጥጥ እርሻዎች ሊለሙባቸው የሚችሉ አካባቢዎች መለየትና የመስኖ ልማት እንዲስፋፋ ድጋፍ ማድረግ፤ ሜካናይዝድ የጥጥ እርሻዎችን የሚያለሙ ባለሀብቶች ያላቸውን ይዞታ ለማስፋፋትም ሆነ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም እንዲችሉ ከሚመለከታቸው ተቋማት የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
20. ለዘርፉ ድጋፍ የሚያደርጉ የምርምር ተቋማትን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ የጥጥና የጨርቃጨርቅ አምራች ማኅበራትን እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማቀናጀት በዘርፉ ችግሮች ላይ ምርምሮች ማካሄድና የምርምር ውጤቶቹ ሲጸድቁ ተግባራዊ ማድረግ፤

21. በጥጥ ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶች የምርት ጥራትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲችሉ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የሚያገኙበትን እና ከአርሶ አደሩ ጋር በማስተሳሰር ኅብረተሰቡ ከልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፤
22. የጥጥ ልማት ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመሠረተ ልማት አገልግሎት እንዲስፋፋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ መሥራት፤
23. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብይት መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት፣ የገበያ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የገበያ ማዕከላቱን አቅም መገንባት እና ግብይቱ የጥጥ ጥራትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲከናወን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤
24. በጥጥ ልማት የተሠማሩ ባለ ሀብቶችን የሥራ እንቅስቃሴ መከታተልና የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ድጋፍ ማድረግ፤
25. የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችን የገበያ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ጥራቱን የጠበቀ ጥጥ ለማምረት የሚያግዝ ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲደረግ መደገፍ
26. በጥጥ ልማቱና ግብይቱ ላይ የነበሩና ያልተፈቱ ችግሮችን መለየትና ችግር ፈቺ አሰራሮችን በመቅረጽ ተግባራዊ እንዲሆኑ መደገፍ ፤
27. የጥጥ ልማቱንና ግብይቱን በተሻለ መንገድ ለመምራትና ለመደገፍ የሚያስችል እቅድ መንደፍ፣ አፈፃፀሙን መከታተል ሪፖርት ማቅረብ እና በጥጥ ልማትና ግብይት ላይ መንግሥትን ማማከር
28. ለጥጥ ምርት በሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ በአመራረት ሂደቱ እና ምርቱን በማጓጓዝና በማከማቸት ረገድ የጥራት ቁጥጥርና የምክር አገልግሎቶችን መስጠት
29. በጥጥ ልማት አካባቢዎች መለስተኛ ላብራቶሪዎችን ማደራጀትና የጥጥ ምርት ጥራት ፍተሻ አገልገሎት መስጠት፤
30. ለተጠቃሚዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፣
31. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ክፍያ መጠየቅ፣
32. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣
33. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን።

7. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. አማካሪ ምክር ቤት፣
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና[45]
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

8. **<u>የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. **<u>የአማካሪ ምክር ቤቱ ተግባራት</u>**

አማካሪ ምክር ቤቱ፡-

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፣
2. የጥጥ ልማትና ግብይት እና የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን፣ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ገምግሞ አስተያየቱን ይሰጣል።[46]
3. የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፣
4. የኢንስትቲትዩቱን የዕቅድ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።

10. **<u>የአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>**

1. አማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎቹን በየሶስት ወሩ ያደርጋል፣ እንዲሁም በመሀሉ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አብዛኛው በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

11. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

---

[45] በ19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 6 ተሻሻለ፡፡

[46] በ19/39(2005) ደ.286 አንቀፅ 7 ተሻሻለ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል።

ለ/ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፣

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. <u>የተሻረ ሕግ</u>

የሚከተሉት በዚህ ደንብ ተሸረዋል፡-

1. የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 118/1997፣
2. የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 125/1998

15. <u>መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 118/1997 ተቋቁሞ የነበረው የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 125/1998 የተቋቋሞ የነበረው የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ለማት ማዕከል የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ዘርፍን አስመልክቶ የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡

16. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 181/2002</u>

## <u>የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አወጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤[47]
2. "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" ማለት በንግድም ዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989[48] አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (11) እና (12) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤
3. "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤

---

[47] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(9) መሰረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[48] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጓሜ የ22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2(13) እና (14)ን ተመልከት፡፡

4. "ቆዳ" ማለት ከትናንሽ ወይም ትላልቅ እንስሳት የሚገኝ ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ ወይም ጥሬ ቆዳው ወይም ሌጦው ለፍቶና ለስልሶ ባለቀለት ደረጃ ሲገኝ ነው፤
5. "የቆዳ ውጤቶች" ማለት ከቆዳ፣ ከሸራ፣ ከፕላስቲክ ወይም ከሰው ሰራሽ ቆዳ የሚሰሩ ጫማዎች፣ ቦርሳዎች፣ ቀበቶዎችና ጓንቶች፣ ወይም ከቆዳ የሚሰሩ ልብሶች እና የመሳሰሉትናቸው፤
6. "የቆዳ ኢንዱስትሪ" ማለት ጥሬ ቆዳ እና ሌጦ ወደ አለቀለት ምርት የመቀየር ሥራንና የቆዳ ውጤቶችን የማምረት ሥራን የሚያጠቃልል ነው፤
7. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

   1. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማ</u>

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ይሆናል።

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፤ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
2. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤

3. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ወደዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ፤ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፤
4. በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
5. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎችን ዘርፍ ልማት የሚያግዙና ዘርፉን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤ ለሠልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፤
6. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤
7. በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤
8. ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤
9. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፤
10. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤
11. የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፤
12. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፤
13. ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወን፤
14. ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያከናውናል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፣
15. ለተጠቃሚዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፤

16. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ክፍያ መጠየቅ፤
17. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
18. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን።

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. አማካሪ ምክር ቤት፣
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. <u>**የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት**</u>

1. የአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የአማካሪ ምክርቤቱ አባላት ቁጥር እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>**የአማካሪ ምክር ቤቱ ተግባራት**</u>

አማካሪ ምክር ቤቱ፡-

1. ኢንስቲትዮቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤
2. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን ጥናቶችንና ምርምሮችን ይገመግማል፣ አስተያየቱንም ይሰጣል፤
3. የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩቱን የእቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።

10. <u>**የአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባች**</u>

1. አማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎቹን በየሦስት ወሩ ያደርጋል ፣ እንዲሁም በመሀሉ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክርቤቱ አባላት መካከል አብዛኛው በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

11. <u>**የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13. <u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. <u>የተሻሩ ህጎች</u>

የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 41/1991 (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

15. <u>መብትና ግዴታ ስለመተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 41/1991 ተቋቁሞ የነበረው የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በሚኒስትሮች

ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 125/1998 ተቋቁሞ የነበረው የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል መብትና ግዴታዎች፣ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ዘርፍን አስመልክቶ ከነበሩት መብትና ግዴታዎች በስተቀር፣ በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

16. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ. ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 182/2002</u>

## <u>የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የብረታ ብረት ኢንዲስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤትደንብ ቁጥር 182/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

2. <u>ትርጓሜ</u>

   በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤[49]
   2. "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (11) እና (12) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤[50]

---

[49] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(9) መሰረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተብሎ ይነበብ፡፡

[50] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጓሜ የ22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2(13) እና (14)ን ተመልከት፡፡

3. “የምርት ልማት” ማለት በኩረጃ ወይም በፈጠራ አዳዲስ ምርቶችን ወይም ቴክኖሎጂዎችን ማመንጨትና ማሰራጨት ነው፤
4. “የምርት ሂደት” ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤
5. “የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ” ማለት የብረት ማዕድናት ውጤት የሆኑ የተለያዩ የብረታብረት ውጤቶችን ለማምረት ግብአት እንዲሆኑ ብረታ ብረቶችን የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤
6. “የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ” ማለት ከብረታብረት የሚሰሩና የምህንድስና ውጤት የሆኑ የካፒታል ዕቃዎችን፣ አካላትን፣ መለዋወጫዎችን፣ መገልገያዎችን እና ሌሎች ብረት-ነክ የንግድ ዕቃዎችን የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤
7. “ውዳቂ ብረታ ብረት” ማለት የብረታ ብረት ወይም የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ተረፈምርት የሆነ ወይም አገልግሎት ያቆሙ የኢንዱስትሪ መሣሪያዎች፣ የወታደራዊ ወይም የሲቪል መሣሪያዎች ወይም ተሽከርካሪዎች ወይም የእነዚሁ ተቀጽላዎች ወይም መለዋወጫዎች የብረት አካል የሆነ ወይም የተጣለ ብረታብረት ነው፤
8. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>
   1. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማ</u>

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የሀገሪቱን የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹት ወዳዳሪ አንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ይሆናል።

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችንና መርሃግብሮችን ማዘጋጀት፤ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
2. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
3. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ ወደዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ ፤ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፤
4. በብረታ ብረት እና በኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
5. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ዘርፉን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤ ለሰልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፤
6. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣
7. በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራ ትቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎትመስጠት፤
8. ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤
9. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተምክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፤
10. ለብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤

11. የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፤
12. የውዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት ስርዓት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ማጥናትና ሲፈቅድም ተግባራዊነቱን መከታተል፤ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውና አዋጪነታቸው የተረጋገጠላቸውን የብረትና ተዛማጅ ማዕድናትን የማቅለጥና የማጣራት ሥራዎችን መደገፍ፤
13. ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወን፤
14. ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፣
15. ለብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፤
16. ለተጠቃሚዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፤
17. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ክፍያ መጠየቅ፤
18. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
19. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን።

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. አማካሪ ምክር ቤት፣
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. <u>**የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት**</u>

1. የአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>**የአማካሪ ቤቱ ተግባራት**</u>

አማካሪ ምክር ቤቱ፡-

1. ኢንስቲትዮቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤

2. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን ጥናቶችንና ምርምሮችን ይገመግማል፣ አስተያየቱንም ይሰጣል፤
3. የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።

10.<u>የአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

1. አማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎቹን በየሦስት ወሩ ያደርጋል፣ እንዲሁም በመሀሉ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አብዛኛው በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

11.<u>የዋና ዳይሬክሩ ስልጣን እና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለክቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፡

   ለ/ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራተጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ በሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግኑኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

   ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. <u>ደንቡ የሚፀናት ግዜ</u>

ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ. ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 193/2003**

**የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 193/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ጥራት" ማለት በቀጥታ የተገለጸንና በተዘዋዋሪ መንገድ የተመለከተን ፍላጎት የማሟላት ችሎታውን የሚገልጽ የአንድ ምርት ወይም አገልግሎት አጠቃላይ ባሕሪ ነው፤
   2. "ጥራት ማስፋፋት" ማለት በየደረጃው በሚገኙ የምርትና አገልግሎት ሂደቶች ላይ በተመጣጠነ የሀብት አጠቃቀም የጥራት ተፈላጊ ሁኔታዎችንና አላማዎችን

በማሟላት የአንድን የአሰራር ሥርዓትና የአመራረት ብቃት ለማሳደግና ለማሻሻል የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ ነው፤

3. “ደረጃ” ማለት ለጋራና ተደጋጋሚ ጥቅም መሟላት ያለባቸው ህጎች፣ መመሪያዎች ወይም የምርት ባህሪያትን እና ተዛማጅ ሂደቶችን ወይም የማምረቻ ዘዴዎችን የሚያስቀምጥ በጋራ መግባባት ላይ ተመሥርቶ ዕውቅና ባለው አካል የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ የአስተሻሸግና የመለያ ምልክት አደራረግ መስፈርቶችን ያጠቃልላል፤
4. “አስገዳጅ ደረጃ” ማለት ምርቶችና አገልግሎቶች የግድ ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች የያዘ ደረጃ ነው፤
5. “የኢትዮጵያ ደረጃ” ማለት ማንኛውም ኤጀንሲው በብሔራዊ የኢትዮጵያ ደረጃነት አፅድቆ የሚያሳውቀው ደረጃ ነው፤
6. “ብሄራዊ የደረጃዎች ምልክት” ማለት ምርቶች አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር መስማማታቸውን ለማረጋገጥ የሚያገለግል የብቃት ማረጋገጫ ምልክት ነው፤
7. “ምርት” ማለት ማናቸውም የኢንዱስትሪ ወይም የግብርና ውጤት ነው፤
8. “አገልግሎት” ማለት ለተጠቃሚው ጥቅም ሲባል በተጠቃሚው ጥያቄ በዋነኛነት በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ሥራ ነው፤
9. “የገበያ ክትትል” ማለት ለገበያ የቀረበ ምርት ወይም አገልግሎት ተገቢውን የደረጃ መስፈርት ስለማሟላቱ ለማረጋገጥ የሚደረግ የቁጥጥር ስራ ነው፤
10. “ማሳወቅ” ማለት በህትመት ውጤቶች፣ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ፣ በምስል ወይም በሌላ መገናኛ ዘዴ ለሚመለከታቸው አካላት ደረጃን ይፋ ማድረግ ነው፤
11. “የተስማሚነት ምዘና” ማለት ምርትን፣ አገልግሎትን ወይም የሥራ አመራር ሥርዓትን የሚመለከቱ ደረጃዎችና ሕጋዊ መስፈርቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤
12. “የተስማሚነት ምዘና አካል” ማለት የሠርተፊኬሽን፣ የኢንስፔክሽን ወይም የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፤
13. “የሥራ አመራር ሥርዓት” ማለት ጥራትን፤ ለመጠበቅና አንድን ድርጅት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ነው፤

14.“ብሄራዊ የጥራት መሠረተ ልማት” ማለት በደረጃዎች ዘርፍ ፣ በሜትሮሎጂ ዘርፍ ፣ በተስማሚነት ምዘና እና በአክሬዲቴሽን ዘርፍ የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ነው፤

15.“ሠርተፊኬሽን” ማለት በተስማሚነት ምዘና ውጤት ላይ ተመሥርቶ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

16.“ኢንስፔክሽን” ማለት የምርት ንድፍ፣ ምርት፣ ሂደት፣ አገልግሎት ወይም የተከላ ስራ ከዝርዝር መስፈርቶች በሙያዊ ምዘና ከሆነ ደግሞ ከጠቅላላ መስፈርቶች ጋር መስማማታቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

17.“የላቦራቶሪ ፍተሻ” ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተስማሚነት ምዘና ባህሪያት መሟላት አለመሟላታቸውን ለማረጋገጥ በግልጽ ተለይቶ የተወሰነ የምርመራ ሥርዓትን ተከትሎ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

18.“አክሬዲቴሽን” ማለት የተስማሚነት ምዘና አካላት አስቀድሞ የተወሰኑ የብቃት መሥፈርቶችን መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በሚካሄድ ግምገማ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

19.“ሚኒስቴር” ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

20.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

21.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

22.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

### 4. ዋና መስሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ማዘጋጀትና ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተፈላጊዎቹን ደረጃዎች አሟልተው መቅረባቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤
2. ደረጃዎችን በመጠቀም የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ሽግግር ማመቻቸት፤
3. ለሀገር በቀል ምርቶችና አገልግሎቶች ብሄራዊ ደረጃዎችን በማዘጋጀት በዓለም ዓቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ።

6. **ስልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ከሃገሪቱ የልማት መርሃ-ግብር ጋር የተጣጣመ የጥራት ማስፋፋት ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የደረጃ ዝግጅት ስትራቴጂ የማዘጋጀት፣ ተግባራዊ የማድረግና አፈፃፀሙን የመከታተል፤
2. የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማዘጋጀት፣ የማጽደቅና የማሳወቅ፤
3. የደረጃዎች ሥራ በሚያከናውኑ ብሔራዊ፣ አህጉራዊ፣ ዓለም ዓቀፋዊ ወይም ሌሎች አካላት ለተዘጋጁ ደረጃዎች እንደየአስፈላጊነቱ እንደ ኢትዮጵያ ደረጃ ዕውቅና የመስጠት፤
4. የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የሚያዘጋጁ ብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን የመመስረትና የአሠራር መመሪያቸውን የመወሰን፤
5. ብሄራዊ የደረጃዎች ምልክትን ቅርጽና ይዘት የመወሰንና በምልክቱ የመጠቀም፣ ፈቃድ የመስጠት፤
6. የደረጃዎች፣ የተስማሚነት ምዘና መመሪያዎችና የቴክኒክ ደንቦች ብሔራዊ መረጃ ማዕከል የማደራጀትና አገልግሎት የመስጠት፤
7. በተጠቃሚው ዘንድ የጥራትና የደረጃዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን መንደፍና ተግባራዊ የማድረግ፤

8. ደረጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኒክ ድጋፎችን፣ ሥልጠናዎችንና የማማከር አገልግሎቶችን በመስጠት የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤
9. ድርጅቶች የራሳቸውን ደረጃ የማዘጋጀት አቅም እንዲያዳብሩ የቴክኒክ ድጋፎችን፣ ሥልጠናዎችንና የማማከር አገልግሎቶችን የመስጠት፤
10. በምርት ሂደት ላይ ብክለትንና ብክነትን ለማስወገድ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ልምድ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የማስፋፋት፤
11. የቴክኒክ ደንቦች አዘገጃጀት የዓለም ንግድ ህግጋት መስፈርቶችን የተከተለ እንዲሆን ለማስቻል ከሚመለከታቸው ብሔራዊና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን የመመስረት፤
12. ብሔራዊ የጥራት ሽልማት ሥርዓት ለመመሥረት የሚያስችል ጥናት የማካሄድና ሲፈቀድም የማስተዳደር፤
13. ደረጃዎችን በሚመለከት በዓለም ዓቀፍ መድረክ የሀገሪቱን ጥቅም መወከልና ሀገሪቱ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነት የመከታተል፤
14. ለብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት መጠናከር የተቀናጀ ድጋፍ መኖሩን ለማረጋገጥ ተገቢነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመሥራት፤
15. በደረጃዎች ዝግጅት፣ አተገባበርና በሚያስከትሉ ተፅዕኖና ተዛማጅ ጉዳዮች ምርምሮችን ማካሄድ፤
16. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤
17. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፤
18. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

7. <u>**የኤጀንሲው አቋም**</u>

ኤጀንሲው፡-

1. ብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት”) እየተባለ የሚጠራ፣
2. በመንግስት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

8. **የምክር ቤቱ አባላት**

   1. ምክር ቤቱ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና ሌሎች አካላት ቱውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።
   2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

9. **የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር**

   ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

   1. ኤጀንሲው አዘጋጅቶ የሚያቀርባቸውን ብሔራዊ የጥራትና የደረጃዎች ስትራቴጂዎችን ያፀድቃል፤
   2. ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክትን በአስገዳጅነት መጠቀም የሚገባቸውን ምርቶች ይወስናል፤
   3. በብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ አስገዳጅ የሆኑ ወይም ያልሆኑ የደረጃ መስፈርቶችን በመገምገም ያፀድቃል፤
   4. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ለሌሎች ደረጃዎች እንደ ኢትዮጵያ ደረጃ የሚሰጥ እውቅናን ያፀድቃል፤
   5. ኤጀንሲው በዚህ ደንብ መሠረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያፀድቃል፤
   6. ለብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሚከፈለውን አበልና ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖችን ለመንግሥት አቅርቦ ያፀድቃል፤
   7. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የዘርፍ አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

10. **የምክር ቤቱ ስብሰባ**

    1. ምክር ቤቱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።
    2. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላቱ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል።
    3. የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚተላለፈው ከአባላቱ በአብዛኛው ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል። ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
    4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ፲ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. **የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀድ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል
   ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
   መ/ ለኢጀንሲው በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤
   ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና ሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ በኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

14. <u>ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት</u>

1. ለማንኛውም ምርት ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክትን ለመጠቀም ምርቱ አግባብነት ካለው የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር መስማማቱ ኃላፊነት በተሰጠው የተስማሚነት ምዝና አካል ተረጋግጦ በኤጀንሲው መፈቀድ አለበት።
2. ማንኛውም በብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት ለመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ስው ምልክቱን መጠቀም የሚችለው ለተፈቀደለት ምርት ብቻ ነው።
3. ኤጀንሲው የደረጃዎች ምልክት የመጠቀም ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ለህዝብ ክፍት የሆነ መዝገብ ይይዛል።
4. የፈቃድ ተጠቃሚው የተሰጠውን ፈቃድ በድርጅቱ ውስጥ በቀላሉ ሊታይ በሚችልበት ቦታና አኳኋን ማኖር አለበት።
5. በብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት የመጠቀም ፈቃድ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ፣ የምልክቱ አጠቃቀም እንዲሁም ከእነዚሁ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

15. <u>በሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. አግባብ ያላቸው የፌዴራልና የክልል ሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚከተለው ሥልጣን በዚህ ደንብ ተሰጥቷቸዋል።

   ሀ/ ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክትን መጠቀም ግዴታ የሆነባቸው ወይም አስገዳጅ የደረጃዎች መስፈርትን ማሟላት የሚገባቸው ምርቶች ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክቱ ሳይደረግባቸው ወይም አስገዳጅ የደረጃዎች መስፈርቱን ለማሟላታቸው ማረጋገጫ ሳይቀርብላቸው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገቡ ወይም ከኢትዮጵያ ግዛት እንዳይወጡ የመከልከል፤

   ለ/ የገበያ ክትትል በማድረግ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች አግባብነት ያላቸውን አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን የመቆጣጠር፤

   ሐ/ አግባብነት ያላቸውን አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶች ባለማሟላታቸው የተያዙ ምርቶች አስፈላጊ ማስተካከያዎች ተደርገውባቸው እንደገና ለገበያ እንዲቀርቡ የመፍቀድ ወይም ሊስተካከሉ የማይችሉና በተጠቃሚው ጤንነት ወይም ደኅንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሲሆኑ የሚወገዱበትን ሁኔታ የመወሰን፤ እና

መ/ ለገበያ ባቀረቧቸው ሰዎች በተገለፀው ወይም የተስማሚነት ምዘና አካላት የጥራት ምልክት በሰጡበት የደረጃ መስፈርት መሠረት በገበያ ላይ የዋሉ ምርቶች በተባለው የደረጃ መስፈርት መሠረት ለገበያ ስለመቅረባቸው አስተማማኝ አገልግሎት በሚሰጠ የተስማሚነት ምዘና አካላት የማረጋገጥና ውጤቱን በመገናኛ ብዙሓን ለህዝብ የማሳወቅ።

2. ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የሕግ አስፈጻሚ አካላት በዚህ አንቀጽ የተሰጣቸውን ሥልጣን በሥራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት የመተባበር ግዴታ አለበት።

16. <u>ፀንተው የሚቆዩ ደንቦች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የማይቃረኑ የደረጃዎች ማህተምና የአገልግሎት ዋጋ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/1982 ድንጋጌዎች በአዲስ ደንብ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

17. <u>መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ</u>

ከሜትሮሎጂ ጋር ከተያያዙት በስተቀር የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች እና የኢትዮጵያ ክሊነር ፕሮዳክሽን ማዕከል በመባል ይታወቅ የነበረው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

18. <u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 3 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 194/2003</u>**

**<u>ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ ደንብ "ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 194/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ስነ-ልክ" ማለት የአለካክ ሳይንስ ነው፤
   2. "ሕጋዊ ስነ-ልክ" ማለት በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ልኬትን፣ የልኬት አሀዶችን፣ የመለኪያ መሣሪያዎችንና የልኬት ዘዴዎችን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚከናወን ተግባር ነው፤
   3. "ካሊብሬሽን" ማለት በተወሰነ፡ ሁኔታዎች ውስጥ በመለኪያ መሣሪያው የተገለፀው የልኬት መጠን፣ የመለኪያ ሥርዓት ወይም የማመሳከሪያ ስረት

በመለኪያ ኢ.ታሎኑ ላይ ከተገለፀ እሴት ጋር ያለውን አንድነት ወይም ልዩነት ለማወቅ የሚደረግ ንጽጽር ነው፤

4. “ልኬት” ማለት የአንድን የተወሰነ መጠን ለማከናወን የተሟላ የመለኪያ መሣሪያ እና ተያያዥነት ያላቸው መሣሪያዎችን በማቀናጀት የሚገኝ ውጤት ነው፤
5. “የልኬት አሃድ” ማለት የአንድ የተወሰነ መሣሪያወይም ምርት መጠን ወይም ብዛት ከኢ.ታሎን ጋር በማነፃፀር በሁለቱ መካከል ያለው ስምምነት የሚገለፅበት አሃድ ነው፤
6. “ኢ.ታሎን” ማለት አንድን አሃድ ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የመጠን እሴቶችንለመወሰን፣ በተግባር ለመግለጽ፣ ለመጠበቅ ወይም ለመቅዳት የተመደበ መሠረታዊ መለኪያ፣ የመለኪያ መሣሪያ፣ የማመሳከሪያ ስሪት ወይም የአለካክ ቅንብር ነው፤
7. “ብሄራዊ የመለኪያ ኢ.ታሎን” ማለት በሀገር ውስጥ ያሉ የሌሎች ተመሳሳይ አሀዶችን መጠን ለመወሰን እንደመሠረት ሆኖ እንዲያገለግል ከፍተኛ የትክክለኝነት መጠን ያለውና በብሄራዊ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ኢ.ታሎን ነው፤
8. “ማመሳከሪያ ስረት” ማለት የመለኪያ መሣሪያዎች ካሊብሬት ለማድረግ፣ የልኬት ዘዴዎችን ለማከናወን ወይም የቁሶችን መጠን ለመወሰን የሚውል ሆኖ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የባሕረ እሴቶች አእርስ በርስ ንፅፅር የተረጋገጠበትና በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ስረት ነው፤
9. “የተመሰከረለት ማመሳክሪያ ስረት” ማለት የምስክር ወረቀት ያለው የአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የባሕረ እሴቶች የተረጋገጡት ሥርዓት ባህሪው የተገለጸበትን አሀድ በተዋረድነት በትክክል የሚገልጽ ሆኖ የእያንዳንዱ የተረጋገጠ እሴት እርግጠኛ ያለመሆን መጠን በተወሰነ አስተማማኝነት ደረጃ የተገለጸበት የማመሳከሪያ ስረት ነው፤
10. “የመለኪያ ኢ.ታሎን” ማለት የክብደት፣ የርዝመት፣ የይዘት፣ የጉልበት፣ የጊዜ፣ የሙቀት፣የአዮን ፈጣሪ ጨረር ልክ ወይም ሌሎች ድርጅቶች የሚወስናቸውን መጠኖች መሥፈሪያ ነው
11. “የመለኪያ መሣሪያ” ማለት የክብደት፣ የርዝመት፣ የይዘት፣ የጉልበት፣ የጊዜ፣ የሙቀት፣ የአዮን ፈጣሪ ጨረር ልክ ወይም ሌሎች ድርጅቶች የሚወስናቸውን የልኬት መጠኖች መስፈሪያ መሣሪያ ነው፤

12.“የእርከን ተዋረድ ትስስር” ማለት የልኬት ውጤትን ወይም መደበኛ የመለኪያ መሣሪያ የልኬት መጠንን በሚመለከት የእርግጠኝነት መጠን ንጽጽሩ ከታወቀና አስተማማኝነቱ ከተመሰከረለት የማመሳከሪያ የልኬት መጠን ጋር በማነፃፀር ያላቸውን ልዩነትና አንድነት ለመወሰን እንዲቻል ቀጣይነት ባለው መንገድ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ትስስሩን መጠበቅ ነው፤

13.“እርግጠኛ ያለመሆን መጠን” ማለት ከልኬት ሥርዓቱ ውጤት ጋር በተያያዘ ለልኬት በቀረበው የተወሰነ መጠን በትክክል እንዳይገኝ አስተዋፆ የሚያደርጉ ጉዳዮች ተሰልተው የሚገኘው የልኬት ውጤት ነው፤

14.“የሳይንስ መሣሪያ” ማለት ለምርምርና ሥርፀት፣ ለትምህርትና ሥልጠና፣ ለጥራት ቁጥጥርና ፍተሻ፣ ለስነልክ ወይም ለሰው ወይም ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎቶች ሥራ ላይ የሚውል መሣሪያ ነው፤

15.“ሚኒስቴር” ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

16.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

17.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

18.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንምይጨምራል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት</u>

3. <u>**መቋቋም**</u>

1. ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>**ዋና መስሪያ ቤት**</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. ከዓለም ዓቀፍ ስነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ ብሄራዊ የስነ-ልክ ስርዓትን የመዘርጋትና በዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማምጣት፤
2. የአገሪቱን ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችና የተመሰከረላቸውን የማመሳከሪያ ስረቶች ከዓለም አቀፍ የመለኪያ ኢታሎኖች ጋር ለማመሳከር፣ ለመጠበቅና ለማሰራጨት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግበር፤
3. በስነ-ልክ ዘርፍ የትምህርትና የምርምር ተግባራትን የመደገፍ፣
4. የሳይንስ መሣሪያዎችን ጥገና ብሔራዊ አቅም መገንባትና የጥገና አገልግሎት የመስጠት፤
5. ለሳይንስ መሣሪያዎች ተጠቃሚዎች የቴክኒክ፣ የስልጠና፣ የምክርና የመረጃ አገልግሎቶችን በመስጠት ተግባሮቻቸውን በብቃት እንዲያከናውኑ የመደገፍ።

6. <u>ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ዓለም አቀፍ የአሃዶች ሥርዓትን በማስተዋወቅና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው የልኬት መስፈሪያዎችን በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማስቻል በሥራ ላይ ያሉ ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎችን ወደ ዘመናዊነት የማሸጋገር፣
2. ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችን የመጠበቅ፤
3. ብሔራዊ የስኑልክ ላቦራቶሪ የካሊብሬሽን አገልግሎት የመስጠት፤
4. ለኢንዱስትሪው በስነ-ልክ ጽንሰ ሃሳብና የተግባር ሥልጠናና የምክር አገልግሎት በመስጠት የራሳቸውን የውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ እገዛ የማድረግ፤
5. የሌሎች ሀገሮችን ምርጥ ተሞክሮዎች መሠረት በማድረግ በስነ-ልክ ዘርፍ የትምህርት ካሪኩለም ተቀርፆ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግና ምርምር የማካሄድ አቅምን በመገንባት ረገድ የዩኒቨርስቲዎችንና የምርምር ተቋማትን የማገዝ፤
6. በሀገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን የልኬት አሃዶች፣ የአሃዶቹን ምልክቶችና ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችን በማሳተም ለሕዝብ የማሳወቅ፤

7. ስነ-ልክን በሚመለከት በዓለም ዓቀፍ መድረክ የሀገሪቱን ጥቅም መወከልና ሀገሪቱ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነት የመከታተል፤
8. ከሌሎች ብሄራዊ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፍ የስነ-ልክ ተቋማት ጋር በሚደረግ የእርስ በርስ የካሊብሬሽን ውጤት ንፅፅር የካሊብሬሽን አገልግሎት አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ በሚካሄድ ፕሮግራም ላይ የመሳተፍ፤
9. ለብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት መጠናከር የተቀናጀ ድጋፍ መኖሩን ለማረጋገጥ ተገቢነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመሥራት፤
10. ከዩኒቨርስቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር በዘርፉ ምርምር ማካሄድና የምርምር ውጤቶቹን ወደ ኢንዱስትሪዎች የማስረፅ፤
11. ስነ-ልክን የተመለከተ የሥርዓተ-ሰነድና መረጃ ማዕከል የማቋቋምና አገልግሎቱን የመስጠት፤
12. የህጋዊ ስነ-ልክ ሥራን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል አስፈላጊውን የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ የመስጠት፤
13. ስለሳይንስ መሣሪያዎች መረጣና አያያዝና አጠቃቀም፣ እንክብካቤ፣ ጥገናና አወጋገድ ለተጠቃሚዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
14. ስለሳይንስ መሣሪያዎች ግዥ፣ አያያዝና አጠቃቀም፣ እንክብካቤ፣ ጥገናና አወጋገድ ለተጠቃሚዎች ስልጠና ይሰጣል፤
15. የሳይንስ መሣሪያዎች ተጠቃሚ ተቋማት የራሳቸው የሳይንስ መሣሪያዎች ጥገና ወርክ ሾፕ እንዲያቋቁሙ የሥልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ እና ለሚያስለጥናቸው ባለሙያዎች የምስክር ወረቀት የመስጠት፣
16. ለሳይንስ መሣሪያዎች ጥገና ወርክሾፖች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣
17. ከተቋማት አቅም በላይ የሆኑ የሳይንስ መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎቶች መስጠት፤
18. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤
19. ዓላማውን በብቃት በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊሆኖ ሲያገኘው ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች አካሎች በውክልና የመስጠት፤
20. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፤በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

21.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎችተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

7. **የኢንሲትዩቱ አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፦

1. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

8. **የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎችይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይአነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪልሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ኢንስቲትዩቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል
   ረ/ የኢንስቲትዩትን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9. **በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

10.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

11.<u>የልኬት አሃዶች እና መሳሪያዎች</u>

በሀገሪቱ ወስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ በኢንስቲትዩቱ ታትመው ከተገለፁ የልኬት አሃዶችና ምልክቶች ውጪ ሌሎች አሃዶችና ምልክቶች እንዲሁም ትክክለኛነቷቸው አስተማማኝ ያልሆነ የልኬት መሣሪያዎች በሥራ ላይ እንዳይውሉ የመቆጣጠር ሥልጣን አግባብ ላላቸው የፌዴራልና የክልል ህግ አስፈጻሚ አካላት በዚህ ደንብ ተሰጥቷል።

12.<u>ብሔራዊ የመለከያ ኢታሎኖች</u>

1. ከዓለም ዓቀፍ የአሀዶች ሥርዓት ጋር በተያያዘ ብሄራዊ የመለኪያ ኢታሎን የልኬት ውጤት በአገሪቱ ውስጥ የመጨረሻው ትክክለኛ የልኬት መጠን ሆኖ ይቆጠራል።
2. ለማንኛውም የህጋዊ ሜትሮሎጂ ልኬት አገልግሎት የሚውል ብሄራዊ የመለኪያ ኢታሎን ያልሆነ የመለኪያ ኢታሎን፦
   ሀ/ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የመለኪያ ኢታሎኖች ጋር የእርከን ተዋረድ ትስስሩን መጠበቅ ይኖርበታል፣ እና
   ለ/ ወቅቱን በጠበቀ መንገድ እውቅና ባለው የካሊብሬሽን ላቦራቶሪ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት።
3. ማንኛውም የመለኪያ ኢታሎን እርግጠኛ ያለመሆን መጠን ሊኖረው ይገባል።
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተገለፀት የመለኪያ ኢታሎኖች ውጭ የሆኑ የመለኪያ ኢታሎኖች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የመቆጣጠር ሥልጣን አግባብ ላላቸው የፌዴራልና የክልል ሕግ አስፈጻሚ አካላት በዚህ ደንብ ተሰጥቷል።

13.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የሕግ አስፈፃሚ አካላት በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 12(4) የተሰጣቸውን ስልጣን በሥራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት የመተባበር ግዴታ አለበት።

14. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ የሳይንስ መሳሪያዎች ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 145/2000 በዚህ ደንብ ተሽሯል።

15. <u>መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ</u>

ከሜትሮሎጂ ጋር የተያያዙ የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች የሳይንስ መሣሪያዎች ማዕከል መብትና ግዴታዎች እና ከጨረራ የልኬት አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

16. <u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትም ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 3 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 287/2005 ዓ.ም**

**የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 287/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:

   1. "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002[51] አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (11) እና (12) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤
   2. "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤
   3. "ምግብ" ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ለኅብረተሰቡ ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን፣ የሚታኘክ ማስቲካ፣ ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከም የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትምባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን አይጨምርም፤

---

[51] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጓሜ የ22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2(13) እና (14)ን ተመልከት፡፡

4. "መጠጥ" ማለት ለሰው መጠጥነት የሚውል ፈሳሽ ነገር ሲሆን የታሸገ ውኃን፣ የፍራፍሬ ጭማቂን፣ ለስላሳ እና የአልኮል መጠጦችን ያካትታል፤
5. "የሕክምና መሣሪያ" ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር ወይም ለማከም ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላብራቶሪ፣ የቀዶ ሕክምናና የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎች፣ የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ ሲሪንጆችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻዎችን፣ ጎዝን፣ ጥጥ፣ ሰው ሠራሽ ጥርሶችን፣ ኬሚካሎችን፣ የጨረር ፊልሞችንና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችንና መገልገያዎችን ይጨምራል፤
6. "ባሕላዊ መድኃኒት" ማለት የዕፅዋት፣ የእንስሳት ወይም የማዕድን ተዋፆ ሆኖ በነጠላም ሆነ በመቀላቀል ለሰውም መሆነ ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ነው፤
7. "መድኃኒት" ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን፣ ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን፣ የባሕል መድኃኒቶችን፣ ደጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒቶችን፣ መርዞችን፣ ደምና የደም ተዋፆዎችን፣ ክትባቶችን ፣ ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶችን፣ ኮስመቲኮችን፣ የሳኒተሪ ዝግጅቶችን እና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤
8. "ኮስመቲክ" ማለት ሰውነትን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደምግባት ለማሣመር ወይም የአካልን ቅርጽና አሠራሩን ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር በገላ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን የቆዳ ቅባቶችን፣ ሎሽኖችን፣ ሽቶዎችን፣ የከንፈር ቀለሞችን፣ የጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ፣ የዓይንና የፊት ማስዋቢያ፣ የጸጉር ማቅለሚያዎች፣ የጠረን መቀየሪያ ዝግጅቶችን፣ ሜዲኬትድ ሳሙናዎችን እና ለእነዚህ ዝግጅቶች መሥሪያ የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤
9. "የምግብ ኢንዱስትሪ" ማለት ማናቸውንም ምግብ የሚያቀነባብር ወይም የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤
10. "የመጠጥ ኢንዱስትሪ" ማለት ማናቸውንም መጠጥ የሚያቀነባብር ወይም የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤

11.“ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ” ማለት መድኃኒት ፣ ባሕላዊ መድኃኒት ፣ ሕክምና መሣሪያ፣ ኮስመቲክ ወይም ከእነዚህ የተወሰኑ ዓይነቶችን አንድ ላይ በማድረግ የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤

12.“ማሸጊያ” ማለት ምግብን፣ መጠጥን ወይም መድኃኒትን በውስጡ ለመሙላት ወይም ለመክተት ወይም ለመጠቅለል የሚያገለግል ማንኛውም መያዣ ሲሆን ከምግቡ፣ ከመጠጡ ወይም ከመድኃኒቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን መያዣዎችን ወይም ለመጠቅለያ የሚያገለግሉ ሌሎች ዕቃዎችን ይጨምራል፤

13.“ባዮኢኩቫለንስ ማዕከል” ማለት ሁለት ዓይነት የመድኃኒት ዝግጅቶች በፍቱንነታቸውና ደኅንነታቸው የሚመሳሰሉ መሆናቸው በምርመራ የሚረጋገጥበት ማዕከል ነው፤

14.“ሚኒስቴር” ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤

15.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ለምግብ፣ ለመጠጥና ለፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ሁለገብ ድጋፍ በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማፋጠን፣ የልማት እመርታ ማምጣት እና ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማብቃት ይሆናል።

6. **የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሐ-ግብሮችን ማዘጋጀትና በመንግሥት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

2. በምግብ፣ በመጠጥና በፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ስርፀት መለየት፤ በባሕላዊ ምርቶች ላይ እና በአዳዲስ ምርቶች ላይ የምርት ሂደትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወንና እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢንዱስትሪው በማሸጋገር ወደ ገበያ እንዲገቡ መደገፍ፤ ኢንዱስትሪው የምርምርና ሥርፀት ክፍሎች እንዲያቋቁም መደገፍ፤
3. የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ለማሳደግ የሚያግዙ የገበያ ጥናትን ጨምሮ ሌሎች የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤ የኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ድጋፍ መስጠት፤ ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
4. ለምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፤ የገበያ እና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
5. የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩትካል ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋሎችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፤ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱት ችግሮች መፍትሔ መስጠት፤ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ መስጠትና ፕሮሞሽን ማካሄድ፤
6. በምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩትካል ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላ እና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
7. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራር እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤
8. ለምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ በምርት ሂደት፣ በምርት፣ ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በማቋቋም መደገፍ፣ ለሚያመርቷቸው ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣ ኢንዱስትሪው የፍተሻ

ላብራቶሪዎች እንዲያቋቁም ማበረታታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሠርተፊኬሽን እንዲያገኙ ማስቻል ፤

9. በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃትን ጠብቆ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እንዲችል በቁርኝት መርሐ ግብር አቅሙን መገንባት፤ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሣሣይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤

10. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርትና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራትና በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፣ ኢንዱስትሪው ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር እንዲኖረው ማገዝ፣ የኢንዱስትሪውን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

11. የምግብ ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና የሚቀመሩትን ተሞክሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለኢንዱስትሪው ድጋፍ መስጠት፤

12. ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት በመጠንና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪው እንዲለማ መደገፍ፣ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ ድረስ በምርቶች እሴት ሰንሰለት መሠረት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤ በተለይም በዘርፉ የተሠማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪው ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪው ጋር ውጤታማ የምርት፣ የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖረው መደገፍ፤

13. የአገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ ለመሠማራት እንዲነሳሱ የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች እንዲለሙ ማበረታታት፣ በኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ውስጥ የሚሠሩ ባለሃብቶችን መደገፍ፤

14. በዘርፉ አዳዲስና ተወዳዳሪ ባለሀብቶችን ለመፍጠር የኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ፕሮግራም መዘርጋትና የኢንኩቤሽን ማዕከላትን ማቋቋም፤

15. የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪው በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን የማሸጊያ ምርቶች ኢንዱስትሪ ልማትን መደገፍ፤
16. በዘርፉ ተዋናዮች የሚገኙ የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ድጋፍ መስጠት፤
17. የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እንዲጠቀም እና የአካባቢ ብክለት እንዳያስከትል ድጋፍ መስጠት፤
18. የባዮ-ኢኩቫለንስ ማዕከል በማጠናከር በኢትዮጵያ ያሉት የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማዕከሉ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤
19. በድኅረ-ምርት የሚያጋጥሙ የምርት ብክነቶችን ለመቀነስ ድኅረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች፣ ዘመናዊ መጋዘኖች፤ ዘመናዊ ትራንስፖርት እና ሌሎች አስፈላጊ የሎጂስቲክስ መሠረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ መደገፍ፤
20. የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ማኅበራት ለዘርፉ ንግድና ኢንቨስትመንት ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት፤
21. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤
22. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
23. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን።

7. **<u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>**

ኢንስቲትዩቱ፦

1. የአማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት") እየተባለ የሚጠራ፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>**የምክር ቤቱ ተግባራት**</u>

ምክር ቤቱ፡-

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፣
2. የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን፣ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ይገመግማል፣ አስተያየቱንም ይሰጣል፣
3. በአቅም ግንባታ መርሐ-ግብሮች ላይ አስተያየትተ ይሰጣል፣
4. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ እየገመገመ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

10.<u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. ምክር ቤቱ በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

11.<u>**የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር፣**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   - ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣
   - ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችት መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
   - ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፣

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.**<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.**<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.**<u> ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ 13 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ደንብ ቁጥር 288/2005 ዓ.ም

## የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀፅ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 288/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002[52] አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (11) እና (12) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ።
   2. "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤
   3. "የምርት ልማት" ማለት በቅጂ ወይም በፈጠራ አዳዲስ ምርቶችን ወይም ቴክኖሎጂዎችን ማመንጨትና ማሰራጨት ነው፤

[52] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጓሜ የ22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2(13) እና (14)ን ተመልከት፡፡

4. “መሠረታዊ ኬሚካሎች” ማለት የኦርጋኒክ እና የኢን-ኦርጋኒክ ኬሚካሎችን የያዙና ለሌሎች ኢንዱስትሪዎችና ለግብርናው ዘርፍ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ኬሚካሎች ናቸው፤
5. “የኬሚካል ውጤቶች” ማለት መሠረታዊ ኬሚካሎችን በግብዓትነት በመጠቀም እና እሴት በመጨመር በቀጥታ ለተጠቃሚዎች የሚውሉ የፕላስቲክ፣ የጎማ፣ የሳሙና፤ የዱቄት ወይም ንጽሕና መጠበቂያ እና የወረቀት መሥሪያ የእንጨት ውጤትና የወረቀት ውጤቶችን ይይዛል፤
6. “የኮንስትራክሽን ግብዓት” ማለት ብረት ነክ ያልሆኑ ለኮንስትራክሽን ግንባታ የሚውሉ እንደሲሚንቶ፣ ሴራሚክስ፣ መስታወት፣ የእንጨት ውጤቶችን እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸውን ምርቶችን ይጨምራል፤
7. “የኬሚካል ኢንዱስትሪ” ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) የተጠቀሱትን ምርቶች የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤
8. “የኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ” ማለት በዚህአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተጠቀሱትን ምርቶች የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፡
9. “የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች ስምምነት” ማለት በአዋጅ ቁጥር 30/1988 የጸደቀውና የማስፈጸሚያ አዋጅ ቁጥር 331/1995 የወጣለት የኬሚካል ጦር መሳሪያ ማልማትን፣ ማምረትን፣ ማከማቸትን እና ለጥፋት ጥቅም ላይ ማዋልን የሚከለክልው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ነው፣
10. “ሚኒስቴር” ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡
11. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ለኬሚካልና ለኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ሁለገብ ድጋፍ በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማፋጠን፣ የልማት እመርታ፣ ማምጣት እና ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማብቃት ይሆናል።

6. **ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ገብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፓሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት እና በመንግሥት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
2. ለኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ እና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
3. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ፣ ለኬሚካልና ለኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት የሚያግዙና ዘርፉን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የስራ አመራርና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተገባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤
4. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤
5. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሠራጪት፤ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ በአፈጻፀም ላይ ለሚከሰቱት ችግሮች መፍትሔ መስጠት፤ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ መስጠትና ፕሮሞሽን ማካሄድ፤
6. በኬሚካልና በኮንስትራክሽን ገብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላ እና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
7. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በማቋቋም መደገፍ፣ ለሚያመርቷቸው

ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣ ኢንዱስትሪዎቹ የፍተሻ ላብራቶሪዎች እንዲያቋቁሙ ማበረታታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሠርተፊኬሽን እንዲያገኙ ማስቻል፤

8. በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃትን ጠብቆ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እንዲችል በቁርኝት መርሐ ግብር አቅሙን መገንባት፤ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሣሣይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤

9. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርትና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራትና በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፣ ኢንዱስትሪው ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር እንዲኖረው ማገዝ፤ የኢንዱስትሪውን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

10. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና የሚቀመሩትን ተሞክሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ኢንዱስትሪዎቹ የሚደገፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

11. ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪው እንዲለማ መደገፍ፤ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ ድረስ በምርቶች እሴት ሰንሰለት መሠረት በዘርፉ ተዋናዮች መካከልያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤ በተለይም በዘርፉ የተሠማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ አምራቾች ኢንዱስትሪው ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ጋር ውጤታማ የምርትጂ የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው መደገፍ፤

12. የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ ለመሠማራት እንዲነሳሱ የኬሚካልና የከንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች እንዲለሙ ማበረታታት፤ በኢንዱስትሪ ቀጠናዎቹ ውስጥ የሚሠሩ ባለሃብቶችን መደገፍ፤

13.በዘርፉ ተዋናዮች የሚገኙ የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ድጋፍ መስጠት፤

14.የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እንዲጠቀም እና የአካባቢ ብክለት እንዳያስከትል ድጋፍ መስጠት፤

15.የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ማኅበራት ለዘርፉ ንግድና ኢንቨስትመንት ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን መስጠት፤

16.በኬሚካል ጦር መሣሪያዎች ስምምነት አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ከአባልነት የሚገኙ የስልጠና፤ የጥናትና ምርምር እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ድጋፎችን ለኬሚካል ኢንዱስትሪው ልማት አቅም ግንባታ መጠቀም፤

17.የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፣

18.ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤

19.የንብረት ባለቤት መሆን ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ

20.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን።

7. **<u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>**

ኢንስቲትዩቱ ፣

1. አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. **<u>የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤

2. የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ዕቅዶችን እንዲሁም የተከናወኑ ጥናቶችንና ምርምሮችን ይገመግማል፣ አስተያየት ይሰጣል፤
3. በአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ እየገመገመ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

10.**<u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>**

1. ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸዉም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

11.**<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራላይ ያውላል፤

   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊያደርጋል፤

   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል።

   ሠ/ በሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል።

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.**<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.**<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.**<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ. ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 295/2005 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚንስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 35 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 295/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002[53] አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (11) እና (12) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤
   2. "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤
   3. "የሥጋና ወተት ምርት" ማለት የእንስሳት ምርትና ተዋፆን ያጠቃልላል፤
   4. "የእንስሳት ምርት" ማለት ሥጋ፣ ወተት፣ አይብ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ምርት ብሎ የሚሰይማቸውን ያጠቃልላል፤

[53] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጓሜ የ22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2(13) እና (14)ን ተመልከት፡፡

5. “የእንስሳት ተዋፆ” ማለት እንደ ቀንድ፣ ሸኮና፣ ደም፣ አጥንትና አንጀት የመሳሰሉ ከእንስሳት እርድ የሚገኙና ተፈላጊነት ያላቸው ተረፈ ምርቶች ሲሆኑ ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ተዋፆ ብሎ የሚሰይማቸውን ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ያጠቃልላል፤
6. “እንስሳት” ማለት ዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል ፣ዶሮና ግመል ማለት ሲሆን ኢንስቲትዩቱ እንስሳት ብሎ የሚሰይማቸውን ያጠቃልላል፤
7. “ቴክኖሎጂ” ማለት በምርምር ፣ በሙከራና በአዲስ የአሠራር ስልት የተገኙና ጥቅም ላይ ሲውሉ የምርት ጥራት፣ ምርታማነትና የአሠራር ቅልጥፍናን የሚጨምሩ የአሠራር ዘዴዎች ናቸው፤
8. “ማቀነባበር” ማለት ማንኛውም ምርት በዓይነት፣ በይዘት ወይም በተዛማጅ ሁኔታ ቀድሞ ከነበረው እሴት ለመጨመር የሚደረግ የአሠራር ሂደትነው፤
9. “ሚኒስቴር” ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤
10. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡
11. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት ቢሾፍቱ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ+**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ለስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ሁለገብ ድጋፍ በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማፋጠን፣ የልማት እመርታ ማምጣት እና ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማብቃት ይሆናል።

6. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሲሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና መርሐ ግብሮችን ማዘጋጀት፤ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
2. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርፀት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች በማሸጋገር ገበያ ውስጥ እንዲገቡ መደገፍ፤ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርፀት ክፍሎች እንዲያቋቋሙ መደገፍ፤
3. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪን ለማሳደግ የሚያግዙ የገበያ ጥናትን ጨምሮ ሌሎች የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ድጋፍ መስጠት፣ ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
4. ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ ፣መተንተን ፣ ማደራጀትና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
5. ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በማቋቋም መደገፍ፣ ለሚያመርቷቸው ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤ ኢንዱስትሪው የፍተሻ ላብራቶሪዎች እንዲያቋቁም ማበረታታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሠርተፊኬሽን እንዲያገኙ ማስቻል፤
6. የእንስሳት ሀብትና ኢንዱስትሪውን አስመልክቶ ባሉት የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የመረጃ ቋት መመስረት፤ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ በየጊዜው እየተገመገሙ ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት፤
7. ለእንስሳት ገበያ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የእንስሳት ምርት የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ክትትል የማድረግ፤

8. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፤ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ጠቃሚ ጥናት ማድረግ፤ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል ማድረግና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱት ችግሮች መፍትሔ መስጠት፤ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ማካሄድና በንዑስ ዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቃዎች እንዲወገዱ ድጋፍ መስጠት፤
9. በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
10. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን መስጠት፣ በዚህ ረገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋርም በመተባበር የዘርፉን የሰው ኃይል ማብቃት፤
11. በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃትን ጠብቆ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እንዲቻል በቁርኝት መርሐ ግብር የአቅም ግንባታ ማከናወን፤ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እናበውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሣሣይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤
12. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርትና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራት፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፣ በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከርና ኢንዱስትሪዎቹ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር እንዲኖራቸው ማገዝ፣ የዘርፉን የዝቅተኛና ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
13. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪውን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የዓለምአቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና የሚቀመሩትን ተሞክሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለኢንዱስትሪዎቹ ድጋፍ መስጠት፤
14. ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪዎች እንዲለሙ መደገፍ፤ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው

ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ በተለይም በዘርፉ የተሠማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት፣ የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው መደገፍ፣

15. የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ ለመሰማራት እንዲነሳሱ የሥጋና ወተት አንዱስትሪ ዞኖች እንዲለሙ ማበረታታት፣ በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ የሚሰሩ ባለሀብቶችን መደገፍ፤
16. በዘርፉ አዳዲስና ተወዳዳሪ ባለሀብቶችን ለመፍጠር ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮግራም መዘርጋትና የኢንኩቤሽን ማዕከላትን ማቋቋም፤
17. በዘርፉ በጥናትና ምርምር የሚገኙ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ድጋፍ መስጠት፤
18. በድኅረ-ምርት የሚያጋጥሙ የምርት ብክነቶችን ለመቀነስ ድኅረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች፣ ዘመናዊ መጋዘኖች፣ ዘመናዊ ትራንስፖርትና ሌሎች አስፈላጊ የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ መደገፍ፤
19. የሥጋና ወተት አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበራት ለዘርፉ ንግድና ኢንቨስትመንት ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት፤
20. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ታዳሽ የሀይል ምንጮችን እንዲጠቀም እና የአካባቢ ብክለት እንዳያስከትል ድጋፍ መስጠት፤
21. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤
22. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
23. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎችተ ዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ፦

1. አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ)፤

2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. <u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>የምክር ቤቱ ተግባራት</u>

ምክር ቤቱ፦

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤
2. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ዕቅዶችን፣ ጥናቶችንና ምርምሮችን ይገመግማል፣ አስተያየቱንም ይሰጣል፤
3. የአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ በየሦስት ወሩ እየገመገመ የመፍትሔ አቅጣጫ ያመላክታል።

10. <u>የአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

1. ምክር ቤቱ በየሩብ የበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቱትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራላይ ያውላል፤

ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸምሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

መ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.**<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.**<u>የሂሣብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሠይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.**<u>የተሻረ ደንብ</u>**

የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር143/2000 (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

15.**<u>ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 143/2000 (እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

16. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከነሃሴ 3 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 1ቀን 2005 ዓ. ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 373/2008</u>

## <u>የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ ደንብ "የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 373/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ማኑፋክቸሪንግ" ማለት ማሽንን፣ መሣሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት ማምረት ነው፤

2. “አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ” ማለት የኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ሕንጻን ሳይጨምር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከብር 100,000 እስከ 1 ሚሊዮን 500,000 ብር (አንድ መቶ ሺህ አንድ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሆነ ኢንዱስትሪ ነው፤
3. “መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ” ማለት የኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ31 እስከ 100 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ሕንጻን ሳይጨምር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከብር 1 ሚሊዮን 500,001 እስከ ብር 20 ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ ብር እስከ ሃያ ሚሊዮን ብር) የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነው፤
4. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
5. “ሚኒስቴር” ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፎችን ሊከፍት ይችላል።

5. **ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ ልማት ሰፊ መሠረት የሚጥሉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን እንዲስፋፉ በማድረግ

ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ማረጋገጥና ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገውን ሽግግር ማፋጠን፤

2. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፣ቀጣይነት ያለውና ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሠረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት ማጠናከርና እንዲፈጠሩ መደገፍና ማስተባበር።

6. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ እቅዶችን፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፣ በመንግሥት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፎች ይቀርጻል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ይሰራል፣ ለተወዳዳሪነታቸው እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
4. የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች በአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲሰማሩ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራ ይሰራል፤
5. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፉና የሚያስተባብሩ የክልል ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤
6. የማኑፋክቸሪንግ ዘርፋን የእሴት ሰንሰለት መሠረት በማድረግ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በፍላጎትና በዕድገት ደረጃ ላይ የተመሠረተ የሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን ማቅረባቸውን ያረጋግጣል፤
7. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎችን ጥናት በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ያካሂዳል፣ ይለያል፣ ይቀምራል፣ ያሰራጫል፤
8. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የዘርፍ ማኅበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

9. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና ለዘርፉ ልማት ጠቃሚ የሆኑ የአዋጭነት ጥናት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
10. ኢንዱስትሪያሊስቶችን ለማጠናከር እና ለመፍጠር የኢንተርፕረነርሺፕ ፕሮግራም በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የካይዘን የጥራትና ምርታማነት ሥርዓት ተቀናጅቶ እንዲተገበር ያመቻቻል፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ያመቻቻል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ሞዴል የኢንኪዩቤሽን ማዕከላትን ያቋቁማል እንዲሁም በክልሎች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፤
11. በክልሎች ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት በማደራጀት መሠረተ ልማት የተሟላላቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች እና የገበያ ማዕከላት እንዲገነቡ ተገቢውን እገዛና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤
12. ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ይደግፋል፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እርስ በእርስና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት አቅርቦትና በምርት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ትስስር እንዲፈጥሩ ያደርጋል፣ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፤
13. ከጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ወደ አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገሩትን ሥርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ተግባራዊ ያደርጋል፤
14. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የሚያመርቷቸው ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከጥናትና ምርምር ተቋማት፣ ከዘርፍ ልማት ኢንስቲቲዩቶች፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ ከካፒታል ዕቃዎች ሊዝ ከሚያደርጉ ኩባንያዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በሰው ሀብት ልማት፣ በጥናትና ምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና መሠረተ-ልማት በቅንጅት ይሰራል፣ ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትስስር ያጠናክራል፣ ያስተባብራል፤

15. አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪ ለማድረግ በጥናት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ፣ የእውቅና እና የሽልማት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤
16. በአገር ውስጥና በውጭ አገር አውደ-ርዕይ፣ አውደ-ጥናት፣ ሴሚናሮችና ተመሳሳይ መድረኮች በማዘጋጀትና በማስተባበር በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተመረቱ ምርቶችና ቴክኖሎጂዎች እንዲተዋወቁና ኢንዱስትሪዎች የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይደግፋል፤
17. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፤
18. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ፣ የደረጃ እና የጥራት ሰርተፊኬሽን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤
19. በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃቱን ጠብቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችል የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪን ለመደገፍ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ያደርጋል፤
20. ተጠሪነታቸው ለሚኒስቴሩ ከሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
21. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፤
22. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
23. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>**የኤጀንሲው አቋም**</u>

ኤጀንሲው፦

1. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የምክር ቤቱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ፣ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ጸሐፊ ይሆናል።

9. **<u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የድጋፍ ማዕቀፎችና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አስመልክቶ አግባብ ያላቸው ተቋማትን አፈጻጸም ይገመግማል፤
2. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሀሳብ ያቀርባል፤
3. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና ሀገራዊ ዕቅዶች አፈጻጸም ይገመግማል፤
4. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሰጡ ድጋፎች፣ የሞዴል ኢንዱስትሪዎች መረጣና ማበረታቻ አሰጣጥ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መፈጸማቸውን ይገመግማል።

10. **<u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>**

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ ይካሄዳል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
2. በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጹ ዕኩል በዕኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ሥር የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረታዊ መርሆዎች ተከተሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ኘሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

   መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲው ይወክላል፤

   ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**12.<u>በጀት</u>**

የኤጀንሲው በጀት በመንግስት ይመደባል።

**13.<u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>**

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**14.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**15.<u>ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 ዓ.ም ተቋቁሞ የነበረው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አነስተኛና መካከለኛ

ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍን የሚመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

16. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 6 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 421/2010</u>

## <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 (በአዋጅ ቁጥር 942/2008 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 5 እና 38 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 421/2010” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. “አክሬዲቴሽን” ማለት አንድ የተስማሚነት ምዘና አካል የተወሰነ የተስማሚነት ምዘና ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን በሚመለከት የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤
2. “የተስማሚነት ምዘና” ማለት ምርት፣ የስራ ሂደት፣ የአሠራር ስርዓት፣ ሰው ወይም ድርጅት የሚመለከታቸውን ደረጃዎችና መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ነው፤
3. “የተስማሚነት ምዘና አካል” ማለት አክሬዲቴሽን ሊሰጠው የሚችል የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት የሚሰጥ የፍተሻ ላቦራቶር፣ የኢንስፔክሽን ተቋም፣ የሠርተፍኬሽን ተቋም፣ የካሊብሬሽንና ቬሪፍኬሽን ላቦራቶር፣ የንጽጽር ፍተሻ እና የሪፈረንስ ማቴሪያል አዘጋጅና አቅራቢ አካል ነው፤
4. “ባለሙያ” ማለት መሪ አሰሰር፣ ቴክኒካል አሰሰር፣ ቴክኒካል ኤክስፐርት፣ አሰልጣኝ፣ የአክሬዲቴሽን ኮሚቴዎች አባል እና ለተለያዩ የጽሕፈት ቤቱ ስራዎች ሙያዊ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ከጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ውጭ ያለ ግለሰብ ነው፤
5. “አሰስመንት” ማለት ጽሕፈት ቤቱ በተስማሚነት ምዘና አካላት ላይ የተቀመጠላቸውን ደረጃዎች እና መስፈርቶች መሠረት በማድረግ በተወሰነ የሥራ ወሰን ብቃታቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ግምገማ ነው፤
6. “የክትትል አሰስመንት” ማለት ከዳግም አሰስመንት በስተቀር አክሬዲቴሽን የተሰጣቸው አካላት የብቃታቸውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረግ አሰስመንት ነው፤
7. “አክሬዲትድ የሆነ ተቋም” ማለት በጽሕፈት ቤቱ ወይም በዓለም አቀፍ ላቦራቶሪ አክሬዲቴሽን ትብብር ተቋም ወይም በዓለም አቀፍ የአክሬዲቴሽን ፎረም ሙሉ አባል በሆነ የአክሬዲቴሽን ተቋም አክሬዲትድ የሆነ የተስማሚነት ምዘና አካል ነው፤

8. “አክሬዲቴሽን ሠርተፍኬት” ማለት በተወሰነ የሥራ ወሰን አክሬዲቴሽን አገልግሎት ማግኘቱንና አክሬዴትድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፤
9. “ተቀባይነት ያላቸው ሕጋዊ ሰነዶች” ማለት አክሬዲትድ በሆኑ ተቋማት የሚሰጡ ሪፖርቶች እና ሰርተፍኬቶች ሲሆኑ አክሬዲትድ በሆኑበት መስክ፣ ብቃታቸው በተረጋገጡ ባለሙያዎች የተፈረመ እና አክሬዲቴሽኑ ከተወሰነ በኋላ የወጡትን ይመለከታል፤
10. “የአክሬዲቴሽን ምልክት” ማለት አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማት አክሬዲቲድ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና አክሬዲትድ በሆኑበት ወሰን እንዲጠቀሙበት በጽሕፈት ቤቱ የሚሰጥ ምልክት ነው፤
11. “የአክሬዲቴሽን ወሰን” ማለት አንድ የተስማሚነት ምዘና አካል አገልግሎት ለመስጠት በተቀመጡ መስፈርቶችና ደረጃዎች ተገምግሞ ብቃቱ የተረጋገጠበት የአገልግሎት ወሰን ነው፤
12. “ሚኒስቴር” ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤
13. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት

3. **ስለ መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ “ጽሕፈት ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ሕጋዊ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
2. የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ በሀገሪቱ ለተስማሚነት ምዘና ተቋማት የሦስተኛ ወገን የአክሬዲቴሽን አገልግሎት የሚሰጥ ብቸኛ ተቋም ነው፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው ብሔራዊ የአክሬዲቴሽን ሥርዓት በመገንባት እና በመተግበር ለሀገሪቱ ምርቶች እና አገልግሎቶች የሚሰጡ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረግ የሀገሪቱን የሀገር ውስጥና የወጪ ንግድ ማቀላጠፍ፤
2. ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎችና መስፈርቶችን በመጠቀም ለተስማሚነት ምዘና ተቋማት በሚሰጥ የአክሬዲቴሽን አገልግሎት የሕብረተሰቡ ጤና፣ ደህንነት፣ አካባቢ እንዲጠበቅ ማድረግ እና ፍትሐዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፤
3. በአገር ውስጥ የሚደረግ የግብይት ቁጥጥርና መንግስታዊ ውሳኔዎች ውጤታማ፣ ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡

6. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ለተስማሚነት ምዘና አካላት አግባብነት ባላቸው ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች መሠረት በብቸኝነት ገለልተኛ የአክሬዲቴሽን አገልግሎት መስጠት፤
2. አክሬዲቴሽንን ለማስተዋወቅ በአክሬዲቴሽን ደረጃዎች፣ አሰስመንት ስልቶች እና ተዛማጅ መስፈርቶች ላይ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን አሰራር ተከትሎ ሥልጠናዎችን መስጠት፤
3. የአክሬዲቴሽን ምልክት የአጠቃቀም መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤ ማስፈጸም፤ በተጨማሪም በአባልነቱ የሚያገኘውን የአህጉራዊ፣ ዓለም አቀፋዊ የአክሬዲቴሽን ምልክቶች ፈቃድ ዓለም አቀፍ አሰራሩ በሚፈቅደው መሠረት ተዋውሎ አክሬዲትድ ለሆኑ ተቋማት መስጠት፤ አፈፃፀሙን መከታተል፤
4. የተስማሚነት ምዘና አካላት የአክሬዲቴሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ማበረታታት፤ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ማስተዋወቅ፤ ስለአክሬዲቴሽን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መሥራት፤
5. አክሬዲቴሽን የተሰጣቸውን፣ የታገደባቸውንና የተሰረዘባቸውን አካላት ዝርዝር መዝግቦ መያዝ፤ ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ፤ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላት ማሳወቅ፤

6. የአክሬዲቴሽን ሂደት የሚመራበትን በተለይም አመልካቾች የሚገመገሙበትንና አክሬዲቴሽን የሚሰጥበትን፣ የሚታገድበትንና የሚሠረዝበትን እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣትና በሥራ ላይ ማዋል፤
7. አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማት በአገኙት የአክሬዲቴሽን ወሰን ላይ በቀጣይነት ብቃታቸውን ማረጋገጣቸውንና የተቀመጡ መስፈርቶችን የማሟላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ የታቀደ ወይንም ድንገተኛ የክትትል አሰስመንት ማድረግ፤
8. የአክሬዲቴሽን ሰርተፍኬትና የአክሬዲቴሽን ምልክት ያለ አግባብ ጥቅም ላይ እንዳይዉል እንዲሁም የአክሬዲቴሽን መረጃ ባልተገባ መልኩ እንዳይተረጎም ክትትል ማድረግ፤ የተፈጠሩ ችግሮች እንዲስተካከሉ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ፤
9. በሥራ አጋጣሚ በደንበኛ ላይ የሚደርሱ የንብረት ጉዳቶችን ለመሸፈን የመድህን ዋስትና የመግባት፤
10. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግስት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፤
11. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋልና በራሱ ስም የመክሰስ ወይም የመከሰስ፤
12. ሀገራችን ከገባቻቸው ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር የማይጣረሱ ስምምነቶችን ከሌሎች አካላት ጋር ማድረግ፤
13. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

7. <u>**የጽሕፈት ቤቱ አቋም**</u>

ጽሕፈት ቤቱ፡-

1. የአክሬዲቴሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

8. <u>**የምክር ቤቱ አባላት**</u>

1. ምክር ቤቱ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚሰየሙ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላትና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ አስፈላጊው የአክሬዲቴሽን ልምድና እውቀት ያላቸው ሰብሳቢውን ጨምሮ ከ 10 እስከ 15 አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡
3. የምክር ቤቱ አባላት የአገልግሎት ዘመን 5 ዓመት ሲሆን በድጋሚ አንድ ጊዜ ለተጨማሪ አምስት ዓመት ብቻ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

9. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በጽሕፈት ቤቱ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የአክሬዲቴሽን ስትራቴጂዎች በመገምገም ያፀድቃል፤
2. ከባለድርሻ አካላት የሚነሱ ከአክሬዲቴሽን ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ጽሕፈት ቤቱን ያማክራል፤
3. አክሬዲቴሽንን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

10. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>

1. ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
2. የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ሲሆን፣ ድምጽ እኩል ለዕኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥርዓት መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የጽሕፈት ቤቱን ሥራ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ላይ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የጽሕፈት ቤቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

መ) አክሬዲት ለሆኑ ተቋማት የአክሬዲቴሽን ሰርተፍኬት ፈርሞ ይሰጣል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

12. <u>በጀት</u>

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

14. <u>የአክሬዲቴሽን ተጠቃሚ በሆነ ተቋም ስለሚሰጡ ሪፖርቶች እና ሰርተፍኬቶች</u>

አክሬዲትድ በሆኑ ተቋማት የሚሰጡ ሪፖርቶች እና ሰርተፍኬቶች አክሬዲትድ በሆኑበት መስክ፣ ብቃታቸው በተረጋገጠ ባለሙያዎች የተፈረመ ከሆነና አክሬዲትድ ከሆኑ በኋላ የወጡ ከሆኑ ተቀባይነት ያላቸው ሕጋዊ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

15. <u>ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

ማንኛውም በአክሬዲቴሽን ተግባር ላይ የተሳተፈ ሰው በሥራ አጋጣሚ ያገኛቸውን መረጃዎች ከሚከተሉት በስተቀር ለሌሎች አካላት መግለጽ የለበትም፦

1. ለጽሕፈት ቤቱ፣
2. ለጉዳዩ ባለቤት፣
3. በፍርድ ቤት በመረጃነት የተጠየቀ እንደሆነ፣
4. መረጃው አግባብነት ባለው መንግስታዊ ተቋም ለተቋማዊ ሥራ ወይም ለወንጀል ምርመራ የተፈለገ እንደሆነ፣
5. ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ፡፡

16.<u>ክልከላ</u>

በአክሬዲቴሽን አሰስመንትና በአክሬዲቴሽን አጽዳቂ ኮሚቴ አባልነት የሚሰማራ ባለሙያ በተስማሚነትና ምዘና የማማከር ሥራ መስራት የለበትም፡፡

17.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማትን ብቃት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ጽሕፈት ቤቱ ለሚያከናውነው የታቀደ ወይንም ድንገተኛ የክትትል አሰስመንት ተቋማቱና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ተቆጣጣሪ ተቋማት፣ ብሔራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲቲዩት እና የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

18.<u>ስለ አክሬዲቴሽን ሠርተፍኬት አሰጣጥና አጠቃቀም</u>

1. አክሬዲቴሽን ሰርተፍኬት አክሪዲት ለሆኑ ተቋማት የሚሰጠው በጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ወይም እርሱ በሚወክላቸው ኃላፊዎች ተፈርሞ ይሆናል፡፡
2. ትክክለኛው የአክሬዲቴሽን ሠርተፍኬት በሕግ ፊት የሚፀናው በሰርተፍኬቱ ላይ የተገለፁትን የብቃት ወሰኖች በተመለከተ ብቻ ይሆናል፡፡
3. የአክሬዲቴሽን ሰርተፍኬቱ ንብረትነቱ የአክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ሲሆን ደንበኛው ሠርተፍኬቱን እንዲመልስ ሲጠየቅ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

19.<u>የተሻረ እና ተፈጻሚነት የማይኖረው ደንብ</u>

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 279/2005 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. ይህን ደንብ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

20.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 13 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ረ/ ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 388/2008 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤትና ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 5 እና 39 መሠረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤትና ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 388/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር ፦

1. “ባዮቴክኖሎጂ” ማለት ሕይወት ያላቸውን ደቂቅ አካላት/ዘአካላት ወይም ሀዋስ ወይም በእነሱ የሚመረቱ ቁሶችን በዘመናዊ የቤተ ሙከራ ዘዴዎች በመጠቀም የተለያዩ ስነ-ሕይወዊ ወይም ኬሚካላዊ ሂደቶችን በማሻሻል ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ የግብርናና የህክምና፣ የኢንዱስትሪ፤ የአካባቢ ጥበቃና የመሳሰሉትን ተግባራት በማከናወን ውጤት የማምጣት ሂደት ነዉ፤
2. “ምርምር” ማለት አዕምሯዊ ዕውቀትን በመጠቀም አዲስ ነገር ለማግኘት፣ ዘዴዎችንና አሠራሮችን ለመፍጠር፤ ለመተንተን የሚደረግ ሳይንሳዊ ጥናት ሲሆን የሰዉ ልጆችን ዕዉቀት በማጎልበት የህበረተሰቡንና የልማት ችግሮችን የሚፈታና ኑሮን የሚያሻሽል እንቅስቃሴ ነው፤
3. “የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት” ማለት ሥነ-ሕይወታዊ ሂደቶችንና ባህርያታቸውን በማጥናት፤ በመረዳትና በማበልጸግ ወደ ጠቃሚ ውጤቶችና አገልግሎት የመለወጥና በግብርና፤ በጤና፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በኢንዱስትሪና በሌሎች የልማት ዘርፎች በዘመናዊ ዘዴ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚከናወን ሳይንሳዊ ምርምር ነው፤
4. “አገራዊ የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ሥርዓት” ማለት በአገሪቱ ውስጥ በባዮ ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ተግባር የተሰማሩት ተቋማት ስብስብ ነው፤
5. “ተቋም” ማለት የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማትን ለማካሄድ በህግ የተፈቀደለት የፌደራል፤ የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ ወይም መንግስታዊ የልማት ወይም የግል ድርጅት ነው፤
6. “የቴክኖሎጂ ሽግግር” ማለት በኢንዱስትሪዎች፤ በዩኒቨርስቲዎች፤ በመንግሥትና በሌሎች ተቋማት መካከል የሚደረግ የሙያ የዕውቀት የክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ዘዴዎችን የአመራረት ዘይቤዎችን የምርት ናሙናዎችን የመለዋወጥ ሂደት ሆኖ በውጤቱም ሳይንሳዊ ቴክኖሎጂአዊ እድገቶች ለተጠቃሚ የሚደርሱበትና ተጠቃሚውም ቴክኖሎጂውን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ ጥቅም፣ ቁሳቁስ ወይም አገልግሎት የሚቀይርበት ሂደት ነው፤
7. “የዕዉቀት ኢኮኖሚ” ማለት በሳይንስ ላይ በተመሠረተ ዕውቀት የሚገነባ ኢኮኖሚ ማለት ነው፤
8. “ተዛማጅ ሳይንሶች” ማለት ከባዮቴክኖሎጂ ጋር ተመጋግበው ሊተገበሩ የሚችሉ ሥነ-ኽይወታዊ ሂደቶችን የሚያጠኑ ወይም በአገልግሎትና ምርት ዝግጅት ላይ

ከሥነ ሕይወታዊ ሂደቶች ጋር በመጣመር የላቀ ምርትና አገልግሎት ሊያስገኙ የሚችሉ ፊዚካል ኬሚካል፣ ወይም ኮምፒዩቴሽናል መሠረት ያላቸው እንደ ኢንፎርሜሽን ቴከኖሎጂ፣ ናኖ ባዮቴክኖሎጂ፣ ባዮማቴሪያል ሳይንስ፣ ባዮ ኦቶሜሽን እና የመሳሰሉት ናቸው፤

9. “በቃይ ወይም ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ” ማለት አዲስ ወይም ነባር በሆነ እና በተሻሻለ እውቀት ላይ መሰረት የሚያደርጉ በፈጣን ልማት ረገድ ከፍተኛ የሆነ የመወዳደሪያ አቅምን መገንባት የሚያስችሉ በኢኮኖሚው በማህበራዊው እና በፖለቲካዊው ምህዳር ተጨባጭና ዘላቂ ለውጥ ወይም እድገት ማስመዝገብ የሚያስችሉ ጠቀሜታቸው ዘርፍ-ብዙ የሆነ፣ ተቀባይነታቸዉ እያደገ የመጣ እና በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ደረጃ ለተፈጠሩትና ለሚፈጠሩት ችግሮች መፍትሄ ለማስቀመጥ ዕድሉን የሚፈጥሩ ቴክኖሎጂዎች ማለት ሲሆን ናኖ ቴክሎጂ ማቴሪያል ሳይንስ፤ ምልስ ምህንድስና፣ አርቴፊሻል ኢንተሌጀንስ እና የመሳሰሉትን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዘርፎች የሚያጠቃልል ነው፤

10. “ናኖ ቴክኖሎጂ” ማለት የንጥረ ነገሮችን ሞለኪዩላራዊ አካላዊ እና ባዮሎጂካላዊ ባህሪዎችንና መዋቅሮችን በአንድ ቢሊዮነኛ ሜትር መለኪያ ወይንም በአቶም ወይንም በሞለኪዩላር ደረጃ በመመራመርና በመቀየር አዳዲስ ባህሪ የተላበሱ ምርቶችን፤ መሣሪያዎችንና ሥርዓቶችን የመፍጠር ሂደት ላይ የሚያጠና ዘርፍ ነዉ፤

11. “ማቴሪልስ ሳይንስ” ማለት ስለተለያዩ ቁሶች አካላት (ማቴሪያሎች) ምንነት የዓይነት (ሴራሚክ፣ ሜታል፣ ፖሊመርና ኮምፖዚት) ፣ ባህሪ፤ አወቃቀር፤ ጠቀሜታ እና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን የሚያጠና፤ በባህሪቸዉም መሠረት መተንተንና መተግበር ላይ የሚያተኩር የሳይንስ ዘርፍ ነዉ፤

12. “ምልስ ምህንድስና” ማለት አንድን የቴክኖሎጂ ዉጤት እንዴት እንደተሰራ በማጥናትና ምርቱን በይበልጥና በቀላል መንገድ እንደገና የመስራት ወይም የማባዛት ሂደት ላይ የሚያተኩር የቴክኖሎጂ ዘርፍ ነወ፤

13. “አርተፊሻል ኢንተሌጀንስ” ማለት አስተዉሎት ተኮር ስርዓቶችንና የኮምፒዉተር ፕሮግራሞችን በማበልጸግ መሳሪያዎችንና አገልግሎቶችን ሰዉ ሰራሽ አስተዉሎት በተላበሰ መልኩ እንዲተገበሩ የሚስያችል የቴክኖሎጂ ዘርፍ ነዉ፤

14.“የገንዘብ ድጋፍ” ማለት መንግሥት ለዘርፉ መሥሪያ ቤቶች ከሚመድበው የምርምርና ልማት ቋሚ የበጀት ድጋፍ በተጨማሪ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ነው፤

15.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 የተመለከተዉ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

16.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ሚኒስትር ነው፤

17.“ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

18.ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ የባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤት

3. **መቋቋም**

የኢትዮጵያ የባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

4. **የምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

1. ጠቅላይ ሚኒስትር ................................ ሰብሳቢ
2. የትምህርት ሚኒስትር .......................... አባል
3. የእርሻ እና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስትር... አባል
4. የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ............................ "
5. የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር...."
6. የኢንዱስትሪ ሚኒስትር .......................... "
7. የእንስሳት እና የዓሳ ሀብት ልማት ሚኒስትር..."
8. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ....... "
9. እንደአስፈላጊነቱ በመንግሥት ዉሳኔ የሚሰየሙ ዘርፎች ኃላፊዎች
10. የባዮቴክኖሎጂ እዉቀትን ከግምት ውስጥ ያስገባ በመንግስት የሚሰየሙ ተመራማሪዎች ................... "
11. የኢትዮጵያ የባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ......አባልና ጸሐፊ

5. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፖሊሲ ያወጣል፣ አገራዊ ስትራተጂ ይነድፋል፣ በአገር ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዋና ዋና የምርምርና ልማት ፕሮግራሞች ይለያል፣ በየዘርፉ በተግባር መተርጎማቸውን ይከታተላል ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
2. በቴክኖሎጂ ሽግግርና ምርምር ቅንጅት በመፍጠር፣ በማስተባበር በመምራት፣ አቅጣጫ በማስያዝ እና አቅም በመገንባት የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት በተለይም በግብርና፣ በጤና፣ በኢንዱስትሪና በአካባቢ መስኮች ለሀገሪቱ ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
3. የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት አገራዊ የልማት ግብ ላይ ያተኮረ፣ በዕቅድ የሚመራ፣ በቅንጅትና ትስስር የሚፈጸም፣ ለምርትና አገልግሎት መሻሻል ቅድሚያ የሚሰጥ፣ በጥራቱና የውጤት ደረጃው ተወዳዳሪ የሆነ፣ ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግና ከበቃይ ቴክኖሎጂዎች ተፈላጊዎችን እያካተተ የሚያድግ ዘላቂ አገራዊ አቅም እንዲፈጠርና እንዲጠናከር አመራር ይሰጣል፣
4. የባዮቴክኖሎጂ ትምህርት፣ ምርምርና ልማትን ለማጠናከር ልዩ የምርምርና የአገልግሎት ማዕከላት የሚቋቋሙበትንና በሥርዓት የሚመሩበትን ሁኔታ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ለአሠራራቸዉም መመሪያ ያወጣል፣
5. በባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት አርያ ለሆኑ ፈጻሚዎች አና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላስገኙ ኢንዱስትሪዎች የስኬት ዕውቅና ይሰጣል፣ ይሸልማል፣
6. ከየዘርፉ የልማት ፍላጎት በመነሳት በባዮቴክኖሎጂ ምርምር ወደ ምርትነት እንዲሻገሩ የሚፈለጉ ቁልፍ የባዮቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚመረጡበትን፣ ከበቃይና መፃኢ ባዮቴክኖሎጂዎች ውስጥ አግባብ ያላቸው ለምርምርና ልማት አገልግሎት እየተመረጡ የሚካተቱበትን ሥርዓት ያፀድቃል፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ተሳስረዉ የሚለሙበትን አቅጣጫ ያስተምጣል፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን ለማቀፍና ወደ ዕውቀት ኢኮኖሚ ለማደግ የሚያግዝ የሳይንስ ምርምር የሚያጠናክር፣ ፈጠራ የሚያበረታታ እንዲሆን የሚወጡ መመሪያዎች መተግበራቸውን ይከታተላል፣
7. ለሥራው አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

6. <u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. ምክር ቤት በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ሲጠራ አስቸኳይ ስብስባ ሊካሄድ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤት የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## የኢትዮጵያ የባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

7. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኃላ ኢንስቲትዩት ተብሎ የሚጠራ) የህግ ሰዉነት ያለዉ ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

8. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

9. **ዓላማ**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በሀገሪቱ በተለያዩ ሴክተሮች ተበታትነው ያሉ የባዮቴክኖሎጂ እና የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ምርምሮችንና የምርምር መሰረተ ልማቶችን ለሀገሪቱ ዕድገት አስተዋጽኦ በሚያመጣ መልኩ በማቀናጀት ሊያሰራ የሚችል ሥርዓት መፍጠር፤
2. የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት በማስተባበርና በመምራት፤ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት፣ በማላመድና በማበልፀግ፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በአገር ውስጥ እንዲፈጠሩ በማመቻቸትና ለዚህ የሚያስፈልገውን አስቻይ አቅም በመገንባት ሀገራችን የባዮቴክኖሎጂ ልማት ተጠቃሚ እንድትሆን ለማብቃት መሥራት፤
3. ለሀገር ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ባላቸው የባዮቴክኖሎጂና የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂዎች ላይ የምርምርና ልማት ሥራዎችን ማካሄድና ሌሎች ተመሳሳይ ምርምሮችን መደገፍ፤

4. የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት በግብርና፣ በጤና፤ በኢንዱስትሪ፣ በአካባቢና ተዛማጅ ዘርፎች በፍጥነት እንዲጠናከርና ምርትና አገልገሎት ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ለተመራማሪዎች የተመቻቸ የምርምር ዕድል እንዲፈጠር የምርምርና ልማት አጋዥ ማዕከላትን መፍጠር፣ ማጠናከር፤ መምራትና ማስተባባር
5. የባዮቴክኖሎጂን ምርምርና ልማት አቅም በፍጥነት ለመገንባት፣ በአካባቢ ደህንነት ጥበቃና በምርት ጥራት ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻልና የምርምርና ልማቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ የአመለካከት፤ የአሠራር፤ የአደረጃጀትና የአፈፃፀም አስቻይ ሁኔታ የሚያሪጋግጥ ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል፤ ውጤቱም ለሕብሪተሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ የሚዉልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
6. የባዮትክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ሥራዎች የማህበረሰቡን እሴትና ሞራል የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

10.<u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ባዮቴክኖሎጂን እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ የተመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የሀገሪቱን የአጭርና ረጅም ጊዜ የባዮቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ልማት ዕቅዶችን በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. በሀገሪቱ በተለያዩ ሴክተሮች ተበታትነዉ ያሉ የባዮቴክኖሎጂ ምርምሮችንና የምርምር መሠረተ ልማቶችን ለሀገሪቱ ዕድገት አስተዋጽዖ በሚያመጣ መልኩ የሚቀናጁበትን የጋራ አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
4. ከምክር ቤቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ሥርዓቱ አካላት የባዮቴክኖሎጂን ምርምርና ልማት በመደጋገፍ፣ በመቀናጀትና በመናበብ ለምርትና አገልገሎት ውጤታማነት ተባብረው አንዲያካሂዱ አቅማቸውን ይገነባል፤ ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤
5. የባዮቴክኖሎጂ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ የመንግስትን የትኩረት አቅጣጫዎች በተከተለ መልኩ ችግር ፈቺ ምርምሮችን ማከናወን ሌሎች ተመሳሳይ ምርምሮች እንዲደረጉ መደገፍ፤ በዘርፉ ለሚደረጉ ምርምሮችም ልዩ ልዩ ድጋፍና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

6. የባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ቁልፍ ለሆኑ የባዮቴክኖሎጂ ፕሮግራሞቸች ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ከውጪ ሃገራት ጋር ለሚደረጉ የትብብር ስምምነቶች መመሪያና ሥርዓት ያወጣል፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማረጋገጥ ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የሚያደርጉትን ጥረት ያስተባብራል፣ በቴክኖሎጂ ምርጫና የሽግግር ሂደት ላይ የቴክኒክና አንዳስፈላጊነቱ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፤
7. ከየዘርፉ የልማት ፍላጎት በመነሳት በባዮቴክኖሎጂ ምርምር ወደ ምርትነት እንዲሻገሩ የሚፈለጉ ቁልፍ የባዮቴክኖሎጂ ዉጤቶችን አስቀድሞ በጥናት ይለያል፤ ምርምር ያደርጋል፣ እንዲደረግባቸዉ ያስተባብራል፤ድጋፍ ይሰጣል፤ ለባዮቴክኖሎጂ ስልጠና፤ ምርምርና ልማት የዕዉቀትና ክህሎት ሽግግርና አቅም ግንባታ አጋር ተቋማትን ያፈላልጋል፤
8. ለባዮቴክኖሎጂ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት የሰው ኃይል አቅም ግንባታ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተጋገዝ እንደአስፈላጊነቱ ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ምርምር በገንዘብ የሚደገፉበትን መንገድ ያመቻቻል፤ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር የጥራት ደረጃ ይገመግማል፤ ጥራት በማረጋገጥ ያግዛል፤
9. ውጤታማ የባዮቴክኖሎጂ የትምህርት፣ የምርምርና የልማት የሰው ኃይል የማቆያና የማትጊያ ሥርዓት እንዲኖር ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅርብ ይሠራል፤ አስፈላጊ ጥናቶችን በማድረግ የውሳኔ ሃሳቦችን ለምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፤ ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፤
10. የባዮቴክኖሎጂን የትምህርትና የምርምር መሠረተ ልማት ፍላጎት አገር አቀፍ ዳሰሳ ያደርጋል፤ የአቅም ግንባታ የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅቶ በምክር ቤት ያስጸድቃል፤ የባዮቴክኖሎጂን ትምህርት፣ ምርምርና ልማት ለማጠናከር ልዩ የምርምርና የአገልግሎት ማዕከላት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ለአተገባበሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ የምርምር ተቋማትን የመሠረተ ልማት ፍላጎቶች ለማሟላት ይሠራል፤
11. የባዮቴክኖሎጂን ትምህርት፣ ምርምርና ልማት ለማጠናከር የሚቋቋሙትን ልዩ የምርምርና የአገልግሎት ማዕከላት ያጠናክራል፣ ያስተባብራል፤ ተደራሽ ያደርጋል፤

ከሚመለከታቸዉ ጋር በመሆን በአጋዥነት አስተዋፅዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ተቋማትን ተሳትፎ ያጠናክራል፤ ተቀናጅተው እንዲሰሩ ያመቻቻል፤

12.ከባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ሥርዓቱ አካላት ለወጡ ቴክኖሎጂዎች ዕውቀት፣ አሰራሮችና ኢንፎርሜሽን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአዕምሮአዊ ንብረት መብት ባለቤትነትን እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

13.የባዮቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትና ማዕከላትን አቅም ያጠናል፤ የጥራትና የብቃት ደረጃ የመለኪያ መስፈርት በማዘጋጀት በመስፈርቱ መሠረት ይገመግማል፤ ዉጤቱንም አግባብ ላለው አካል በግብዓትነት እንዲያገለግል ያቀርባል፤

14.በባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ሥርዓቱ አካላት የሚቀርቡ አገራዊ መረጃዎችን እና ሳይንሳዊ ጽሁፎችን ያሰባስባል፤ ያደራጃል፤ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ለተመራማሪዎች ተማሪዎችና ተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፤

15.በባዮቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚደረጉ የምርምርና ልማት ተግባራት የማህበረሰቡን የባህልና ሞራል እሴቶች የጠበቁ የዘርፉን የምርምር ሥነ-ምግባር የሚያከብሩ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

16. ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ከሀገር ለማስወጣት ቁጥጥር እንዲደረግባቸዉ በሕግ የተለዩ የባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ፍቃድ መስጠት፣ መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እገዳ ማድረግ፤

17.የባዮተክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች ፣ ጋይድላይኖች፣ ማኑዋሎች፣ ያዘጋጃል፤ በምክር ቤቱ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

18.ከሌሎች በውጭ ሀገር ከሚገኙ የተለያዩ አቻ አካላት ጋር ትብብር መመስረትና ጠቃሚ ልምዶችንና አለራሮችን ቀምሮ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና ለምርምር አጋዥ የሆኑ የቴክኖሎጂ፤ የቴክኒክ እና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

19.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

20.ዓላማውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል።

11.<u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና
2. ከተለያዩ የባዮቴክኖሎጂ ዘርፎች የተውጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎችና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

**12.** <u>**የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ፡ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከምክር ቤቱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂ እና ዝርዝር ፕሮግራም ይቀርፃል፤ ኢንስቲትዩቱን ያደራጃል፤
   ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤
   ሰ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ ክንዉንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል።
3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ለኢንስቲትዩቱ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

**13.** <u>**የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር**</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡

1. የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ስራዎችን ያከናዉናሉ፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል።

14.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

15.<u>ስለ ሒሳብ መዝገብ</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክል የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች ይመረመራሉ

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16.<u>ተባብሮ ስለመስራት</u>

ኢንስቲትዩቱ ከብዝሀ ሕይወትና ከደህንነት ሕይወት ጥበቃ (ባዮሴፍቲ) ጋር ተያያዥነት ባላቸው የባዮቴክኖሎጂ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል።

17.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ 1 ቀን 2008 ዓ.ም.**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 393/2009

## የኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤትን እና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት እና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 393/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1. "ስፔስ" ማለት ከመሬት ከባቢያዊ አየር ውጭ ያሉትን የተፈጥሮ አካላት በሙሉ የሚያጠቃልል ክፍል ነው፤
2. "ኤሮስፔስ" ማለት መሬትና ከመሬት ከባቢያዊ አየር ውጭ ያሉትን የተፈጥሮ አካላት በሙሉ የሚያጠቃልል ክፍል ነው፤
3. "ኤሮስፔስ ሳይንስ" ማለት መሬትና ከመሬት ውጭ ያሉትን የተፈጥሮ አካላትን በሙሉ የሚያጠና ዘርፈ ብዙ ሳይንስ ሲሆን አስትሮኖሚ፣ አስትሮፊዚክስ፣ ሳተላይት ቴክኖሎጂ፣ የመሬት ምልከታ፣ ሪሞት ሴንሲንግ፣ ጂኦዴት፣ ስፔስ ሳይንስ፣ ኤሮናቲክስ፣ አስትሮናቲክስ፣ ስፔስ ኢንጂነሪንግ፣ አትሞስፌሪክ ሳይንስና የመሳሰ ሉትን የሙያ መስኮች በሥሩ አካቶ ይይዛል፤
4. "ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ" ማለት በኤሮስፔስ ሳይንስ ተጠንተው የሰው ልጅ ለልዩ ልዩ ሥራ የሚጠቀምባቸው ቴክኒኮችን፣ ውጤቶችን፣ መሣሪያዎችን እና ዘዴዎችን ያጠቃልላል፤
5. "የኤሮስፔስ ልማት" ማለት የህዋ አካላትን የመመርመር፣ የማጥናትና ተግባራዊ የሚሆኑ የህዋ ቁሶችን ለመንደፍ ለማምረትና ለማምጠቅ የሚካሄድ የምርምር ተግባርና የቴክኖሎጂ ልማት ነው፤
6. "ኤሮናቲክስ" ማለት ኤርክራፍት ዲዛይን፣ ማኑፋክቸር እና ተግባራዊ የሚደረግበት ሳይንስ ሲሆን የኤርክራፍት ሳይንስን፣ ክህሎትን፣ የንድፈ ሀሳብን እና የተግባራዊነቱን ሥራ ጥናት የሚያካትት ነው፤
7. "አስትሮናቲክስ" ማለት የስፔስ ክራፍትና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችን የሚያጠና ሳይንስ፣ እንዲሁም የስፔስ ክራፍት ዲዛይን፣ ግንባታንና ኦፕሬሽን የሚያጠና ዘርፍ ነው፤
8. "ምርምር" ማለት አዲስ ነገር ለመፍጠር፣ ለማላመድ፣ ለማሻሻል፣ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ በሳይንሳዊ ዘዴ የሚካሄድ ተግባር ነው፤

9. "የህዋ ቁሶች" ማለት በኤሮስፔስ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ታስበው የተነደፉና የተፈበረኩ ቁሶች ማለትም የማምጠቂያ ማሽኖችን፣ እንደሳተላይት፣ መንኩራኩር እና የእነዚህን አካላት ያካትታል፤

10. “የስፔስ ላይ በረራ ወይም እንቅስቃሴ” ማለት በሲቪል አቪየሽን አስተዳደር ከሚተዳደረዉ የአየር አገልግሎት ውጭ ያለ ሌላ የበረራ እንቅስቃሴ ነው፤

11. "ሚኒስቴር እና ሚኒስትር" ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ሚኒስትር ማለት ነው፤

12. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

13. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፤

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት

3. **መቋቋም**

የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

4. **የምክር ቤቱ አባላት**

1. ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራ ይሆናል።
2. የምክር ቤቱ አባላት በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰየሙት የምክር ቤት አባላት አሰያየም የስፔስ ሳይንስ እውቀትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል።
4. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር የምክር ቤቱ ጸሐፊ ይሆናል።

5. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

   ሀ) የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎችን፣ ዕቅዶችንና ስትራቴጂዎችን በመገምገም ለሀገሪቱ ፈጣንና ቀጣይነት ላለው ልማት አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ አቅጣጫና አመራር ይሰጣል፤

   ለ) የኢንስቲትዩቱን ዕቅድ ያጸድቃል፣አፈጻጸሙን ይገመግማል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለቀጣይ ተግባር የሚያግዝ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤

ሐ) የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕቅድ በታቀደው መጠንና ጊዜ እንዲሳካ አስፈላጊውን እገዛና ክትትል ያደርጋል፤

2. ምክር ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

6. <u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት</u>

7. <u>**መቋቋም**</u>

1. የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ ኢንስቲትዩት እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡
2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

8. <u>**ዋና መሥሪያ ቤት**</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

9. <u>**ዓላማ**</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. ሀገራችን የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚሰጠውን ፈርጀ ብዙ ጥቅም አሟጣ መጠቀም እንድትችል ማድረግ፤
2. ሀገራችን በኤሮስፔስ ሳይንስ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችላት በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የታነጹ ምሁራንን ከሀገሪቱ ፍላጎት አንጻር ማፍራት፤
3. የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማትን ማፋጠን የሚያስችሉ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂዎችን በምርምር ማልማት፣ ማጠናከር እና ተግባራዊ ማድረግ፤
4. ኢትዮጵያ በኤሮስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ጠንካራ አስተዋፅኦ ያላት ሀገር እንድትሆን ማስቻል።

10.<u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በኤሮስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ዙሪያ ምርምሮችን ማካሄድ፤
2. የሀገሪቱን ነባራዊና መጻኢ ሁኔታ ያገናዘበ የስፔስ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን መቅረጽ እና በመንግሥት ሲጸድቅ ተግባራዊ ማድረግ፤
3. የሀገሪቱን የኤሮስፔስ ልማት ዕቅዶችን ማዘጋጀት እና በመንግሥት ሲጸድቅ ተግባራዊ ማድረግ፤
4. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ከስፔስ ሳይንስ ጋር የተገናኙ ሥራዎችን መደገፍና ከአገሪቱ ልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን መቆጣጠር፤
5. የኤሮስፔስ ልማት ሥራዎችን መንደፍ፣ ማምረትና ማምጠቅ፤
6. የመስኩን የሰው ኃይል በሚያስፈልገው መጠንና ጥራት፣ በተፋጠነ ሁኔታ መፍጠር የሚያስችል ስትራቴጂዎችን መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፤
7. የአገሪቱን ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ለመገንባት የሚያግዙ የምርምር ማዕከላት ማቋቋም፤
8. ለስፔስ ልማት አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ መሣሪያዎችን የአገሪቱ ማኑፋክቸሪንግ ሴክተር ማምረት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ድጋፍ ማድረግ፤
9. ለኤሮስፔስ ልማት አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀትና እውነታ አፈላላጊ ቅኝቶችን ማካሄድ፤
10. በስፔስ ሥራ ላይ ለመሠማራት ለሚፈልጉ አካላት ፍቃድ መስጠት፣ አሠራራቸውን መቆጣጠር፤ ተግባራዊ የሚሆኑ የህዋ ቁሶችን መመዝገብ፤ በአጠቃላይ ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ የሚነሱና በሀገሪቱ አየር ክልል ውስጥ የሚካሄዱ የስፔስ እንቅስቃሴዎችን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር መቆጣጠር፤
11. ከሀገር ደህንነትና ጸጥታ ጋር የተገናኙ የስፔስ በረራ ወይም እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
12. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸውና ለሴክተሩ ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ ሌሎች አጋር አካላት ጋር ትብብር መፍጠርና እንዲጠናከር ማድረግ፤

13. ከብሔራዊ ጥቅማችን ጋር የሚጣጣሙ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶችን መፈራረም፣ በሕግ አውጪው አካል ሲጸድቁ ተግባራዊ ማድረግ፤

14. ዓላማውን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን።

11. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

1. ኢንስቲትዩቱ፡-

ሀ) በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና

ለ) አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሾሙት ዋና ዳይሬክተሮች በስፔስ ሳይንስ ዘርፍ አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መሆን አለባቸው።

12. <u>የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ኢንስቲትዩቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የስራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

13. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፦

1. የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደ ራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ስራዎችን ያከናውናሉ፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል።

14. **<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል።

15. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

16. **<u>የእንጦጦ ኦብዘርቫቶሪና የምርምር ማዕከል</u>**

የእንጦጦ ኦብዘርቫቶሪና የምርምር ማዕከል በኢንስቲትዩቱ አስተዳደር ሥር ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።

17. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው፣ መንግሥታዊ ተቋም ወይም የግል ድርጅት የኢንስቲትዩቱ ዓላማ እንዲሳካ የመተባበር ግዴታ አለበት።

18. **<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

19. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ

አዲስ አበባ ጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሣለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## አዋጅ ቁጥር 1079/2010

## የኢትዮጵያ ጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያን ፈጣንና ዘላቂ ልማት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ከሆኑት ግብአቶች አንዱ አስተማማኝ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን በመሆኑ፤

በአገር ውስጥ የሚከናወኑ በአየር ፎቶግራፍ፣ በቅየሳ፣ በካርታ ሥራ እና በሪሞት ሴንሲንግ ዘዴዎች የአገሪቱን ጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን የማሰባሰብና የማቀናበር ሥራዎች ተገቢውን የአሰራር ዘዴ እንዲከተሉ፣ ደረጃቸውና ጥራታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ለተጠቃሚው ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ፤

መረጃን በተቀናጀና በተደራጀ ሁኔታ ለብሔራዊ ጥቅም እንዲውል ለማስቻል የአየር ፎቶግራፎች፣ የቅየሳ መረጃዎች፣ የካርታዎች እና የሪሞት ሴንሲንግ ሥራዎች ውጤት የሆኑትን መሠረታዊ የምድር መረጃዎች እና ተመሳሳይ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን በአንድ ማዕከላዊ ስፍራ እንዲገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ይህንም ዓላማ በተግባር ላይ ለማዋል አስፈላጊው ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው የፌደራል አስፈጻሚ አካል ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር አዋጅ ቁጥር 1079/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "የአየር ፎቶግራፍ" ማለት ለቅየሳ፣ ለካርታ ሥራ ወይም የመሬትን ሀብት ለማጥናት እንዲቻል የመሬትን ገጽታ ከአየር ላይ በመቅረጽ የሚያዝ ማንኛውም ፖዘቲብ፣ ኔጋቲቭ ወይም አሃዛዊ ምስል ነው፤
   2. "ኮሚሽን" ወይም "ኮሚሽነር" ማለት እንደ ቅደምተከተሉ የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ወይም የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ነው፤
   3. "የጠቅላላ ተግባር ካርታ" ማለት መሠረታዊ ካርታ ሆኖ ለሁለ-ገብ አገልግሎት የሚዘጋጅ ካርታ ነው፤
   4. "ጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን ሲስተም" ወይም "ጂአይኤስ" ማለት ጂኦግራፊያዊ ማጣቀሻ የያዘ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለመተንተንና ለእይታ ለማቅረብ የሚረዳ የኮምፒዩተር መረጃ ሥርዓት ነው፤
   5. "ጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን" ማለት ወቅታዊ ሆኖ በአየር ፎቶግራፍ፣ በቅየሳ፣ በካርታ አነሳስ፣ በሪሞት ሴንሲንግና ጂአይኤስ ዘዴዎች የሚሰበሰብ፣ የሚከማች፣ የሚደራጅ፣ የሚቀናበር እና ለተጠቃሚ የሚቀርብ ጂኦግራፊያዊ ማጣቀሻ ጋር የተዛመደ የቦታ መረጃ ነው፤
   6. "ካርታ" ማለት የገሀዱ ዓለም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካላት በመስፈርት ልኬት መሠረት ተመጥነው ለእይታ የሚቀርቡበት ግራፊክ መገለጫ ነው፤
   7. "ካርታ ሥራ" ማለት የገሀዱን ዓለም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካላት በመስፈርት ልኬት መጥኖ ለማሳየት የሚከናወን የቅየሳ፣ የአየር ፎቶግራፍ፣

የፎቶግራሜትሪ፣ የካርቶግራፊ፣ የሪሞት ሴንሲንግ ወይም ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን ነው፤

8. "ካርታ ዕድሣት" ማለት በሰው ሠራሽ እና ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ምክንያት በመሬት ላይ የተከሰቱ ለውጦችን የሚያሳዩ አዳዲስ መረጃዎችን በነባሩ ካርታ ውስጥ አካቶ በመሥራት ካርታውን ወቅታዊ ማድረግ ነው፤
9. "ብሔራዊ የጂኦዴቲክ መቆጣጠሪያ ነጥቦች" ማለት የቦታዎችን የአግድሞሽ እና/ ወይም የከፍታ መጠን ለመቆጣጠር በጂኦዴቲክ የቅየሳ ዘዴ የሚቋቋሙ የቅየሳ ሥራ መቆጣሪያ ነጥቦች ናቸው፤
10. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ተቋም ነው፤
11. "ሪሞት ሴንሲንግ" ማለት ምርምር ከሚካሄድበት ቁስ ወይም ክስተት ጋር አካላዊ ንክኪ ሳይኖር በርቀት መረጃ ተቀባይ በሆነ መሣሪያ መረጃን ከቁሱ ወይም ከክስተቱ የመሰብሰብ ጥበብ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ነው፤
12. "የሣተላይት ምስል" ማለት በብርሃን፣ ኢንፈራሬድ እና የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ስፔክትረም የሬድዮ ሞገድ በሚታይ ርቀት ምስል ማንሳት በሚችሉ ሳተላይቶች የተቀረፀ አሃዛዊ መረጃ ነው፤
13. "መሥፈርት" ማለት በካርታ ላይ የሚገኙ ሁለት ነጥቦች መካከል ያለ ርቀትና በመሬት ላይ በሚገኙ ተመሳሳይ ቦታዎች ነጥቦች መካከል ያለ ንፅፅራዊ ርቀት በሂሳባዊ ቀመር የሚገኝበት ነው፤
14. "የተለየ ተግባር ካርታ" ማለት በጠቅላላ ተግባር ካርታ ላይ ተመርኩዞ ለአንድ ለተወሰነ ጉዳይ የሚዘጋጅ ካርታ ነው፤
15. "ቅየሣ" ማለት በአንድ የተወሰነ መሬት ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አካሎች አንጻራዊ አቅጣጫ፣ ርቀትና ከፍታ በመለካት የቦታውን መጠንና ቅርጽ ለማሳየት የሚከናወን ተግባር ነው፤
16. "አትላስ" ማለት በመጽሐፍ መልክ የተዘጋጀ በማብራሪያና በገላጭ ቻርቶች የተደገፈ ካርታ ነው፤
17. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ወታደራዊና ሀገራዊ ደህንነትን በሚመለከቱ የጂኦ-ስፓሺያል መረጃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ ዓላማ፣ ሥልጣን እና ተግባራት

4. **መቋቋም**
   1. የኢትዮጵያ ጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት[54] (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
   2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ይሆናል፡፡
5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡
6. **ዓላማዎች**

   ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦
   1. የአየር ፎቶግራፍ፣ የቅየሣ፣ የካርታ ሥራ፣ የሪሞት ሴንሲንግ እና ተዛማጅ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ሥራዎችን ማቀድና ማከናወን፣ ውጤቱንም መዝግቦ መያዝና ለተጠቃሚው ማሰራጨት፤
   2. በኢንስቲትዩቱ የተመረተውን የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን በመሰብሰብና በማዕከል ማደራጀት ውጤታማ በሆነ አግባብ መረጃውን ተደራሽ በማድረግ ድግግሞሽን ለማስቀረት እና ወጪን መቀነስ በሚያስችል መልኩ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤
   3. በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱ የአየር ፎቶግራፍ፣ የቅየሳ፣ የካርታ ሥራ፤ የሪሞት ሴንሲንግ እና ተዛማጅ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ተግባራትን ጥራትና ደረጃዎች መቆጣጠርና ማስተባበር፣ ለማንኛውም የቅየሳ የካርታና የሪሞት ሴንሲንግ ባለሙያ የሙያ ደረጃና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤ ዝርዝሩ በደንብና በመመሪያ ይወሰናል፤

[54] በ25/8(2011) አ.1097 አንቀፅ 36(24) መሰረት የተቋሙ ስያሜ ከ “ኤጀንሲ” ወደ “ኢንስቲትዩት” በግልፅ ሳይነገር ተቀይሯል፡፡ በዚህም መሰረት በአዋጁ ውስጥ ስያሜው ተቀይሮ ተቀምጧል፡፡

4. የቅየሳ፣ የካርታ ሥራና የሪሞት ሴንሲንግ እና ተዛማጅ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ሥራ ምርታማነትና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሚረዱ የምርምርና ሥልጠና ሥራዎች ማከናወን፣

7. <u>ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የአገሪቱ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ማዕከል ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን መሰብሰብ፣ ማምረት፣ ማከማቸት፣ ማደራጀት፣ ማስተዳደር እና ማሰራጨት፤
2. አቅጣጫን፣ ርቀትንና ከፍታን ለመወሰን የሚያስችሉ የጂኦዴቲክ የመሬት መቆጣጠሪያ ምልክቶችን በሀገር ውስጥ መዘርጋት፣ የተዘረጉትን መጠበቅ፣ ማስጠበቅና ማስተዳደር፤
3. የቅየሣ ሥራዎችን ማከናወን፣ ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ መተንተን እና የተገኘውን ውጤት ማሰራጨት፤
4. የጠቅላላ ተግባር ካርታ ማዘጋጀት፣ ማምረትና ማሰራጨት፤
5. የተለየ ተግባር ካርታ ማዘጋጀት፣ ማምረትና ማሰራጨት፤
6. የተዘጋጁትን የጠቅላላ ተግባርና የልዩ ተግባር ካርታዎችን ወቅታዊ ሁኔታውን እንዲያሳዩ ለማድረግ የካርታ ዕድሳት ሥራ መሥራት፤
7. አገራዊና ክልላዊ አትላሶችን እንዲሁም በተለየ ርዕስ የሚያተኩሩ አትላሶችን ማዘጋጀት፣ ማሳተምና ማሰራጨት፤
8. በሌሎች አካላት የሚሰሩትን የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ምርቶችን ማስተባበር እና መቆጣጠር፤
9. በአገሪቱ ውስጥ በፌደራል ደረጃ በጂኦ-ስፓሻል ተግባራት ላይ ለሚሰማሩ ግለሰቦችም ሆነ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤
10. የአገሪቱ ዓለም አቀፍ ድንበር እና የክልል ወሰኖች በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ሲወሰኑ በካርታ ላይ ማስፈር፤ እንዲሁም አግባብ ላላቸው አካላት መተለም፣ ማመላከትና ማስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፤
11. የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ሥራዎችን ለመስራት የሚያስችል የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያግዝ የሥልጠና ፕሮግራም መንደፍና ማሰልጠን፤

12. የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ሥራዎችን በተገቢው ሁኔታ ለማምረት የሚያስችሉ የምርምር ሥራዎችን ማቀድ እና ማከናወን፤
13. በወጪ መጋራት መርህ ላይ የተመሰረተ የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ማጥናት እና በመንግሥት ሲጸድቅ ተግባራዊ ማድረግ፤
14. የንብረት ባለቤት መሆን፤ ውል መዋዋል፤ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
15. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

**ክፍል ሦስት**

**አደረጃጀት እና አሰራር**

8. **የኢንስቲትዩቱ አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና
2. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

9. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን በኮሚሽኑ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ (6) የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ሰራተኞች በፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ፕሮግራም እና ማስፈጸሚያ በጀት አዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤በመንግሥት ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት እያዘጋጀ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤

ሰ) በየጊዜው ከኮሚሽኑ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባራቱ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና ለሌሎች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡

10.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፡-

1. የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፡፡
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የተሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሠራል፡፡

11.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

1. በመንግሥት የሚመደብ በጀት፤
2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ከሰበሰበው የውስጥ ገቢ የሚፈቀድ ገንዘብ፡፡

12.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡[55]
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

13.<u>ክልከላ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 7(10) እና በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰው፡-

1. የጂኦዴቲክ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መመስረት፤

---
[55] በማሻሻያ ቁጥር 13/2010 ታረመ፡፡

2. የጠቅላላ አገልግሎት ካርታ ማዘጋጀት፤
3. ኢንስቲትዩቱን አስቀድሞ ሳያስፈቅድ የአየር ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም የተለየ ተግባር ካርታ ማዘጋጀት፣ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችና በሌሎች በማናቸውም ሚዲያዎች እነዚህን ፎቶግራፎች ማባዛት፣ ማሳተም፣ ማሰራጨት ወይም መሸጥ፤

አይችልም፡፡

14.<u>የባለቤትነት መብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያዘጋጃቸው እና እንዲዘጋጁ በሚያደርጋቸው ካርታዎች፣ የአየር ፎቶግራፎች፣ የሪሞት ሴንሲንግ መረጃዎች፣ የቅየሳ መረጃዎች፣ የጂኦዴቲክ መቆጣጠሪያ ነጥቦች፣ አትላሶች፣ የቦታ ስም መድብሎች፣ ሌሎች ተዛማጅ አሃዛዊና ግራፊክ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን፣ ሕትመቶች፣ መጽሔቶች፣ ላይ የባለቤትነት መብት ይኖረዋል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ጥቅም ወይም ትርፍ ለማግኘት ሲል የልዩ ተግባር ካርታዎችንና አትላሶችን ለማዘጋጀት፣ ለመሥራት፣ ለማተም ወይም ለማሰራጨት ኢንስቲትዩቱ ያመረታቸውን የአየር ፎቶግራፎች፣ የጠቅላላ ተግባር ካርታዎች እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ባለቤት በሆነባቸው ሌሎች የምድር መረጃ ውጤቶችና ሥራዎች ለመጠቀም ከኢንስቲትዩቱ ጋር አስቀድሞ ስምምነት ላይ መድረስና በመንግሥት በተወሰነው ተመን መሠረት የፈጠራ መብት ሮያሊቲ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

15.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦች ያወጣል፡፡
2. ኢንስቲትዩቱ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

16.<u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር 193/1973 (እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

17.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 29 ቀን 2010ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 440/2011

## የጂኦስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 32(9) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፤

የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባር በአዋጁ ላይ ያልተመለከተ በመሆኑንና ይህንን በዝርዝር በደንብ ማመልከት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32 (9) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የጆኦ-ስፓሺል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 440/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
2. "ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን" ማለት በቃኝ ወይም በተለያዩ የቅየሳ መሣሪያዎች በመታገዝ ከህዋ፣ ከአየር ወይም ከምድር ላይ በመሆን በገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር ያለውን ተፈጥሯዊ ሀብት ወይንም ሰው ሰራሽ ገጽታዎችንና ወሰኖችን፣ የጂኦግራፊያዊ መገኛ ቦታቸውን እና ባህሪያቸውን የሚያሳይ የተጠናቀረ ኢንፎርሜሽን ነው፡፡
3. "ጂኦስፓሻል መረጃ መሠረተ ልማት" ማለት የተለያዩ አይነት ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽኖች የሚሰበሰቡበት፣ የሚቀናበሩበት፣ የሚደራጁበት፣ የሚተነተኑበት፣ ስታንዳርዳይዝ የሚደረጉበት፣ በሜታ ዳታ ስርዓት፤ የቴክኖሎጂ፣ የፖሊሲዎች እና ተቋማዊ አደረጃጀትን የያዘና መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ምቹ በሆነ መንገድ ተደራሽ ለማድረግ የሚደራጅ ማዕቀፍ ነው።
4. "ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ" ማለት ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽንን ለማሰባሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለመተንተን እንዲሁም ለማሰራጨት የሚያስችሉ በህዋ፣ በአየር እና በመሬት ላይ የሚንቀሳቀሱ ወይም የሚተከሉ ቴክኖሎጂዎች ናቸው፡፡
5. "ሪሞት ሴንሲንግ" ማለት ስለ አንድ አካል ወይንም ክስተት ምንም አይነት አካላዊ ንክኪ ሳይኖር ከህዋ፣ ከአየር ወይም ከምድር ላይ በሚቃኙ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን የመሰብሰብ ሳይንስ ነው።
6. "ጂኦደሲ" ማለት የመሬትን ቅርጽ፣ ስፋት፣ ይዘት እና የመጠነ ለውጥ ሂደትን የምናጠናበት ሳይንስ ማለት ነው፡፡
7. "ጂኦ ዳይናሚክስ" ማለት የመሬትን ቅርጽ፣ ስፋት፣ ይዘት እና የመጠነ ለውጥ በጊዜ ሂደት የሚቀያየርበትን ሁኔታ የምናጠናበት ሳንሳዊ ሂደት ነው፡፡
8. "ፎቶግራሜትሪ" ማለት በመሬት ገጽ ላይ የሚገኝ የማንኛውም አካል ትክክለኛ ቦታ ከአየር ወይንም ከህዋ ከተነሳ ፎቶ ወይንም የሳተላይት ምስል በመለካት

ለማወቅ የሚደረግ የፎቶግራፍ ወይንም የሳተላይት ምስል ፕሮሰሲንግ እና ልኬት ሳይንስ ነው።

9. “ጂአይኤስ” ማለት የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን እና ተያያዥ ገላጭ ኢንፎርሜሽኖችን ለማስገባት፣ ለማከማቸት፣ ለመተንተን፣ ለማስተዳደር እንዲሁም ለእይታ ለማቅረብ እና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስርአት ነው።
10. “የቅየሳ ቴክኖሎጂዎች” ማለት በመሬት ላይ የሚገኙ ገጽታዎችን ከፍታ ወይንም ቁመት፣ ርቀት፣ አንግል፣ አቅጣጫ ለመለካት የሚጠቅሙ በአካል ወይም በርቀት የምንጠቀማቸው መሳሪያዎች ናቸው።
11. “ጥሬ ዳታ” ማለት ያልተተነተነ እና አይነተኛ ትርጉም ያልተሰጠው ጥቅም ላይ የሚውል ጥሬ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ግብአት ነው።
12. ” ጂኦስፓሻል ዳታ” ማለት ያልተተነተነ እና አይነተኛ ትርጉም ያልተሰጠው ለጠቀሜታ የሚውል ጥሬ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ግብአት ነው።
13. “የተጣራ ጂኦስፓሻል ዳታ” ማለት የተተነተነ እና ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውል የተለየ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን መረጃ ማለት ነው፡፡
14. “ሜታ ዳታ” ማለት ስለአንድ ዳታ የሚቀርብ ጥቅል ኢንፎርሜሽን ሆኖ ስለ ኢንፎርሜሽኑ ምንጭ፣ የዳታ ይዘት፣ ወቅታዊነት፣ ማን እንዳዘጋጀው፣ ጥራቱ…ወዘተ የያዘ ገላጭ ኢንፎርሜሽን ነው።
15. ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን አሰባሰብ” ማለት ከህዋ፣ ከአየር እና ከምድር ላይ በመሆን የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚደረግ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን አሰባሰብ ነው።
16. “ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ክምችት” ማለት የተሰበሰበ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽንን በተለያዩ የዳታ ቤዝ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ማከማቸት ነው።
17. “ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ትንተና” ማለት የተለያዩ የጂአይኤስ፣ የሪሞትሴንሲንግ፣ ፎቶግራሜትሪ እና የቅየሳ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽንን መተንተን ነው።
18. “ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ስርጭት” ማለት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶችን በመጠቀም የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽንን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ ነው።

19.“የጂኦስፓሻል ፖሊሲ” ማለት የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ ደህንነትን፣ባለቤትነትን፣ ግደታንና መብት ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ ማዕቀፎች ማለት ነው።

20. “የተነባበረ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን” ማለት ተመሳሳይ ቦታ እንዲሁም የኮኦርዲኔት ስርአት የሚጋሩ በአይነት ከአንድ በላይ የሆኑ የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ስብስብ ነው።

21.“ካርታ” ማለት የገሀዱ ዓለም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካላት ገጽታና አቀማመጥ በመስፈርት ልኬት መሠረት ተመጥነው የሚቀርቡበት ግራፊክ መገለጫ ነው፡፡

22.“ካርታ ሥራ” ማለት የገሀዱን ዓለም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካላት በመስፈርት ልኬት መጥኖ ለማሳየት የሚከናወን የቅየሳ፣ የአየር ፎቶግራፍ፣ የፎቶግራሜትሪ፣ የካርቶግራፊ፣ የሪሞት ሴንሲንግ ወይም ተመሳሳይ የጂኦስፓሻል መረጃን ተጠቅሞ ግራፊክ መገለጫ የማዘጋጀት ተግባር ወይም ስራ ነው፡፡

23.“ካርታ ዕድሣት” ማለት በሰው ሠራሽ እና ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ምክንያት በመሬት ላይ የተከሰቱ ለውጦችን የሚያሳዩ አዳዲስ መረጃዎችን በነባሩ ካርታ ውስጥ አካቶ በመሥራት ካርታውን ወቅታዊ ማድረግ ነው፡፡

24.“ብሔራዊ የጂኦዴቲክ መቆጣጠሪያ ነጥቦች” ማለት የቦታዎችን የአግድሞሽ እና የከፍታ መጠን ለመቆጣጠር በጂኦዴቲክ የቅየሳ ዘዴ የሚቋቋሙ የቅየሳ ሥራ መቆጣሪያ ነጥቦች ናቸው፡፡

25.“ሳተላይት” ማለት ለተለያየ አገልግሎት የሚውል በመሬት ዙሪያ በራስ ምህዋር የሚሽከረከር ሰው ሰራሽ ቁስ ነው፡፡

26.“የሣተላይት ምስል” ማለት በብርሃን፣ ኢንፈራሬድ እና የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ስፔክትረም የሬድዮ ሞገድ በሚታይ ርቀት ምስል ማንሳት በሚችሉ ሳተላይቶች የተቀረፀ አሀዛዊና ግራፊክስ መረጃ ነው፡፡

27. “መሥፈርት” ማለት በመሬትም ላይ ሆነ በአየር ላይ የሚገኙ ሁለትና ከዚያ በላይ አካላት መካከል ርቀት፣ ክብደት፣ መጠን ያለ ንፅፅራዊ ልኬት የሚለካበት ማለት ነው፡፡

28.“የተለየ ተግባር ካርታ” ማለት በጠቅላላ ተግባር ካርታ ላይ ተመርኩዞ ለአንድ ለተወሰነ ጉዳይ የሚዘጋጅ ካርታ ነው፡፡

29.“ቅየሣ” ማለት በአንድ የተወሰነ መሬት ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አካሎች አንጻራዊ አቅጣጫ፣ ርቀትና ከፍታ በመለካት የቦታውን መጠንና ቅርጽ ለማሳየት የሚከናወን ተግባር ነው፤

30.“አትላስ” ማለት በመጽሐፍ መልክ የተዘጋጀ በማብራሪያና በገላጭ ቻርቶች የተደገፈ ካርታ ነው፤

31.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፤

32.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

**3. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

**4. ዓላማዎ**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በጆኦስፓሻል ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ጂኦ-ኢንፎርሜሽን ዘርፍ የምርምር ስራዎችን ማከናወን፣ የጂኦስፓሽል መሰረተ ልማት መገንባት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በማላመድ እና በመጠቀም የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚ አካላት ተደራሽ ማድረግ፤
2. በጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ልማት እና ምርምር ግብዐት ሊሆኑ የሚችሉ የአቅጣጫ ጠቋሚ ሳተላይት መረጃዎችን፤ የመሬት ምልከታ፣ የአየር ፀባይ እና የአየር ንብረት ሳተላይት ምስሎችን፣ የአየር ፎቶግራፎችን፣ የቅየሣ፣ የካርታ ሥራ፣ እና ተዛማጅ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን መረጃዎችን ከአገሪቱ የልማት ሥራዎች ጋር እንዲተሳሰሩ በማድረግ የተለያዩ የምርምር ተግባራትን ማቀድና ማከናወን፣ ውጤቱን በሳይንሳዊ ዘዴዎች በመተንተን ለተጠቃሚው ተደራሽ በማድረግ፤
3. በአገሪቱ ውስጥ የሚተገበሩ የቅየሳና የጂኦዴቲክ ኔትወርክ መሰረተ ልማት ግንባታ፤ የመሬት ምልከታ፣ የአየር ፀባይ እና የአየር ንብረት ሳተላይት ምስል ቀረጻዎችን፣ የአቅጣጫ ጠቋሚ ሳተላይት መረጃዎችን፣ የአየር ፎቶግራፍ፣ የካርታ ሥራ፤ እና ተዛማጅ የጂኦ-ስፓሺያል መረጃዎችን መሰብሰብ፤ማደራጀት፤ ማስተባበር፤መቆጣጠር እና ለተጠቃሚው ተደራሽ በማድረግ፤

4. በጂኦ-ስፓሺያል ሳይንስ፣ቴክኖሎጅ እና ኢንፎርሜሽን ዘርፍ የምርምርና ስርፀት ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችሉ የጥናት እና ምርምር ማዕከላትን እና ላቦራቶሪዎችን በማደራጀት የምርምር ስራዎችን ማከናወን፤
5. በጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ዘርፍ ተጠቃሚ ተቋማትን በስልጠና አቅማቸውን በመገንባት እና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር ምርታማነትና ተጠቃሚነታ ቸውን ማሳደግ፤
6. በጂኦ-ስፓሺያል የሙያ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የሙያ ደረጃና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፡፡

5. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በጂኦስፓሻል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ፖሊሲና እስትራቴጂ ይነድፋል፣የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል በመንግስት ሲጸድቅ ይተገብራል፤
2. የጂኦስፓሻል ምርምርን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን፣ ላቡራቶሪዎችን፣ መረጃ መቀበያ ጣቢያዎችን፣ የመረጃ ማቀነባበሪያና ማከማቻ መሰረተ ልማቶችን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የምርምር መሰረተ ልማት ያደራጃል፤
3. የጂኦስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ሥራዎችን በተገቢው ሁኔታ ለማምረት የሚያስችሉ
   የምርምር ሥራዎችን ያቅዳል፣ ያከናውናል፤
4. በጂኦስፓሻል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አቅምን ለመገንባት የምርምርና ልማት ማዕከላትን ያደራጃል፤
5. የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽንን ይሰበስባል፣ ያመርታል፣ ይተነትነል፤ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
6. አቅጣጫን፣ ርቀትንና ከፍታን ለመወሰን የሚያስችሉ የጂኦዴቲክ ኔትወርክ፣ የመሬት ቅየሳና መቆጣጠሪያ ምልክቶችን በሀገር ውስጥ ይዘረጋል፣ ይጠግናል፤ያስፋፋል፤ያስተዳድራል፤
7. የተለያየ መሰፈረት ያላቸውና ለተለያየ አገልግሎት ሊዉሉ የሚችሉ ካርታዎችን ያዘጋጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤ እንዲሁም የተለየ ተግባር ካርታ ያዘጋጃል፤

8. የተዘጋጁትን የጠቅላላ ተግባርና የልዩ ተግባር ካርታዎችን የካርታ ዕድሳት ሥራ ያከናዉናል፤
9. አገራዊና ክልላዊ አትላሶችን እንዲሁም ልዩ አትላሶችን ያዘጋጃል፣ያሳትማል፤ ያሰራጫል፤
10. የጂኦዴቲክ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን፣ የጂኦ-ስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ካርታ ዝግጅትን እና የአየር ፎቶግራፍ የማንሳት ተግባራትን ይቆጣጠራል፤
11. በጂኦስፓሻል ተግባራት ላይ ለሚሰማሩ ግለሰቦችም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ተቋማትን ይደግፋል፤
12. የአገሪቱን ዓለም አቀፍ፣የክልል፣የዞን፣የወረዳ እና የቀበሌ ወሰኖች በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ሲወሰኑ በካርታ ላይ ያሰፍራል፤ ሲጸድቅም ለተጠቃሚ አካላት ያሰራጫል፤
13. በጂኦስፓሺያል ኢንፎርሜሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ተቋማት የአቅም ግነባታ ስልጠና ይሰጣል፤ ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፤ ያማክራል፤
14. በጂኦስፓሻል ዘርፍ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙ ተቋማት ጋር ትብብር ይፈጥራል፤
15. የኢንስቲትዩቱን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

6. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፦

1. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር፤ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና
2. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጉ መሰረት በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያቀርባል።

3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

8. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

1. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ስራዎችን ያከናውናሉ፤
2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

9. <u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

10. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

11. <u>ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 16 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

## ጠቅላይ ሚኒስትር

**ደንብ ቁጥር 438/2011**

## የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት በፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 32(8) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፤

የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር በአዋጁ ላይ በዝርዝር ያልተመለከተ በመሆኑና ይህንን በዝርዝር በደንብ ማመልከት እና አደረጃጀቱንም መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 438/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ፦

1. "ቴክኖሎጂ" ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በጽንሰ ሃሳብ፣ በመሳሪያ ወይም በአመራረት ወይም በአግልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት የተከማቸ የአሰራር እውቀት ነው፤
2. “ኢኖቬሽን” ማለት አዳዲስ የቴክኖሎጂ እውቀቶችን፣ግንኙነቶችን ወይም የመግባቢያ ዘዴዎችን ለማመንጨትና በተቀናጀ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ ሂደት ነው፤
3. "የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃ" ማለት ቴክኖሎጂዎችን፣ የምርምር ውጤቶችን እና የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት በጽሁፍ ወይም በኦዲዮ ቪዥዋል ወይም በተለያዩ ዘዴዎች ተጠናቅሮ የሚገኝ መረጃ ማለት ነው፤
4. “ምርምር” ማለት አዲስ እውቀትን ለማመንጨትና ጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ነባር እውቀትን ጥቅም ላይ ለማዋል ስርዓት ባለው መንገድ የሚከናወን ተግባር ነው፤
5. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፤
6. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
7. በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡

## 3. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

## 4. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በመንግስት ተለይተው ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሴክተሮች ተበታትነው የሚገኙ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምሮችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ

በሚያመጣ መልኩ የማቀናጀትና የማስተሳሰር ስራዎችን መስራት፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የምርምር መሰረተ-ልማቶችን መገንባት፤

2. በመንግስት ተለይተው ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሴክተሮች አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንዲታገዙና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የምርምርና ልማት ስራዎችን መስራት፤ ቴክኖሎጂዎችን ማጎልበት፣ ፕሮቶታይፖችን ማውጣትና መሰል ተግባራትን መደገፍ፤ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተደራሽ ማድረግ፤
3. ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ምርምር ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ በተለያዩ ምጡቅ ቴክኖሎጂ ስነ-ዘዴዎች አማካኝነት ትንተና ማካሄድ፤እሴት በመጨመር መረጃዎችን ማሰራጨት፤
4. በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሃገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት የሚያሳድጉ ሴክተሮችን በመለየት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምሮችን ማስተባበር፣ መተግበርና ተደራሽ ማድረግ።

5. <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሰረት ያደረጉ የአጭርና የረዥም ጊዜ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የምርምር ትግበራ እቅዶችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፣ በመንግስት ሲፀድቁ ያስፈፅማል፤
2. ለሀገሪቱ እድገት አስፈላጊ የሆኑ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የጥናትና ምርምር መስኮችን በመለየት ችግር ፈቺ ምርምሮችን ያካሂዳል፤ በፕሮቶታይፕ፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤
3. ለተመረጡ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምር ሚውሉ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ-ሙከራና የሰርቶ ማሳያ ማዕከላትን በማቋቋም የሀገር ውስጥ የፈጠራ ክህሎት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤
4. ሀገራዊ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የምርምርና ፕሮቶታይፒንግ አቅምን ለመገንባት የሚረዱ አጫጭር ስልጠናዎችንና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ውጤቶች እና ሙከራዎች ወደ ማህበረሰቡ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

6. ለሀገሪቱ ልማት የሚውሉ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፎች መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ እንዲሁም ለሀገራዊ እቅድና ለፖሊሲ ግብዓት እንዲሆን ይደረጋል፤ እሴት የታከለባቸውን መረጃዎች በዳይሬክቶሪዎች፣ በሲስተሞች፣ በፖርታሎች፣ በሪፖዚተሪዎች፣ በሚዲያዎች፣ በህትመቶች እና ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም ተደራሽ ያደርጋል፤
7. ከሌሎች የሀገሪቱ የልማትና የማህበረሰብ ተቋማት ጋራ በመተባበር የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በሀይ ፐርፎርማንስ ኮምፕዩቲንግ፣ በቢግ ዳታ አናሊቲክስና በተለያዩ ምጡቅ ቴክኖሎጂ ስነ-ዘዴዎች አማካኝነት የማደራጀትና የመተንተን አገልግሎት ይሰጣል፤
8. ዓለም የደረሰበትን የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት ኢኮኖሚውን ሊያሳድጉ በሚችሉት ላይ ምርምሮችን ያካሂዳል፤ በፕሮቶታይፕ ያወጣል፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤
9. የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ዘዴዎችንና መርሃ-ግብሮችን ማዘጋጀትና መረጃዎችን ማሰባሰብ ፤
10. የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በመተንተን እሴት አክሎ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፤
11. ከሀገር ልማት አንጻር ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የቴክኖሎጂ መረጃዎች በመምረጥ ረገድ ተጠቃሚዎችን መደገፍ፤
12. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሲገቡ ዝርዝር መረጃዎችን በመያዝ ምን ዓይነት ቴክኖሎጂ የት እንደሚገኝ የተሟላ የመረጃ ቋት መያዝ፤
13. የሀገሪቱን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አመላካቾች በመለየት የአመላካቾቹን የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት መዘርጋት፣ መረጃዎቹን በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግና ተንትኖ ማሳተም፤
14. የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በሚመለከት የተጠቃሚዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ መልዕክት የሚያስተላልፉ ጽሑፎችን ያካተቱ መጽሔቶችን፣ሌሎች ጽሑፎችንና የማስታዎቂያ ቁሶችን እያዘጋጀ ማሰራጨት፤
15. የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ከማደራጀት፣ ከመተንተንና ከማሰራጨት ጋር የተያያዙ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ አማራጭ ሃሳቦችን ማቅረብ፤
16. የሀገሪቱን የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ሥርዓት በማዕከላዊነት መምራትና ማስተባበር፤

17.ከቴክኖሎጂ መረጃ ትንተና አቅም አንጻር የሚታየውን ፈጣን እድገት በመከታተል ለምርምርና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋማት ድጋፍና ወቅታዊ መረጃ መስጠት፤

18.ሪፖርቶችን መጽሔቶችንና መጻህፍትን የመሳሰሉ ወቅታዊ የሆኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ጽሁፎችን በማሰባሰብ ለተመራማሪዎች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለማምረቻ ተቋማት ማሰራጨትና የቤተ መፃህፍት አገልግሎት መስጠት፤

19.በሀገር ውስጥና በዉጭ ሀገር ከሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ትብብር መመስረትና ጠቃሚ ልምዶችን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችንና አሰራሮችን ቀምሮ ወደ ሀገራችን ውስጥ ማስገባትና መተግበር፤

20.ጠንካራ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የመረጃ ኔትዎርክ መዘርጋት፤ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ተቋማት እንዲቋቋሙ መደገፍና የመረጃ ኔትወርኩን አቅም በየጊዜው እያሳደጉ መሄድ፤

21.ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ተመጣጣኝ ክፍያ መጠየቅ፤

22.የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

23.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

6. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
2. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

7. <u>**የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያቀርባል።

3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ወይም ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

8. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

1. የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ስራዎችን ያከናውናሉ፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

9. **<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል፡፡

10. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

11. **<u>የተሻረ ደንብ</u>**

የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 257/ 2004 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

12. **<u>ደንቡ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ.ም**

**አብይ አህመድ አሊ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ቀ/ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**አዋጅ ቁጥር 66/1989 ዓ.ም**

**የመንገድ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

የመንገዶች ልማት፣ ጥገናና ማሻሻያ ለአገሪቱ የተቀላጠፈ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመንገዶች ጥገና በቂና የማያቋርጥ የገንዘብ ፈሰስ የሚሻ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 66/1989" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡

   1. "መንገድ" ማለት አውራጐዳና፣ የገጠር መንገድና የከተማ መንገድ ሲሆን ድልድይን ይጨምራል።

2. “የመንገድ ደኅንነት እርምጃዎች” ማለት በመንገድ አጠቃቀም ላይ አደጋ እንዳይደርስ የሚከላከሉ ሥራዎችን መሥራትንና የትራፊክ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ምልክቶችንና መሣሪያዎችን በመንገድ ላይ ማኖርን ያጠቃልላል።
3. “የመንገድ ተጠቃሚ” ማለት የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም የመንገድ ትራንስፖርት ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው።
4. “ባለሞተር ተሽከርካሪ” ማለት በሜካኒካል ወይም በኢሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀስ ሆኖ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ የግል አውቶሞቢል፣ ጎታች መኪና ወይም ባለሞተር ብስክሌት በሚል ስያሜ የሚጠራ ተሽከርካሪ ነው።
5. “መንግስት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው።
6. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል።
7. “የመንገድ ኤጀንሲ” ማለት መንገዶችን ለማልማት፣ ለመጠገንና ለማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው የመንግሥት፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል ነው፡
8. “ቦርድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8(1)(ሀ) መሠረት የተቋቋመ የመንገድ ፈንድ ቦርድ ነው።
9. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. **መቋቋም**

የመንገድ ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንዱ” እየተባለ የሚጠራ) ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ የገንዘብ ሚኒስቴር[56] በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

4. **የፈንዱ ዓላማ**

የፈንዱ ዓላማ ለመንገድ ጥገናና ለመንገድ ደህንነት እርምጃዎች የሚያስፈልጉትን ወጪዎችን መሸፈን ይሆናል።

5. **የፈንዱ ምንጮች**

[56] በ22/12(2008) አ. 916 አንቀፅ 9(9) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

1. ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች ይሰበስባል፡-

   ሀ/ በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤

   ለ/ ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ፤

   ሐ/ በክብደት ላይ ከተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ሚደሻ ክፍያ፤

   መ/ ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት፤

   ሠ/ እንደአስፈላጊነቱ ከሚጣል ከማናቸውም ሌላ የመንገድ ታሪፍ።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) ድንጋጌ መንገዶችን በሚጠቀሙ ባለሞተር ተሾከርካሪዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

6. <u>የፈንዱ ተሰብሳቢ ገንዘብ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(1)(ለ) ፣ (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) መሠረት የሚሰበሰበው ገቢ መጠን በሚስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል።

2. በመንግሥት የሚመደበው በጀት በየወሩ መጀመሪያ በፈንዱ ሂሣብ ገቢ ይደረጋል፤

3. ለመንገድ ጥገና የተጣለ የነዳጅ ታሪፍ የሚሰበሰበውና በፈንዱ ሂሣብ ገቢ የሚደረገው በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት አማካይነት በየወሩ ይሆናል ።

4. በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚሰበሰበውና በፈንዱ ሂሣብ ገቢ የሚደረገው በእያንዳንዱ ክልል የትራንስፖርትና መገናኛ ቢሮ ወይም አግባብ ባለው ሌላ የክልሉ አካል ሲሆን የተሰበሰበው ገንዘብ እስከየወሩ መጨረሻ ገቢ ይሆናል።

5. ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን የሚጣል የገንዘብ ቅጣት የሚሰበሰበውና በፈንዱ ሂሣብ ገቢ የሚደረገው የተሽከርካሪ ክብደት መቆጣጠሪያ ደንብን ለማስፈጸምሥልጣን በተሰጠው አካል ሲሆን የተሰበሰበው ገንዘብ እስከየወሩ መጨረሻ ገቢ ይሆናል።

6. እንደአስፈላጊነቱ ከሚጣል ከማናቸውም ሌላ የመንገድ ታሪፍ የሚገኝ ገቢ የሚሰበሰበውና በፈንዱ ሂሣብ ገቢ የሚደረገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚሰይመው አካልና በሚወስነው ጊዜ ይሆናል ።

7. በዚህ አንቀጽ መሠረት ገንዘብ በፈንዱ ሂሣብ ገቢ ያደረገ ማንኛውም አካልና የገንዘብ ሚኒስቴር በየወሩ ማብቂያ ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስለገቢው ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባሉ።

7. **ስለክፍያዎች**

ከፈንዱ ሂሣብ ገንዘብ ወጭ ሆኖ የሚከፈለው በጸደቀው ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለተከናወኑ ሥራዎች፣ ለተገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሲሆን አከፋፈሉም ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

8. **ስለፈንዱ አካላት**

1. ፈንዱ፡-

ሀ/ ከመንግሥት፣ ከክልሎችና ከመንገድ ተጠቃሚዎች የሚወከሉ አባላት የሚገኙበት ቦርድ፤ እና

ለ/ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ[57] ይሆናል።

9. **ስለቦርዱ አባላት**

1. የቦርዱ አባላት ቁጥርና የአወካከላቸው ሥርዓት በመንግሥት ይወሰናል።
2. የቦርዱ ሰብሳቢ በመንግሥት ይሰየማል።
3. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም ማንኛውም አባል በወከለው አካል ለተጨማሪ ሥራ ዘመናት እንደገና ሊመደብ ይችላል።
4. አንድን የቦርድ አባል የመደበ አካል በማናቸውም ጊዜና ምክንያት ሊያነሳውና በሌላ ሊተካው ይችላል ።
5. የቦርድ አባላት ቁጥር በሞት፣ ሥራን በፈቃድ በመልቀቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ቢቀነስ ክፍት ቦታው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ይሞላል።
6. የቦርዱ ሥልጣን በቦርዱ አባላት ቁጥር ማነስ ምክንያት አይነካም።
7. ማንኛውም የቦርድ አባል በቦርዱ ውስጥ ካለው ሥራ ጋ ር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ማንኛውም ተግባር ማከናወን የለበትም። በቦርዱ ውስጥ ካለው ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ጉዳይ ሲያጋጥመው ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ጉዳዩ ከሚታይባቸው የቦርዱ ስብሰባዎች ሁሉ ራሱን ማግለል አለበት ።

10. **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. ፈንዱን ያስተዳድራል፤

[57] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ አንቀጽ 33 (12)(መ) መሰረት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

2. ስለፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤
3. ለፈንዱ መግባት ያለባቸው ገቢዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውንና በፈንዱ ሂሣብ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤
4. የመንገድ ኤጀንሲዎችን ዓመታዊ የመንገድ ጥገና ፕሮግራሞች ከመጽደቃቸው በፊት ይገመግማል፤ ፕሮግራሞቹ በተቀነባበረና በተቀናጀ ዘዴ እንዲዘጋጁ ያማክራል፤
5. በዓመቱ ውስጥ በፈንዱ የሚሸፈኑ ሥራዎችን በተመለከተ ለመንግሥት ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በዕቅዱ መሠረት የፈንዱን ገንዘብ ያከፋፍላል፤
6. በፈንዱ አከፋፈል ላይ ተጠያቂነትና ግልጽ አሠራር መኖሩን ያረጋግጣል፤
7. የመንገድ ኤጀንሲዎችን የሥራ አመራር ሪፖርቶች እየተቀበለ ይገመግማል፣ የፈንዱን አጠቃቀም በተመለከተ የሚጠናቀሩ ሪፖርቶችን አዘገጃጀት ይቆጣጠራል፤
8. በፈንዱ የተከናወኑትን የመንገድ ጥገና እና የመንገድ ደኅንነት እርምጃዎች ተግባራት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት ያስደርጋል፣ የኦዲት ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ በኦዲት ሪፖርቶቹ መሠረት ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፣
9. ለመንገድ ጥገና ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጮችና የታሪፍ ደረጃዎችን በተመለከተ ለመንግሥት ሃሳብ ያቀርባል፣
10. ከመንገድ ጥገናና ከፈንዱ ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
11. በኦዲተር የተመረመረ የፈንዱ ዓመታዊ ሂሣብ እንዲጠናቀርና ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤
12. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤ ሥራቸውን ይመራል፣ ያስተባብራል።

11. <u>**የቦርዱ ስብሰባዎች**</u>

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ ይደረጋል። ሆኖም በሰብሳቢው ሲጠራ ቦርዱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ።

3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው። ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

12. <u>ስለፈንዱ ጽሕፈት ቤት</u>

1. የፈንዱ ጽሕፈት ቤት ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።
2. ጽሕፈት ቤቱ በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና[58] አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

13. <u>የጽሕፈት ቤት ስልጣንና ተግባር</u>

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. የቦርዱ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ያረጋግጣል፤
2. የፈንዱን ሂሣብና ሪኮርድ ይይዛል፤
3. የቦርዱን ሥራ አመራር ስብሰባዎች ሪኮርዶች ይይዛል፣ ለፈንዱ መግባት የሚገባው ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ በፈንዱ ሂሣብ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፤
4. የፈንዱን የሂሣብ መግለጫዎች እያዘጋጀ በየዓመቱ ለቦርዱ ያቀርባል፤
5. ስለፈንዱ ገቢዎችና አጠቃቀም፣ ስለመንገድ ጥገና ጠቀሜታ መንገድን አለመጠገን ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች፣ ጥራት ያለው መንገድ ለተጠቃሚዎች ስለሚያስገኘው ቁጠባና ስለመሳሰሉት የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችንና ወቅታዊ ሕትመቶችን ያመነጫል፣ ያሠራጫል፤
6. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

14. <u>የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን፤ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር፦

[58] በ1/17(1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) "ኃላፊ" የሚለው "ዋና ዳይሬክተር" በሚል ተተካ፡፡

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች በመከተል ቦርዱ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል

ረ/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ የሥራ ክንውን ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣

ሰ/ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

3. የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ለጽሕፈት ቤቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

4. እርሱን ሙሉ ለሙሉ ተክቶ ከ30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ኃላፊ ሲወክል ውክልናው በቅድሚያ ለቦርዱ ቀርቦ መጽደቅ አለበት።

15.<u>በጀት</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

2. የፈንዱ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ ሰኔ 30 ቀን ያበቃል።

16.<u>ስለኦዲት</u>

1. ለዋናው ኦዲተር በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፈንዱ ሂሣብ ቦርዱ በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል ።

2. ሂሣቡ የሚመረመረው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ ምርመራ መርሆዎችና ሥርዓት መሠረት ሆኖ የኦዲት ሪፖርቱ ቦርዱና የገንዘብ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጡበት ይቀርብላቸዋል።

3. የቴክኒክ ምርመራ በተመረጡ ተግባራት ላይ በየዓመቱ ይከናወናል ።

17.<u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገገባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

18. <u>አዋጁ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት 27 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

**አዲስ አበባ የካቲት 27 ቀን 1989 ዓ. ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክፕሬዚዳንት**

## <u>ደንብ ቁጥር 247/2003</u>

## <u>የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር፡-

   1. "መንገድ" ማለት ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድረው ማንኛውም መንገድ ሲሆን በመንገዶች ክልል ውስጥ የሚገኙ ድልድዮችን፣ ፉካዎችን፣ የውሃ መውረጃ ቦዮችን፣ የትራፊክ ደህንነት ምልክቶችንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤
   2. "የመንገድ ሥራ" ማለት የመንገድ ግንባታ፣ ጥገና፣ ማሻሻል ወይም መልሶ ግንባታ ሲሆን ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ይጨምራል፤

3. "ድንገተኛ ሁኔታ" ማለት ትራንስፖርትን ሊያስተጓጉል የሚችል በመንገድ ላይ የሚከሰት ናዳ፣ የመሬት መንሸራተት፣ የመኪናግጭት ወይም ሌላ ክስተት ነው።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን (ከዚህ በኃላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል።
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ይሆናል።

4. <u>ዋና መሥሪያ</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በማናቸውም ሥፍራዎች ማቋቋም ይችላል።

5. <u>የባለሥልጣኑ ዓላማ</u>

የባለሥልጣኑ ዓላማ

1. መንገዶችን ማልማትና ማስተዳደር
2. የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር፤ እና
3. በመንገዶች ሥራ የደረጃ ወጥነትን ማረጋገጥ፤ ይሆናል።

6. <u>የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ይኖሩታል።

1. መንገዶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፤
2. የመንገዶችን አመዳደብ መመሪያ ያወጣል፤ ብሔራዊ የመንገድ አውታርንና የመንገዶች ደረጃን ይመድባል፣ ይሰይማል፤ የመንገዶችን የዲዛይን ደረጃ ያወጣል፤
3. የአገሪቱን የመንገድ አውታር አስመልክቶ የተቀናጀ ዕቅድ ያወጣል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
4. የአጭርና የረጅም ጊዜ የመንገድ ልማት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም ተገባራዊ ያደርጋል፤
5. ለመንገድ ሥራ የሚያስፈልጉትን ዲዛይኖችና የፊዚቢሊቲ፣ የአካባቢና ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

6. የመንገድ ሥራዎች እንዲከናወኑ ያስደርጋል፤ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በራሱ ኃይል የመንገድ ሥራዎችን ያከናውናል፤
7. የሥራ እና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይዋዋላል፣ ሥራዎች በየውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይቆጣጠራል ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤
8. አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንገዶችን ዲዛይን የሚሠሩ ወይም የቁጥጥርና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አማካሪዎችን እንዲሁም በመንገድ ሥራዎች ላይ የሚሠማሩ ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን ዘዴዎች ይወስናል፤
9. የመንገድ ሥራዎች በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚከናወንበትን አማራጭ ይወስናል፤
10. የትራፊክ ደኅንነት ምልክቶች እንዲዘጋጁና በመንገዶች ላይ እንዲኖሩ ያደርጋል፤
11. የተሽከርካሪ ክብደት ደንቦችን በመንገዶች ላይ ያስከብራል፤
12. ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም አስቸኳይ እርምጃ በመውሰድ መንገዱ አገልግሎቱን እንዲቀጥል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ለሚመለከተው የመንግስት አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
13. መንገዶችን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችም በሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
14. ከክልል የመንገድ ኤጀንሲዎችና አግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት ሲጠየቅ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
15. ለመንገዶች ልማት የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል እንደአስፈላጊነቱ ያሰለጥናል፤
16. መንገዶችን ከጉዳትና አለአግባብ ከመጠቀም ይጠበቃል፤ በመንገዶች ላይ የሚከሰቱ መሰናክሎችን ያስወግዳል ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፤
17. ከመንገዶች ግራና ቀኝ ለሥራው የሚያስፈልገውን የመሬት መጠን ይወስናል፤

18. ለመንገድ ሥራዎች እንዲሁም ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለመጋዘኛ ማሳረፊያና ለሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች ያለክፍያ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
19. በሕግ መሠረት ለባይዞታዎችና ለባለንብረቶች ካሣ በመክፈል ለመንገድ ሥራዎች የሚያስፈልግ መሬት ያስለቅቃል።
20. በመንገዶች ክልል ውስጥ የተገኙ ህገወጥ ንብረቶችን ያስነሳል፤
21. በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውንም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች አግባብ ባለው ሕግ መስረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፤
22. የመንገድ ሥራዎች በሚካሄዱበት ወቅት ለአካባቢ ጥበቃ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ያደርጋል፤
23. በክፍያ የሚያገለግሉ መንገዶችን ይወስናል፤ ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣ ለመንገድ ፈንድ ገቢ ያደርጋል፤
24. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
25. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የባለስልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፦

1. አባላቱና ሰብሳቢው በመንግሥት የሚሰየሙ ቦርድ፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ባለሥልጣኑን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን እንዲሁም የባለሥልጣኑን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ለመንግሥት ከመቅረባቸው በፊት ይገመግማል፤ ሲፈቀድም በየጊዜው አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
2. ባለሥልጣኑ የሚመራባቸውን መመሪያዎች ያጸድቃል፣

3. የባለሥልጣኑን አዲት ሪፖርት ይመለከታል፣ ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፤
4. የባሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በሚያቀርባቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይወስናል።

9. <u>**የቦርዱ ስብሰባ**</u>

1. ቦርዱ በየወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሲሰበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብዛኞቹ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10. <u>**የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋናው ዳይሬክተር የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር፦

ሀ/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 6 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት የባለሥልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል

ሐ/ የባለሥልጣኑን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን፣ ዓመታዊ የሥራ ኘሮግራሞችና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ በመንግስት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ባለሥልጣኑ የሚመራባቸውን መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲጸድቁም ሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ በጸደቁ የባለሥልጣኑ ኘሮግራሞችና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርቶች ለቦርዱ ያቀርባል ፤

ሰ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል

ሸ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቦርዱን በማስፈቀድ ክርክሮችን ከፍርድ ቤት ውጪ ይጨርሳል፡፡

3. ዋናው ዳይሬክተር ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

11.**በጀት**

የባለሥልጣኑ በጀት

1. በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤ እና
2. በአዋጅ ቁጥር 66/1989 መሠረት ከመንገድ ፈንድ ከሚመደብ ገንዘብ፤ የተውጣጣ ይሆናል፡፡

12.**የሂሳብ መዛግብት**

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

13.**ደንቡ የሚፀናት ግዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 1 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 300/2006**

**የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 29(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 300/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "አዋጅ" ማለት የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   3. "የመድን ፈንድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 19 መሠረት የተቋቋመው የመድን ፈንድ ነው፤

4. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) የህግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ አንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. <u>የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ስለመድን ፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤
2. ለተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች በአዋጁ አንቀጽ 20 መሠረት ካሳ ይከፍላል፤
3. በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ካሣ የተከፈለባቸውን የሞትና የአካል ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት መረጃዎች ይሰበሰባል፤
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የሚኒስቴሩን ፈቃድ በመጠየቅ የተወሰኑ ተግባራቱ አግባብነት ባላቸው ተቋማት በውክልና እንዲከናወኑ ያደርጋል፤
5. ለመድን ፈንዱ የተለየ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል፣ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎችን ያዘጋጃል፤
6. ለመድን ሽፋን የምስክር ወረቀትና ተለጣፊ ህትመት ከፈንዱ ሂሳብ ወጪ በማድረግ እንዲታተም ያደርጋል፤ ለመድን ሰጪዎች ባሰራጨው መጠን የህትመቱን ወጪ በማሰባሰብ ወደፈንዱ ሂሳብ ተመላሽ ያደርጋል፤
7. የመድን ፈንዱን የፋይናንስ ምንጭ ለማጎልበት ከፈንዱ ክምችት ላይ ለመጠባበቂያ የሚይዘውን ቀንሶ ቀሪውን መንግሥት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ኢንቨስት ያደርጋል፤

8. ስለመድን ፈንድ ገቢዎችና አጠቃቀም፣ ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ወቅታዊ ህትመቶችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፤
9. ከተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማካሄድ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
10. አዋጁን እና አዋጁን ለማስተግበር የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያስፈጽማል፤
11. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
12. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

6. <u>**የኤጀንሲው አቋም**</u>

ኤጀንሲው፡

1. የመድን ፈንድ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና
3. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

7. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

1. ቦርዱ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከመድን ኩባንያዎች የተውጣጡ በሚኒስትሩ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።
2. የቦርዱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

8. <u>**የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንናጡ ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ይቆጣጠራል፤
2. ከተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮችን እና በአዋጁ አንቀጽ 4(4) እና አንቀጽ 23(2) መሠረት የሚቀርቡ የአረቦንና የመድን ፈንድ ተመን ጥናቶችን ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
3. ስለመድን ፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤

4. በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት ደርሶባቸው በአዋጁ አንቀጽ 20 መሠረት ተገቢው ካሣ አልተከፈለንም በማለት ቅሬታ የሚያቀርቡ ጉዳተኞችን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
5. የፈንዱን ሂሳብ ኦዲት ያስደርጋል፣ ሪፖርቱን ይገመግማል፣ በሪፖርቱ መሠረት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤
6. የኤጀንሲው የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች፣ ዓመታዊ ፕሮግራሞችና በጀት ለመንግሥት ከመቅረባቸው በፊት ይገመግማል፤ ሲፈቀዱም አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
7. በኤጀንሲው በሚቀርቡለት የመድን ፈንድ አስተዳደርን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ይወስናል።

9. **<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>**

1. ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።
2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባከ ተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራላይ ያውላል፤

   ለ/ የኤጀንሲውን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኤጀንሲውን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች

ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተገመገመ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተገመገመ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

11.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

12.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

13.<u>ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

በተሸከርካሪ አደጋ ሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና አዋጅ ቁጥር 559/2000 ተቋቁሞ የነበረውን የመድን ፈንድ ጽሕፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በአዋጁ አንቀጽ 32 መሠረት ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

14.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 2 ቀን 2006 ዓ. ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ቀ/ <u>ለከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች</u>**

## <u>ደንብ ቁጥር 251/2003</u>

## <u>የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀፅ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **<u>አጭር</u>**

   ይህ ደንብ “የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 251/2003” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም ሁለት ሺ ወይም ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የስራ ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፤
2. "የከተማ መሬት" ማለት በማንኛውም ክልል በከተማ አስተዳደር ወሰን ውስጥ ያለ መሬት፤ ነው፤
3. "ይዞታ" ማለት የከተማ ቦታ የሊዝ ሥሪት በሚመራበት ሕግ መሠረት አግባብ ባለው አካል ተፈቅዶ በሊዝ የተያዘ የከተማ ቦታ ወይም በዚሁ ሕግ መሠረት እውቅና የተሰጠው ነባር የከተማ ቦታ ይዞታ ነው፤
4. "መሬትና መሬት ነክ ንብረት" ማለት መሬትንና በመሬቱ ላይ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይጨምራል፤
5. "ሕጋዊ ካዳስተር" ማለት አንድን መሬት የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የቦታው የይዞታ ባለመብትነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ነው፤
6. "የከተማ አስተዳደር" ማለት በሕግ ወይም በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ውክልና የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፤
7. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
8. "ሚኒስቴር" ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው[59]፤
9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
10. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲው" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።

[59] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 29(14) መሰረት የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

5. **ዓላማ**

ኤጀንሲው፡-

1. የተጠናከረ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት በመዘርጋት ሀገራዊ የተቀናጀና የተናበበ የህጋዊ ካዳስተር የመረጃ ቋት በማደራጀት፣
2. የይዞታና የንብረት ባለቤትነት አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን በማረጋገጥ፤
3. ለቀልጣፋ የከተማ መሬት ነክ ንብረት ገበያ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ማንኛውም ሰው በንብረቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆን በማስቻል፤
4. የመሬት ባለይዞታና የመሬት ነክ ንብረት ባለቤት በተለያዩ ከተሞች ባፈራው የሀብት መጠን ተገቢውን የሀብት ፊጠራ ታክስ እንዲከፍል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት የሚመች መረጃ እንዲደራጅ በማድረግ እና
5. ህገወጥነት ከለላ እንዳያገኝና መሬት ያልተገባ የጥቅም ምንጭ የማይሆንበትን ሥርዓት በመፍጠር፤

ለልማት የተመቻቸ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መሰረት የመጣልና የከተሞችን ልማት የማፋጠን ዓላማ ይኖረዋል።

6. **የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረትን ለመመዝገብ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን ይነድፋል ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የምዝገባ የሕጋዊ ካዳስተር ደረጃዎች እንዲወጡ ያደርጋል፤
2. መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ይዘረጋል፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መለያ ከዶች ሥርዓት ያወጣል፤ እንዲሁም የመለያ ኮዶቹ በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች ተጣጥመው ተፈጻሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
3. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና የመሬት ይዞታን ለማረጋገጥ የወጡ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ደረጃዎችና የአሠራር ሥርዓቶች በተገቢው ሁኔታ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

4. የፌዴራልና የክልል ከተሞች የምዝገባ ተቋማትን በማስተባበር በቴክኖሎጂ የተደገፈና ወጥ የሆነ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ በፌዴራልና በክልል ተቋማት መካከል ደረጃውን የጠበቀ፣ የሚናበብና ቀጣይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ መረጃውን ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
5. የካዳስተር ባለሙያዎች ስልጠና ፕሮግራም ስለሚስፋፋበትና የሙያ ብቃት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ስለሚጠናከርበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤
6. በከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት አመዘጋገብና በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየትና ተገቢውን መፍትሄ በመፈለግ የምዝገባ ሥርዓቱን ቅልጥፍና ያረጋግጣል፤
7. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባን የሚያከናውኑ ተቋማት እንዲያደራጁ ለክልል ከተሞች ድጋፍ ያደርጋል፤ ተቋማቱ ደረጃውን የጠበቀ ምዝገባ ለማከናወን እንዲችሉም የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፤
8. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል
9. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የኤጀንሲው አቋም</u>**

ኤጀንሲው፡-

1. የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የምክር ቤቱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ። ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ጸሐፊ ይሆናል።

9. **<u>የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባራት</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረትን ለመመዝገብ በሚነደፉ ዋና ዋና ግቦች ላይ ይመክራል፣ ሀሳብ ያቀርባል፤
2. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረትን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የመረጃ መሠረተ ልማትን የማልማት፣ የማመንጨት፣ የማምረት፣ የማሻሻልና የማስተዳደር ሂደቶችን አፈጻጸም ይገመግማል፤ በጥናትና በግብረ መልስ በተለዩ ችግሮች ላይ ተወያይቶ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ ለተፈጻሚነታቸውም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤
3. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባን ሀገራዊ አፈጻጸምና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ በተገቢው ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አቅም መገንባቱን ይከታተላል ይገመግማል፤
4. በሚመለከታቸው ክልሎች ጥምረት ቻርተር ባላቸው ከተሞች ዙሪያ ያለው ልማትና እድገት የየክልሎቹን አጠቃላይ ፕላን የተከተለ መሆኑን የሚያረጋግጡ ክልሎች አቀፍ መድረኮች እንዲፈጠሩ ያስተባብራል አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤ ይገመግማል።

10.<u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ ይካሄዳል ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
2. በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>**የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኤጀንሲውን የረጅምና የአጭር ጊዜ የስራ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የስራ መርሐ ግብርና በጀት ያዘጋጃል፣ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀትና የሥራ መርሐግብር መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

   ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ በሆነ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

ኤጀንሲው ከመንግሥት በሚመደብ በጀት ይተዳደራል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

14. <u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንበ በፌዴሪል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ጠቅላይ ሚኒስትር

**ደንብ ቁጥር 374/2008**

**የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "የምግብ ዋስትና" ማለት መጠን እና ጥራትን ባማከለ መልኩ በዘላቂነት ምግብ በማግኘት የእያንዳንዱ ግለሰብ የነፍስ ወከፍ የዕለት ፍጆታን እስከ 2,200 ካሎሪ

እንዲደርስ እና የተመጣጠነ የሥርዓተ ምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ በማድረግ ጤናማና አምራች ዜጋ እንዲሆን ማድረግ ነው፤

2. “የስረ ዕድል ፈጠራ” ማለት የመሥራት አቅም እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡ ዜጎችን በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የሥራ ዘርፎች ማሠማራት ነው፤
3. “ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ” ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ሕንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 ወይም በኢንዱስትሪው ዘርፍ 100,000 ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው።
4. “አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ” ማለት የኢንተርፕራይዙ ባለቤት፣ የቤተሰቡ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ 6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ሕንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 እስከ 500,000 ወይም በከተማ ግበርና፣ በባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራና በግንባታ ዘርፍ ከብር 100,001 እስከ 1,500,000 ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው።
5. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
6. “ሚኒስቴር” ማለት የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ነው፤
7. “ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2,000 እና ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ ላይ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፤
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲውተ ጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፎች ሊከፍት ይችላል።

5. **ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡

1. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ መሥራት ለማይችሉ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት እየቻሉ ሥራ ለሌላቸው እና ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት በማሻሻል የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ፤
2. የጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሠረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን መደገፍና ማስተባበር፤
3. በጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ በከተማ ግብርና፣ በግንባታ፣ በንግድ እና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍና በማሳደግ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ የሥራ ዕድል በከተሞች እንዲፈጠር፣ የነዋሪዎች ገቢ እንዲሻሻል እና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ፤
4. የዜጎችን የተመጣጠነ የሥርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ።

6. **ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራትይኖሩታል፡-

1. የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
2. የልማታዊ ሴፍቲኔት፣ የኑሮ ማሻሻያ እና የጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የድጋፍ ማዕቀፎች ይቀርፃል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

3. ለከተሞች ምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሔ ይሰጣል፤
4. የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ ዕድል ፈጠራ የሚደግፉና የሚያስተባብሩ ተቋማት የድጋፍ ማዕቀፎች የማስፈፀም አቅም ይገነባል፤
5. የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
6. የእሴት ሰንሰለትን እና የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ድጋፍ ሰጪ ተቋማት የሚያቀርቡትን የሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ያስተባብራል፤
7. በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የሥራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ሥልጠና ሥራዎችን በስፋት እንዲሠሩ የሚያግዝ የህዝብ ንቅናቄ በከተሞች እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤
8. የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር በከተሞች የማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ እንዲሁም ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና ፍልሰት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የመከላከልና የተሃድሶ ሥራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፤
9. ከተሞችን በየፈርጃቸው ለማወዳደር በሚወጡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ምዘና እና ማወዳደሪያ መስፈርቶች ውስጥ የከተሞች ምግብ ዋስትና ጉዳይ እንደአንድ መስፈርት መካተቱን ይከታተላል፤
10. ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ በመደገፍ ከሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፤
11. በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የሥራ ዕድል ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ሥራ የሌላቸውን፤ መሥራት የሚችሉና የማይችሉ ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ያሰራጫል፤

12. ከድህነት ወለል በታች ላሉት ተጠቃሚዎች የተለየ ፓኬጅ ቀርጾ ወደ ሥራ ያሠማራል፣ በጊዜ ገደብ እንዲመረቁም ያደርጋል፤
13. ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናት በመቀመርና በማስፋት የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎችን ይተገብራል፤
14. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግሥት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፤
15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከስሳል፤ ይከሰሳል፤
16. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የኤጀንሲው አቋም</u>**

ኤጀንሲው፡-

1. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግስት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል።

8. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

1. የምክር ቤቱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

9. **<u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ፣ የድጋፍ ማዕቀፎች፣ ሀገራዊ ዕቅዶች አፈፃፀምና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አስመልክቶ አግባብ ያላቸው ተቋማትን አፈፃፀም ይገመግማል፤
2. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ሃሳብ ያቀርባል፤
3. በልማታዊ ሴፍቲኔትና በኑሮ ማሻሻያ ለሚታቀፉ ተጠቃሚዎች፣ የሥራ ዕድል ለሚፈጠርላቸው ዜጎች እና ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ላሉት አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ ድጋፎች፣ የሞዴል

ኢንተርፕራይዞች መረጣና ማበረታቻ አሰጣጥ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መፈፀማቸውን ይገመግማል፤

4. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትናን ለመደገፍ የሚውሉ የፋይናንስ ምንጮችንና ወጪዎችን ይከታተላል፤ ይደጋፋል፤ ይገመግማል።

10.<u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ ይካሄዳል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
2. በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀፅ 6 ስር የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረታዊ መርሆዎች ተከተሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የስራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

12.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

13.<u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

14.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡

15.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

16.<u>መብትና ግዴታ ስለመተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 ተቋቁሞ የነበረው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉት አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የሚመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል፡፡

17.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል

**አዲስ አበባ የካቲት 8 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 857/2006 ዓ.ም

## የፌደራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

*የመሠረተ ልማት ሥራዎች ከሚለቀቁ የመሬት ይዞታዎች ከሚነሱ ንብረቶች ካሣ አተማመንና አፈፃፀም፣ ከመዋዕለ ንዋይ አጠቃቀም፣ ከመሠረተ ልማት ቀጣይነትና ተደራሽነት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው፤*

*የመሠረተ ልማት ሥራዎች ሲካሄዱ አንዱ በሌላው ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት የሚያስከትለው የአገልግሎቶች መቋረጥና የአካባቢ ብክለት በተጠቃሚውና በመንግስት ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እያስከተለ በመምጣቱ፤ በዚህ ምክንያት እየታዩ ያሉትን ችግሮች ለማስወገድ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስችል የማስተባበርና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለው ተቋም በሕግ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤*

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የፌደራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 857/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦.

1. "መሠረተ ልማት" ማለት ከመሬት በላይ ወይም ከመሬት በታች ያለ መንገድ፣ የባቡር ሐዲድ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ ቴሌኮሚኒኬሽ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ መስኖ፣ የውሃ መስመር ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ግንባታዎችንም ይጨምራል፤
2. "የመሠረተ ልማት ሥራ" ማለት በሚመለከተው አስፈፃሚ አካል የሚካሄድ የመሠረተ ልማት ግምባታ፣ መስመር ዝርጋታ ፣ ጥገና፣ ማሻሻያ፤ መልሶ ግንባታ ወይም መሥመር ዝርጋታ ሲሆን ተየያዥነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎች ይጨምራል፤
3. "አስፈጸሚ አካል" ማለት የመሠረተ ልማት አቅርቦት የሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ነው።
4. "ድንገተኛ ሁኔታ" ማለት በመሠረተ ልማት ሥራ ምክንያት ወይም በመሠረተ ልማት ላይ በድንገት የሚደርስ አደጋ ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚያጋጥም የአደጋ ክስተት ነው፡
5. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡
6. "ንብረት" ማለት መሰረተ ልማቱ በሚካሄድበት መሬት ላይ ያለ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሲሆን ሰብልና ተክሎችን ይጨምራል፤
7. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የፌደራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኢጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **የኤጀንሲው ዓላማ**

የኤጀንሲው ዓላማ በመንገዶች ማስተር ኘላን ላይ የተመሠረተ፡ የተቀናጁ የመሠረተ ልማት ሥራዎች እንዲካሄዱ ማስተባበርና በተቀናጀ የመሠረተ ልማት ሥራ ምክንያት ለሚነሱ ንብረቶችና ለሚለቀቁ የመሬት ይዞታዎች የካሣ ግምት ቀመር ማዘጋጀት ይሆናል።

6. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ሀገራዊ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ዕቅድና ማስተር ኘላን ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ አስፈፃሚ አካላትም ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም በክልሎች እንዲተገበሩ ያደርጋል፡
2. በክልሎች ውስጥ ለሚካሄዱ የተቀናጁ የመሠረተ ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡
3. በመሠረተ ልማት ሥራዎች ምክንያት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ የይዞታ መፈናቀልና የንብረት ጉዳት በሕጉ መሰረት ስለሚከፈለው ካሣ አገማመት ቀመር ያዘጋጃል፣ መረጃ ይይዛል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል
4. በፀደቁ የአጭርና የረጅም ጊዜ የመሠረተ ልማት ዕቅዶች መሠረት የተዘጋጁ የሥራ ፕሮግራሞችን ይገመግማል፣ ይፈቅዳል፤
5. ከአስፈጻሚ አካላት የሚቀርቡ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ከማቀናጀት አኳያ ይገመግማል፣ የበኩሉን አስተያየት ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፡

6. የመሠረተ ልማት መረጃዎችን ያደራጃል፣ ይይዛል፣ ሲጠየቅም ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፡
7. የተገነቡ ወይም የተዘረጉ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን የሚያሳዩ ምልክቶችን፣ የኮድ፣ የዲዛይንና የቀለም ዓይነቶች ይወስናል፣ የሚመለከታቸው አሰፈፃሚ አካላትም በምልክቶቹ መሰረት ለመፈፀማቸው ይከታተላል፤
8. ለእያንዳንዱ የመሠረተ ልማት አስፈጻሚ አካል ተገቢውን ምልክት በአስፈላጊው ቦታ ላይ እንዲያደርግ መመሪያ ያስተላልፋል፤ ስለመፈጸሙም ይቆጣጠራል።
9. የተቀናጁ የመሠረተ ልማት ሥራዎች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች የተፈጥሮ የአካባቢ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር መመሪያ ያወጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡
10. ስለተቀናጁ የመሠረተ ልማት ስራዎች እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና ይሰጣል፡
11. ድንገኛ ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር አስቸኳይ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡
12. ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችሉ እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ ባለሙያዎችን የያዙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤
13. እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል የሚያወጣው ስታንዳርድ እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ስታንዳርድ በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፤
14. ከመሰረተ ልማት ሥራዎች በተጨማሪ በተፈቀዱ የግንባታ ስራዎች ላይ ተመስርተው ለሚካሄዱ ግንባታዎች፣ መስመር ዝርጋታዎችና ተያያዥነት ላላቸው ሥራዎች ፈቃድ ይሰጣል፡
15. ከኤጀንሲው ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ኤጀንሲው ከፈቀደው ውጪ የተፈጸመ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
16. በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቀናጁ የመሠረተ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
17. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

18.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የኤጀንሲው አቋም</u>**

ኤጀንሲው፡-

1. የስራ አመራር ቦርድ በኋላ (“ቦርድ”) እየተባለ የሚጠራ፣
2. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. **<u>የቦርዱ አባላት</u>**

ሰብሳቢውን ጨምሮ የቦርዱ አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ፣ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. **<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኤጀንሲውን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን እንዲሁም የኤጀንሲውን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን፣ ዓመታዊ የሥራ ኘሮግራምና በጀት ለመንግስት ከመቅረባቸው በፊት ይገመግማል፣ ሲፈቀዱም በየጊዜው አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (12) መሠረት ለሚቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች አባላት የሚከፈለውን አበል ይወስናል፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (16) መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤
4. የኤጀንሲውን የኦዲት ሪፖርት ይመለከታል፣ ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፤
5. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በሚያቀርባቸው ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይወስናል።

10. **<u>የቦርዱ ስብሰባ</u>**

1. ቦርዱ በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፤ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲዉን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ በፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች ሕጎች መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን፣ ዓመታዊ የሥራ ኘሮግራሞችንና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፀድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲጸድቁም ሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ በፀደቁ የኤጀንሲው ኘሮግራሞችና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ረ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል

ሰ/ በቦርዱ የፀደቁትን የኢጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርቶች ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግስት ይመደባል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ፣ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. <u>የአስፈጻሚ አካላት ኃላፊነት</u>

1. እያንዳንዱ አስፈጻሚ አካል የመሠረተ ልማት ዕቅዱን ሲያዘጋጅ የመንገድ መሠረተ ልማት ዕቅድን እና ማስተር ኘላንን መሠረት በማድረግ ይሆናል።
2. አስፈጻሚው አካል የመሠረተ ልማትን ዕቅድ ለኤጀንሲው ሲያቀርብ ልማቱ በሚካሄድበት አካባቢ ያሉትን መረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል።
3. ማንኛውም አስፈጻሚ አካል የመሰረተ ልማት ሥራ ለማካሄድ በሌሎች የመንግስት አካላት የሚሰጡት የመሠረተ ልማት ፈቃዶች እንደተጠበቁ ሆነው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የኤጀንሲውን ፈቃድ ማግኘት አለበት።
4. አስፈጻሚው አካል ሥራውን ሲያካሂድ ከሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎች ጋር ያልተጣጣመ ሆኖ ካገኘው ይህንኑ በፍጥነት ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል።

15. <u>የቅሬታ አፈታት ሥነ ሥርዓት</u>

1. በተቀናጀ የመሠረት ልማት ሥራ ምክንያት የሚነሳ ማናቸውም ቅሬታ የአስፈጻሚው አካል ውሳኔ በደረሰው በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሑፍ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይችላል።
2. ኤጀንሲው የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ውሳኔውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያሳውቃል።
3. ከካሣ ክፍያ ጋር በተያያዘ ኤጀንሲው በሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ጉዳዩን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

16. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማስፈፀም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት።

17. <u>ስለ ሌሎች ህጐች ተፈጻሚነት</u>

1. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

2. የክልል የመሠረተ ልማት ሥራዎችን የማቀናጀት ተግባር የዚህን አዋጅ መሰረታዊ መርሆዎች በመከተል በሚወጡ የየክልሉ ሕጎች መሠረት ይመራል።

18. **ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

19. **አዋጁ የሚፀናበት ግዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 16 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 289/2005 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲምክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 289/2005” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓም**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. "ሚኒስቴር" ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው፤[60]
2. "ፕሮጀክት ማኔጅመንት" ማለት አንድን የግንባታ ፕሮጀክት በተያዘው ጊዜ፣ በተመደበው በጀትና አስቀድሞ በተቀመጡ የመለኪያ መስፈርቶች መሠረት ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን ያካተተ የማቀድ፣ የማደራጀት፣ የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ ነው፤
3. "ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት" ማለት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ባለቤትነት የሚከናወኑ የህንፃ፣ የመንገድ፣ የባቡር፣ የንጹህ ውኃ አቅርቦትና ስርጭት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የግድብ፣ የመስኖ ልማት፣ የኃይል ማመንጫ መሠረተ ልማቶችና መሰል ሥራዎችን እና ከአንድ ሜትር በላይ ጥልቀትና ከፍታ ያለው ማናቸውም የምህንድስና ጥናት፣ ዕቅድና ዲዛይን ስራዎችን ያጠቃልላል፤
4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አስፈጻሚ ዋና ዋና ተዋናዮችን የፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅም በመገንባት የአገሪቱን የአጭርና የረጅም ጊዜ የኮንስትራክሽን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በጊዜ፣ በፋይናንስና በጥራት የላቀ እንዲሆን ማድረግና በአገሪቱ የተጀመረውን ፈጣን ልማት በላቀ ደረጃ ማስቀጠል ይሆናል።

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

[60] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(15) መሰረት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

1. ተወዳዳሪ የሆነ አገራዊ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅም ለመገንባት የሚረዱ የፖሊሲ ሀሳቦችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሀ-ግብሮችን ማመንጨት እና በመንግሥት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
2. የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ክፍተቶችን በመለየት ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መስጠት፤
3. በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት ለሚሠማሩ ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የሠርተፊኬሽን ሥርዓት እንዲኖር እና ብቃትና ክህሎት ላይ የተመሠረተ የሥራ ሥምሪት ተግባራዊ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
4. የቴክኖሎጂ አቅም እንዲፈጠርና እንዲሸጋገር የሚያስችሉ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ዘዴዎችን በመለየት በኢንዱስትሪው ውስጥ የማስረጽ ሥራ መሥራት፤
5. በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ባለቤቶች፣ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጋራና በተናጠል የሚፈፀሙ ኃላፊነቶችን በመለየት ወጥ የሆነ የፕሮጀክት ሥርዓት አሠራር መቅረጽና ማስተዋወቅ፤
6. በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት መስክ የማማከር አገልግሎት መስጠት
7. ለኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀትና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት፤
8. ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ክህሎትና ዕውቀት እንዲስፋፋና እንዲዳብር የጥናትና ምርምር ተግባራትን ማከናወን፤
9. ለኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ክህሎት ዕድገት አጋዥ በሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤
10. ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የመንግሥትና የግል ተቋማት እና የሙያ ማህበራት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤
11. በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አፈጻጸም ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተምክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፤

12. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር የኮንስትራክሽን ፕሮግራምና ፕሮጀክት ማኔጅመንት ክህሎት ማሳደግን በተመለከተ በመተባበር የመሥራት፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን የማካሄድ እንዲሁም በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር የማገዝ፤
13. ለሚሠጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤
14. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
15. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን።

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ፦

1. አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኃላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. <u>**የምክር ቤቱ አባላት**</u>

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>**የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባራት**</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤
2. የኮንስትራክሽን ፕሮግራምና ፕሮጀክት ማኔጅመንት ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን፣ ጥናቶችንና ምርምሮችን ይገመግማል፤ አስተያየት ይሰጣል፤
3. የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ እየገመገመ የመፍትሔ አቅጣጫ ያመላክታል።

10. <u>**የምክርቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

11.<u>**የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

   ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈግፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>**በጀት**</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

**13.የሂሳብ መዛግብት**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**14.ደንቡ የሚፀናበት ግዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 439/2011**

**የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

መንግሥት በአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በፌደራል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32(16) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፤

የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን በዚሁ አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ (34) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት" ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 439/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

1. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
2. "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47(1) የተመለከቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆኑ ክልሎች ሲሆኑ አዲስ አበባን እና የድሬደዋ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡
3. "የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ" ማለት የተለያዩ ተፈጥሮአዊ እና የተፈበረኩ ግብዓቶችና ሀብቶችን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ወደሆኑ የግንባታ ውጤቶች የሚለውጥና ዕሴት የሚፈጥር የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፡፡
4. "ኮንስትራክሽን ሥራዎች" ማለት ከመሬት በላይ እና በታች የሚከናወኑ የምህንድስና ፊዚካል መሰረተ ልማትን ጨምሮ በቋሚ ንብረቶች፣ በአገልግሎቶችና በመሣሪያዎች የሚታገዙ የጉልበት ሥራዎች ጥምር ሆኖ በህንጻ ሥራዎች፣ በመሰረተ ልማት ሥራዎች፣ በማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ሥራዎች፣ በሪክላሜሽን ሥራዎች፣ በወደብ እና በሌሎች የሲቪል ግንባታ ሥራዎችን እንደ አዲስ የማልማት፣ የማስፋፋት፣ የመገጣጠም፣ የመጠገን፣ የማሻሻል፣ የማወላለቅ ወይም የማፈራረስ ተግባር ነው፡፡
5. "የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት" ማለት በመንግሥት፣ በግሉ ዘርፍ እና በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ጥምረት የሚከናወኑ ማናቸውም የምህንድስና ጥናት፣ ዕቅድ፣ ዲዛይን እና የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

6. “የሥራ ተቋራጭ” ማለት ህጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ የኮንስትራክሽን ሥራዎች የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው እና የንግድ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፡፡
7. “አማካሪ ድርጅት” ማለት ህጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአማካሪነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው እና የንግድ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፡፡
8. “ባለሙያ” ማለት ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ በኮንስትራክሽን ሥራዎች እንዲሳተፍ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡
9. “ደረጃ” ማለት ሥልጣን በተሰጠው አካል ለጋራና ተደጋጋሚ ጥቅም መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፣ ሕጎች እና ተዛማጅ ሂደቶችን ሳሟላ ባለሙያ፣ ድርጅት፣ ማሽነሪ እና ሌሎች ደረጃ ለሚሰጣቸው አካላት የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፡፡
10. “ጥራት” ማለት በቀጥታ የተገለጸን እና በተዘዋዋሪ መንገድ የተቀመጠን ፍላጎት የማሟላት ችሎታውን የሚገልጽ የኮንስትራክሽን ሥራ ግብዓት፣ ውጤት ወይም አገልግሎት አጠቃላይ ባህሪ ነው፡፡
11. “ቁጥጥር” ማለት የኮንስትራክሽን ሥራዎች በተቀመጡ ሕጎች፣ ኮዶች እና ደረጃዎች መሰረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡
12. “የአደጋ ኢጋጣሚዎች” ማለት በኮንስትራክሽን ሥራዎች ሂደት ውስጥ እና አገልግሎት እየሰጡ ባሉ ግንባታዎች ላይ የሚደርስና በሰው፣ በአካባቢ እና በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችል የጉዳት ኢጋጣሚ ነው፡፡
13. “የውሃ ስራዎች” ማለት በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ላይ የተሰጠውን ትረጉም ይይዛል፤
14. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
15. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥርያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡

4. ዓላማ

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል:-

1. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አገራዊ ፍላጎቶችን ማሟላት እንዲችል ቀልጣፋ፣ በተገቢው ወጭ፣ በተያዘለት ጊዜ እና ጥራት የሚፈጸም መሆኑን መቆጣጠር፤
2. የኢንዱስትሪው ባለሙያዎችን፣ የሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችን እና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የሥራ አፈጻጸም በመቆጣጠር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከአገሪቱ ፍላጎት ጋር አብሮ እያደገ የሚሄድ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የዜጎችን፣ የአካባቢ ደህንነትን እና ጤንነትን ያረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ፤

የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን እና ውጤቶችን ጥራት እና ደረጃ ቁጥጥር ማረጋገጥ፤

5. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር የግንባታ ዘዴው ዘመናዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘትና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራትና ቁጥጥር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት እንዲሰፍን ያደርጋል፤
2. አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ አፈፃፀሙን ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ ደህንነት፣ በሰራተኞችና በህብረተሰቡ ጤንነት እና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፤
4. በኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚሳተፉ አካላት የሥራ ውል ዝግጅትና አፈጻጸም ወጥነት ኖሮት እንዲፈጸም ለማድርግ የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤
5. በኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚኖሩ የሙያ ደረጃዎች እንዲዘጋጁ እና እንዲሻሻሉ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ አፈጻጸማቸውን ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል፤

6. የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፤ ሲጸድቅ ፕሮጀክቶችን ይመዘግባል፤ አፈጻጸማቸውን ይደግፋል፤
7. ከውሃ ሥራዎች ውጪ ያሉ የግንባታ ህጎች፣ ኮዶችና ደረጃዎች እንዲዘጋጁ እና እንዲሻሻሉ ያደርጋል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊነቱን ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤
8. የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ደረጃ መስፈርት እንዲዘጋጅና እንዲሻሻል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤
9. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ደረጃ ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
10. በፌደራል በጀት የሚሰሩ ግንባታዎች ዲዛይን በአግባቡ መሰራታቸውን ይፈትሻል፤ያረጋግጣል፤ በዲዛይናቸው እና በውላቸው መሰረት ስለመገንባታቸው ምርመራ ያደርጋል፤ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
11. ከውሃ ስራዎች ውጪ በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ቁጥጥር ያደርጋል፣ የድርጅቶቹን አፈጻጸም መረጃ ይይዛል፤ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይከታተላል፤ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
12. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኮንስትራክሽን ገበያ አመላካቾችን ያዘጋጃል፤ የግንባታ ሞዴል ዋጋዎችን ያዘጋጃል፤ የግምት ቀመሮችን ያወጣል፤ ያጸድቃል፤ ይቆጣጣራል፤
13. የኮንስትራክሽን ሥራዎችን እና ግንባታዎችን ደህንነት በመከታተል ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጉዳቶችን ይለያል፣ ጉዳቶችን ለማስተካከል የሚያስችሉ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
14. በኮንስትራክሽን ሥራዎች እና ግንባታዎች ላይ የሚፈጠሩ የአደጋ አጋጣሚዎች እና ጉዳቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይፈትሻል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣ የሕግ ተጠያቂነት እንዲኖር ይከታተላል፤
15. የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ግንባታዎች የህፃናትን የወጣቶችን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፤ የአካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሣታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

16. በተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ በዘርፉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሠራጫል፤ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤
17. የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፤ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

6. **የባለሥልጣኑ አቋም**

ባለሥልጣኑ፡-

1. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣እና
2. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

   ሀ) ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ (5) የተመለከቱትን የባላሥልጣኑን ሥልጣን እና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ) በፌደራል የሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳደራል፡፡

   ሐ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድለት ሥራ ላይ ያውላል፤

   መ) በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደረጋል፤

   ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በየሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

   ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤
3. ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

8. **የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት ምክትል ዋና ዳይሬክሩ:-**

1. የባለስልጣኑን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ የስራ ዘርፎችን ያከናውናል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

9. <u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡፡

1. በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤
2. ከሚሰጣቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ገቢ፡፡

10.<u>የሒሳብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

11.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ህዳር 5 ቀን 2011 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 8 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**በ/ <u>ለውሃ የመስኖ እና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች</u>**

**<u>አዋጅ ቁጥር 201/1973</u>**

**<u>ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ[61] ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>**

**<u>ኢትዮጵያ ትቅደም</u>**

[61] በ12/1(1998) አ.471 አንቀፅ 33 (2) መሠረት "ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት" የሚለው "ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ" በሚል ተተክቷል፡፡

የአየርን ጠቃሚ ውጤቶች ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ኑሮ እድገት እንዲውሉ ለማድረግ የአየር ሁኔታና ጠባይን ማጥናትና መመርመር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያን ከባቢ አየር መቆጣጠር እና መጠበቅ የአየርን ጎጂ ውጤቶቸ ለማስወገድ የሚረዳ ሆኖ በመገኘቱ፤

እነዚህን ብሔራዊ ፍላጎቶች ለማሟላትና ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ረገድ ኢንተርናሽናል ግዴታዎችን ለመወጣት ሚቲዎሮሎጂን መረጃን የሚሰበስብ፣ የሚተነትንና የሚያጠናቅር ማዕከላዊ ተቋም ጠቃሚ በመሆኑ፤

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስልጣንና ሃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቀጥር110/1969 ዓ.ም አንቀፅ 5/6 መሰረት ሚከተለው ታውጇል፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "ብሔራዊ የሚቲዮሮሎጂ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 201/1973 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት" ማለት የሚቲዎሮሎጂን መረጃን በመጠቀም የአየር ሁኔታንና ጠባይን ማወቅ አስፈላጊ ለሚሆንባቸው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ስራ መስኮች የሚሰጥ አገልገሎት ነው፤
   2. "የሚቲዎሮሎጂ መረጃ" ማለት በሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎችና በሰው ተመዝግቦ የከባቢ አየርን ሁኔታና ባህሪየትን የሚገልፅ ማናቸውም መረጃ ማለት ነው፤
   3. "ሚኒስትር" ማለት የማዕድን፣ ሀይል ማመንጫና የውሃ ልማት ሚኒስትር ነው፡[62]
   4. "ሰው" ማለት በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

3. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ኤጀንሲ (ከዚህ በኃላ " ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግስት ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

[62] በ22/12 (2008) አ.916 አንቀፅ 9 (16) መሰረት "የውሃ የመስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር" በሚል ይነበብ፡፡

2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሰሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ በት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችን እንደአስፈላጊነቱ በሌላ ቦታ ሊያቋቁም ይችላል።

5. **የአዋጁ ተፈፃሚነት ገደብ**

ይህ አዋጅ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ለምርምር ብቻ በሚያካሂዱትና ለሀገር መከላከያ የሚውል የሚቲዎሮሎጂ ስራ ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

6. **ዓላማዎች**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት፤
2. አየር እንዳይበከል መቆጣጠርና የተፈጥሮ ሚዛኑን መጠበቅ፤ እና
3. ኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ረገድ በኢንተርናሽናል ስምምነቶች መሰረት ያለባትን ግዴታ በተሻለ አኳሀን መወጣት

7. **ስልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልገው ተግባርና ስልጣን ይኖረዋል። ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፤

1. የልዩ ልዩ ብሔራዊ የስራ እንቅስቃሴዎችና የልማት ፕሮግራሞችን ፍላጎት የሚያሟሉና የኢትዮጵያን የተፈጥሮ አካባቢዎች የሚወክሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን በሀገሪቱ ወስጥ ማቋቋምና ማካሄድ፤
2. የሚቲዎሮሎጂ መረጃን በሙሉ መሰብሰብ፤
3. ኢትዮጵያ ተዋዋይ በሆነችባቸው የኢንተርናሽናል ሰምምነቶች መሰረት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን መለዋወጥ፤
4. የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን በህግ መሰረት ማቋቋምና መካሄድ፤
5. የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችንና የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ ውጤቶችን ማሳተምና ማሰራጨት፤
6. ለአስጊ የአየር ሁኔታ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤ ምክርና ትምህርት አዘል መግለጫዎችን በየጊዜው በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ማሠራጨት እና በሚጠይቅበት ጊዜ ለማንኛውም ሰው የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት፤

7. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም በአገሪቱ ውስጥ በማንኛውም ሰው የተሰበሰበውን ማናቸውንም የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ማዕከላዊ በሆነ መንገድ ማከማቸትና ማስተዳደር፤
8. የአገሪቱ አየር እንዳይበከል መቆጣጠርና የተፈጥሮ ሚዛኑም እንዳይዛባ ማድረግ፤
9. ማንኛውም ሰው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመመዝገብና ለመሰብሰብ ሲጠይቅ አስፈላጊነቱን አመዛዝኖ መፍቀድ፤
10. ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ረገድ በኢንተርናሽናል ደረጃ ተወስነው መንግስት ያጸደቃቸውን ስምምነቶች በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤
11. ስለሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሔድ፤ ጠቃሚ ውጤቶችንም በስራ ላይ ማዋል፤
12. ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ዋጋና ልዩ ልዩ ክፍያዎችን አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት አስወስኖ ዋጋ ማስከፈል፤
13. ሚቲዎሮሎጂን የሚመለከት ማናቸውንም ስብሰባ፤ ጉባኤ ወይም ሴመናር መንግስትን ወክሎ መሳተፍ፤
14. ውል መዋዋል፤
15. በስሙ መክሰስና መከሰስ፤
16. ዓላማውን ለማሳካት የንብረት ባለቤት መሆን፣ ንብረት መያዝ፣ በመያዣ መስጠት፣ መሸጥ፣ መለወጥ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ማስተላለፍ።

8. <u>የውክልና ስልጣን ስለመስጠት</u>

ኤጀንሲው ስራውን በተቀላጠፈ አኳኋን ለማናወን ከተግባርና ስልጣኑ በከፊል በውክልና ለማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ሕዝባዊ ድርጅት መስጠት ይችላል።

9. <u>የስራ አመራር</u>

ኤጀንሲው፦

1. አንድ ዋና ዋና ዳይሬክተር[63]፤ እና
2. አስፈላጊው ሰራተኞች፤

ይኖሩታል።

10. <u>ዋናው ዳይሬክተር</u>

[63] በ12/1(1998( አ.471 አንቀፅ 33(2) “ዋና ስራ አስኪያጅ” የሚለው “ዋና ዳይሬክተር” በሚል ተተክቷል፡፡

1. ዋናው ዳይሬክተር በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት ይሾማል።
2. ዋናው ዳይሬክተር ከሚኒስትሩ በሚሰጠው ጠቅላላ መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ስራና አስተዳደር በበላይነት ይመራል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 በተመለከተው ጠቅላላ አነጋገር ሳይወሰን ዋናው ዳይሬክተር የሚከተሉትን ያከናውናል፤

   ሀ/ በመንግስት ሰራተኞች ማስተዳደሪያ ሕግ መሰረት ሰራተኛን ይቀጥራል፣ ያሳድጋል፣ ያዛውራል፣ ያስተዳድራል፣ ከሥራ ያሰናብታል፤

   ለ/ አግባብ ባላቸው የፋይናንስ ህጎች መሰረት፤

   1) የስራ ፕላንና ፕሮግረም እንዲሁም ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤
   2) ለድረጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮገራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   3) የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርትና በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ መግለጫ አዘጋጅቶ ያቀርል፤ እንዲሁም፤
   4) ለስራው አግባብ ያለውን ሁሉ ይፈፅማል፤

   ሐ/ ለኤጀንሲው የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀሲንው ሰራተኞች በውክልና ይሰጣል፤ ሆኖም እርሱ በሌለበት ጊዜ ስለእርሱ ተወክሎ የሚሰራው ሰው ሚኒስትሩ የሚስማማበት ይሆናል።

   መ/ ከሚኒስትሩ በየጊዘው የሚተላለፍለትን ለስራው አግባብ ያላቸውን ሌሎች ተግባሮች ይፈፅማል።

11.<u>የገንዘብ ምንጮች</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፤

1. ኤጀንሲ የሚሰበስባቸውን የአገልግሎት ዋጋዎችና ክፍያዎች፤
2. የኤጀንሲውን ተግባር ለማስፈፀም የሚገኘው ማንኛውም ሌላ ገንዘብ፤ እና
3. እንደአስፈላጊነቱ መንግስት የሚሰጠው የበጀት ድጋፍ።

12.<u>ስለሂሳብ መዛግብት አያያዝ</u>

ኤጀንሲው የተሟላና ትክክለኛ የገቢና የወጪ መዝገብ የሂሳብ አያያዝ ደንብ በሚጠይቀው መሰረት ይይዛል።

13.<u>የሌሎች ግዴታ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 የተመለከተው ቢኖርም፣ ማንም ሰው ያዘጋጃቸውን የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ለኤጀንሲው የመስጠት ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም ሕዝባዊ ድርጅት በአካባቢው ሚገኘውን የኤጀንሲውን የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ መጠበቅ ኃላፊነት አለበት።
3. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 መሠረት ከዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት ገደብ ውጪ የሆኑ ድርጅቶች ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ረገድ የሚያካሔዱትን ስራ ከኤጀንሲው ጋረ የማቀነባበር ኃላፊነት አለባቸው።

14.**<u>ክልከላ</u>**

ማንም ሰው ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰብ ወይም ማሰራጨት አይችልም።

15.**<u>የሚኒስትሩ ስልጣን</u>**

ሚኒስትሩ፡-

1. በየቦታው የሚያካሂዱትን የሚቲዎሮሎጂ ስራዎችን የማስተባበር፣ እና
2. ይህን አዋጅ በሚገባ ስራ ላይ ለማዋል ደንብ የማውጣት ስልጣን፣ ተሰጥቶታል።

16.**<u>ቅጣት</u>**

ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡትን ደንቦች የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት ይቀጣል።

17.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህን አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታኅሳስ 22 ቀን 1973 ዓ.ም**

**ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ**

**<u>ደንብ ቁጥር 244/2003</u>**

**<u>የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና 39 መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 244/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ "ሕዝባዊ ተሳትፎ" ማለት በዓባይ ወንዝ ላይ ለሚሠራው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ ለማሰባሰብ፣ የገንዘብ መዋጮ ለመሰብሰብ፣ ግንባታውን በስፋት ለማሳወቅ ወይም ለማበረታታት ታስበው በማናቸውም የህብረተሰብ አደረጃጀቶች፣ በሙያ ማህበሮች ወይም ቡድኖች የተዘጋጁ ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ ሰልፎች፣ ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮችን የመሰሉ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል።

3. **መቋቋም**

1. የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሲ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት (ከዚህ በኃላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

4. **የምክር ቤቱ ዓላማዎች**

ምክር ቤቱ፦

1. ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ኅብረተሰቡ የሚያደርገው ሁለገብ ተሳትፎ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግና በሂደቱም የኅበረተሰቡን የቁጠባ ባህልና በራስ የመተማመን መንፈስ የሚዳብርበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
2. የታለቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መሠራት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለታችኛው ተፋሰስ አገሮችም የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በማስረዳት የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይም አጎራባችና የተፋሰሱ አገሮች ለልማቱ በጋራ ይቆሙ ዘንድ መላ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሰፊ የማግባባት ሥራ የሚሠሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ዓላማዎች ይኖሩታል።

5. **የምክር ቤቱ አባለት**

ብሐራዊ ምክር ቤቱ፦

1. ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት፤
2. ከሕዝቡና አግባብ ካላቸው ማኅበራትና ድርጅቶች፤ እና

3. በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሕዝብ ተሳትፎን ለማረጋገጥ አስተዋፆ ሊያደርጉ ከሚችሉ ሌሎች አካላት፤ የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል።

6. **<u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት የኖሩታል፤

1. በዚህ ደንበ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ መርሃ ግብሮችንና ፕሮጀክቶችን ለመንደፍ የሚያስችል ሃሳብ ያቀርባል፣ መንግሥትን ያማክራል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
2. ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከርና በመቀናጀት መላው ኅብረተሰብ እንዲሁም በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለግድቡ ሥራ ገንዘብ በማሰባሰብ እና በገጽታ ግንባታ እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታታል፣ ያስተባብራል፤
3. ከግድቡ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ልምድ በመነሳት መላ ኢትዮጵያውያን በሁሉም የአገር ግንባታ መስኮች ተሳትፏቸውን እንዲያጠናክሩ ያበረታታል፤
4. ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስፈልጉ የሕዝብ ዲፕሎማሲና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ያበረታታል ፣ ያስተባብራል፤
5. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የምክር ቤቱ አካላት</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።

1. በክልልና እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች፤
2. እንደአስፈላጊነቱ በውጪ የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች፤
3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤ እና
4. ብሔራዊ ጽሕፈት ቤት።

8. **<u>ስለምክር ቤቱ ፕሬዝዳንትና ጸሐፊ እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት</u>**

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንትና ፀሐፊ እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ።

9. **<u>የምክር ቤቱ ፕሬዝደንት ስልጣንና ተግባር</u>**

የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሰረት ለምክር ቤቱ የተሰጡት ሥልጣንና ተንባራት በአግባቡ መፈጸማቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፣
2. የምክር ቤቱንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች ይመራል፣
3. የምክር ቤቱን ውሳኔዎች አፈጻጸም ይከታተላል፣
4. ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የሕዝብ ተሳትፎን ለማስፋት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

10.<u>**የምክር ቤቱ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር**</u>

ፀሐፊው፦

1. ምክር ቤቱንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን በፀሐፊነት ያገለግላል፣
2. የምክር ቤቱና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
3. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይቆጣጠራል፣
4. በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

11.<u>**የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**</u>

የምክር ቤቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፦

1. የምክር ቤቱን አስተያየት መሰረት በማድረግ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ መርሀ ግብሮችን፣ ፕሮጀክቶችንና የአፈጻጸም ዕቅዶችን በመንደፍ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተከታትሎ ያስፈጽማል፣
2. የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ሲጠናቀቅ በሥሩ በመከናወን ላይ ያሉትን የሕዝብ ተሳትፎ መርሃ ግብሮችና ፕሮጀክቶችን ለመንግሥት አቅርቦ በማስወሰን አግባብነት ላላቸው መንግሥታዊ አካላት ያስረክባል፣
3. ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የሕዝብ ተሳትፎ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

12.<u>**ስለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት**</u>

1. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት፦

   ሀ/ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፣

   ለ/ ዋና መሥሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ከአገር ውጭ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፣

ሐ/ በመንግሥት በሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በዋናው ዳይሬክተር የሚታጩና ምደባቸው አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚጸድቅ ረዳት ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፤

መ/ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚውጣጡና ሌሎች ጊዜያዊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

2. ጽሕፈት ቤቱ የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይፈጽማል።

13. <u>የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የራሱን የስብሰባ ሥርዓትና የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት የአሠራር መመሪያ ያወጣል።

14. <u>በጀት</u>

የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት በጀት በመንግሥት ይመደባል።

15. <u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

16. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣና</u>

የምክር ቤቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

17. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሚያዝያ 7 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 12 2003 ዐ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 293/2005 ዓ.ም</u>**

**<u>የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና አንቀፅ 35 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **<u>አጭር ርዕሰ</u>**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 293/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር

1. "የውሃ ቴክኖሎጂ" ማለት ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ መገኛን ለመፈለግ፣ ለመገንባት፣ ለማምረት እና ለማሰራጨት እንዲሁም የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ፣ የመስኖ አገልግሎትና የውሃ ኃይል ተቋማት ኦፕሬሽንና ጥገናን በሚገባ ለማስተዳደር በተግባር ላይ የሚውል ቴክኖሎጂ ነው፤
2. "የውሃ ልማት" ማለት የውሃ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ የማልማት ሥራ ነው፤
3. "የውሃና ተዛማጅ ሥራዎች" ማለት የውሃ ልማትና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንደ ውሃ አቅርቦትና መስኖ ተቋማት ጥገና፣ የውሃ ጉድጓድ መቆፈሪያዎችና የኤሌክትሮ ሜካኒካል መሳሪያዎች ጥገና እና ሌሎች መሰል ተግባራት ናቸው፤
4. "ስልጠና" ማለት ከውሃ ልማት ጋር በተያያዘ በዘርፉ ለተሰማሩና ወደፊት ለሚሰማሩ ሰልጣኞች የሚሰጥ መደበኛና አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠና ነው፤
5. "ሚኒስቴር" ማለት የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤[64]
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. ዋና መስሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በውሃ ልማት እና ተያያዥነት ባላቸው ዘርፎች ለተሰማሩ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርን ተደራሽ ማድረግ፤

[64] በ22/12(2008) ኢ.916 አንቀፅ 9(16) መሰረት የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ በሚል ይነበብ፡፡

2. በዘርፉ የተሰማራውንና የሚሰማራውን የሰው ሃይል ከሌሎች በዘርፉ ሙያ ከሚያሰለጥኑ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ በመስራት በተግባር ተኮር ስልጠና ማብቃት፤ እና
3. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚፈለጉ አሰልጣኞችን ማፍራትና አቅም መገንባት።

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ከዓለም አቀፍ አሰራር አንጻር የተለዩ የክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት በሥራ ላይ በተለያዩ ደረጃዎች ለተሰማሩ የውሃና ተዛማጅ ስራዎች ባለሙያዎች አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠና በመስጠት ማብቃት፤
2. በዘርፉ በአገር ውስጥ ማሟላት የማይቻለውን ክፍተት ለማሟላት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ማምጣት፤
3. ከዘርፉ የሙያ ደረጃዎችና ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር በተያያዘ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሚሰጡ ተቋማት መምህራን ዘንድ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት አጫጭር ተግባር ተኮር የአሰልጣኝ ስልጠናዎች መስጠት፤
4. በዘርፉ የትምህርትና ስልጠና ፍላጎት መሰረት በውሃና ተዛማጅ ስራዎች ላይ በሚሰሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚፈለጉ መምህራንን ማፍራት፤
5. በዘርፉ የሰው ኃይል ፍላጎት መሠረት በሀገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የብቃት ማዕቀፍ ከፍተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች ላይ የረጅም ጊዜ ስልጠና መስጠት፤
6. የውሃ ሀብት ልማትን ለማሳደግ የሚረዱ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወን፤
7. በዘርፉ ተፈላጊ ባለሙያዎችን ለሚያፈሩ የትምህርትና የስልጠና ተቋማት የስልጠና ፕሮግራሞች ማደራጀትና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ረገድ የቴክኒክና የምክር ድጋፍ መስጠት እና የብቃት ምዘና ማዕከል አገልግሎት መስጠት፤
8. በሌሎች ተቋማት ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የዘርፉን ስፔሻላይዝድ ላብራቶሪ በማደራጀት አገልግሎት መስጠት፤

9. በዘርፉ የሚፈለገውን የሰው ኃይል ልማት በተመለከተ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ተባብሮ መስራት፤ በጋራ ምርምሮችን በማካሄድ በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲጠናከር ማገዝ፤
10. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግስት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፤
11. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፤ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
12. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን።

7. **የኢንሲትዩቱ አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. **የምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. **የምክር ቤቱ ተግባራት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤
2. የውሃ ልማትን ለማፋጠን በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ ስትራቴጂዎችን፣ አቅዶችን፣ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፤
3. በኢንስቲትዩቱ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
4. የኢንስቲትዩትን የእቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ በመገምገም አስተያየት ይሰጣል።

10. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

1. ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣
   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ ለማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኢንስቲትዩትን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤
   ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 30 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 308/2006</u>**

**<u>የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀፅ 34 እንዲሁም በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 3 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒሰትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 308/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣

1. "አዋጅ" ማለት የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 ነው፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተመለከቱት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።
3. "ሚስቴር" ማለት መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው።[65]

[65] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(16) መሰረት የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪደ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የኢነርጂ ዘርፉን ተወዳዳሪነት ማበረታታት፤
2. ብቃት ያለው፣ አስተማማኝ፣ ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከአደጋ ነፃ የሆነ የኢሌክትሪክ አቅርቦትን ማረጋገጥ፤ እና
3. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን ማስፋፋት።

6. **የባሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
2. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
3. ዓላማዎቹን እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. **የባለስልጣኑ አቋም**

ባለሥልጣኑ: -

1. የኢነርጂ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

8. **የቦርዱ አባላት**

1. ቦርዱ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላት ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከአምስት የማያንሱ አባላት ይኖሩታል።

2. የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ድምጽ የማይሰጥ የቦርዱ አባል ይሆናል።
3. የማንኛውም የቦርድ አባል የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ለተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና ሊሰየም ይችላል።
4. ማንኛውም የቦርድ አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቦርድ አባልነቱን በሚፃረር ተግባር ላይ መሳተፍ አይኖርበትም።
5. አንድ የቦርድ አባል የጥቅም ግጭት ሲያጋጥመው የጥቅም ግጭቱን ለቦርዱ በመግለጽ ይህንኑ ጉዳይ ከሚመለከቱ የቦርዱ ስብሰባዎች ራሱን ማግለል ይኖርበታል።

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር በአዋጁ አንቀጽ 5 የተመለከተው ይሆናል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የባለሥልጣኑን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የባለሥልጣኑን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ያስተደደራል፤

ሐ/ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ በጀት እና የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጀል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ይፈጽማል፤

መ/ ለባለሥልጣነ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሳበ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሞሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተሩ ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>ስለመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989 ተቆቁሞ የነበረው የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

15.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 14 ቀን 2006 ዓ. ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 441/2011

## የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ (5) እና አንቀጽ (34) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 441/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
   2. "ውሃ" ማለት የገጸ-ምድርና የከርስ-ምድር ውሃ ነው፡፡

3. “ተፋሰስ” ማለት ወደ አንድ መልክዓ ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገጸ ምድር ውሃዎችን የማያካልሉት አካባቢ ነው፡፡
4. “ባለስልጣን” ማለት የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ማለት ነው፡፡
5. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማናቸውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
6. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. **የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፎች ሊኖረው ይችላል፡፡

4. **ዓላማ**

የባለስልጣኑ አጠቃላይ ዓላማ ዘለቄታዊና የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም ፍትሐዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ በተፋሰስ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል፡፡

5. **የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባራት**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያደርጋል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ይተገብራል፣
2. በተፋሰሶች ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
3. በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
4. የተፋሰሶችን ጥበቃና ዘላቂ ጥቅም በተመለከተ እቅድ ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
5. የተፋሰሶችን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ እቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፤

6. ተፋሰሶችን ከብክለትና ከጉዳት ለማዳን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ይለያል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይተገብራል፤
7. ለክልሎች በህግ የተሰጠ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሶች ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል አግባብ ባለው ህግ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል፣ በፈቃዱ ላይ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
8. በተፋሰሶች ውስጥ የሚደረጉ የመስኖ መስፋፋት ስራዎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
9. የወንዝ አቅጣጫ አመራር ስራ ይሰራል፤
10. በተፋሰሶች የሚገኘውን የውሃ ሃብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደር እና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያጠናቅራል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤
11. የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ለሚኒስቴሩ ተገቢውን የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
12. ከክልል መንግሥት አካላት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፤
13. ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ከሌሎች አገሮች ጋር ለመወያየት አግባብ ላለው አካል አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤
14. የተፋሰስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ይመሠርታል፤ ያስተዳድራል፤
15. የተቀናጀ የተፋሰስ መሪ እቅድ ያዘጋጃል፣ ይከልሳል፣ ሲፀድቅም ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤
16. የተፋሰሶችን የውሃ ሀብት ልማትና አስተዳደር እቅድ ያዘጋጃል፣ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
17. የውሃ አካላትንና ተያያዥነት ያላቸውን ስነምህዳሮች ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤
18. የጎርፍ መከላከያ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ትንበያ ሥራን ያከናውናል፣ ከጎርፍ እና ከድርቅ ጋር በተያያዘ የተፈጥሮ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የሰዎችና የእንስሳት ህይወት እና ንብረት ከአደጋ ለመታደግ አግባብነት ካለቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችን ያከናውናል፤

19. ከአንድ በላይ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይንም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ አገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ጥናት ያዘጋጃል፤ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
20. ድንበርና ድንበር ዘለል ወንዞችንና የከርሰ-ምድር የውሃ ሀብቶችን ፍትሐዊ፣ ህጋዊና ዘለቄታዊ አጠቃቀም" ያጠናል፣ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ የዓለም አቀፍ ውሎችን በተመለከተ የድርድር ምክረ-ሃሳቦችን ያቀርባል ፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
21. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
22. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

6. **<u>የባለስልጣኑ አደረጃጀት</u>**

ባለስልጣኑ፤

1. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
2. አስፈላጊው ስራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባራት</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑ ስራ አስፈጻሚ በመሆን የባለስልጣኑን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ:-
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ (5) የተመለከቱትን የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባራት ስራ ላይ ያውላል፤
   ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የባለስልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፤
   ሐ) የባለስልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል፤
   መ) ለባለስልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለስልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለስልጣኑን የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለስልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

8. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባራት</u>**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ:-

1. የባለስልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጠውን የሥራ ዘርፍ ያከናውናል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

9. **<u>በጀት</u>**

የባለስልጣኑ በጀት በፌደራል መንግሥት ይመደባል፡፡

10. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ባለስልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ ሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡
2. የባለስልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

11. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር 5 ቀን 2011 ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 12 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 442/2011

## የውሃ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የውሃ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፤ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 442/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

   1. "የውሃ ልማት" ማለት የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማት ነው፤
   2. "ንፁህ መጠጥ ውሃ" ማለት የኢትዮጵያ የመጠጥ ውሃ የጥራት ደረጃን ያሟላ ውሃ ነው
   3. "ሳኒቴሽን አገልግሎት" ማለት ማናቸውንም ከቤትና ከተለያዩ ተቋማት የሚወጣውን ፍሳሽ በተገቢው መንገድ መሰብሰብ፤ ማስወገድና ማስተዳደርን ያካትታል፤

4. “ፍሳሽ” ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከፋብሪካና ከሌሎችም ቦታዎች ተበክሎ የሚወጣ ፈሳሽ ነው፤
5. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
6. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
7. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፤ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

4. **የኮሚሽኑ ዓላማ**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በሃገሪቱ ጤናማና አምራች ዜጋ ለመፍጠር እንዲሁም ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት የሚያስችል ዘላቂና አስተማማኝ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ጥናት፤ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሽፋን ማሳደግ፤
2. የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ የሃገሪቱን የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፡፡

5. **የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በከተማና በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችሉ የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል፤ ያስተባብራል፤
2. በከተማና በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችሉ የመሰረተ ልማቶችን ክልሎችን በመደገፍ ያከናውናል፤
3. የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተቋማት ግንባታ በወጪ ማስመለስ እና በፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፤
4. ከፌደራል መንግስት በጀትና ከውጪ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ግንባታዎች በጥናትና ዲዛይናቸው

መሠረት የጥራት ደረጃውን ጠብቀው መከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

5. ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
6. ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ያሰራጫል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፤
7. የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤
8. ለንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሥራዎች የሚውል ተጨማሪ ፋይናንስ ከባለድርሻ አካላት፣ ከለጋሾች እና ከአጋሮች ያፈላልጋል፤
9. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለመጠጥ ውሃ ግልጋሎት የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ አጥንቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
10. በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በአገልግሎት ሰጪነት፣ በአማካሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በምርትና ዕቃ አቅርቦት የተሰማሩ የግል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
11. በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይሰራል፤
12. በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ወገኖች ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይሰራል፤
13. በውሃና ሳኒቴሽን ጥናትና ዲዛይን፣ ግንባታ፤ ኦፕሬሽንና ጥገና እንዲሁም ተቋማት አስተዳደር ሥራ ላይ ወጣቶችና የግሉ ዘርፍ ተሳታፊ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል፤
14. የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሥራን በማስፋት በተለይ በውሃ-አጠር አካባቢዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችና እንስሳትን ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

15. የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማቶች አካባቢያዊና ማህበራዊ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያስከትሉ እንዲሁም የታከመ ፍሳሽና ተረፈ-ውጤቶችን መልሶ መጠቀም እንዲቻል ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤
16. በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ሥራዎች ላይ በየደረጃው የተጠቃሚው ህብረተሰብ ተሳትፎ መኖሩን ያረጋግጣል፤
17. የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ተቋማት አዋጪ የሆኑ የታዳሽ ኢነርጂ አማራጮችን በመጠቀም አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
18. ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የተቀናጀ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ የአስቸኳይ ጊዜ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ይሰጣል፤
19. ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
20. የዘርፉን የማስፈፀም አቅም የሚያሳድጉ ተግባራትን ያቅዳል፤ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
21. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ይከሰሳል፤ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

6. **<u>የኮሚሽኑ አቋም</u>**

ኮሚሽኑ፡-

1. በመንግስት የሚሾሙ ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነሮች፤ እና
2. አስፈላጊው ሰራተኞች

ይኖሩታል ፡፡

7. **<u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኮሚሽኑን ሰራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ) የኮሚሽኑን የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኮሚሽኑ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. <u>**የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ምክትል ኮሚሽነሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ ፣ በማደራጀት ፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ያግዛል፤
2. በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡ የስራ ዘርፎች ያከናውናል፤
3. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

9. <u>**በጀት**</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

10. <u>**የሂሳብ መዛግብት**</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግባት ይይዛል፡፡
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ሂሳብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

11. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 16 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 444/2011**

**የመስኖ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመስኖ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 444/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:

   1. "የመስኖ ልማት" ማለት በፌደራል መንግሥት በጀት ጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታቸው የሚከናወኑ የመካከለኛ እና የሰፋፊ መስኖና ድሬኔጅ ልማት ነው፤
   2. "ድሬኔጅ" ማለት ከመስኖ ማሳ ትርፍ ውሃ ማስወገድ ሲሆን ጨዋማ የመስኖ መሬቶችን በማጠንፈፍ መልሶ ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግን ያካትታል፤
   3. "ውቅሮች" ማለት በመስኖ ማሳ ላይ የሚገነቡ የውሃ ማስተላለፊያ ቦዮች እና ተያያዥ ግንባታዎች ናቸው፤

4. “መካከለኛ መስኖ” ማለት በመስኖ የሚለማው የመሬት ስፋት ከ፪፻ እስከ ፫ሺ ሄክታር ነው፤
5. “ሰፊ መስኖ” ማለት በመስኖ የሚለማው የመሬት ስፋት ከ፫ሺ ሄክታር በላይ ሲሆን ነው፤
6. “ሚኒስቴር” ማለት የውሃ፤መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤
7. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማናቸውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማናቸውም ስፍራ ሊኖሩት ይችላል፡፡

4. **የኮሚሽኑ ዓላማ**

በመካከለኛና በሰፋፊ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሊለሙ የሚችሉ አካባቢዎችን በመለየት፣ ተገቢ ጥናትና የዲዛይን ስራዎች እንዲካሄዱ በማድረግና እንደአስፈላጊነቱም የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ በማድረግ በሀገራችን በምግብ ራስን መቻል፤ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ማቅረብና ለኤክስፖርት አስተዋፅኦ በማድረግ የህብረተሰቡን የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

5. **የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመስኖ ልማት የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ያመነጫል፤ ሲፀድቅም አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
2. የውሃ ሀብቱንና በመስኖ ሊለማ የሚችለውን የመስኖ መሬት መሠረት በማድረግ የመስኖ ልማት እንዲካሄድ ያደርጋል፤
3. በመካከለኛና በሰፋፊ የመስኖ ልማት የጥናት፤ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች ላይ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እንዲሣተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
4. እንደአስፈላጊነቱ የመካከለኛና የሰፋፊ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ጥናት፤ ዲዛይንና ግንባታ ያከናውናል፤ ወይም እንዲከናወኑ ያደርጋል፤

5. የመካከለኛና የሰፋፊ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ምርታማነት በሚያሳድጉ ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲደገፉና ውሃ ቆጣቢ አሠራር እንዲከተሉ ያበረታታል፤
6. በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ጥናት የተለዩ የሀገሪቱን የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውሃ ሃብት ለመስኖ ልማት የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
7. የመስኖ ልማት ሽፋን እንዲያድግ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
8. የመካካለኛ እና የሰፋፊ መስኖና ድሬኔጅ ልማት እቅዶችን አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ፋይናንስ እንዲያገኙ በተለያዩ ዘዴዎች ያስተዋውቃል፤ ሕግን መሠረት በማድረግ ባለሃብቶች ማትጊያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
10. በአገሪቱ የመካከለኛና የሰፋፊ መስኖ ልማት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓት ይዘረጋል፤
11. በመስኖና በድሬኔጅ ልማት ላይ የተሰማሩ አማካሪና ተቋራጭ ድርጅቶችን አቅማቸው እንዲገነቡ ያደርጋል፤
12. በመስኖ ልማት የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ እንዲካተቱ በማድረግ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤
13. በመካከለኛና በሰፋፊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ህብረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
14. ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የተቀናጀ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
16. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

6. <u>የኮሚሽኑ አደረጃጀት ኮሚሽኑ፡-</u>

   1. ኮሚሽኑ በመንግሥት የሚሾሙ ኮሚሽነር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፤ እና
   2. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ) የኮሚሽኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፤
   ረ) የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡
3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኮሚሽኑ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. **የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባራት**

ምክትል ኮሚሽነሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ያግዛል፤
2. በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን የሥራ ዘርፎች ያከናውናል፤
3. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

9. **በጀት**

የኮሚሽኑ በጀት በፌደራል መንግሥት ይመደባል፡፡

10. **የሂሳብ መዛግብት**

1. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ሂሳብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

11. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ህዳር 5 ቀን 2011 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 19 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ተ/ ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**አዋጅ ቁጥር 194/1992 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ማቋቋሚያ አዋጅ**

ስለሀገሪቱ መልከዐ ምድርና ከመሬት በታች ስላለው ተፈጥሮ የሥነ ምድር መረጃዎችን መሰብሰብ ለኢንዱስትሪ፣ ለኢነርጂና ለእርሻ መስፋፋት መሠረትና ወሳኝ በመሆኑ፤

የማዕድን ሀብትን መፈለግ፣ መመርመር፣ ማጥናትና የጂኦሎጂ መረጃ መሰብሰብ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጠቃሚ በመሆኑ፤

ማናቸውንም የሀገሪቱን የሥነ ምድር መረጃዎች መሰብሰብ፣ ማስቀመጥና በባለቤትነት መያዝ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይን ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 194/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ሥነ ምድር" ማለት ምድርን፣ ምድር የተገነባባቸውን ነገሮች፣ በምድር ላይና በምድር ውስጥ የተከናወኑትን ወይም በመከናወን ላይ ያሉ ለውጦችንና ሌሎችን በመሬት ውስጥ የሚካሄዱ የተፈጥሮ ክስተቶችን የሚያጠና ሣይንስ ሆኖ በጂኦሎጂ፣ በጂኦፊዚክስ፣ በጂኦኬሚስትሪ፣ እንዲሁም በሌሎችም ዘዴዎች በመጠቀም ስለምድር የሚከናወኑ ጥናቶችን ይጨምራል፤
2. "ምርመራ" ማለት ማዕድናትን ለማግኘትና ልዩ ልዩ የሥነምድር መረጃዎችን መሰብሰብ በጂኦሎጂ፣ በጂኦፊዚክስ፣ በጂኦኬሚስትሪ፣ ወይም በሌሎች አመቺ የሥነምድር ሣይንስ ዘዴዎች በመጠቀም የሚካሄድ ሥራ ነው።
3. "ስባት" ማለት ክብደቱ ወይም ይዘቱ በታወቀና በተወሰነ የምድር አካል ውስጥ የሚገኝ የማዕድን መጠን ነው፣
4. "መረጃ" ማለት ከጂኦሎጂካል፣ ከሀይድሮጂኦሎጂካል፣ ከጂኦተርማል፣ ከጂኦፊዚካል፣ ከጂኦኬሚካል፣ ከቁፋሮና ከላቦራቶሪ ጥናት የተገኙ ማናቸውንም መረጃዎችን የሚያጠቃልል ሆኖ ሪፖርቶችን፣ ካርታዎችን ፎቶግራፎችን፣ ፕላኖችን፣ ቻርቶችን፣ ግራፎችን፣ ሴክሽኖችን፣ ሌጐችን እንዲሁም የማዕድናት፣ የድንጋዮችንና የሌሎች ናሙናዎችን ሁሉ ይጨምራል፤
5. "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው የምድር ክፍል ሆኖ በምድር ላይ ወይም ምድር ውስጥ በተፈጥሮ ተከማችቶ የሚገኝ ነው፤
6. "የማዕድን ሀብት ክምችት" ማለት በአንድ በተወሰነ ሥፍራ በከርሰ ምድር ውስጥ በአካባቢው ከሚገኝ የማዕድን ስባትና መጠን በላይ በሆነ ሁኔታና ለምርት ብቁነት አለኝታ ያለው በተፈጥሮ ተሰብስቦ የሚገኝ የአንድ ማዕድን ወይም የስብስብ ማዕድናት ክምችት ነው፤
7. "ሚኒስትር" እና "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትርና ሚኒስቴር ነው፤

8. “ሪሞት ሴንሲንግ” ማለት ለምርመራ የሚውል በአውሮፕላንና በሰው ሰራሽ የመሬት ሳተላይት አማካይነት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል የጥናት ዘዴ ነው።

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ (ከዚህ በኋላ “ሰርቬይ” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለና የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።
2. ሰርቬዩ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የሰርቬዩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. **የሰርቬዩ ዓላማ**

የሰርቬዩ ዓላማ በሥነምድር ጥናት ዘዴዎች ስለምድርና በውስጧ ስለሚገኙ ማዕድናት ምርምር ማካሄድና ማናቸውንም የማዕድን ሀብት ክምችት መፈለግ፣ መመርመር፣ እንደአስፈላጊነቱም መገመትና ማዕድኑ የሚገኝበትን ድንበር ለይቶ ማመልከት ነው።

6. **የሰርቬዩ ሥልጣንና ተግባር**

ሰርቬዩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

1. የጂኦሎጂ ካርታ ሥራ መሥራት፣ ማዘጋጀትና ማተም፣
2. የአየርና የመሬት ጂኦፊዚካልና የሪሞት ሴንሲንግ ጥናት ማካሄድ፣
3. የማዕድን፣ የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ፣ የጂኦተርማል፣ የሀይድሮጂኦሎጂ እና የኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ መሠረታዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በየብስና በውሃ አካላት ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የክምችቱን መጠን መገመትና ክምችቱ የሚገኝባቸውን ሥፍራዎች ድንበር ለይቶ ማመልከት፣
4. ዓላማውን ለማሳካት ባስፈለገ መጠን የእሳተ ገሞራ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የመሬት መደርመስ፣ የሚትዮራይት መውደቅና የመሳሰሉትን የተፈጥሮ ክስተቶችና ውጤቶችን የሚመለከት ጥናት ማካሄድ፣ ውጤቱንም እንደሁኔታው ለሚያስፈልጋቸው ማሳወቅ፣

5. በሰርቬዩ የአጭርና የረጅም ጊዜ የሰው ኃይል ፍላጐት መሠረት ሠራተኞችን ማሠልጠን፣
6. የሥነምድር ሳይንስ ጥናትን በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ፣ በባለቤትነት መያዝ፣ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋ በማስከፈል ወይም ያለክፍያ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፣ እንዲሁም መጽሔቶችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፣
7. ከሥራው ጋር አግባብ ያለውን መረጃ ሁሉ ከማንኛውም ምንጭ መጠየቅና ማግኘት፣
8. የሥነምድር ምርምርና ጥናትን በሚመለክት በማንኛውም ስብሰባ፣ ጉባዔና ሴሚናር ላይ መንግሥትን ወክሎ መሳተፍ፣
9. ከመንግሥት በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣
10. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ማስተላለፍ፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ እና ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮች ማከናወን።

7. <u>**የሰርቬዩ ድርጅታዊ አቋም**</u>

ሰርቬዩ፡-

1. አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤
2. አንድ ዋና ጂኦሎጂስት፤ እና
3. የሚያስፈልጉት ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. <u>**ስለዋናው ሥራ አስኪያጅ መሾም**</u>

የሰርቬዩ ዋና ሥራ አስኪያጅ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል።

9. <u>**ስለዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋናው ሥራ አስኪያጅ የሰርቬዩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከሚኒስትሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የሰርቬዩ ሥራ በሚገባ ለመከናወኑ የበላይ ኃላፊ ይሆናል።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ሥራ አስኪያጅ፤

   ሀ/ በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣

ያስተዳድራል፣ ያዛውራል፣ ያሳድጋል፣ ከሥራ ያሰናብታል፤ ሆኖም የሰርቪዩ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና የአበል መጠን መንግሥት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፤

ለ/ የሰርቪዩን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ እያዘጋጀ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

ሐ/ የሰርቪዩን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

መ/ ለሰርቪዩ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ የሰርቪዩን የሥራ ክንውንና የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሪፖርት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

ረ/ የሰርቪዩን ዋና ጂኦሎጂስትና የመምሪያ ኃላፊዎችን በመምረጥ ለሚኒስትሩ አቅርቦ ያሾማል፣

ሰ/ ሰርቪዩ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ሰርቪዩን ይወክላል።

3. ዋናው ሥራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የሰርቪዩን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል።
4. ለሰርቪዩ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣኑንና ተግባሩን ለዋናው ጂኦሎጂስትና ለሰርቪዩ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

10.<u>**የዋናው ጂኦሎጂስት ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. የሰርቪዩን የጂኦሳይንስ ጥናትና ተዛማጅ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል።
2. ዋናው ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ጊዜ እሱን ወክሎ ይሠራል።

11.<u>**የበጀት ምንጭ**</u>

የሰርቪዩ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፤

1. ከመንግሥት የሚሰጥ ድጐማ፣
2. ሰርቪዩ የሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋና ሌሎች ክፍያዎች፣ እና
3. ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ።

12.<u>**የሂሣብ መዛግብት ስለመያዝ**</u>

1. ሰርቬዩ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶችን ይይዛል፤
2. የሰርቬዩ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች ዋናው ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

13. <u>የተሻረ ሕግ</u>

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 230/1975 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

14. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

15. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት 28 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 28 ቀን 1992 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ቸ/ <u>ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች</u>**

**<u>ደንብ ቁጥር 260/2004</u>**

**<u>ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 260/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ሀገር አቀፍ ፈተና" ማለት የሀገሪቱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና ስርዓተ ትምህርት መሠረት በማድረግ በሀገር ደረጃ የሚተዳደር ፈተና ነው፤
2. "የፈተና አስተዳደር" ማለት የተፈታኞች ምዝገባን፣ የፈተና ዝግጅትን የፈተና ህትመትን፣ የፈተና አሰጣጥን፣ እርማትን፣ ውጤት አጠነቃቀርንና ውጤትን በምስክር ወረቀት መግለጽን ያጠቃልላል ፤
3. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል ፤
4. "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ (ከዚህ በኃላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት ውሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፎች ሊከፍት ይችላል።

5. **ዓላማዎች**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡

1. ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን በማስተዳደር ወደ ሚቀጥለው የትምህርት እርከን የሚዛወሩ ተማሪዎችን መለየት፤
2. ወደ መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎችን በሚመለከት ፍትሃዊ የተማሪዎች ምደባ ማከናወን፤
3. የትምህርት ምዘና ማከናወንና የሚመለከታቸውን የክልል መሥሪያ ቤቶች አቅም ለማዳበር ድጋፍ መስጠት።

6. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን ያስተዳድራል፤ ሚስጥራዊነታቸውና ደህንነታቸው መጠበቁን ያረጋግጣል፤
2. ሀገር አቀፍ ፈተናዎች የሚሰጡባቸው የትምህርት መስኮችን ይለያል፤ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. የሀገር አቀፍ ፈተናዎችን ውጤትና ተከታታይ ምዘናዎችን በመተንተን የትምህርት ምዘና ያካሂዳል፤
4. በትምህርት ምዘና ውጤትና በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መልካም ተሞክሮዎች ላይ በመመሥረት ለሚመለከታቸው የክልል አካላት ሙያዊ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤
5. የሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ማስረጃዎች ማከማቻ ማዕከል ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤ ለተፈታኞች የፈተና ውጤት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
6. በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎችን ፍላጎት፣ የፈተና ውጤታቸውንና የተቋሞቹን የቅበላ አቅም መሰረት በማድረግ የተማሪዎች ምደባ ያከናውናል፤
7. በመንግሥት በጸደቀ ተመን መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል ፤
8. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
9. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>**የኤጀንሲው አቋም**</u>

ኤጀንሲው፦

1. ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ፣
2. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

1. የቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክትር የቦርዱ አባልና ጸሃፊ ይሆናል።

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉትሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በኤጀንሲው በተዘጋጁ የሀገር አቀፍ ፈተናዎች አስተዳደር፣ የትምህርት ምዘና እና የተማሪዎች ምደባ ስትራቴጂዎች ላይ ይመክራል፣ በሚኒስቴሩ ሲጸድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
2. የሀገር አቀፍ ፈተናዎች አስተዳደር፣ የትምህርት ምዘና እና የተማሪዎች ምደባ የሥራ መመሪያዎችን ያወጣል፤ አፈጸጻማቸውን ይከታተላል፤
3. ሀገር አቀፍ ፈተናዎች እንዲሰጡባቸው በተለዩ የትምህርት መስኮች ላይ ይመክራል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል
4. የኤጀንሲውን አገልግሎት አሰጣጥ በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርዱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፉሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፌው ውሳኔ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኤጀንሲውን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኤጀንሲውን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የኤጀንሲውን ስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቃደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፣

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፣

ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጸጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግስት ይመደባል።

13.<u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ</u>

ሀገር አቀፍ የፊተናዎች ድርጅት በመባል ከሚታወቀው አካል ጋር የተያያዙ የሚኒስቴሩ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**ቸ/ ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 199/2003**

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ማሰልጠኛ ተቋም" ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ላይ የተሰማራ የመንግሥት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ነው፤
2. "የትብብር ሥልጠና" ማለት የማሰልጠኛ ተቋሞችና የልማት ድርጅቶች በትብብር የሚሰጡት ሥልጠና ነው፤
3. "የሙያ ብቃት ምዘና" ማለት ተፈላጊ ብቃት ላይ የተደረሰ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚከናወን ማስረጃ የማሰባሰብና በተገኘው መረጃ መሠረት ተፈላጊው ብቃት መያዙን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤
4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
5. "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፎችን ሊከፍት ይችላል።

5. <u>ዓላማዎች</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የሀገሪቱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በአግባቡ ተደራጅቶና ጥራቱ ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲካሄድ የማድረግ፤
2. ዜጎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ተገቢውን ሥልጠና ማግኘታቸውንና የሚሰጡት ሥልጠናዎችም የሀገሪቱን የልማት ትልምና የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን የመከታተልና የሥራ ፈጣሪነትን ባህል የማጎልበት፤

3. የጥቃቅንና የአነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም የማጎልበት።

6. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራትይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ለማስፈጸም የሚያስችል ስታንዳርድና የሕግ ማእቀፍ ረቂቆች ያዘጋጃል፤ ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል
2. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅራቢዎች የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ማዕከላት መሆናቸውንና በቴክኖሎጂ ሽግግሩም በገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፈጠራቸውን ያረጋግጣል፤
3. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር በዘርፉ ሀገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማእቀፍ ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
4. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥራ ገበያውን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የሙያ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
5. በጸደቁት የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመሥርቶ የምዘና መሣሪያዎችን ያዘጋጃል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ትምህርቶች ከጸደቁት የሙያ ደረጃዎች በመነሳት መዘጋጀታቸውንና ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
6. የሙያ ብቃት ምዘናና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል
7. የማሰልጠኛ ተቋማትና የሙያ ምዘና ማዕከላት እውቅና የሚያገኙበትን መመዘኛ መመሪያ ይመጣል፣ አፈጸጸሙን ይቆጣጠራል፤
8. የትብብር ሥልጠና አፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
9. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራኃላፊዎችንና አሰልጣኞችን የብቃት መስፈርት ይወስናል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
10. እንደአስፈላጊነቱ በፌዴራል መንግሥት የሚቋቋሙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መምህራንና አሰልጣኞችን፣ ማሰልጠኛ ተቋማትን ያስተዳድራል፤
11. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ስኬታማ እንዲሆኑ ለክልሎች ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፤
12. የግል ባለሀብቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሀገሪቱን የልማት እቅድና የሥራ ገበያውን ፍላጎት መሠረት እስካደረጉ ድረስ ጥራቱን የጠበቀ የቴክኒክና

ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ የልማት ድርጅቶች በትብብር ሥልጠና እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

13. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጣና እሴቶች፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ወገኖች እና የገጠሩ ማህበረሰብ አባላት ተመጣጣኝ የተሳትፎ እድል ማግኘታውን ያረጋግጣል፤

14. የውጤት ተኮር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ትግበራ በጥናትና ምርምር እንዲጎለብት ያደርጋል፤

15. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የድህረ ሥልጠና ክትትል ጥናቶችን ያካሂዳል፤

16. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል ይከሰሳል

17. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ህጋዊ ተግባሮችን ያከናውናል።

## 7. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፦

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክትርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

## 8. <u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

1. የምክር ቤቱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ጸሐፊ ይሆናል።

## 9. <u>የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕግ ረቂቆች ላይ ይመክራል፣ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
2. ኤጀንሲው የሚያዘጋጀውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማእቀፍ ያጸድቃል

3. ኤጀንሲው አግባብ ባለው ሕግና በዚህ ደንብ መሠረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መርምሮ ያጸድቃል፤
4. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን አፈጻጸም ለማሳካት የባለድርሻዎችን ትብብር ያጠናክራል፤ በሂደትም ኢንዱስትሪው የባለቤትነት ሚናውን እየያዘ መሄዱን ያረጋግጣል፤
5. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይገመግማል፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን ይቀርባል፤
6. የኤጀንሲውን ዓላማዎች ለማሳካት በሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሃሳብ ያቀርባል፤
7. ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሊያገኘው ከአባላቱ መካከል ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን የያዙ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

10.<u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ ይካሄዳል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
2. በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>**የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ሥር የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የሚኒስቴሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 25 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 245/2003

## የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 245/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፤

2. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
3. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ላይ 47(1) ላይ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል
4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኃላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታዎች ቅርንጫፎች ማቋቋም ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክና ሙያ መምህራን ቴክኒሺያኖችን እንዲሁም የአመራር አካላትን በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት ማብቃት፤
2. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የማስፈጸም አቅምን መገንባት፣
3. የአገሪቱን ኢንዱስትሪ በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት የሚያጎለብት የቴክኖሎጂ ሽግግር መደገፍ፤
4. ውጤታማ የምርምር ሥራዎችን በማካሄድ ውጤት ተኮር የስልጠና ስርአትን መደገፍ።

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መምህራን የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች መቅረጽና ስራ ላይ ማዋል፤

2. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ለተሰማሩ ባለሙያዎች በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና መስጠት፤
3. ጥራቱን የጠበቀ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የሚያግዙ አጫጭር ስልጠናዎችና የምክር አገልግሎት መስጠት፤
4. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የውጪ ሀገር ተቋማት እና ተዛማጅ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት መመስረት፤
5. አግባብነት ላላቸው የክልል ተቋማት የቴክኒክ እገዛና ምክር መስጠት፤
6. ሰልጣኞች ለሰለጠኑበት ደረጃ የሚመጥን የስልጠና ምስክር ወረቀት መስጠት፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የላቀ አስተዋፆ ላበረከቱ ሰዎች ሜዳሊያ ወይም ሌለ ሽልማት መስጠት፤
7. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶች፣ ሲምፖዚየሞችና ሌሎች ስብሰባዎች ማዘጋጀት፣ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ጠቃሚ የሆኑ ምርምርና ጥናቶችን በማካሄድ ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
8. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፤ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ
9. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፤

7. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ

1. አስተዳደር ቦርድ (ከዚህ በኃላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. ዳይሬክተር፤ እና
3. አስፈላጊው ይኖሩታል።

8. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከመንግስት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ በሚኒስትሩ የሚሰየሙ የቦርድ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኢንስቲትዩቱ ዳይሬክተር ድምፅ የማይሰጥ ሆኖ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

9. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. አግባብነት ያላቸው የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ኢንስቲትዩቱ የሚተዳደባቸው አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን ያወጣል፤
2. የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር ገምግሞ እንዲጸድቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
3. ለሚኒስቴሩ በሚቀርበው የኢንስቲትዩቱ እቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት ላይ ይመክራል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ መደበኛ ስበሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቦርዱ አባላት በስበሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድመፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ የኖረዋል።
4. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰበ ስነ ስረዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኢንስቲትዩትን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 9(1) መሠረት በወጡ ፖሊሰዎችና መመሪያዎች እንዲሁም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የደመወዝ ስኬል መሰረት የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኢንስቲትዩቱ የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ አዘገጅቶ በቦርዱ ከተመከረበት በኋላ ለሚኒሰቴሩ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈፅማል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱ የስራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተመከረበት በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ሰ/ በማኒስቴሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ሃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በአዋጁ አንቀፅ 62 መሰረት ይመደባል።

13.<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ስር የነበረውና የኢትዮ-ቻይና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በመባል ይታወቅ የነበረው ተቋም ሙብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 261/2004

## የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 261/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፤
   2. "የከፍተኛ ትምህርት ተቋም" ማለት የመንግሥት ወይም የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

3. "ከፍተኛ ትምህርት" ፣ "የግል ተቋም" እና "የመንግሥት ተቋም" እንደቅደም ተከተላቸው በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (8) ፣ (12) እና (13) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤
4. "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

የኤጀንሲው ዓላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና አግባብነትና ጥራት ማረጋገጥ ይሆናል።

6. <u>የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በአዋጁ አንቀጽ 89 የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
2. የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን የሙያ ብቃት ምዘና የሚካሄድበትን ስርዓት ይዘረጋል፤
3. የትምህርት አግባብነትና ጥራትን በተመለከተ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ያሳድጋል፤
4. በመንግሥት በፀደቀ ተመን መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፤
5. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
6. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **የኤጀንሲው አቋም**

ኤጀንሲው፡-

1. የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **የቦርዱ አባላት**

1. የቦርዱ አባላት ስብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ጸሃፊ ይሆናል።

9. **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኤጀንሲው በሚያመነጨው የትምህርት አግባብነትና ጥራት የሚሻሻልበትንና የሚጎለብትበት አጠቃላይ ፖሊሲ ላይ ይመክራል፤ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
2. አግባብ ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ግምገማና እውቅና አሰጣጥ በሚመለከት በኤጀንሲው የሚዘጋጁ መመዘኛዎችን፣ መመሪያዎችንና የአሠራር ሥርዓቶችን ያጸድቃል፤
3. ኤጀንሲው የሚያስከፍላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች የሚመለከት የወሳኔ ሃሣብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

10. **የቦርዱ ስብሰባዎች**

1. ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርዱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልአተጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.**<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራላይ ያውላል፤

   ለ/ የኤጀንሲውን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሳርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኤጀንሲውን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊያደርጋል፤

   መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

   ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ያችላል።

12.**<u>በጀት</u>**

የኤጀንሲው በጀት በመንግስት ይመደባል።

13.**<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.**<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>**

ከከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ሥራዎች ጋር የተያያዙ የሚኒስቴሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

15. <u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 19 ቀን 2004 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 276/2005 ዓ.ም</u>

## <u>የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 276/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 ቁጥር ነው፤
   2. "ከፍተኛ ትምህርት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(8) የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤
   3. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
   4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል (ከዚህ በኋላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የማዕከሉ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **<u>ዋና መስሪያ ቤት</u>**

የማዕከሉ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **<u>የማዕከሉ ዓላማ</u>**

የማዕከሉ ዓላማ የአገሪቱ የትምህርት ጥራትና ብቃት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ለማስቻል በትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ጥናትና ምርምር በማካሄድ በትምህርት አስተዳደር፣ በትምህርት ፕሮግራሞች፣ በምርምር፣ በመምህራን ልማትና በሰው ኃይል ልማት የፖሊሲና ስትራቴጂ መነሻ ሃሳቦችን ማመንጨትና አስተማማኝ አገራዊ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ማገልገል ይሆናል።

6. **<u>የማዕከሉ ስልጣንና ተግባር</u>**

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 90 እና አግባብ ባላቸው ሌሎች አንቀጾች የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
2. አገር አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና የብቃትማ ዕቀፍ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
3. አገራዊ የትምህርት ጥራት ደረጃዎች ላይ ሚኒስቴሩን ያማክራል፣ ለአፈጸጻሙም መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤
4. በጥናትና ምርምር ውጤቶችና የህዝብ ወቅታዊ ጥያቄዎች በሆኑ ትምህርት ነክ ጉዳዮች ዙሪያ በባለድርሻ አካላት መካከል ውይይትና ክርክር እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የህዝብ አስተያየት ያሰባስባል፤ ግኝቱን አጠቃሎ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፤
5. በትምህርት ዘርፍ አመራርና ኮሚሽን አግባብነት ያላቸውን አካላት ያማክራል፤
6. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
7. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **<u>የማዕከሉ አቋም</u>**

ማዕከሉ፡-

1. አማካሪ ካውንስል፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>የአማካሪ ካውንስል አባላት</u>

1. የአማካሪ ካውንስሉ አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎች ሆነው በሚኒስትሩ ይሰየማሉ።
2. የአማካሪ ካውንስሉ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>የአማካሪ ካውንስሉ ተግባራት</u>

አማካሪ ካውንስሉ፡-

1. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማመንጨት፣የትምህርት ጥናትና ምርምር ጥራትና ልህቀትን በማሻሻል፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአዋጁ መሠረት በሚሰጥ ጥቅል በጀትና የመንግሥት ድጎማ አመዳደብ እና በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ማዕከሉን ያማክራል፤
2. በፖሊሲና ዕቅዶች ተፈጻሚነት ላይ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ይለያል፣ ምክንያቶችን ያጣራል፣ የማሻሻያና የማስተካከያ ሃሳቦችን ያቀርባል፤
3. በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በተመዘገበው ለውጥና ዕድገት ላይ ሙያዊ ግምገማና ምዘና ያደርጋል፤
4. ለማዕከሉ ዓላማ መሳካት ወሳኝ በሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ማዕከሉን ያማከራል።

10. <u>የአማካሪ ካውንስሉ ስብሰባዎች</u>

1. አማካሪ ካውንስሉ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።
2. ከካውንስሉ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የካውንስሉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ካውንስሉ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብሊ ያወጣ ይችላል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የማዕከሉን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የማዕከሉን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የማዕከሉን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ/ ለማዕከሉ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤
   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ማዕከሉን ይወክላል፤
   ረ/ የማዕከሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብሪ ፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለማዕከሉ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለማዕከሉ ሌሎች ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የማዕከሉ በጀት በመንግስት ይመደባል።

13. <u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

1. ማዕከሉ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣ መዛግብት ይይዛል።

2. የማዕከሉ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

ከከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ጋር የተያያዙ የሚኒስቴሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለማዕከሉ ተላልፈዋል።

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

ነ/ <u>ለጤና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች</u>

<u>አዋጅ ቁጥር 276/1994</u>

<u>ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ላይ የሚገኝ ተላላፊ በሽታ በመሆኑ፤

በሽታው በግለሰቦች ላይ ከሚፈጥረው የሕመም ስቃይና ሞት፤ በተጨማሪ በርካታና ውስብስብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚያስከትል በመሆኑ፡

ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ቅንጅት ያለውና በሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የመከላከልና የቁጥጥር ዘመቻ ተደርጎበት ሥርጭቱ ካልተገታ በስተቀር ሊያስከትል የሚችለው የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ቀውስ እጅግ የሚያስፈራ በመሆኑ፤

የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመግታት የተለያዩ መንግሥዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተና በስፋት የሚያሳትፍ ሀገር አቀፍ

አካል እንዲሁም ራሱን የቻለ መንግሥታዊ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 276/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. "ምክር ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 የተቋቋመው ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ነው፣
2. "ጽሕፈት ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 የተቋቋመው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ነው፤
3. "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 (1) በተደነገገው መሠረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲምክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደርና የድሬዳዋ ከተማ ምክር ቤትን ይጨምራል፤
4. "መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት" ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሕጋዊ አቋም ያለውና የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ በመከላከልና በመቆጣጠር ተግባር ተሳትፎ ያለው ማኅበር፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የሃይማኖት ተቋም ነው።

**ክፍል ሁለት**

**ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት**

3. **መቋቋም**

ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

4. **የምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፤
2. የፌዴራል መንግሥት ሚኒስትሮች፤
3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፤
4. የክልል ርዕሳነ መስተዳድር፤
5. በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፤
6. የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት[66] ኮሚሽነር፤
7. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር፤[67]
8. የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽነር፤[68]
9. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፤
10. የሚከተሉት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ኃላፊዎች፤

    ሀ/ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፣[69]

    ለ/ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት፣

    ሐ/ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣

    መ/ በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች፤
11. የሚከተሉት የሃይማኖት ተቋሞች መሪዎች፡-

    ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣

    ለ/ የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት፣

    ሐ/ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን፣

    መ/ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነየሱስ ቤተክርስቲያን፣

    ሠ/ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፤
12. የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ዲሬክተር፤
13. የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ፕሬዝዳንት፤
14. የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር ፕሬዚዳንት፤
15. የኢትዮጵያ ህክምና ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት፤

---

[66] በ22/15(2008) ደ.363 መሰረት "ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር" በሚል ይነበብ፡፡

[67] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(5) መሰረት "የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስትር" በሚል ይነበብ፡፡

[68] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(11) መሰረት "የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር" በሚል ይነበብ፡፡

[69] 20/79(2006) አ.858 "የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን" ሆኗል፡፡

16. [70]

17.የኢትዮጵያ አሠሪዎች ማኅበር ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት፣

18.የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፤

19.የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት፤

20.የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ዜጎች ማኅበራት መሪዎች፤

21.የዚህ አዋጅ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች፤

22.በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ታዋቂ ግለሰቦች።

5. <u>**የምክር ቤቱ ዓላማዎች**</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር አግባብ ያላቸው አካላት ለችግሩ ይበልጥ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግና የኅብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲያጎለብቱ በማበረታታት ጤናማ አመለካከትና ባህሪ የሚዳብርበትን ሁኔታ መቀየስ፤
2. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረጉት የኤች.አይ. ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ጥረቶች በተናጠል ሳይሆን በተቀናጀ መልክ እንዲካሄዱና ወጣቶችና ሴቶችን ጨምሮ ለበሽታው ይበልጥ የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል እንዲችሉ አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
3. ከኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች የጤና፤የሥነ ልቡናና የምክር አገልግሎትና አስፈላጊውን የማቴሪያል ድጋፍ የሚያገኙበትን እንዲሁም ሰብአዊ መብታቸው የሚከበርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
4. የአገሪቱ የኤድስ ፖሊሲ ከአጠቃላይ የጤና ፖሊሲው ጋር ተቀናጅቶ ተግባር ላይ የሚውልበትን መንገድ ለመቀየስና የበሽታውን ሥርጭት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ዕቅድና ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚረዱ ሃሳቦችን ማመንጨትና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የጥናትና የምርምር ተግባሮችን ማበረታታት፣

[70] ይህ ንዑስ አንቀፅ በአማርኛው ላይ የተዘለለ ሲሆን ሆኖም በእንግዘኛው ላይ “the president of the Ethiopian labor unions confederations” በሚል ተቀምጧል፡፡

5. በተጠናከረና በተቀናጀ መልክ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም ከአገር ውስጥና ከውጭ እርዳታ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

6. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1. ዓላማውን ለማስፈጸም በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሃሳብ ያመነጫል፤
2. ከአገር ውስጥና ከውጭ እርዳታ ለማሰብሰብ ለለጋሾች ጥሪ ያቀርባል፣ ስለዕርዳታው አጠቃቀም አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፣ አፈጸጸሙን ይከታተላል፣
3. የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን አፈጻጸምና በዚሁ ዙሪያ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ ይገመግማል፤ የማሻሻያና የማጠናከሪያ ሃሳቦችን ያቀርባል፤
4. በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት አመርቂ ውጤት ላስገኙ ተቋማትና ግለሰቦች ሽልማት ይሰጣል፤
5. የራሱን ዓርማ ቅርጽና ይዘት ይወስናል፣
6. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሃሳቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎች ያቋቁማል።

7. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል፤ ሆኖም በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፤
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡
3. የምክር ቤቱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት

8. **መቋቋም**

1. የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ[71] ይሆናል፤

9. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

10. **ዓላማ**

የጽሕፈት ቤቱ ዓላማ የአገሪቱን የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ፖሊሲ አፈጻጸም ማስተባበርና መምራት ይሆናል።

11. **ሥልጣንና ተግባር**

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤
2. የምክር ቤቱን አስተያየት አካቶ የተዘጋጀ አገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ለመንግሥት አቅርቦ ያስጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤
3. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላትንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
4. ኅብረተሰቡ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግንዛቤ እንዲኖረው አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችና ዓውደ ጥናቶች ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
5. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ አኅጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤
6. በአገሪቱ ያለውን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ገፅታ መረጃዎች ያሰባሰባል፣ ያጠናቅራል፤ እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሰራጫል፤
7. ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፤
8. በልገሳ የተገኘው ገንዘብና ከመንግሥት የሚመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

12. **የጽህፈት ቤቱ አቋም**

---

[71] በ17/1(2003) አ.691 አንቀጽ 33(20) ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

ጽሕፈት ቤቱ፦

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. በመንግሥት የሚሾም አንድ ኃላፊ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

13.<u>ስለቦርድ አባላት</u>

1. የሥራ አመራር ቦርዱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ፖሊሲን በማስፈጸም ረገድ ጉልህ ሚና ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የምክር ቤቱ አባላት ከሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በመንግሥት ይመደባል።

14.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የሥራ አመራር ቦርዱ፤

1. ጽሕፈት ቤቱ የሚከታተላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ መልኩ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. ከፕሮግራምችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር ተያይዘው በሚነሱና አመራር በሚሹ ጉዳዮች ላይ እንደ አግባቡ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም ከአስተያየቱ ጋር ለመንግሥት ያቀርባል፤
3. የጽሕፈት ቤቱን መዋቅርና የሰው ኃይል ፕላን መርምሮ ለመንግሥት ያቀርባል፤
4. ለመንግሥት የሚቀርበውን የጽሕፈት ቤቱን በጀትና ሪፖርት ያጸድቃል፤
5. በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ይወስናል።

15.<u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

3. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

16.<u>የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ይመራል፤ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፦

ሀ/ በቦርዱ ስብሰባዎች በአባልነት ይሳተፋል፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፤

መ/ የጽሕፈት ቤቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣

ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል

ሰ/ የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

3. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቀልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱ በማይኖርበት ጊዜ የሚወከለው ሰው ከ30 ቀናት በላይ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

17.<u>በጀት</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ መደበኛ በጀት በመንግሥት ይመደባል።
2. ጽሕፈት ቤቱ ለሚያስፈጽማቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገው በጀት ከመንግሥት፤ በለጋሽ ድርጅቶችና በኅብረተሰቡ ከሚደረግ የገንዘብ መዋጮና ከውጭ ከሚገኝ የመንግሥት ብድር የተውጣጣ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው በጀት የገንዘብ መዋጮዎቹ ከተደረጉበት የብድርና የዕርዳታ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩና በሥራ አመራር ቦርዱ በጸደቀ የጽሕፈት ቤቱ የግዥና የወጭ አፈጻጸም ሥርዓት መሠረት በጥቅም ላይ ይውላል።

18.<u>የባንክ ሂሳብ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(2) የተመለከተው ገንዘብ በጽሕፈት ቤቱ ስም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል።

19.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ለተመለከቱት የገንዘብ ምንጮች የተለያዩ የሂሳብ መዝገቦች ይይዛል፣
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዘግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

20.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ጽሕፈት ቤቱ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ፖሊሲ አፈጻጸምን በማስተባበርና በመምራት ረገድ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

21.<u>ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

22.<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት በመባል የሚታወቀው አካል መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጽሕፈት ቤቱ ተላልፈዋል።

23.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 4 ቀን 1994ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ 4 ቀን 1994 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

## <u>አዋጅ ቁጥር 553/1999</u>

## <u>የመድኃኒት ፈንድን እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

ጤና ለሕዝብ የተደላደለ ሕይወትና ምርታማነት መሠረት በመሆኑንና መድኃኒትም በጤና አገልግሎት ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ፤

ለጤና አገልግሎት ከሚመደበው መዋዕለ ንዋይ ለመድኃኒት የሚውለው ወጭ ከፍተኛ በመሆኑ፤

ጥራታቸው የተረጋገጠ መሠረታዊ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመንግሥት የጤና ተቋማት አስተማማኝና ዘለቄታ ያለው የመድኃኒት አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል የሚያስፈልግ ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ ህብረተሰቡ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አሠራር መቀየስ ተገቢ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመድኃኒት ፈንድን እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 553/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. "መድኃኒት" ማለት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከል፣ ለማስታገስ ወይም ለማከም የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የሕክምና መገልገያዎችንና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤
2. "የሕክምና መገልገያ" ማለት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ የሰውነት አካል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መገልገያ ሲሆን፣ የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ ሲሪንጆችን፣ መርፌዎች፣ ፋሻ፣ ጉዝ፣ ጥጥና መሰል ዝግጅቶች፣ ኬሚካሎችንና ፊልሞችን ይጨምራል፤
3. "የህክምና መሣሪያ" ማለት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ የሰውነት አካል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ጥገናና የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤
4. "የመንግሥት የጤና ተቋም" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደር የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤
5. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47(1) የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፣
6. "አግባብ ያለው አካል" ማለት የጤና ተቋማትን ብቃትና የመድኃኒትን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ለማረጋገጥ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፣
7. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው።

## ክፍል ሁለት

## የመድኃኒት ፈንድ

3. **መቋቋም**

የመድኃኒት ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንዱ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡

4. **የፈንዱ ምንጮች**

ፈንዱ የሚከተሉት ምንጮች ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ከመድኃኒት አቅርቦት ከሚገኝ የተጣራ ገቢ፤
2. ከመንግሥት በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ፤ እና
3. ከለጋሽ አካላት በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ እርዳታ።

5. **የፈንዱ አጠቃቀም**

ፈንዱ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን እንዲሸፍን ከተደረገ በኋላ ተመልሶ በማዟዟር ለመድኃኒት ግዥ እና ለመድኃኒት አገልግሎት ማስፋፊያና ማጠናከሪያ እንዲውል ይደረጋል።

## ክፍል ሦስት
## የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ

6. **መቋቋም**

1. የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

7. **ዋና መሥሪ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል።

8. **ዓላማ**

የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የመንግሥት ጤና ተቋማት ጥራታቸው የተረጋገጠ መሠረታዊ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ እንዲያቀርቡ የማስቻል፣
2. የመድኃኒት አቅርቦቱን በማጠናከርና ዘለቄታዊነቱን በማረጋገጥ የጤና አገልግሎቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ የማድረግ፣
3. ፈንዱ ወጪውን እንዲሸፍን ከተደረገ በኋላ ተመልሶ በማዟዟር እራሱን በማሳደግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱትን ዓላማዎች እውን ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት።

9. <u>የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በመድኃኒት ፈንድ በመጠቀም በሀገሪቱ ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮሩ ጥራታቸው የተረጋገጠ መሠረታዊ መድኃኒቶችን በበቂ መጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመንግሥታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥና የስርጭት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤
2. ዘመናዊ የክምችት አስተዳደር ለማስፈን የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችትና ያልተቋረጠ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፣
3. የክምችትና የሥርጭት አውታሮችን ፍትኃዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ ያስፋፋል፤ ያጠናክራል፤
4. አግባብ ባለው አካል ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶችን ለመንግሥት የጤና ተቋማት ያቀርባል፣ አግባብ ሆኖ ሲገኝ በበቂ መጠን ሊቀርቡ ያልቻሉ የተመረጡ መድኃኒቶችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መንግሥታዊ ላልሆነና ለግል የጤና ተቆማት ያቀርባል፤
5. የማጓጓዣ ሥርዓትን በማመቻቸት መድኃኒቶችን በቀጥታ ለወረዳዎች ሆስፒታሎችና እንደአመቺነቱ ለጤና ጣቢያዎች ያደርሳል።
6. በዘርፉ ከሚዘረጋው ስርዓት ጋር የሚጣጣም ዘመናዊ የሎጅስቲክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ይዘረጋል፤

7. የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የግዥ፣ የስርጭት፣ የማከማቸትና የማጓጓዝ ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገብራል፤ አፈፃፀመንም ይገመግማል፣
8. በሚያከናውናቸው የሥራ ዘርፎች ላይ ሙያዊ የምክር አገልግሎትና ሥልጠና ይሰጣል።
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ኮማቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውን ይመራል፤ ያስተባብራል፤
10. ለሚሰጠው አገልግሎት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ክፍያ ያስከፍላል፤
11. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
12. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

10. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው ፦

1. አንድ ቦርድ፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

11. <u>የቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ አቅራቢነት አግባብ ካላቸው የፌደራል መንግስት አካላት በመንግስት የሚሰየሙና ከክልሎች የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል።
2. የቦርዱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ በመንግሥት ይወሰናል።

12. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የኤጀንሲውን ስትራቴጂዎችና የአፈጸጸም መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የኤጀንሲው ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ክትትል በማድረግ ያረጋግጣል፤

4. የመድኃኒት ፈንድን አሰባሰብና ከፈንዱም ላይ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ የሚሆንበትን የአሰራር ሥርዓት ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤
5. የመድኃኒት ግዢ፤ ክምችትና ሥርጭት አሰራር መመሪያዎችን ያጸድቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውንም ይከታተላል፤
6. ኤጀንሲው ከባንክ የሚበደረውን የገንዘብ መጠንና አከፋፈሉን ይወስናል፤
7. ለኤጀንሲው ዳይሬክተሮች ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ያፀድቃል፤
8. ዓመታዊ የሒሳብ ሪፖርት ያፀድቃል፣ የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ይሰማል፣ በቀረበለት የኦዲት ሪፖርት ተመስርቶ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ ሪፖርቱንም ይፋ ያደርጋል፣
9. ስለሚሸጡ ቋሚ ንብረቶችና ከመዝገብ የሚፋቁ ሂሳቦችን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፤
10. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ኮሚቴውን ይመራል፤ ያስተባብራል፤
11. ኤጀንሲው የሚያስከፍለውን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ይወስናል

13. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ይሰበሰባል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ሁለት ሶስተኛ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል። ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ ኣንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

14. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የቦርዱ አጠቃላይ አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተመለከቱትን የድርጅቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ/ የኤጀንሲውን ሂሣቦች በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ሠ/ ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ ስለኤጀንሲው የሥራ እንቅስቃሴ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተሳልፍ ይችላል።

15.<u>የመድኃኒት ግዢና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም ስርዓት</u>

1. አጠቃላይ የመንግሥት ግዢ መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ኤጀንሲው የራሱ የሆነ የግዢ መመሪያ ይኖረዋል።

2. መንግሥታዊ የጤና ተቋማት በሙሉ የመሠረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ፍላጐቻቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ ጥያቄ በማቅረብ ይገለገላሉ።ኤጀንሲው የተጠቀሱትን መድኃኒቶች ለማቅረብ በማይችልበት ወቅት ለጠያቂዎች ተገቢውን አማራጭ መፍትሔ ይሰጣል። ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል።

3. የመሠረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦትና አገልግሎት የተሰጣቸው መንግሥታዊ የጤና ተቋማት እና ሌሎች አካላት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ መሠረት ለኤጀንሲው ተገቢውን ክፍያ ይፈጽማሉ።

16.<u>በጀትና የኃላፊነት መጠን</u>

1. የኤጀንሲው በጀት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15(3) መሠረት ከሚሰበስበው ገቢ የሚሸፈን ሆኖ በቦርዱ መጽደቅ አለበት።
2. ኤጀንሲው ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

17. <u>የባንክ ሂሣብ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው ገንዘብ በኤጀንሲው ስም በተከፈተ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ይሆናል።

18. <u>ስለክፍያዎች</u>

ከመድኃኒት ፈንድ ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው በጸደቀው ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በቦርዱ መመሪያ መሠረት ይሆናል።

19. <u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

ኤጀንሲው የመድኃኒት ፈንዱን የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

20. <u>ኦዲት</u>

የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በውጪ ኦዲተሮች ይመረመራሉ። በኦዲተር የተመረመሩ የሂሣብ መግለጫዎች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባሉ።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

21. <u>መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ</u>

የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ አክስዮን ማኅበር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

22. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያ ወጣ ይችላል።
2. ቦርዱ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

23. <u>የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።:/

24. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## ደንብ ቁጥር 189/2002

## የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 34 እና በምግብ፣ መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 2(43) እና 55(1) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 189/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤
2. "ምግብ" ፣ "መድኃኒት" ፣ "የጤና ባለሙያ" ፣ "የህክምና ባለሙያ" ፣ "የጤና ተቋም" እና "ክልል" በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤
3. "የመድኃኒት ባለሙያ" ማለት አግባብ ባለው አካል የሙያ ስራ ፍቃድ የተሰጠው ፋርማሲስት፣ ድራጊስት ወይም ፋርማሲ ቴክኒሻን ነው፤
4. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃሂትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የባለሥጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

የባለሥልጣኑ ዓላማ፦

1. የምግብ ደህንነትና ጥራትን፤
2. የመድኃኒት ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀምን፤
3. የጤና፣ የህክምናና የመድኃኒት ባለሙያዎችን ሙያዊና የስነ ምግባር ብቃትን፤
4. የጤና ተቋሞችን ድርጅታዊ ብቃትን፤ እና
5. የሀይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ለግልና ለሕብረተሰብ ጤና ተስማሚ መሆኑን፤ በማረጋገጥ የተጠቃሚውን ጤንነት መጠበቅ ይሆናል ።

6. **የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር**

1. ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

ሐ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

መ/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ህጋዊ ተግባሮችን ያከናውናል።

2. ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል አግባብ ላላቸው የክልል አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

7. **<u>የባለስልጣኑ አቋም</u>**

ባለሥልጣኑ፡-

1. አማካሪ ቦርድ፣
2. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>የአማካሪ ቦርዱ አባላት</u>**

1. የአማካሪ ቦርዱ አባላት በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሰየማሉ። የአባላቱ ስብጥርም፡-

ሀ/ ከጤና ባለሙያዎች ማህበራት፣

ለ/ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣

ሐ/ ከተጠቃሚዎች ማህበራት፣ እና አግባብ ካላቸው ሌሎች ማኅበራት፣ ተቋማትና ባለሙያዎች፤

የተውጣጣ ይሆናል።

2. የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል የሚሰየም ይሆናል።

9. **<u>የአማካሪ ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

አማካሪ ቦርዱ፡-

1. ባሰሥልጣኑን በፖሲሲና ስትራቴጂ ነክ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤
2. እንደ አስፈላጊነቱ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፤
3. የራሱን የስብሰባና የአሰራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል።

10. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሰልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለ ሥልጣኑ ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች ህግን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የባለስልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።
   ሐ/ የባለስልጣኑን አመታዊ ስራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
   መ/ ለባሰሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤
   ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11.<u>**የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባር**</u>

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-
   ሀ/ የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤ እና
   ለ/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጣቸውን ሥራዎች ያከናውናሉ።
2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

12.<u>**በጀት**</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.የሂሳብ መዛግብት

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት መያዝ አለበት።
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.መብትና ግዴታ ስለመተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 176/1991 ተቋቁሞ የነበረው የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

15.ደንቡ የሚፀናበት ግዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 191/2003**

**የኢትዮጵያ የጤና መድህን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ ኣካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 5 እና 34 እና በማህበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ቁጥር 690/2002 አንቀጽ 10 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፤

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የጤና መድህን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 191/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ ኣገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የማህበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ቁጥር 690/2002 ነው፡

2. “ሚኒስቴር” ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው።
3. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፤፤

3. <u>**መቋቋም**</u>

1. የኢትዮጵያ የጤና መድህን ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ በሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>**ዋና መስሪያ ቤት**</u>

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል።

5. <u>**ዓላማ**</u>

የኤጀንሲው ዓላማ የጤና መድን ስርዓትን ለማስፈፀም ይሆናል።

6. <u>**የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር**</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የጤና መድህን ሥርዓትን ለማስፈጸም ቀልጣፋና ብቃት ያለው አሠራር ይዘረጋል፤ ይተገብራል፤
2. ለጤና መድህን ሥርዓት የሚከፈለውን ወርሃዊ መዋጮ ይሰበስባል፣ ያስተዳድራል፤
3. ብቃታቸው ከተረጋገጠ የጤና ተቋማት ጋር ውል ይዋዋላል፣ ክፍያ ይፈጽምላቸዋል፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ይከታተላል፤
4. አባላት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን አስተያየትና ቅሬታ ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ ተገቢውንም መፍትሄ ይሰጣል።
5. የጤና መድህን መተግበር ባለባቸው ተቋማት ሁሉ እየተተገበረ መሆኑን ያረጋግጣል፤
6. የጤና መድህን የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን መንገድ ያመቻቻል፤ በዚሁ መስክ የተሰማሩትን ያበረታታል፣ ያስተባብራል፤
7. የጤና መድህን ሥርዓቱን በተመለከተ ተከታታይነት ያለው የሕዝብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይስጣል፤

8. የጤና አገልግሎት ፓኬጆችንና የመዋጮውን መጠን ለመከለስ አስፈላጊውን ጥናት ያደርጋል፣ ውጤቱንም ከአስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል በመንግሥት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባሮቻቸውን ይመራል፣ያስተባብራል፤
10. መንግሥት በሚሰጠው መመሪያ መሠሪት ኢንቨስት ሊያደርግ ይችላል፤
11. የጤና መድህን ሥርዓቱን የፋይናንስ አቋም ዘላቂነት የሚያረጋግጡ እርምጃዎች ይወስዳል፤
12. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል በስሙ በስሙ ይከሰሳል፤ ይከሰሳል
13. አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል በውክልና አግባብ ላላቸው ተቋማት ይሰጣል።
14. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፦

1. የስራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኃላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡ እና
3. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይኖሩታል፤

8. <u>ስለቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ በመንግስት የሚሰየሙ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤
   ሀ/ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን አንድ ተወካይ፤
   ለ/ ከኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌዴሬሽን አንድ ተወካይ፤
   ሐ/ ከሌሎች አግባብ ካላቸው አካላት የተውጣጡ አባላት፤
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ድምጽ ሳይኖረው በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል።
3. የቦርድ ኣባላት በመንግሥት የሚወሰን ወርሃዊ አበል ይከፈላቸዋል፤፤

9. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

2. የኤጀንሲውን መዋቅርና የደመውዝ ስኬል በመንግሥት ለማፀደቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
3. ለኤጀንሲው ዳይሬክተሮች ተጠሪ የሆኑ የስራ ኃላፊዎችን ቅጥር፡ ምደባና ስንብት ያፀድቃል፤
4. የኤጀንሲውን ስትራቴጂዎችና የውስጥ አሠራር መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
5. የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በመንግሥት ለማጸደቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤
6. የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ሪፖርት ያፀድቃል፤ የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፣ በቀረበለት የኦዲት ሪፖርት ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤ ሪፖርቱንም ለባለድርሻዎች ይፋ ያደርጋል፤
7. ኢንቨስትመንትን ጨምሮ ለጤና መድህን ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን ያፀድቃል፤
8. አግባብ ባላቸው የጤና መድህንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤
9. በኤጀንሲው ተግባር ስር በሚሸፈኑ ጉዳዮች ላይ መመሪያዎችን ያወጣል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በሦስት ውር አንድ ጊዜ የሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ወይም ከአባላት ውስጥ በአንድ ሦስተኛው ሲጠየቅ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. ከቦርድ አባላት በስብሰባው ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሳባው ከተገኙ አባላት በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን</u>

1. የአንድ የቦርድ አባል የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል ሆኖም ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ እንደገና እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የቦርድ አባል የአገልግሎት ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ከአባልነት መሰናበት ቢፈልግ ይህንኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሲጠናቀቅ የነባሩ ቦርድ፣ ስብሳቢ ከስድስት ወራት ለማይበልጥ ጊዜ በቀጣዩ ቦርድ ውስጥ በአባልነት እንዲቀጥል ይደረጋል።

12.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የቦርዱ አጠቃላይ አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ስር የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

ለ/ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ህግን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፣

ሐ/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራና የበጀት ዕቅድ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ/ የኤጀንሲውን መመሪያዎች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል።

ሠ/ ስለኤጀንሲው የሥራ አንቅስቃሴ የሚገልፅ ሪፖርት በቦርዱ አስጸድቆ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

ረ/ ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፣

ሰ/ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለቦርዱ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

13.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣

ሀ/ የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

ለ/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጧቸውን ሥራዎች ያከናውናሉ።

2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

14. <u>በጀትና የኃላፊነት መጠን</u>

1. ኤጀንሲው ለሠራተኞች ደመወዝና ለአስተዳደራዊ ወጪዎች መሸፈኛ የሚያስፈልገው በጀት ከፌዴራል መንግሥት ይመደብለታል።
2. ኤጀንሲው ለአገልግሎት ወጪዎች ክፍያ የሚያስፍልገውን በጀት በአዋጁ አንቀጽ 6 ከተጠቀሱት ምንጮች ያገኛል።
3. ኤጀንሲው ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፤፤

15. <u>የባንክ ሂሳብ</u>

ኤጀንሲው በስሙ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል።

16. <u>ስለክፍያዎች</u>

ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው በጸደቀው የኤጀንሲው ዓመታዊ የሥራ መርሐ ግብርና በቦርዱ መመሪያ መሠረት ይሆናል።

17. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የጤና መድህን ሥርዓትን ገንዘብ በተመለከተ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።
3. በኦዲተር የተመረመሩ የሂሣብ መግለጫዎች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በአራት ወራት ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባሉ።

18. <u>ተፈፃሚኒት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነትት አይኖረውም።

19. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ህዳር 23 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**ደንብ ቁጥር 301/2006 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 35 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 301/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. “ምርምር” ማለት አዕምሯዊ እውቀትን በመጠቀም አዲስ ነገር ለማግኘት፣ ዘዴዎችንና አሰራሮችን ለመፍጠር፣ ለመተንተን የሚደረግ ጥናት ሲሆን የሰው ልጆችን እውቀት በማጎልበት የጤና ችግሮችን የሚፈታና ኑሮን የሚያሻሽል እንቅስቃሴ ነው፤
2. “የቴክኖሎጂ ሽግግር” ማለት በኢንዱስትሪዎች፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በመንግሥትና በሌሎች ተቋማት መካከል የሚደረግ የሙያ፣ የእውቀት ፣ የቴክኖሎጂ፣ የአመራረት ዘይቤዎችን፣ የምርት ናሙናዎችን የመለዋወጥ ሂደት ሆኖ በውጤቱም ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ እድገቶች ለተጠቃሚ የሚደርሱበትና ተጠቃሚውም ቴክኖሎጂውን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ ጥቅም፣ ቁሳቁስ ወይም አገልግሎት የሚቀይርበት ሂደት ነው፤
3. “በስርዓተ ጤና ላይ የሚደረግ ምርምር” ማለት የህክምና አገልግሎት አሰጣጥን፣ የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶችን አቅርቦት፣ የሰው ኃይል ሥልጠናና አመዳደብ፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም፣ የጤና መረጃ ስርዓትን፣ የጤናውን ዘርፍ ፖሊሲና አስተዳደርን በተመለከተ የሚደረግ ችግር ፈቺ ጥናት ነው፤
4. “ድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር” ማለት የህብረተሰብ ጤና ችግሮችን ለመቀነስ የሚደረግ የጤና ቅኝት፣ የመተንበይ፣ አደጋውን የመለየት፣ የመከላከል፣ የመዘጋጀት፣ ተገቢ ምላሽ የመስጠት፣ የመቆጣጠርና ከህብረተሰብ ጤና አደጋ ተፅኖ ቶሎ የማገገም ሂደት ነው፤
5. “ሪፈራል ዲያግኖስቲክ ምርመራ” ማለት በሌላ ላብራቶሪ ሊሠራ የማይችል የምርመራ ዓይነት ወይም በሌላ ላብራቶሪ ተሠርቶ ተጨማሪ ማረጋገጫ የሚሻ የምርመራ ዓይነት ነው፤
6. “ሪፈራል አናሊቲካል ምርመራ” ማለት ከሌላ የምግብ፣ የውሃና የአካባቢ ናሙና ምርምራ ላብራቶሪዎች አቅም በላይ የሆነና ተጨማሪ የጥራት ማረጋገጫ የሚፈልግ የምርመራ ዓይነት ነው፤
7. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
8. “ሚኒስቴር” ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. **የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች**

   ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

   1. በአገር አቀፍ የህብረተሰብ ጤና ምርምር አጀንዳ ላይ ተመሥርቶ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የጤናና ሥነ ምግብ ችግሮች ላይ ምርምር ማድረግ እና ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ እውቀትን በማመንጨት በመቅሰምና በማሰራጨት የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል፤
   2. የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቅኝት በማካሄድ ስጋቶችን ቀድሞ መለየትና በቂ ዝግጅት በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በተገቢ ሁኔታ መከላከል፣ ሲከሰትም ማንቂያ ማስጠንቀቂያና ወቅታዊ መረጃ ማስተላለፍ፣ ፈጣንና ብቁ ምላሽ መስጠት እንዲሁም የተጎዳውን የህብረተሰብ ክፍል ከጤና አደጋው ተጽኖ በፍጥነት እንዲያገግም ማድረግ፤
   3. የኢንስቲትዩቱን ላብራቶሪዎችን በሰለጠነ የሰው ኃይልና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ በማጠናከር ችግር ፈቺ ምርምሮችን ማካሄድ፤ ለህብረተሰብ ጤና አደጋ ውጤታማ ምላሽ መስጠት፤ ሪፈራል ዲያግኖስቲክና አናላቲካል ምርመራዎችን ማካሄድ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ የጤናና የምግብ ሳይንስ ላብራቶሪዎችን አቅም በመገንባት ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል።

6. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት**

   ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

   1. የህብረተሰብ ጤናና ሥነ ምግብን በተመለከተ አገራዊ የምርምር አጀንዳ ይቀርፃል፣ በአጀንዳው ላይ የተመረኮዘ ምርምር ያካሂዳል፤ በተገኙ የምርምር

ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ የፖሊሲ ሐሳብ ያቀርባል፣ የምርምር ውጤቶችን ያሰራጫል፣ የተሰሩ ምርምሮችን ፋይዳ ይገመግማል፤

2. በአገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ ምርምሮች የሚቀናጁበትና ውጤታማ የሚሆኑበት አሰራር ይዘረጋል፤ አገር አቀፍ የምርምር መረጃ ቋት ይመሰርታል፣ ክልሎችና ሌሎች ተቋማት ለሚያከናውኗቸው ምርምሮች ድጋፍ ይሰጣል፤
3. ለህብረተሰቡ ዋና ዋና የጤና ችግሮች የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማስረጽ ክትባትን፣ የበሽታ መመርመሪያ ኪቶችን፣ የምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ ምርምር ውጤቶችን እና ሌሎች ለጤና አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶችንና ውጤቶችን እንደአስፈላጊነቱ ያመርታል ወይም በአገር ውስጥ በስፋት እንዲመረቱ ሳይንሳዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
4. በስርዓተ ጤናውና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ምርምሮች እና ግምገማዎችን በማድረግ በሽታን ለመከላከል እና ጤናን ለማበልፀግ የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፤
5. የአካባቢና የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤና መሠረት ያደረጉ የህብረተሰብ ጤና ምርምሮች ይሰራል፤
6. በተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች፣ በሥነ ምግብ፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ በጤና ሥርዓቱ ላይ እና በሌሎች መሰል የጤና ጉዳዮች ላይ አገራዊ ዳሰሳና ቅኝቶችን ያካሂዳል፤
7. የምግብ እጥረትና ያለመመጣጠን የሚያስከትሏቸው በሽታዎች የሚወገዱበትን መንገድና በቤተሰብ ደረጃ የአመጋገብ ሁኔታ እንዲሻሻል የሚያስችል ምርምር ያካሂዳል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፤
8. በባህል መድሃኒቶችና ሕክምና ዘዴዎች እንዲሁም በዘመናዊ መድሃኒቶች ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ ፍቱንነታቸው፣ ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የተረጋገጠላቸው የባህል መድሃኒቶች በዘመናዊ መንገድ የሚመረቱባቸውን ስልቶች ይቀይሳል፣ በጤና አገልግሎት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተቱ የሚያስችላቸው ሃሳብ ያቀርባል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለባህል መድሃኒቶች የሚውሉ ዕፅዋቶች እንዳይጠፉ ለመጠበቅ ለሚደረጉ ሥራዎች የበኩሉን ድጋፍ ይሰጣል፤

9. በማንኛውም የህብረተሰብ ጤና ምርምር ላይ የምርምር ተሳታፊውን ደህንነት፣ መረጃ አያያዝ፣ በአጠቃላይ የምርምር ስነምግባርን እና መልካም የምርምር አሠራርን የሚመለከቱ የአፈታፀም መመሪያዎችና ማንዋሎችን ያወጣል፤
10. ከአገር ውስጥና የውጭ አገር ተቋማት ጋር የጋራ ምርምሮችን ይሰራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ምርምሮችን የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት በሌሎች አካላት አማካኝነት እንዲሰሩ ያደርጋል፤
11. በህብረተሰብ ጤና ምርምር በድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥርና የላብራቶሪ ጥራት ስርዓት በሚመለከት ተጨባጭ ፍላጎቶችን መሰረት ያደረጉ የአጭር ጊዜና የሥራ ላይ ስልጠናዎች ይሰጣል፣ የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት ረገድም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ይተባበራል፤ እንደአስፈላጊነቱም የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
12. በተመረጡ የጤና ሥጋቶች፣ በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ በሽታዎች፣ የሥነ ምግብ ችግር እና የአካባቢ ጤና ችግሮችን በተመለከተ ቅኝት ያካሂዳል፣ ይተነትናል፣ ወቅታዊ መረጃ ያሰራጫል፤
13. የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ ስልቶችን ይቀይሳል፤ የአፈፃፀም መመሪያዎችን ያወጣል፣ የዝግጁነትና የምላሽ ዕቅድ ያዘጋጃል አቅም ይገነባል፣ ጠንካራ የቅንጅትና የትብብር ሥርዓት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ተጋላጭነት ዳሰሳና የጤና አደጋ ሥጋት ትንተና ያካሂዳል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤
14. ወረርሽኝ ወይም ሌላ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ወይም የህብረተሰብ ጤና አደጋ ሥጋቶች ሲከሠቱ እንደአግባብነቱ በቦታው ተገኝቶ ምርመራ ያካሂዳል፤ ክስተቶችን ያረጋግጣል፣ ያነቃል፣ ያስጠነቅቃል፤ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፣ ግብዓቶችን ያንቀሳቅሳል ወይም እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ ለሚደረጉ የምላሽ ሥራዎች ድጋፍ ይሰጣል፤
15. ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ጤናን በተመለከተ የደረሰውን ጉዳት በማጥናት ወደነበረበት እንዲመለስ ድጋፍ ያደርጋል፤

16.በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቀውስ የሚያስከትሉ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን በተመለከተ ዓለም አቀፍ የጤና ህጎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

17.የሪፈራል ዲያግኖስቲክ እና አናሌቲካል የላብራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፤

18.የአገሪቱ ላብራቶሪዎች ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የላብራቶሪ ጥራት ሥርዓትን የሚመለከቱ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ የሚያስችላቸውን ስራዎችን ይሰራል፤

19.ለሚሰጠው የማማከር፣ ሪፈራል፣ ዲያግኖስቲክ እና አናሌቲካል የላብራቶሪ አገልግሎቶች መንግሥት ባጸደቀው ተመን መሠረት ክፍያ ያስከፍላል፤

20.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

21.ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፦

1. አማካሪ ቦርድ፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>የአማካሪ ቦርዱ አባላት</u>

የአማካሪ ቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. <u>የአማካሪ ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

አማካሪ ቦርዱ፦

1. ኢንስቲትዩቱን በፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ሌሎች አንኳር ተቋማዊ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤
2. እንደ አስፈላጊነቱ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

10.<u>የአማካሪ ቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. አማካሪ ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።
2. ከአማካሪ ቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

3. የአማካሪ ቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አማካሪ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋናዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 4/1988 በዚህ ደንብ ተሽሯል።

15.<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

በደንብ ቁጥር 4/1988 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

16.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 7 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## <u>ደንብ ቁጥር 330/2007</u>

## <u>የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 35 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 330/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ደም" ማለት በሰውነት ውስጥ የሚዘዋወር ፈሳሽ ሆኖ በውስጡ ነጭና ቀይ የደም ሴሎች፣ ፕላትሌቶችን፣ እና ፕላዝማ የያዘ ነው፤

2. “ደም ልገሳ” ማለት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ከሰብዓዊ አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ የሆነ፤ የሀይማኖት፣ የፆታ እና የዘር ልዩነት የማያደርግ የአብዛኛውን ኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ የሚጠይቅ ደም የመስጠት ሂደት ነው፤
3. “አገልግሎት” ማለት ንጹህ እና በቂ ደም በመሰብሰብ፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት ላይ የሚሠራ ተቋም ነው፤
4. “የደም ህክምና” ማለት ደም እና የደም ተዋጽኦ ህመምተኛው መውሰድ እንዳለበት በሕክምና ባለሙያ ሲረጋገጥ የሚሰጥበት ሂደት ነው፤
5. “የደም ተዋፅኦ” ማለት ቀይ እና ነጭ የደም ሴሎች፣ ፕላትሌቶች እና ፕላዝማ ናቸው፤
6. “የደም ተዋጽኦዎችን ማዘጋጀት” ማለት ከተሰበሰበው ደም ላይ ቀይ እና ነጭ የደም ሴሎችን፣ ፕሌትሌቶች እና ፕላዝማ በመለየት በየምድባቸው ማዘጋጀት ነው፤
7. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
8. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ “አገልግሎት” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የአገልግሎቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፎች ይኖሩታል።

5. <u>የአገልግሎቱ ዓላማ</u>

የአገልግሎቱ ዓላማ በቂ፣ ደህንነቱ የተረጋገጠ እና በወቅቱ የተዘጋጀ ደምና የደም ተዋጽዖዎችን እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ደም የሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲያገኙ ማድረግ ይሆናል።

6. **የአገልግሎቱ ሥልጣን ተግባራት**

የአገልግሎቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ያኖሩታል፦

1. የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በመገናኛ ብዙሃን እና በሌሎች ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር የበጎ ፍቃድ የደም ለጋሾችን ቁጥር ማበራከት፤
2. በትምህርት፣ በጤና፣ መንግስታዊ መንግስታዊ ባልሆኑ፣ በሃይማኖት እና በሌሎች መሰል ተቋማት ጨምሮ በሕብረተሰቡ ውስጥ በተቋቋሙት እና ወደፊት ለሚቋቋሙት የደም ለጋሾች ክበባት ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ፤
3. ደምና የደም ተዋጽዖዎች ከበጎ ፈቃድ ለጋሾች መገኘቱን ማረጋገጥ፣ ደምና የደም ተዋጽዖዎች መሰብሰብ፣ አስፈላጊውን የላቦራቶሪ ምርመራ ማድረግ፣ ማዘጋጀት፣ ተገቢ በሆነ መልኩ በማከማቸትና ደህንነቱ ተመርምሮ የተረጋገጠ ደም የደም ተዋጽዖዎች ህክምና ለሚሰጡ ጤና ተቋማት ማሰራጨት፤
4. የጤና ተቋማትን የደም አገልግሎት ወይም የደም አጠቃቀም ለማሻሻል ማጠናከር፣ በማንኛውም ጊዜ የደም ክምችት በየጤና ተቋሙ መኖሩን ማረጋገጥ፣ የሆስፒታል ደም ህክምና ኮሚቴዎች መመስረታቸውንና በአግባቡ መስራታቸውን ማረጋገጥ፤
5. ለጤና ተቋማት በቂና ደህንነቱ የተጠበቀ ደምና የደም ተዋጽዖ ማቅረብ፤
6. በብሔራዊ ደረጃ የደም ክምችት መኖሩን ማረጋገጥ፣ የክልል የደም ባንኮችን ማስተባበር፣ ትስስር መፍጠር እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
7. እንደ አስፈላጊነቱ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር የተገናኙ ምርምሮችን ማከናወን፣ የአጭር ጊዜና የሥራ ላይ ስልጠና ለሠራተኞች መስጠት እና የአገልግሎት አሰጣጡን በመስኩ ከሚገኘው ዘመናዊ እውቀትና ቴክኖሎጂ ጋር በማዛመድ ማሳደግ፤
8. ደም ለመሰብሰብ፣ ለመለየት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሠራጨት፣ ለማስወገድ እና የደም እና የደም ተዋጽዖን ለክሊኒክ አገልግሎት ለማዋል የሚያስችል የአሰራር መመሪያዎችን ማውጣት፤
9. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፤ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

10.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

7. **የአገልግሎቱ አቋም**

አገልግሎቱ፡-

1. በሚኒስትሩ የሚመደብ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
2. አስፈላጊ ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

8. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአገልግሎቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የአገልግሎቱን ሥልጣንና ተግባራትን ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የአገልግሎቱን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የአገልግሎቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

   መ/ ለአገልግሎቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች አገልግሎቱን ይወክላል፤

   ረ/ የአገልግሎቱን የስራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለአገልግሎቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአገልግሎቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. **የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉ ሥልጣንና ተግባራት ኖራቸዋል፦

1. የአገልግሎቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡት ሌሎች ስራዎችን ያከናውናሉ፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው በውክልና የሚሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናለ።

10. <u>በጀት</u>

የአገልግሎቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

11. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. አገልግሎቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የአገልግሎቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

12. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

አገልግሎቱ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር ሊያወጣ ይችላል።

13. <u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 30 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 376/2008**

**የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ ቁጥር 5 እና 39 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 376/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

1. "ምርምር" ማለት አዕምሯዊ እውቀትን በመጠቀም አዲስ ነገር ለማግኘት፣ ዘዴዎችን እና አሰራሮችን ለመፍጠር፣ ለመተንተን፣ የምርምር ውጤቶችን ለማላመድ፣ ለማሻሻል በቤተ ሙከራም ሆነ ከቤተ ሙከራ ውጭ የሚደረግ ተግባር ነው፤
2. "የሕክምና ምርምር" ማለት ቅድመ ክሊኒካል፣ ክሊኒካል እና ተሸጋጋሪ ምርምር በማካሄድ አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ ዕውቀቶች ለማስገኘት የሚደረግ ምርምር ነው፤
3. "ቅድመ ክሊኒካል ምርምር" ማለት ከክሊኒካል ሕክምና ሙከራ በፊት የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ጤና ነክ ምርምር ሆኖ ባዮኢንፎርማቲክስ፣ ጄነቲክስ፣ ሞለኪዩላር ባዮሎጂ፣ ኢሚዩኖሎጂ፣ ማይክሮባዮሎጂ የመሳሰሉትን የሚያካትት ከሰውነት ውጭም ሆነ በላብራቶሪ እንስሳት ላይ የሚደረግ ምርምር ነው፤
4. "የሕክምና ሙከራ" ማለት አዲስ ለሆነ ወይም ስለተሻሻለ መድሀኒት፣ ክትባት፣ የሕክምና ዘዴ እና ስለመሳሰሉት ፈዋሽነትና ደህንነት ሳይንሳዊና አስተማማኝ ማረጋገጫ ለማግኘት ፈቃደኛ በሆኑ ሰዎች ላይ ቁጥጥር እየተካሄደ የሚደረግ ሙከራ ነው፤
5. "ባዮሜዲካል ምርምር" ማለት የህክምናውን ዘርፍ ዕውቀት ሊያሳድግ የሚችል ቅድመ ክሊኒካል ምርምር ሆኖ በውስጡም መሠረታዊ፣ ተግባራዊ፣ ኦፕሬሽናል እና ተሸጋጋሪ የሆኑ ምርምሮችን የሚያቅፍ ነው፤
6. "መሠረታዊ የህክምና ምርምር" ማለት የአንድን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት ከመሠረቱ ለመረዳት እና አዳዲስ ዕውቀቶችን ለማስገኘት በተደራጀ ሁኔታ የሚከናወን ምርምር ነው፤
7. "ተግባራዊ የሕክምና ምርምር" ማለት የጤና ችግርን ለመፍታት የሚያስችልና በቀጥታ ምርምሩ እንዳለቀ ወደ ተግባር ሊገባ የሚችል ምርምር ነው፤
8. "ተሸጋጋሪ የሕክምና ምርምር (ትራንስናሽናል ሪሰርች)" ማለት መሠረታዊ የሆኑ የሕክምና ምርምር ዉጤቶችን በመውሰድ የጤና ችግሮችን ሊፈታ ወደሚችል ሳይንሳዊ ዘዴ ለማሸጋገር የሚያስችል ጥናት ነዉ፤
9. "ኦፕሬሽናል የህክምና ምርምር" ማለት በህክምና ወይም ጤና እንክብካቤ ሥራ አፈፃፀም ላይ ለውጤታማነት እንቅፋት የሆኑ ወይም የሚሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረግ ምርምር ነው፤

10.“ሜዲካል ባዮ ቴክኖሎጂ ምርምር” ማለት የሥነ-ሕይወት (ባዮሎጂካል) አካላትን ነባራዊ ሂደቶችን ወይም ከዚያ የሚወለዱ ዘዴዎችን በመጠቀም የጤና ክብካቤ እና ህክምናን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ምርምሮች እና የተለያዩ ውጤቶችን ወይም ለዚህ የሚያግዙ ዕውቀቶችኝን ለማስገኘት የሚደረግ ምርምር ነው፤

11.“ባዮኢንፎርማቲክስ” ማለት የኮምፒዩተር ቴክኖሎጅን በመጠቀም የሥነ ሕይወት መረጃን በማከማቸት፣ ለመተንተን እና ለማደራጀት የሚያስችል ሳይንሳዊ መንገድ ነው፤

12.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

13.“ሚኒስቴር እና ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

14.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማ</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የባዮሜዲካል፣ የህክምና እና የሚዲካል ባዮቴክኖሎጂ የምርምር ሥራዎችን በማከናወን፣ በመቅሰም እና በማላመድ የሕብረተሰቡን የተሻለ የሕክምና አገልግሎት፣ ጤንነት እና ደህንነት ማረጋገጥ፤
2. አዳዲስ እና የተሻሻሉ የሕክምና ምርመራ ዘዴዎች፣ ክትባቶች እና መድሀኒቶች ላይ የህክምና የክሊኒካል ሙሙራዎችን በማካሄድ የሕብረተሰቡን ጤና ማሻሻል፤

3. በባዮሜዲካል፣ ክሊኒካል እና በሜዲካል ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ዘርፎች ላይ ለከፍተኛ የትምህርት እና ሌሎች መሰል ተቋማት የአቅም ግንባታ ሥራ መስራት፤ እና
4. በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ በህክምና ምርምርና ሥልጠና ዘርፍ የልህቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል።

6. <u>የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ለሕክምና አገልግሎት ማደግ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸውን የባዮሚዲካል ቴክኖሎጂ፣ የሜዲካል፣ የክሊኒካል፣ ጀነቲክስ፣ ባዮኢንፎርማቲክስ፤ ሲሰተምስ ኢፒዲሞሎጂ እና የሜዲካል ባዮቴክኖሎጂ የምርምር ሥራዎችን አጀንዳ ይቀርጸል፤ በአጀንዳው ላይ ተመርኩዞ ምርምሮችን ያካሂዳል፤ የውጤቶችን ፋይዳ ይገመግማል፤
2. በተገኙ የህክምና ምርምር ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ የፖሊሲ ምክረ ሀሳብ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
3. የምርምር ውጤቶችን ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤ የምርምር ግኝቶችን ወደ ምርት ሊቀይሩ ለሚችሉ አካላት ያስተላልፋል፤ እንደአስፈላጊነቱም ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ የህክምና ምርምር ዘርፉን ለማጠናከር የሚያስችሉ የገንዘብ ምንጮችን፣ የቴክኒክ ድጋፎችን እና ሌሎች ዓብአቶችን ያፈላልጋል፤ ከባለድርሻ እና ከሌሎች አካላት ጋር ትስስር ይፈጥራል፤
4. ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገር ተቋማት ጋር በመተባበር የሕክምና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ምርምሮችን በጋራ ለማካሄድ ለሌሎች አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
5. በተቋሙ የተሰሩ የምርምር ግኝቶች በሀገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የአዕምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት መብት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፤
6. በሕክምና ምርምር ላይ በተሰማሩ ተመራማሪዎች የተገኙ የምርምር ውጤቶች የሚቀርቡበት፣ የሚገመገሙበት እና የወደፊት የሕክምና ምርምር አቅጣጫዎች ላይ የውይይት መድረክ ያዘጋጃል፤
7. የህክምና ሙከራ ለማካሄድ የሚያስችል አገራዊ አቅም ይገመግማል፣ ክሊኒካል የህክምና ሙከራ ለማካሄድ አቅም ያላቸውን አጋር ድርጅቶች ይለያል፤

8. የሕክምና ሙከራ ለማካሄድ የሚያስችል ሀገራዊ አቅም ይገነባል፣ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የህክምና ሙከራ ሊያከናውኑባቸው የሚችሉባቸውን ቦታዎች እና የሕክምና ሙከራ ዓይነቶች ፍላጎት ይለያል፤ በአዳዲስ እና በተሻሻለ የምርመራ ዘዴዎች፣ መድሀኒቶች እና ክትባቶች ላይ የሕክምና ሙከራ ያካሂዳል፤
9. በማንኛውም የሕክምና ምርምር ላይ የምርምር ተሳታፊውን ደህንነት፣ የመረጃ ሚስጢራዊነት እና የምርምር ሥነ ምግባር የሚመለከቱ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ የምርምር መርሆዎችን በሚያከናውናቸው የምርምር ሥራዎች ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
10. ለሕክምና አገልግሎት ማደግ አስተዋጽኦ ያላቸውን የፈጠራ፣ የተሸጋጋሪ፣ የኦፐሬሽናል እና የትግበራ ምርምሮችን ለመስራት የሚያስችል ተቋማዊ መዋቅር ይዘረጋል፣ የግንዛቤ ደረጃን ያጎለብታል፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያሟላል ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር በተዛመደ ሁኔታ መሠረታዊ የህክምና ምርምር መሣሪያዎችን ያሟላል፤
11. በሕክምና ምርምር ዘርፍ ላይ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት ረገድ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ይተባበራል፤ የባለሙያዎችን የትምህርት አቅም ያጎለብታል፤ ጠቃሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግሮችን ያደርጋል እንደአስፈላጊነቱም የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
12. በህክምና ምርምር ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተመራማሪዎች በየዓመቱ ሽልማት ይሰጣል፤
13. በህክምና ምርመራና ስልጠና ከክልሎች እና ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለውን ትብብር ያጠናክራል፤ የዕውቀት ሽግግር እና የጋራ ተጠቃሚነት ያጎለብታል፤
14. በሌሎች አካላት የማይሰሩ የዲያግኖስቲክ እና አናሊቲካል የላብራቶሪ ምርምራ ጥያቄ ሲቀርብለት አገልግሎት ይሰጣል፤ መንግስት በሚያጸድቀው የአገልግሎት ተመን መሰረት ክፍያ ያስከፍላል፤
15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤
16. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ያከናውናል።

7. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

1. ኢንስቲትዩቱ

ሀ/ አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፣

ለ/ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

ሐ/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚሾሙት ዋና ዳይሬክተሮች በህክምና ምርምር ዘርፍ በቂ ልምድ እና አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መሆን አለባቸው።

8. **የቦርድ አባላት**

1. የቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ ይሰየማሉ፣ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰየሙት የቦርድ አባላት አሰያየም የሙያ ስብጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል።
3. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን 5 ዓመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጡ አይችሉም።

9. **የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት**

ቦርዱ፦

1. ኢንስቲትዩቱን በምርምር፣ በፖሊሲ፣ እስትራቴጂ እና ሌሎች አንኳር ተቋማዊ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፣
2. የሳይንስ እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

10. **የቦርዱ ስብሰባዎች**

1. ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል።
2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

11. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤
   ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

1. የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናሉ፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል።

13.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

14.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖሩታል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

15.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 11 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ዳሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ኘ/ <u>ለሰራተኛና እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች</u>**

**<u>ደንብ ቁጥር 202/2003</u>**

**<u>የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “የግል ድርጅች ሠራተኞች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/2003” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**
   1. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል።
3. **ዋና መሥሪያ**

   የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።
4. **ዓላማ**

   የኤጀንሲው ዓላማ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ማድረግ ይሆናል።
5. **ሥልጣንና ተግባር**

   ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   1. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በሥራ ላይ ያውላል፤
   2. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዕቅድን ለማስፈጸም ቀልጣፋና ብቃት ያለው አሠራር ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤
   3. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ሥርዓት ይዘረጋል፣ መዋጮ ይሰበስባል፣ በሚመለከተው የመንግሥት አካል በኩል በተገቢው ጊዜና መጠን መሰብሰቡን ያረጋግጣል፣ የግል ድርጅቶች ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰነዶችንና መዛግብትን አስቀርቦ ወይም በግል ድርጅቶች ተገኝቶ ይመረምራል፤
   4. የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችንና ከፈንዶቹ ጋር የተያያዙ ሀብቶችን ያስተዳድራል፤
   5. የግል ድርጅት ሠራተኞችን ለጡረታ መብት ብቁ የሚያደርጉ ማስረጃዎችን በቅድሚያ አሰባስቦ ይይዛል፤
   6. የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የጡረታ መዋጮ ሂሣብ መዝገብ በማይዙ፣ ማስረጃ በማይልኩ እና መረጃ በማይሰጡ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

7. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ መብትን ለማስከበር የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ብቃትና ተቀባይነት፣ የጥቅም ዓይነት እና መጠኑን ይወስናል፣ ክፍያ ይፈጽማል፤
8. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
9. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን በትሬዠሪ ቦንዶችና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ትርፋማና አስተማማኝ በሆኑ ሌሎች ኢቨስትመንቶች ላይ ያውላል፤
10. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ በየተወሰነ ጊዜ በሂሣብ ስሌት አዋቂዎች እንዲጠና ያደርጋል፤
11. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፕሮግራሞች ስለሚጠናከሩበት ሁኔታ ጥናት እያካሄደ ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
12. በሥልጣንና ተግባሩ ሥር የሚካተቱ ጉዳዮችን በሚመለከት መመሪያዎችን ያወጣል፤
13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
14. ዓላማውን ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

6. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፦

1. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

7. <u>የቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ የመንግሥት፣ የአሠሪና የሠራተኛ ተወካዮች ይኖሩታል፤ የተወካዮቹም ቁጥር እኩል ይሆናል። ጠቅላላ ብዛታቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የቦርዱ ሰብሳቢና መንግሥትን የሚወክሉ አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ። የአሠሪና የሠራተኛ ተወካዮች የሆኑ የቦርዱ አባላት የሚመረጡበት ሥርዓት በመንግሥት ይወሰናል።
3. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

8. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

1. ቦርዱ የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

ሀ/ የኤጀንሲውን ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያፀድቃል፤

ለ/ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅዱንና ፈንዱን የሚመለከቱ አጠቃላይ የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፤

ሐ/ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (12) መሠረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያጸደቃል።

9. **የቦርዱ ስብሰባ**

1. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊስበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብዛኞቹ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው። ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ደንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከተውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራዊ በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን ስትራቴጂ፣ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች ለቦርዱ ያቀርባል ሲጸድቁም ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያስተላልፋል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል በኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11.<u>በጀት</u>

ኤጀንሲው ከጡረታ ፈንዱ በሚመደብ በጀት ይተዳደራል። ሆኖም ኤጀንሲው ሥራውን ለመጀመር እንዲችል በመንግሥት የማቋቋሚያ በጀት ይመደባል።

12.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

13.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 16 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**አ/ <u>ለባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ህጎች</u>**

**<u>ደንብ ቁጥር 174/2002</u>**

**<u>የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ ደንብ "የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 174/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ሚኒስቴር" የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤
2. "ሞዴል ሆቴል" ማለት ማዕከሉ በሥልጠና ወቅት ለተግባር መለማመጃ የሚጠቀምበት ሆቴል ነው፤
3. "የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት
   ሀ/ የመኝታ፣ የምግብና መጠጥ ፣ የመዝናኛ እና መሰል አገልግሎቶችን፤ ወይም
   ለ/ የማስጎብኘት፣ የጉዞ ውክልና እና መሰል አገልግሎቶች የሚሰጥ ድርጅት፤
   ነው፤
4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል (ከዚህ በኃላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የማዕከሉ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. **ዓላማ**

ማዕከሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የቱሪዝም ኢንዱስትሪን ዕድገትና ልማት ለማፋጠን የሚያስፈልገውን በጽንሰ ሐሳብና በተግባር የሰለጠነ የሰው ኃይል በጥራትና በብቃት ለማፍራት የቅድመ ሥራ ስምሪት ሥልጠና መስጠት፤
2. በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የአጭርና የረዥም ጊዜ የሙያ ማሻሻያና የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤

3. በሆቴልና በቱሪዝም ሙያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤ በዘርፉ የልህቀት ማዕከል በመሆን ለመሰል ተቋማት የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤
4. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አስፈላጊ የምክር አገልግሎት መስጠት።

6. <u>**የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማውጣት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የቅድመ ሥራ ስምሪት እና የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፤
2. ለሆቴልና ቱሪዝም መስክ እድገትና ልማት ጠቃሚ የሆነ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ግኝቶችንም ያሠራጫል፣
3. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
4. በሆቴልና ቱሪዝም መስክ በዓበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች፤ በምርምር ውጤቶችና አዳዲስ አስተሳሰቦች ላይ ሴሚናሮችን፣ ሲምፖዚየምችንና ወርክ ሾፖችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤
5. በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ሞዴል ሆቴሉን ይቆጣጠራል፣ የአገልግሎት ጥራቱንም ያሳድጋል፤
6. በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በሌሎች ዘዴዎች እየተገለገለ አቅሙን በመገንባት የስልጠና ብቃቱን ያሻሽላል፤
7. በሀገር ውስጥና በሌሎች ሃገሮች ከሚገኙ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት ይመሠርታል፤
8. ለሚሰጣቸው የሥልጠና እና የምክር አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>**የማዕከሉ አቋም**</u>

ማዕከሉ፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)
2. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣
3. አካዳሚክ ጉባዔ፣ እና
4. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

8. **የቦርዱ አባላት**

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የማዕከሉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤
2. የማዕከሉን መዋቅርና የሥራ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤
3. የማዕከሉን ዓመታዊ የሥልጠናና የሥራ ፕሮግራም፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ እንዲሁም በጀት መርምሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በሚኒስቴሩ አማካይነት ለመንግሥት ቀርቦ የፀደቀው ዕቅድ፣ በጀትና ፕሮግራም በማዕከሉ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤
4. የማዕከሉን ሥራ አፈፃፀም ሪፖርት እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
5. የማዕከሉን ሥልጠናና የአካዳሚክ መመሪያዎችን ያፀድቃል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
6. ማዕከሉ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ካሉ መሰል ተቋሞች ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል።

10. **የቦርዱ ስብዕባ**

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. **የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር፦

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን የአካዳሚክ ሠራተኞች እንዲሁም በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ሌሎቹን የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የማዕከሉን ዓመታዊ ሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለማዕከሉ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፤

ረ/ የማዕከሉን አካዳሚክ ጉባዔ በሰብሳቢነት ይመራል፤

ሰ/ በቦርዱ ስብሰበዎች ላይ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረው ይሳተፋል፤

ሸ/ የማዕከሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቀ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለማዕከሉ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የማዕከሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፦

1. የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

13. <u>የአካዳሚክ ጉባኤው አባላት</u>

የማዕከሉ አካዳሚክ ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር .......... ሰብሳቢ
2. የማዕከሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ...... አባል
3. የማዕከሉ የትምህርት ዲፓርትመንት ኃላፊዎች ........ አባላት
4. የማዕከሉ ሬጂስትራር ...... አባል

5. በማዕከሉ ቋሚ መምህራን የሚመረጡ ሁለት (አንድ ሴት) የመምህራን ተወካዮች ............ አባላት
6. በማዕከሉ ተማሪዎች የሚመረጡ ሁለት (አንደ ሴት) የተማሪዎች ተወካዮች.... አባላት

14. **<u>የአካዳሚክ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር</u>**

የማዕከሉ አካዳሚክ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. የማዕክሉን የአካዳሚክ መመሪያ ያዘጋጃል፤ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የማዕከሉን የሥልጠና ፕሮግራሞች እየመረመረ እንዲፀድቁ ለቦርዱ ያቀርባል፤
3. ማዕከሉ አዲስ የሥልጠና መስክ ለመጀመር ወይም ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ለማሻሻል ሲያቅድ ይዘቱን መርምሮ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ያቀርባል፤
4. የማዕከሉን አካዳሚክ ካሌንደር መርምሮ ያፀድቃል፤
5. የሠልጣኞችን ፈተናና ምዘና በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤
6. በየሴሚስተሩ፣ በየዓመቱና በየኮርሱ ማጠቃለያ የሰልጣኞችን የትምህርት ውጤትና ደረጃ ይገመግማል፤ የተመራቂ ሰልጣኞች ውጤት መርምሮ ያጸድቃል፤
7. ለሰልጣኞች ሠርቲፊኬት፣ ዲፕሎማና ሽልማት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያጠናል፤ በቦርድ ሲፈቀድም ተግባራዊ ደርጋል፤
8. ለማዕከሉ መምህራንና ሠልጣኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ፤ ያደርጋል፤
9. የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ያወጣል፤
10. ሌሎች በቦርዱ የሚሰጡ የአካዳሚክና የሥልጠና ጉዳዮችን ያከናውናል።

15. **<u>በጀት</u>**

የማዕከሉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

1. በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤ እና
2. ከሥልጠናና ከምክር አገልግሎት የሚገኝ ገቢ።

16. **<u>ስለ ሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ማዕከሉ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

2. የማዕከሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በእርሱ በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

17. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በመባል የሚታወቀው አካል መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለማዕከሉ ተላልፈዋል።

18. <u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 254/2003</u>**

**<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትርን ለማቋቋም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀፅ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 254/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ሚኒስቴር" ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤
2. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር (ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ ትያትር" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የብሔራዊ ትያትር ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የብሔራዊ ትያትር ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል።

5. **ዓላማ**

ብሔራዊ ትያትር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ትውፊታዊ ትውን ጥበባትን ማሳደግ፣ መጠበቅና ማራመድ፤
2. በፈጠራ ጥበብ ውበት እያዝናኑ ቁምነገር በማስተላለፍና የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ሕብረተሰቡ በሀገር ልማት፣ በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና መልካም አስተዳደር በማስፈን እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያበረታቱ ልዩ ልዩ ኪነ-ጥበባዊ ሥራዎችን በማዘጋጀት ማቅረብ።

6. **የብሔራዊ ትያትር ሥልጣንና ተግባር**

ብሔራዊ ትያትር የሚክተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ባህላዊ እሴታቸው ተጠብቆና ኪነጥበባዊ ውበት ይዘው በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዛናዊነት እንዲቀርቡና እንዲታወቁ የማድረግ፤
2. የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ትክክለኛ ባህላዊ ገፅታ የሚያንፀባርቁ ትውፊታዊ ትውን ጥበባትን ከምንጫቸው በማጥናትና በፅሁፍ፣ በምስልና በናሙና ቁሳቁስነት በማደራጀትና በመጠበቅ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉና በአገልገሎት ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤
3. የሀገሪቱን የኪነጥበብ እንቅስቃሴ እድገት ወደፊት ለማራመድ የዘርፉ ባለሙያዎች ኪነጥበባዊ ሥራዎቻቸውን በክልል፣ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ መድረኮች እንዲያቀርቡ የቴክኒክና የመረጃ እገዛ የማድረገና የማበረታታት፤
4. የአገሪቱን የኪነጥበብ እድገት ወደፊት ለማራመድ የሚያገዙ ሴሚናሮች፣ ወርክሾፖች፣ ኮንፈረንሶችንና የምክክር መድረኮችን የማዘጋጀትና የማካሔድ፤

5. በኪነጥበባት ዘርፍ የተሠማሩ ሙያተኞችና አመራሮችን አቅም ለማሳደግ የትያትር፣ የሙዚቃ፣ የውዝዋዜ፣ የመድረክ አጠቃቀም እና የአመራር ስልጠና የመስጠት፤
6. ኅብረተሰቡን ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለልማት ለማነሳሳት፣ ኪነጥበባዊ ብቃት ያላቸው ተውኔቶችና ሙዚቃዎችን በማዘጋጀት በመድረክና አመቺ በሆኑ መገናኛ ብዙኃን የማቅረብ፤
7. ለኪነጥበባዊ ሥራዎች ዝግጅት አገልግሎት የሚውሉ መድረኮችን የማደራጀት
8. በኪነጥበብ መስክ የተሰማሩ የፈጠራና የምርምር ባለሙያዎችን የማበረታታትና የመደገፍ፤
9. የሀገሪቱን ትውን ጥበባት ለአፍሪካ ህዝቦች በማስተዋወቅና የልምድ ልውውጦችን በማድረግ የአህጉሩን አንድነትና የባህል ትስስር የማጠናከር፤
10. ዓለም አቀፋዊ ኅብረትና ወዳጅነትን ለማጎልበት የሌሎች አገሮች ኪነጥበባዊ ቡድኖችን ማስተናገድ እና ለኪነ ጥበባት ዕድገት በትብብር የመስራት፤
11. ከሚያቀርባቸው የትያትርና የሙዚቃ ትርኢቶች እና ከሌሎች አገልገሎቶች የሚገኝ ገቢን የመሰብሰብ፣ የንብረት ባለቤት የመሆን ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤
12. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

7. <u>**የብሔራዊ ትያትር አቋም**</u>

ብሔራዊ ትያትር፦

1. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፤ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል።

8. <u>**የዋናው ዳይሬክተር ሥልጣንና**</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የብሔራዊ ትያትር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የብሔራዊ ትያትር ሥራዎችን ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የብሔራዊ ትያትር ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የብሔራዊ ትያትርን የሥራ ፕሮንራምና ዓመታዊ በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በመግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የብሔራዊ ትያትርን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ/ ለብሔራዊ ትያትር በተፈቀደው የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ብሔራዊ ትያትርን ይወክላል፤

ረ/ የብሔራዊ ትያትርን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለብሔራዊ ትያትር ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለትያትር ቤቱ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9. **<u>በጀት</u>**

የብሔራዊ ትያትር በጀት በመንግሥት ይመደባል።

10. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ብሔራዊ ትያትር የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የብሔራዊ ትያትር የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

11. **<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር በመባል ይታወቅ የነበረው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለብሔራዊ ትያትር ተላልፈዋል።

12. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 28 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

## ደንብ ቁጥር 294/2005 ዓ.ም

## የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (እንደተሻሻ) አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 35 መሠረት ይህን ደንበ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 294/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. “ቱሪስት” ማለት በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢ ለጉብኝት፣ ለመዝናናት፣ ዘመድ ወይም ወዳጅ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ዓለምአቀፍ ጉባዔዎችን ለመሳተፍ፡ ለጥናትና ምርምር፣ ሀይማኖታዊ ግዴታዎችን ለመወጣት፣ የስፖርት ዝግጅቶችን ለመከታተል ወይም ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ አገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው፤
2. “ቱሪዝም” ማለት ቱሪስቶች በሚያደርጉት ጉዞ፣ ጉብኝትና ቆይታ በሚያካሂዱት እንቅስቃሴና ግንኙነት የሚፈጠር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ክስተት ነው፤
3. “የቱሪዝም ልማት” ማለት በማንኛውም የአገሪቱ ክልል የሚገኙ ባህላዊ እሴቶችን፤ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን፤ ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን በዘላቂነት በማልማት እንዲጠበቁና ለህዝቦች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ለማድረግ የሚከናወን ሥራ ነው፤
4. “የቱሪዝም ማርኬቲንግ” ማለት የዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ጐብኝዎችን ፍላጐት በማጥናት የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ የቱሪስት መዳረሻዎች፣ የቱሪዝም ምርቶችና አገልግሎቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን፣ የቱሪስት ፋሲሊቴሽን ሥራዎችን በማከናወን የቱሪዝም ሀብቶችን በስፋት በማስተዋወቅና የሽያጭ ተግባራትን በማካሄድ አገሪቱ ከቱሪዝም ዘርፍ የምታገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ የሚከናወን ሥራ ነው፤
5. “የቱሪዝም ተዋናይ” ማለት በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላትን፣ መንግስትን፣ የግል ባለሀብቱን፣ ማኅበረሰቡንና ቱሪስቱንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው፤
6. “የቱሪስት መረጃ ማዕከል” ማለት ቱሪስቶች አገሪቱን ለመጎብኘትና በአገሪቱ ለሚኖራቸው ቆይታ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የሚደራጁበትና በአካል፣ በስልክ ፣ በፋክስ፣ በኢ-ሜይል እና በመሳሰሉት መንገዶች መረጃ የሚሰጥበት ተቋም ነው፤
7. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
8. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
9. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት

### 3. መቋቋም

የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "በምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

### 4. የምክር ቤቱ አባላት

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ .............. ሰብሳቢ፤

ለ/ ሚኒስትሩ ...................... ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ/ የቱሪዝም ቦርድ ሰብሳቢ .................. አባል፤

መ/ በሰብሳቢው የሚሰየሙ አግባብ ያላቸውን ሚኒስቴሮች የሚመሩ ሚኒስትሮች፤ የክልል ፕሬዚዳንቶች እና የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ከንቲባዎች ............................ አባላት፤

ሠ/ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ .............................. አባል፤

ረ/ የኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተርስ አሶስየሽን ፕሬዚዳንት ......................... አባል፤

ሰ/ የሆቴሎች እና ሬስቶራንቶች አሰሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ............ አባል፤

ሸ/ የሆቴል ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት......................................... አባል፤

ቀ/ የቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳን ....................................... አባል፣

በ/ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት......................................... አባል፤

ተ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ .................. አባል፤

ቸ/ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ተወካይ ............ አባል፤

ኀ/ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ተወካይ ............................... አባል፤

ነ/ የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ተወካይ .........አባል፤

ኘ/ የኢትየጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲየን መካነ ኢየሱስ ተወካይ .......... አባል፤

አ/ በሰብሳቢው የሚሰየሙ የግል ባለሀብቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ........... አባላት፤

ከ/ የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር .............. ፀሃፊ።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የፌደራልና የክልል ባለስልጣናት እንዲሁም የኤክስፖርት

አስተያየት እንዲያቀርቡ የሚጋበዙ ባለሙያዎች በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊፈቅድ ይችላል።

5. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአሃገሪቱ የሚካሄዱ የቱሪስት መዳረሻዎች ልማት እና የቱሪዝም ማርኬቲንግ ሥራዎች የእድገትና የልማት አቅጣጫዎችን በበላይነት የመምራት፤
2. የቱሪዝም ሴክተርን እድገት የሚገቱ ዋና ዋና ማነቆዎችና ቁልፍ ችግሮች እንዲፈቱ አስፈላጊውን መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት የመስጠትና ተፈጻሚነታቸውን የማረጋገጥ፤
3. ለቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ ሥራዎች ስኬታማነት የተለያዩ ተቋማት ድጋፍና ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት፤
4. ድርጅቱ ሊከተላቸው በሚገቡ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ የመስጠት።

6. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

1. ምክር ቤቱ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ወይም በምክትል ሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሲሰበሰብ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ስብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሶስት
## የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት

7. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ድርጅቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

8. **ዋና መስሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፎችን ሲከፍት ይችላል።

9. **የድርጅቱ ዓላማ**

የድርጅቱ ዓላማ በአገሪቱ የተፈጥሮ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ሌሎች መስህቦች ላይ ተመስርቶና የቱሪዝም ተዋንያንና ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀትና በመምራት የቱሪስት መዳረሻ ልማትና የቱሪዝም ማርኬቲንግ ሥራዎች ዘላቂና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸው እንዲረጋገጥ በማድረግ ከቱሪዝም የሚገኘውን ጠቀሜታ ማጎልበት ይሆናል።

10. **የድርጅቱ ስልጣንና ተግባር**

ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ የማገልገል፤
2. የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች በውጭ አገርና በአገር ውስጥ የማስተዋወቅ፤
3. የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦችና አገልግሎቶች መረጃ ማዕከላትን በመግቢያ በሮችና በማዕከል የማደራጀት፣ የማስተባበርና የመምራት፤
4. የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦችጀ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ፤
5. የማርኬቲንግ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ መረጃዎችንና የጥናት ዓይነቶችን የመለየት ፣ የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ የማደራጀት እና የማሰራጨት፤
6. የቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ የአገልግሎት ክፍተት በመለየት የስልጠና ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
7. ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር የመፍጠር፤
8. ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የልማት ክፍተት በጥናት በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ የማበረታታት፤
9. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮች የማካሄድ፤

10.ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፎች በማዘጋጀት ስራ ላይ የማዋል፤

11.በውጭ አገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ትብብራዊ ግንኙነት የመመሥረት፤

12.የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

13.ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

11.<u>**የድርጀቱ አቋም**</u>

ድርጅቱ፦

1. የቱሪዝም ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

12.<u>**የቦርዱ አባላት**</u>

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትና ከግሉ ዘርፍ ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

13.<u>**የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት**</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በምክር ቤቱ በሚሰጡ አጠቃላይ አቅጣጫዎች ላይ በመመስረት የአገሪቱን መልካም ገጽታና ዘላቂ ተወዳዳሪነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ የቱሪስት መዳረሻዎች ልማት እና የቱሪዝም ማርኬቲንግ ሥራዎች በድርጅቱ መከናወናቸውን የመከታተል፤
2. በአገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ ልማት ስራዎች እንዲጠኑና የቱሪዝም አማራጮች እንዲስፋፉ አቅጣጫ የመስጠት፤
3. ለዘላቂ የቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ ስራዎች አስፈላጊ የሆኑ የድጋፍ አግባቦችን እየለየ ለተግባራዊነታቸው ክትትል የማድረግ፤
4. የድርጅቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት የመምራት፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀቱ ለሚኒስቴሩ ከመተላለፉ በፊት የመመርመርና የማጽደቅ፣ የሥራ አፈፃፀሙን የመገምገም፤
5. የድርጅቱን የሥራ መመሪያዎች የማጽደቅ፣

6. እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን የማቋቋም።

14.<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቦርዱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

15.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የድርጅቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የድርጅቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሰረት እንዲሁም የድርጅቱን ዓላማ በማስፈፀም ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የድርጅቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ ሲፀድቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   መ/ ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የስራ ዕቅደ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል፤

   ረ/ የድርጅቱን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

16.**በጀት**

የድርጅቱ በጀት በመንግስት ይመደባል።

17.**የሂሳብ መዛግብት**

1. ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።
2. ድርጅቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

18.**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሃሴ 21 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

ከ/ **ለገቢዎች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 160/2001**

**የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

በተካሄደው የመሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ለውጥ ጥናት ግኝት መሠረት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ የሚያስፈልገው ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 603/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 160/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1. "ሎተሪ" ማለት የሽልማት አሸናፊው በዕድል፣ በዕጣ አወጣጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የሚታወቅበት ጨዋታ ወይም ድርጊት ሲሆን ቶምቦላን ወይም ራፍልን፣ ሎቶን፣ ቶቶን፣ ፈጣን ሎተሪን፣ የቁጥር ሎተሪን፣ የተደራራቢ ሽልማት ሎተሪን፣ የፕሮሞሽን ሎተሪን፣ ቢንጎን፣ የስፖርት ውርርድ ሎተሪንና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን ይጨምራል፣
2. "የገንዘብ ሎተሪ" ማለት ሽልማቱ በገንዘብ የሚሰጥ ሎተሪ ነው
3. "ቶምቦላ ወይም ራፍል" ማለት የሎተሪ ቲኬቶቹ ቅድሚያ ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚታተሙ፣ አሸናፊው በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለይና ሽልማቱ በዓይነት የሚሰጥ ሎተሪ ነው፤
4. "የስፖርት ውርርድ ሎተሪ" ማለት በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ የሚከናወኑ የስፖርት ውድድሮችን መሠረት በማድረግ የሚደረግ ውርርድና ሽልማቱ በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጥ ሎተሪ ነው፤
5. "ሎቶ" ማለት አስቀድሞ ከተለዩ ተከታታይነት ካላቸው ቁጥሮች መካከል ተጫዋቹ የሚፈልጋቸውን የተወሰኑ ቁጥሮች በመምረጥ አሸናፊ መሆን አለመሆኑ በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚወሰንበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፤
6. "ቶቶ" ማለት በዋናነት በእግር ኳስ ጨዋታ ወቅት በሚደረግ ውርርድ ሽልማቱ በገንዘብ የሚሰጥ፣ እና

   ሀ/ ከተወራረዱት መካከል ብዙ አሸናፊዎች የሚኖሩ ከሆነ ለሽልማቱ የተመደበው ገንዘብ ለአሸናፊዎቹ እኩል የሚካፈል፣ ወይም

   ለ/ ውድድሩ በተባለው ሰዓት ባይካሄድ፣ ውጤቱ ቢሰረዝ ወይም የጨዋታው ዓይነት ቢለወጥ አሸናፊዎቹ በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለዩበት፣ ሎተሪ ነው።
7. "ፈጣን ሎተሪ" ማለት ተሳታፊዎች የሎተሪውን ቲኬት በመፋቅ ሽልማቱን ማግኘት ወይም ማጣታቸውን ወዲያውኑ የማያውቁበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፤

8. “የቁጥር ሎተሪ” ማለት የሎተሪ ቲኬቶቹ በቅድሚያ ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚታተሙና አሸናፊው በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለይ የገንዘብ ሎተሪ ነው፤
9. “የተደራራቢ ሽልማት ሎተሪ” ማለት ተሳታፊው በአንድ የሎተሪ ቲኬት ከዋናው ሽልማት ሌላ ተጨማሪ ሽልማት የሚያገኝበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፤
10. “ኮንቬንሽናል ቢንጎ” ማለት በቢንጎ ማጫወቻ ክበብ በመገኘትና በቅድሚያ ካርድ በመግዛት ተሳታፊዎች ከአጫዋቹ የሚሰጡ ትዕዛዞችን ከራሳቸው የመጫወቻ ቁጥሮች ጋር እያመሳከሩ አሸናፊ መሆን አለመሆናቸው የሚታወቅበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፤
11. “ዘመናዊ ቢንጎ” ማለት ተሳታፊዎች በሎተሪ ቲኬቶች ላይ የሚሰጡ ትዕዛዞች መሰረት በማድረግ የዕድል ቁጥሮችን ከመጫወቻ ቁጥሮች ጋር እያመሳከሩ አሸናፊ መሆን አለመሆናቸው የሚታወቅበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፤
12. “የፕሮሞሽን ሎተሪ” ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭን ለማስፋት በምርት መጠቅለያ ወይም ክዳን ውስጥ ተደብቀው የሚገኙ ዕጣዎችን፣ ከምርቱ ወይም ከአገልግሎቱ ግዢ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚታደሉና ባለዕድል የሚያደርጉ ኩፖኖችንና ካርዶችን ወይም ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከናወንና ሽልማቱ በዓይነት የሚሰጥ ሎተሪ ነው፤
13. “የሎተሪ ሥራ” ማለት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ማናቸውንም ዓይነት ሎተሪ በማዘጋጀት በአገር ውስጥ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ ማጫወትና ዕጣ ማውጣት ወይም ማናቸውንም ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን ነው።
14. “ሰው” ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
15. “ባለሥልጣን” እና “የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር</u>

### 3. <u>እንደገና መቋቋም</u>

1. የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር (ከዚህ በኋላ "አስተዳደር" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል።
2. የአስተዳደሩ ተጠሪነት ለባለሥልጣኑ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የአስተዳደሩ ዋና መሥሪ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን እንደ አስፈላጊነቱ በአገሪቱ ውስጥ በማናቸውም ቦታ ሊያቋቁም ይችላል።

5. **ዓላማ**

የአስተዳደሩ ዓላማ ሎተሪን በማካሄድ ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት እገዛ የሚያደርግ ገቢ ማመንጨትና የሎተሪ ሥራን መቆጣጠር ይሆናል።

6. **የአስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር**

አስተዳደሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. የሎተሪ ሥራን ያካሂዳል፣ ዕጣ የሚወጣበትን ቀን፣ የሽልማቱን መጠንና ሁኔታ፣ሽልማቱ የሚቀይበትን የጊዜ ገደብና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በሎተሪ ትኬቶች ላይ ያመለክታል፣ አሸናፊ የዕጣ ቁጥሮችንም ለሕዝብ ያስታውቃል፤
2. ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከልዩ ልዩ የሎተሪ ዓይነቶች ከሚገኘው ገቢ ላይ ለዕድለኞች መከፈል ያለበት ድረሻ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤
3. የአሸናፊ ዕጣ የተከፈለባቸውን ከሽያጭ የተረፉ የሎተሪ ቲኬቶች በውጭ ኦዲተር ከተመረመሩ በኃላ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ ያደርጋል፤
4. በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ለሎተሪ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤
5. የሎተሪን ጨዋታ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ የመሣሪያ ዓይነቶችንና መመዘኛዎችን ይወስናል፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
6. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
7. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፤

8. ህገወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል።

## 7. የአስተዳደሩ አቋም

አስተዳደሩ፣

1. በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣
2. በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚሾም ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

## 8. የዋና ዳይሬክተሩ እና የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ዋና ዳይሬክተሩ ከባለሥልጣኑ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአስተዳደሩን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳሬክተር፤

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የአስተዳደሩን ስልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፣

   ለ/ የአስተዳደሩን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ይውላል፤

   ሐ/ ለአስተዳደሩ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

   መ/ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ቢኖርም ከአስተዳደሩ የሥራ ባህሪ አንጻር በባለሥልጣኑ በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የአስተዳደሩን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

   ሠ/ የአስተዳደሩን ሠራተኞች ልዩ የደመወዝ ስኬልና የጥቅማጥቅም ክፍያ አጥንቶ በባለሥልጣኑ በኩል ለመንግሥት ቀርቦ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

   ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ አስተዳደሩን ይወክላል፣

   ሰ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፍርድ ቤት ውጭ ክርክሮችን በስምምነት ይጨርሳል፤

   ሸ/ አዳዲስ የሎተሪ ጨዋታዎችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ጥናቶችን ለባለሥልጣኑ እያቀረበ ያስወስናል፤

   ቀ/ የአስተዳደሩን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል።

3. ዋናው ዳይሬክተር ለአስተዳደሩ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአስተዳደሩ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።
4. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት፤
   ሀ/ የአስተዳደሩን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤
   ለ/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
   ሐ/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

9. <u>የገቢ ምንጭ</u>

አስተዳደሩ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፤

1. የሎተሪ ቲኬት ሽያጭ
2. ከጋራ ሽርክና ሥራ የሚገኝ ገቢ እና፤
3. የፈቃድና የኮሚሽን ክፍያዎች።

10. <u>የገቢ አጠቃቀም</u>

1. ከአስተዳደሩ ገቢ ላይ ለሎተሪ ዕድለኞች የተከፈለውና ለሥራ ማስኬጃ የዋለው ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው የተጣራ ገቢ አስተዳደሩ የሚይዘው የመጠባበቂያ ሂሳብ ብር 1 ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) እስከሚሆን ድረስ ወደዚሁ ሂሣብ ገቢ ይደረጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የመጠባበቂያ ሂሣብ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለሎተሪ ዕድለኞች ክፍያ ለመፈጸም የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል።
3. የመጠባበቂያ ሂሣብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ለተመለከተው ዓላማ በመዋሉ ምክንያት የጐደለ እንደሆነ ከአስተዳደሩ የተጣራ ገቢ ላይ እየተቀነሰ እንዲተካ ይደረጋል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (3) የተመለከተዉ ተቀናሽ ከተደረገ በኋላ ተራፊው ሂሣብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያደርጋል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ፈሰስ የተደረገው ሂሣብ በአስተዳደሩ ስም በመንግሥት ለሚታቀዱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ይውላል።

11.ስለ ሂሳብ መዛግብት

1. አስተዳደሩ የጥንድ ሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመከተል የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል።
2. አስተዳደሩ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

## ክፍል ሶስት

## የሎተሪ ስራ ስለማካሄድና ስለፍቃድ አሰጣጥ

12.የሎተሪ ስራ ስለማካሄድ

1. አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5)፣ (6)፣ (7)፣ (8)፣ (9) እና (11) ላይ የተመለከቱትን የሎተሪ ዓይነቶች የማካሄድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) የተመለከቱትን የሎተሪ ሥራዎች የካፒታል፣ ቴክኖሎጂ ፣ የዕውቀትና የሥራ አመራር ብቃቱ ካላቸው ተሳታፊዎች ጋር በጋራ ሽርክና ሊያካሂድ ይችላል፡
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (3) ፣ (4) ፣ (10) እና (12) የተመለከቱት የሎተሪ ሥራዎች በማንኛውም ሰው በፈቃድ ሊካሄዱ ይችላሉ።

13.ለሎተሪ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (3) መስረት የሎተሪ ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ እንዲስጠው ሲፈልግ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማያያዝ ማመልከቻውን ለአስተዳደሩ ያቀርባል።
2. አስተዳደሩ የቀረበለት የፈቃድ ማመልከቻ የተሟላ መሆኑንና ባለሥልጣኑ በመመሪያ ያወጣቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል።

14.ፈቃድን ስለማገድና መሠረዝ

1. ማንኛውም ባለፈቃድ የዚህን ደንብ ወይም ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪዎችን ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም ከተፈቀደለት ውጭ የሠራ እንደሆነ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እስኪወሰድ ድረስ አስተዳደሩ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል።
2. አስተዳደሩ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፤

   ሀ/ ፈቃዱ የተገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ ወይም መግለጫ በመቅረቡ የሆነ እንደሆነ

   ለ/ ፈቃዱ የአስተዳደሩ ስምምነት ሳይኖር ለሌላ ሰው ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ

   ሐ/ ፈቃዱ የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ ወይም የአገሪቱን ደህንነት የሚጎዳ የወንጀል ተግባር ሲሰራበት ወይም የማጭበርበር ተግባር ሲፈጸምበት ከተገኘ፤

   መ/ ፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከታገደና ባለፈቃዱ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ፤

   ሠ/ ባለፈቃዱ የንግድ ሥራውን የተወ ወይም የከሰረ እንደሆነ፣

   ረ/ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ፍቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ።
3. አስተዳደሩ አንድን ፈቃድ ከማገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት እርምጃውን የሚወስድበትን ምክንያት ለባለፈቃዱ በጽሑፍ በመግለጽ ባለፈቃዱ ጽሁፉ በደረሰው በሰባት ቀናት ውስጥ የበኩሉን አስተያየት በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፡
4. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተገለጸው መሠረት መልስ ካልሰጠ ወይም የሰጠው መልስ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አስተዳደሩ ፈቃዱን የማገድ ወይም የመሠረዝ ውሳኔ ይሰጣል። በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል።

15.<u>ስለፈቃድ እድሳት</u>

1. ከአንድ ዓመት በላይ ለሚካሄድ የሎተሪ ሥራ የሚሰጥ ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ መታደስ አለበት።
2. ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የበጀት ዓመት ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት።

3. አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሰረት ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ የሚያበቃ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር ማመልከቻው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ያድሳል።

16. **ቁጥጥር ስለማድረግ**

1. አስተዳደሩ፣
   ሀ/ የዚህን ደንብና ደንቡን ለማስፈጸም የሚወጡ መመሪያዎች እንዲሁም ፈቃድ የተሰጠባቸው ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
   ለ/ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን ወይም ማናቸውንም ሌላ ዘዴ በመጠቀም የዕድል ይዘት ያላቸው ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ይቆጣጠራል።
   ሐ/ ያለፈቃድ የሚካሄድ የሎተሪ ሥራን የማስቆም ትዕዛዝ ይሰጣል፤ ጥፋተኛውም በሕግ መሠረት እንዲቀጣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል።
2. አስተዳደሩ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማውጣት በማናቸውም አመቺ ሰዓት ወደ ማንኛውም የሕንጻ ይዞታ በመግባት ህገ ወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል።

17. **ክልከላ**

1. ማንኛውም ሰው ከአስተዳደሩ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ማናቸውንም የሎተሪ ሥራ ማካሄድ አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው የሎተሪ ሥራ ለማካሄድ የተሰጠውን ፈቃድ ያለአስተዳደሩ ስምምነት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም።

18. **ስለፈቃድ ክፍያዎች**

ለፈቃድ ማውጫና ማሳደሻ የሚጠየቀው ክፍያ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

19. **የኮሚሽን ክፍያ**

1. አስተዳደሩ የሎተሪ ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ ሲሰጥ ወይም ሲያድስ ከፈቃድ ክፍያው በተጨማሪ፦
   ሀ/ ለቶምቦላ ወይም ለስፖርት ውርርድ ሎተሪ ሲሆን ሎተሪው ቲኬት ሽያጭ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በሚገመተው ጠቅላላ ገቢ ፣

ለ/ ለፕሮሞሽን ሎተሪ ሲሆን ለሽልማት ሊውል በታቀደው ምርት ወይም አገልግሎት ጠቅላላ የመሸጫ ዋጋ የገቢ ግብርን ጨምሮ፣ ወይም

ሐ/ ለኮንቬንሽናል ቢንጎ ሲሆን ባለፈቃዱ በየጊዜው በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ፣ ላይ ተሰልቶ 15% የኮሚሽን ክፍያ ይሰበሰባል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) የተመለከተው ሥራ የኮሚሽን ክፍያ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይከፈል ከቀረ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሠረት ሊወሰድ የሚችለው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍያው ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር የ20% መቀጫ ያስከትላል፤ ሆኖም ጠቅላላ መቀጫው ከሚፈለገው የኮሚሽን ክፍያ 100% ሊበልጥ አይችልም።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. ቅጣት

ድርጊቱ በወንጀል ሕግ መሠረት የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፤

1. ማንኛውም ሰው የጸና ፈቃድ ሳይኖረው የሎተሪ ሥራ ካካሄደ ከብር 50,000 እስከ 100,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል፤
2. ማንኛውም ሰው፤

   ሀ/ የህንፃ ይዞታውን ለሕገ-ወጥ ሎተሪ ሥራ ማካሄጃ እንዲውል ያከራየ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የፈቀደ፣ ወይም

   ለ/ በአስተዳደሩ ቁጥጥር እንዲያደርግ የተመደበን ሠራተኛ ቁጥጥር ወደ ሚደረግበት የሕንፃ ይዞታ እንዳይገባ የከለከለ ወይም የቁጥጥር ሥራው እንዳይካሄድ በማናቸውም መንገድ ያስናከለ፣

   እንደሆነ ከብር 10,000 እስከ 20,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት አስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።

### 21. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

### 22. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

1. የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 535/1999 ይተዳደር የነበረው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለአስተዳደሩ ተላልፈዋል።
2. ይህን ደንብ የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

23.**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በነገሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 27 ቀን 2001 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 437/2011**

**የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፣ ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ**

በፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የጉምሩክ ኮሚሽን በህግ የተቋቋመ በመሆኑ፤

የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን በህግ በመደንገጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፣ ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 437/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

1. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
2. "ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የጉምሩክ ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው፡፡
3. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችና የጉምሩክ ጣቢያዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

4. **ዓላማ**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፤
2. ወደ አገር በሚገቡና ወደ ውጭ አገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፤
3. አግባብነት ያላቸውን የጉምሩክ ህጎችና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውንና ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤
4. ወደ አገር እንዳይገቡና ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ወይም ስለአገባባቸውና ስለአወጣጣቸው ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች መቆጣጠር፤
5. የጉምሩክ ማጭበርበርን እና ኮንትሮባንድን መከላከልና መቆጣጠር፡፡

5. **የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፣ በህግ መሰረት ቀረጥና ታክስ እንዲሁም የፈቃድ እና የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

2. የጉምሩክ ህጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የአስመጪዎች፣ የላኪዎች ወይም በማንኛውም ሰው ይዞታ ስር የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፤
3. በጉምሩክ ወደቦች፣ በወሰን አካባቢዎች እና በመተላለፊያ መንገዶች የጉምሩክ መቅረጫና መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ አጥንቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያቋቁማል፤ ‹
4. የጉምሩክ መጋዘን ያቋቁማል፣ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች የሚከማቹበትን ሥፍራ ይወስናል፣ ዕቃዎች በአግባቡ መያዛቸውን ይቆጣጠራል፤
5. የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፣ በዚህ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና መጓጓዣዎችን ይይዛል፣ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤
6. በጉምሩክ ወደቦችና በወሰን አካባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ ጣቢያዎች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይፈትሻል፣ የጉምሩክ ስነስርዓት ተፈፅሞቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ያረጋግጣል፤
7. ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ወደ ውጭ እገር እንዳይላኩ በሕግ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸውን ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመባቸውን ዕቃዎች ይይዛል፣ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤
8. ገቢና ወጪ ዕቃዎችን በተመለከተ መረጃዎችን ይይዛል፣ ያደራጃል፤ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤
9. ስለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አጣጣል፣ አተማመንና አሰባሰብ እንዲሁም ስለኮንትሮባንድ መከላከልና ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት አጥንቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
10. በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ባለቤት የሌላቸው፣ የተተዉ ወይም የተወረሱ ዕቃዎችን ያስተዳድራል፣ ይሸጣል፣ ያስወግዳል፤
11. በጉምሩክ ህጎች መሰረት ልዩ ልዩ ፈቃዶችን ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤
12. ለጉምሩክ ሥራ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችንና የተለያዩ ጽሁፎችን ያዘጋጃል፤

13. የቀረጥና ታክስ ስሌቶችን፣ አሰባሰብ፣ ሒሳብ አያያዝና ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ዘመናዊ የአሠራር ዘዴዎችንና ሥርዓቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
14. ብቃት ያላቸው የጉምሩክ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፤
15. በመስኩ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ የቀረጥ ነፃ መብቶችንና ማበረታቻዎችን አጠቃቀም በመከታተልና በመቆጣጠር ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
16. የጉምሩክ ወንጀሎችን በሚመለከት የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፤
17. የጉምሩክ ህግን ለማስከበር የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋል፤
18. የጉምሩክ ሕግ እንዲያስከብር የተመደበለትን የፖሊስ ኃይል በስራ ላይ ያሰማራል፤ የተመደበው የፖሊስ ኃይልን በሚመለከት ከፌደራል ፖሊስ ጋር በጋራ ያቅዳል፣ ይፈጽማል፣ ይገመግማል፤
19. የጉምሩክ ላቦራቶሪ ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤
20. ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አመራር መሠረት የጉምሩክ አስተዳደርን በሚመለከት ዓለምዓቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፤
21. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ለመከሰስና ለመክሰስ ይችላል፤
22. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

6. <u>የኮሚሽኑ አቋም ኮሚሽኑ፣</u>
   1. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነሮች፤
   2. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤ እና
   3. በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የሚመደብ የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል ይኖሩታል፡፡

7. <u>የኮሚሽነሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኮሚሽኑን ሠራተኞች በደንብ ቁጥር 155/2000 መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ይውላል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) የፍትሐብሔር ክርክሮችን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ሊጨርስ ይችላል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፤ ሰ) ስለ ሥራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የኮሚሽኑ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

8. <u>**የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር ምክትል ኮሚሽነሮች፡-**</u>

1. የየስራ ዘርፋቸውን ተግባሮች በማቀድ፣በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳሉ፡፡
2. በኮሚሽነሩ የሚሰጧቸውን ሌሎች ስራዎች ያከናውናሉ፡፡
3. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ የተወከለው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

9. <u>**በጀት**</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

10. <u>**የሂሳብ መዛግብት**</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

11. **ተፈፃሚ የማይሆኑ ህጐች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ደንብና መመሪያ በደንቡ በተሸፈኑ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

12. **ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ኀዳር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ወ/ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 256/2004

### የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንናተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 256/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. “ካይዘን” ማለት የማያቋርጥ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ አስተሳሰብና መሳሪያ ነው፤
2. “ሚኒስቴር” ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤[72]
3. “የካይዘን አማካሪ” ማለት የማምረቻና አገልግሎት ተቋማትን ስለካይዘን አስተሳሰብና መሣሪያዎች ለማሰልጠንና ለማማከር ብቁ የሆነ ሰው ነው፤
4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት (በዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል[73]።

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **የኢንስቲትዩቱ ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ መሰረተ-ሰፊና የማያቋርጥ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በማከናወን ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ይሆናል።

6. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የካይዘን አስተሳሰብና መሳሪያዎችን ለማስረጽ የሚያስችል ስትራቴጂና ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ያስፈጽማል፤
2. የመንግስትን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች ለማስፈጸም የሚያበቃ ሀገራዊ የጥራትና የምርታማነት ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎችን ያከናውናል፤
3. ለጥቃቅን፣ ለአነስተኛ፣ ለመካከለኛ እና ለከፍተኛ የማምረቻ ተቋማት የካይዘን ማስተማሪያና የምክር አገልግሎት መስጫ ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤

[72] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(5)(ሐ) በገልፅ ሳይነገር “የፐብሊክ እና ሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር” ሆኖ ተሻሻለ፡፡

[73] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 38(5)(ሐ) በገልፅ ሳይነገር ተሻሻለ፡፡

4. ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ባለሙያዎች የካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣አፈፃፀሙንም ይደግፋል፤ ይከታተላል፤
5. ለመካከለኛና ከፍተኛ ተቋማት የካይዘንሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤
6. በአገልግሎት ሰጪና በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የካይዘን አስተሳሰብንና መሳሪያዎችን በየደረጃው ለማስረጽ የሚያስችሉ የሥልጠና፣ የማማከርና የማስተባበር ሥራዎችን ያከናውናል፤
7. ተቋማት ካይዘንን እንዲተገብሩ እና የጥራትና የምርታማነት ባህልን እንዲያዳብሩ የሚያነቃቃ የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፤
8. የካይዘን የጥራትና ቁጥጥር እና የምርታማነት ማሻሻያ ቡድኖች በየተቋማቱ እንዲመሠረቱ የድጋፍ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችን ይመዘግባል፤ ዕውቅናም ይሠጣል፤
9. በካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑ የላቀ አፈፃፀም ለሚያሳዩ ድርጅቶች የዕውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት ያዘጋጃል ፣ ያስፈጽማል ፣ የጥራት ምልክትም እንዲያውለበልቡ ይፈቅዳል፤
10. በካይዘን የተገኘውን መሻሻል ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤
11. የካይዘን ትግበራን አፈፃፀም ለመገምገም የሚያስችሉ የውጤት መለኪያዎችን ያዘጋጃል፣ በተግባር ላይም ያውላል፤
12. ለካይዘን አሰልጣኞችና አማካሪዎች የብቃት ግምገማና ማረጋገጫ ሥርዓት ይዘረጋል፤
13. የካይዘን ትግበራ ምርጥ ተሞክሮ የመቀመር፣ የማስፋፋትና ሞዴል ድርጅቶችን የማፍራት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ዓመታዊ ሕትመቶችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፤
14. የጥራት ወርን በመሰየም በሃገር አቀፍ ደረጃ የመወያያና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ያዘጋጃል፤
15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

16. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. **አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፦

1. ምክር ቤት
2. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. **የምክር ቤቱ አባላት**

1. የምክር ቤቱ አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግስት ይሰየማሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል።

9. **የምክር ቤቱ ተግባራት**

ምክር ቤቱ፦

1. ጥራትንና ምርታማነትን ለማሻሻል በኢንስቲትዩቱ የሚዘጋጁ የካይዘን ስትራቴጂዎችንና ዕቅዶችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤
2. በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤
3. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈጻጸም በየሦስት ወሩ ይገመግማል፣ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል።

10. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

1. ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አብዛኞቹ በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል

   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

   ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.<u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ. ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 203/2003**

**የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 203/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ (ከዚህ በኃላ "ኢጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል።

3. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

4. **ዓላማ**

የኤጀንሲው ዓላማ የመንግሥት ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ማድረግ ይሆናል።

5. **ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በሥራ ላይ ያውላል፤
2. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ እቅድን ለማስፈጸም ቀልጣፋና ብቃት ያለው አሠራር ይዘረጋል ይተገብራል፤
3. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ሥርዓት ያዘረጋል፣ መዋጮ ይሰበስባል፣ በሚመለከተው የመንግሥት አካል በኩል በተገቢው ጊዜና መጠን መሰብሰቡን ያረጋግጣል፣ አሠሪ መሥሪያ ቤቶች ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰነዶችንና መዛግብትን አስቀርቦ ወይም በአሠሪ መሥሪያ ቤቶች ተገኝቶ ይመረምራል፤
4. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችንና ከፈንዶቹ ጋር የተያያዙ ሀብቶችን ያስተዳድራል፤
5. የመንግሥት ሠራተኞችን ለጡረታ መብት ብቁ የሚያደርጉ ማስረጃዎችን በቅድሚያ አሰባስቦ ይይዛል፤
6. የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የጡረታ መዋጮ ሂሣብ መዝገብ በማይዙ፣ ማስረጃ በማይልኩ እና መረጃ በማይሰጡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤
7. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መብት ለማስከበር የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ብቃት እና ተቀባይነት፣ የጥቅም ዓይነት እና መጠኑን ይወሰናል፣ ክፍያ ይፈጽማል፤
8. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

9. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችን በትሬዠሪ ቦንዶችና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ትርፋማና አስተማማኝ በሆኑ ሌሎች ኢንቨስትመንቶች ላይ ያውላል፤
10. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችን በየተወሰነ ጊዜ በሂሣብ ስሌት አዋቂዎች እንዲጠኑ ያደርጋል፤
11. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፕሮግራሞች ስለሚጠናከሩበት ሁኔታ ጥናት እያካሄደ ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
12. በሥልጣንና ተግባሩ ሥር የሚካተቱ ጉዳዮችን በሚመለከት መመሪያዎችን ያወጣል፤
13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
14. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

6. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ፣
2. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

7. <u>የቦርዱ አባላት</u>

1. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፤
2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

8. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ቦርዱ የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

   ሀ/ የኤጀንሲውን ስትራቴጂ፣ ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያጸድቃል፤

ለ/ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድንና ፈንዶቹን የሚመለከቱ አጠቃላይ የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፤

ሐ/ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (12) መሠረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያጸድቃል።

9. **የቦርዱ ስብሰባ**

1. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሲሰበሰብ ይችላል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብዛኞቹ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ገባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው። ሆኖም ድምጹ አኩል ለአኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ደንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከተውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን ስትራቴጂ፣ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ጠጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቁም ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ያስተላልፋል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11.**<u>በጀት</u>**

ኤጀንሲው ከጡረታ ፈንዱ በሚመደብ በጀት ይተዳደራል።

12.**<u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>**

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

13.**<u>ስለመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

በአዋጅ ቁጥር 495/1998 እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

14.**<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 16 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**<u>ደንብ ቁጥር 321/2006 ዓም</u>**

**<u>መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

በትምህርት፣ በሥልጠና፣ በምርምር፣ በምልከታ፣ በትንተና እና በሥርፀት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሀሳቦችን በማመንጨት የህዳሴውን መድረክ የአመራር ጥያቄ ሊመልስና የታላቁን መሪ ራዕይ በአስተማማኝ ሁኔታ በማሳካት የህዳሴውን ጉዞ ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚያስችል የአመራር መገንቢያ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 35 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 321/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "ጉባኤ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 መሠረት የተቋቋመው የአካዳሚው ሴኔት ነው፣
2. "ሠልጣኝ" ማለት አካዳሚው በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ተመልምሎ ሥልጠና ላይ ያለ ሰው ነው፣
3. "የአካዳሚው ዘርፍ" ማለት የአካዳሚው አካል የሆነ ዲፓርትመንት፣ ፋኩሊቲ ክፍል፣ ማዕከል ወይም ትምህርት ቤት ነው፣
4. "የአገልግሎት ክፍያ" ማለት አካዳሚው በእውቀት ላይ ተመስርቶ ለሚሰጠው የስልጠና የምርምርና ሌሎች አገልግሎቶች የሚያስከፍለው ክፍያ ነው፣
5. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
6. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ</u>

3. <u>መቋቋም</u>

1. መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ (ከዚህ በኋላ "አካዳሚ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የአካዳሚው ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የአካዳሚው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. <u>የአካደሚው መርሆዎች</u>

አካዳሚው የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት በሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ይመራል፡-

1. ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አመለካከትና አስተሳሰብ መያዝ፣

2. ሁልጊዜ መማር፣ መማማር እና መመራመር፤
3. ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር፤
4. በብዝሃነት፣ በሕዝብ ወሳኝነትና ተጠቃሚነት ማመን፣
5. ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፤
6. ለውጥን በቀዳሚነት ማራመድ።

6. <u>የአካዳሚው ዓላማዎች</u>

አካዳሚው የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የታነፀ፣ የአመራር ጥበቦችን የተካነ፣ በፈጠራ ችሎታው የተመሰገነ፣ ለሕዝብ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ የመስጠት ጥልቅ የአስተሳሰብ ክህሎት ያለው አመራር በየደረጃው ማፍራት የሚችል ጥልቀትና ምጥቀት ባላቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ የተመሠረተ አስተማማኝና ሁሉን አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መዘርጋት፤
2. የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ፍልስፍናን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚተገብርና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብን በፅኑ መሠረት ላይ በመገንባት ዲሞክራሲያዊ አንድነት እንዲሰፍን የሚደረገውን ሁለንተናዊ ጥረት በበላይነት የሚመራ የህዳሴዉን አመራር በየደረጃዉ መፍጠር፤
3. የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ዓለም አቀፋዊ አሕጉራዊና አካባቢያዊ ሥልጠናዎችን በመስጠትና ፎረሞችን በማዘጋጀት ማስፋት፤
4. አገሪቱ የጀመረችው የህዳሴ ጉዞ ግቡን እንዲመታ የሕዝቡን ንቅናቄ የሚመራና ከልማታዊ መንግሥት አጠቃላይ ዓላማዎችና መርሆዎች በሚፈልቁ ተልዕኮዎች ላይ በመመስረት የአመራር አቅም ግንባታ ማካሄድ፤
5. ለአገራችንና አካባቢያችን ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ተጨባጭ አንድምታ ያላቸውን ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች በመከታተልና በመተንተን የሰልጣኞችን ንድፈ ሃሳባዊና ተግባራዊ አመራር ማሳደግና የታላቁን መሪ አስተምህሮዎች በማስጨበጥ ወደፊት የማራመድ ችሎታቸውን ማሳደግ፤
6. ዕውቀትን በማዳበር፣ በማስፋፋትና በማስተላለፍ የሥራ ክቡርነትንና የሕብረተሰብ ብልፅግናን የሚያራምድ አስተሳሰብ እንዲሰርጽና የባህሪ፣ የሥራ ባህል ለውጥና ዕድገት እንዲመጣ የሚጠበቀውን ኃላፊነት መወጣት፤

7. ሠልጣኞች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች፣ እኩልነትና ዲሞክራሲያዊ አንድነት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር።

7. <u>**የአካዳሚው ተግባርና ሃላፊነት**</u>

አካዳሚው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. ለህዳሴው ጉዞ በንድፈ ሃሳብ ዕውቀት የዳበረ፣ በአመለካከትና ክህሎት የጎለበተ፣ የሥራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ያለው አመራር ማዘጋጀት፤
2. ለአካዳሚው ዓላማ መሳካት በአገራዊ፣ በአካባቢያዊ፣ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ በቂ ዕውቀት ያላቸው፣ በሥነምግባር የታነጹ፣ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያላቸው ብቁ መምህራን መልምሎ ማዘጋጀት፤
3. በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና ዙሪያ ለአገር ውስጥ ለውጭ ለተለያዩ የአመራር አካላትና ባለሙያወዎች ሥልጠና መስጠት፤
4. የሠልጣኙን ግንዛቤ፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድጉና ለችግሮች አፈታት የሚረዱ የተመረጡ ልምዶችን በመቀመር ሥልጠና መስጠት፤
5. የመንግሥት ፖሊሲዎችን አተገባበርና ውጤታማነት ማጥናት በቅድመ ሥልጠና፣ በሥልጠና ላይና ከሥልጠና በኋላ ክትትል ማድረግ፣ የብቃትና ጥራት ደረጃን መለካት፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በጥናትና ምርምር በማስደገፍ ግኝቶቹን ለሥልጠና በሚመጥን መልኩ በግብዓትነት ማቅረብ፤
6. ተመጋጋቢነትና ቀጣይነት ያለው የአመራር ግንባታ ሥርዓት በመዘርጋት በየደረጃው ያለውን አመራር አገራዊ፣ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አውድ ላይ አቅማቸውን መገንባት፣
7. ለሥልጠናው አግባብነት ያላቸው የስልጠና አሰጣጥ፣ የምዘናና ግምገማ ሥርዓቶችን ማደራጀት፣
8. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በስፋት በመጠቀም የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የምርምር፣ የግንኙነትና የማስረፅ ሥራዎችን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፤
9. በአገር ውስጥና በውጭ ካሉ አካዳሚዎች፣ የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አቻ ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር፤
10. የጉባኤውን ውሳኔና የሚቀረጸውን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በማድረግ ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን በአግባቡ ላጠናቀቁ ሰልጣኞች የምስክር

ወረቀት፣ ዲፕሎማ፣ የባችለር ዲግሪ፣ የማስተርስ ዲግሪ፣ የዶክትሬት (ፒ.ኤች.ዲ) ወይም ተመሣሣይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ መስጠት፤

11. የትምህርትና ሥልጠና መጽሔቶች እና ጋዜጦች ማዘጋጀት፣ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ፍልስፍና ላይ ተገቢውን የጥናት የምርምር የምልከታና ትንተና ሥራዎችን ማካሄድ፣ ማሳተምና ማሠራጨት፤

12. ሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች ተልዕኮዎቻቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ተቋማዊ አቅማቸውን በማጎልበትና የስልጠና ፕሮግራሞች ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ እንዲፈፀሙ ድጋፍ ማድረግ፤

13. በቦርዱ በሚፀድቅ ተመን መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ፤

14. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤

15. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

8. <u>**የአካዳሚው አቋም**</u>

አካዳሚው፦

1. መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤
2. ተጠሪነቱ ለቦርዱ የሆነ የትምህርትና ሥልጠና ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤
3. በመንግስት የሚሾሙ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች፤
4. የአካዳሚው ጉባኤ፤ እና
5. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

9. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢ፤
2. በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት፤
3. የአካዳሚው ፕሬዚደንት፤
4. እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ ወይም በአካዳሚው የሚመደብ ፀሐፊ።

10. <u>**የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት**</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. የአካዳሚው ከፍተኛው የውሳኔ ሰጭ አካል በመሆን አካዳሚውን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የአካዳሚውን የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የምርምርና የሥርፀት አጠቃላይ ፖሊሲ አቅጣጫ ይወስናል፤
3. የአካዳሚውን አደረጃጀት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፤
4. አካዳሚው የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የበላይነት በቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ወሳኝ የአመራር ኃይል መፍለቂያ እንዲሆን በበላይነት ይመራል፤
5. የአካዳሚውን ስትራቴጅያዊ ዕቅድ መርምሮ ያጸድቃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
6. አካዳሚው ሊከተላቸው ስለሚገቡ ሌሎች ወሳኝና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች አቅጣጫ ይሰጣል።

11.<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አንድ ሦስተኛ በሆኑት የቦርድ አባላት ውሳኔ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
2. ከቦርዱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል፤
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

12.<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

የምክር ቤቱ ሰብሳቢ የአካዳሚው ፕሬዚዳንት ሆኖ የአካዳሚው ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ የሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች ኃላፊዎች እና ቁጥራቸው እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰኑ ከአካዳሚው እና ከሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።

13.<u>የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. በስትራቴጅያዊ ጉዳዮች እና ቦርዱ በጋራ መታየት አለባቸው ብሎ በሚወስናቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ቦርዱን የማማከር፤

2. የአካዳሚውንና ሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች የትምህርትና ሥልጠና እንቅስቃሴዎች የመከታተያ፣ የማስተባበሪያና የመገምገሚያ መድረክ በመሆን የማገልገል፣
3. መንግሥት በየበጀት ዓመቱ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት በሚያስቀምጣቸው የትኩረት ነጥቦችና አቅጣጫዎች ላይ በመመስረት በየደረጃው ያለውን አመራር የንድፈ ሃሳባዊ ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ክህሎት፣ ሥነ-ምግባርና ሌሎች ክፍተቶችን በዳሰሳ ጥናት በመለየት ለአካዳሚው ቦርድ መነሻ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፣
4. የአካዳሚውን የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ቀረፃና ትግበራ ተመጋጋቢነትና ቀጣይነት የማረጋገጥ፣
5. ሥርዓተ ትምህርቱን ለማጎልበት፣ ውጤታማ ሥልጠና ለማካሄድና የአካዳሚውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ልምዶችን በመቀመር ለሥልጠና ግብዓቶች እንዲያገለግሉ የማድረግ፣ ተፈፃሚነታቸውን የማረጋገጥ፣
6. የመስክ ምልከታ ቦታዎችን በመምረጥ ለሥልጠና ግብዓት የማዘጋጀት፣
7. በቦርዱ የሚወጡ ልዩ ልዩ የአሠራር መመሪያዎችና አቅጣጫዎች በአካዳሚዎቹ በጥብቅ የሚፈፀሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣
8. የሥልጠናና የምርምር ፍሳሾትን መሠረት በማድረግ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅቱ የአካዳሚውን ተልዕኮና ራዕይ በሚያሳካ መልኩ መደራጀቱን የማረጋገጥ፣ በአፈፃፀም የሚታዩ ጉድለቶችን በማጥናትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት መነሻ ውሳኔ ሃሳብ ለቦርድ የማቅረብ፣
9. የአካዳሚውን ዓመታዊ የስልጠና ዕቅዶች በመመርመርና በማደራጀት ለቦርዱ መነሻ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፣ ሲፀድቅም በተቀመጠው አቅጣጫ፣ የጊዜ ሰሌዳና አሰራር መሠረት መፈፀሙን የማረጋገጥ፣
10. በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

14. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

1. ምክር ቤቱ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሦስተኛ ሲደገፍ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

15.<u>የፕሬዝዳንቱ ተግባርና ሃላፊነት</u>

1. የአካዳሚው ፕሬዚዳንት የአካዳሚው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአካዳሚውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ፦
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ (7) የተመለከቱትን የአካዳሚውን ተግባራትና ኃላፊነቶች በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ አካዳሚው በብዛት፣ በዓይነት፣ በጥራት እና በብቃት የሚፈለገውን ያህል አመራር ማፍራቱን ያረጋግጣል፤
   ሐ/ መማር ማስተማርን፣ ምርምርንና ሥልጠናን የሚያበረታታ አመቺ ተቋማዊ ሁኔታን ይፈጥራል፤ ቀጣይነቱንም ይገነባል፤
   መ/ የአካዳሚው የምርምርና የሥልጠና ተግባራት መንግሥት ቅድሚያ በሚሰጣቸው የሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ላይ ማተኮራቸውን ያረጋግጣል፤
   ሠ/ የአካዳሚው የትኩረት አቅጣጫ፣ ደንብና መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች አግባብ ባለው የመንግሥት ፖሊሲና ሕግ መሠረት መቀረጻቸውን ያረጋግጣል፤
   ረ/ የአካዳሚውን ተቋማዊ የደረጃ መለኪያዎች ያዘጋጃል፣ የአካዳሚው የኮሚሽን ሥራዎች በወጡት የደረጃ መለኪያዎች መሠረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣
   ሰ/ የአካዳሚውን ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በቦርዱ በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣

ያስተዳድራልን፤

ሸ/ የአካዳሚውን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤

ቀ/ ለአካዳሚው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

በ/ አካዳሚው ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ አካዳሚውን ይወከላል፤

ተ/ የአካዳሚውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቸ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮች ያከናውናል።

3. ለአካዳሚው ሥራ ውጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለምክትል ፕሬዝዳንቶች እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ኃላፊነቱን በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

16.<u>የምክትል ፕሬዝደንቶች ተግባርና ሃላፊነት</u>

የአካዳሚው ምክትል ፕሬዚዳንቶች በኃላፊነት የተመደቡበትን ዘርፍ የመምራት፣ በአካዳሚው ውስጥ የማስተማርና የማሰልጠን ተግባርና ኃላፊነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተጓዳኝ ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖራቸዋል፦

1. ፕሬዚዳንቱ ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የማማከርና የማገዝ፣
2. በፕሬዚዳንቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፤
3. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ በፕሬዚዳንቱ ውክልና የተሰጠው ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሬዚዳንቱን ወክሎ የመሥራት።

17.<u>የጉባኤው አባላት</u>

ጉባኤው፦

1. በፕሬዚዳንቱ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ በፕሬዚዳንቱ የሚመደቡ አባላት ይኖሩታል፤
2. ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል።

18.<u>የጉባኤው ተግባርና ሃላፊነት</u>

በቦርዱ የሚሰጡት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባኤው የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮችን በሚመለከት የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአካዳሚውን የትምህርትና የሥልጠና ጊዜ ይወስናል፤
2. የአካዳሚውን የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችንና ሥርዓተ ትምህርት ይወስናል፣ የትምህርትና የሥልጠና ዘርፎች የሚያካሂዱቸውን የጥናትና ምርምር ሥራዎች ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ ያደርጋል፤ አቅጣጫ ያስይዛል፤
3. የሠልጣኞችን አቀባበል፣ የትምህርትና ሥልጠና ደረጃ አወሳሰንን እና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል፣
4. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ፣ የባችለር ዲግሪ፣ የማስተርስ ዲግሪ ወይም የዶክትሬት (ፒ.ኤች.ዲ) ወይም ተመሣሣይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ የሚሰጥበትን አግባብ ይወስናል፤
5. የአካዳሚውን ልዩ ልዩ የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን ያጸድቃል፤
6. በአካዳሚው የሚሰጠውን የትምህርትና የሥልጠና አግባብነትና ጥራት ማረጋገጫና የሠልጣኞች ምዘና ሥርዓትን ያወጣል፣ አጠቃላይ የመውጫ ፈተና አሰጣጥንና ደረጃዎችን ይወስናል፤
7. በቦርዱ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ የሰልጣኞች አስተዳደር፣ የአካዳሚው የትምህርትና ሥልጠና ነክ ጉዳዮች፣ የትምህርት ኃላፊዎች የምርጫ ሥነ-ሥርዓት፣ የመምህራን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲሲፕሊን፣ ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፣ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. በፕሬዚዳንቱ የሚመሩለትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

19.<u>**የጉባኤው ስብሰባዎች**</u>

1. ጉባኤው ለሥራው በሚያስፈልግ መጠን በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የጉባኤው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

20.<u>**የአካዳሚው ሌሎች ዘርፎች**</u>

በዚህ ደንብ በአንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተመለከቱት አካላት እንደተጠበቁ ሆነው የአካዳሚው ልዩ ልዩ የትምህርትና ሥልጠናን የምርምርና ስርፀት እና ሌሎች ዘርፎች አመሰራረትና አሠራር በቦርዱ ይወሰናል።

21.<u>በጀት</u>

የአካዳሚው በጀት፦

1. በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤
2. ከሚሰጠው አገልግሎት ከሚሰበሰብ ክፍያ፤
3. ከውርስ፣ ከስጦታ እና ዕርዳታ፤ እና
4. ከሌሎች የገቢ ምንጮች፣ የተውጣጣ ይሆናል።

22.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. አካዳሚው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የአካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

23.<u>መመሪያ የማውጣት</u>

1. ይህንን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም ቦርዱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።
2. አካዳሚው ይህን ደንብና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

24.<u>ደንቡ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ ከዛሬ ነሐሴ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

ኸ/ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 291/2005

## የኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤትደንብ ቁጥር 291/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "ብዝሀ ህይወት" ማለት በየትኛውም ሥርዓተ ምህዳር ውስጥ በሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች መካከል የሚገኝ ተለያይነት እና ከሚገኙበት ሥነ-ምህዳር ጋር ያላቸውን መስተጋብር ሲሆን ይህም በዝርያዎች ውስጥ፣ በዝርያዎች እና በሥርዓተ ምህዳሮች መካከል የሚገኝ ተለያይነትን ይጨምራል፤
   2. "የብዝሀ ህይወት ናሙና" ማለት የዕጽዋት፣ የእንስሳት ወይም ደቂቅ አካላት ዘረመል ወይም ዝርያ ናሙና ሲሆን ልውጥ ህያዋንን አይጨምርም፤

3. “ሥርዓተ ምህዳር” ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ ውስጥ የዕጽዋትና እንስሳትና ደቂቅ አካላት ስብስብ ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች ጋር በመስተጋብር ያለመቋረጥ በሚሠራ ዝግመተ-ለውጥ ውስጥ የሚኖሩበት ሥርዓት ነው፤
4. “ኢዘቦታ ጥበቃ” ማለት የዕጽዋት፣ እንስሳትና ደቂቅ አካላትን በራሂ ወይም ዝርያዎች ከተፈጥሮ የመኖሪያ አካባቢያቸው ውጭ መጠበቅ ነው፤
5. “በራሂ” ማለት ህይወት ባለው ነገር ውስጥ የሚገኝ ተወራራሽ ባህሪን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍና ባህሪን የሚወስን ሞሊኩል ነው፤
6. “ዘቦታ ጥበቃ” ማለት ሥነ ምህዳሮችንና ህይወት ያላቸው ነገሮችን የተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢዎችን መጠበቅ እና ዝርያዎችን በተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው ማቆየትና ብዛታቸው ዘላቂ ወደ ሆነ መጠን እንዲያንሰራራ ማድረግ ሲሆን የቤት እንስሳት ወይም የሰብል ዝርያዎችን በሚመለከት ልዩ ባህሪያቸውን ያገኙበት አካባቢ ነው፤
7. “ዘለቄታዊ አጠቃቀም” ማለት ወደፊት የተለያይነት ማሽቆልቆልን በማያስከትል ሁኔታና መጠን ብዝሀ ህይወትን መጠቀም ነው፤
8. “አርክቦት” እና “የማህበረሰብ ዕውቀት” የሚሉት በጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር 482/1998 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤
9. “የአርክቦት ውል” የሚለው ሃረግ በጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 169/2001 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤
10. “ሚኒስቴር” ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው[74]፤
11. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
12. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት አካል ሆኖ

[74]በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(18) መሰረት የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፤

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የአገሪቱ ብዝሀ ህይወት ሀብትና ተያያዥ የማህበረሰቦች ዕውቀት በአግባቡ መጠበቃቸውንና በዘላቂነት ጥቅም ላይ መዋላቸውን እንዲሁም እነዚህን በመጠቀም ከሚገኘው ጥቅም አገሪቷና ማህበረሰብና ፍትሀዊና ሚዛናዊ ድርሻ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይሆናል።

6. **ስልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እና ፍትሀዊና ሚዛናዊ ጥቅም ተጋሪነትን የሚመለከቱ የፖሊሲና የህግ ሀሳቦችን ማመንጨትና ሲፈቀዱም ሥራ ላይ ማዎልና መዋላቸውን መከታተል፤
2. በአገሪቷ የሚገኘውን የዕጽዋት፣ የእንስሳትና ደቂቅ አካላት፣ ተለያይነትና ስርጭት በመቃኘትና በማሰስ የአገሪቷን ብዝሀ ህይወት ሀብት መጠንና ባሀሪያት መለየትና መገምገም እንዲሁም የሚገኙበትን ሁኔታ በየጊዜው መከታተል፤
3. የብዝሀ ህይወት ጥበቃን፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲሁም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ ምርምሮችን ማካሄድ፤ እንዲሁም በብዝሀ ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽኖ የሚያደርሱ ሂደቶችንና የእንቅስቃሴ ዓይነቶችን በመለየት የሚያደርሱትን ተጽኖ በየጊዜው መከታተል እና የማንበሪያና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልቶችን መወሰን፤
4. በኢዘቦታ መጠበቅ የሚገባቸውን ነባርና የተሻሻሉ ዝርያዎች ናሙና በመሰብሰብ በኢዘቦታ ማንበር፣ ባህሪያቸውን መተንተን መገምገም እና ለቀጣይ ምርምርና ልማት የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

5. የአገሪቱን ቁልፍ የብዝሀ ህይወት ቦታዎች በመቃኘት በማሰስና በማጥናት ሥርዓተ ምህዳርን መሠረት ያደረገ የአጠባበቅ ዘዴን በመከተል በዘቦታ መጠበቅ ወይም የሚጠበቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
6. ብዝሀ ሀይወት የተመናመነባቸው አካባቢዎችን በማጥናትና በመለየት በኢዘቦታ ተጠብቀው ከሚገኙት የጀነቲክ ሀብቶች በመጠቀም ተመልሰው እንዲተኩ ማድረግ ወይም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
7. የአገሪቷ ማህበረሰቦች እያካሄዱ ያሉትን ጠቃሚ ልማዳዊ የዝርያዎች አጠቃቀም፣ጥበቃና ልውውጥ ሥርዓትን በማበረታታት፣ የተለያዩ የብዝሀ ህይወት ዝርያዎችን እንደአስፈላጊነቱ ከውጭ አገር በማስሞጣትና ቀደም ሲል ከአገር የወጡትን ዝርያዎች በማስመለስ የአገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብት ማበልጸግ፤
8. አገሪቷ ለተቀበለቻቸው ብዝሀ ህይወትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተጠሪ በመሆን ከክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
9. የብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እና አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን በሚመለከት የክልሎችንና ባለድርሻ አካላትን አቅም ለመገንባት የሚውሉ መመሪያዎችና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ መስጠት፣ ማሰልጠን እና ሌሎች አስፈላጊ ቴክኒካዊ ድጋፎችን መስጠት፣ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤
10. በአገሪቱ የሚገኙ የብዝሀ ህይወት ሀብቶችን በራሂ አሻራ በመለየት መዝግቦ እንዲጠበቁ እና በባለቤትነት እንዲታወቁ ማድረግ፤
11. በአርክቦት ህግ መሠረት የአርክቦት ውሎችን ተደራድሮ መዋዋል፣ የአርክቦት ፈቃድ መስጠት እና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤
12. አግባብ ባላቸው የአገሪቱ ህጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት አገሪቷ በብዝሀ ህይወት ሀብቷ ላይ ያላትን የሉዓላዊነትና የጥቅም ተጋሪነት መብት ለማስከበር አግባብነት ያላቸው እርምጃዎችን መውሰድ፤
13. የብዝሀ ህይወት ናሙና ከውጭ አገር ለማስመጣት የሚያስችል መመሪያ ማውጣትና የማስገቢያ ፈቃድ መስጠት፤
14. የአገሪቱ የብዝሀ ህይወት መረጃዎች የሚጠበቁበትንና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሥርዓት መዘርጋት፣

15. በህብረተሰቡ ዘንድ ስለብዝሀ ህይወት ሀብት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲሁም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ተገቢው ግንዛቤ እንዲሰርጽ ከመገናኛ ብዙሀን፣ ከትምህርት ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአህዝቦት ተግባራትን ማከናወን፤
16. የዕጽዋትና የእንሰሳት ቤተመዘክር በማደራጀት ለተመራማሪዎችና ሌሎች ተጠቃሚዎች አገልግሎት መስጠት፤
17. ከብዝሀ ህይወት ጋር የተያያዙ የአገሪቷ ማህበረሰቦች ዕውቀቶችን በመለየትና በማጥናት እንዲጠበቁ ማድረግ እንዲሁም እንዲከበሩና በሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ፍትሃዊና ሚዛናዊ ጥቅም ተጋሪነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
18. የአገሪቷ ማህበረሰቦች ዕውቀቶች ያለ ህጋዊ የአርክቦት ፈቃድ ሌላ ወገን እጅ ገብተው ጥቅም እያስገኙ ከሆነ ጉዳዩን በመከታተል የሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ከጥቅሙ ፍትሃዊና ሚዛናዊ ድርሻ እንዲያገኙ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤
19. የአገሪቱ ብዝሀ ህይወት ከውጭ በሚገቡ ልውጥ ህያዋን እና ወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይበክልና ጥፋት እንዳይደርስበት ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፤
20. የዕጽዋት አጸዶች ማቋቋምና ማስተዳደር፤
21. የብዝሀ ህይወት ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀቶች ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እና አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመተባበር መስራት፤
22. የብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ዘላቂ አጠቃቀም እና አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን በሚመለከት የማማከር አገልግሎት መስጠት፤
23. የአገሪቱ የብዝሀ ህይወት ሀብት ስለሚገኝበት ሁኔታ በየጊዜው ዘገባ እያዘጋጀ ለመንግስትና ለህዝብ እንዲደርስ ማድረግ፤
24. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሀላፊነቶቹ በከፊል ለሚመለከታቸው መንግስታዊ መሥሪያቤቶች በውክልና መስጠት፤
25. ለሚሰጠው አገልግሎት በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ፤
26. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤

27.ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

7. **የኢንስቲትዩቱ አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፦

1. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፤ እና
2. አስፈላጊው ሰራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **የዋናው ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን በሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤

   ሐ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ ኢንስቲትዩቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

   ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9. **በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ይመደባል።

10.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

11.<u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር ቁጥር 120/1990 (በአዋጅ ቁጥር ቁጥር 381/1996 እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

12.<u>ደንቡ የሚጸናበት ግዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 327/2007 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

በሀገራችን የሚካሂዱት የልማት ስራዎች ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ የደን ልማት አያያዝና አጠቃቀምን የሚያረጋግጡ በማድረግ የታቀደውን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስትራተጂ ግብን ለማሳካትና ሀገራችን ከተፈጥሮ ሀብቶቿ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ ማስቻል በማስፈለጉ፤

ለአካባቢና ለደን ምርምር ሥራዎች ትኩረት በመስጠት የሀገሪቱን ከፍተኛ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ በተቀናጀና በአንድ ወጥ የምርምር ሥርዓት ውስጥ ማደራጀት በማስፈለጉ፤

መንግሥት ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የአካባቢና ደን ሚኒስቴርን ያቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የደን ምርምርን ከአባባቢ ጥበቃ ምርምር ጋር በኢንስቲትዩት ደረጃ ማስተሳሰር በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 5 እና 45[75] መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 327/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

---

[75] የአማርኛ ቅጅ ላይ "አንቀጽ 45" የሚለው በእንግሊዝኛው ቅጅ ደግሞ "አንቀጽ 35" የሚል ሲሆን ትክክለኛው የእንግሊዘኛው ቅጇ ነው፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "የአካባቢና የደን ምርምር" ማለት በደንና ጥምር እርሻ ደን ልማት፣ አያያዝ፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና የአካባቢ ጥበቃ ላይ ምርምር ማካሔድ፣ ቴክኖሎጂዎች፣ መረጃዎችና ዕውቀቶችን ማውጣት፣ ማሰራጨት እና ማስተቀወቅ ነው፤
2. "ሥነ- ምህዳር" ማለት በአንድ በተወሰነ አካባቢ ውስጥ የዕጽዋት፣ እንስሳት እና ደቂቀ አካላት ስብስብ ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች ጋር በመስተጋብር ያለማቋረጥ በዝግመተ ለውጥ ውስጥ የሚኖሩበት ሥርዓት ነው፤
3. "አካባቢ" እና "ብክለት" የሚሉት ቃላት እንደየቅደም ተከተላቸው በአካባቢ ብከለት ቁጥጥር አዋጅ 300/1995 አንቀጽ 2 (6) እና (12) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤
4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደርንም ይጨምራል፤
5. "ማዕከል" ማለት የአካባቢና የደን ምርምር ሥራዎችን የሚያካሂድ የአካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩቱ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ነው፤
6. "ሚኒስቴር" ማለት የአካባቢና የደን ሚኒስቴርነው[76]፤
7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
8. በወንድ ፆታ የተገለፀው ማንኛውም አነጋገር ሴትንም ያካትታል።

## 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

## 4. ዋና መስሪያ ቤት

---

[76] በ22/16(2008) አ.916 አንቀፅ 9(18) መሰረት የአካባቢ፣ደን እና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

5. <u>ዓላማ</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በሀገራችን የትኩረት አቅጣጫዎች እና የተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ለደን ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ቴክኖሎጂዎችን መለየት፣ ማስገባት፣ ማላመድ፣ ጥቅም ላይ ማዋል እና ማፍለቅ፤
2. በአካባቢና ደን ምርምር ማዕከላት ወይም በውል አማካይነት የአካባቢና ደን ምርምር በሚያከናውኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች መሰል ተቋማት የሚካሄዱትን የአካባቢና ደን ምርምር ተግባራትን ማስተባበር፤
3. የአካባቢና የደን ምርምርን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና በልማት ፍላጐት ላይ ያተኮረ ለማድረግ የሚያስችል አቅም መገንባት እና ሥርዓት መዘርጋት፤
4. የአካባቢና የደን ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ።

6. <u>ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የሀገሪቱን የልማትና የምርምር ፖሊሲዎች መሰረት በማድረግ የአካባቢና የደን ጥበቃ ምርምር ስትራቴጂ የመንደፍ፣ የስራ ፕሮግራምና እቅድ የማዘጋጀት፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ የማድረግ እንዲሁም በሚመለከታቸው ክፍሎች ተግባራዊ መሆኑን የመከታተላል፤
2. ከአገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የአካባቢና የደን ምርምር ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ የሚያስችል መመሪያ የማዘጋጀት፤ እንደ አግባቡ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በጀታቸውን በመገምገም በመመሪያው መሠረት መዘጋጀታቸውን የማረጋገጥ እና ለመንግሥት አቅርቦ የማስጸደቅ፤
3. መንግሥት በሚፈቅደው በጀት መሠረት የአካባቢና የደን ምርምር ማዕከላትን፣ ላቦራቶሪዎችን እና ጣቢያዎችን የማደራጀት፣ አዳዲስ ማዕከላትንና ጣቢያዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ ክልሎች እና ስነ ምህዳሮች እንዲቋቋሙ የማድረግ ወይም የተቋቋሙት እንዲታጠፉም የማድረግ ፤

4. ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ የአካባቢና የደን ምርምር ውጤቶችን ተጠቃሚው እንዲያውቃቸው ለማድረግ አግባብ ካላቸው ኤክስቴንሽን አካላት ጋር በመተባበር የአህዝቦት ተግባር የማከናወን፤
5. በሀገሪቱ ጎልቶ የሚታየውን የአካባቢ መራቆት፣ የበረሃማነት መስፋፋት እንዲሁም የዝርያዎች መጥፋትን ለመቀነስና የደን ውጤቶች የአቅርቦት ችግርን ለመፍታት የሚያስችሉ ፈጣን እድገት ያላቸውን የዕፅዋት ዝርያዎችን የማላመድ እና የማሰራጨት፤
6. በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ምክንያት በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን የሚዛን መዛባት፣ ብክለትን እና ተዛማጅ ችግሮችን በመለየት የሚቀንሱበትን እና መልሰዉ የሚያገግሙበትን መንገድ የማመቻቸት፤
7. በሀገር ውስጥና በውጭ አገራት የተካሄዱና የሚካሄዱ ለአካባቢና ደን ምርምር የሚጠቅሙ ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማከማቸት እና የማሰራጨት፤ የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓትን የመገንባት እና የማስተባበር፤
8. ለክልል የግብርና፣ የአካባቢና የደን ምርምር ማዕከላት እና ለሌሎች ተገልጋዮች ተገቢውን የመረጃ አገልግሎት የመስጠት፤ ጥያቄም ሲቀርብ አቅም በፈቀደ መሰረት የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ፤
9. በኢንስቲትዩቱ እና በሌሎች አካላት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽና የሀብት ብክነት እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የመዘርጋት እና አፈፃፀሙንም የመከታተል፤
10. ከዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ አካባቢ እና ሀገራዊ የደን ምርምር ተቋማት እና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አካላት ጋር ግንኙነት መመሥረትና ትብብር የማድረግ፤
11. በአካባቢና የደን ምርምር ላይ የተሰማራን ማንኛውም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን የመያዝ፣
12. በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት ከአገልግሎት ተቀባዮች የአገልግሎት ክፍያ የመሰብሰብ፤
13. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

14. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

7. **<u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>**

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
2. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

8. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኢንስቲዩቱን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት፣ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈፀም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች መንግስት ለግብርና ተመራማሪዎች ባጸደቀው መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኢንስቲትዩትን ስትራተጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9. **በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

10. **የሂሳብ መዛግብት**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲትዩቱ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

11. **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 79/7989 (በአዋጅ ቁጥር 382/1996 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 16 መሠረት ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት የተላለፉ የደን ምርምር እና የደን ዉጤቶች አጠቃቀም ምርምር ተቋማት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

12. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 17 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

# አዋጅ ቁጥር 575/2000 ዓ.ም

## የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ዓይነት የተፈጥሮ ውበት ያላቸው ብርቅዬ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ባለቤት በመሆኗና ይህም ሀብቷ በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ ሚና ያለው ሆኖ ለቱሪዝም፣ ለትምህርትና ለሳይንስ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ፣

ይህ ሀብት በተገቢው መንገድ እንዲጠበቅና እንዲለማ በማድረግ ቀጣይነት ያለው ጥቅም ለመስጠት እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መንግሥት በአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት ላይ እተባባሰ የመጣውን የእልቂት አደጋ ለመግታትና ከሀብቱ አገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች እንድታገኝ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና አሁን ካለው ዓለም አቀፍ የዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ ልማትና አጠቃቀም አኳያ ንዑስ ዘርፉን ማጠናከር በማስፈለጉ፤

በአገሪቱ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ትኩረት ሰጥቶ ለመንቀሳቀስና ከመስኩ የሚገኘውን ጥቅም ለማጎልበት በፌዴራል ደረጃ ይህን የሚያስፈጽም አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 575/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "የዱር እንስሳት አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፣

2. “የዱር እንስሳት”፣ “የዱር እንስሳት ሀብት”፣ “የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ” እና “የዱር እንስሳት ውጤት” በዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ 2 ሥር የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፣
3. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ “ባለሥልጣን” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ጽሕፈት ቤቶች በሌሎች ሥፍራዎች ይኖሩታል።

5. <u>ዓላማ</u>

የባለሥልጣኑ ዓላማ የአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲለማ፤ እንዲጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ይሆናል።

6. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የዱር እንስሳት ሀብት ልማትን፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን በተመለከተ የፖሊሲና የሕግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀዱም በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
2. በሥሩ የተቀቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላል፣
3. በውጭ ቱሪስቶች ለሚካሄድ አደን ፈቃድ ይሰጣል፣
4. ሆቴል፣ ካምፕ፣ ሎጅና ሌሎች አገልግሎቶች በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ እንዲቋቋሙ ፈቃድ ይሰጣል፣
5. ማናቸውንም የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድና የጤና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

6. የዱር እንስሳት ውጤት በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ ለተመለከተው ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ ውጤቱንም ይለካል፤
7. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እንዲመዘገቡ ለማስቻል ዓለም አቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ እነዚህኑ መስፈርቶች ጠብቀው መተዳደራቸውን ይከታተላል፣
8. ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ ዕርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ወገኖች ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመሰርታል፤
9. የዱር እንስሳት ሀብትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤ ለሚመለከታቸው ዓለም ዓቀፍ ተቋማትም በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጀ ያስተላልፋል።
10. የዱር እንስሳትን በተመለከተ በማናቸውም ዓለም አቀፍ ስብሰባ ወይም ጉባዔ መንግሥትን ይወክላል፣
11. የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና የሥልጠና ፕሮግራም ያካሄዳል፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ያሰባስባለ፣ ያቀነባብራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
12. ለክልሎች በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ረገድ አስፈላጊውን እገዛ ይሰጣል፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት በውክልና ይሰጣል፣
13. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፤
14. ከፌዴራል መንግሥት ጋር በተገባ የኮንሴሽን ውል መሠረት በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራል፤
15. በመንግሥት በጸደቀ ተመን መሰረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፤
16. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል. ይከሰሳል፤
17. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

7. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፣

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

8. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከተውን የባለ ሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፣
   ለ/ በፌደራል ሰቪል ሰርቪስ ሕግ መሰረት የበለስልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥረል፣ ያስተዳደራል፤
   ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፤ ሰፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣
   መ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   ሠ/ ባለ ሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤
   ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተ ላልፍ ይችላል።

9. **<u>በጀት</u>**

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

10. **<u>የሂሣብ መዛግብት</u>**

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የባለስልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገነዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰየማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፤

11. **<u>የተሻሻሉና የተሻሩ ህጎች</u>**

1. የዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (17) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (17) ተተክቷል፤

"17/ "ባለሰልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው"

2. በዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) እና አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ "ሚኒስቴሩ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር" በሚለው ተተክቷል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተጠቀሱትን በስተቀር በዱር እንስሳት አዋጅ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "ሚኒስቴሩ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ባለሥልጣኑ" በሚለው ተተክቷል።
4. የዱር እንስሳት አዋጅ አንቀጽ 13 ተሰርዞ አንቀጽ 14፣15፣16፣17፣18፣19 እና 20 እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 14፣15፣16፣17፣18 እና 19 ሆነዋል።

12.<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የዱር እንስሳት የሥራ ዘርፍን የሚመለከቱ የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

13.<u>አዋጁ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 411/2009

## የብሔራዊ ደህንነት ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀፅ 5 እና የደህንነት ሕይወት አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 22 መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የብሔራዊ ደህንነት ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 411/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፤

   1. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
   2. "አዋጅ" ማለት የደህንነት ሕይወት አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለ) ነው፤
   3. በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## የብሔራዊ ደህንነት ህይወት አማካሪ ኮሚቴ

3. **መቋቋም**

   1. የብሔራዊ ደህንነት ህይወት አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ በዚህ ደንብ ውስጥ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የኮሚቴው ተጠሪነት ለሚኒስትሩ ይሆናል።

4. **ዓላማ**

   የኮሚቴው ዓላማ ደህንነተ ህይወትን በሚመለከት መንግስትን ማማከር ነው።

5. **የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት**

ኮሚቴው፦

1. በልውጠ ህያዋን እንቅስቃሴ፣
2. በደህንነተ ህይወት ጉዳዮች የሚወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች፣
3. በልውጠ ህያዋን እንቅስቃሴ በተመለከተ ለማህበረሰብ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያግዙ ውጤታማ ዘዴዎች መለየት እና
4. በማናቸውም የደህንነተ ህይወት ጉዳዮች ላይ ከሚኒስትሩ በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በሚኒስትሩ በኩል በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት መንግስትን የማማከር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

## 6. <u>የኮሚቴ አባላት</u>

1. የኮሚቴው አባላት ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል።
2. የኮሚቴው አባላት አግባብነት ያለው ሙያዊ ክህሎትና ልምድን እንዲሁም ተቋማዊ አግባብነት ያለው ውክልናን መሠረት በማድረግ ከመንግሥታዊ አካላት እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ብዙሃን ማህበራትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተውጣጡ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚቋቋመው ኮሚቴ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የሚከተሉትን የሙያ ስብጥሮች የሚያካተት ይሆናል፦

   ሀ) ባዮቴክኖሎጂ፤

   ለ) በዘረመል ምህንድስና፣

   ሐ) የብዝሃ ህይወት፣

   መ) የተፈጥሮ ሳይንስ፣

   ሠ) የአካባቢ ሳይንስ፣

   ረ) የህክምና ወይም የጤና ሳይንስ

   ሰ) የምግብ ሳይንስ

   ሸ) የእንስሳት ሳይንስ

   ቀ) በማኅበራዊ ሳይንስ እና

   በ) እንደ አስፈላጊነቱ አግባብ ያለውን ሌላ ሙያ ዘርፍ።

## 7. <u>የኮሚቴው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

የኮሚቴው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ኮሚቴውን ይሰበስባል፣ ሥራዎች ይመራል፤
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን ኃላፊነትና ተግባራት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
3. መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል።

8. **<u>ስለኮሚቴው ስብሰባ</u>**

1. ኮሚቴው ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ በሰብሳቢው ጥሪ ኮሚቴው በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።
3. ከኮሚቴው አባላት ከሁለት ሦስተኛው በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
4. የኮሚቴው ምክረ ሀሳብ በስምምነት የሚተላለፍ ይሆናል፤ ልዩነት በሚፈጠር ወቅት አብላጫው ምክረ ሀሳብ እና የልዩነት ሀሳቦች ተካተው ለሚኒስትሩ ይቀርባሉ።

9. **<u>የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን</u>**

1. የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለሶስት ዓመት ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስትሩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር የኮሚቴ አባል በድጋሚ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን እንዲሰየም ማድረግ ይችላል።

10. **<u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>**

1. በኮሚቴው በይፋ እንዳይወጣ የተወሰነን መረጃ የኮሚቴው አባላት ሚስጢራዊነቱን መጠበቅ አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የተላለፈ የኮሚቴ አባል አግባብነት ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የብሔራዊ ደህንነት ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት</u>

11. **<u>ጽሕፈት ቤት</u>**

የብሔራዊ ደህንነት ሕይወት አማካሪ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት በሚኒስቴሩ ስር የሚደራጅ ይሆናል።

12.**<u>የጽሕፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ጽሕፈት ቤቱ:-

1. ማንኛውንም የደህንት ህይወት ጥያቄ በማደራጀት ለኮሚቴው ያቀርባል፤
2. የኮሚቴውን ምክረ ሀሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤
3. የኮሚቴውን የክንውን ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚኒሰትሩ ያቀርባል፤
4. የኮሚቴውን ምክረ ሀሳብ እና ሌሎች ሰነዶችን በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል።

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

13.**<u>መመሪያ ስለማውጣት</u>**

ይህን ደንብ ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

14.**<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 9 ቀን 2110 ዓ.ም**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አ/ ለስፖርት ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 249/2003

## የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 34 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፣

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 249/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ኮሚሽን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 692/2003 የተቋቋመዉ የስፖርት ኮሚሽን ነው።[77]
   2. "የአካዳሚክ ሠራትኛ" ማለት በማስተማር፤ በማሰልጠን እና/ወይም በምርምር ሥራ የተሰማራ ሠራተኛ ነው፤
   3. "የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ" ማለት የአስተዳደር፣ የቢዝነስ አመራር፣ የፋይናንስና የሂሳብ ሥራ፣ የአገልግሎቶች አቅርቦት፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናውን የአካዳሚው ሠራተኛ ነው፤
   4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
   5. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
   6. ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

[77] በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 40(1)(ለ) አዋጁ ተሽሮ የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የተላለፈ በመሆኑ "ኮሚሽኑ" የሚለው "ሚኒስቴሩ" በሚል ይነበብ፡፡

1. የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ (ከዚህ በኋላ “አካዳሚው” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. አካዳሚው ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ይሆናል ።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የአካዳሚዉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ሥፍራ የማሠልጠኛ ማዕከሎች ሊኖሩት ይችላል።

5. **ዓላማዎች**

አካዳሚው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ለሀገር አቀፍና ለዓለም አቀፍ ውድድሮች በአካልና በአእምሮ ከፍተኛ ብቃት ያላቸዉንና ሥነምግባራቸውን የጠበቁ ምርጥ ወጣት ስፖርተኞች ማፍራት፤
2. በተለያዩ የስፖርት መስኮች ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
3. ለስፖርቱ ጥራት አስተዋፆ ሊያደርጉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ላይ ማካሄድና የተገኙ ውጤቶችን ማሰራጨት፤
4. በሀገር ደረጃ ለተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች የእውቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል።

6. **የአካዳሚው ስልጣንና ተግባር**

አካዳሚው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የስፖርት ዘርፍ የሙያ ደረጃዎችና ስልጠና ሥርዓተ ትምህርት የማዘጋጀትና በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና ሲያገኝ ተግባራዊ የማድረግ፤
2. የክልሎችን፣ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴንና የብሔራዊ የስፖርት ፌዴሬሽኖችን ፍላጎት እና ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሰልጣኞችን ምልመላ፣ ቅበላና ስልጠና የማካሄድ፤
3. ከክልሎች ታዳጊ ሕፃናትን በመመልመል፣ በመቀበልና በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች በማሰልጠን ለሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ውድድሮች በአካላዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ ስብዕናቸው ከፍተኛ ብቃትና ተወዳዳሪነት ያላቸውን ምርጥ ወጣት ስፖርተኞች የማፍራትና ስልጠናውን በሚገባ ላጠናቀቁ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤
4. ሠልጣኞች ከስፖርት ስልጠና ጎን ለጎን መደበኛ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፤

5. ሠልጣኞች በሀገሪቱ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት እንዲሁም የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በተለያዩ መንገዶች እንዲሳተፉ የማስቻል፤
6. በሚዘጋጁት የሙያ ደረጃዎች መሰረት በስፖርት አሰልጣኝነት፣ በስፖርት አስተዳደር፣ በስፖርት ሕክምና፣ በስፖርት ሕግና በመሳሰሉት ስፖርት ነክ መስኮች ለባለሙያዎች የአጭር ጊዜና ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን የመስጠትና የብቃት ምዘና ፈተናውን ለሚያልፉ ሰልጣኞች የምስክር ወረቀትና ዲፕሎማ የመስጠት፤
7. በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ምርምር የማካሄድ፤
8. በክፍያ ወይም ያለ ክፍያ የማማከርና የስልጠና አገልግሎት የመስጠት፤
9. ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የስፖርት ሥልጠናና የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት የመመስረት፤
10. የንብረት ባለቤት የመሆን ፣ ውል የመዋዋል ፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤
11. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

7. <u>**የአካዳሚው አቋም**</u>

አካዳሚው ፦

1. የአስተዳደር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ ቦርድ ” እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3. አስፈላጊዉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. <u>**የቦርዱ አባላት**</u>

1. ቦርዱ ሰብሳቢዉን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸዉም እንደ አስፈሳጊነቱ ይወሰናል።
2. የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር ድምፅ የማይሰጥ ሆኖ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

9. <u>**የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአካዳሚዉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤
2. የአካዳሚውን የአሰራር መመሪያዎች ያፀድቃል፤

3. የአካዳሚውን ልዩ ልዩ የአካዳሚክና የምርምር ክፍሎች አመሰራረትና አሰራር እንዲሁም የአስፈጻሚ አካላቱን ምደባ ያፀድቃል፤
4. የትምህርትና ስልጠና ፣ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች የአካዳሚውን ተልዕኮና ዓላማ መሠረት ያደረጉና የዘርፉን ፍላጎት ለማሳካት የሚረዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
5. የአካዳሚውን ሰልጣኞች የቅበላ መስፈርት የትምህርት ሚኒስቴርን በማማከር ይወስናል፤ በሥራ ላይ እንዲውል መደረጉንም ያረጋግጣል፤
6. አካዳሚው የሚያስከፍላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች እና ያለክፍያ የሚሰጡት አገልግሎቶች በመንግሥት እንዲወሰኑ ለኮሚሽኑ ሃሳብ ያቀርባል፤
7. አካዳሚው ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል፤
8. የአካዳሚውን አርማ ያፀድቃል፤
9. በአካዳሚው አካላት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ እቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤
10. የአካዳሚው የሥራ ዕቅድና በጀት ለኮሚሽኑ ከመቅረበቸው በፊት ይመረምራል፤
11. ለኮሚሽኑ የሚቀርቡትን የአካዳሚውን ዓመታዊ የሥራ አፈዓፀምና ሪፖርቶች ያፀድቃል፤
12. የአካዳሚውን የኦዲት ሪፖርት በመመርመር በሪፖርቱ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል።

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቦርድ አባላት በማንኛዉም ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የአካዳሚው ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአካዳሚውን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የአካዳሚውን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ የአካዳሚውን የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የአካዳሚክ ሠራተኞችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የአካዳሚውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተመከረበት በኋላ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ/ ለአካዳሚው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤
   ሠ/ የአካዳሚዉን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተመከረበት በኋላ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤
   ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ አካዳሚውን ይወክላል፤
   ሰ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለአካዳሚው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአካዳሚው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12. <u>በጀት</u>

የአካዳሚዉ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. አካዳሚው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የአካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

14. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

ጥሩነሽ ዲባባ ብሔራዊ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል በመባል የሚታወቀው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለአካዳሚው ተላልፈዋል ።

15. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 18 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 400/2009**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባካሄደው አራተኛ ልዩ ስብሰባ ስፖርትን በተመለከተ የወጣውን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ዓለም አቀፍ ስምምነትን በአዋጅ ቁጥር 554/1999 ያፀደቀው በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 39 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 400/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አባሪ 1 የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "የአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ" ማለት ማንኛውንም በስፖርቱ ውስጥ ያለን አትሌት የሚረዳ ወይም አብሮ የሚሰራ አሰልጣኝ፣ አለማማጅ፣ ማናጀር፣ ወኪል፣ የቡድን ሠራተኞች፣ ኃላፊዎች፣ የህክምና ሠራተኞች፣ ወጌሻዎች፣ ወላጆች ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ነው፤
   2. "ዶፒንግ" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ በአለም አቀፉ የፀረ-ዶፒንግ ሕግ ከአንቀጽ 2.1 እስከ 2.10 የተዘረዘሩት የፀረ-ዶፒንግ ሕግ መጣስ ክስተት ነው፤
   3. "የአበረታች ቅመሞች ቁጥጥር" ማለት ከምርመራ ውጤት ሥርጭት ዕቅድ እስከ ይግባኝ ሰምቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚወሰንበት ያሉትን ሁሉንም ደረጃዎችና ሂደቶች አካቶ የአድራሻ መረጃዎችን መሰብሰብን፣ ለምርመራ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውም ናሙና መውሰድንና ማከማቸትን፣ የላቦራቶሪ ምርመራን፣ በህክምና

ምክንያት የሚፈቀዱ መድኃኒቶችን ማጣራትንና መፍቀድን፣ እስከ ውጤት አያያዝ እና መስማት ድረስ ያለውን አጠቃላይ ሂደት እና ደረጃዎች የሚያጠቃልል ነው፤

4. "ፌዴሬሽን" ማለት በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጠውና ከዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የስፖርት አሶሲየሽን፣ የስፖርት ፌዴሬሽን እና የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴን የሚያካትት የስፖርት ማህበር ነው፤
5. "ፈቃድ" ማለት ለፕሮፌሽናል የስፖርት አካል፣ ለአሰልጣኝ፣ ለወኪል፣ ወይም ለስፖርት ሙያተኛ አስፈላጊውን የስፖርት ተግባር ለማከናወን እንዲችል ተብሎ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
6. "ሚኒስቴር" ማለት የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ነው፤
7. "ብሔራዊ የኦሎምፒክ ኮሚቴ" ማለት በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጠውና ከዓለም አቀፉ የኦሎምፒክ ኮሚቴ ጋር ግንኙነት ያለው የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ነው፤
8. "ጽሕፈት ቤት" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት ነው፤
9. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
10. "እውቅና የተሰጠው የስፖርት ድርጅት" ማለት ስፖርትን ለማሳደግ በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ነው፤
11. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) ላይ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ያጠቃልላል፤
12. "አህጉራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ድርጅት" ማለት በአባል አገራት አማካይነት የተቋቋመ የፀረ-አበረታች ቅመሞች የሕግ ማዕቀፎች የአባል አገራት ሕግ አካል እንዲሆኑ እና እንዲተገበሩ የማድረግ፣ የማቀድና ናሙና የመሰብሰብን፣ የናሙና ውጤት አያያዝን፣ በህክምና ምክንያት የሚፈቀዱ መድኃኒቶች አሰራር ክለሳን፣ የችሎት አሰያየምን እና በአህጉር ደረጃ የትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን ጨምሮ

እነሱ በሚወክሏቸው አካባቢዎች ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን የሚመራና የሚያስተባብር ድርጅት ነው፤

13.“የምዝገባ ምስክር ወረቀት” ማለት አስፈላጊውን የስፖርት እንቅስቃሴ ለመምራትና ለማስተዳደር ለስፖርት አካል የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ነው፤

14.“የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ስምምነት” ማለት ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገው 33ኛው የድርጅቱ ስብሰባ ላይ የፀደቀው የፀረ-አበረታች ቅመሞች ስምምነት ሲሆን፣ የስምምነቱ ፈራሚ አገራት በስፖርት ላይ የፀረ-አበረታች ቅመሞች አቋምን በመውሰድ በስምምነታቸው ላይ ያደረጓቸውን ማናቸውንም ማሻሻያዎች የሚያጠቃልል ነው፤

15.“የዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ” ማለት በዓለም ዙሪያ ከዶፒንግ ነጻ የሆነ የስፖርት እንቅስቃሴን ለማስተባበር የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

16.“የዓለም አቀፍ የፀረ- አበረታች ቅመሞች ሕግ” ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን የስፖርት ፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴን ለማቀናጀት በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ የተዘጋጀ ሕግ ነው፤

17.በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት ስለመቋቋም

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ “ጽሕፈት ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ሆኖ የፋይናንስ፣ አስተዳደራዊ እና ሌሎች የየዕለት ተግባራትን ራሱን ችሎ ያከናውናል።
3. ጽሕፈት ቤቱ ከማንኛውም መንግስታዊ አካል እና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ ይሰራል።

### 4. ዋና መስሪያ ቤት

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።

### 5. ዓላማ

በአገር አቀፍ ደረጃ ዶፒንግን በመከላከልና በመቆጣጠር ንፁህ ስፖርት እንዲስፋፋና ውጤታማ አትሌቶች እንዲፈሩ ለማድረግ ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩል፦

1. የተለያዩ የትምህርት፣ የሥልጠና እና የሕዝብ ንቅናቄ ተግባራትን በማከናወን በዶፒንግ ዙሪያ በሕዝቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል፤
2. በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ወይም በሚኖር የውጭ አገር ዜግነት ያለው አትሌት ላይ በየጊዜው የተለያዩ ምርመራዎችን በማካሄድ እና የኢንተለጀንስ ተግባራትን በማከናወን አበረታች ቅመሞችን ተጠቅመው በሚገኙበት ወቅት ክስ በማቅረብ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
3. የዚህ ደንብ አንቀጽ 6(27) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገር አቀፍ ደረጃ የስፖርት ማህበራትን፣ ክልሎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በመደገፍ የፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴን ያስተባብራል።

6. <u>**የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**</u>

ጽሕፈት ቤቱ በአለም አቀፉ የፀረ- አበረታች ቅመሞች ህግ እና አለም አቀፍ መስፈርት መሰረት በስፖርቱ ውስጥ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ በቀጥታ ተፈፃሚ የሚሆኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕጉን ጨምሮ ከዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ሕጎችና ደንቦች ጋር የተጣጣመ እና በየደረጃው ዶፒንግን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ብሔራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ፖሊሲ እና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
2. በየደረጃው ህብረተሰቡንና በተለይም ደግሞ የስፖርቱን ማህበረሰብ በዶፒንግ እና በስፖርቱ ውስጥ በሚያስከትላቸው ጉዳቶች ዙሪያ ለማስተማር የሚያስችሉ የተለያዩ የሥልጠናና የግንዛቤ መፍጠሪያ ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤ ተግባራዊ ያደረጋል፤
3. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በየጊዜው ማሻሻያ ተደርጎባቸው የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
4. አትሌቶች ላይ የዶፒንግ ምርመራዎችን ያካሂዳል፤

5. የዶፒንግ ሕግን በሚጥሱ አትሌቶች እና የአትሌት ደጋፊ ሠራተኞች ላይ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ 2 ፣ 10 እና 23.2.2 መሠረት ቅጣት ይጥላል፤
6. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ እና በየጊዜው በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በሚወጡ እና ማሻሻያ በሚደረግባቸው የተለያዩ መመሪያዎች እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች መሠረት ለአትሌቶች፣ ለአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዲሁም ለዶፒንግ ቁጥጥር ባለሞያዎች ከናሙና አሰባሰብ ሂደት እና ምርመራ ጋር በተያያዘ ተከታታይ መረጃ ይሰጣል፤
7. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ 14.4 መሠረት የመንግሥትንና የዓለም አቀፉን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ግዴታዎችን ለማሟላት ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በየዓመቱ መረጃዎችን ይሰጣል፤
8. የስፖርተኞች ጤና እና ደህንነት በአግባቡ እንዲጠበቅ ለማድረግ በውድድርና መዝናኛ ስፖርቶች ላይ ከተከለከሉና በሰው ሰራሽ መንገድ የአካል ብቃትን ለማሻሻል ከሚዘጋጁና ከተከለከሉ የዶፒንግ ዘዴዎች የፀዳ ፍትኃዊ የውድድርና ተሳትፎ ሥርዓት እንዲኖር ያበረታታል፤
9. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ 2 መሠረት የአበረታች ቅመሞች የሕግ ጥሰት እንዳይፈፀም ይከላከላል፤
10. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕጎችና በኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ መሠረት የአበረታች ቅመሞች የሕግ ጥሰቶች ጉዳይን የሚመለከት የውጤት አስተዳደር ኮሚቴ ያቋቁማል፤
11. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጤት አስተዳደር ኮሚቴው በኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ መሰረት ዶፒንግን በሚመለከቱ ጥፋቶች ዙሪያ የዲስፕሊን እርምጃዎችን ለመውሰድ የመጀመሪያ ደረጃ ውሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ እንዲሰራ ያደርጋል፤
12. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ 4.4 መሠረት የተደነገገው የሥልጣን ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የተከለከሉ አበረታች ቅመሞች ለህክምና አገልግሎት እንዲውሉ ለማድረግ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ገምግሞ የሚወስን የህክምና ንዑስ ኮሚቴ ያቋቁማል፣

13. በስፖርት ውስጥ የሚፈጸሙ ከዶፒንግ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ምርመራ ያደርጋል፤
14. ከአህጉር እና ከዓለም አቀፍ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፤
15. የዓለም አቀፉን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ፣ ሌሎች ስምምነቶች እና የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት የፀረ-አበረታች ቅመሞች ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ያደረጋል፤ የዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ዶፒንግን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
16. የዓለም አቀፉን የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ ጥሰው ከተገኙ እና የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈባቸው ማናቸውም ግለሰቦች እና ድርጅቶች በተገኙና ለአትሌቶች፣ ለፌዴሬሽኖች እና ለስፖርት ድርጅቶች በሚሰጡ የተወሰኑ ወይም ሁሉም የገንዘብ እና ከስፖርት ጋር የሚዛመዱ ድጋፎች ላይ እገዳ ይጥላል፤
17. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ መሠረት የዶፒንግ ጥሰት በመፈጸማቸው ምክንያት በአትሌቶች እና በአትሌት ደጋፊ ሠራተኞች ላይ የተጣለ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የሰው ኃይል እና ከስፖርት ጋር የሚዛመዱ ቅጣቶች በመንግሥትና በሕዝባዊ ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤ በዓለም አቀፍ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ 10 እና 23.2.2 በግልጽ የተዘረዘሩ ውጤቶችንም ይተገብራል፤
18. ሁሉም የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ሌሎችም አካላት ዶፒንግን ከአገሪቱ ለማስወገድ ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች ለጽሕፈት ቤቱ እንዲሰጡ ያበረታታል፤ ይደግፋል፤
19. በስፖርት ዶፒንግ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ጥናትና ምርምር እንዲደረግም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
20. የፀረ-አበረታች ቅመሞች አስተዳደር እና ሥራ አመራር ሥርዓትን ተግባራዊ ያደርጋል፤

21. በፀረ-አበረታች ቅመሞች በሕጉ መሠረት አድራሻ ይመዘግባል፤ የተመዘገበው የምርመራ ማህደርም በፀረ-አበረታች ቅመሞች አስተዳደርና ሥራ አመራር ሥርዓት ውስጥ እንዲያዝ ያደርጋል፤
22. ጽሕፈት ቤቱ ባወጣው የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ መሠረት የአትሌቶችንና የሌሎች አካላትን የግል መብት ይጠብቃል፤
23. የተከለከሉ አበረታች ቅመሞችን ዝርዝር በተመለከተ በየጊዜው በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ አማካይነት የሚደረገውን ማሻሻያ ወዲያውኑ በመቀበል ተፈፃሚ ያደርጋል፤
24. በአገር አቀፍ ደረጃ በየእርከኑ የሚካሄደውን የፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴ ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለሚታዘቡ ታዛቢዎች ተገቢውን እውቅና ይሰጣል፤
25. በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ አንቀጽ 6.1 መሠረት የናሙና ትንተና ሲካሄድ በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እውቅና ከተሰጣቸው የምርመራ ላብራቶሪዎች መካከል ይመርጣል፤
26. ከዶፒንግ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ የሚያስፈልግ ማንኛውም ማስረጃ እንዲቀርብለት መጥሪያ መላክ፣ ምርመራ ማድረግ ወይም ማዘዝ ይችላል፤
27. በኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነ ዶፒንግን የመመርመር እና የመቆጣጠር ሥልጣኑን ተግባራዊ ያደርጋል፤
28. ሥራዎችን በተገቢው መንገድ በማከናወን ዓላማውን ለማስፈፀም ውል ይዋዋላል፤ የንብረት ባለቤትና ባለይዞታ ይሆናል፤ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
29. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (28) የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራትን በዓለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ በልዩ ሁኔታ ለዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች እና ዋና ዋና የስፖርት ኩነት የሚያዘጋጁ አካላት ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ጋር ተጣጥመው እንዲፈፀሙ ያደርጋል።

7. <u>**የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀት**</u>

ጽሕፈት ቤቱ፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) ፤
2. በመንግስት የሚሰየም ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣
3. አስፈላጊ ሠራተኞች

ይኖሩታል።

8. **ስለቦርድ አባላት**

1. ቦርድ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከአምስት እስከ ከሰባት የሚሆኑ በመንግስት የሚሰየሙ አባላት ኖሩታል።
2. የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባል እና ጸሐፊ በመሆን በስብሰባው ላይ ይሳተፋል።
3. የሚከተሉት ሰዎች የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ሆነው መሰየም አይችሉም፦

ሀ) ለጽሕፈት ቤቱ የንግድ ዕቃዎችን የሚያቀርብ ሰው ወይም ቅርበት ያለው አካል፤ ወይም

ለ) የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኛ እና የሠራተኛው የቤተሰብ አባል፤ ወይም

ሐ) የፖለቲካ ፓርቲ አመራር፤ ወይም

መ) የማንኛውም ምክር ቤት አባል፤ ወይም

ሠ) አትሌቶች፣ የአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ ፌዴሬሽኖች እና የስፖርት ድርጅቶች፤ ወይም

ረ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) ሥር ከተጠቀሱት ድርጅቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ሰው፤ ወይም

ሰ) በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ወንጀል ፈጽሞ ሥልጣን ባለው በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ ያልተሰየመ ሰው፤ ወይም

ሸ) በጤና እክል ወይም በአዕምሮ ሕመም ሳቢያ ሥራውን በአግባቡ ማከናወን የማይችል ሰው።

9. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች እንዲሁም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት እና አፈፃፀም በመከታተልና በመገምገም አቅጣጫ ማስቀመጥ፤
2. የስፖርት ዶፒንግን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶች፣ ጥናቶች እና ምርምሮች ዙሪያ ግምገማ በማድረግ የውሳኔ አስተያየት ማቅረብ፤

3. እንደ አስፈላጊነቱ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የውጤት አስተዳደር፣ የተከለከሉ ቅመሞችን ለህክምና መጠቀምን የሚመለከት፣ የጥናት እና ምርምር እና ሌሎች ኮሚቴዎችን ማቋቋም፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን የእያንዳንዱን ኮሚቴ አባላት ብዛት የመወሰን፤
5. ለእያንዳንዱ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚሆነውን የሥራ አመራር ቦርድ አባል የመሰየም፤
6. ልዩ ሙያ ያላቸውን ሰዎች በቦርዱ አጋር አባልነት እንዲሳተፉ የመወሰን፤
7. ጽሕፈት ቤቱን በዕለት ተዕለት ሥራዎች ዙሪያ ማማከር፤
8. ሌሎች የጽሕፈት ቤቱን ዓላማ ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ማከናወን።

10. **<u>የቦርዱ ስብሰባ</u>**

1. ቦርዱ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ አስፈላጊ ሲሆን በሰብሳቢው ጥሪ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።
2. በስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለዕኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. ማንኛውም የቦርድ አባል የጥቅም ግጭት ሊያስነሳ የሚችል ጉዳይ ሲኖር ለቦርዱ በማሳወቅ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት።

11. **<u>የቦርዱ የሥራ ዘመን</u>**

1. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመታት ይሆናል፤ ሆኖም በድጋሚ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን ሊመረጡ ይችላሉ።
2. ከቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አባላት መካከል በራሱ ፍላጎት፣ በህመም፣ በብቃት ማነስ ወይም በመሳሰሉት ምክንያቶች ከቦርድ አባልነት በሚለቅበት ጊዜ ምትክ የቦርድ አባል በመንግሥት ይሰየማል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተለያዩ ምክንያቶች የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አባል ከአባልነት በሚሰናበትበት ወቅት በምትኩ እንዲሰየም ጽሕፈት ቤቱ ለመንግሥት ሪፖርት ያደርጋል።
4. መንግሥት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሪፖርት ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ምትክ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ይሰይማል።

5. የተተኪ የቦርድ አባላት የሥራ ጊዜ የለቀቁት የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ይሆናል።

12.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ) የጽሕፈት ቤቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ በቦርዱ አስገምግሞ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ይተገብራል፤
   መ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደ በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤
   ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤
   ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት አዘጋጅቶ በቦርዱ አስገምግሞ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
   ሰ) ከቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

13.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. በዚህ ደንብ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ዓላማዎች ተግባራዊ በማድረግ፣ ሥልጣንና ተግባራቱን ሥራ ላይ በማዋል፣ የጽሕፈት ቤቱን ተግባራት በማቀድና አስተባብሮ በመምራት ረገድ ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል።
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

**14.<u>በጀት</u>**

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል።

**15.<u>የሒሳብ መዛግብት</u>**

1. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዝገብ እና ሰነዶችን ይይዛል።
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትንና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተሩ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**16.<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

1. ማንኛውም ሰው በማንኛውም የፀረ-አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴ ውስጥ እና በጽሕፈት ቤቱ በሚከናወን የምርመራ ሥራ ላይ ጽሕፈት ቤቱን የመተባበር ግዴታ አለበት፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፦
   ሀ) እያንዳንዱ የስፖርት ማህበር በፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ እንዲሁም በጽሕፈት ቤቱ የውጤት አስተዳደር መመሪያ በቀጥታ ተገዥ ይሆናል፤ በስሩ ባሉ ሁሉም አትሌቶች፣ የአትሌት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ አሰልጣኞች፣ ማኔጀሮች፣ ወኪሎች፣ የቡድን ሰራተኞች፣ ኃላፊዎች፣ የህክምና ሰራተኞችና ወጌሻዎች እና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ከኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ሕግ እና ከዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች አሰራር ጋር የተጣጣመ የራሱ የማስፈፀሚያ መመሪያ ያዘጋጃል፤
   ለ) የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያ ጥሰትን በሚመለከት ማንኛውም ሰው ለጽሕፈት ቤቱ ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን ብሔራዊ የስፖርት ፌዴሬሽን ከሆነ ለዓለም አቀፉ የስፖርት ፌዴሬሽን ጭምር ማሳወቅ አለበት።

**17.<u>የሥራ ነጻነት</u>**

ቦርዱ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እና የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ከማንኛውም ሰው ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው ይሰራሉ።

18. <u>*መመሪያ የማውጣት ስልጣን*</u>

*ጽሕፈት ቤቱ የዓለም አቀፍ የፀረ-አበረታች ቅመም ሕጎችን እና ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የፀረ-አበረታች ቅመሞች መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።*

19. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

*ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።*

**አዲስ አበባ መጋቢት 15 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ዘ/ ለብሔራዊ ፐላን እና ልማት ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች

## አዋጅ ቁጥር 442/1997 ዓ.ም

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ[78] ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአገሪቱን የስታቲስቲክስ ክንውን በተቀላጠፈና በተቀናጀ መንገድ በማደራጀት ወቅታዊና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለኢኮኖሚያዊና ለማኅበራዊ ልማት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትል፣ ለምርምርና ቁጥጥር፣ ለፖሊሲ ቀየሳና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች በሚያገለግሉበት ሁኔታ አሰባስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከአገሪቱ የስታቲስቲክስ የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣም የስታቲስቲክስ መረጃ ሰጪዎችን፣ የመረጃ አመንጪዎችንና ተጠቃሚዎችን እንደዚሁም የባለሥልጣኑንና የሠራተኞቹን ኃላፊነትና ግዴታ የሚወስን ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 442/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣[79]
   2. "ኤጀንሲ" ማለት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ነው፣
   3. "ስታትስቲክስ" የሚለው ነጠላት ትርጉሙ እውነታዎችን የመሰብሰብና የመተንተን ሳይንሳዊ የአጠናን ስልትን ሲመለከት በብዙ ትርጉሙ ደግሞ ዕውነታዎችን የሚገልፁ አሃዛዊ መረጃዎችን የሚያመለክት ነው፤
   4. "ውህብን" ማለት በቆጠራ ወይም በመለካት የተሰበሰበ አሃዛዊ የመረጃ ክምችት ነው፣

[78] በ12/1 (1998) አ.471 አንቀጽ 33 (2) "ባለስልጣን" የሚለው "ኤጀንሲ" በሚል ተተክቷል፡፡
[79] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(6) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

5. “ቆጠራ” ማለት ወሰኑ በውል በታወቀና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ዲሞግራፊያዊ ዘርፎች ላይ የሚደረግ አጠቃላይ ወይም ሙሉውን የሚሸፍን ቆጠራን በማካሄድ መሠረታዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመገምገምና ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባር ነው፤
6. “የናሙና ጥናት” ማለት መረጃ ከሚፈለግበት ከጠቅላላው ውስጥ በከፊል ወይም የሚያስፈልገውን ያህል በመምረጥ በየትኛውም የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና የዲሞግራፊያዊ ዘርፎች ወካይ የሆኑ መረጃዎች የመሰብሰብና በዚህም መሠረት የማጠናቀር፤ የመገምገምና ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች የማሰራጨት ተግባር ነው፤
7. “የማያቋርጥ ምዝገባ” ማለት የአስተዳደር ክፍፍልን ተከትሎ በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም በአነስተኛ የአስተዳደር እርከን ደረጃ በሕጋዊ የማያቋርጥ ምዝገባ ሥርዓት የወሳኝ ኩነቶችን ወይም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ድርጅቶችን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የመመዝገብ ተግባር ነው፤
8. “አስተዳደራዊ መዛግብት” ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም ተቋሞች ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከዕለት ተዕለት ሥራቸው የሚመነጩ መረጃዎችን በማጠናቀርና በማቀናበር የሚያዘጋጇቸው ሰነዶች ናቸው፣
9. “ሀገራዊ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም” ማለት የባለሥልጣኑ የሥራ መመሪያ ሰነድ ሆኖ እንዲያገለግል በየተወሰነ ጊዜ የሚዘጋጅ ሕጋዊ የስታቲስቲክስ ዕቅድና መርሃ ግብር ነው፣
10. “ሀገር አቀፍ ባህርይ ያለው ስታቲስቲክስ” ማለት ወካይ በሆነ መልኩ ከመስክ ተሰብስቦ ሲጠቃለል በአገሪቱ ከተሞች ወይም ገጠር ወይም በአገር ደረጃ ውጤት የሚያስገኝ መረጃ ማለት ነው።
11. “መደበኛ ስተቲስቲክስ” ማለት በባለሥልጣኑ መደበኛ ስተቲስቲክስ ተብሎ የተወሰነ ነው፣
12. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተጠቀሰው ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡ ’

13.“የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም” ማለት የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት አካል ሲሆን የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ልማት ድርጅትን ይጨምራል።

14.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊና ዲሞግራፊያዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በማሰራጨት ተግባር ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፣
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ይህ አዋጅ የአገር መከላከልና የደኅንነት ጉዳዮችን በተመለከተ በሚያዙ ሚስጢራዊ መረጃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

4. <u>**መቋቋም**</u>

1. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

5. <u>**ዋና መሥሪያ ቤት**</u>

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

6. <u>**የኤጀንሲው ዓላማ**</u>

የኤጀንሲው ዓላማ፡-

1. በቆጠራ፣ በናሙና ጥናት፣ በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና የዲሞግራፊያዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በተቀናጀ አሠራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት፣ እና
2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች አካላት የስታቲስቲክስ መዝገብ አያ ያዝ፣ የማያቋርጥ የምዝገባ አሠራርና የሪፖርት ሥርዓት እንዲዘረጉ የቴክኒክ ምክርና ድጋፍ የማድረግ፤ እንዲሁም ስለማያቋርጥ ምዝገባ፣ የአስተዳደራዊ መዛግብት

መረጃ ክምችቶች በመፍጠርና የአያያዝ ሥርዓት በማደራጀት ምክርና ድጋፍ ለመስጠት የማያስችል አቅም የመገንባት ይሆናል።

7. **<u>የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኤጀንሲው የአገሪቱ የስታቲስቲክስ ማዕከል ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1. የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በቆጠራ፣ በናሙና ጥናቶች፣ በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት ይሰበስባል፣ እንዲሰበሰቡም ያደርጋል፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያቀነባብራል፣ ይተነትናል፣ በጽሑፍ ያወጣል፣ ያሰራጫል፣
2. በየወቅቱ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የስታቲስቲክሰ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ የበጀት ረቂቅ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማትም በሥራ ላይ ማዋላቸውን ያረጋግጣል፣
3. ከመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ወይም ተቋማት ወይም የግል ድርጅቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የስታቲስቲክስን ሥራ በተመለከተ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
4. የስታቲስቲክሰ አሠራር ዘዴዎችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባር ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
5. በመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ ውስጥ በስታቲስቲክስ ሥራ ለተሰማሩ ሠራተኞች መሠረታዊ አጫጭር ስታቲስቲክስ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፣
6. አገራዊ የስታቲስቲክስ ሥራን ለማሻሻልና የሥራ መደራረብን ለማስወገድ የሥራ አፈጻጸም ፕሮግራሞችና መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውንም ያረጋግጣል
7. የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በተመለከተ ሥርዓት ይወስል፣ ትርጉምና ምደባ ያወጣል፤ የሚሰበስበውን መረጃ ዓይነትና ዝርዝር እንደዚሁም የሚሰበሰብበትን ጊዜ ይወስናል፣ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል፣
8. ዓለም አቀፍ ስታቲስቲካዊ ደረጃን ለመጠበቅ በአገሪቱ የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ከሌሎች ሀገሮች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር ተነጻጻሪ እንዲሆኑ ያደርጋል።

9. በሀገራዊ የቆጠራና ናሙና ጥናት አማካይነት የሚሰበሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የዲሞግራፊያዊ መረጃዎች የክልል መንግሥታትን ፍላጎት የሚያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
10. የክልል መንግሥታት ጥያቄ ሲያቀርቡ አስፈላጊውን የስታቲስቲክስ መረጃ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና በጽሑፍ የማውጣትና የማሠራጨት ዝግጅትን በመምራትና በማስተባበር ረገድ ይረዳል፣ እንደዚሁም የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት መቋቋሙን ያረጋግጣል፤
11. የስታቲስቲክስ ተግባራትን ለማከናወን ከለጋሽ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ዕርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት በሚኒስቴሩ እንዲፀድቅለት ያቀርባል፣
12. ከተያዘው ዕቅድና ፕሮግራም ውጪ ለሚቀርቡ የጥናት ጥያቄዎች ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ለጥናቶቹ የሚያስፈልጉ የተወሰኑ ወጪዎችን እንዲሸፍኑ በማድረግና ቅደም ተከተል በማውጣት ጥናቶችን ያከናውናል፣
13. በሁሉም የስታቲስቲክስ ዘርፎች በስታቲስቲክስ ሙያ ሥልጠና ለሚሰጡ ማዕከላት ከውጪ ስለሚገኝ የሥልጠናና የቴክኒክ ዕርዳታ አጠቃቀም አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፣
14. የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብን በሚመለከት የመንግሥት መ/ቤቶች ወይም ተቋማትና ሌሎች አካላት በተግባር ሊያሟሉትና ሊከተሉት የሚገባውን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
15. በስታቲስቲክስና ተመሳሳይ ዘርፍ ከተቋቋሙ አገራዊ የሙያ ማህበራት ጋር ትብብር ይፈጥራል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ኮንፈረንሶች በሚካሄዱበት ጊዜ አስፈላጊውን ዕርዳታ ይሰጣል፣
16. ለሚያሰራጫቸው የጥናትና የቆጠራ ውጤቶች እንዲሁም ጥሬ መረጃዎች ለመጠቀም የአገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፣
17. በስታትስቲክስ ጉዳይ ሁሉ ለመንግሥት ምክር ይሰጣል።
18. በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች የተሰጡትን ተግባሮች ያናውናል። ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

8. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፦

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር[80]፣
2. ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በመመካከር በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና
3. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

9. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግበር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   ሀ/ በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፣
   ለ/ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
   ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣
   መ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
   ሠ/ ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀም ለማሳካት ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

10. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣

1. በሥራቸው የተመደቡትን መምሪያዎች እና አገልግሎቶች ሥራ ያስተባብራሉ፣ ይመራሉ፣

[80] በ17/1 (1998) አ.471 አንቀጽ 33(2) “ዋና ሥራ አስኪያጅ” የሚለው “ዋና ዳይሬክተር” በሚል ተተካ፡፡

2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ በሚሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ዋና ዳይሬክተሩን ተክተው ይሠራሉ፣
3. በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡዋቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ።

11. <u>የስታትስቲክስ ምክር ቤት መቋቋም</u>

1. የስታቲስቲክስ አገር አቀፍ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ምክር ቤቱ አግባብ ካላቸው የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች፣ ከዘጠኙ ክልሎች፣ ከአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ መስተዳድሮች እና ከሌሎችም የሚቋቋም ይሆናል፣
3. የምክር ቤቱን አባላት ሚኒስትሩ ከዋና ሥራ አስኪያጁ ጋር በመመካከር ይሰይማል፣
4. ሚኒስትሩ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ይሆናል።

12. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1. በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን ሀገራዊ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም የማፅደቅ፣
2. በሥራ ላይ የዋለውን ሀገራዊ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም የመገምገም፤
3. ከአስተዳደራዊ መዛግብትና ከተለያዩ ምዝገባዎች የሚሰበሰቡ የእስታትስቲክስ መረጃ ክምችቶች በስርዓቱ የሚያዙበትን ተስማሚ ስልት የመምረጥና የማፅደቅ፤
4. አገር አቀፍ የስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማሻሻልና የአቅም ግንባታና የሰው ኃይል ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ መመሪያዎችን የማውጣት፣
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ንዑሳን ኮሚቴዎችን የማቋቋም።

13. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>

1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
2. ምክር ቤቱ ምልዐተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ነው።
3. ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**14.በጀት**

ኤጀንሲው የሚከተሉት የገንዘብ ምንጮች ይኖሩታል፡ አጠቃቀሙም በሃገሪቱ የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም መሠረት ይሆናል።

1. መንግሥት ከሚመድብለት በጀት፣
2. ኤጀንሲው ከሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ፣ እና
3. የቆጠራዎችና የጥናቶች ውጤት ከሆኑ ሪፖርቶች፣ ከጥሬ መረጃዎችና ከሌሎች የስታቲስቲክስ መጽሔቶችና ዶክመንቶች ሽያጭ ገቢ።

**15.የሂሳብ መዛግብት**

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂግብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኤጀንሲው ሂሳብና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**16.የእስታትስቲክስ መረጃዎች የመስጠት ግዴታ**

1. የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው ወይም አዲስ የሚያወጣ ማንኛውም ተቋም ፈቃዱን በሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በኩል በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ በሚቀርብ መጠይቅ ወይም ቅጽ ላይ ስለተቋሙ አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ በመሙላት የመመዝገብ ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም ሰው መረጃ እንዲሰጥ በኤጀንሲው ሲጠየቅ መረጃውን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስጠት አለበት።
3. ማንኛውም የመሬት፣ የሕንጻ፣ የንግድ ተሽከርካሪ፣ የአውሮፕላን፣ የመርከብ ወይም የመኖሪያ ቤት ባለቤት ወይም ባለይዞታ በኤጀንሲው ሠራተኛ ወይም ውክልና የተሰጠው ሰው የባለሥልጣኑን መታወቂያ ወረቀት ወይም የውክልና ደብዳቤ በማሳየት ከጥዋቱ 12 ሰዓት እስከ ቀኑ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ገብቶ አስፈላጊውን የስታቲስቲክስ መረጃ እንዲሰበሰብ መፍቀድ አለበት።
4. ማንኛውም ሰው ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም በቃለ መጠይቅ፣ በስልክ ወይም መጠይቅ ሞልቶ በፖስታ በመላክ መረጃ አንዲሰጥ ሲጠየቅ የሚፈለገውን የስታቲስቲክስ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት።
5. በማንኛውም ሰው የሚሰጥ የስታቲስቲክስ መረጃ ትክክለኛ፣ የተሟላና ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ካለምንም ክፍያ የሚገኝ መሆን አለበት።

6. መረጃውን የሚሞላው ራሱ መረጃ ሰጪው ከሆነና ኤጀንሲው በሚልከው መጠይቅ ላይ ትክክለኛውን መረጃ ሞልቶና ፈርሞ እንዲልክ ከተጠየቀ ይህንን የማድረግ ግዴታ አለበት።
7. ማንኛውም ሰው ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም የሠራቸውን የስታቲስቲክስ ጥናታዊ ሪፖርቶች ቅጂ ለኤጀንሲው የመስጠት ግዴታ አለበት።

17.<u>የመረጃ ሚስጥራዊነት</u>

1. ኤጀንሲው በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር፣
   ሀ/ ማንኛውም ሰው የሰጠውን መግለጫ በሙሉም ሆነ በከፊል፣
   ለ/ ለሰዎች ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ማንኛውንም መልስ፣ ወይም
   ሐ/ መግለጫውን ወይም መልሱን የሰጠውን ግለሰብ ለመለየት በሚያስችል ሁኔታ ከመግለጫው ወይም ከመልሱ የተዘጋጀ ሪፖርት፣ ተዋጽኦ ወይም ጽሑፍ ማሳተም፣ በማስረጃነት ማቅረብ ወይም በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ሥራ ለማይሰራ ሰው ማሳየት አይችልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተደነገገው በተባለው ሪፖርት ተዋጽኦ ወይም ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙት መረጃዎች ልዩ በመሆናቸውና የሚመለከቱትም የንግድ ወይም የሥራ ዓይነት በመስኩ ብቸኛ በመሆኑ ምክንያት መግለጫውን ወይም መልሱን የሰጠውን ሰው ለመለየት የሚቻል ቢሆንም የተባለውን ሪፖርት፣ ተዋጽኦ ወይም ጽሑፍ ከማሳተም አይከለክልም። ሆኖም ሪፖርቱ፣ ተዋጽኦው ወይም ጽሑፉ ምን ጊዜም ቢሆን የንግዱን ወይም የሥራውን የመሥሪያ ዋጋም ሆነ የሚገኘውን ትርፍ ለማወቅ የማያስችል መሆን የለበትም።

18.<u>ክልከላ</u>

ማንኛውም ሰው ከኤጀንሲው ፈቃድ ሳያገኝ አገር አቀፍ ባህሪይ ያላቸውን የስታቲስቲክስ ጥናቶች ማካሄድ አይችልም።

19.<u>ቅጣት</u>

1. በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት የበለጠ ቅጣት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የስታቲስቲክስ ሥራ የሚያከናውን ሰው፣
   ሀ/ በሥራው ምክንያት ያገኘውን የስታቲስቲክስ መረጃ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለግል ጥቅም ያዋለ እንደሆነ፣ ወይም የተባለውን መረጃ

ያለሕጋዊ ሥልጣን ያሳተመ ወይም ለማንኛውም ሰው ያስተላለፈ እንደሆነ፣ እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል።

ለ/ እያወቀ ሐሰተኛ የስታቲስቲክስ መረጃ ያዘጋጀ፣ ያወጣ እንደሆነ፣ ወይም የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችን ወይም መጠይቆችን ከመረጃ አመንጪው ሣይጠይቅ በራሱ የፈጠራ መረጃ የሞላ እንደሆነ ወይም የዚህ ዓይነቱን ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ያስተሳለፈ እንደሆነ፣ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ወንጀሉ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በማሰራጨት ሂደት ከላይ ያስከተለው ተፅዕኖ በጣም ከባድ ከሆነ እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

2. በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የበለጠ ቅጣት የማያስከትል ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሰረት የእስታስቲክስ መረጃ ተጠይቆ ያዘገየ እንደሆነ እስከ ስድስት ወራት በሚደርስ እሥራት ወይም በገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የስታቲስቲክስ መረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የተመለከተው ወንጀል ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል የተፈጸመ እንደሆነ፣ እስከ አሥር ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) የተመለከተው ወንጀል ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል የተፈጸመ እንደሆነ፣ እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀፅ 2 የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ህጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል በሚሆንበት ጊዜ ሥራው የሚመለከተው ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በአንቀጽ 2(ሀ) ወይም 2 (ለ) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል።

6. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የስታትስቲክስ መረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ሀሰተኛ መረጃ ያቀረበ ወይም እንዲቀርብ ያደረገ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት የበለጠ ቅጣት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር አስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተው ወንጀል ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል የተፈጸመ እንደሆነ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተው የተፈፀመው ህጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል በሚሆንበት ጊዜ ሥራው የሚመለከተው ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሠረት ይቀጣል።

20. <u>**ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**</u>

1. ሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ኤጀንሲው ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

21. <u>**ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**</u>

1. የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ትዕዛዝ ቁጥር 79/1964 እና የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት አዋጅ ቁጥር 303/1964 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

22. <u>**የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**</u>

በአዋጅ ቁጥር 8/1980 አንቀጽ 41(11) መሠረት ተቋቁሞና በአዋጅ ቁጥር 41/1985 አንቀጽ 57 መሠረት ሥራውን ቀጥሎ የነበረው የጠቅላይ ስታቲስቲክስ መሥሪያ ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

23. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ግዜ**</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ 12 ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዝያ 12 ቀን 1997 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 436/2011

## የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ

የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32(11) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፣ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የኢንስቲትዩቱን ስልጣንና ተግባር በአንድ ላይ በማሰባሰብ የኢንስቲትዩቱን አደረጃጀት መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት፣ እና ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ተሰጥተዋል በሚል በመቀመጡ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም አንቀጽ 34 መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 436/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

3. **ዓላማ**

   የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦችን ማመንጨት እና የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶችን ማዘጋጀት ይሆናል፡፡

4. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

   ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   1. በሥራ ላይ ባሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ጥናትና ምርምር የማካሄድ፤ ጥልቀትና ወቅታዊነት እንዲኖራቸው የማድረግ፣ በየወቅቱ ያለውን ዕድገትና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦችን የማመንጨት፤

2. ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ አዳዲስ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሃሳቦችን ማመንጨትና የፖሊሲ ሰነድ ማዘጋጀት፤
3. የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያስከተሉትን ውጤት መገምገም፣ በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት ጥናትና ምርምር በማካሄድ የመፍትሔ ሀሳብ የማመንጨት፤
4. ለሚያካሂደው ጥናትና ምርምር የሚያስፈልጉትን መረጃዎች መሰብሰብና ዳታ ቤዝ ማዘጋጀት፣ በሌሎች አካላት የተሰበሰቡትንም የመጠቀም፤
5. የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚዳብሩበትን መድረኮች፣ ሴሚናሮች እና ወርክሾፖችን የማዘጋጀት፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር አጫጭር ስልጠናዎች የማዘጋጀትና የመስጠት፣ እንደአስፈላጊነቱ የምርምር ውጤቶችን የማሳተምና የማሰራጨት፤
6. የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤
7. ለዓላማው መሳካት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ተቋማት ጋር ግንኙነት የመመስረት፤
8. የአገሪቷን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኝነት፣ዝግጁነት እውቀትና ፍላጎት ያላቸው ተመራማሪዎችን መፈለግ፣ ማደራጀትና ማብቃት፤
9. የዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ተልዕኮን የሚያሳኩ የጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋማት ዓይነትና ተልዕኮ እንዲሁም ትስስር ምን መሆን እንዳለበት የውጭ ሀገር ልምድ የመቀመር፤
10. የሥርዓቱን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በተቀመጠው ልማታዊ አቅጣጫ መገንባት የሚያስችሉ የመንግስት ድጋፍና አመራር የሚያጠናክሩና የኢኮኖሚውን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያረጋግጡ ተቋማት ግንባታ በተመለከተ ጥናትና ምርምር የማካሄድ እና መነሻ ሀሳብ የማቅረብ፤
11. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና፣ የመከሰስ፤
12. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

5. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም ኢንስቲትዩቱ፡-**</u>
   1. በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና
   2. አስፈላጊው ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

6. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>**
   1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ስራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-
      ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
      ለ) የኢንስቲትዩቱን ተመራማሪዎች፤ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ እና ሌሎች ሰራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
      ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
      መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
      ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤
      ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፡፡
   3. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>**
   1. የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤
   2. በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
   3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

8. **<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

ሀ) በመንግስት ከሚመደብለት በጀት፤

ለ) አላማውን ለማሳካት ከሚያገኛቸው ማናቸውም ስጦታ፣ እርዳታ እና ሌሎች ገቢዎች ፤

ሐ) ከምክር አገልግሎት ክፍያዎችና ከሕትመቶች ሽያጭ ገቢ ይሆናል፡፡

9. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራሉ፡፡

10. <u>ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር 311/2006 እና የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር 54/1991 በዚህ ደንብ ተሸረዋል፡፡

11. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

ፐ/ **ለውሃ ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ማቋቋሚያ ህጎች**

**አዋጅ ቁጥር 268/1994 ዓ. ም**

**የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

ሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል የውሃ አቅርቦትንና የሳኒቴሽን አገልግሎትን ማጎልበትና ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የመስኖ እርሻ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት አንዱ በመሆኑ ለልማቱ መስፋፋት ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እነዚህንም ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነውን ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች በማእከል በማሰባሰብ ሁሉም ፍትሐዊና ርትአዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አሠራር መቀየስ ተገቢና ለዚሁም የውሃ ልማት ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 268/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "የውሃ ልማት" ማለት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፡ የመስኖ ልማት እና የሳኒቴሽን አገልግሎት ነው፡
   2. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፤
   3. "ሳኒቴሽን" ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከመሳሰሉት ተቋማት ሚውጣን ፍሳሽ አሰባስቦ በማጣራት ተገቢውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ ውሃ ማስገኘት ነው፤

4. “የመስኖ ልማት” ማለት ማንኛውም ለእርሻና ለግጦሽ የሚውል መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ነው።
5. “የውሃ አቅርቦት” ማለት ለመጠጥና ለሌሎች ግልጋሎቶች የሚውል ደረጃውን የጠበቀ የተጣራ ውሃ ነው፤
6. “ቦርድ” ማለት የውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ ነው፤
7. “ተቋም” ማለት የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ድርጅት፣ እንዲሁም የመስኖ የህብረት ሥራ ማህበር ነው፣[81]
8. “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የውሃ ሀብት ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው።[82]
9. “ተዘዋዋሪ ፈንድ” ማለት ከተበዳሪዎች ተመላሽ የሚደረግና ጽሕፈት ቤቱ ለተበዳሪዎች መልሶ የሚያበድረው ገንዘብ ነው፣[83]

## ክፍት ሁለት

## ስለፈንዱ መቋቋም

### 3. መቋቋም

1. የውሃ ልማት ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንዱ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለዚህ አዋጅ ዓላማ ማስፈጸሚያ ይውላል።

### 4. የፈንዱ ዓላማ

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡

1. በውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለው ለሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የውሃ አቅርቦት አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፡
2. የመስኖ ልማትን በማስፋፋትና ዘለቂታዊነቱን በማረጋገጥ በምግብ ራስን ለመቻል ለሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስቻል፤

---

[81] በ14/37(2000) አ.581 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡
[82] በ22/12(2008) አ.916 9(16) መሰረት የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡
[83] በ14/37(2000) አ.581 አንቀፅ 2(2) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱትን ዓላማዎች ዕውን ለማድረግ ወጪን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሠረተ የረጅም ጊዜ ብድር ማበደር[84]፤

5. **የፈንዱ ምንጮች**

1. ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

ሀ/ ከፈንዱ ዓላማ ጋር በተያያዘ ከውጭ መንግሥታት እና ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ የገንዘብ እርዳታና ብድር፣

ለ/ ከፌዴራል መንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤

ሐ/ ከልዩ ልዩ ምንጮች።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ገንዘብ ለፈንዱ ሲባል በጽሕፈት ቤቱ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሣብ በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[85] ተቀማጭ ይደረጋል። ጽሕፈት ቤቱ የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ ሊኖረው ይችላል።

3. አበዳሪዎችና ለጋሽ ድርጅቶች ወለድን በሚመለከት የሚያስቀምጡት ቅድመ ሁኔታ ከሌለ ቦርዱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚወስነው ጣሪያ ሳያልፍ በብድር ላይ የሚከፈለውን የወለድ መጠን ይወስናል።[86]

6. **ስለሚለቀቀው ገንዘብ**

በፀደቀው ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለሚከናወኑ ሥራዎች ከፈንዱ ሂሣብ ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚለቀቀው የገንዘብ ብድር መጠን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

7. **በፈንዱ ተጠቀሚ ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች**

1. በፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆን ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆን አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተደነገገው በተጨማሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(4) መሠረት በቦርዱ የሚፀድቁ መመዘኛዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ[87]።

8. **ስለፈንዱ ሂሣብ**

---

[84] በ14/37(2000) አ.581 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡
[85] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(6) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡
[86] በ14/37(2000) አ.581 አንቀፅ 2(4) ተሻሻለ ፡፡
[87] 14/37(2000) አ.581 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡

1. ጽሕፈት ቤቱ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት ትክክለኛና የተሟላ የሂሣብ መዛግብት በተለይ ይይዛል።
2. የፈንዱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው ይመረመራሉ። የኦዲተሩ የምርመራ ውጤት የበጀት ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባል።

## ክፍል ሦስት
## ስለፈንዱ አስተዳደር

### 9. የውሃ ልማት ፈንድ ፅሕፈት ቤት መቋቋም

1. የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ በሚኒስትሩ ይሆናል።

### 10. ዋና መሥሪያ ቤት

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሃገሪቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል።

### 11. የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር[88]

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. የቦርዱ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከተተላል፤ ያረጋግጣል፤
2. የፈንዱን ሂሣብና ሪኮርድ ይይዛል፡
3. የቦርዱን ሥራ አመራር የስብሰባ ሪኮርዶችን ይይዛል፡
4. ቦርዱ በሚያፀድቀው የብድር አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት በየዓመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሰበሰበውን ገንዘብ ለተበዳሪዎች በብድር ይሰጣል።
5. ለፈንዱ መግባት የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኘውን ተሰብሳቢ ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ ይሰበስባል፣ በፈንዱ ሂሳብም ገቢ በማድረግ በተዘዋዋሪ ፈንድ ይዞ ለተመሳሳይ የብድር አገልግሎት ያውለዋል።

---

[88] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) በ14/37(2000) አ.581 አንቀፅ 2(6) ተሻሻሉ፡፡

6. ፈንዱን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሣቦችን ለቦርዱ ያቀርባል፤
7. የንብረት ባለቤት ይሆናል፡ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

12.<u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፦

1. የውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ
2. በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር[89]፤ እና
3. ሠራተኞች ይኖሩታል።

13.<u>ስለቦርድ አባላት</u>

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

14.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. ፈንዱን በበላይነት ያስተዳድራል
2. ስለፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤
3. ለፈንዱ መግባት ያለባቸው ገቢዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውን እና በፈንዱ ሂሣብ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤
4. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የብድር አሰጣጥ አወሳሰን መመዘኛዎችን ያወጣል
5. የፈንዱን ኦዲት በኦዲት ሪፖርቶች ይገመግማል፤ በሪፖርቱ መሠረት ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳውን ያረጋግጣል፡ በኦዲተር የተመረመረው ዓመታዊው የፈንዱ ሂሣብ እንዲጠናቀርና ይፋ እንዲሆን ያስደርጋል፤
6. ፈንዱ ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ ይፈልጋል፤
7. ከፈንዱ ጋር በተያያዘ ዓመታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
8. የጽሕፈት ቤቱን የሥራ ምርምርና በጀት ይመረምራል፡ ለመንግሥት አቅርቦ ያስፀድቃል፤
9. የጽሕፈት ቤቱን ዋና ዳይሬክተር ለመንግሥት በማቅረብ ያሾማል።

15.<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

---

[89] በ1/17(1998) አ.471 አንቀፅ 33(2) “ዋና ሥራ አስኪያጅ” የሚለው “ዋና ዳይሬክተር” በሚል ተተክቷል፡፡

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ ይደረጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ሲጠራ ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአት ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሣኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው። ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## 16.የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

1. የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ያቅዳል፣ ይመራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን ዋና ዳይሬክተሩ፡-
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል
   ለ/ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች በመከተል ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤
   ሐ/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፈቀደም ተግባራዊ ያደርጋል፡
   መ/ ለጽሕፈቱ ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ የደርጋል፡
   ሠ/ በጽሕፈት ቤቱ ደረጃ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረገው ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፡
   ረ/ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለጽሕፈት ቤቱ ሥራ ትልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## 17.በጀት

1. የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

2. የጽሕፈት ቤቱ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ ሰኔ 30 ቀን ያበቃል።

18. <u>ስለሂሣብ መዛግብት አያያዝ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ ትክክለኛና የተሟሉ መዛግብትን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ይይዛል።
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው ይመረመራሉ። የኦዲተሩ የምርመራ ውጤት የበጀት ዓመት ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

19. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገገባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

20. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር 23 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 23 ቀን 1994 ዓ. ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**